# አንድ አምላክ
# አንድ መልዕክት

ሚስጥሩን ያግኙ
ጉዞውን ያድርጉ



ፒ. ዲ. ብራምሰን

# እናንተ እንደዚህ ታስባላችሁ?

To:
CC:
Subject: the bible

ሰላም ! ኢየሱስ መሲህ ሆኖ ነው የመጣው ፣ እኔም ያንን አምናለሁ፤ነገር ግን በፍጹም አምላክ ነኝ ብሎ አያውቅም። በፍጹም አልተሰቀለም። ኢየሱስ ተሰቅሎ ቢሆን እንኳን ፣ በዚያ ምክንያት የሰዎች ኃጢአት ተደምስሷል ማለት አይደለም። ይሄ ኃጢአተኛ የምትሉት ነገር አይገባኝም። እኔ እንደማምነው እና እንደሚገባኝ መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው ውሸት ሲሆን በተጨማሪም በውስጡ የሚገኙ መጽፍት ሁሉ ስለተስተካከሉ ተበርዟል... ሰላም ፣

አሕመድ

- የምንጊዜም የዓለም ከፍተኛ የሽያጭ ደረጃ የያዘው መጽሐፍ ተዓማኒ ነውን?
- ታሪኩንና መልዕክቱን ሳቢ ግን አከራካሪ ያደረገው ምንድን ነው?
- በዓለም ላይ 10000 ሐይማኖቶች እያሉ ፣ ግራ መጋባት ብቸኛው ምርጫችን ነውን?

እውነቱን እወቁ። ከመሞትዎ በፊት ከሚቆጠረው

ጊዜ ወደማይቆጠረው ጊዜ ይጓዙ።

“ይሄ መጽሐፍ ከባድ ጥያቄዎችን ይመልሳል። እምነትን ያጠነክራል። ምስጢራዊ በሆነም መንገድ የነፍሳችንን ጥልቅ ስፍራ በመድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኘናል።”
—ሰሜን አሜሪካዊ አንባቢ

“በጣም ሞጋች። ከእግዚአብሔር ጋር የምናሳለፈውን ዘላለም የሚገልጽበት መንገድ አስገራሚ ነው። አሁኑኑ መንግሥተ ሰማያት መግባት ፈልጌያለሁ።
—የመካከለኛው ምሥራቅ አንባቢ

**ፒ.ዲ. ብራምሰን** እና ባለቤቱ ቤተሰባቸውን ያሳደጉት በሰሃራ ጠርዝ በምትገኝ ሙስሊም በሚበዛባት ሐገር ነው። የብራምሰን ጽሁፎች የሚመነጩት ለቅዱሳት መጽሐፍት ካለው ፍቅርና በሺዎች ከሚቆጠሩ ሙስሊም ጓደኞቹ፣ ጎረቤቶቹና ከሚጻጻፉት ሰዎች ጋር ካደረገው ውይይት ነው። በተጨማሪም ኪንግ ኦፍ ግሎሪ ፣ ለሁሉም ዕድሜ ተስማሚ የሆነ መጽሐፍና ፊልም እና ዘ ዌይ ኦፍ ራይቺየስነስ የተሰኘ በአፍሪካ ፣ ኢሲያ እና መካከለኛው ምሥራቅ ለመሰራጨት በበርካታ ቋንቋዎች የተተረጎመ 100 ፕሮግራሞችን የያዘ፣ በቀደም ተከተል የተዘጋጀ ተከታታይ የሬዲዮ ፕሮግራም ጸሐፊ ነው።

ISBN 978-1-62041-022-6
9 781620 410226 >

www.one-god-one-message.com

# አንድ አምላክ
# አንድ መልዕክት



ሚስጥሩን ያግኙ
ጉዞውን ያድርጉ

# አንድ አምላክ
# አንድ መልዕክት



ፒ. ዲ. ብራምሰን
ምስል በ
ዲ.ሲ. ብራምሰን

**አንድ አምላክ አንድ መልዕክት**
መልዕክት በ ፒ. ዲ. ብራምሰን
ምስል በ ዲ.ሲ. ብራምሰን

ኮፒ ራይት © 2022 ሮክ ኢንተርናሽናል
መብቱ የተጠበቀ ነው
Amharic Edition of
ONE GOD ONE MESSAGE
Copyright © 2007, 2022 by ROCK International

ISBN 978-1-62041-022-6
አሳታሚ ሮክ ኢንተርናሽናል

• Relief, Opportunity & Care for Kids
• Resources Of Crucial Knowledge
P.O. Box 4766, Greenville, SC 29608, USA
www.rockintl.org • resources@rockintl.org

በተለየ ሁኔታ ካልተጠቀሰ በስተቀር ጥቅሶቹ የተወሰዱት © 1954 ዓ.ም በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ከታተመው የቀ.ኃ.ሥ ትርጉም (ቀት) የተወሰዱ ናቸው ፣ አመት ተብለው የተጠቀሱ ጥቅሶች © 1993 ዓ.ም በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም የተወሰዱ ናቸው።

የሽፋን ምስል እና ምስሎች በ ዲ.ሲ. ብራምሰን
የገጽ ግንባታ በ ክሪስተን ጎልሰን፣ ዛሪፍ ሚና፣ ፒ.ዲ. በራምሰን

አንድ አምላክ አንድ መልዕክት በሌሎች
ቋንቋዎች ማግኘት ለምትፈልጉ
**www.one-god-one-message.com**

ይህንን መጽሐፍ ለመተርጎም
pdbramsen@rockintl.org

በኢትዮጵያ የታተመ


“የቀዘቀዘ ውኃ ለተጠማች
ነፍስ ደስ እንደሚያሰኝ፥
ከሩቅ አገር የመጣ መልካም
ምስራች እንዲሁ ነው።”
ነብዩ ሰለሞን
(ምሳሌ 25:25)



# ማውጫ

መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

## ክፍል ፩
## ለጉዞው መዘጋጀት
እንቅፋትን መጋፈጥ

1. እውነትን ግዛት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7
2. መሰናክሎቹን ማለፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 18
3. ተበርዟል ወይስ ተጠብቋል . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32
4. ሳይንስ እና መጽሐፍ ቅዱስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 45
5. የእግዚእብሔር ፊርማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 55
6. አስተማማኝ ምስክር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 66
7. መሠረት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 77

## ክፍል ፪
## ጉዞ
ሚስጥሩን ማግኘት

8. እግዚአብሔር ምን ይመስላል . . . . . . . . . . . . . . . . . . 87
9. እሱን የሚመስል የለም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 103
10. ልዩ ፍጥረት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 118
11. የእኩይ መግባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 130
12. የኃጢአትና የሞት ሕግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 140
13. ምሕረትና ፍትሕ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 149
14. እርግማን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 156
15. ጥንድ ችግሮቻችን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 164

16.የሴቷ ዘር . . . . . . . . . . 176
17.ማን ሊሆን ይችላል . . . . . . . . . . 186
18.የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ . . . . . . . . . . 205
19.የመሰዋዕት ሕግ . . . . . . . . . . 214
20.ቅጽበታዊ መሰዋዕት . . . . . . . . . . 224
21.ተጨማሪ ደም መፋሰስ . . . . . . . . . . 235
22.ጠቦቱ . . . . . . . . . . 246
23.የመጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜ . . . . . . . . . . 258
24.በሙሉ ተከፍሏል . . . . . . . . . . 267
25.ሞት ተሸነፈ . . . . . . . . . . 278
26.ሐይማኖተኛ እና ከእግዚአብሔር የራቀ . . . . . . . . . . 290

## ክፍል ፫
## የጉዞ ማብቂያ
እርግማኑን መስበር

27.ደረጃ 1 ፦ የእግዚአብሔር ያለፈ ጊዜ መርሐ ግብር . . . 309
28.ደረጃ 2፦ የእግዚአብሔር የአሁን ፕሮግራም . . . . . . . . 329
29.ደረጃ 3፦ የእግዚአብሔር የወደፊት ፕሮግራም . . . . . 349
30.የገነት ቅምሻ . . . . . . . . . . 368
መውጪያ ቃል . . . . . . . . . . 383
የግርጌ ማስታወሻዎች . . . . . . . . . . 385
የውይይት መመሪያ — ጉዞውን በተመለተ ማሰላሰል . . . . 423



# መግቢያ

የመንደሯ ሽማግሌ “**ለሰራኸው በጎ ሥራ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት ይገባኸል፣ ለምትሰብከው መልዕክት ግን ሲዖል መግባት ይገባኸል!**” አለኝ።

ላለፉት አስር ዓመታት ጓደኛዬ እና ባለቤቱ ፣ ሰሃራ ዳርቻ ላይ በምትገኘው የዚህ ሰውዬ መንደር ውስጥ ሲኖሩ ቆይተዋል። የመስኖ ፕሮጀክት እና ጤና ጣቢያም መስርተዋል። የነብያትንም ታሪክ እና መልዕክት ሊያዳምጣቸው ለፈቀደ ሁሉ ተናግረዋል።

እንደ ከተማው ሽማግሌ ከሆነ ጓደኛዬ “መንግስተ ሰማያት መግባት ይገባኸል” የተባለው ምን ቢያደርግ ነው?” መልካም ሥራ ስለ ሰራ ነው።

ታዲያ “ሲዖል መግባት ይገባኸል” የተባለው ምን ቢሰራ ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርቶ የነብያቱን መልዕክት በማስተማሩ ነው።

የመንደሯ ሽማግሌ የጓደኛዬን ስራ እና መልዕክት የተረዳበት መንገድ ትክክል ነው? በከፊል ትክክል ነው? ሙሉ በሙሉስ ተሳስቷል?

ምን ማሰብ እንዳለባችሁ እርግጠኛ ካልሆናችሁ ፣ ይሄ መጽሐፍ ለእናንተ ነው።

## የት

እኔ የተወለድኩት አሜሪካ ሲሆን፣ ይሄ መጽሐፍ ግን የተወለደው አፍሪካ ውስጥ ነው።

፦ የሴኔጋል ሳህል[1] ክልል፣ ምዕራብ አፍሪካ።

፦ የንጋት የጸሎት ጥሪ ተጠናቅቋል። የማለዳው የመጀመሪያ ብርሃን ፒንክ እና ቡርቱካናማ ጨረር በአሸዋማው እና ቁጥቋጦ በወረረው አድማስ ላይ ያንጸባርቃል። የአየሩ ሁኔታ ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ቀዘቃዛ ነው፣ ነገር ግን በቅርቡ ይቀየራል። በደሳሳ ጎጇችን ደጅ ላይ ላፕ ቶፔን ይዤ ተቀምጫለሁ። ቁልፎቹን ከሰሃራ አቧራ ለመከላከል የተለጠፈው ንጹህ ፕላስቲክ፣ በአየር ላይ

ተንጠልጥሏል። አልፎ አልፎ ከሚሰማው የአህያ ማናፋት እና ከአውራ ዶሮ ጩኸት በስተቀር መንደሩ ጸጥ ብሏል። ብቸኛው የሚሰማኝ ድምጽ ሐሳብን ወደ ቃላት ቃላትን ወደ ምንባብ በሚቀይሩት በቁልፎቹ ላይ የሚንቀሳቀስ ጣት ነው።

## ለምን

የምጽፈው በሕይወት ፤ በደስታ ፤ በሠላም እና ለሕይወቴ ዓላማ በመስጠት የባረከኝ አንድዬ ልጽፈው የሚገባኝ ነገር ስለ ሰጠኝ ነው።

የምጽፈው እኔና ባለቤቴ ሦስት ልጆቻችንም ካሳደግንበት እና አብዛኛውን የአዋቂነት ሕይወታችንን ባሳለፍንበት በተለይም ሴኔጋል ውስጥ ለሚገኙት ለሙስሊም ወዳጆቼ ካለኝ ልባዊ አክብሮት እና ፍቅር የተነሳ ነው።

በቅርብ ዓመታት ውስጥ በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ሙስሊሞች ከሺህ የሚበልጡ ኢሜይሎች ተቀብያለሁ። አስተያየታቸውና ጥያቄዎቻቸው ቸላ መባል የለባቸውም።

የምጽፈው “መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነኝ ስለሚል እውነት ነው” ወይም “ቁርዓንም እውነት ነው ምክንያቱም ማንም እሱን የሚመስል መጽሐፍ አይጽፍም!” የሚል ተደጋጋሚ ውትወታ እንጂ የተሻለነገር ከሐይማኖት መሪዎች ማግኘት ስላልቻሉ ለደከሙ ሰዎች በማዘን ነው።

የምጽፍበት ምክንያት የሰው ልጅ ልብ ወጥ ከሆነው የእግዚአብሔር መልዕክት ውጪ የሆነ ነገር ለማመን ያለው ዝንባሌ ስለሚያስደንቀኝ ነው።

## ምን

በሕይወታችን የማናገኘውን ዕድል ይሰጠናል፦ ይሄም ዕድል የዓለምን የሽያጭ ስንጠረዥ በተቆጣጠረው መጽሐፍ ውስጥ በዝግታ በመጓዝ የነብያትን መልዕክትና የጻፈውን ማወቅ ነው። ይህንን መንፈሳዊ ጉዞ የሚካፈሉ ሰዎች በርካታ እንቅፋቶችን እንዲያሸንፉ (ክፍል ፩)፣ ምስጢራውን ዓለም ጥሰው እንዲገቡ (ክፍለ ፪) እና ወደ ከበረው ባለብዙ ገጽታ ወደ ሆነው መንግሥት እና ወደሚያረካው እውነት እንዲገቡ ዕድል ይሰጣቸዋል (ክፍል ፫)።

## ለምን

ይሄ ጉዞ በዋነኛነት የተዘጋጀው ለ “አንድ አምላኪዎች” ማለትም በአንድ አምላክ ለሚያምኑ ነው። ነገር ግን “ብዙ አምላኪዎች” እና “አምላክ ሁሉን ነገር ነው” የሚሉ ሰዋውያን እና ኢ አማንያንም[2] እኩል ሊያነቡት ይችላሉ። የእኔ ዘላለማዊ ሕይወት ይህንን መጽፍ በማንበብ በደ.ርዘን የሚቆጠሩ ሰዓታትን ያክል ዋጋ አለው ለሚል ለየትኛውም ሰው የሚሆን ነው። ይህንን መጽሐፍ ድምጽን ከፍ አድርጎ ለማንበብ የሚወሰደው ያንን ያህል ሰዓት ነው።

የኋላ ታሪካችሁ ምንም ይሆን ምን፣ በምንም እመኑ ወይም አትመኑ ፣ ብዙዎቹ እናከብረዋለን የሚሉትን ጥቂቶች የሚያነቡትን መጽሐፍ ለማጥናት ተጋብዛችኋል።

ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት ነብዩ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪና ባለቤት ይህንን ጥያቄ አቀረበ፦ “ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ።” (መዝሙር 119:18)

የምናየውን ነገር ላንወደው ብንችልም እንኳን ፣ ከማየት ግን አንቆጠብ።

አብሯችሁ ተጓዥ የሆነው፣
**ፒ.ዲ. ብራምሰን**



# ክፍል ፩
# ለጉዞው መዘጋጀት
## እንቅፋትን መጋፈጥ


1 እውነትን ግዛት

2 መሰናክሎችን ማለፍ

3 ተበርዟል ወይስ ተጠብቋል

4 ሳይንስ እና መጽሐፍ ቅዱስ

5 የእግዚአብሔር ፊርማ

6 አሰተማማኝ ምስክር

7 መሠረት



# 1

# እውነትን ግዛት

“እውነትን ግዛት እንጂ አትሸጣት።”
—ነብዩ ሰለሞን (ምሳሌ23:23)[3]

በቢሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ተሞላ የገበያ ስፍራ ሄዳችሁ እንበል።

አዎ፣ በቢሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ያለበት።

ዐይን ማየት እስከሚችለው ድረስ አሥር ሺህ የሚሆኑ ሱቆችና ዳሶች ይገኛሉ። ከሁሉም አቅጣጫዎች ፣ ትጉህ ቸርቻሪዎች ይጣራሉ፣ ይጮኸሉ፣ ይለፈልፋሉ፣ ይሟገታሉ፣ ይማጸናሉ፣ አንዳንዶች በለሆሳስ ሲጸልዩ ሌሎች ደግሞ በድምጽ ማጉያ ይጸልያሉ፣ ሁሉም ልትገዙት የምትፈልጉትን ነገር እንደሚያቀርቡ ይናገራሉ፦

**እውነት!**

አያስቅም። የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ማተሚያ ቤት አሥር ሺህ የሚሆኑ የተለያዩ የሐይማኖት ዓይነቶቸች በዓለም ላይ እንደሚገኙ የሚገልጥ ኢንሳይክሎፔዲያ አሳትሟል። ይሄ ደግሞ በእነዚህ ሐይማኖቶች ውስጥ የሚገኙትን ኑፋቄዎች እና ቤተ እምነቶች አያካትትም።[4]

ስለዚህ ምን እንግዛ ? ማንን እንመን?

ብቸኛና እውነተኛ አንድ አምላክ ብቻ ካለና እሱ ለሰው ልጆች ስላለው ዕቅድ ከገለጠ፣ እንዴት አድርገን ልናውቀው እንችላለን?

ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ነብዩ ኢዮብ ተመሳሳይ ጥያቄ አንስቶ ነበር።

> “ነገር ግን ጥበብ የምትገኘው ወዴት ነው? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው? ሰው መንገድዋን አያውቅም በሕያዋን ምድር አትገኝም። …በምዝምዝ ወርቅ አትገኝም፤ ብርም ስለ ዋጋዋ አይመዘንም። …ስለ ዛጕልና ስለ አልማዝ አይነገርም። የጥበብ ዋጋ ከቀይ ዕንቍ ይልቅ ይበልጣል።” (ኢዮብ 28፡12፤13፤15 ፤18)
> [ይሄ ማለት ምዕራፍ 28 ቁጥር 12 ፤ 13 ፤15 ፤ 18]

ታዲያ ግራ እንደተጋባን እና እርግጠኛ እንዳልሆንን በሕይወት ውስጥ እንመላለስ? ወይስ የአንዱን እውነተኛ አምላክ ጥበብ እና እውነት እንወቅ።

ይሄንን ልንደርስበት ነው።

## የመጽሐፍት ስብስብ የሆነው መጽሐፍ

ባይብል (መጽሐፍ ቅዱስ) የሚለው ቃል የመጣው ቢብሊያ ከተሰኘ የግሪክ ቃል ነው፣ ትርጉሙም የመጽሐፍት ስብስብ የሆነ መጽሐፍ ወይም ቤተ መጽሐፍ ማለት ነው።



ለሁለት ሺህ አመታት ያክል በእነ አዳም፣ ኖህ፣ አብርሐም በኩል እና ለነሱ፣ በቃል መልዕክቱን ሲያስተላልፍ ከቆየ በኋላ እግዚአብሔር ከ15 ምዕተ ዓመታት ውስጥ መልዕክቱን በጽሁፍ ለማስቀመጥ 40 አካባቢ ሰዎችን ተጠቀመ። መልዕክተኞቹም ነብያት ወይም ሐዋርያት ተብለው ይጠራሉ። ነብይ የሚለው ቃል ቀጥተኛ ፍቺው የሚናገር ማለት ነው። ሐዋርያ ማለት መልዕክተኛ ማለት ነው። ዛሬ በአንድ ቅጽ የጻፉት መጽሐፍ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ በእጃችን ይገኛል። እንደ ቅዱሳት መጽሐፍት፣ የነብያት መጽሐፍት እና የእግዚአብሔር ቃል የሚሉት ቃላት መጽሐፍ ቅዱስን ለመግለጥ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ቶራ፣ መዝሙር እና ወንጌላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ክፍሎችን ይገልጣሉ። በአረብኛ ቅዱሳት መጽሐፍት አል ኪታብ አል ሙቀዳስ ማለት ቅዱሳን መጻሕፍት ይባላሉ።

በየክፍለ ዘመናቱ መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ የሚገኙ መጽሐፍትን መጽሐፍትን ሁሉ ብዙ በመሸጥ ይበልጣል። በሽያጭ ይበልጣል። እስከ ዛሬ ድረስ በክፍል ወይም በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በ2400 ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን በሌሎች 1940 ቋንቋዎች ደግሞ በመተርጎም ላይ ይገኛል።[5] የሚደርስበት ሌላ መጽሐፍ የለም።

በዝነኝነት ተወዳዳሪ የሌለው ከመሆኑ ባሻገር፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በጣም የተጠላ እና የተፈራ መጽሐፍ ነው። ባለፉት ክፍለ ዘመናት ፣ በዓለም ላይ የሚገኙ መንግሥታት እና መሪዎች፣ ሴኩላር የሆኑትም ሐይማኖተኞች፣ ይህንን የሁል ጊዜ ከፍተኛ ሽያጭ ያስመዘገበ መጽሐፍ ሕገወጥ ብለውታል ይዘውት የተገኙ ዜጎችንንም አሳደዋል ገድለዋል።[6] እስከ ዛሬ ድረስም አንዳንድ ሃገራት ይሄ ፖሊሲ አላቸው። አንዳንድ “ክርስቲያን” ሃገራት[7] ከሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና ተቋማት ታግዷል።

## ተገርፈዋል

እኔ ልጅ እያላሁ አባቴ ሪቻርድ የሚባል ጓደኛ ነበረው፣ ይሄ ሰው ለአሥራ አራት ዓመታት በምዕራብ አውሮፓ የኮሙኒስት ሃገራት እስር ቤቶች እንቅልፍ እየተከለከለ ፣ እየተራበ፣ ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ እየተገረፈ ፣ በማቀዘቀዣ ቤት ውስጥ እየቆለፈበት በጋለ ብረት እየተወጋ እና በቢላዋ እየተቆረጠ አሳልፏል። አንዳንድ ጥልቅና ለማየት የሚዘገንኑ ጠበሳዎቹን በዐይኔ አይቻለሁ። የሪቻርድ ባለቤት ታስራ በእስር ቤት ካምፕ የጉልበት ሥራ እንድትሰራ “በወንጀል ድርጊት” እንደ ባሏ ተደርጋ ነበር።[8]

በዚህ ኢ አማኒ በሆነ ሀገር ላይ የፈጸሙት ወንጀል ምን ይሆን?

ወንጀላቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለሌሎች ሲያስተምሩ መገኘታቸው ነበር።

## ተጠልተዋል

ጓደኛዬ ዐሊ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነበረ። አባትየው ወንዶቹ ብቻ የሚገኙበት የቤተሰብ ስብሰባ አዘጋጅቶጠራ።

ትልቁ አጎታቸውም በስፍራው ላይ ነበር።

ታናናሽ ወንድሞቹም ተጠርተው ነበር።

የበኩር ልጅ የሆነው ዐሊ ይገኝ የነበረው በመካከለኛው ምስራቅ ነበር።

የዐሊ አባት በስሜት የተሞላ ንግግር አደረገ፣ ንግግሩንም በዚህ መልክ አጠቃለለ፦ “ቤተሰባችንን አሳፍረኸል! ሃይማኖታችንን ክደሃል! ቤቱን ለቀህ ውጣ መቼም እንዳትመጣ። ፊትህንም ሁለተኛ እንዳላየው!”

አጎትየውን እንዲህ ሲል በተጨማሪ ተናገረ “አዎ፣ በነገው ዕለት ካልወጣህ ዕቃህን በሙሉ መንገድ ላይ እጥለዋለሁ!”

ቁጣው ለምን አስፈለገ?

መጽሐፍ ቅዱስን ለአንድ ዓመት ያህል ካነበበ በኋላ፣ ዐሊ ለማመን መረጠ።

## ሕያው ቃል

መጽሐፍ ቅዱስን እንዲህ አወዛጋቢ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

መንግሥታት እንዲከለክሉት ወላጆችም ልጆቻቸው ስላመኑት ልጆቻቸውን እንዲክዱ ያደረጋቸው ነገር ምክንያት ምንድን ነው?

በሚሊዩን የሚቆጠሩ “አንድ አምላኪዎች” ከኢ አማንያን ጋር ፣ ለዚህ ጥንታዊ ሥነ ጽሑፍ የጋራ ጥላቻ እንዲኖራቸው ያደረገው ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው፣ የሚሰራ፣ የሚወጋ፣ እና የሚለይ መሆኑን መናገሩ ከዚህ ጋር የሚያገናኘው ነገር አለ።

> “የእግዚአብሔር ቃል **ሕያው** ነውና፥ **የሚሠራም**፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ **ይወጋል**፥ የልብንም ስሜትና አሳብ **ይመረምራል**”
> (**ዕብራውያን** 4:12)

## በመጽሐፉ ጸንቶ መቆም

ባለቤቴ ፣እኔ እና አሁን ትልልቅ የሆኑ ልጆቻችን ያለፉትን 25 ዓመታት በአብዛኛው ያሳለፍነው ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ በምትገኘው ሴኔጋል ውስጥ ነው። ጎረቤቶቻችን የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች ናቸው። ሙስሊም ማለት የሚገዛ ማለት ነው። በሙስሊሞች የሚከበርው መጽሐፍ ደግሞ ቁርዓን ይባላል። የምጽፈው ነገር የመነጨው በሴኔጋል እና በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ከሙስሊም ጓደኞቼ እና ወዳጆቼ ጋር ካደረግኳቸው በሺዎች የሚቆጠሩ የግል ጭውውቶች ነው።

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስን እና ቁርዓንን ያጠናሁ ቢሆንም አንድ አምላክ አንድ መልዕክት የሚያተኩረው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። ከዓመታት በፊት ሴኔጋላዊ ጓደኛዬ እና እኔ በሴኔጋል በሚገኘው በዎሎፍ ቋንቋ 100 ተከታታይ የሬዲዮ ፕሮግራሞችን አዘጋጅተናል።[9] እያንዳንዱ ፕሮግራም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ነብያት አንድ ታሪክ እና አንድ መልዕክት የያዘ ነው። አንዳንድ አድማጮ ች “ለምን ቁርዓንንስ አታስተምርም?” የሚል ጥያቄ አቅርበውልኝ ነበር። መልሴ የሚከተለው ነው፦

በዚህ ሃገር ልጆች ሦስት ወይም አራት ዓመት ሲሞላቸው ቁርዓንን መቅራት ይጀምራሉ። የቁርዓን አስተማሪዎች እና ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ አካባቢ ይገኛሉ። ነገር ግን በቶራ፣ በመዝሙር እና በወንጌላት ውስጥ የሚገኙ መልዕክቶችን የሚያስተምር ማን ነው?" እንደምታወቁት ቁርዓን እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጽሐፍት በእግዚአብሔር ለሁሉም የተሰጡት "በውስጡ ብርሃን ያለበት... መሪና ገሳጭ" (ሱራ 5:46[10]) ቁርዓንም እንዲህ ይላል፦ "ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን **ከአንተ በፊት መጽሐፉን**[መጽሐፍ ቅዱስን] **የሚያነቡትን ጠይቅ**" (ሱራ10:94[11])። በመጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምኑት ቁርዓን እንዲህ ይላል፦ **"እላንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁ ወደናንተ የተወረደውን እስከታቆሙ (እስከምትሰሩባቸው) ድረስ** በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን ቁረአን" (ሱራ5:71) ከመጽሐፉ ሰዎች መካከል መጽሐፉን ሲያነብ እንደኖረ እና ለሦስት አሥርት ዓመታት ያህል ጸንቶ እንደኖረ ሰው ስምታችሁት የማታውቁትን የነብያትን ታሪክን እና መልዕክት ማስተዋወቅ ትልቅ ዕድል ነው። እነዚህ መጽሐፍት አንዳንዶቹ ከቁርዓን በ2000 ዓመት ቀድመው የተጻፉ ሲሆኑ የትም ቦታ የማይገኝ እውነት ይዘዋል።

## የእሱ ታሪክ

ወላጆቻችሁ"እንግዳበፍጹምአትመኑ"እያሉአስተምረዋችሁ ይሆናል። አንድን ሰው በእርግጠኝነት ከማመናችሁ በፊት፣ ስለዚያ ሰው ታሪክ ማወቅ መቻል አለባችሁ።

የምታምኗቸውን ጥቂት ሰዎች አስቡ።

ለምንድን ነው የምታምኗቸው?

የምታምኗቸው ከቆይታ ብዛት ተዓማኒ መሆናቸውን ስላወቃችሁ ነው። መልካም እንጂ ክፉ አላደረጉባችሁም። አንድ ነገር እናደረግላችኋለን ብለው ከነገሯችሁ በኋላ አድርገውላችኋል። አንድ ነገር እንሰጣችኋለን ካላችሁ፣ ሰጥተዋችኋል። ተዓማኒ መሆናቸውን ያወቃችሁበት ምክንያት ታሪካቸውን ስላወቃችሁ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከወንዶች፣ ከሴቶች እና

ከሕጻናት ጋር ስላደረገው ግንኙነት በመቶዎች የሚቆጠሩ ታሪካዊ ትረካዎችን ያቀረባል። እያንዳንዱ ታሪክ የሰማይና የምድር ፈጣሪን ለማግኘት ቃሉን ለመሰማት እና በሰው ልጆች የሺዎች ዓመታት ታሪከ ውስጥ ሥራዎቹን ለማየት ዕድል ይፈጥራል። ምን አይነት ነው? አዎ፣ ታላቅ ነው ፣ ነገር ግን ታላቅነቱ በምን አይነት መንገድ ነው? የማይለዋወጥ ነው? ራሱን ተቃርኖ ያውቅ ይሆን? ቃሉን ይጠብቅ ይሆን? ያታልለን ይሆን ? ሊታመን ይገባው ይሆን?

የእሱ ታሪክ እነዚህን ጥያቄዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎችን ይመልሳል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የታሪክ መጽሐፍ ሲሆን የሰው ልጅን ትልቁን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የራሱንም ታሪክ ይናገራል።

## ታላቁ ድራማ

ሁሉም ሰው መልካም ታሪክ ይወዳል።

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድነት ተጣምረው፣ ከታሪኮች ሁሉ ማራኪ የሆነ አንድ ታሪከ የሚሰጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ታሪኮችን ይዟል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔርና ሰው የሚያወራው ትረካ ታላቁ ምስጢራዊ ድራማ፣ የፍቅርና የጦርነት፣ የዕኩይ እና የበጎ ፣ የግጭትና የድል ታሪክ ነው። ከፍጥረት ጅማሬ ጀምሮ እስከ መጪው ዘመን ድረስ ለሕይወት ጥያቄ ምክንያታዊ የሚያረካ ምላሽ ይሰጣል። ከሌላው ታሪክ የተለየ ጡዘት እና ወደር የሌለው መደምደሚያ አለው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ሴኔጋል ውስጥ በሚገኘው ቤታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ታሪክ በአንድ ቡድን ውስጥ ለሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ነግሬ ከጨረስኩ በኋላ ፣ ከሴቶቹ መካከል አንዷ እንባዋ እየፈሰሰ እንዲህ አለች “የሚገርም ታሪክ ነው! እግዚአብሔርን የማያምኑ ሰዎች እንኳን እሱ የምንጊዜም ምርጥ የፊልም ጸሐፊ እንደሆነ ማመን አለባቸው!” ይህች ሴት እግዚአብሔር ራሱ ጸሐፊና ጀግና በሆነበት በክፍለ ዘመናችን ድራማ ውስጥ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚገናኙ ተረድታ ነበር።

## ታላቁ መልዕክት

መጽሐፍ ቅዱስ ከተነገሩን ምርጥ ታሪኮች ሁሉ የበለጠውን ታሪክ ይዟል። በትረካዎቹ ውስጥ ተነግሮ የማያውቅ የሚወደድ ከእግዚአብሔር የተላከ መልዕክት ይዟል።

ባለፉት ዓመታት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት በተመለከተ በሺዎች ከሚቆጠሩ ሙስሊሞች ጋር ተነጋግሬያለሁ። በርካቶቹ የግል ጓደኞቼ ናቸው ፤ ሌሎቹን ደግሞ የማውቃቸው በኢሜይል ነው። በሁለቱም ዐውዶች ውስጥ ብዙዎቹ ውይይቶቻችን በአንድ ጥያቄ ሊጠቀለሉ ይችላሉ፦

የአንዱ እውነተኛ አምላክ መልዕክት ምንድን ነው?

## የኢሜይል ምላሽ

ይሄ ጥያቄ በበርካታ መልክ ይቀርባል።

የሚከተለው ኢሜይል ከመካከለኛው ምስራቅ የተላከልኝ ነው፤ ላኪውን አሕመድ ብለን እንጥራው።[12]

ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

ሰላም ነህ። ኢየሱስ መሲህ ሆኖ ነው የመጣው ፣ እኔም በዚያ አምናለሁ ነገር ግን አምላክ ነኝ ብሎ አያውቅም። ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ[13]) በፊት የመጣ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ነበር፤ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ክርስቲያኖች በሙሉ ሙስሊም መሆን መቻል አለባቸው ፣ ምክንያቱም ክርስቶስ በዓለም መጨረሻ ሲመጣ የሚገዛው በአዲስ ኪዳን ሳይሆን በቁርዓን ነው።

ክርስቶስ በፍጹም አልተሰቀለም ምክንያታዊ መሆን ከፈለክ ፣ ኢየሱስ ተሰቅሎ ቢሆን እንኳን ፣ ከዚያ የተነሳ የሰዎች ኀጢአት ተሰርዟል ማለት አንችልም። ይሄ ለእኔ ምንም ስሜት አይሰጠኝም። ከዚህም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር ብቸኛ እና ልዩ ልጁን መሰዋዕት አደረገው ልትለኝ ትችላለህ። እኔም እንዲህ እልኻለሁ እግዚአብሔር ታላቅ ከሆነ ከሰዎች የሚፈልገውን ሊነግራቸው አይችልም "ውድ ልጁን" መሰዋዕት ሳያደርግ ሳያሰቃይ ኀጢአታቸውን ይቅር ሊል አይችልም???! ኀጢአት የምትሉት ነገር ለእኔ አይገባኝም።

እስልምና ወደ ምድር ከተላኩ ሐይማኖቶች ሁሉ ፍጹሙ ነው፤ እውነት ነው ብዬ እንዳስብ የሚያደርገኝም ያ ነው በተጨማሪም በእግዚአብሔር የተላከ የመጨረሻ ሐይማኖት ነው። በሆነ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ሐሳብ ምን እንደሆነ እንደትገምቱ አልተተዋችሁም።

ቁርዓን ከነብይ የተላከ ታላቅ ተዓምር ነው! እሺ ተመሳሳይ የሆነ አንድ ጥቅስ ወይም የሚቀርበው እንኳን ጻፉ ! አትችሉም በተከበረው የዐረብኛ ቋንቋ እንደበታችሁን የፈታችሁ ብትሆኑ እንኳን አትችሉም...

ከዚህም በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ የእውነተኛውን ፣ የነብዩ መሐመድን መምጣት የሚያሳዩ ትንቢታት አሉ...

እኔ እንደማምነው እና እንደማወቀው አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው የተሳሳተ እና መጻሕፍቱ በሙሉ ስለተነካኩ፣ የተበረዘ ነው...

ወዳጄ ለመረጃ እንዲሆንህ ፣ አዲስ ኪዳንን አንብቤያለሁ እውነት ለመፈለግ

> ሳይሆን ለግል ፍላጎቴ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜ
>
> እናም በታላቅነት፣ በእርግጥም የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ፣ በመልዐኩ በኩል ከነብዩ መሐመድ የተላከውን ቁርዓንን የሚቀርብ መጽሐፍ በዓለም ላይ የለም። ይህ ስህተት ነው የምትል ከሆነ አሳይ [ከነስህተቱ የተጠቀሰ[14]]
>
> ሰላም፣ "አሕመድ"

አሕመድ ያቀረበው ሙግት እና አስተያየት ችላ ሊባል አይገባም።

ፈጣሪያችን እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን በቀላሉ ስለማይመለከታቸው፣ እኛም በቀላሉ ማየት የለብንም። በጥንታውያን የነብያት መጽሐፍት እግዚአብሔር በአህመድ ለተነሱ ጥያቄዎች ግልጽ ምላሽ ስጥቷል ፤ ምክንያቱም ከዘላለም ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው፦

የብቸኛው እውነተኛ አምላክ መልዕክት **ምንድን** ነው?

ነብዩ ኢዮብ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን አንስቶ ነበር፦

"…ጥበብ የምትገኘው ወዴት ነው?" (ኢዮብ 28:12)

"ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን እንዴት ይችላል?" (ኢዮብ 9:2)

## ጉዞው

ግራ በተጋባና በሺዎች በሚቆጠሩ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ምላሾች በሚሰጡበት ዓለም ፣ የእኔን ምላሽ መቀላቀል ዓላማዬ አይደለም። ከዚህ ይልቅ የመጽሐፍት ስብስብ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ የሕይወትን ዋና ዋና ጥያቄዎችን ለመመለስ አብራችሁኝ ጉዞ እንድታደርጉ እጋብዛችኋለሁ። አብረን በምንጓዝበትም ጊዜ እንደ ቅዱሳት መጽሐፍት፣ እውነት የሆነው ምን እንደሆነ እናያለን በአሕመድ እና በሌሎች ለተነሱ ጥያቄዎች ነብያት የሚሰጡትን ምላሽ እናሰላስላለን።

የመግቢያ ገለጻ ከሚሰጥበት ጊዜ ጀምሮ (ክፍል ፩ ፦ ምዕራፍ 1-7) ጉዟችን መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምርበት ቦታ ላይ ይጀምራል፦ የዓለም ታሪክ ጅማሬ። ከዚያ ተነስተን በጊዜ ውስጥ አልፈን እስከ ዘላለም እንጓዛለን። (ክፍል ፪ እና ፫፦ ከምዕራፍ 8-30)

ጉዟችን የሚጠናቀቀው መንግሥተ ሰማያትን ራሱን ከጎበኘን በኋላ ነው።

## የጉዞ አማራጭ

አንድ አምላክ አንድ መልዕክት ሦስት መጽሐፍት በአንድ ያሰባሰበ ተጷርጎ ሊታይ ይችላልል። ክፍል ፩ ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያነቡ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች ይዳስሳል። ክፍል ፪ ከታሪኮች ሁሉ የበለጠውን ታሪክ ዋና መልዕክት ይገልጣል። ክፍል ፫ ከመጋረጃው ጀርባ ገብቶ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው አስገራሚ ዓላማ በጥልቀት ይመለከታል።

ብዙ ተጓዦች የመጀመሪያውን ክፍል ለጉዞ ለሚያደርጉት ዝግጅት በጣም ጠቃሚ አድርገው ያዩታል። ቢሆንም እንኳን አስቀድማችሁ የነብያት መጽሐፍት ተዓማኒ መሆናቸውን ካወቃችሁ እና መልዕክቱ መልዕክቱ ቶሎ የሚገባችሁ ከሆነ ወደ ክፍል ፪ መግባት ትችላላችሁ። አንዴ ጉዞውን ካጠናቀቃችሁ በኋላ ክፍል ፩ ማንበብ ትችላላችሁ።

ያለ ጥድፊያ መጓዝ ከፈለጋችሁ ፥ መጽሐፍቱን ለአንድ ወር እንዲበቃችሁ በ 30 ምዕራፎች በመክፈል በቀን አንድ ምዕራፍ ማሰላሰል ትችላላችሁ። ሙስሊም ከሆናች ይህንን የ 30 ቀናት ጉዞ በረመዷን ወቅት ማድረግ ትችላላችሁ፤ ቁርዓን “በሐይማኖት ማስገደድ የለም፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው መንገድ በርግጥ ተገለጠ” በተጨማሪም “በአላህ ወደኛ በተወረደው (ቁረአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነብያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።” (ቁርዓን ፣ ሱራ 2:256 ፣ 136 ፒክትሃል[15]) ስለሚል በመተማመን ጉዟችሁን መቀጠል ትችላላችሁ።

የትኛውንም መንገድ ምረጡ ፣ ለጉዞ የሚረዳችሁ ጠቃሚ ጥቆማ ይኸውላችሁ፦ አንድ ጊዜ ከጀመራችሁ የጉዞውን የትኛውንም ክፍል አትዝለሉ።

እያንዳንዱ ቀጣይ ክፍል በቀደመው ላይ የተመሠረተ ነው’። ምንም እንኳን ያያችሁትን ሁሉ ወዲያውኑ መረዳት ባትችሉም፤ ማነበባችሁን እና ማሰላሰላችሁን እስከ መጨረሻ ገጽ ድረስ ቀጥሉ። አንዳንድ የጉዞው ክፍሎች እንግዳና ሞጋች ሊሆኑ ይችላሉ ፤ ነገር ግን በጉዟችሁ ላይ ጥማችሁን የሚያረካ የበረኸ ውስጥ ምንጭ ታገኛላችሁ።

ምንም ያክል ቁጥር ያለው እንቅፋት ቢያጋጥማችሁ ጉዟችሁን ቀጥሉ።

## እውነት

በምድር ላይ የሚገኙ በርካታ ሰዎች የሕይወትን ታላላቅ ጥያቄዎችን በተመለከተ እውነቱ እና ውሸት ማንም ሰው ሊያውቅ አይችልም ብለው ያስባሉ፦ የሰው ልጅ ዝርያ የተገኘው ከየት ነው? ምድር ላይ ያለሁት ለምድን ነው? ወዴት እያመራሁ ነው ? ትክክለኛ የሆነው እና ስህተት የሆነው ምንድን ነው ?

ዛሬ በምዕራባውያን ዘንድ "ሁሉም ነገር አንፃራዊ ነው?" ወይም "ፍፁማዊ እውነትን ሰው ሊያውቅ ይችላል ብሎ ማስብ ስህተት ነው" የሚሉ ሐሳቦችን መናገር የተለመደ ነው፡፡ የእነዚህን አባባሎች ራሳቸውን የሚቃረኑ ስህተቶች ለማሳየት፣ ብዙ ዲግሪ መያዝ አያስፈልግም፡፡ ፍጹማዊ እውነት ከሌለ ያንን አመለካከት የያዙ ሰዎች "ስለ ሁሉ ነገር" ለምን ይናገራሉ ወይም የትኛውንም ነገር ለምን "ስህተት" ይላሉ?

እውነትን ለሰው ልጆች የገለጠውን የዓለማትን ፈጣሪ በሰዎች አሰተያየት ስለማይመራ ልናመስግነው ይገባል፡፡ በቅን ልብ ለሚፈልጉት እንዲህ ይላል፦

> "**እውነትንም ታውቃላችሁ** እውነትም አርነት ያወጣችኋል…" (ዮሐንስ 8:32)

## ትክክለኛ ምርጫ

ከጥቂት ዓመታት በፊት የ79 ዓመት ዕድሜ ያለው ጎረቤቴ ሙሳ ታሞ ነበር፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዳነብለት በሣምንት ሦስት ቀን እንድጎበኘው ጠየቀኝ፡፡ ሙሳ ቁርዓንን ዕድሜውን በሙሉ አጥንቷል፤ ነገር ግን ቁርዓን ሙስሊሞች በሙሉ እንዲቀበሏቸው እና እንዲያነቧቸው የሚያዛቸውን የሙሴን ቶራ ፣ የዳዊትን መዝሙር ፣ ስለ ኢየሱስ የተጻፉትን ወንጌላት ለማንበብ ጊዜ አልወሰደም ነበር፡፡[16]

ሙሳ ቁልፍ ታሪኮችን በቀደም ተከተላቸው ስናጠና በጥንቃቄ ያዳምጥ ነበር፤ የረከሱ ኃጢአተኞች በፈጣሪያቸው እና በዳኛቸው እንዴት ጻድቅ እንደሚባሉ ተማረ፡፡ ከአንድ ጊዜ በላይ ሙሳ "ከእያንዳንዱ ትምህርት በኋላ ስለተማርናቸው ነገሮች አሰላስላለሁ እንጂ አላስብም !" ሲል ነገረኝ፡፡

አንድ ቀን በመጻሕፍት ውስጥ የተገለጠውን አንድ እውነት ከተማረ በኋላ በግልጽ በሚታይ ተስፋ መቁረጥ ፣ ሙሳ በቅርቡ ተቀምጣ ለነበረችው ለባለቤቱ "ለምንድን ነው አንድም ሰው እነዚህን ነገሮች ያላስተማረን?" አላት፡፡

በስተኋላም የሙሳ ጎረቤቶች ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ እያጠና መሆኑን ሲያውቁ ወሬው ተዛመት፡፡ ጫናው ሰለ በረታበት፥ ሽማግሌው ወዳጄ ለአጭር ጊዜ መምጣት እንዳቆም ጠየቀኝ፤ እንዲህ በማለትም አብራራልኝ “እውነቱን አልቀበልም እያልኩ አይደለም፤ በቤተሰቤ ላይ እየደረሰ ያለው ጫና ከፍተኛ ነው፡፡”

ለስድስት ሣምንታት ከጠበቅኩ በኋላ (ሀሜቱ እስኪቆም) ባለቤቴና እኔ ሙሳንና ቤተስቡ ለመጎብኘት ሄድን፡፡ እሱም ሞቅ ባለ ሁኔታ ከተቀበለን በኋላ በደንብ የታሰበባቸው ጥያቄዎች ጠየቀ፡፡ ከመሄዳችን በፊት እንዲህ አለ “አስፈላጊው ነገር ከመሞቴ በፊት ትክክለኛ ውሳኔ መወሰኔ ነው!”

ሙሳ “እውነትን ግዛት እንጂ አትሸጣት”[17] የሚለው ቃል አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ ነበር፡፡ ከአራት ወራት በኋላ ውድ ወዳጃችን አረፈ፡፡

ያሳለፍናቸውን ጊዜያት በማስታወስ ለጥያቄ የሰጠውን መልስ አልረሳም፦ “ሙሳ ዛሬ ብትሞት ዘላለምን የምታሳልፊው የት ነው?”

ትንሽ ካቅማማ በኋላ “መንግሥተ ሰማያት እገባለሁ!” ሲል መለስ፡፡

“እንዴት ታውቃለህ?” ስል ጠየቅኩት፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱን በሁለት እጁ ይዞ እንዲህ ሲል ምላሽ ሰጠ “ይሄንን ስለማምን!”

## የተስፋ ቃል

ይህንን ጉዞ እንደ ሙሳ ከመሞታችሁ በፊት ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰን ለምትፈልጉ ሰዎች መታሰቢያ አድርጌዋለሁ፡፡ እውነተኛው አምላክ እጃችሁን ይዞ እያንዳንዱ እንቅፋት እንድታልፉ ይርዳችሁ፣ በተጨማሪም እሱ ማን እንደሆነ እና ምን እንደሰራላችሁ በግልጽ እና በትክክል እንድትረዱ ይምራችሁ፡፡

> “እናንተ ትሹኛላችሁ፥ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ፡፡” (ኤርሚያስ 29:13)

ይሄ እግዚአብሔር ለእናንተ የገባው የተስፋ ቃል ነው፡፡




“አላዋቂነት ሳታስቡት ይገድላችኋል”

— የወሎፍ አባባል

ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት ፣ እግዚአብሔር እንዲህ አለ “ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል”(ሆሴዕ 4:6) እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ሰዎች የኮሌጅ ዲግሪ ያላቸውን ጨምሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ነብያት የጻፉትን በተመለከተ ምንም ሳያውቁ ይሞታሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስን ጥንታዊነት እና ተጽዕኖ ከግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን መሠረታዊ ነገር የማውቅን ሰው የተማረ ነው ማለትን እንችል ይሆን?

የዓለም ሕዝብ በሺዎች የሚቆጠሩ ሐይማኖቶችን እንደ ፈጠረ ሁሉ ፣ ቅዱሳት መጽሐፍትን ቸል ለማለት በሺዎች የሚቆጠሩ ምክንያቶች አሉት። በዚህ ምዕራፍ እና በሚቀጥለው ምዕራፍ ከእነዛ ውስጥ አሥሩን ምክንያቶች እንመለከታለን። አንድ ጊዜ ጉዟችንን ከጀመርን እንዲህ አይነት መሰናክሎችን መጠበቅ እና በርካቶቹን ደግሞ ማለፍ አለብን።

## ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የማይቀበሉባቸው አሥር “ምክንያቶች” ፡-

### 1. “አፈ ታሪክ”

ሴኩላራዊ በሆኑ ምዕራባውያን እና የአውሮፓ ሃገራት፣ መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች ከተፈጠሩ ደስ ከሚሉ አፈ ታሪኮችና

ከሚያማምሩ አባባሎች የተለየ አይደለም። ብዙዎች እንዲህ አይነት አስተሳሰብ የሚይዙት መጽሐፍ ቅዱስን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ሳያጠኑ ነው።

በሰር አርተር ኮናን ዶይል ልብ ወለዳዊ ታሪክ ዘ ሴሌብሬትድ ኬዝ ኦኦፍ ሼርሎክ ሆልምስ ፣ የምርመራ ባልደረባዉ ዶ/ር ዋትሰን የተለየ የወንጀል ድርጊት ሲያጋጥመው እንዲህ የሚል ጥያቄ ይጠይቀዋል፦

"ከዚህ ተነስተህ ምን ድምዳሜ ላይ ደረስክ?"

ሆልምስ "ምንም መረጃ የለኝም" ሲል ይመልሳል። "አንድ ሰው መረጃ ሳይኖረው ጽንሰ ሃሳብ ማፍለቁ ትልቅ ስህተት ነው። ጽንሰ ሐሳቡ ከእውነታው ጋር እንዲስማማ ከማድረግ ይልቅ፣ ጽንሰ ሐሳቡን እንዲስማማ እውነታውን ማጣመም ይጀምራል።" [18]

ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ይህንን "ትልቅ ስህተት" ይሰራሉ። ድምዳሜያቸው ላይ ያለበቂ መረጃ ይደርሳሉ፤ በተጨማሪም የራሳቸውን ንጽረተ ዓለም እና የህይወት ዘዬ እንዳይለውጡ እውነታዎቹን ይጠመዝዛሉ።

## 2. "በርካታ ፍቺዎች"

ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የማያነቡት አንደኛው ቡድን "መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ይላል!" ሲል ሌላኛው ደግሞ ይህንን በመቃወም "በፍጹም ያንን ማለቱ አይደለም! የሚለው ይህንን ነው!" ሲል በስማታቸው ነው። ከዚህ በመነሳት መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት አይቻልም የሚለው ቅድመ ዕሳቤ ብዙ የሚስገርም አይደለም።

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ በተወሰኑ የሕይወት ጉዳዮች[19] ዙሪያ የተለያዩ አመለካከቶች እንዲኖሩ ቢፈቅድም ፣ ዘላለማዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ግን የተለያየ ፍቺ እንዲኖር በር አይከፍትም። የእግዚአብሔርን መጽሐፍ መረዳት ይቻላል ፣ ነገር ግን የሚናገረውን ማስተዋል አለብን።

ዝነኛው ሼርሎክ ሆልምስ ለዋትሰን እንዲህ ይለዋል "ታያለህ ነገር ግን አትመለከትም። ልዩነቱ ግልጽ ነው። ለምሳሌ ወደዚህ አዳራሽ የሚያስገባውን ደረጃ ብዙ ጊዜ አይተኸዋል"

"ብዙ ጊዜ አይቼዋለሁ።"

"ምን ያህል ጊዜ?" ሲል ጠየቀ ሆልምስ።

"እንግዲህ መቶ ጊዜ ያህል" ሲል መለሰ ዋትሰን።

"ስንት ደረጃዎች አሉት?"

"ስንት! አላውቅም"

“አያስገርምም! አልተመለከትክም! ነገር ግን አይተኻል። ነጥቤ ያ ነው። አስራ ሰባት ደረጃዎች እንዳሉት አሁን አውቄያለሁ። ምክንያቱም አይቻለሁ፤ ተመልክቻለሁም።”[20]

በተመሳሳይ መልኩ በርካታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት የተሰባሰቡ ሐሳቦችን ብዙዎች አይተዋል የተመለከቱ ግን ጥቂቶች ናቸው። ከዚህም የተነሳ ሰዎች የተለያዩ ፍቺዎችን ቢሰጧቸው አይደንቅም።

ግልጽ የሚያደርግልን የሚከተለው ጥያቄ ነው፦ የእግዚአብሔርን መልዕክት መረዳት እፈልጋለሁ? የተሰወረ ሐብት በምፈልግበት መሰጠት እና ትጋት የእግዚአብሔርን እውነት ለመፈለግ ዝግጁ ነኝ? ንጉስ ሰለሞን እንዲህ ብሏል፦ “ረቂቅ እውቀትን ብትጠራት፥ ለማስተዋልም ድምፅህን ብታነሣ፤እርስዋንም እንደ ብር ብትፈላልጋት፥ እርስዋንም እንደ ተቀበረ ገንዘብ ብትሻት፤ የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት ታውቃለህ፥ የአምላክንም እውቀት ታገኛለህ።” (ምሳሌ 2፡3-5)

### 3. “ክርስቲያኖች”

ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን የማይቀበሉት እንከተለዋለን በሚሉ ሰዎች ከተሰራው ክፋት የተነሳ ነው። “‘መናፍቃን’ በመስቀል ዐርማነት የታረዱባቸው የመሰቀል ጦርነቶችስ?” ሲሉ ይጠይቃሉ። “የምርመራውስ ጉዳይ? በዚህ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን የሚሉ ሰዎች የሚፈጽሙትስ ግፍስ?” እውነታው ግን ክርስቲያን (ክርስቶስን የሚመስል ማለት ነው) የሚለውን መጠሪያ የያዘ፣ የኢየሱስን ፍቅር እና ርህራሄ የማያሳይ ግለሰብ፣ እየኖረው ያለው የኢየሱስን ምሳሌና ትምህርት የማያሳይ ሕይወት ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፦ “ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ።” (ማቴዎስ 5፡43-44 አመት)

ሌሎች እንዲህ ሲሉ ይጠይቃሉ፤ “በአጨበርባሪነት ፣ በስካር እና በዝሙት የሚኖሩ ክርስቲያኖችስ?” በድጋሚ በሞራላዊ ርኩስት ውስጥ የሚኖር ግለሰብ፣የሚከተለውን የሚሉትን ቅዱሳት መጽሐፍትን ባለመታዘዝ የሚኖር ሰው ነው፥ “ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም

አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።" (1 ቆሮንቶስ 6:9-11) "መጽደቅ" ማለት የጻድቅነታችን መታወጅ ነው። በሰተኋላ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በምናደርገው ጉዞ ሳጢአተኞች በእግዚአብሔር እንዴት ይቅር እንደሚባሉና ጻድቅ እንደሚባሉ እናያለን።

አሁንም ሌሎች እንዲህ ሲሉ ይጠይቃሉ "በማርያምና በቅዱሳን ሐውልት ፊት የሚሰግዱ ክርስቲያኖችስ?" በአጭሩ እነዚህን ነገሮች የሚለማመዱ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ የቤተክርስቲያናቸውን ልማድ እየተከተሉ ነው፦ "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ለእናንተ ጣዖት አታድርጉ፥ የተቀረጸም ምስል ወይም ሐውልት አታቁሙ፤ ትሰግዱለትም ዘንድ በምድራችሁ ላይ የተቀረጸ ድንጋይ አታኑሩ።" (ዘሌዋውያን 26:1) በሐውልታት ስር መሰገድ፣ የሰው ልጅን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ሥልጣን በላይ ማየት ብቸኛውን እውነተኛ አምላክ ሳያውቁ ልማዳዊ በሆነ መንገድ መጸለይ የጣዕት አምልኮ አይነቶች ናቸው። ብዙዎች ክርስቲያን እና ካቶሊክ የሚሉ ቃላት አንድ አይነት እየመሰሏቸው ግራ ይጋባሉ። አይደሉም። ክርስትናና ፕሮቴስታንትም አንድ አይነት አይደሉም። ጋጣ ውስጥ መኖር አንድን ሰው ፈረስ እንደማያደርገው ሁሉ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መግባት እና መውጣትም ክርስቲያን አያደረገውም።

## 4. "ግብዞች"

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ላለማንበባቸው የሚሰጡት ሌላው ምክንያት "ሁሉም ግብዞች ናቸው" የሚል ነው። በሚያሳዝን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን የሚሉ ሰዎች፥ አንድ ነገር ያምናሉ ሌላ ነገር ይኖራሉ። የእግዚአብሔርን መልዕክት ያጣምማሉ ስሙንም ለራሳቸው ዓላማ ይጠቀሙበታል። ብዙ ሰባኪያን ራሳቸውን የማይገዙ እና ሥነምግባር የጎደላቸው ናቸው። አንዳንዶች ገንዘብ ከላካችሁላቸው በጤና እና በገንዘብ እንደምትባረኩ ይናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ያሉትን አሰመሳዮች እንዲህ ሲል ያጋልጣል "አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ፥ እግዚአብሔርን መምሰል

ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እንደነዚህ ካሉት ራቅ።” (1ጢሞቴዎስ 6:5)

ኢየሱስ በሱ ዘመን ለነበሩ ራስ ወዳድ ፣ ግልብ የሐይማኖት መሪዎች እንዲህ ብሏቸዋል፦

> “እናንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ፦ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ።”
> (ማቴዎስ 15:7-9)

> ለደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ እንደህ ብሏል “ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና።”
> (ማቴዎስ 6:5)

ምንም እንኳን እያንዳንዳችን በሆነ አይነት ግብዝነት (ያልሆንነውን ነን በማለት) ተጠያቂ ብንሆንም፥ የሌላ ሰው ግብዝነት ፈጣሪያችንን እንዳናውቅ እና እሱ ያሰበው አይነት ሰዎች እንዳንሆን፣ በቃሉ በኩል እንዲለውጠን ከማድረግ እንድንቆጠብ አያደርገንም?

## 5. “ዘረኛነት”

አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን የማይቀበሉት የተወሰኑ ቡድኖችን ከሌሎች ቡድኖች አስበልጦ ያያል በሚል ነው። ምንም እንኳን ብዙዎቻችን በሆነ ዐይነት የዘር መድልዖ ወይም ጎሰኝነት (አንደኛውን ጎሳ ከሌላው አሰበልጦ ማየት)፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ግልጽ ነው “እግዚአብሔር አያዳላም።” (ሐዋርያት 10:34 አመት)

ለምሳሌ ነብዩ ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሴት እንዳገባ ታውቃላችሁ?[21] የሶርያውያን የጦር መሪ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ባዋረደ ጊዜ፥ እግዚአብሔር በነብዩ ኤልሳዕ በኩል ከለምጽ እንዳነጻው የሚናገረውን ታሪክ አላነበባችሁም?[22] ወይም ደግሞ እግዚአብሔር የአይሁድ ነብይ የሆነውን ዮናስን የንሰሐና የመዳን መልዕክቱን ለነነዌ (ኢራቅ ውስጥ የምትገኝ) አላዘዘውም? ዮናስ ነነዌያውያንን ስለሚጠላቸው እግዚአብሔር እንዲያጠፋቸው ፈልጎ ነበር ፣ እግዚአብሔር ግን ወዷቸው ምህረትን አሳያቸው።[23] በእግዚእብሔር ዓለምን የመቤዠት ታሪክ ውስጥ ፋርስ (ኢራን) የተጫወተችውን ሚና ታውቃላችሁ?[24] ምንም እንኳን አይሁድ

ሰማርያ ባይደርሱና ሳምራውያንን “ርኩስ” ብለው ቢጠሯቸውም ልብ የሚነካውን ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት የዘላለም ሕይወት ያካፈለበትን ታሪክ አይታችኋል?[25]

ዓለማችን በዘረኝነት ተጥለቀልቋል፤አምላካችን ግን ዘረኛ አይደለም። በእሱ ዐይን አንድ ዘር አለ፤ እሱም የሰው ዘር ነው።

> “ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም። ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፣ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ፦ እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደ ተናገሩ፥ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን።” (ሐዋርያት 17:24-28)

እግዚአብሔር ሰዎችን “ከአንድ ደም” አበጀ የሚለው አዋጅ በዘመናዊ ሳይንስም የተረጋገጠ ነው። ሳይንስ እንዲህ ይላል “የሰው ልጅ የዘረ መል ኮድ ወይም ጂኖም በዓለም ላይ 99.9 በመቶ ተመሳሳይ ነው። የቀረው ለግላዊ ልዩነቶቻችን ተጠያቂ የሆነው ዲኤን ኤ ነው፤ ማለትም ለምሳሌ የዐይን ቀለም ወይም የበሽታ ተጋላጭነት።”[26]

“የሰማይና የምድር” ፈጣሪና ባልቤት “ከሁላችን ሩቅ ያልሆነው” ለእኔ እና ለእናንተ በግል ይጠነቀቃል፣ “ጌታን እንድንፈልግ” እና መልዕክቱንም እንድንረዳ ይፈልጋል። የልደታችንን ዝርዝር በሙሉ አቀናጅቷል። ከእያንዳንዱ ሐገር፣ ቋንቋ፣ ባህልና ቀለም የመጡ ሰዎችን ይወዳል፤ በተጨማሪም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስሙን እንዲጠሩ ይጋብዛቸዋል።

## 6. “የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ግድያን ይፈቅዳል”

የሚከተለው ኢሜይል የደረሰኝ ከኢሰማኒ (ወይም ሴኩላር ሂዩማኒስት ተብሎ መጠራትን ይመርጣል)፦

መልሰህ ርዕሰ ጉዳይ የኢሜይል ምላሽ

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ “እኔ ጌታ እግዚአብሔር በምህረትና በርህራሄ የተሞላሁ በቀላሉ የማልቆጣ ታላቅ ፍቅርንን ታማኝነትን የማሳይ ነኝ” ጥሩ ራስን የማሞካሸ ቃላት ናቸው ፣ ነገር ግን እንዳቸውም ከድርጊቱ ጋር ሊታረቁ አይችሉም። በታህሳስ 2004 ዓ.ም በደቡብ ምሥራቅ ኢሲያ በተከሰተው ሱናሚ ሩብ ሚሊዮን ሰዎች እንዲሞቱ ሲፈቀድ እግዚአብሔር አፍቃሪ አይመስልም። ወደ ከነዓን መግባት ተብሎ በሚጠራዉ ጉዞ የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ሰላማዊ የሆኑ ወንዶች ፣ ሴቶች ሕፃናት እና ጭቅላዎች እንዲገደሉ ያዝዛል.... ታዲያ ለምንድን ነው የሰው ልጆች “ፈጣሪ” ተብሎ ከሚጠራ አካል የበለጠ ርህራሄ የኖረው ለምንድን ነው? መከልከል እየቻልኩ ግጭት፣ ጥላቻ፣ ጦርነት፣ ግድያ፣ ስቃይ፣ ሐዘን እና ሰቆቃ በዚህች ፕላኔት ላይ እንዲኖሩ በፍጹም ለፈቅድ አልችልም። በጣቴ ድምጽ ምልክት በመስጠት ብቻ አሁኑኑ አስቆመዋለሁ !

ብዙዎች “እግዚአብሔር መልካምና ሁሉን ቻይ ከሆነ ክፋትን ያላስቆመው ለምንድን ነው?” ሲሉ ይጠይቃሉ። ነገር ግን ጥቂቶች “እግዚአብሔር መልካምና ሁሉን ቻይ ከሆነ፥ እኔ ክፉ ነገር ስሰራ የማያስቆመኝ ለምንድን ነው?” ሲሉ ይጠይቃሉ። እግዚአብሔር በክፋት ላይ እንዲፈርድ እንፈልጋለን፣ ነገር ግን እኛ ላይ እንዲፈረድ አንፈልግም።

ይህንን ወጥነት የሌለው አስተሳሰብ ልብ ካላችሁ፣ ሂዩማኒስት ነኝ ነው የሚለው ወንድማችን ከባድ ጥያቄዎችን እንዳነሳ መቀበል አለብን። ምንም እንኳን ቀላል ምላሾች ባይኖሩም፣ አጥጋቢ ምላሾች ግን አሉ። ወደኋላ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በምናደረገው ጉዞ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ፊት ለፊት በምናይበት እና የኃጢአትን ዘለቄታዊ ጦስ በምናይበት ጊዜ የእግዚአብሔርም ምላሽ ግልጽ ይሆንልናል። ከዚያ በፊት ግን ፈጣሪያችን የወንዶች፣ የሴቶች፣ የሕጻናት እና የጨቅላዎች ሕይወትን የሚቀጥፍ ቅጣትን ሲፈቅድና ሲያዝ እንዳንፈርድበት የሚያደርጉን ሦስት መርሖዎች የሚከተሉት ናቸው፦

### 1) ሰው የሚያየው ጥቂቱን ሲሆን እግዚአብሔር ግን ሙሉውን ያያል።

ሰዎች “ንጹሐን” ሰዎች “ያለ ጊዜያቸው” የሞቱበት “ኢፍትሐዊ” አሳዛኝ ተግባራት ብለው የሚመድቡትን ነገር እግዚአብሔር የሚያየው ከዘላለም አንጻር ነው። የዚያ ሰው ቅጽበታዊ ምድራዊ ሕይወት የዋናው ትዕይንት መግቢያ ነው።[27]

ሕይወታችን በዐይናችን ከምናየው የበለጠ ነገር ነው። ይህንን በምሳሌ ለመሰረዳት ጽንስን በእናቱ ማህጸን ውስጥ ተመልከቱት። በተገደበው ንጽረተ ዓለሙ ውስጥ ሆኖ ምክንያታዊ መሆን ከቻለ እግዚአብሔርን እንዲህ ሊለው ይችላል፦ “እኔና እና ሌሎች ያልተወለዱ ሕጻናት በጽንስ ከረጢት ውስጥ መቋጠር ያሰፈለገን ለምንድን ነው? ወጪ ያሉ ሕጻናት ሲስቁና ሲጫወቱ እንሰማለን እኛ ግን ያለነው እዚህ ጨለማ ውሃማ ዓለም ውስጥ ነው! ተገቢ አይደለም! እኔ ጽንሱ እንኳን ከፈጣሪ የበለጠ ርህራሄ ያለኝ ለምንድን ነው?

በግልጽ እንደምናየው ፣ ያልተወለዱ ልጆች ፈጣሪያቸውን በዚህ መልኩ አይሞግቱም አዋቂዎች ግን ይህንን ያደርጋሉ። “ነገር ግን ለእግዚአብሔር መልስ የምትሰጥ አንተ ማን ነህ? ሥራ ሠሪው ‘ለምን እንደዚህ ሠራኸኝ ይለዋልን?’” (ሮሜ 9:20 አመት)

2) **ለሰው ስህተት የሆነው ነገር ለእግዚአብሔር ስህተት አይደለም።**

የሕይወት ምንጭና መሠረት አንደ መሆኑ መጠን የማጥፋት መብት አለው። ነብዩ ኢዮብ ንብረቱን በሙሉ እና አስር ልጆቹን በተከታታይ አደጋ ካጣ በኋላ “ዕራቁቴን ከእናቴ ማሕጸን ወጣሁ፤ ዕራቁቴን እሄዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ ፣ የእግዚአብሔር ስም ብሩክ ይሁን።” (ኢዮብ 1:21-22 አመት)

የሚቀጠለው ጉዟችን ከመጋረጃ በሰተጀርባ ያለውን ያልተለመደ ግን እንግዳ ነገር ግን ጥበበኛ የእግዚአብሔር ንድፍ እናያለን።[28] ሉዓላዊውን የአጽናፈ ዓለሙን ገዢ ፣ ሰዎች እንዲወዱት እና እንዲታዘዙት የማያስገድደውን አምላክ እናገኘዋለን። ዓለም አሁን ባለበት አሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ የሆነበትን ምክንያት እናያለን።

3) **በመጨረሻም ፍጹም የሆነውን ፍትሁን ለሁሉም ይፈጽማል።**

ያለፈውን እና የአሁኑ ችግር ለመረዳት ጥረት ስናደርግ፣ እኛ ሳንሆን ፈጣሪያችን ስለያንዳንዱ ነፍስ መረጃ እንዳለው ማስታወስ ይረዳናል። እግዚአብሔር የሚሰራው በእኛ የሥነ ምግባር መመሪያ ሳይሆን በራሱ መመሪያ ነው። ትክክልና ስህተት የሆነውን ነገር ልንነግረው እንችልም፣እሱ ግን ይነግረናል። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሰዎች ሌሎች ላይ ከባድ ተጽዕኖ የሚፈጥር የተሳሳተ ምርጫ እንዲያደርጉ ቢፈቅድም፣ ስለ ክፋት ግድ የለውም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ወንድ፣ ሴት፣ ሕፃናት ሳይል በእሱ የጽድቅ መለኪያ መሰረት በሰው ሁሉ ላይ

የሚፈርድበት የፍርድ ቀን እየመጣ ነው። የፍቅርና የፍርዱ ጥግ ወሰን የለውም።[29] "እግዚአብሔርም የፍርድ አምላክ ነውና... እርሱን በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ ብፁዓን ናቸው።" (ኢሳያስ 30:18)

እናንተም ልክ ኢሜይል እንደላከልን ሰው "ከፈጣሪ የበለጠ ርህራሄ" እንዳላቸሁ የሚታምኑ ከሆነ ማንበባቸሁን ቀጥሉ። እግዚአብሔር ምስጢሩን የሚገልጠው ለትሁታን እና ለመስማት ትዕግስቱ ላላቸው ሰዎች ነው።

> "ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።" (ዘዳግም 29:29)

## 7. "የእግዚእብሔር ቃል... የለውም"

አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን ችላ ማለታቸውን "መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፈ ቢሆን ኖሮ ዝሙት ስለመፈጸም ፣ የዘመዳማቾች የወሲብ ግንኙነት ፣ ዘር ማጥፋት ፣ ክህደት ጣዖት አምልኮ እና የመሳሰሉትን አፈንጋጭ ታሪኮች አያካትትም ነበር።" እንደ እነሱ የእስትንፋሰ እግዚአብሔር እና መገለጥ መረዳት ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔርን ቃል በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ በማሰቀመጥ የተወሰነ መሆን መቻል አለበት።

ምንም እንኳን ቅዱሳት መጽሐፍት ሰዎችን በታሪክ ዐውድ ውስጥ ከፈጣሪያቸው ጋር ማስተዋወቅ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ቃልና ስራ መመዝገቡ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅን ኀጢአትና ጥፋት መዘገቡ ሊያስገርመን ይገባልን? እግዚአብሔር ክብሩን ፣ ንጽሕናውን ፣ ፍትሐዊነቱን ፣ ምህረቱን እና ታማኝነቱን የሰው ልጅ ውድቀት ላይ ተመስርቶ የመግለጥ መብት የለውምን? ለሁሉን ቻዩ አምላክ ራሱን እና መልዕክቱን መግለጥ አለበት ወይም የለበትም ?

> "እናንተ ነገሮችን ትገለብጣላቸሁ፡ ሸክላ ሰሪውን እንደ ሸክላ ትመለከታላቸሁ! ለመሆኑ ተሠሪ ሠሪውን ፣ 'እርሱ አልሰራኝም' ይለዋልን? ሸክላ ሠሪውን 'እርሱ ምንም አያውቅም' ይለዋለን?" (ኢሳያስ 29:16አመት)

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የፈቀደው ነገር ግን

ያልተስማማባቸው ታሪካዊ ሁኔታዎችን ይዘግባል፡፡ እውነተኛው እና ህያው አምላክ መጥፎ ሁኔታዎች ወደ ጥሩ ሁኔታዎች በመለወጥ ደስ ይሰኛል፡፡ አስገራሚ የሆነውን የያዕቆብ አስራ አንደኛ ልጅ ወደ ሆነው ዮሴፍን ታሪክ ምናልባት አንብባችሁት ይሆናል (ዘፍጥረት 37-50)፡፡ አስሩ ወንድሞቹ ጠሉት ፣አጎሳቆሉት ለእስማኤላውያን በባርነት ሸጡት፡፡ ዮሴፍ ፍትሐዊ ባልሆነ ሁኔታ ወደ እስር ቤት ተጣለ፣ ነገር ግን ዮሴፍ ወደ ግብጽ ባለስልጣንነት ያደገው ወንድሞቹንም ያዳነው ፣ግብጻውያንን እና የአካባቢውን ሰዎች ከረሃብ ያዳነው ከዚያ መከራ ውስጥ ነበር፡፡ በስተኋላም ወንድሞቹ አይነተኛ የልብ ለውጥ ካመጡ በኋላ ዮሴፍ እንዲህ አላቸው፦ “እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሚታየው የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው፡፡” (ዘፍጥረት 50:20አመት)

## ፰. “በመጣረስ የተሞላ”

ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ በሚጋጭ ነገር የተሞላ መሆኑን አጥብቀው ይናገራሉ፤ ነገር ግን በተጨባጭ ለማጥናት ጊዜ የሚወስዱ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ቅዱሳት መጽሐፍትን ሌላ ሰው በተናገረው ነገር ላይ ተመስረቶ መፈረጅ ተገቢ ነውን? የትኛውንም መጽሐፍ ከአንድ ቦታ አንድ ሳረግ ከሌላ ቦታ ደግሞ አንድ ሳረግ በማንበብ ብቻ መረዳት ይቻላልን? ታላቅ መጽሐፍን ማንብበ ያለብን የመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ስህተትን ወይም በምንባብ ውስጥ የሚገኝን አለመጣጣም ለማወቅ ማንበብ ተገቢ ነውን? በፍጹም አይገባም፡፡ በርካታ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡት በዚህ መልክ ነው፡፡

ከዓመታት በፊት ከአንድ ድረ ገጽ ላይ የተቀዳ ረጅም ስህተቶችን እና ግጭቶችን የተባሉ ነገሮችን ያካተተ ኢሜይል ደረሰኝ፡፡

ከኢሚይሉ ላይ የተወሰዱ ነገሮች እነሆ፦

ርሰሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

መጽሐፍ ቅዱሳችሁ እርስ በርሱ ይጋጫል። ለምሳሌ፦

- በመጀመሪያ ቀን እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ ፣ በመቀጠልም ብርሐንና ጨለማን ለየ (ዘፍጥረት 1:3-5) ጨለማ እና ቀንን የምትለየው ፀሐይ እስከ አራተኛ ቀን ድረስ አልተፈጠረችም ነበር። (ዘፍጥረት 1:14-19)
- አዳም የተከለከለውን ፍሬ በበላህ ጊዜ መሞት ነበረበት። (ዘፍጥረት 2:17)። አዳም 930 ዓመት ኖረ (ዘፍጥረት 5:5)።

> • ኢየሱስ በሰዎች አይፈርድም (ዮሐንስ 3:17 ፣ 8:15 ፣ 12:47)።
> ኢየሱስ ይፈርዳል። (ዮሐንስ 5:22 ፣ 27-30፣ 9:39 ፤ ሐዋርያት 10:42 ፣ 2ቆሮንቶስ 5:10)።
> • የመሳሰሉት።
>
> አሁን አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ አፈልጋለሁ፦ የናንተ ሐይማኖት ከመቀበሌ በፊት ጥያቄዎችን እንድጠይቅ አዕምሮዬን እንድጠቀም ይፈቅድልኛል ወይስ ዐይኔን እንድጨፍን እና ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳቆም ያደርገኛል? ምክንያቱም ራሴን፣ እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ ይህንን ያክል ስህተት ሊፈጽም ይችላል ወይ ብዬ ስጠይቅ መልሱ በፍጹም የሚል ነው። [ከነስህተቱ የተጠቀሰ]

አዎ "ኑና **እንዋቀስ**" (ኢሳያስ 1:18) የሚለው አምላክ ራሱ "ጥያቄዎችን እንድጠይቅና አዕምሮዬን እንድጠቀም" ይፈልጋል። እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በራሳችን ቃሉን እንድናሰላስል ይጋብዘናል። "መጣረሶች" ብሎ አንድ ሰው የዘረዘረውን ነገር መቀዳት እና መለጠፍ ይህንን ሊያሳካ አይችልም። ሰለሞን እንዲህ ብሏል "የዋህ ቃልን ሁሉ ያምናል፤ ብልህ ግን አካሄዱን ይመለከታል።" (ምሳሌ 14:15)

ለጸሐፊው "መጣረሶች" መፍትሔው ቅዱሳት መጽሐፍትን በጥንቃቄ መመርመር ነው።[30] ለአሁኑ ቢሆንም እንኳን ሁላችንም በዚህ ጉዳይ ላይ እንስማማለን፦ ጥንቃቄ የተሞላበት ምርመራ ማድረግ የማንፈልግ ሰዎች ሕይወት አጭር ፣ ዘላለምም በጣም ረጅም ነው።

በጣም የሚጣፍጥ፣ ፈሳሽ ያለው ማንጎ በልታችሁ ከሆነ ጣዕሙን ለሌላ ሰው መግለጽ በቂ አይደለም። መቀመስ አለበት። በተመሳሳይ መልኩም አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚላችሁ መቀበል ብቻውን በቂ አይደለም። ራሳችሁ መቅመስ አለባችሁ።

"እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም"
(መዝሙር 34:8)

አንድ ሰው ካለው ዘላለማዊ ፍላጎት መካከል አንደኛው የቅዱሳት መጽሐፍትን ማጥናት ነው፣ "እንዲማያሳፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንዲሚረዳ የተመሠከረለት ሠራተኛ" (2ጢሞቴዎስ 2:15 አመት) ለዐውዱ (የተባለው መጣረስ ይገኝበታል የተባለውን ሙሉ ክፍል የሚገኝበትን) ትኩረት አለመሰጠት የእውነትን ቃል በአግባቡ የማጥናት ትክክለኛ መንገድ አይደለም።

በምሳሌ ለማሳየትም እንዳንፈርድ የሚያዘዙን የመጽሐፍ ቅዱስ ሲኖሩ፣ እንድንፈርድ የሚያዙኑም አሉ።[31] እነዚህ ክፍሎች

ይጣረሳሉ? በፍጹም፣ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው። በሌላ በኩል የእግዚአብሔር መጽሐፍ ውሱን እውቀት እንዳለው ፍጡር ፣ ራስን ከማጽደቅ እና ስህተት ከመፈለግ አንጻር የሌላን ሰው መነሻ ሐሳብ መፍረድ(መበየን) አይገባም። በሌላ በኩል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርቼ ከፉን ከደግ ለይቼ እንድፈርድ እና ቅዱሳት መጽሐፍት በሚሉት ላይ ተመስርቼ እውነትን ከሰህተት እንድለይ ታዘዝለሁ።

ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ የተባሉ መጣረሶችስ?


እኔ በግሌ ለእንደነዚህ አይነት መጣረስ ለሚመስሉ ነገሮች የግሌን መፍትሄ አግኝቻለሁ። ሌላ ያገኘሁት ነገር፣ ሰዎች ቅዱሳት መጽሐፍትን ለመረዳት ፍላጎት እስኪኖራቸው ድረስ ድረስ ፣ በፊት የነበሯቸው መጣረሶች ሲፈቱ አዲስ መጣረሶችን ያገኛሉ።[32]

የእግዚአብሔርን መልዕክት መረዳት ትፈልጋላችሁ? የራሳችሁን ሐሳብ ለመፈለግ ወደ እግዚአብሔር መጽሐፍ አትሂዱ፣ የእሱን ሐሳብ ፈልጉ። መጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ በመጽሐፍ አጥኑ። የምታነቡትን ለመፍታት አጥብቃችሁ አትፈልጉ። ራሱን እንዲፈታ ፍቀዱለት። በበርካታ ምዕተ ዓመታት በበርካታ ነብያት የተጻፉት ቅዱሳት መጽሓፍት የራሳቸው ጥሩ ማብራሪያዎች ናቸው።[33]

> "የጠለቀውንና የተሠወረውን ይገልጣል፤ በጨለማ ያለውን ያውቃል፥ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው።"
>
> (ዳንኤል 2:22)

## ፱. "አዲስ ኪዳንን አላምንም"

ከጥቂት ጊዜያት በፊት ፣ ከአንዲት ሴት ይህንን ኢሜይል ደረሰኝ፦


ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

በአዲስ ኪዳን አላምንም። እኔ የማምነው በመጀመሪያው አዲስ ኪዳን ነው። ከእግዚአብሔር የመጣ የትኛውም ቃል ሊታረም እና እንደ አዲስ ሊጻፍ ይችላል ብዬ አላምንም። [ከነ ስህተቱ የተጠቀሰ]

ልክ እንደ በርካታዎቹ፣ ይህቺኛዋም ጸሐፊ የእግዚአብሔር መጽሐፍ የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን መጸሐፍት እንዳሉት አልተረዳችም። የቅዱሳት መጽሐፍት ሁለት ክፍሎች የእግዚአብሔር ቃል "እንደታረመና እንደተስተካከለ" የሚያሳይ ሳይሆን አስቀድሞ የተነገረው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው

ዕቅድ፣ እንደ ተፈጸመ እና እየተፈጸመ እና እየተፈጸመ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

በታሪክ ውስጥ ያሉ ክስተቶች በተከሰቱበት ቀን ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ የአብርሐም ልደት የተከሰተው በግምት ከ 2000 ዓ.ዓ እንደ ሆነ ተረድተናል የኒውዮርክ መንታ ሕንጻዎች መፍረስ ግን የተከናወነው በ2001 እ.ኤ.አ ነው።[34] የዓለም ታሪክ ለሁለት የተከፈለ ነው። የእግዚአብሔርም መጽሐፍ ልክ እንደዚሁ ለሁለት የተከፈለ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳችን ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን አለው። ኪዳን ሕጋዊ ማስረጃ፣ ኮንትራት በሁለት አካላት መካከል የተደረገ ስምምነት ነው።[35] ለአሁኑ እስቲ የቅዱሳት መጽሐፍትን ሁለት ክፍሎች በወፍ በረር እንመልከት። በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስንጓዝ ፣ የሁለት ክፍሎች ዓላማና ሳይል ግልጽ ይሆናል።

**ክፍል ፩ ፦ ብሉይ ኪዳን።** በዕብራይስጥ እና በአረማይክ የተጻፉት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት "ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ [ቶራ ተብሎ ይጠራል] ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።" (ሉቃስ 24:44) እነዚህ ጽሁፎች በአንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ በሰላሳ ነብያት በኩል የተላለፉ ሲሆን እግዚአብሔር ከአዳም ፍጥረት ጀምሮ እስከ ፋርስ አገዛዝ ድረስ (400ዓ.ዓ ገደማ) በሰው ልጅ ታሪክ ጣልቃ የገባበትን መረጃ ያቀረባል።

ከነቢያት አንጻር ብሉይ ኪዳን በመቶዎች የሚቆጠሩ ታሪካዊ ኩነቾ ከመፈጸማቸው በፊት ከአንድ የጊዜ ጥግ ወደ ዓለም ፍጻሜ በመመልከት ይናገራሉ።[36]

ብሉይ ኪዳን ከኢየሱስ መወለድ መፊት እግዚአብሔር ለሰዎቾ የገባውን ኪዳን ያሳያል(ዓዓ)። የግሪኩ ክርስቶስ የዕብራይስጡ መሲህ ማለት ሲሆን ፍቺውም የተቀባው ወይም የተመረጠው ማለት ነው። ያተፈጸሙ ቁልፍ ክስተቶችን አሰቀድሞ በመናገር ቅዱሳት መጽሐፍት ዓለምን ከኅጢአትና ከሚያስከትለው ነገር ሊያድን የሚመጣውን መሲህ ወደፊት ያሳዩ ነበር።

> "እነሆ፣ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር…"
> (ኤርሚያስ 31:31)

**ክፍል ፪ ፦ አዲስ ኪዳን።** በግሪክ የተጻፉት የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ወንጌል (ወይም ኢንጂል በአረብኛ "መልካም ዜና") ይባላሉ። ከሥምንት ባላነሱ ሰዎች በመጀመሪያው ክፍል

ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ላ የተጻፉ ሲሆን አዲስ ኪዳን የመሲሁን የመጀመሪያ ወደ ምድር መምጣት ይዘግባሉ። በተጨማሪም የብሉይ ኪዳን መለኮታዊ ማብራሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን፣ ታሪክ እንዴት እንደሚጠናቀቅ ይናገራሉ። ሁሉም ትንቢታት በብሉይ ኪዳን ካሉት ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

አዲስ ኪዳን ከመሲሁ መምጣት የተነሳ እግዚአብሔር የሰጠውን ትልቅ ስጦታ ይገልጣሉ(ዓም)። እነዚህ ቅዱሳት መጻህፍት ወደ ኋላ የሚያሳዩ ሲሆን በመቶዎች የሚቆጠሩና በነብያት የተነገሩ ትንቢታትን ፍጻሜ ያሳያሉ።


ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ሁሉ አዲስ ኪዳን መሲሁ ወደ ምድር የሚመለስበትን ጊዜ ወደፊት ያሳያሉ። መሲሁ "እኔ ሕግንና ነቢያትን [ብሉይ ኪዳን]ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ **ልፈጽም** እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።" (ማቴዎስ 5:17) ያለው በምክንያት ነው።

በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መካከል ምንም አይነት ግጭት የለም። ተዘርቶ በቅሎ ትልቅ ዛፍ ሆኖ እንደሚያድግ ሁሉ እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ያዘጋጀው ዕቅድ በብሉይ ኪዳን ተዘርቶ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ትልቅ ዛፍ ይሆናል። የእግዚአብሔር መጽሐፍ እያንዳንዱ ክፍል የሚያሳየው እንድንረዳዉ የሚፈልገውን መልዕክት ነው።

ኢሜይሉን የላከቸው "ከእግዚአብሔር የመጡ ቃላት ለታረሙ እንደ አዲስም እንደገና ሊጻፉ አይችሉም" ያለቸው ሴትዮ ትክክል ነች። መገንዘብ ያቃታት ጉዳይ "ከእግዚአብሔር የመጡ ቃላት" ሊፈጸሙ የሚችሉ እና የሚፈጸሙ መሆናቸውን ነው።

## 10. "የተበረዘ"

እስካሁን ድረስ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ አንብበው እንዳይረዱ እና እንዳያምኑ የሚያደርጉ ዘጠኝ እንቅፋቶችን አንስተናል። ነገር ግን ከሙስሊም ወንድሞቼ በተድጋጋሚ የምሰማውና እስካሁን ድረስ መልስ ያለተሰጠበት ጉዳይ አልተነካም። አሕመድ በኢሜይሉ አስቀድሞ ጥቅሶልናል፦


መልስት
ርዕሰ ጉዳይ
የኢሜይል ምላሽ

እኔ እንደማምነው እና እንደማውቀው መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው ስህተት መሆኑን እና ሁሉም መጽሐፉ ስለተነካኩ የተበረዘ መሆኑን ነው...

ታዲያ አሕመድ ትክክል ነው? የመመመሪያው አዲስ ኪዳን ተበርዟልን? የሚቀጥለው ክፍል ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጣል።



# 3

# ተበርዟል ወይስ ተጠብቋል

“ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል፥ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።”

ነብዩ ኢሳያስ (ኢሳያስ 40:8)

ከዚህ የሚከተሉት ከአራት የተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከተላኩ ኢሜይሎች ላይ የተወሰዱት ክፍሎች፣ አንድ ቢሊዮን በላይ የሚሆነው ሕዝብ ያለውን ሐሳብ ይገልጣሉ፦

ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ


መለኮታዊ መጽሐፍትን እናምናለን፣ የምናምነው ግን የመጀመሪያውን ነው።

ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

እናንተ ያላችሁ አዲስ ኪዳን እና ብሉይ ኪዳን ቃላቶቻቸው የተለወጡ መሆኑን አትርሱ። በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ግን ቃላቶቹ ለበርካታ ዓመታት ተመሳሳይ ናቸው።

ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ከሚያቅለሸልሽ እምነታችሁ ጋር እንዲስማማ እንደገና የተጻፈ ፣ የተጨመረበት እና እንደገና በድጋሚ የታረመየተበዘአ መጽሐፍ ነው።




አኔ እንደማምነው መጽሐፍ ቅዱስ ከክፍለ ዘመናት በፊት ወይም ከሺህ ዓመት በፊት ተበርዟል ፣ ሁሉም ባይሆን እንኳን አዲስ ኪዳን ጳውሎስ በተባለ ሐሰተኛ ነብይ የተበረዘ ግብስባሽ ነው። ስለዚህ ለአኔ መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ የጽሁፍ ብክነት እና / ወይም ቀረጦ መቀጠል ነው።

እነዚህ በሙሉ ውንጀላዎች ተቀባይነት አላቸውን? ወሰን የሌለው አምላክ ከብዙ ዓመታት በፊት ለነብያቱ የገለጠላቸውን ቅዱሳት መጽሕፍት ውሱን የሆነው የሰው ልጅ እንዲበርዝ እና እንዲነካካ ፈቀዷል?

## ለሙስሊሞች የግል ሐሳብ

በዚህ ስፍራ ላይ ሙስሊም አንባቢዎቼን በቀጥታ ማናገር እፈልጋልሁ።

እናንተ ራሳችሁ እንደምታውቁት ቁርዓን እንደሚናገረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጽሐፍት ማለትም ቶራ(ተውረት)፣ መዝሙር (ዘቡር) እና ወንጌል (ኢንጂል) በእግዚአብሔር የተሰጡት **"ብርሃንና መሪ"** ነው (ሱራ 5:44-51) በተጨማሪም እንዲህ ይላል "ወደ አንተም [መሐመድ] መጽሐፉን **ከበፊት ያለውን መጽሐፍ** [መጽሐፍ ቅዱስን] **አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባቂ ሲኾን በውነት አወረድንላቸው"** (ሱራ 5:48) "ወደነሱ የምናወረደላቸው የኾኑ ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም[አላህ] የማታውቁትም ብትኾኑ የመጽሐፉን[መጽሐፍ ቅዱስ] ባለቤቶች ጠይቁ" (ሱራ 21:7) ፡ በተጨማሪም ቁረዓን እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል "ወደነዚያ በመጽሐፉ በዚያም **መልክተኞቻችንን በርሱ በላክንበት** ወዳስተባበሉ (አታይምን?) ወደፊትም ያውቃሉ።... በገሀነም ወስጥ(ይጎተታሉ) ከዚያም በእሳት ይማገዳሉ።" (ሱራ 40:70-72)

ቁርዓን በተደጋጋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፉ መሆናቸውን ይናገራል በተጨማሪም የማይቀበላቸው ወደ ሲዖል እንደሚላክ ተናግሯል። ቁርዓን የሚለው ይሄንን ነው።[37]

እንደዚህ ያሉ ቁርዓናዊ ንግግሮች በበርካታ ሙስሊሞች ዘንድ ግራ መጋባትን ይፈጥራሉ፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እና ቁርዓን የእግዚአብሔርን ጠባይና ለሰው ልጆች ያለውን እቅድ ስር ነቀል በሆነ ልዩነት ስለሚያስቀምጡ ነው። ለዚህም ነው

አብዛኞቹ ሙስሊሞች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተበርዘዋል ሲሉ የሚናገሩት።

የሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የጠቀስነውን ድምዳሜ በደንብ እንዲስቡበት ረድቷቸዋል።

## በአብዛኛው ለሙስሊሞች የቀረቡ ጥያቄ

- እግዚአብሔር የራሱን መጻሕፍት መጠበቅ ይችላል ብላችሁ ታምናላችሁ?
- ካመናችሁ ለመጠበቅ ፍቃደኛ ይሆናል ብላችሁ ታምናላችሁ?
- የነብያት ቅዱሳት መጽሓፍት ተበርዘዋል ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ፦
  - መቼ ነው የተበርዙት?
  - የት ነው የተበረዙት ?
  - ማን ነው የበረዛቸው? ክርስቲያኖች ወይም አይሁዶች መጽሐፍ ቅዱስን ለውጠዋል ብላችሁ የምታምኑ ከሆን ብዙዎች በፈቃደኝነት የሞቱለትን መጽሐፍ ለምን መበረዝ አሰፈለገ ?[38]
  - ምን ማስረጃ ማቅረብ ትችላላችሁ?
  - ወሰን የሌለው አምላክ ውሱን የሆኑ የሰው ልጆች የተጻፈውን የራሱን ዘገባ እና ለሰው ልጆች የሰጠውን መገለጥ ለምን እንዲበርዙ ፈቀደ?
- አምላክ እንደ ሙሴና እንደ ዳዊት ያሉ ነብያትን መጽሐፍት ሰዎች እንዲበርዙ ከፈቀደ እናንተ የምታምኑት መጽሐፍስ እንዲህ እንዳልሆነ በምን ታውቃላችሁ?

ዓላማዬ ሰዎችን በጥያቄ ማፋጠጥ አይደለም፤ ብዙዎች ይህንን የመበርዝ ክስ ስለሚያምኑ እና ዘላለማዊ ጦስ ስላለው አንድነድ ጥያቄ ለጨምር እነሆ ፦

- የመጽሐፍ ቅዱስ መጸሐፍት የተነካኩት ቁርዓን ከመሰጠቱ በፊት ነው በኋላ?

ማንበባችሁን ከመቀጠላችሁ በፊት ለዚህ ጥያቄ በፊትም ቢሆን በኋላ ምላሽ ስጡ። ከመቀጠላችሁ በፊት መልሱን ጽፋችሁ ትቀጥሉ ይሆናል።

## በፊት?

ምላሻችሁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት ቁርዓን ከመጻፉ በፊት ተበርዟል የሚል ከሆነ ለምን ቁርዓን ቅዱሳት መጽሐፍት ለሰው ልጆች መታለል ሳይሆን “መሪ”፣ ጨለማ ሳይሆን “ብርሃን” ለምን ይላቸዋል? ቁርዓን “የኢንጅል ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ”? (ሱራ 5:46-47) ታዲያ ለምንድን የሚከተለውን የሚያውጀው፦ “የአላህ ቃላት መልለወጥ የላትም”? (ሱራ 10:64)

የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተዓማኒ አይደሉም ከተባለ፣ ለምን ቁርዓን የሚከተለውን ትዕዛዝ ይሰጣል፦ “ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ” (ሱራ 10:94 ሻኪር)[39], በተጨማሪም “እውነተኞች እንደኾናችሁ ተወራትን አምጡ አንብቡዋትም በላቸው፡፡” (ሱራ3:93)

ጥቂቶች “በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ፡፡” (ሱራ 3:78) ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው ግን ያልተበረዙና ምንም እንከን የሌላቸው መሆኑ ተገልጧል፡፡

## በኋላ?

በሌላ በኩል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት የተበረዙት ቁርዓን ከተጻፈ በኋላ ነው ካላችሁ፣ ዛሬ በስርጭት ላይ የሚገኙ መጽሐፍ ቅዱሶች የተተረጎሙት ቁርዓን ከመጻፉ ከበርካታ ምዕተ ዓመታት በፊት ከተገኙ ጥንታዊ ቅጂዎች ላይ ነው፡፡

ቁርዓን ለመጀመሪያ ጊዜ በተነበበ ጊዜ ቅዱሳት መጻህፍት በአውሮጳ፣ ኢሲያ እና አፍሪካ ተሰራጭተው ነበር በተጨማሪም እንደ ላቲን ፣ ሶሪያ፣ ኮፕቲክ ፣ ጎቲክ ፣ ግዕዝ እና አርሜንያ ቋንቋ ተተርጉመው ነበር፡፡[40]

እስቲ ስለዚህ አስቡ፡፡ ይህንን ያህል ታዋቂ የሆኑ ፣ በበርካታ ቋንቋዎች የተተረጎሙ ፣ በመቶ ሺዎች የተራቡ እና በሚታወቀው ዓለም ውስጥ በፍጥነት ከተሰራጩት ውስጥ ጥቂት ሰዎች እንዴት ሊበርዙት ቻሉ? እስቲ አስቡ የበኩር ቋንቋ ቅጂዎችን እና ቁጥር ስፍር የሌላቸውን የትርጉም ስራዎች ለመሰብሰብ ሞክረው ዛሬ የምናየውን አይነት ወጥነት በእነዚህ ትርጉሞች ውስጥ ለመፍጠር ሲሞከሩ እስቲ አሰቡ፡፡ የማይቻል ተግባር ነው፡፡

ድምዳሜው ግልጽ ነው፦

- መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን ከመጻፉ በፊት ተበርዞ ነበር ካልን በርካታ ቁርዓናዊ ጥቅሶችን ይጣረሳል፡፡[41]

- መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን ከተጻፈ በኋላ ነው የተበረዘው ማለት ደግሞ በሺ በሚቆጠሩ ቅጂዎች የተደገፈውን ታሪካዊ እና ሥነ ቅርሳዊ መረጃ ይቃረናል።

ይሄ ድምዳሜ አዳዲስ ጥያቄዎችን ያስነሳል።

እነዚህ በሺዎች የሚቆጠሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች እና ትርጉሞች ከየት የመጡ ናቸው?

ዋናዎቹ ቅጂዎች ያሉት የት ነው?

## የበኩር ቅጂዎች እና የእነሱ "ዝርያዎች"

በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ ፣ መጽሐፍትን ጨምሮ ይደበዝዛሉ በተጨማሪም ያረጃሉ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ የበኩር ቅጂዎች (የእጅ ቅጂዎች ተብለውም ይጠራሉ) በቀላሉ አይገኙም። ነገር ግን በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሙዚየሞች እና ዩኒቨርስቲዎች ክነብያት በኩር ጽሁፍ የተግኙ "ዝርያዎች" ተጠብቀው ይገኛሉ።

ቶራም፣ ወንጌላትም ፣ የፈላሳፋው አሪሳጣጣሊስ ፣ የታሪክ አዋቂው ፍላቪየስ ዮሲፈስ ወይም እጅግ በጣም የቅርብ ጊዜው ቁርዓን[42] ዋና ቅጂዎች አርጅተው ጠፍተዋል። ይሄ ሁሉንም ጥንታውያን መጽሐፍት በሙሉ የሚመለከት ነው። የበኩሮቹ "ዝርያዎች" ብቻ ይገኛሉ።

በሴኔጋል ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ብለው ያምናሉ። አይተማመኑበትም። በተቃራኒው ግን በግሪዮታቸው ይተማመናሉ። ግሪዮት በቃል የሚነገር ታሪክ አዋቂ ሲሆን ዋና ስራውም የቤተሰቡን ፣ የነገዱን እና የከተማውን ታሪክ በቃል መያዝና ያንን ታሪክ ለሚመጣው ትውልድ ማስተላለፍ ነው። የግሪዮት ዝርዝር የቤተሰብ መረጃን የማስታወስ እና በሚያጠግብ ደረጃ መግለጥ የሚያስገርም ነው። ምንም እንኳን ግርዮትስ በስራቸው የተጉ ቢሆኑም እንኳን አንዳንድ መረጃዎች ትክክለኛ ገጽታቸው እና ዝርዝር መረጃቸው ከጊዜ ብዛት ይጠፋል። በሰዎች መካከል እውነት በቃል ማቆየት በትክክለኛነት ደረጃ፣ ከጽሁፍ ጋር አይወዳደርም።


ብዙ ሰዎች የሰዎችን የቃል ምስክርነት ለማመን ፈጣን ሆነው በጽሁፍ የቀረበውን የእግዚአብሔርን መረጃ ለማመን የሚከብዳቸው ለምንድን ነው?

ይሄ ጥበብ የተሞላ አካሄድ ነው?

“የሰውን ምስክር ብንቀበል
የእግዚአብሔር ምስክር
ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል…
በእግዚአብሔር የማያምን
እግዚአብሔር …የመሰከረውን
ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ
አድርጎታል።” (1ዮሐንስ 5:9-10)



## ጥቅልሎች እና ጸሐፍት



ቅዱሳት መጻህፍት የተጻፉት ወረቀት፣ የሕትመት መሳሪያ እና ኮምፒውተሮች ከመኖራቸው በፊት ነው። ነብያት የእግዚአብሔርን ቃል ይጽፉ የነበረው ከእንስሳት ቆዳ በተዘጋጅ ጥቅልል ወይማ ፓፒረስ ላይ ነበር። እነዚህ የበኩር ቅጂዎች በጸሐፍት በእጅ ይገለበጡ ነበር።

ጸሐፍት በጥንት ዘመን ይኖሩ ከነበሩ ባለሙያዎች የሚለዩት ማንበብ፣ መጻፍ ፣ ህጋዊ መዛግብትን ይገለብጡ ነበር። ጥቂት ጸሐፍት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባትን ይገለብጡ ነበር። ዋና ዓላማቸው በፍጹም ትክክለኝነት መገልበጥ ነበር። “ከአንዳንድ መጽሐፍት ማብቂያ ላይ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ብዛት እና የተኛው ቃል መጽሐፉ መካከል ይገኝ እንደነበረ ይገልጡ ነበር፡ ይህንንም የሚያደርጉት በሰትኋላ የሚመጥእው ጸሐፊ በሁለቱም መንገድ ቆጥሮ አንድም ፊደል አለመሳቱን ለማረጋገጥ ነበር።” [43]

ምንም እንኳን የበዛ ጥንቃቄ ቢያደርጉም ፣ ጥቃቅን ግድፈቶች በቅጂዎች ውስጥ ይገኙ ነበር ፦ የተዘለለ ቃል፣ ሳረግ ወይም አንቀጽ ወይም በተሳሳተ ሁኔታ የተገለበጠ ፊደል ይገኝ ነበር።[44] ነገር ግን በጥንት ቅጂዎች ውስጥ የተገኘ የትኛውም ልዩነት በአንድም መሠረታዊ እውነት ላይ ተጽዕኖ አይፈጥርም።

ምሁራን በጥንታውያን መጽሐፍት ውስጥ ፣ ዓለማዊም ይሁኑ መንፈሳዊ በሚገኙ እዚህ ግባ በማይባሉ ስህተቶች ችግር ኖሮባቸው አያውቅም። እነዚህ ልዩነቶች በእጅ በተገለበጡ ጽሁፎች ውስጥ መገኘታቸው መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልተለወጠ ደጋፊ ማስረጃ ሆነው ይቀርባሉ። ከቁርዓን በተለየ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን “ፍጹም ቅጂ” ለማድረግ በማሰብ የተገለበጠ እና የተረፈው እንቃጠል አልተደረገም።[45]

እግዚአብሔር መልዕክቱን ለእኛ ጠብቆልናል። ታዲያ አሁን በእጃችን የሚገኙት ቅዱሳት መጽሐፍት ሐዋርያት እና ነብያት የጻፉት ለመሆኑ እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው?

## የሙት ባህር ጥቅልል

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሚታወቁት ጥንታውያን የብሉይ ኪዳን መጽሓፍት ቅጂዎች(በነብያት በ 1500 እና በ 400 ዓዓ የተጻፉ) በ900 ዓም የተገኙ ነበሩ። በዋናዎቹ በቅጂዎቹ እና በበኩር ጽሁፎቹ መካከል ከነበረው ክፍተት የተነሳ እና የጥንት መጽሐፍት ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በተደጋጋሚ የተገለበጡ ከመሆናቸው የተነሳ ተቺዎች ነብያት የጻፉትን ነገር በእርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም ይሉ ነበር።[46]

በመቀጠልም የሙት ባህር ጥቅልሎች ተገኙ።

ዓመት ምህረት ፦ 1947 እ.ኤ.አ

ቦታ፦ ሙት ባህር አቅራቢያ ቂርበት ቁምራን

ሰበር ዜና፦ አንድ ከበዲዊን ጎሳ የተገኘ እረኛ የጠፋ ፍየል ሲፈልግ የዕብራይስጥ ፣ የአረማይስጥ እና የግሪክ ጥቅልሎችን የያዘ ማሰሮ ዋሻ ውስጥ አገኘ።

በ 1947 እና 1956 225 የሚሆኑ መጻሕፍ ቅዱሳዊ ቅጂዎች በአሥራ አንድ ዋሻዎች ውስጥ ተገኙ። ምሁራን እነዚህን ጥቅልሎች በ 250 ዓዓ እና 68 ዓም የተጻፉ መሆናቸውን አሰቀምጠዋል። ብዙዎቹ ቅጂዎች ከ 2000 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያላቸው ናቸው። አስገራሚ ግኝት!

እነዚህ ጥቅልሎች በቁምራን ዋሻዎች ውስጥ የተደበቁት በ 70 ዓም (ሮም ኢየሩሳሌምን ባወደመችበት ዘመን) ኤሴናውያን በተባሉ የአይሁድ ቡድኖች ነበር። እነዚህ ሰዎች እነሱ ላይ ምንም አይነት ነገር ይድረስ እነዚህሥነ ጽሁፎች ለሚቀጥለው ትውልድ ለማድረስ ወስነው ነበር። አይሁድ ራሳቸው ሲገደሉ ወይም በአሕዛብ መካከል ሲበተኑ ቅዱሳት መጻህፍት ግን ተጠብቀው ነበር። ለ 1900 ዓመታት ፓፒረስ እና የብራና ጥቅልሎች በሸክላ ማሰሮ ውስጥ በአመቺ ሁኔታ ደረቅ በሆነው የሙት ባህር ክልል ተደብቀው ቆይተው ነበር።

የእነዚህ ጥንታውያን መዛግብት መገኘት ዜና ለዓለም በደረሰ ጊዜ በቅርብ ጊዜ ካሉት አንድ ሺህ ዓመት ዕድሜ ካላቸው ቅጂዎች ጋር ተጨባጭ ልዩነት ይኖራቸዋል ብለው ጠብቀው ነበር። ምናልባትም “መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል” የሚለው ጥያቄ ሊረጋገጥ ይችላል ብለው ጠብቀው ነበር።

ተጠራጣሪዎች አዝነው ነበር። የተገኙት ብዙም ዋጋ የሌላቸው የፊደል አጠቃቀም እና የ ሰዋሰው ልዩነቶች ብቻ ነበሩ። ጥንታውያን ቅጂዎች በአሁኑ ዘመን ከሚገኙ መጽሐፍ ቅች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት እና መልዕክቶችን ይዘው ነበር።

ቅዱሳት መጽሐፍት ተበርዘዋል ወይም ተለውጠዋል ለሚለው ሐሳብ ከሙት ባህር ጥቅልል በመነሳት የተሰጠው ብያኔ ምን የሚል ነበር? "እስካሁን ያለው ማስረጃ እንዲህ አይነት ለውጥ እንዳልተፈጸመ ያሳያል።"[47]




## በታሪክ ውስጥ በአግባቡ የተጠበቀ መጽሐፍ

እንደ አዲስ ኪዳን ከሆነ ከ 24000 በላይ ቅጂዎች ፣ 5300 በበኩር የግሪክ ቋንቋ ፣ 230 ደግሞ ከ 6ኛው ክፍለ ዘመን በፍት የተግኙ ቅጂዎችን ጨምሮ ይገኛል። ይሄ አዲስ ኪዳንን በታሪክ ውስጥ በአግባቡ የተጠበቀ መጽሐፍ ያደርገዋል።

በንጽጽር የግሪክ ፈላሳፋ የሆነውን ከ 384 እሰከ 322 ዓዓ የኖረውን የአሪሰጣጣሊስን ጸሁፎች ተመልከቱ። አሪስጣጣሊስ በዓለም ታሪክ ውስጥ ከተነሱ ተጸዕኖ ፈጣሪ አሳቢያን መካከል አንዱ ነው። ነገር ግን ስለሱ ፍልስፍና እና ሎጂክ የምናውቀው

ነገር ሁሉ በ1100 ዓም በተገኙ ጥቂት ቅጂዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ይሄም ከዋናው ቅጂ የ 1400 ዓመታት ርቀት አለው። እስካሁን ድረስ ግን የአሪስጣጣሊስ ሐሳብ እና ቃላት ተጠብቀው እንደቆዩ ማንም ሰው ጥያቄ አያነሳም።

ከአዲስ ኪዳን በሺዎች የሚቆጠሩ ቅጂዎች ባሻገር ምሁራን ከአዲስ ኪዳን ከ325 ዓም (በጣም ጥንታዊው የአዲስ ኪዳን ቅጂ የተገኘበት ዓመት) በፊት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆኑ ምንባባት የተጠቀሱ በሺዎች የሚቆጠሩ ምንባባት ተገኝተዋል። እነዚህ ጥቅሶች በጣም በዝርዝር የተቀመጡ ከመሆናቸው የተነሳ መላው አዲስ ኪዳን ከእነዚህ ጽሁፎች ብቻ እንደገና ሊዋቀር ይችላል።[48]

መረጃዎች የሚያሳዩት አዲስ ኪዳን ከጥንታውያን ሸነ ጽሁፎች መካከል በአግባቡ የተጠበቀ መጽሐፍ ነው።

## የተለዩ መጽሐፍ ቅዱሶች

ምናልባት አንድ ሰው እንዲህ ሲል ሰምታችሁ ይሆናል "ነገር ግን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ አይነቶች አሉ! ትክክለኛው የትኛው ቅጂ ነው?"

በጥንታውያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅጂዎች እና የተለያዩ የእነዚህ መጻሐፍት ትርጉሞች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህ የበኲር ሥነ ጽሁፎች በጸሐፍት አማካይነት ከረጅም ጊዜ በፊት፣ ከቁርዓን በርካታ ክፍለ ዘመናት አስቀድሞ፣ የተገለበጡ ናቸው። ዛሬ በሕትመት ላይ የሚገኙ መጽሐፍ ቅዱሶች ከእነዚህ ጥንታውያን ቅጂዎች የተተረጎሙ ናቸው።[49] መጽሐፍ ቅዱስ በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉስ ከበኲር ቋንቋዎች (ዕብራይስጥ፣ አረማይስጥ፣ ግሪክ) ወደ 2400 የተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎመ ነው።

ከእነዚህ መካከል አንዱ እንግሊዝኛ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ደርዘን በሚሆኑ ምረጥ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ይገኛል። የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ትንሽ ለየት ያሉ ምንባባት አሏቸው ፣ ይሄም ደግሞ ቃላት ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጎሙ የሚከሰት ነው። ተረጓሚዎቹ የሚመርጧቸው ቃላት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ ፣ ነገር ግን በታማኝነት ሲተረጎሙ ትርጉሙ እና መልዕክቱ ተመሳሳይ ይሆናል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በዋነኛነት ጥቅም ላይ የቀድሞው ትርጉም (ቀት)ነው። ትክክለኛ በዚህ ዘመን በአማርኛ የተዘጋጀ የቃል ለቃል ትርጉም ነው። ለመረዳት ሰለሚቀል አዲሱ መደበኛ

ትርጉም (አመት) በርካታ ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሁለቱ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ ጥቅሶችን ለምሳሌ ተመልከቱ፦

> የቀት፦ "ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል፡፡"
>
> (ማቴዎስ 6:16)

> አመት ፦ "ስትጾሙ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፣ እነርሱ መጾማቸው እንዲታወቅላቸው ሆን ብለው በፊታቸው ላይ የሐዘን ምልክት ያሳያሉና ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል፡፡"
>
> (ማቴዎስ 6:16አመት)

ምንም እንኳን ቃላት የተለያዩ ቢሆኑም ፣ ትርጉሙ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

## እግዚአብሔር ታላቅ ነው

አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የእግዚአብሔርን የተጻፈ ቃል ሰዎች በርዘውታል የሚለው ክስ ውድቅ ማድረጊያ ወሳኝ መረጃ ቀኑን ሙሉ በመስጊድ ውስጥ ሲነገር የሚውለው ነገር ነው፡፡

ዛሬ ጠዋትም ሰምቼዋለሁ፡፡

> "አላሁአክበር! አላኋአክበር!"
> "እግዚአብሔር ታላቅ ነው! እግዚአብሔር ታላቅ ነው!"

አዎ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፡፡ በዘመናት መካከል ከሚገኙ ሰዎች የበለጠ ነው፡፡ ለአሕዛብ መባረክ እና ለራሱ ስም ሲል እውነተኛው እና ሕያው አምላክ የራሱን መልዕክት ለትውልድ ሁሉ ጠብቆ አኑሮታል፡፡

እግዚአብሔር የራሱ ዓለም ፈጣሪ እና አጽኚ ነው፥ የቃሉ ጸሐፊ እና ጠባቂ ነው፡፡

> "አቤቱ፣ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል፡፡"
>
> (መዝ 119:89)

## መጨረሻ የሌለው እንቅፋት

እዚህ ቦታ ላይ ስንደርስ ለጉዞ እየተዘጋጀ ያለ እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንዲታቀብ የሚያደረገውን መሰናከል ያለፈ መሆኑን ማሰብ ይጠቅማል። ነገር ግን ልምምዳችን የሚያሳየው ሌላ ነገር ነው። ለበርካቶች በእውነት መንገድ ላይ ሁል ጊዜ ሌላ ተጨማሪ መሰናክል ይኖራል።[50] በቅርብ ጊዜ የሚከተለው ኢሜይል ደረሰኝ ፦

> መልስት | ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ
>
> ሰለ ምላሽህ አመሰግናለሁ። አንድ ቦታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፦ “ሰውን በመልካችን እናብጅ”። ሁል ጊዜ “በመልካችን” (እኛ) የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንን ነው ስል አጠይቃለሁ። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች አሉ አይደል? ትክክለኛው የትኛው ነው? በርካታ ሐይማኖቶች አሉ አይደል? ሐይማኖቶች ባይኖሩ ኖሮ መንትያዎቹ ሕንጻዎች ይኖሩ ነበር አይደል? ክርስትና ለበዙ ሰው ሕይወት መጥፋት ሃላፊነት አለበት አይደል? በተጨማሪም ሰለምታምነው ነገር እርግጠኛ የሆንከው እንዴት ነው? ለምን? ለምን? ለምን? ለዘመናት አፈ ታሪክን በተመለከት ጥያቄዎችን እያነሳን መልሶችን እየፈጠርን በርካታ ሰባኪዎች ገንዘብ መሰቢያ እያደረጉት መቀጠል እንችላለን። እግዚአብሔርን የፈጠረው ማን ነው?
>
> አመሰግናለሁ።

ምንም እንኳን የእግዚአብሔር መጽሐፍ ለዚህ ሰው ጠጣር ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ የሚሰጥ ቢሆንም፣ የሆነ ቦታ ላይ ከመቃብር ወዲህ ባለው ዓለም ዘላለማዊ እውነትን ማግኘት የፈለጉ ሰዎች በስዎች **ለምኖች** ላይ ከማተኮር ይልቅ **የእግዚእብሔርን ቃላት** ማሰላሰል ጠቃሚ ነው።

## ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሰን ችላ እንዲሉ የሚያደርጓቸው እውነተኛ ምክንያቶች

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የእግዚእብሔርን እውነት የማይቀበሉትን እውነተኛ ምክንያት ይገልጣል።
ሦስቱን እነሆ፦

### 1. የረከሰ ልብ

አንዳንድ ሰዎች ቅዱሳት መጽሐፍትን የማያሰላስሉበት ምክንያት ፈጣሪ ባለቤታቸውን ማወቅ ስለማይፈልጉ ነው።

የሰውን ልብ ስንገመግም (ደም የሚረጨውን ማለት ሳይሆን ፣ ውስጣዊ አስተሳሰብን የሚቆጣጠረው - ነፍስን ማለት ነው) መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላሉ ፦ "የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ። ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም።" (መዝሙር 14: 1-3)

የሰው ልጅ መጽሐፍ ቅዱስን አለመቀበል ከተበረዘ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለውም፣ ዋናው ጉዳይ የተበረዘ ልብ ነው።

ንጉስ ሰለሞን እንዲህ ሲል ጽፏል "እግዚአብሔር ሰዎችን ቅኖች አድርጎ እንደ ሠራቸው፥ እነሆ፥ ይህን ብቻ አገኘሁ፤ እነርሱ ግን ብዙ ብልሃትን ፈለጉ።" (መክብብ 7:29) ለተፈጥሯዊ ዝንባሌያችን ከተተውን በራሳችን መንገድ መሄድን እንመርጣለን፤ የራሳችንን ስልት እንቀይሳለን ፤ በአባቶቻችን እምነት ኖረን እንሞታለን። እግዚአብሔርን ለማወቅ ላለመሞከር እንኳን ምክንያት እንፈልጋልን። በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የምናደርገውን ጉዞ ከጀመርን ከአጭር ጊዜ በኋላ ፣ ለምን እንደዚህ እንደሆንን እንረዳለን። ለአሁኑ ፣ እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ጥሩ ምክንያት አለው ፦ "የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።" (ማቴዎስ 13:9)[51]

## 2. ጭንቀት እና ሐብት

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መልዕክት የማይረዱበት ምክንያት ዋናው ትኩረታቸው እዚህ እና አሁን ላይ ስለሆነ ነው። "ለዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ በመታለል ታንቆ።" (ማቴዎስ 13:22አመት)

የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ በአካል ንአበ ርጊዜ ዕድሜ ልኩን ሁሉ የነብያትን ቅዱሳት መጽሐፍት ችላ ስላለ ሰው ታሪክ ተናግሮ ነበር። ምናልባትም ይሄ ሰው ቅዱሳት መጽሐፍት ተዓማኒ አይደሉም በማለት ህሊናውን ለማስታምም ሳይሞክር አልቀረም። ምንም ይሁን ጉዳዩ ፣ ሰውየው ሞተና ራሱን ሲዖል ውስጥ አገኘ። ፈሪውን ሰው በግልጽ ለማስጥነቀቅ እግዚአብሔር በገነት ከሚገኘው አብርሐሃም ጋር ጥቂት እንዲያወራ ለዚህ ሰው ፈቀደለት። ባለጠጋው ሰውዬ ምላሱን እንዲያቀዘቅዝለት ጥብታ ውሃ ጠየቀ ነገር ግን ምንም ነገር አላገኘም። ይሄ ሰው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያለተስፋ እንደቀረ ባወቀ ጊዜ

አብርሐምን ከሙታን መካከል አንድ ሰው ልኮ በሕይወት ያሉ አምስት ወንድሞቹ እንዲያስጠነቅቅለትለመነው "ወደዚህ የስቃይ ቦታ እንዳይመጡ።"

የአብርሐም ምላሽ ግልጽ ነበር።

> "ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።" (ሉቃስ 16:27-31)

ከተዓምራዊ ምልክቶችና ድንቃ ድንቆች ይልቅ እግዚአብሔር የተጻፈ ቃሉ የእውነቱ የጸና ማረጋገጫ እንዲሆነ ወስኗል። የነብያቱን ቅዱሳት መጽሐፍት ያቀረበልን እና ጠብቆ ያቆየልን ለእኛ ሲሆን "እንድናደምጣቸው" ይፈልጋል።

### 3. የሰው ፍርኸት

አንዳንድ ሰዎች ፈጽመው መጽሐፍ ቅዱስን የማያጠኑት ሌሎች ሰዎች የሚሰጧቸውን ምላሽ በመፍራት ነው።

አንድ ጎረቤቴ እንዲህ ብሎኝ ነበር "ቤተሰቤን ባልፈራ ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስን አነብ ነበር!" መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ይለኛል "ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል፤ በእግዚአብሔር የሚታመን ግን እርሱ ይጠበቃል።" (ምሳሌ 29:25)

እናንተስ? እናከብራቸዋለን የሚሏቸው ነብያት የጻፏቸውን ጽሁፎች ስታነቡ ቢይዟችሁ ቤተሰባችሁ እና ጓደኞቻችሁ የሚያስቡት ፣ የሚናገሩት ወይም የሚሰሩት ነገር ያስፈራችኋል?

አትፍሩ። "በእግዚአብሔር የሚታመን ግን እርሱ ይጠበቃል።"

ከእግዚአብሔር አንጻር መልዕክቱን ቸል ለማለት ምንም አጥጋቢ ምክንያት የለም።



# 4

# ሳይንስ እና መጽሐፍ ቅዱስ

“ምድሪቱንም በታችዋ አንዳች አልባ ያንጠለጥላል።”
— ነብዩ ኢዮብ (ኢዮብ 26:7)

ከበርካታ ዓመታት በፊት በከርሠ ምድር የሚገኝ ዋሻ ጎብኝተን ነበር። አስጎብኚያችን አስገራሚ የዐለት ቅርጾችን ፣ ሳታላስታይትስ እና ስታላግማይትስ ስታሳየን የሚከተለውን አለች ፦ “ይሄ ሁሉ የጀመረው በጠብታ ውሃ ነው። ጥልቀት የሌለው መሬት ገብ ባህር አካባቢውን ከ330 ሚሊዮን ዓመታት በፊት ሸፍኖት ነበር፣ በመሆኑም በስተኋላ የዝቅጥ አለት ንብርብር የሆኑ ነገሮችን ሊፈጥር ችሏል…”

ሰውገና ከጅማሬው ጀምሮ በስፍራው ላይ ተገኝቶ የተመለከተው ይመስል ሳይንሳዊ በሚመስል መልኩ የቀረበ ነው። በምትናግረበት ጊዜ እግዚአብሔር ለነብዩ ኢዮብ ይናገር የነበረው ቃል ጆሮዬ ላይ ያቃጭል ነበር፦ “ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ? ታስተውል እንደ ሆንህ ተናገር።” (ኢዮብ38:4) ከጉዟችን በኋላ አስጎብኚያችንን አመሰገንኩ እና የሥነ ምድር ባለሙያዎች እንዴት ይሄንን ሁሉ ሚሊዮን ዓመት ዐወቁት ብዬ ጠይቅኳት። በእርግጠኝነት እንደማያውቁ አመነች ፤ በመቀጠልም “እንድናገር የሰለጠንኩትን ነው የነገርኩህ።” አለችኝ።

## እውነተኛ ሳይንስ

ሳይንስ የሚለው ቃል ከላቲን ሴይንቲያ ከሚባል ቃል የተገኘ ሲሆን ፍቺውም ዕውቀት ማለት ነው። ግሱ ሲሬ ማለት ሲሆን

ፍቺውም ማወቅ ማለት ነው።[52] ማወቅ ማለት ከጥርጥር በላይ በሆነ ሁኔታ እውነት የሆነ ማለት ነው። ምንም እንኳን ሳይንቲስቶች ጽንሰ ሐሳብን ሳይንስ ማለት ቢመርጡም ፣ ያ ግን ሳይንስ አያደርገውም።


በ 1970ዎቹ አጋማሽ ፈረንስያዊው የንጉስ ፈይሰል የግል ሐኪም ዶክተር ማውሪስ ቡካሊ ዘ ባይብል ፣ ዘ ቁርዓን ኤንድ ሳይንስ የተሰኘ መጽሐፍ ጽፏል። ይሄ መጽሐፍ በሙስሊሙ ዓለም በሚገኙ የመጽሐፍ መደብሮች እና መስጊዶች በብዛት ይታያል። መጽሐፉ መጽሐፍ ቅዱስ ከዘመናዊ ሳይንስ ጋር ይጋጫል ይላል። ቡካሊ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ የተመዘገበው የሥነ ፍጥረት ትረካ "ፐሮባብሊሜንት ላ ትራድክሽን ዷ ኡን ሚቴ" (ምናልባትም ከአፈ ታሪክ የተገለበጠ) ነው ይላል፤ ምክንያቱም ከተለዋዋጩ የሰው የአጽናፈ ዓለም ጅማሬ ጽንሰ ሐሳብ ጋር ስለማይመሳሰል ነው።[53] እንደ ብዙዎቹ ቡካሊ የዝግመተ ለውጥን ጽንሰ ሐሳብ[54] ከእውነተኛ ሳይንስ ጋር እኩል ያደርገዋል።

ቅዱሳት መጽሐፍት የተሰጡት ቁሳዊ ሳይንስን ለማስተማር ሳይሆን ፣ መንፈሳዊ ሳይንስን ለመግለጥ ነው። እግዚአብሔር መጽሐፉን የሰጠን እሱ ማን እንደሆን ፣ ምን እንደሚመስል እና ለእኛ ምን እንደሰራልን ሊያሳየን ነው። በተጨማሪም ከየት እንደመጣን፣ ምድር ላይ ለምን እንዳለን በመጨረሻም የት እንደምንሄድ ሊያሳየን ተሰጥቶናል። እንዲህ አይነት መረጃ ሊገኝ እና በጥናት ቤተ ሙከራም ሊረጋገጥ አይቻልም። ቢሆንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም የህይወት ክፍሎች ላይ ያተኮረ ነው። በተጨማሪም ቅዱሳት መጽሐፍት በተጻፉ ጊዜ የሰው ልጅ የማያውቀው ፍጥረታዊወን ዓለም የሚመለከት መረጃ ማካተቱም የሚያስገርም አይደለም።

## እግዚአብሔር መጀመሪያም ብሎታል

በዘመናችን ሳይንቲስቶችከማግኘታቸው በፊት በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገቡ የሳይንሳዊ መረጃ ሰባት ምሳሌዎችን እናንሳ። በስተኋላ ቅዱሳት መጽሐፍትን እግረ መንገዳችንን ስንመረምር ሌላ አሰገራሚ የሳይንስ ምሳሌዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን።

1. ክብመሬትበርካታየታሪክመጽሐፍትእንደሚያስተምሩት ግሪኮች ከ500 ዓዓ "ምድር ክብ እንደሆነች ጽንሰ ሐሳብ



አቅረበው ነበር… የግሪክ ፈላስፋዎች እንደደመደሙት ምድር የሞላላ ክብ ቅርጽ ብቻ ሊኖራት ይችላል እንደነሱ አስተያየት ያ "ፍጹም" ቅርጽ ነው፡፡[55] ነገር ግን ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት ነብዩ ኢዮብ እግዚአብሔር **"ምድሪቱንም በታችዋ እንዳች አልባ ያንጠለጥላል፡፡** ብርሃንና ጨለማ እስከሚለያዩበት ዳርቻ ድረስ፥በውኆች ፊት ላይ ድንበርን አደረገ፡፡" (ኢዮብ 26:7,10) ሲል ዐውጇል፡፡ ከግሪኮች አራት መቶ ዓመት በፊት ነብዩ ሰለሞን እግዚእብሔት "በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ፥" (ምሳሌ 8:27) ብሏል፡፡ በ700 ዓዓ አሁንም ከሁለት መቶ ዓመት ከግሪክ ፈላስፎች ቀደም ብሎ "እርሱ በምድር ክበብ ላይ ይቀመጣል" (ኢሳያስ 40:22) ሲል ኢሳያስ ተናግሯል፡፡ የዕብራይስጡ ክብ የሚለው ቃል ሞላላ ወይም ክብ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ስለዚህ ስለ ምድር ክብ ቅርጽ አሰቀድሞ የተናገረው እንግዚአብሔር ነው ወይስ ግሪካውያን? አዎ የምድር ንድፍ አውጪ የሆነው እግዚአብሔር ነው፡፡

2. የውሃ ዑደት የኢዮብ መጽሐፍ የውሃ ዑደትን በተጨማሪ ይገልጽልናል ፦ **"የውኃውን ነጠብጣብ ወደ ላይ ይስባል፥** ዝናብም ከጉም ይንጠባጠባል፤ደመናት ያዘንባሉ፥ በሰዎችም ላይ በብዙ ያንጠባጥባሉ፡፡ የደመናውንም መዘርጋት፥ የማደሪያውንም ነጐድጓድ የሚያስተውል ማን ነው?" (ኢዮብ 36:27-29) መጽሐፍ ቅዱስ የዝናቡ ዑደትን ሲገልጽ እርጥበት ትነት ይሆናል ፣ በደመና ውስጥም ወደ ጥቃቅን የውሃ ጠብታዎች ይቀየራል፣ በመቀጠልም ጠብታዎችን በማሰባሰብ ትልቅ ሲሆኑ በአየር ላይ ይሰቀላቸዋል፡፡ ኢዮብ በደመና ውስጥ ሊሰባስብ ስለሚችለው ከፍተኛ መጠን ስላለው ውሃ ይናገራል፦ "ውኆችን በደመናዎቹ ውስጥ ያስራል፥ ደመናይቱም ከታች አልተቀደደችም፡፡" (ኢዮብ 26:8)[56]

3. የጋራ ዝርያ ከሦስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት ነብዩ ሙሴ እንዲህ ብሏል "አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም

አወጣ፤ **የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና**።” (ዘፍጥረት 3:20) እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ሁሉም የሰው ልጆች ከአንድ እናት የተገኙ ናቸው። እስከ 1987 እ.ኤ.አ. የዝግመት ለውጥ ሳይንቲስቶች ይሄ ጉዳይ አላሳመናቸውም ነበር። ከዓለም ዙሪያ በተወሰዱ እንግዴ ልጆች በዘረመል ውስጥ በሚገኙ ማይቶኮንዶሪያዎች(ከእናት ወደ ልጅ ሳይለዋወጥ በሚተላለፍ ቀመር) የሰው ልጅ ዘረመል ኮድ ላይ በተደረገ ጥልቅ ምርምር የሰው ልጆች በሙሉ ከአንድ ሴት የዘር ግንድ እንደ ተገኙ በጥናቱ ተረጋግጧል።[57] ከበርካታ ዓመታት በኋላ ጥናቶቹ የሰው ልጆች ከአንድ የወንድ የዘር ግንድ እንደተገኙም አርጋግጠዋል።[58] እነዚህ ተመራማሪዎች ጥረታቸው እና ወጪያቸው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት የሚያረጋግጥ መሆኑን ብዙም አልተገነዘቡም ነበር።

4. ሕይወት በደም ውስጥ ሙሴ በተጨማሪ እንዲህ ብሎ ነበር፡ “የሥጋ ሕይወት **በደሙ ውስጥ** ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።” (ዘሌዋውያን 17:11) ይሄ እውነት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ገዳይ የሆነውን የደም ማፍሰስ ስልት ሲጠቀም የነበረውን የሕክምናው ዘርፍ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው በቅርብ ጊዜ ነው።[59]

5. የምድር ዕድሜ ከሶስት ሺህ ዓመታት በፊት ነብዩ ዳዊት ምድር አንድ ቀን **“ትጠፋለች”** “እንደ ጨርቅ **ታረጃለች**” (መዝሙር 102:26) ዘመናዊ ሳይንስ ምድር ፍጥነቷ እየቀነሰ እንደሆነ ይስማማል፣ የማግኔት ስበት ብቃቷም እያረጀ ነው፤ በተጨማሪም ጥበቃ የሚያደርግላት የኦዞን ንጣፍ እየሳሳ ነው።

6. የሥነ ባህር ሳይንስ ዳዊት በተጨማሪ እንዲህ ብሎ ነበር “በባሕር **መንገድ** የሚሄደውንም ሁሉ።” (መዝሙር 8:8) አድሚራል ፎንቲየን ማውሪን (1806-1873) ሕይወቱን እነዚህ የባህር ሞገዶች ለማግኘትና ለመመዝገብ እንዲሰጥ ያደረገቸው ይህቺ ትንሽ ሐረግ ነበረች። እግዚአብሔር በባህር ውስጥ “መንገድ” አለ ካለ እነዚህ በካርታ ላይ መስፈር አለብኝ ሲል አሰበ። ማውሪ ይህንን በማድረጉ “የሥነ ባህር አባት” ተባለ።[60]

7. ሥነ ፈለክ ከ2000 ዓመታት በፊት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ነበር “የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ

ከሌላው ኮከብ ይለያልና።" (1ኛ ቆሮንቶስ 15:41) በጥሬ ዐይናችን ስንመለከተው ብዙ ከዋክብት ተመሳሳይ ይመስላሉ። ነገር ግን ዛሬ ክፍተኛ ጉልበት ባላቸው ቴሌስኮፖች እና የብርሃን ሞገድ ትንተናዎች በተገኘው መረጃ መሰረት የሥነ ፈለክ ባለሙያዎች የሚከተለውን ይሉናል፡ "ከዋክብት በቀለማቸው፣ በድመቀታቸው ይለያያሉ። አንዳንድ ከዋክብት እንደ ጸሐይ ቢጫ ይመስላሉ። ሌሎች ሰማያዊ እና ቀይ ብርሃን ይለቃሉ።"[61] "እያንዳንዱ ኮከብ ልዩ ነው"[62] ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

## ጭፍን እምነት?

ምንም እንኳን በርካታ የሳይንስ ምሳሌዎች ሊጠቀሱ ቢችሉም የሰባቱ ምሳሌዎች ግልጽ ትምህርት ግን የሚከተለው ነው፦ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ የሳይንስ መጽሐፍ ባይሆንም፣ ሳይንስን በተመለከተ ሲናገር ትክክለኛ እና እውነት ነው።

አንዳንዶች የመጽሐፍ ቅዱስን እምነት "ጭፍን እምነት" ይሉታል። ነውን? ወይስ ደግሞ በማይለዋወጥ መረጃ ላይ የተመሰረተ ብሩህ እምነት ነውን? መርጃው በዘለቄታዊነት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር በሚስማማበት ጊዜ፤ ሙሉ በሙሉ ልናብራራው ወይም ልናረጋግጠው የማንችለውን ነገር እንኳን ሲገልጥ፣የእነዚህን ሥነ ጽሁፎች እውነተኛነት መቀበል ጥበበኛነት ነው ወይስ ሞኝነት ነው?

እግዚአብሔር የአስተሳሰብ ስህተት እንድንሰራ አይፈልግም የመጽሐፉን ተዓማኒነት የሚያረጋግጡ ነገሮችን "በብዙ ማስረጃ" (ሐዋርያ 1:3) አቀርቦልናል።

## ታሪክ፣ መልክዓ ምድር፣ ሥነ ቅርስ

ባለፈው ምዕራፍ ብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን በአግባቡ ከተጠበቁ ጥንታውያን መጽሐፍት መካከል አንዱ መሆኑን የሚያረጋግጡ መረጃዎችን መርምረናል። በእነዚህ መጽሐፍት ውስጥ የተቀመጠው ተጨባጭ መረጃስ? ሊታመን ይችላል?

እያንዳንዱ ገጹ በሰዎች፣ በቦታ እና በክስተት የተሞላ ከመሆኑ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ ለምሁራን ትክክለኛነቱን እንዲያረጋግጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ዕድሎች ይሰጣቸዋል።

ታሪክ፣ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና ሥነ ቅርስ የሚናገሩት ምንድን ነው?

ለበርካታ ዘመናት በርካታ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ትክክለኛነት አመኔታ ለማሳጣት ሞክረዋል። ከእነዚህ መካከል አንዱ ሰር ዊሊያም ሚቼል ራምሴ (1851-1939) የተሰኘው የዓለማችን ታላቅ የሥነ ቅርስ ተመራማሪ ነው። ራምሴ የዩኒቨርስቲ ተማሪ እያለ የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ተጠራጠረ። ነገር ግን ያገኛቸው ግኝቶች ሃሳቡን እንዲቀይርና የሚከተለውን እንዲጽፍ አደረገው "ሉቃስ የመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጠው የታሪክ ዐዋቂ ነው ሁኔታዎችን የገለጸበት መንገድ ትክክል መሆኑ ብቻ ሳይሆን... ይሄ ሰውዬ ከታላላቅ የታሪክ ጸሐፊያን ተርታ ሊመደብ ይገባዋል።"[63]

ሉቃስ ሐኪም ፣ የታሪክ ጸሐፊ የጌታ ተከታይ እና የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ነው። ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት 95 መልከዓ ምድራዊ ቦታዎችን (32 ሐገራትን፣ 54 ከተሞችን እና ዘጠኝ ደሴቶችን) እና ታሪካዊ ሰዎችን እና ክስተቶችን ይጠቅሳሉ። ተቺዎች ሉቃስ በዘገበው እና ታሪካዊ ፣መልከዓ ምድራዊ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሚገኝ የታሪክ መጽሐፍት በሚዘግቡት መካከል ክፍተት ለማግኘት እጅግ በጣም ደክመዋል። የሉቃስ ጽሁፎች ግን በሁሉም መልኩ ትክክለኛ መሆናቸው ተረጋግጧል።

በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የሚገኝ አንድ ነጥብ ብቻ ይህንን ታሪክ ያረጋግጥልናል። ይሄ ሳረግ የናዝሬቱን ኢየሱስን ምድራዊ አገልግሎት ታሪካዊ ዐውድ ለማሳየት የገባቸ ናት።

> "**ጢባርዮስ ቄሣርም** በነገሠ በአሥራ አምስተኛይቱ ዓመት፥ ጴንጤናዊው ጲላጦስም በይሁዳ ሲገዛ፥ ሄሮድስም በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዥ፥ ወንድሙ ፊልጶስም በኢጡርያስ በጥራኮኒዱስም አገር የአራተኛው ክፍል ገዥ፥ **ሊሳኒዮስም** በሳቢላኒስ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሆነው ሳሉ፥ሐናና **ቀያፋም** ሊቃነ ካህናት ሳሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ።" (ሉቃስ 3:1-2)

## ሉቃስ ትክክል ነበር?

በርካታዎቹ ስሞች እና ዝርዝሮች ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ "ሉቃስ ትክክል ነበር?" ብለን እንድንጠይቅ ያደርጉናል። እንደ ፈተና የተጠቀሱ አራት ሰዎችን እንመረምራቸው ፣ ስሞቹ በቀደመው ጥቅስ ውስጥ ደመቅ ብለው ተጽፈዋል።

አንደኛ፣ ሉቃስ የሮም ቄሳር የሆነውን ጢባርዮስ ቄሳርን እና ሐገረ ገዢውን ጴንጤናዊውን ጲላጦስን ይጠቅሳል። እነዚህ ሰዎች በታሪክ ውስጥ ነበሩ? በ1961 ሄሮድስ ባሳደሰው ቲያትር አቅራቢያ (በተጨማሪም በሉቃስ ተጠቅሷል [ሐዋርያት 12:19-24]) ጴንጤናዊው ጲላጦስ ሐገረ ገዢ እንደሆነ እና ጢባርዮስ ቄሳር ገዢ እንደ ነበረ የሚናገር አንድ ሜትር ርዝመት ያለው የድንጋይ ላይ ጽሁፍ ተገኝቷል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያለው ታሪክ አዋቂ ዮሲፈስ (37-101 ዓም) ተመሳሳይ ሰዎችን፣ ቦታዎችን እና ክስተቶችን ጠቅሶ ጽፏል።[64]

ሉቃስ ልክ ነበር።

ሉቃስ ሊሳንዮስን የተባለ ግለሰብ በሶርያ ክፍለ ሃገር የአልቤን አገረ ገዢ (የጋራ አገር ገዢ) እንደ ነበር ይናገራል። ሊሳንዮስ በታሪክ አዋቂዎች ዘንድ የግሪኳ ኪልቂስ ከተማ ገዢ የነበረ እና ሉቃስ ከመጻፉ ከ60 ዓመታት በፊት (በ 27 ዓም) እንደተገደለ ስለሚታወቅ፣ ለበርካታ ዓመታት ምሁራን ይህንን ተጨባጭ ስህተት በማለት ሉቃስ እንደተሳሳተ ይናገሩ ነበር። ነገር ግን የታሪክ አዋቂዎች የሶሪያዋ አቢለኔ ግዢ የነበረውን ሊሳንዮስ ከ 14 እሰከ 29 ዓም እንደተጻፈ የሚገመተው እና ስሙን የያዘው ጽሁፍ በደማስቆ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ምንም አያውቁም ነበር፦ ሃገር ገዢው ሊሳኒዮስ።[65] ስለዚህም ሊሳንዮስ የተባሉ ሁለት ሰዎች ነበሩ ማለት ነው።

ሉቃስ ትክክል ነበር።

ሉቃስ ስለ ቀያፋም ጽፎ ነበር፤ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሁለተኛ ሊቀ ካህን ስለነበረው ቀያፋም ጽፎ ነብር። በታህሳስ ወር 1990 በአሮጌዋ ኢየሩሳሌም የመንገድ ግንባታ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ድንገት የቀያፋን ቤተሰብ መቃብር አገኙ። የሥነ ቅርስ ባለሙያዎችም ወደ ስፍራው ተጠሩ። መቃብሩም ከኖራ የተሰሩ ሳጥኖችን ይዞ ነበር። በጣም በሚያምር ሁኔታ ከተበጁት ሳጥኖች መካከል አንዱ የቀያፋ ልጅ ዮሴፍ የሚል ጽሁፍ ነበረበት። ኢየሱስን ያሰረው ሊቀ ካህን ሙሉ ስም ነበር።[66] በሳጥኑ ውስጥም 60 ዓመት የሚሆነው ወንድ አጽም ተገኝቶ ነበር፤ ይሄ ደግሞ እርግጠኛ በሚባል ደረጃ የአዲስ ኪዳኑ ቀያፋ ነው።[67]

ሉቃስ ልክ ነበር።

ኔልሰን ጉሌክ የተባሉት ታዋቂ የሥነ ቅስ ባለሙያ እንዲህ ብለው ነበር "በግልጽ እና በማያሻማ ሁኔታ አንዲቷንም የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የሚቃረን ሥነ ቅርሳዊ ግኝት አልተገኘም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ መጽሐፍ

ቅዱሳዊ ሐሳቦችን በዝርዝር የሚያጸኑ የሥነ ቅርስ ግኝቶች ተገኝተው ነበር።”[68] ይሄንን በዓለም ላይ በሚገኙ ሐይማኖቶች ከበሬታ ስላገኙት መጽሐፍት ማለት አንችልም። ለምሳሌ የሞርሞን መጽሐፍ ታሪካዊና መልክዓምድራዊ መዛባቶች እንዳሉብት ሥነ ቅርሳዊ ግኝቶች አሳይተዋል።[69]

በዊተን ኮሌጅ የሥነ ቅርስ ክፍለ ሳላፊ የሆኑት የሥነ ቅርስ ባለሙያው ጆሴፍፈሪአርኪዮሎጂኤንድባይብልሂስተሪበሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ሲሉ ደምድመዋል “የመጀመሪያዎቹን የዘፍጥረት መጽሐፍ 50 ምዕራፎች በእጆቼ ገልጬ አየኋቸው በአዕምሮዬም በሥነ ቅርስ ምርምር ተረጋግጠዋል ወይም ይበልጥ ግልጽ ሆነዋል ፤ እነዚሁኑ ተመሳሳይ ነገሮች ስለቅሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማለትም ስለ አዲስ ኪዳንም ብሉይ ኪዳንም ልንል እንችላለን።”[70]

## ሳይንስ ሊያረጋግጠው የማይችለው ነገር

እውነተኛ ሥነ ቅርሳዊ መረጃ በወጥነት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት እና ትክክለኛ ታሪካዊ መዝገብነት ሲያረጋግጥ ፤በመለኮታዊ እስትንፋስ መጻፉን ግን ሊያረጋግጥ አይችልም። ምንም እንኳን የሚያስገርሙ ሳይንሳዊ ሐሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢገኙም ፣ ሳይንስ ግን የትኛውም መጽሐፍ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አያረጋግጥም። ይሄንን ማለት ያስፈለገው የእነሱ ቅዱስ መጽሐፍ ጥቂት ሳይንሳዊ የሚመስሉ ሐሳቦችን ስለያዘ በእግዚአብሔር የተጻፈ ነው ብለው ለማሳመን የሚመከሩ ሰዎች ስላሉ ነው።

መንፈሳዊ እውነት በሳይንሳዊ ግኝት ሊረጋገጥ አይችልም ፣ ይሄም በቻ ሳይሆን በአንድ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ሳይንሳዊ ሐሳብ ከእግዚአብሔር የመሆኑ ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። ብዙ ጊዜ በዚህ ምድር ላይ የቆየው ስይጣንም ስለ ሳይንስ ብዙ ያውቃል። በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የምናደርገውን ጉዞ ስንጀምር አስቀድመን የቀደመውን ሰማያዊ መልዐክ ፣ አሁን ግን ስይጣን እና ዲያብሎስ ተብሎ የሚጠራውን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ እናገኘዋለን። ለአሁን ዲያብሎስ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ብልህ እንደሆነ እና ሰዎችን አሰገራሚ ነገር እንዲጽፉ ሊያደርግ እንደሚችል ብቻ እንገንዘብ።

ነብዩ ዳንኤል እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ምርጥ መጽሐፍት እንዲጽፍ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ጠቢብ ሰው ነው፤ ነገር ግን ወደ ተፈጥሯዊ

ችሎታ ስንመጣ የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚቃወመው ስይጣን “ከዳንኤል የበለጠ ጠቢብ” (ሕዝቅኤል 28:3) ነው። ዲያብሎስ ከሐሰተኛ ሐይማኖት ጀርባ የሚገኝ መሪ ነው። በማታለል ጥበብም ብቁ ነው። ዲያብሎስ የሚለው መጠሪያውም ከሳሽ ወይም ተቃዋሚ ማለት ነው።

አንድ የዐረብ ምሳሌ አደጋውን በአጭሩ ያስቀምጠዋል፦ “ተጠንቀቁ! አንዳንድ ሐሰተኞች

## ግጥም ሊያረጋግጠው የማይችለው ነገር

አንዳንድ ሐይማኖቶች የትኛውም ሰው ደግሞ ሊጽፈው ስለማይችል ከእግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣል ሲሉ ይናገራሉ።[71] አሕመድ በዚህ ኢሜይል እንደተናገረው፦

> ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ
>
> ቁርዓን ለነብዩ ታላቅ ተዓምር ነው! እሺ እንደሱ ያለ ወይም ወደሱ የሚቀርብ አንድ ጥቅስ ጻፋ!! ከፍተኛ ደረጃ ባለው ዐርብኛ ደ አፍህን የፈታህ ብትሆን እንኳን ያንን ማድረግ አትችልም ... በዓለም ላይ በታላቅነት ወደ ቁርዓን የሚቀርብ ምንም ነገር የለም... ይሄንን ማፍረስ ከቻልክ ሞክረው።

የአሕመድ ሙግት በቁረዓን ሁለተኛው ሱራ (ምዕራፍ) ላይ የተመሰረተ ሲሆን እሱም እንዲህ ይላል፦ “በባሪያቸን ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ” (ሱራ2:23)

ይሄንን በምሳሌ ለመግለጽ ወደ ስዕል ውድድር ገባሁ እንበል ፤ የራሴን ስዕል አስገባሁ፤ ዳኛ ራሴ ሆኜ ፤ ራሴ አሸናፊ መሆኔን ከተናገርኩ በኋላ “ማንም እንደ እኔ ሊስል አይችልም። እኔ የዓለም ታልቁ ሰዓሊ መሆኔን የምትጠራጠሩ ከሆነ እንደኔ ያለ ስዕል ሳሉ”

ይሄ የእኔ ስዕል ምርጡ ስዕል መሆኑን ሊያረጋግጥ ይችላል? እኔ ታላቅ ሰዓሊ መሆኔን ያረጋግጣል? በፍጹም። ነገር ግን ማንም ሰው እኔ መሳቴን ሊያረጋግጥ አይችልም። ለምን? ውበት በተመልካቹ ዐይን የሚወሰን ነዋ።

በግጥም ፤ በሥነጽሁፋዊ ውበት ነው የማናወዳደረው። አንጻራዊ ነው።

መጽሐፍቅዱሳችን በዕብራውያን ግጥምና ከአእምሮ በላይ በሆኑ የቁጥር ስርዓቶች የተሞላ ነው።[72] ነገር ግን እግዚአብሔር በእሱ እንድናምን የሚፈልገው በስሥነጽሁፋዊ ውበት ተማርከን

አይደለም።

ሳይንስ እስትንፋሰ እግዚአብሔርን እንደማያረጋግጥ ሁሉ አስገራሚ ድምጸት ያላቸው ቃላትም መጽሐፉ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን አያረጋግጡም።

ስይጣን ፣ ታላቁ ሌባ እና ኮራጅ አስገራሚ ግጥሞችን እና “ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል” (ይሁዳ 16) እንዲጻፍ ሊያደርግ እንደሚችል በአዕምሮ መያዝ ተገቢ ነው። በተለይ ደግሞ ቃሎቹ ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር ከተናገርው ጋር የሚቃረን ከሆነ ቅዱሳት መጽሐፍት እንዳንታለል ያዙናል “በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ።” (ሮሜ 16:18)

ሳይንስም ይሁን፣ ሥነ ቅርስ፣ ግጥም የትኛውም መጽሐፍ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል መሆኑን አያረጋግጥም። ይሄ የእስትንፋስ እግዚአብሔር ማረጋገጫ መመስረት ያለበት በከፍተኛ የብያኔ አሰጣጥ ሂደት ማለትም በጠንካራ እና የማያሻማ መረጃ ላይ ተመስርቶ ነው።

ይሄን ማስረጃ ወደ ማየቱ አሁን እንሂድ።



# 5

# የእግዚአብሔር ፊርማ

“አሕዛብ ሁሉ በአንድነት ይሰብሰቡ…፦
እውነት ነው ይበሉ።”
— እግዚአብሔር (ኢሳያስ 43:9)

ብዙዎቹ ሕጋዊ ሰነዶች መደበኛ ፊርማ ያስፈልጋቸዋል። ስልጣናዊ መዛግብት እና ኪዳናት የሆኑት የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የተፈረሙት በእስኪብርቶ ሳይሆን እጅግ በጣም ለየት ባለ የተፈጸመ ትንቢት በተባለ ፊርማ ነው።



> “…የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የፊተኛውም እኔ ነኝ ፣ የኋለኛውም እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም። እስቲ እንደኔ ማን አለ? ይናገር ፤ ሕዝቤን ከጥንት ስመሠርት ምን እንደነበር ገና ወደ ፊት ምን እንደሚሆን ይናገር ፣ በፊቱ ያስረዳ፣ ስለሚመጣው አስቀድሞ ይናገር። … ይህን አሰቀድሞ ማን ዐወጅ ? ከጥንትስ ማን ተናገረ? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን?” (ኢሳያስ 44:6 ፤ 45:21 አመት)

የእግዚአብሔርን አመክንዮ በደንብ መረዳት መቻል አለብን። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳችን በትክክል በተፈጸሙ ዝርዝር ትንቢታት የተሞላ ነው፤ ከዚህ የተነሳ ላለፈው ለአሁኑም ለወደፊቱም ጊዜ ልንተማመንበት ይገባል።

## አዎንታዊ ማረጋገጫ

ታሪክ ከመፈጸሙ በፊት ሊናገር የሚችለው ከጊዜ ውጪ የሚኖረው እሱ ብቻ ነው።

ሟች ወንዶች እና ሴቶች አንዳንድ ጊዜ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ምሁራዊ ግምታቸውን ሊሰጡ ይችላሉ። ወደፊትን እንደ ተፈጸመ አድርጎ ሊያይ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከአሁን ጀምሮ ወደፊት በሺህ ዓመታት ውስጥ ሊከናወን የሚችለውን ነገር የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከመለኮታዊ መገለጥ ባሻገር ሰዎችም፣ መላዕክትም ፣ አጋንንትም፣ ሰይጣንም የወደፊቱን ጊዜ በተመለከተ ሊናገሩ አይችሉም።

አንዳንድ ሰዎች “ጠንቋዮች ፣ ንግርተኞችስ የወደፊቱን ጊዜ ይተነብያሉ!” ሊሉ ይችላሉ።

አንደኛ ሰይጣን በሱ ቁጥጥር ስል ላሉ ሰዎች “ፈቃዱን ለማድረግ በዲያብሎስ ሕያዋን ሆነው ከተያዙበት ወጥመድ ወጥተው፤” (2ጢሞ 2:26) ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እውቀት ሊሰጥ ይችላል።

ሁለተኛ፣ ለብዙ ሺህ ዓመታት የሰው ልጆችን ሲከታተል የኖረው ሰይጣን ዋና ኮራጅ እና የሥነ ልቦና ሊቅ የእግዚአብሔርን “ፊርማ” በማስመሰል እየተካነ መጥቷል።

ሶስተኛ ፣ ምንም እንኳን ሰይጣን አንዳንድ ሁኔታዎች የሚጓዙበትን መንገድ በመናገር ረገድ የተሳካለት ቢሆንም የወደፊቱን ግን አያውቅም። “ትንቢቶቹም፤ ብዙ ጊዜ የተሳሳቱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ግልጽ አይደሉም። ለምሳሌ አንድ ጠንቋይ አንዲት ወጣት ሴትን “በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ እውነተኛ ፍቅር አግኝተሽ ታገቢያለሽ” ቢላት፣ እኔ እና እናንተ እንዲህ አይነት “ትንቢት” በተወሰነ የመፈጸም ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ እናውቃለን። ስለተፈጸሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ስንነጋገር ፣ እየተነጋገርነው ያለነው እንደዚህ ስላሉ አሻሚ ትንቢታት አይደለም።

እስቲ ሦስት የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢታት ምሳሌዎች ማለትም ሰለ ቦታዎች ፣ ስለ ሰዎችና ስለ ግለሰቦች የተነገሩ ትንቢታትን እንመልከት።

## ስለ ቦታ የተነገሩ ትንቢታት

600 ዓዓ አካባቢ ነብዩ ሕዝቅኤል የጢሮስ ከተማ ስለ ሆነቸው የፊንቄ ሰዎችን የሚመለከት ትንቢት ተናግሮ ነበር። በዮርዳኖስ ዳርቻ የምትገኘው ጢሮስ ለሁለት ሺህ ዓመታት

ያክል የዓለም ማዕከል ሆና ነበር። የባህር ላይ ልዕልት በመባል ትታወቅ ነበር። ነገር ግን የሳያልነት ጣሪያ ላይ በደረሰችበት ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል በእግዚአብሔር ፊት ካሳየችው ርኩሰት እና አላዋቂነት የተነሳ ሊመጣባት ስላለው ጥፋት ዝርዝር ትንቢት እንዲናገር እና እንዲጽፍ አድርጎታል።

ነብዩ ሕዝቅኤል የሚከተለውን ትንቢት ተናግሮ ነበር፦

1. በርካታ አሕዛብ በጢሮስ ላይ ይነሳሉ። (ሕዝቅኤል 26:3)
2. በንጉስ ናቡከደናጾር ስር የምትገኘው ባቢሎን የመጀመሪያ አጥቂዋ ትሆናለች። (ቁ.7)
3. የጢሮስ ግድግዳዎች እና ምሶሶዎች ይፈርሳሉ። (ቁ.4 ፣9)
4. የጢሮስ ሰዎች በሰይፍ ይጠፋሉ። (ቁ.11)
5. የከተማዋ ፍርስራሽ ወደ ባህር ይጣላል። (ቁ.12)
6. እንደ "የተራቆተ ድንጋይ" (ቁ.4) እፍቃታለሁ።
7. የአሳ አጥማጆች የሥራ ቦታ "የመረብ ማስጫ አደርጋታለሁ" (ቁ. 5 ፣14)
8. ታላቋ ጢሮስ "ከእንግዲህ ወዲህ አትሠሪም፤ እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁና" (ቁ.14)

ዓለማዊ የታሪክ መዛግብት እነዚህ ስምንት ዝርዝር ትንቢታት እንደተፈጸሙ ይመሰክራል፦

1. በርካታ ሃገራት በጢሮስ ላይ ተነስተውባታል።
2. የመጀመሪያዋ በንጉስ ናቡከደናጾር የምትመራዋ ባቢሎን ነበረች።
3. ከአስራ ሦስት ዓመታት ከበባ በኋላ (585 – 572 ዓዓ) ናቡከደናጾር የጢሮስን ግድግዳ እና ማማዎች አፈራርሶ የሕዝቅኤልን የመጀመሪያ ትንቢት ፈጸመ።
4. ናቡከደናጾር አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ሜዲትራኒያን ባህር ውስጥ ከሚገኘው ከጢሮስ ደሴት ምሽግ ያመለጡ ኗሪዎችን ጨፈጨፈ።
5. ዓለማዊ ታሪካዊ መዛግብት እንደሚያሳዩት በ 332 ዓዓ "ታላቁ እስክንድር የጢሮስ ደሴትን የተወሰነ ክፍል በመያዝ የመጀመሪያው ሰው ሆነ። ይህንንም ሊያደርግ የቻለው መሬት ላይ የሚገኘውን ከተማ በማፍረስ እና ያንን ተጠቅሞ ወደ ደሴቷ ድልድይ በመገንባት ነው"[73] ስለዚህም ሳያውቀው ፍርስራሿን ወደ ባህር እጥላለሁ የሚለውን ትንቢት ፈጸመ። የእስክንድር ድል የፊንቄን አገዛዝ ማብቂያ ሆነ።[74]

6. ከተማዋ “የተራቆተ ድንጋይ” እርቃኗን ቀረች።
7. “መረብ ማስጫ” ሆነች።
8. በቀጣዮቹ ዓመታት ጢሮስ እንዷገና ለመገንባት በርካታ ጥረቶች ተደርገው ነበር ፤ በተደጋጋሚ ግን መልሳ ትጠፋ ነበር። ዛሬ በሊባኖስ ውስጥ ጢሮስ የምትባል ዘመናዊ ከተማ አለች፤ ነገር ግን የጥንታውያን ፊንቄያውያን ከተማ ግን እንደ ተነገረው ትንቢት እንዷገና ልታንሰራራ አልቻለችም። ከዚህ በታች ያለውን የድንጋይ ንጣፍ የመንገድ ዳርቻ ፎቶግራፍ ላይ ናሽናል ጂኦግራፊ እንዲህ የሚል ርዕስ ስጥቶታል “የዛሬዎቹ ፊንቄያውያን ጢሮስ ከእነዚህ የድንጋይ ጥርጊያዎች እና ሮማውያን ከሰሩት ማማዎች ስር ተቀበራ ትገኛለች። ጥቂት ቁፋሮ ብቻ ወደ ጠፋው የፊንቄያውያን ዓለም ያደርሰናል።”[75]

እነዚህን ስለ ጢሮስ ከተማ የተነገሩ ስምንት ትክክለኛ ትንቢታትን ሕዝቅኤል ጥበቡን ተጠቅሞ የመናገር ዕድሉ ምን ያክል ነው?

ነገር ከመፈጸሙ በፊት የሚያየው እግዚአብሔር ብቻ ከመሆኑ የተነሳ ለሕዝቅኤል ይህንን መረጃ የሰጠው እግዚአብሔር መሆን መቻል አለበት።

## ስለ ሕዝቦች የተነገሩ ትንቢታት

መጽሐፍ ቅዱስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ስለ በርካታ ሐገራት የተነገሩ ትንቢታትን ይዟል፦ ግብጽ፣ ኢትዮጵያ፣ ዐረብ። ፋርስ፣ ሩሲያ፣ እስራኤል እና ሌሎች።

ወደሚቀጥለው የተፈጸመ ትንቢት ምሳሌያችን ስንሄድ፣ በአዕምሮኣችን መያዝ የሚገባን ዓላማችን ትንቢታቱ የምንፈልገውን እንዲሉልን ለማድረግና ፖለቲካዊና ሐይማኖታዊ አጀንዳ ለማስፈጸም አይደለም። ዓለማችን ቅዱሳት መጽሐፍት የሚሉትን መናገር ነው።

አንዲት ሐገርን የሚመለከት በቀላሉ ሊፈታ የሚችል ነገር ግን ሊቀበሉት የሚቸግር የተፈጸም ትንቢት እነሆ።

1920 ዓዓ እግዚአብሔር ለአብርሐም እንዲህ ሲል ቃል ገባለት “ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ አለው።” (ዘፍጥረት 12:7)

በስተኋላም እግዚአብሔር ተመሳሳይ ትንቢት ለይስሐቅ እና ያዕቆብ ደገመላቸው።[76]

ለመጀመሪያ ጊዜ ዕብራውያን በስተኋላ እስራኤላውያን በመጨረሻም አይሁድ የተባሉት የአብርሐም ፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ ዝርያዎች ናቸው።

ከመቶዎች ዓመታት በኋላ አምላካቸውን የማይታመኑ እና የማይታዘዙ ከሆነ የሚሆነውን ነገር ነገረው፦

> “እናንተንም ከአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፥ ሰይፍንም አስመዝዝባችኋለሁ፤ ምድራችሁም የተፈታች ትሆናለች፥ ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆናሉ።”
> (ዘሌዋውያን 26:33)

> “እግዚአብሔር እንድትገባ በሚያደርግበት ምድር ለአሕዛቡ ሁሉ መሸማቀቂያ ፣ ማላገጫና መዘባበቻ ትሆናለህ።” (ዘዳግም 28:37፣ 65 አመት)

ብሉይ ኪዳን ተመሳሳይ ትንቢታትን ይዟል።

በ 30 ዓም የነብያቱን ቃል በሚያጸና መልኩ የናዝሬቱ ኢየሱስ የእስራኤልን መጥፋት ተናገረ፦ “ሲቀርብም [ኢየሱስ] ከተማይቱን [ኢየሩሳሌም] አይቶ አለቀሰላት፥እንዲህ እያለ፦ ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፤ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል። ወራት ይመጣብሻልና፥ ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም በየበኩሉም ያስጨንቁሻል፤ አንቺንም በአንቺም ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን ወደ ታች ይጥላሉ፥ በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉም፥ የመጎብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና።” (ሉቃስ 19:41-44) ሰለ ቤተ መቅደሱ ስለራሱ ሲናገርም ፣ ኢየሱስ እንዲህ ሲል አስቀድሞ ተናገረ፦ “ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ።” (ሉቃስ 21:6)

ከአርባ ዓመታት በኋላ እነዚህ ሁኔታዎች ተፈጸሙ።

በ 37 ዓም የተወለደው ታሪክ አዋቂው ዮሲፈስ የዐይን እማኝ ምስክርነቱን አሰፍሮልናል። እሱ እንደጻፈው በ70 ዓም የሮም ወታደሮች ኢየሩሳሌምን ከበቧት ፣ ዙሪያዋን ቅጥር ሰሩ ፣ ለሦስት ዓመታት ያክል ከከበቧት በኋላ ሰራዊቱ አየሩሳሌም አወደሙ። ምንም እንኳን ቄሳር ራሱ ታላቁን ቤተ መቅደስ እንዲያተርፉት ቢያዘም፣ በቁጣ የነደዱት የሮም ወታደሮች በእሳት አያያዙት ውስጡ የነበሩ አይሁድም ተገደሉ። የቤተ መቅደሱ ወርቅና ብር ቀልጦ በደንጋዮቹ መካከል ፈሰሰ። ኢየሱስ እንደተናገረው “ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን”

ተፈጸመ።"[77] በተጨማሪም ሙሴ እና ነብያት እንደተናገሩት አይሁድ በዓለም ዙሪያ ተበተኑ። ለመጪዎቹ ሁለት ሺህ ዓመታት ስደተኞቹ አይሁድ "ለአሕዛብም ስድብና ማላገጫ" እና "ማረፊያ ቦታ የሌላቸው" ሲሆኑ ታሪክ የትንቢታትን ፈጻሜ መሰከረ።

ምንም አይነት የግል ስሜት ይኑረን ፣ ማንም ሰው ሊክደው የማይችለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት ፍጻሜ ሌላ ገጽታ አለ። እግዚአብሔር ለነብያት እንደተናገረው ምንም አይነት ሁኔታ ይከሰት አይሁድ በአሕዛብ መካከል አንደ አንድ ሕዝብ ተጠብቀው ነበር፣ አንድ ቀንም እግዚአብሔር ለአብርሐም ፣ ለይስሐቅ እና ለያዕቆብ ወደ ሰጠው ምድርእንደሚመለሱ ይናገረ ነበር።

ሙሴ ስለ እስራኤል ልጆች ሲናገረ ፦ "አንተን ከበተነበት ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሃል።" (ዘዳግም 30:3) "የሕዝቤን የእስራኤልን ምርኮ እመልሳለሁ፥ የፈረሱትንም ከተሞች ሠርተው ይቀመጡባቸዋል፤… በምድራቸውም እተክላቸዋለሁ፥ ከእንግዲህም ወዲህ ከሰጠኋቸው ከምድራቸው አይነቀሉም፥ ይላል አምላክህ እግዚአብሔር።" (አሞጽ 9:14-15)

በዓለም ላይ የሚገኙ የዜና አወታሮች በሙሉ የእነዚህን ሁኔታዎች ፍጻሜ መሰከረዋል።

በአይሁድ ሕዝብ ላይ የተፈጸመው ነገር በዓለም ታሪክ ወስጥ የተለየ ነው። አንደኛው ነገር የመቀላቀል ሕግን በቀጥታ የሚቃወም ነው። ይሄ ሕግ አንዲት ሐገር በሌላ ሐገር ስተሸነፍ ተፈጻሚ የሚሆን ነው። በጥቂት ትውልዶች በኋላ ተበታተነው የሚገኙት ቀሬታዎች በሰፈሩባቸው ሐገራት ካሉ ሕዝቦች ጋር የቀላቀላሉ። እርስ በርስ ይጋባሉ ፣ አዲስ ቋንቋ እና ባህል ይለምዳሉ፤ በተጨማሪም ማንነታቸውን ያጣሉ። አይሁድ ግን እንዲህ አልሆኑም። ምንም እንኳን በሚሊዮን የሚቆጠሩት አሰገራሚ በሆነ ሁኔታ ለመቀላቀል እና ለመዋጥ ቢሞከሩም አልቻሉም።[78]

እንደምንረዳዉ ብዙዎች ይህንን እውነት ለመቀበል የሚያም ሆኖባቸዋል። በቅርቡ ሊባኖስ ውስጥ የሚገኝ ወንድም እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፦ የትንቢት ፍጻሜን በተመለከተ(እግዚአብሔር አይሁድን ወደ ምድሪቷ ለማምጣት ቃል የገባውን ተስፋ) እንድምታውን ችላ ብዬ ይህንን እምነት ለቀበል አልችልም። የምቀበለው ከሆነ ዓላማዬን ያስተጓጉልብኛል።

እስቲ በግልጽ እንነጋገር። አይሁድ እንደ ሕዝብ መትረፍ እና እንደ ሕዝብ እና እንደ ሀገረ መመስረት ዕውቅና መሰጠት የአሰራኤል መንግስት ፖሊሲስ መቀበል ማለት አይደለም። ሊባኖሳዊውን ጓደኛዬን እረዳዋለሁ አዝንለታልሁ። በ1948

የእናቱ ቤተሰቦች እና ጎረቤቶቿ፣ ከሌሎች በርካቶች ጋር ከቤታቸው ተባረው ነበር። ሐገራቸው አሰቃቂ መከራ ደርሶባታል። ቢሆንም እንኳን ልንረዳው የሚገባው ነጥብ የሚከተለው ነው፦ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ተንቢተ የተነገረው ትንቢት ዐይናችን እያየ እየተፈጸመ ነው።

በዚህ ዘመን አብዛኛዎቹ አይሁድ እናከብራቸዋለን የሚሏቸውን ነብያት የተናግሩትን ነገረ አለመቀበላቸው የትንቢት ፍጻሜ ነው። እንደ ሐገር መንፈሳዊ ዕውሮች ናቸው "ብሉይ ኪዳን [ቶራቸው] ሲነበብ ያ መጋረጃ ሳይወሰድ እስከ ዛሬ ድረስ ይኖራልና፤" (2ቆሮንቶስ 3:15) እንደ ሐገር ወደፊት ንስሐ (ስር ነቀል የአዕምሮ እና የልብ ለውጥ)ገብተው እና ዕድሜ ጠገቡን የእግዚእብሔርን መልዕክት እስካለተቀብሉ ድረስ እንደ ሐገር ሙሉ የእግዚአብሔር በረከት ውስጥ አየገቡም።[79]

በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በምናደርገው ጉዞ ፍጻሜ ላይ እነዚህ ክስተቶች በእግዚአብሔር የዘመን ፍጻሜ አጀንዳ ውስጥ እንዴት እንደሚፈጸሙ እንመለከታለን። በተጨማሪም ደግሞ አንዳንድ ትንቢታት እግዚአብሔር ለመካከለኛው ምሥራቅ እና ለዓለም ሁሉ ሰላለው ዕቅድ እንሰማለን።

> "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።" (ኤርሚያስ 29:11)

## ሰለ ግለሰብ የተነገሩ ትንቢታት

በመላው ብሉይ ኪዳን ውስጥ የተበታተኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ እግዚአብሔር ወደ ዓለለም ሊልከው ቃል ስለገባው ነጻ አውጪ መሲህ ይናገራሉ። የሙት ባህር ጥቅልሎች አንዚህ ትንቢታት የተጻፉት ከመሲሁ መወለድ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት እንደሆነ ይናገራሉ። የእነዚህ ትንቢታት ናሙናዎች የሚከተሉት ናቸው።

- በ 1900 ዓዓ ለአብርሓም የተነገረ ትንቢት ፦ **መሲሁ ወደ ዓለም የሚገባው በአብርሐምና በይስሃቅ የዘር ግንድ በኩል ነው።** (ዘፍጥረት 12:2-3 ፣ 22: 1-18 ተፈጽሟል፦ ማቴዎስ 1)
- በኢሳያስ የተነገረ ትንቢት ፣ 700 ዓዓ ፦ **ከድንግል የሚውለድና ምድራዊ የዘር አባት አይኖረውም** (ኢሳያስ 7:14, 9:6፣ ተፈጽሟል ፦ ሉቃስ 1:26-35 ፣ ማቴዎስ 1:18-25)

- በሚኪያስ የተነገረ ትንቢት፣700 ዓዓ፦ **በቤተልሄም ይወለዳል።** (ሚኪያስ 5:2 ተፈጽሟል፦ ሉቃስ 2:1-20 ፣ ማቴዎስ 2:1-12)
- በሆሴዕ የተነገረ ትንቢት 700 ዓዓ ፦ **ከግብጽ ይጠራል።** (ሆሴዕ 11:1 ተፈጽሟል ፦ ማቴዎስ 2:13-15)
- በሚልኪያስ የተነገረ ትንቢት፣ 400 ዓዓ፦ **መሲሁ መንገድ ጠራጊውን ተከትሎ ይመጣል።** (ሚልኪያስ 3:1 ፣ኢሳያስ 40:3-11 ተፈጽሟል ሉቃስ 1:11-17 ፣ ማቴዎስ 3:1-12)
- በኢሳያስ የተነገረ ትንቢት ፣ 700 ዓዓ፦ **ዕውራን እንዲያዩ፣ ድንቆሮዎች እንዲሰሚ ፣ ሽባዎች እንዲራመዱ ፣ እና ወንጌል ለድሆች ለመስበክ ምክንያት ይሆናል።** (ኢሳያስ 35፡5-6 ፤ 61:1 ተፈጽሟል ፦ ሉቃስ 7:22 ፣ ማቴዎስ 9 ወ.ዘ.ተ)
- በኢሳያስ የተነገረ ትንቢት፣700 ዓዓ ፦ **በገዛ ወገኖቹ ይናቃል፡**፡ (ኢሳያስ 53:2-3 ፣በተጨማሪም መዝሙር 118:21-22። ተፈጽሟል፦ ዮሐንስ 1:11 ፣ማርቆስ 6:3, ማቴዎስ 21:42-46 ወ.ዘ.ተ.)
- በዘካርያስ የተነገረ ትንቢት፣ 500 ዓዓ፦ **በሰላሳ ስቅል እንደሚሸጥ እና ያም ገንዘብ መሬት መግዣ እንደሚሆን ተናግሯል።** (ዘካርያስ 11:12-13። ተፈጽሟል ፦ ማቴ 26:14-16፣ 27:3-10)
- በነብዩ ኢሳያስ የተነግረ ትንቢት፣ 700 ዓዓ፦ **መሲሁ በውሸት ይናቃል፣ በሐሰት ይወነጀላል፣ ይፈረድበታል በአይሑድና በአሕዛብ ይገደላል።** (ኢሳያስ 50:6 ፣ 53:1-12, በተጨማሪም መዝሙር 2 እና 22 ፣ ዘካሪያስ 12:10 ተፈጽሟል፦ ዮሐንስ 1:1፣ 11፡45-57 ፣ማርቆስ 10:32-34 ፣ ማቴዎስ 26 እና 27)
- በዳዊት የተነገረ ትንቢት፣ በ 1000ዓዓ፦ **እጆቹ ይወጋሉ በተመልካቹቸ መቀለጃ ይሆናል ልብሱን በዕጣ ይከፋፈሉታል ወ.ዘ.ተ።** (መዝሙር 22:16 ፣8 ፣ 18 ተፈጽሟል፦ ሉቃ 23:33-37 ፣24:39) (ልብ እንድትሉት የሚያሰፈልገው ይሄ ትንቢት የተነገረው ሮማውያን የሞት ፍርደ ማስፈጸሚያ አደረገው ሳይፍለስፉት በፊት ነው።)
- በኢሳያስ የተነገረ ትንቢት፣ 700 ዓዓ፦ **ምንም እንኳን እንደ ክፉ ወንጀለኛ የተገደለ ቢሆንም ፣ የሚቀበረው ግን በሐብታም ሰውዬ የመቃብር ስፍራ ነው።** (ኢሳያስ 53:8-9፣ ተፈጽሟል፦ ማቴዎስ 27:57-60)
- ዳዊት ትንቢት፣ 1000ዓዓ፦ **የመሲሁ አካል በመቃብር ውስጥ አይበስብስም ፣ ሞትን ያሸንፋል።** (መዝሙር 16:9-11 [በተጨማሪ የሚከተሉትን ይመልከቱ ፦ ማቴዎስ 16:21-23 ፣ 17:22-23 ፣20:17-19 ፣ ወዘተ] ተፈጽሟል ፦ ሉቃስ 24፣ ሐዋርያት 1 እና 2)

የይሆንታ (ፕሮባቢሊቲ) ሕግ እነዚህን የተረጋገጡ ትንቢታት አንድ ሰው ብቻ ሊፈጽመው እንደማይችል ያመልክታል።

ነገር ግን የሆነው ይኸው ነው።

በስተኋላም ፣ ተመልሳቸሁ ይህንን ዝርዝር ማየት ትፈልጉ ይሆናል፣መጽሐፍቅዱሳቸሁን አንሱና እያንዳንዱን የብሉይ ኪዳን ትንቢታትን እና በአዲስ ኪዳን የተመዘገበውን ፍጻሚኣያቸውን አንብቡ።

## ትንቢታዊ ምልክቶች እና አገላለጾች

በመቶዎች ከሚቆጠሩ ትንቢታት በተጨማሪ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መልከቶችና አገላለጾች ይገኛሉ (በተጨማሪም አካል፣ ምስላዎች ፣ ጥላ፣ ጥቁምታዎች እና ምሳሌዎች ተብለው ይጠራሉ)። እግዚአብሔር እነዚህን እያንዳንዳቸውን የነደፋቸው ሰለ ራሱ እና ለሰው ልጆች ስላለው ዕቅድ የሚታዩ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች እንዲሆኑ ስለፈለገ ነው።

በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በምናደረገው ጉዞ ፣ በርካታ እንዲህ አይነት ምልክቶችና እና አገላለጾችን እናያለን። ለምሳሌ አንድ የተለመደ ምሳሌ የተሰዋ ጠቦት ነው ፣ ይሄም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከምዕራፍ 19 እስከ 26 ባሉት ምዕራፎች ተብራርቷል።

በምዕራፍ 21 ለየት ያለውን እግዚአብሔር ሕዘቡ እንዲሰራልት ያዘዘውን ድንኳን የመገናኛው ድንኳን በተመለከት እንማራለን። የመገናኛው ድንኳን እና ከእሱ ጋር አብረው የሚሄዱት ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔርን ማንነት ሐጢአተኞች እንዴት ይቅር ተብለው ከእሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር እንዴት ብቁ እንደሚሆኑ የሚያሳይ፣ የሚታይ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ነው።

የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍን እና የናዝሬቱ ኢየሱስን እያወዳደርን ስናጠና በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የተሰጠውን አሰገራሚ ጥቁምታ እንመለከታለን። በዮሴፍ እና በኢየሱስ ሕይወት መካከል በመቶዎች የሚቆጠሩ መመሳሰሎች አሉ። እግዚአብሔር የዮሴፍን ሕይወት ከ 1700 ዓመታት በኋላ የሚመጣውን የኢየሱስን ሕይወት ለማሳየት ምሳሌ አደርጎ ይጠቀምበታል።[80]

ለእነዚህ አገላጾችና ትንቢታት አንድ ምክንያታዊ የሆነ ማብራሪያ አለ፦

እግዚአብሔር።

## የትንቢት ዓላማ

በምድር ላይ እያለ መሲሁ እንዲህ አለ፦

"ሲፈጽም እኔ እንደሆንኩ ታምኑ ዘንድ ይሄ ከመሆኑ በፊት አሁን ነገርኳችሁ።" (ዮሐንስ 13:19 አመት)

የወደፊቶቹን ጊዜያት የሚያመለክቱ ትንቢታት ፣ ተከትሏቸው የመጣው ፍጻሜ እግዚአብሔር የመልዕክተኞቹንና እና የመልዕክቱን እውነተኛነት ያረጋገጠበት መንገድ ነው። በቃሉ ያለንን መታመን ለማጠንከር እውነተኛውና ሕያዉ አምላክ "በመጀመሪያ መጨረሻውን፥ ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ፤ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ።" (ኢሳያስ 46:10)

ቀጣዩ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የምናደርገው ጉዞ፥ የሚጀምረው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ ዓለም ጅማሬ በሚተርከው የዘፍጥረት መጽሐፍ የሚጀምር ነው። ይሄ ጉዞ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ መጽሐፍ ፣ ሰለ ዓለም ታሪክ መደምደሚያ በሚናገረው ራዕይ መጽሐፍ የሚያበቃ ነው።

ያላረጋግጠናቸው ያለፉ እና ልናያቸው የማንችላቸውን የወደፊት ታሪኮች የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ዐርፍተ ነገሮችን እውነተኛ መሆናቸውን እርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው? ነገ ጸሐይ እንደምትወጣ እርግጠኛ በምንሆንበት አመክንዮ ተጠቅመን እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ለበርካታ ሺህ ዓመታት የፀሐይ ሥርዓት አልተዛነፈም። ምድር መሽከርከሯን አላቆመችም። ፀሐይ በየቀኑ ትወጣለች፣ ትጠልቃለች። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢትም እንደዚያው ነው። ሊረጋገጥ በቻለው ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል አልተዛነፈም።

## የእግዚአብሔር ሙግት

አንዳንድ የሐይማኖት ሰዎች ቅዱስ መጽሐፋቸው የተፈጸሙ ትንቢታትን ይዟል ይላሉ። ሰዎች እንዲህ ሲሉ ከሰማችሁ ከቅዱስ መጽሐፋቸው እጅግ በጣም አሳማኝ የሚሏቸውን ሦስት ወይም አራት ትንቢታት እንዲሰጧችሁ በትህትና ጠይቋቸው። እሺ ይሏችኋል ብዬ አላምንም፣ እሺ ካሉ ግን ትንቢታቱ ጉዳዩ ከመፈጸሙ በፊት መሆን አለመሆናቸውን አጣሩ ፣ ፍጻሜያቸውን ለማጣራት ከዓለማዊ ታሪክ ጋር አነጻጸሯቸው። ከእኔ ልምድ እንደዚህ አይነት

ትንቢታት፣ በጣም ጥቂት እና ግልጽ ያልሆኑ ናቸው፡፡

እውነተኛው እና ሕያው የሆነው አምላክ ለሁሉም ሐይማኖቶችና በምናብ ለተፈጠሩ አማልክት የሚከተለውን ሙግት የሚያቀረበው ለጥሩ ምክንያት ነው፦

> “ክርክራችሁን አቅርቡ፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ማስረጃችሁን አምጡ፥ ይላል የያዕቆብ ንጉሥ። ያምጡ፥ የሚሆነውንም ይንገሩን፤ ልብም እናደርግ ዘንድ ፍጻሜአቸውንም እናውቅ ዘንድ፥ የቀደሙት ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ተናገሩ፥ የሚመጡትንም አሳዩን። አማልክትም መሆናችሁን እናውቅ ዘንድ በኋላ የሚመጡትን ተናገሩ፤ እንደነግጥም ዘንድ በአንድነትም እናይ ዘንድ መልካሙን ወይም ክፋውን አድርጉ። እነሆ፥ እንዳልነበረ ናችሁ፥ ሥራችሁም ከንቱ ነው፤ የሚመርጣችሁም አስጸያፊ ነው።”
>
> (ኢሳያስ 41:21-24አመት)

በትክክል የተፈጸሙ በርካታ እና ዝርዝር ትንቢታትን ስንመለከት መጽሐፍ ቅዱስ ለየት ብሎ ሊታይ ይገባል፡፡

እውነተኛውና ህያው አምላክ መልዕክቱን ለማረጋገጥ ታሪኩን ከመፈጸሙ በፊት በመጻፍ አረጋግጦታል፡፡

የተፈጸመ ትንቢት የእሱ ፊርማ ነው፡፡



# 6

# አስተማማኝ ምስክር

“ውሃ ምን አይነት እንደሆነ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ዓሳን አትጠይቁ” የቻይናውያን አባባል

ይህንን አስቡ፡፡

አንድ ሞቃት ቀን ለመዋኘት እያሰባችሁ በወንዝ ዳርቻ እየተጓዛችሁ ነው፡፡ ነገር ግን ውሃው እንደሚስማማችሁ እና እንደማይስማማችሁ ለማወቅ ትፈልጋላችሁ፡፡ ግፊቱ ፈጣን ነው ወይስ አይደለም? ውሃው በጣም ቀዝቃዛ ይሆን? ሁኔታውስ ምቹ ነው?

የቻይናውያን አባባል “ዓሳን አትጠይቁ” ሲል ይመክረናል፡፡

በዚያ ወንዝ ውስጥ የሚኖሩ ዓሣዎች ለእናንተ መረጃ ለመስጠት “ወሃው ምን አይነት እንደሆነ” ለመናገር ብቁ ያልሆኑት(የናንተን ቋንቋ ለመናገር ካላመቻላቸው ባሻገር)? ዓሳዎች ጠቃሚ መረጃ ለመስጠት የማይችሉበት ምክንያት ከሚኖሩበት ውሃ ውጪ ነገሩን የሚመረምሩበት ምንም ማገናዘቢያ ነጥብ የላቸውም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የምንኖርበት ዓለም እና ለምን እዚህ እንደሆንን ለመረዳት ከፈለጋችሁ ይህንን አይነት መረጃ መምጣት ያለበት ከሰው የተገደበ ራሱ ላይ ካተኮረ ንጽረተ ዓለም ነፃ በሆነ መልኩ ነው፡፡ አሰደሳቹ ዜና የሰማይ አምላክ ለሚፈልጉት ሰዎች ይህንን መረጃ አቅርቧል፡፡

> “ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሰጽ፣ ለማቅናት በጽድቅ መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፡፡”
> (2 ጢሞቴዎስ 3:16)

ቅዱሳት መጽሐፍት “እሰትንፋሰ እግዚአብሔር ያለባቸው” በእስትንፋስ እግዚእብሔር የተጻፉ መሆናቸውን የምናውቀው እንዴት ነው? በቀደመው ምዕራፍ ፈጣሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተፈጸሙ ትንቢታትን በማስቀመጥ የማረጋገጫ ማህተሙን እንዳስቀመጠ ተናግረናል፡፡ የወደፊቱን ጊዜ በተመለከተ 100% ትክክለኝነት መናገር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሔር የመገለጡን ተዓማኒነት ያረጋገጠበት ሌላ መንገድ በበርካታ ምዕተ ዓመታት ውስጥ ለበርካታ ነብያት በመግለጥ ነው፡፡

## አንድ ምስክር ብቻውን በቂ አይደለም

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው “በማንኛውም ወንጀል ወይም ሕግ በመተላለፍ ሰውን ጥፋተኛ ለማድረግ፣ **አንድ ምስክር አይበቃም፤ ጉዳዩ በሁለት** ወይም **በሶስት ሰዎች** መረጋገጥ አለበት” (ዘዳግም 19:15 አመት)

ይሄ መርህ በዓለም ዙሪያ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በፍርድ ቤት የአንድን ነገር እውነትነት ለማረጋግጥ ከአንድ በላይ ምስክር ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩ እውነተኛ ነው ተብሎ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት በበርካታ ተዓማኒ ምንጮች መረጋገጥ መቻል አለበት፡፡

ይህንን እውነት ለመግለጥ እግዚአብሔር፦ “አንድ ምሥክር በቂ አይደለም” የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፦ “ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ… እርሱ ባለፉት ትውልዶች አሕዛብን ሁሉ በገዛ ራሳቸው ጐዳና ይሄዱ ዘንድ ተዋቸው፡፡ ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሠራ፣ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም፡፡” (ሐዋርያት 14:15-17) የሚለውን የራሱን ሕግ ቸል አላለም፡፡

ከሰው ተነጥለው በርቀት የሚኖሩ በምድር ላይ የሚኖሩ ነገዶች ውጫዊ የፍጥረት ምስክርነት (እግዚአብሔር የፈጠረውን በመመልከት) እና የኅሊና ውስጣዊ ምስክርነት

(ውስጣዊ የሆነ የትክክለኛ ፣ ሐሰተኛ እና ዘላለማዊ የሆነ ነገር ምስክርነት) አላቸው። ስለዚህም እግዚብሔር የሰው ልጅ “ምክንያት የለውም”[81] ይላል። ቢሆንም እንኳን እሱን እና የእሱን እውነት በትጋት ለሚፈልጉ ሰዎች የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ ተጨማሪ መገለጥ እንደሚሰጥ ቃል ይገባል።

## ዘለቄታዊ ምስክርነት

እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክርነት አልተወም።

በሰው ልጅ የሺህ ዓመት ታሪክ መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በቀጥታ በመናገር ወይም እወነቱን ለመጀመሪያዎቹ ሰዎች በቃል ምስክርነት አሳውቋል።

የመጀመሪያው ሰው አዳም 930 ዓመታት ኖረ። በሰው ልጅ ታሪክ የመጀመሪያው ሺህ ዓመት ታሪክ ውስጥ የኖሩ ሰዎች ሰለ ፈጣሪ ባለቤታቸው እውነት ዋነኞቹን ምስክሮች ማለትም አዳምና ሄዋንን መጠየቅ ይችሉ ስለነበር ምንም ምክንያት የላቸውም።[82] የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች አማካይ የዕድሜ ዘመን ጋር ሲነጻጸር አሥራ አንድ ጊዜ በላይ ይረዝም ነበር፤ ፈጣሪም “የዘመኖቻችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት፥ ቢበረታም ሰማንያ ዓመት ነው” (መዝሙር 90:11 አመት) አድርጎ አስተካክሎታል።

በ1920 ዓዓ በሰተኋላ አብርሐም ሲለ የጠራውን የዕድሜ ባለጠጋ መረጦ ነበር። እግዚእብሔር አሕዛብን ሁሉ ስለ ራሱ እና ለሰው ልጆች ስላለው ዕቅድ ጠቃሚ ትምህርት በእሱ በኩል ሊያስተላልፍ አብረሐምን ሕዝብ ሊያደርገው ቃል ገባለት። እግዚአብሔር ነብያትን ቅዱሳት መጻህፍትን እና መሲሁን ወደ ዓለም ለመላክ ያሰበው በመረጠው ሕዝብ በኩል ነበር። በ1940 ዓዓ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል የእሱ ተወካይ እንዲሆን አንድን ሰው መረጠ። የሰውየው ስም ሙሴ ነበር።

## የጽሁፍ ምስክርነት

እግዚአብሔር ሙሴ የመጀመሪያውን የመጽሐፉን ክፍል ቶራን እንዲጽፍ አነሳሳው። የሰማይና የምድር ፈጣሪ እውነቱን ለመጭው ትውልድ እስከ መጨረሻው ዘመን ደረሰ በጽሑፍ ለማቅረብ ዐቀደ። የሚጻፉትን ቃላት በሙሴ አዕምሮ ውስጥ አሰቀመጠ። እግዚአብሔር በሙሴ እጅ በሚፈጸሙ ተዓምራት ቃሉን በአሕዛብ ፊት አጸና። በተጨማሪ እግዚአብሔር ለግብጻውያን እና ለእስራኤላውያን በተናገራቸው የወደፊት

ክስተቶች አማካኝነት ተገለጠ። ሙሴ እንደተናገረው ነገር ሁሉ ሆነ። እግዚአብሔር ለተገቢ ጥርጣሬ እንኳን ቦታ አልተወም።

በጣም ግትር ተጠራጣሪ የሚባል ሰው እንኳን በሙሴ በኩል የተናገረው አምላክ እውነተኛ እና ሕያው መሆኑን መናገር ነበረበት።[83]

በ 1500 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ከጻፉ የበርካታ ነብያት ዝርዝር መካከል ሙሴ የመጀመሪያው ነበር።[84] ነብያቱ ከተለያዩ የኋላ ታሪክ የነበራቸው ሰዎች ናቸው። አንዳንዶች መደበኛ ትምህርት ተምረዋል።

ምንም እንኳን በተለያዩ ትውልዶች ውስጥ የኖሩ ቢሆኑም የጻፉት መልዕክት ከመጀመሪያው አሰከመጨረሻው የተስማማ መልዕክት ጽፈዋል።

እግዚአብሔር እንደ ሙሴ ፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን እና ተጨማሪ ስላሳ ሰዎችን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍትን እንዲጽፉ መረጣቸው። ቃሉን በተፈጸሙ ተሰፋዎች ፣ ትንቢታት እና ተዓምራዊ ምልክቶችና ድንቆች አጸና።

በአዲስ ኪዳን በመሲሁ አነሳስ፣ ሕይወት ፣ ቃል፣ ስራ ፣ ሞት እና ትንሳኤ የተጻፈው በአራት ሰዎች አማካኝነት ነው፦ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ እና ዮሐንስ። እነዚህ አራት ሰዎች የወንጌልን ታሪክ (በአረብኛ ኢንጅል የሚባለውን) ጻፉ በዚህም ለዓለም አራት የተለያዩ ምስክርነቶችን አበረከቱ። እግዚአብሔር ጴጥሮስን (ዓሳ አጥማጅ) ፣ ያዕቆብና ይሁዳን (የኢየሱስ የእናት ልጆች) እና ጳውሎስን (ምሁር እና የቀድሞ አሸባሪ) አነሳሳና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን የአሁን እና የወደፊት አስገራሚ ዝርዝር እንዲያቀርቡ አደረገ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ሐዋርያው ዮሐንስ የመጨረሻውን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ የዚህ የምናውቀው ዓለም ታሪክ እንዴት እንደሚያበቃ ምስል ከሳች በሆነ ሁኔታ የሚገልጸውን መጽሐፍ ጻፈልን።

## አዝልቆታዊ ምስክርነት

በጥቅሉ እግዚአብሔር ወደ አርባ የሚሆኑ ጸሐፍትን ከአሰራ አምስት በላይ ክፍለ ዘመን ለሚሆን ጊዜ ለሰው ልጅ የሰጠውን መገለጥ እንዲጽፉ ተጠቀመ። አብዛኛዎቹ እነዚህ ምስክሮች እርስ በእርሳቸው የማይተዋወቁ ቢሆኑም ከታሪኩ እና መልዕክቱ ተከታታይነት አንጻር እርስ በእርሳቸው የሚጣጣሙ ናቸው።

በአንድ የሕይወት ዘመን እንኳን መልዕክቱ ሳይዛባ እንዲህ አይነት ትረካዎችን ሊያስተላለፍ የሚችል ማን ነው?

"ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፍቃድ የመጣ አይደለም።" (2ጴጥሮስ 1:21አመት)

ላለፉት ክፍለ ዘመናት ብዙኹን የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት እና መልዕክታቸውን ለማጣጣል ሞክረዋል። የጳውሎስ መልዕክቶች በተለየ ሁኔታ ተተችተዋል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ የጳውሎስን መልዕክት በትኩረት እንድንመለከት ያዘናል፦ "እንዲህም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፤ በመልእክቱም ሁሉ ደግሞ እንደ ነገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ። በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ።" (2ጴጥሮስ 3:15-16አመት)

ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈው ሁሉ ነብያት ከጻፉት ጋር የተሰማማ ነው። ጳውሎስ ራሱ እንዲህ ሲል አረጋግጧል "ከእግዚአብሔርም ዘንድ ረድኤት ተቀብዬ ለታናሹም ለታላቁም ስመሰክር እስከዚች ቀን ድረስ ቆሜአለሁ፤ ነቢያትና ሙሴ ይሆን ዘንድ ያለውን፥... ነቢያትን ታምናለህን?" (ሐዋ 26:22፣ 27)

## ተመሳሳይ ወይ ተመሳሳይ ያልሆኑ

የምስክር እውነተኛነት የሚለካው በሰውየው ምስክርነት ውስጥ በተካታተው እውነት ላይ ብቻ ሳይሆን ምንም አይነት የተዛነፈ ነገር ሳይገኝበት ሲቀር ነው። ይሄንን በሚከተለው ምሳሌ ውስጥ ማየት እንችላለን፦

> በአንድ ጸሐያማ ቀን አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለመፎረፍ ያላቸውን ፍላጎት ሊገታ የሚችል ነገር አልተገኘም። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት የትምህርት ክፍለ ጊዜው ያመለጣቸው የመኪናቸው ጎማ ስለ ተነፈሰ እንደሆነ ተናገሩ። ይበልጥ እንዲረጋጉም ፈገግ ብላ "ነገር ግን ትላንትና ፈተና አመለጣችሁ አለቻቸው።" ነገር ግን ቀጠል አድርጋ በተጨማሪም "ተቀመጡና እርሳሶቻቸሁን እና ወረቀት አውጡ። የመጀመሪያው ጥያቄ፦ የተነፈሰው የትኛው ጎማ ነው የሚል ነው?"[85]

ልጆቹ ይህንን አንድ ነጥብ በተመለከተ የሰጡት እርስ በርሱ የሚጋጭ መልስ የፈጠራ ታሪካቸውን ውሸትነት አሳበቀባቸው።

ከእነዚህ አራት ወጣቶች እርስ በርስ የሚጋጭ ምስክርነታ በተጻራሪ የእግዚአብሔር ምስክርነት ተመሳሳይ ነው። በደርዘን የሚቆጠሩ ምስክሮች እና ሊቆጠሩ የማይችሉ ትውልዶች ውስጥ የሚገኙ ጸሐፊዎች በመጠቀም ፈጣሪያችን ራሱን እና ዕቅዱን እንከን በሌለው ተመሳሳይነት ጽፏል።

እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ የሰው ልጅ ሐይማኖቶች እና ፍልስፍናዎች በሞሉበት በሚናወጥ ባህር ውስጥ እግዚአብሔር ነፍሳችንን ልናሳርፍበት የምንችለውን ዐለት አቅርቦ ጠብቆ አቆይቶልናል። ያም ዐለት ቃሉ ነው።

> "ከእርሱም ይልቅ **እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤…** ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ።… ነገር ግን **ሐሰተኞች ነቢያት** ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ በመካከላችሁ ደግሞ **ሐሰተኞች አስተማሪዎች** ይሆናሉ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል። ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም።" (2ጴጥሮስ 1:19 – 2:3)

## ሐሰተኛ ነብያት

ስለዚህም እግዚእብሔር ስግብግብ እና ራስ ወዳድ ከሆኑ ና "በሚያስት ቃል ይበዘብዟችኋል" ከሚያደርጉ ነብያት እና መምህራንን በተመለከተ ያስጠነቅቃል።[86] መጽሐፍ ቅዱሳችን ለእግዚአብሔር እንናገራለን የሚሉ የበርካታ ሰዎችን ታሪክ ይዟል፣ ነገር ግን ይሄ መልዕክት የመነጨው "ከውሸት መንፈስ" (1 ነገስት 22:22) ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ 850 ሐሰተኛ ነብያት እና አንድ እውነተኛ ነብይ ኤልያስ የነበረበትን የእስራኤል ታሪክ ዘመን ይገልጻል። ምንም እንኳን 7000 ሰዎች ለብቸኛው እውነተኛ አምላክ ታማኝ ቢሆኑም እንኳን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሌሎች ግን ራስ ወዳድ የሆኑና ሐሰተኛ ምስክሮችን ወደ መታመን ተቃርበው ነበር።[87]

ከታማኝ ነብያት መካከል አንዱ የሆነው ሚኪያስ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር፦

> “እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚያስቱ ነቢያት እንዲህ ይላል፤ በጥርሳቸው ሲነክሱ በሰላም ይሰብካሉ፤ በአፋቸው ግን አንዳች በማይሰጥ ሰው ላይ ሰልፍን ያስቡበታል።”
> (ሚኪያስ 3:5)

ይሄ የታሪክ አካሄድ ነው፣ ኢየሱስም ያስጠነቀቀው ከዚህ የተነሳ ነው።

> “በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱምየቀጠነ ነውና፥የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው። **የበግ ለምድ ለብሰው** ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን **ነጣቂዎች ተኲላዎች** ከሆኑ **ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።** ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ **ክፉ ፍሬ** ያደርጋል።” (ማቴዎስ 7:13-17)

በበርካታ ክፍለ ዘመናት መካከል በርካታ ክፉ ነብያት እና አሰተማሪዎች መጥተው ሄደዋል። ጥቂቶች በመቶዎች እና በሺዎች በሚቆጠሩት ላይ ተጽዕኖ ፈጥረዋል። ሌሎቹ ደግሞ በሚሊዮን እና በቢሊዮን የሚቆጠሩ ነፍሳትን “ወደ ጥፋት መንገድ” መርተዋል።

ሐሰተኛ ነብያትን “ወደ ጥፋት” ከሚከተሉ “ብዙ” ሰዎች መካከል እንዳትሆኑ የዛን ሰውዬ ትምህርት በዚህ ወንፊት አበጥሩት ፦

> የእውነተኛ ነብይ መልዕክት ሁልጊዜ ቀደመውት የመጡ እና እውነተኛነታቸው ከተረጋገጠላቸው ቅዱሳት መጽሐፍት ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

የእግዚአብሔር ነብያት ነን ያሉ ሰዎችን **ሶስት አጋጣሚዎችን** ተመልከቱ። እነዚህ እውነተኛ ነብያት ናቸው ወይስ ሐሰተኛ?

## ገጠመኝ #1፦ የተቀበረ “መሲህ”

ታሪክ ራሳቸውን ነብያት እና መሲሆች ነን ብለው የጠሩ ከክርስቶስ በኋላ የተነሱ እንዷ ነበሩ ይናገራል።[88] አንደኛው አቡ ኢሳ ይባላል።

የፋርሱ አቡ ኢሳ በ7ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የኖረ ሰው ነው። ወደ ድል እንደሚመራቸው ቃል ስለገባ ተከታዮቹ መሲሁ ነው ብለው ያስቡ ነበር ምንም እንኳን ያልተማረ ቢሆንም መጽሐፍት እንደጻፈ ተዘግቧል። ነገር ግን ይሄ መልዕክት ቅዱሳት መጽሐፍትን የሚጻረር ነበረ።

አቡ ኢሳ ተከታዮቹ በቀን ውስጥ ለሰባት ጊዜ ያህል እንዲጸልዩ ጦርነት ላይም እሱን እንዲከተሉ እና መለኮታዊ ጥበቃ እንደሚኖራቸው አሰተምሯቸው ነበር። ነገር ግን አቡ በወጊያው ውስጥ ሞተ እንደገና ሊነሳ ስላልቻለ ተቀበር ፣ ተከታዮቹም መሲሁ እንዳልሆነ ለመናገር ተገደው አመኑ።

አቡ ከመምጣቱ ከበርካታ ጊዜያት በፊት ኢየሱስ ተከታዮቹ አስጠንቅቆ ነብር።

> "ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ፤ አስቀድሜ ነገርኋችሁ።" (ማቴዎስ 24:24-25)

## ገጠመኝ #2 ፦ ራስን የማጥፋት "ነብይ"

ጂም ጆንስ ዘፒፕልስ ቴምፐል የሚባል ኑፋቄ መሰርቶ ነበር። በ1970 ዎቹ መጀመሪያ ላይ ጆንስ በሳንፍራንሲስኮ ካሊፎርንያ ታዋቂ ሰባኪ ነበር። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችም በፖለቲካ እና ድሆችን ለመረዳት በሚያገለግል ፕሮጀክት ውስጥ ውስጥ እንዲሳተፉ አስተባብሮ ነበር። ጆንሰን ራሱን "ነብዩ" ብሎ ይጠራ ነበር፣ በተጨማሪም ካንስርን መፈወስ እና ሙታንን የማስነሳት ሳይል እንዳለው ተናግሮ ነበረ።

ወዲያውኑ ጂም ጆንስ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ ተከታዮቹ በድቡባዊ አሜሪካ ወምትገኘው "ጆንስ ታወን" ጉያና ተከትለውት እንዲሄዱ አደረገ። በዚህ አዲስ ማህበረሰብ "ነብዩ ጂም" ለደቀ መዛሙርቱ የሰላምና የደስታ ሕይወትን እንደሚያገኙ ቃል ገባላቸው። ነገር ግን ትልቅ ውሸት ነበር።

ጆንስ ግን የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ነበር። በሳንፍራንሲስኮ ክሮኒክል እንደተዘገበው "ሕዳር 18 [1978] ጆንስ ተከታዮቹን ሳይናይድ በመውሰድ ራሳቸውን እንዲገድሉ አዘዘ። አንወስድም ያሉት በግድ እንዲወስዱ ተደረገ። ልጆች በመርፌ መልክ ተስጥቷቸው እንዲሞቱ ተደረገ። ወዲያውኑም የጆንስ የራሱን ጨምሮ የ914 ሰዎች አስከሬን በጆንስ ታወን ተገኘ።"[89]

## ማስረጃ #3 ፦ ያልተረጋገጠ "ቅዱስ መጽሐፍ"

ዮሴፍ ስሚዝ የተወለደ 1805 በሰሜን አሜሪካ ነበር። በድህነትና እና በአጉል አምልኮ ውስጥ ስላደገ ወጣት ሆኖ የእግዚአብሔር ነብይ እንደሆነ ይናገር ነበር። የብርሃን መልዐክ በሆነው ሞሮኒ በኩልም እግዚአብሔር በተከታታየ ራዕዮች እንደተናገረው ይናገር ነበር።

ስሚዝ እንዲህ በሎ ነበር "ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠረኝ የተለየ ሳይል ቁጥጥር ስር ውዬ ነበር፣ መናገር እንዳንችል ምላሴን እሰከ ማሰር የሚያደርስ ከፍተኛ ተጽዕኖም ነበረው። ድቅድቅ ጨለማ ዙሪያዬን ከበበኝ ድንገት ለጠፋ እንደሆነ የሚመስል ግዜ ላይ እንዳለሁ ተሰማኝ።" በመቀጠልም ስሚዝ ከጭንቅላቱ በላይ "ከፀሐይ በላይ የሚያበራ የእሳት የእሳት አምድ እንደታየው እና ቀሰ በቀስም እየወረደ ላይ ወደቀብኝ" ይላል።[90] ስሚዝ እግዚአብሔር አዲስ ቅዱስ መጽሐፍ ማለትም መጽሐፈ ሞርሞንን እንደገለጠለት ተናገረ። ለተከታዮቹም መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የመጣ ቢሆንም አዲሱ መጽሐፍ ግን የእግዚአብሔር የመጨረሻው መገለጥ እንደሆነ ነገራቸው። ስሚዝ ሰዎች ጸሎት እንዲያነበንቡ፣ እንዲጾሙ፣ ምጽዋት እንዲሰጡ ፣ መልካም ስራ እንዲሰሩ እና እሱን እንደ ነብይ እንዲቀበሉ አስተማራቸው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እሱ ራሱ የራስ ወዳድነት እና የአመንዝራነት ሕይወትን ይኖርና እና ትክክል እንደሆነ ይናገር ነበር።

ምንም እንኳን የዮሴፍ ስሚዝ "መገለጦች" በሌላ ምስክሮች የተረጋገጡ ባይሆኑም (እሱ ሦስት ምስክሮች እንዳሉት ይናገራል) በተጨማሪም የእሱ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክ እና ከሥነ ቅርስ[91] ጋር የሚጋጭ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት በሚሊዩን የሚቆጠሩ የሞርሞን እምነት ተከታዮች ይገኛሉ። ባለጠጋዎቹ የሞረሞን አብያተ ክርስቲያናት ሚሲዮናውያንን በዓለም ዙሪያ ይልካሉ። በየቀኑም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሞርሞን ይሆናሉ (በተጨማሪም የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ)፤ ብዙዎቹ ሞርሞኖች ቅን እና መልካም ሰዎች ናቸው፤ ነገር ግን "የነብዩ ዮሴፍን መልዕክት" መጽሐፍ ቅዱስ ወጥ የሚገኙ ነብያት ካስተማሩትና ከጻፉት ጋር ስናወዳድረው ፣ ሁለት በጣም የተለያዩ መልዕክቶችን እናገኛለን።


ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታችንን ምንም ያክል ብሩህ አዕምሮ ያለው ይሁን እርስ በርሱ በሚጋጭና ባልተረጋገጠና ራሱን ነብይ ብሎ በሰየመ ሰው መልዕክት ላይ ተመርኩዞ መወሰን ጠቢብነት

አይደለም፡፡ “ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልዐክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና፡፡” (2 ቆሮንቶስ 11:14)

## የተረጋገጠ መልዕክት

ግራ በተጋባ እና ብዙዎች “የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት” (ሮሜ 1:25) በለወጡበት ዓለም ብቸኛው እውነተኛ አምላክ የእሱን እውነት ከተቃዋሚ መልዕክቶች ለይቶ አሰቀምጦታል፡፡

እግዚአብሔር መልዕክቱን ግልጽ ያደረገበት እና ያረጋገጠበት አንደኛው መንገድ ቀሰ በቀስ ፣ ተመሳሳይነቱን እንደ ጠበቅ በበርካታ ነብያት በኩል ለበርካታ ትውልድ መግለጡ ነው፡፡



በዚህ ምሳሌ ውስጥ የሚገኙት አርባዎቹ ወንዶች በአሥራ አምስት ክፍለ ዘመናት ውስጥ ፣ የእግዚአብሔርን ተመሳሳይ እና የተረጋገጠ መልዕክት የጻፉ መልዕክተኞችን የሚወክል ነው፡፡



ብቸኛዎቹ ሰዎች በሰተኋላ የመጡ እና የሚጋጩና ያልተረጋገጡ መልዕክቶችን የሚወክሉ መልዕክተኞች ናቸው፡፡

ባለፉት ጥቂት ምዕራፎች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የሚያሳዩ በርካታ ማረጋገጫዎችን አይተናል፡፡ እነዚህን ሌሎቹ ማስረጃዎች ምን ያክል አሳማኝ ቢሆኑም በጣም አሳማኙ የእግዚአብሔር መልዕክት ማረጋገጫ የሚገኘው እሱን በማዳመጥ ፣ በመረዳት እና በመቀበል ነው፡፡

በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የተገለጠው ትዕይንት ከምናስባቸው ሳይላት የበዛና የበለጠውን የሚገልጡ ናቸው፡፡ ይሄ

የፈጣሪያችንን የከበረና ፍጹም ሚዛናዊ የሆነ ባህርይ ያሳያል። ሰዎችን ከሞት ፍርሃት ነፃ ያወጣል፤ በተጨማሪም እርግጠኛ የሆነውን የዘላለም ሕይወት ተስፋ ይስጣቸዋል። ጠባያቸውን እና ባህርያቸውን ይለውጣል። ወደ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ይመራቸዋል።

የትኛውም አጋንንት ወይም ሰው ይህንን አይነት መልዕክት ሊያቀርብ አይችልም።

ነገር ግን የእኔን ቃል መሰማት የለባችሁም።

“**ሁሉን ፈትኑ** መልካሙንም ያዙ፤” (1ተሰሎንቄ 5:21)



# 7
# መሠረት

“ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።”
(ማቴዎስ 7:24)

የናዝሬቱ ኢየሱስ የተራራ ላይ ስብከቱን ያጠቃለለው በሚከተሉት ቃላት ነው፦

> “ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፤ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፤ ወደቀም፤ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።” (ማቴዎስ 7:24-27)

ሞገዱን በተቋቋመው እና በፈራረሰው ቤት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መሠረቱ።

ጠቢቡ ሰው ቤቱን የገነባው ዐለት ላይ ነው፤ ሞኙ ሰው ግን ቤቱን የገነባው በሚንሸራተት አሸዋ ላይ ነው።

እግዚአብሔር ሰዎች እንዲረዱ እና እንዲያምኑት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ነብያት በኩል ለመልዕክቱ የሚያስፈልገውን የዐለት መሠረት አስቀምጧል። ያ መሠረት ደግሞ ቶራ (የሙሴ ሕግ፣ ፔንታቱክ ወይም ተውረት ተብሎ የሚጠራው ነው።)

## የጅማሬው መጽሐፍ

የሙሴ ሕግ የመጀመሪያዎቹን አምሥት መጽሐፍት ይይዛል። የመጀመሪያው መጽሐፍ ዘፍጥረት ወይም ጅማሬ ይባላል። ዘፍጥረት የጅማሬ መጽሐፍ ነው በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር የምድርን፣ የሕይወትን ፣ የሰው ልጆችን ፣ የጋብቻን ፣ የቤተሰብን፣ የማህበረ ሰብን ፣ የሃገራትን እና የቋንቋዎችን ጅማሬ ያሳውቃል። ዘፍጥርት ለሕይወት ምስጢራዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል። እግዚአብሔር ምን አይነት አምላክ ነው? ሰው ከየት መጣ? እዚህ ያለነው ለምንድን ነው? የእኩይ ምንጭ ምንድን ነው? ሰዎች መከራ የሚቀበሉት ለምንድን ነው? ፍጹም የሆነው አምላክ ፍጹማን ያልሆኑ ሰዎችን የሚቀበለው እንዴት ነው?

ለእነዚህ እና ሌሎች ወሳኝ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዳበሩት በሰተኋላ ቢሆንም ፣ ለእነዚህ ጥያቄዎች መሰረት ያስቀመጠው ግን በዘፍጥረት ውስጥ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው መጽሐፍ ተከትሎት ለሚመጣው ሁሉ መሠረት ነው።

## የእግዚአብሔር ታሪክ

መጽሐፍ ቅዱስ በሺዎች ዓመታት ውስጥ የተከሰቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ታሪኮችን ይዟል። እነዚህ ታሪኮች በአንድነት ሰምተነው የማናውቀውን አንድ ታሪክ ይፈጥራሉ። በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር አንድ ዐብይ መልዕክት፣ ተናግሮ የማያውቅ አንድ ዜና አሰቀምጧል።

የእግዚአብሔር ድራማዊ ታሪክ በርካታ የጡዘት ነጥቦችን ይዟል። ቅዱሳት መጽሐፍትን እየመረመርን በምንጓዝበት ጊዜ አንደኛውን የታሪክ ጣሪያ የምናገኘው በወንጌላት ውስጥ ነው። ሌላኛው አሰገራሚ ጣሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ መጽሐፍ የሚገለጥ ነው፣ ርዕሱም ራዕይ ወይም መገለጥ ነው።

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ዕቅዱን ለሰው ልጆች የገለጠ ቢሆንም ፣ይሄ ዕቅድ ለብዙ ሰዎች ሚስጥር እንደሆነ ቀጥሏል።

## የመጀመሪያውን ነገር የመጀመሪያ ማድረግ

የዘፍጥረት መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ 1189 ምዕራፎች 50 ይይዛል።[92] መጽሐፍ ቅዱስን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው በቀጥታ ለማንበብ ሦስት ቀን እና ሦስት ሌሊት ይፈጃል።

ቀጥለን በምናደርገው ጉዞ ምንም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን አብዛኛዎቹን ታሪኮች የምናልፋቸው ቢሆንም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ዕቅድ “ትልቁን ምስል” የሚያሳዩ ተወዳጅ እና ቁልፍ ታሪኮችን ግን እንነጋኛለን። አብዛኛውን የጉብኝታችንን ጊዜ የምናሳልፈው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሌላ ስፈራ የሚገኙ እውነቶች ስለሚያሳዩንየመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ የሆኑት የመጀመሪያ አራት ምዕራፎች ላይ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ጥቂት ምዕራፎች አስፈላጊነት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ለልጅ ታሪክ በምንናግርበት ወይም በምናነብበት ጊዜ ፣ ከየት ነው የምንጀምረው? ከታሪኩ መሀል ጀምረን ከዚህም ከዚያም አንድና ሁለት መሰመር እያነበብን ወደ መጨረሻው እንዘላለን? በፍጹም ከመነሻው እንምራለን። መጽሐፍ ቅዱስን በሚመለከት በርካታ አንባቢያን ከስፍራ ወደ ሰፍራ ይዘላሉ። ምናልባትም የእግዚአብሔር ቃል ምስጢር የሆነባቸው የመጀመሪያዎቹን ገጾች ቸል ስላሉ ይሆን? አህመድ በኢሜይሉ “ሐጢአተኛ የምትሉት ነገር አይገባኝም” (ምዕራፍ 1) ካለው ጋር የሚስማማ ይሆን?

የእግዚአብሔር ታሪክ ጅማሬ ካልገባን ቀሪውን ታሪክ ለማድነቅ ከባድ ይሆንብናል። ነገር ግን የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ምዕራፎች ከገቡን ፣ ቀሪው በአስደናቂ ሁኔታ ይገባናል።[93]

## የመነሻ ታሪክ

አንድ የስንዴ ቅንጣት አስቡ። ብዙ አይመስልም፤ ቀላል በምትመስለው ዘር ውስጥ ተሰውሮ ፍሬ ለማፍራት የሚያስፈልገው ውስብስብ የሆነ ቀመር እና እምቅ ኃይል በዚያ ተክል ውስጥ ይገኛል።

> “ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች።” (ማርቆስ 4:28)

እግዚአብሔር ጥራጥሬዎችን ፣ ፍራፍሬዎችን እና አትክልትን ወዲያውኑ እንዲበስሉ አድርጎ አልሰራቸውም ታሪኩ እና መልዕክቱ በሙሉ በአንድ ጊዜ እንዲገለጥ አልፈለገም። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ አካል የሚያሰፈልጉትን ተክሎች በሂደት እንዲያድጉ አድርጎ እንደሰራቸው በሂደት በሚገለጥ እውነት

በኩል የሚገኘው የሰው ልጅ የነፍስ ምግብም እንደዚያው እንዲሆን ፈቅዷል።

> “ትእዛዝ በትእዛዝ፥ ትእዛዝ በትእዛዝ፥ ሥርዓት በሥርዓት፥ ሥርዓት በሥርዓት፥ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ነው።”
> (ኢሳያስ 28:10)

የዘፍጥረት መጽሐፍ እግዚአብሔር የእውነትን ዘር በጥንቃቄ የዘራበት ለም መሬት ነው። ይሄ ዘር ሲያፈራ እና ሲበስል ሕይወትን እና እርካታን ለዓለም የሚሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ይሆናል።

## ሽል

ለዘመናዊ ቴክኖሎጂ ምስጋና ይግባውና በፊት በሚስጥራዊነት ተሸሽገው የነበሩ ነገሮች አሁን ይታያሉ። ለምሳሌ ዛሬ የሰው ልጅ ሽል ዕድገትን ጥርት ያለ ምስል ማየት እንችላለን። ይገርማል! በስምንት ሳምንታት ውስጥ፣ በእናትየዋ ማሕጸን ውስጥ የሚገኘው የዳበረ እንቁላል የለውዝ ፍሬ የሚያክል ሕጻን ይሆናል፣ ይህ ህጻንም አይኖች፣ ጆሮዎች ፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ ክንዶች፣ እጆች እና እግሮች ያለው ነው። የራሱ የሆነ የጣት አሻራም አለው። ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ የተበጀ ባይሆንም ሁሉን ነገር ይዟል።

በተመሳሳይ መልኩ በዘፍጥርት መጽሐፍ ውስጥ የማንገኘውና ፈጣሪያችን ስለ ራሱና ለሰው ልጅ ስላለው ዕቅድ የገለጠው መሠረታዊ እውነት ሽል እንደሆነ እናውቃለን። ነገር ግን ቀሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል “የእግዚአብሔር ምስጢር” (ራዕይ 10:7) ወደ ምሉዕነት ያድጋል።

እስከ ዛሬ ድረስ የእግዚአብሔር ማንነት እና ዓላማዎች ለበርካታ ሰዎች ምስጢር ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር “ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ **ምሥጢር** ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ **ተገልጦአል፤**” (ቆላስያስ 1:26) ስላደረገ ምስጢራነቱ አስፈላጊ አልነበረም።

እግዚአብሔር ምስጢሩን እንድናውቅ ይጋብዘናል ነገር ግን ለመረዳት መፈለግ መቻል አለብን።

## ከዚህም ከዚያም

መጽሐፍ ቅዱሳችን ምስል እንደ መገጣጠም ጨዋታ ያለ ነው፡፡

አንዳንድ ነገሮች የሚገጣጠሙበት ሂደት የማያሳስት ሲሆን፣ የሌሎች ደግሞ ያን ያህል ግልጽ አይደለም፡፡ ትዕግስትና ጽናት ይፈለጋሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰላሰል ጊዜ ስንወስድ ግራ መጋባቱ ይተንና እርስ በርሱ የሚስማማው ንድፍ ጎልቶ ይታየናል፡፡

በቅርቡ በሊባኖስ ከሚገኝና ጋዜጠኛ ለመሆን ከሚፈልግ ሰው ጋር መልዕክት ተለዋውጬ ነበር፡፡ ምንም እንኳን እስካሁን ያልተገናኘን ቢሆንም ወዳጆች ሆነናል፡፡ ለእኔ በላከው የመጀመሪያ ኢሜይሉ እንዲህ ብሎ ነበር፦

> ርዕሰ ጉዳይ — የኢሜይል ምላሽ
>
> እኔ ሰለ ተጨባጭ እውነት አዎንታዊ ማረጋገጫ ላይ ይደረሳል ብዬ አላምንም።

እኔም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቅድመ እሳቤ ወደ ጎን አስቀምጦ መጽሐፍ ቅዱስን በራሱ እንዲያነብ እና ለራሱ እንዲናገር እንዲፈቅድለት አበረታትቼው ነበር፡፡ ይህንን አያደረገ እንደነበር ከኢሜይሉ መረዳት እንችላለን፦

> ርዕሰ ጉዳይ — የኢሜይል ምላሽ
>
> አዲስ ኪዳንን በዐረብኛ አንብቤያለሁ ፣ ብሉይ ኪዳንን ለማንበብ አቅጃለሁ። ከዚህ በፊት ያነበብኩት ከዚህም ከዚያም ነበር። አሁን ብዙ እጠይቃቸው የነበሩ ጥያቄዎች ተመልሰው አግኝቻቸዋለሁ ... ታዲያ ከዚህ ንባብ ምን አገኘሁ? ጥልቅ አክብሮት [ለመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት] ፣ የግለሰብን ሕይወት ሊለውጥ እንደሚችል ኃይል ፣ ጥብቅ ትዕዛዛዝት ከመስጠት ይልቅ እውነተኛ ለውጥ የሚያመጣ... አድርጌ እንዳየው አደረገኛል። በእጃችን ስለሚገኘው ነገር እርግጡን ለማወቅ መንገድ እንዳለ ተረድቻለሁ።

በቅርቡ የሚከተለውን አሰተውሎ ነበር፦

> ርዕሰ ጉዳይ — የኢሜይል ምላሽ
>
> ከረጅም ጊዜ በፊት ልወስደው ይገባኝ የነበረውን እርምጃ ወሰጃለሁ። “መጽሐፍ ቅዱስን አንብቤያለሁ” ማለት ብቻ በቂ እንዳልሆነ አይቻለሁ። በተገቢው ሁኔታ መነበብ ያለበት መጽሐፍ ነው። በርካታ ጥያቄዎቼ ያንን መጽሐፍ ሳነብ እንደጠፋ የሚያሳይ ነው።

ለዚህ ሰው ፣ የእግዚአብሔር መልዕክት በግልጥ ይታየው ጀምሯል፡፡

ከቆይታ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናደርገው ጉዞ፣ ቀልብ የሚቆጣጠረው የአንዱ እውነተኛ አምላክ ታሪክ እና መልዕክት በዚህ ታላቅ ታሪክ እንቆቅልሽ ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ጠጠሮችን ስናስገባ ግልጽ እየሆነ ይመጣል፡፡ ሌሎቹ “ቁርጥራጭ ነገሮች” የሚገቡበትን ስፍራ የምናውቀው መጽሐፍ ቅዱስን ለራሳችን ስናነብ ነው፡፡

## የፍቅር ደብዳቤዎች

አንዲት ወጣት ሴት ስለ ወደደ አንድ ወታደር የሚነገር ታሪክ አለ፡፡ ለእሷ ያለው ፍቅር ጥልቅ ቢሆንም ፣ እሷ ለእሱ ያላት ስሜት ግን ግልጽ አልነበረም፡፡ በጊዜውም ወታደሩ ወደ ሩቅ ቦታ ተላከ፡፡ በታማኝነትም ለልጅቷ ደብዳቤ የጻፈ ቢሆን እሷ ግን ምንም አልላከችለትም፡፡

በመጨረሻም የመመለሻው ቀን ደረሰ፡፡ ልክ እንደደረሰም የመጀመሪያ ስራው በጣም የሚወዳት ሴት መጎብኘት ነበር፡፡ ቤቷ አገኛት፡፡ ምንም እንኳን እሱን በማግኘቷ የተደሰቸ ለማስመሰል በትሞክርም ፣ አቧራ የለበሰው ሳጥን ግን ልቧ ያለበትን እውነተኛ ሁኔታ አሳየ፡፡

ሳጥኑ ከእሱ በተላኩ ያልተከፈቱ ደብዳቤዎች የተሞላ ነበር፡፡

## ከሰማይ ወደ ምድር

ቅዱሳት መጽሐፍት ከእግዚአብሔር የተላኩ ተከታታይ ደብዳቤዎች ናቸው፡፡ በጽሁፉ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ራሱን ለእናንተ እያስተዋወቀ፣ ፍቅሩን እየገለጠ እና በእሱ ዘላለማዊ ቤት ውስጥ በክብር እና በደስታ እንዴት እንደምትኖሩ እየነገራችሁ ነው፡፡

ከ2700 ዓመታት በፊት የላከው “ደብዳቤ” በከፊል እነሆ፦

> “እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፥ ወደ ውኃ ኑ፥ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ፡፡ ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፥ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? አድምጡኝ፥ በረከትንም ብሉ፥ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው፡፡ ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ፤ ስሙ ሰውነታችሁም

በሕይወት ትኖራለች፤ የታመነችይቱን የዳዊትን ምሕረት፥ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ። …ማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው።” (ኢሳያስ 55:1-3 ፣9)

በፍቅር፣
**ፈጣሪያችሁ**

የእሱን ደብዳቤ ከፍታችሁ ታውቃላችሁ? አንብባችሁስ ታውቃላችሁ? ምላሽስ ሰጥታችሁት ታውቃላችሁ?

ጉዞውን እንጀምር።



# ክፍል ፪
# ጉዞ


## ሚስጥሩን ማግኘት


8 እግዚአብሔር ምን ይመስላል
9 እሱን የሚመስል የለም
10 ልዩ ፍጥረት
11 የእኩይ መግባት
12 የኀጢአትና የሞት ሕግ
13 ምሕረትና ፍትሕ
14 እርግማን
15 ጥንድ ችግሮቻችን
16 የሴቷ ዘር
17 ማን ሊሆን ይችላል
18 የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ
19 የመሰዋዕት ሕግ
20 ቅጽበታዊ መሰዋዕት
21 ተጨማሪ ደም መፋሰስ
22 ጠቦቱ
23 የመጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜ
24 በሙሉ ተከፍሏል
25 ሞት ተሸነፈ
26 ሐይማኖተኛ እና ከእግዚአብሔር የራቀ



# 8

# እግዚአብሔር ምን ይመስላል



ጉዞውን የምንጀምረው እግዚአብሔር ከሚጀምርበት ቦታ በዘመናት መካከል ከተነገሩ ነገሮች መካከል ከታላቁ ነው።

"በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" (ዘፍጥረት 1:1)

የእግዚአብሔርን መኖር ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራ የለም። የታወቀ ነው።

ሰው በሌለበት የባህር ዳርቻ ላይ እየተጓዛቸሁ ፣ ትኩስ የእግር ዱካዎች አሸዋው ላይ ካያቸሁ ፣ በደመ ነፍስ ብቻቸሁ እንዳልሆናቸሁ እርግጠኛ መሆን ትቸላላቸሁ። እነዚህ ተራቸውን ጠብቀው የተቀመጡ ዱካዎች ራሳቸውን እንዳልፈጠሩ ታውቃላቸሁ። ንፋስና ውሃ እንዳላበጇቸው ታውቃላቸሁ። አንድ ሰው እነዚያን የእግር ዱካዎች ፈጥሯቸዋል።

ያንን ታውቃላቸሁ።

ነገር ግን በርካታ ሰዎች የእግር ዱካዎቹ ያረፉበት አሸዋ እና የእግር ዱካዎቹን ያበጀው የሰው ልጅ በሌላ አካል እንደተበጁ አያውቁም። ፍጥረትን ከፈጣሪው ውጪ ለማብራራት ሙከራ ሲያደርጉ ፣ በርካቶች የተንበረቀቁ ጽንሰ ሐሳቦችን አፈለቁ ፣ አንዳንዶች በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታትን ወደኋላ ሄደው የተያያዙ መንስኤዎችን በሐሳባቸው ፈጠሩ።

ነገር ግን "መጀመሪያ" የሚሏቸው ጋር ሲደርሱ ዋናውን "መንስዔው ማን ነው?" ለመመለስ አልተቃረቡም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ **ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤** ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤" (ሮሜ 1:19-20 አ.መ.ት)

ምክንያቱም ተራ ነው፦ ንድፍ ነዳፊ ያስፈልገዋል።

እንደ የእግር ዱካ ፣ መኪና እና ኮምፒውተር ያሉ ሰው ሰራሽ ነገሮች እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንደ ሀገር ፣ ሕዋስ እና ሰርዓተ ጠፈርም ያስፈልጋቸዋል። በጥሬ ዐይናችን አየነው፣ በማይክሮስኮፕ ወይም ቴሌስኮፕ አየነው፣ ልናስወግደው የማንችለው ወስብስብነት እና ውስብስብ የሆነ የጠፈር ስርዓት ፈጣሪ እና ደጋፊ ያስፈልገዋል።

የእግር ዱካ የእግር ዱካ ፈጣሪ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ፣ አጽናፈ ዓለሙም የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ ያስፈልገዋል።

> "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፡ የሰማይም ጠፈር ይእጁን *ሥራ* ያውጃሉ።" (መዝሙር 19:1አመት)

ይሄ የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ ማን ነው? ምን አይነት እንደሆነ ልናውቅ የምንችለው እንዴት ነው? ራሱን ስላሳወቀን ልናውቅ እንችላለን።[94]

## ዘላለማዊ

ቀደም ብለን ሸሙጥ በሚመስል መልኩ "እግዚአብሔርን የፈጠረው ማን ነው? ፈስቼዋልሁ" ካለን የኤሜይል መልዕክት ተቀብለን ነበር። ምላሹ፦ ማንም። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው። "በመጀመሪያ **እግዚአብሔር**" የሚለው ቃል ፈጣሪያችን እንደማንም እንደምንም እንዳልሆነ ይነግረናል።

> "ተራሮች ሳይወለዱ፥ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ።" (መዝሙር 90:2)

ያለፈ ጊዜ፣ አሁን እና ወደፊት ለእግዚአብሔር ተመሳሳይ ናቸው። እሱ "...የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ..." (ራዕይ 4:8)

በጊዜ የማይገደብና ልንረዳው የማንችለው ነው።

የትኛውም ፍጡር ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ሊያውቅ አይችልም። እሱ "ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ" (ኢሳያስ 57:15)

አይለወጥም። "አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።" (መዝሙር 102:27)

## ታላቅ

እግዚአብሔር ከምንገምተው ነገር ሁሉ በላይ ነው።

ዘላለማዊው አምላክ የታወቀ ስለሆነ ህልውናውን ለማረጋገጥ ምንም ሙከራ አያደርግም ስለዚህ ህልውናውን ለማብራራት ሙከራ አያደርግም ፣ ምክንያቱም ውሱን አዕምሮ ከጊዜ ፣ ከቦታ እና ከቁስ ውጪ ያለን ነገር ለመረዳት አቅም የላቸውም።

እንደ ትንሽ ልጅ ፣ ወደ ስማይ ተመልክቼ ወደላይ የምችለውን ርቀት ያህል ብጓዝ የአጽናፈ ዓለሙ መጨረሻ ላይ እደርሳለሁ ብዬ አስብ ነበር።

ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባሁት ግን እኔ ከፈጠሩከት መጨረሻ በተቃራኒ ያለውን ዓለም ነው!

አንዳንድ ነገሮችን ልንረዳ የምንችለው ፈጣሪ የገለጠልን በማመን ብቻ ነው።

በእውነተኛ እና የተረጋገጠው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለን እምነት ከፍተኛ ደረጃ ላለው ጥበብ እና ዕውቀት ቁልፍ ነው።

> "ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀረብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት።... ዐለት በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን ፤ ስልህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።"
> (ዕብራውያን 11:6፣3 አመት)

ዘመናዊ ሳይንስ "የሚታየው ከሚታየው እንዳልተፈጠረ" ያረጋግጣል። የፊዚክስ ሊቃውንት ቁስ የማይታዩ አተሞች ፣ ከማይታዩ ኤሌክትሮኖች እና ፕሮቶን እና ከኒውትሮን በተስራ ማዕከል ዙሪያ በሚሽከረከሩ እነሱ ደግሞ ከተለያዩ ቁሳቆሶች ...? የሰው ልጆች በርካታ ነገሮችን አግኝተናል፣ ነገር ግን ዕውቀታችን በጣም ጥቂት ነው። ጠቢብ የሆኑ ሰዎች የሰው ልጅን እውቀት ውሱንነት ያወቃሉ።

ሳይንስ ሊያፈርሰውም ሊያረጋግጠውም ያልቻለው ነገር “አጽናፈ ዓለሙ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተፈጠረ” የሚለውን ቃል ነው። ይህንን ልናውቅ የምንችለው እግዚአብሔር በሰጠን ስድስተኛ የስሜት ሕዋስ ፦ እምነት ነው።

የሕይወትን ታላላቅ ጭብጦችና ሚስጥሮች “**የምንረዳው** በእምነት ነው”። ለዚህም ምክንያቱ ግልጥ ነው፦

“እግዚአብሔር ከሰው ይበልጣል” (ኢዮብ 33:12)

ታላቁ አምላክ ስለራሱ የገለጠው ተጨማሪ ነገር ምንድን ነው?

## ገደብ የለሽ

እሱ ሁሉን ቻይ ነው። “አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ እነሆ፥ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋቸ ክንድህ ፈጥረሃል፥ ከአንተም የሚያቅት ነገር የለም።” (ኤርሚያስ 32:17 አ.መ.ት) ፈጣሪ ከፍጥረቱ የላቀ ነው። እሱ ከምናስበው ሁሉ በላይ እና ያለፈ ነው።

እሱ ሁሉን አዋቂ ነው። “አንተ መቀመጤንና መነሳቴን ታውቃለህ ፡ የልቤን ሐሳብ ገና በሩቁ ታስተውላለህ” (መዝሙር 139:2 አመት) ፈጣሪ ሁሉን ያለፈውን፣ የአሁኑን የወደፊቱን ያውቃል። በጊዜ ብዛትም ጠቢብ እየሆነ አይሄድም። “ጌታችን ታላቅ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ ለጥበቡም ቍጥር የለውም።” (መዝሙር 147:5)

እሱ በሁሉ ቦታ ይገኛል። “ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?” (መዝሙረ 139:7) በቦታ የማይወሰነው አምላክ ከእኔም ከእናንተም ጋር መሆን ይችላል። በሰማይ ከሚገኙ መላዕክት ጋር እየተነጋገረ በምድር ላይ ከሚገኙ የሰው ልጆች ጋር ይነጋገራል።

እሱ ገድብ የለውም።

## መንፈስ

ገደብ ሰሌለበት አምላክ በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ ልስጣቸሁ፦

“እግዚአብሔር መንፈስ ነው።” (ዮሐንስ 4:24)

እግዚአብሔር የማይታይ፣ የማይገደብ እና በአንድ ጊዜ

በሁሉም በታና እና ጊዜ መገኘት የሚችል ማንነት ያለው መንፈስ ነው። ምንም እንኳን ማንም ሰው ባያስፈልግም ራሱን በመረጠው መንገድ ለመግለጥ ነፃነት አለው። ቅዱሳት መጽሐፍት እግዚአብሔር ራሱን ለወንዶች እና ለሴቶች በበርካታ ጊዜያት በልዩ እና በሚታይ ሁኔታ "እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር።" (ዘጸአት 33:11) እንደገለጠ ይዘግባሉ።

የላቀ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ለዚህ ዓላማ በፈጠራቸው መንፈሳውያን ፍጡራን መታወቅ፣ መታመን እና መመለክ ይፈልጋል።

> "ነገርግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።" (ዮሐንስ 4:23-24)

## የመናፍስት አባት

የእግዚአብሔር አንደው መጠሪያ "የመናፍስት አባት" (ዕብራውያን 12:9) ነው።

ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት[95] በማይቆጠሩ ሚልዮኖች ያሉ ሳያላን፣ አስገራሚ የሆኑ መላዕክት ተብለው የሚጠሩ መንፈሳውያን ፍጡራን ፈጥሯል። የፈጠራቸውም በሰማያዊ ቤቱ አብረውት እንዲኖሩ ነው። መላዕክት ማለት መልዕክተኛ ወይም አገልጋይ ማለት ነው። ዘላለምን የሚካፈሉት በፍቅር የሚገዙለት ተገዢዎችን መንግስት ለማቋቋም ያቀደው እግዚአብሔረ እነዚህን መንፈሳውያን ፍጡራን ለዘላለም እንዲያውቁት፣ እንዲያመልኩት ፣ እንዲታዘዙት ፣ እንዲያገለግሉት እና ለዘላለም በእሱ ደስ እንዲሰኙ ፈጥሯቸዋል።

> "አየሁም፥ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፤" (ራዕይ 5:11)

ከመጀመሪያው መላዕክት ስለማይራቡ የፈለግውን ያህል በርካታ መላዕክትን ፈጥሯል። እነዚህ መናፍስት ከፈጣሪያቸው ጋር የተካፈሏቸው ጥቂት ባህርያት ቢኖሯቸውም በምንም አይነት

መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አይደሉም። እግዚአብሔር ከፍተኛ ደርጃ ያለው ዕውቀት ሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም ስሜት፣ ፍቃድ እና ከእሱ ጋር የመግባባት ፍቃድም ሰጥቷቸዋል። እንደ ፈጣሪያቸውም መታየት ለሚጠይቅ ተልዕኮ እስካልተላኩ ድረስ ለሰው ልጆች አይታዩም።[96]

መንፈሳውያን ፍጡራን በሚገኙበት የእሱ መንግስት ብቸኛው ያልተፈጠረ ፣ ገደብ የሌለበት፣ ሁሉን ቻይ ፣ ሁሉን አዋቂ እና ገደብ የሌለው መንፈስ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

## ከሁሉ በላይ

> "…በአንድ ተስፋ… አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ፤ **ከሁሉ በላይ የሚሆን** በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።" (ኤፌሶም 4:4-6)

ምንም እንኳን "ከሁሉ በላይ" የሆነው እሱ በጊዜ እና በቦታ የማይገደብ ቢሆንም በዚህ አጽናፈ ዓለም ውስጥ እሱ የሚገኝበት እና የሚነግስበት ቦታ አለ "እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።" (መዝሙር 103:19) የእግዚአብሔርን ቅርብነት እና ታላቅነት ሲያሰላስል ንጉስ ሰለሞን እንዲህ ሲል ጸለየ፦

> "በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፥ **ሰማይ ከሰማያትም** በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም…" (1 ነገስት 8:27)

እግዚአብሔር ሦስት የተለያዩ ሰማያት እንዳሉ ይናግራል። ሁለቱ ለሰው ልጆች የሚታዩ ሲሆን አንዱ ግን አይታይም።

ከባቢ አየራዊ ሰማይ የምንለው ቀና ብለን ሰናይ የምናየው የከባቢ አየር ሰማይ ነው።

ሥነ ፈለካዊ ሰማይ በለን የምንጠራው እግዚአብሔር ፕላኔቶቸን እና ከዋክብትን ያስቀመጠበት ሰማይ አለ።

ሌላኛው ሰማየ ሰማያት ብለን የምንጠራው በሩህ የሆነው እግዚአብሔር የሚኖርበት ሰማይ ነው። የፈጣሪያችን ሰማያዊ መኖሪያ እና የመላዕከት መኖሪያ የላይኛው ሰማይ፣ ሶስተኛው ሰማይ፣ የአብ ቤት፣ ማደሪያው ፣ መንግስተ ስማያት እና በቀላሉም ሰማይ ተብሎ ይጠራል።[97]

> “እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፤ የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ። ከማደሪያው ቦታ ሆኖ በምድር ወደሚኖሩ ሁሉ ተመለከተ፤እርሱ ብቻውን ልባቸውን የሠራ ሥራቸውንም ሁሉ የሚያስተውል።” (መዝሙር 33:13-15)

## እግዚአብሔር አንድ ነው

የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ ይናገራል፦ “በመጀመሪያም **እግዚአብሔር**።”

የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት “አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤” (ዘዳግም 6:4) “አምላክ አንድ ስለ ሆነ።” (ሮሜ 3:30)

እግዚአብሔር አንድ ነው።

ተወዳዳሪ የለውም። እኩያም የለውም።

በእነዚህ መርሆዎች ማመን ማለትም አንድ አምላክ እንዳለ ማመን አንድ አምላኪነት ይባላል። አንድ አምላኪነት ከብዙ አምላኪነት (በበርካታ ወንድ እና ሴት አማልክት ማመን) እና ሁሉ አምላክ አምላክ ሁሉ (አምላክ ሁሉን ነገር ነው ሁሉ ነገር አምላክ ነው) ከሚለው ጋር ግልጽ ተቃርኖ አለው። ብዙ አምላኪዎች እና ሁሉ አምላክ እና አምላኩ ሁሉ የሚሉ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ያለውን ልዩነት ያደበዝዛሉ። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ባህርይ ያለው አካል መሆኑን ይክዳሉ።

## ውስብስብ

“በመጀመሪያ እግዚእብሔር” ተራ እውነት ቢሆንም ተራ እውነት ግን አይደለም።

የማይገደበው አምላክ ቀላል አይደለም። እሱ ውስብስብ ነው። የእሱ አንድነት ባለብዙ ገጽታ አንድነት ነው።

የዕብራይስጡ “እግዚአብሔር” የሚለው ቃል የመጠሪያ ስም ኤሎሂም ባለ ብዙ ቁጥር ተባዕታይ ቃል ነው። የዕብራይስጥ ሰዋሰው ነጠላ(አንድ) ፣ ከአንድ የበለጠ (ሁለት ብቻ) እና ብዙ (ሦስትና ከዛ በላይ) አለው። ኤሎሂም ሰዋሰዋዊ ብዙ ሲሆን ነገር ግን የነጠላ ፍቺ አለው።

አንዱ እውነተኛ አምላክ ውስብስብ እና በችሎታውም የማይገደብ ነው። የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዲህ ይላል፦

> "በመጀመሪያ **እግዚአብሔር** ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ **የእግዚአብሔርም መንፈስ** በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር። **እግዚአብሔርም፦** ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ።" (ዘፍጥረት 1:1-3)

ስለዚህም የእግዚአብሔር መጽሐፍ የመክፈቻ ዐርፍተ ነገር የፍጥረት ስራውን እንዴት እንዳከናወነ ይነግረናል። ይህንን ያከናወነው በመንፈሱ እና በቃሉ ነው።

አንደኛ፣ የራሱ እግዚአብሔር መንፈስ ትዕዛዙን ለመፈጸም ከሰማይ ተልኮ ነበር። ርግብ በጎጆዋ ላይ እንደምታንጃብበው አዲስ በተፈጠረው ዓለም ላይ "**የእግዚአብሔር መንፈስ** ይረብብ ነበር"። "መንፍስ" ለሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የእብራይስጥ ቃል ሩአህ ሲሆን መንፈስ፣ ትንፋሽ ወይም ኃይልን ያሳይ ነበር። የ "እግዚአብሔር መንፈስ" የእግዝአብሔር የራሱ ብርታት ሰጪ መገኘት ነው።

> "**መንፈስህን** [ሩአህ]ትልካለህ ይፈጠራሉም፥ የምድርንም ፊት ታድሳለህ።" (መዝሙር 104:30)

በመቀጠልም ፣ እግዚአብሔር ተናገረ። በመጀመሪያው የዘፍጥረት ምዕራፍ አሥር ጊዜ "እግዚአብሔር አለ" ይላል። እግዚአብሔር ሲናገር ፣ ያዘዘው ነገር ይፈጸማል።

> "**በእግዚአብሔር ቃል** ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ **በአፉ እስትንፋስ** [ሯአህ]" (መዝሙር 33:6)

እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረው በቃሉ እና በመንፈሱ ነው።

## ተግባቦት ፈጣሪው

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በንግግር የመፍጠሩ እውነታ ስለ እግዚአብሔር ሌላ ነገር ያስተምረናል፦

እሱ ተግባቦት ይፈጥራል።

ፍጥረት ከመፈጠሩ በፊት ግንኙነት ነበር።

> "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" (ዮሐንስ 1:1-2)

ቃል የተሰኘው ቃል ከግሪኩ ሎጎስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም፦ የሐሳብ መግለጫ ማለት ነው፡፡[98] በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ሎጎስ የእግዚአብሔር የግል መጠሪያ ነው፡፡ እግዚአብሔር እና ቃሉ አንድ ናቸው፡፡

ሁሉ ነገር የተፈጠረው በቃል ነው፡፡

አግዚአብሔር ዓለምን በማስብ ብቻ ወደ ህልውና ማምጣት ይችል ነበር ፣ ዓለምም ስፍራውን ይዞ ይገኝና ይሰራም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን ይህንን አላደረገም፡፡ ሐሳቡን ገለጠ፡፡ ተናገረ፡፡

ቃል ቀደም ተከተላቸው በጠበቁ ስድስት ቀናት ውስጥ ዓለምን ወደ ሕልውና አመጣ፡፡

ሁሉን ቻዩ አምላክ ይህንን ለማከናወን ስድስት ቀናት ያስፈልጉት ነበር?

በፍጹም፣ በጊዜ የማይወሰነው ምንም አይነት ጊዜ አያስፈልገውም ነበር፡፡ ነገር ግን የእኛን ዓለም በዚህ መልኩ በመፍጠር እግዚአብሔር ሰባት ቀናትን የያዘ ሳምንት[99] መፍጠር ብቻ ሳይሆን ፣ ስለ ማንነቱና እና ስለ ጠባዩ ፍንጭ ሰጥቶናል፡፡ ይሄ ደግሞ የማይታወቅን አምላክ ማመን፣ መውደድ እና ማምለክ ስለማይቻል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

አሁን ደግሞ በፈጣሪ በራሱ የተዘገበውን ከፍጥረት ሂደት በመመልከት፣ በማዳመጥ እንማር፡፡

## 1ኛ ቀን፦ ብርሐን እና ጊዜ - እግዚአብሔር ቅዱስ ነው

> "እግዚአብሔርም፦ ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ፡፡ እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ፥ እግዚአብሔርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ፡፡ እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፥ ጨለማውንም ሌሊት አለው፡፡ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ አንድ ቀን፡፡" (ዘፍጥረት 1:3-5)

በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ብርሃንን ወደ ፍጥረት ትዕይንት አመጣ፡፡ መሬት የ24 ሰዓት ጡዘት እንድትፈጽም በማድረግ ቀንና ሌሊትን የሚለየው የሥነ ፈለክ ሰዓት በማሳለጥ ጊዜን ፈጠረ፡፡ ነገር ግን እስካሁን እግዚአብሔር ፀሐይን፣ ጨረቃ እና ከዋክብትን እስከ አራተኛ ቀን አልፈጠረም፡፡

ሳይንቲስቶች ጸሐይ ሳትፈጠር ብርሃን ነበር የሚለውን ሐሳብ ትክክል አይደለም በማለት የሚከራከሩበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሄ ጉዳይ

አክትሟል። ዛሬ በፍጥረት ዝርዝር የማያምኑ ሳይንቲስቶች ብርሃን እንኳን የምድር ጸሐይ ከመፈጠሯ በፊት ብቻውን እንደነበረ ያምናሉ።[100]

ፈጣሪ የምድርን ብርሃን ተሸካሚዎችን (4ኛ ቀን) ከመፍጠሩ በፊት ብርሃንን በመስጠት (1ኛ ቀን) የብርሃን ማለትም የአካላዊ እና መንፈሳዊ ብርሃን ምንጭ መሆኑን ማሳየቱ ነበር። ከእሱ ውጪ ያለው ጨለማ ብቻ ነው።

በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ጉዟችንን ስንቀጥል የብርሃን ምንጮቻችን ደጋግመን እናገኛለን፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ራሱ “ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤” (ራዕይ 22:5 አመት) የሚሆንበትን መንግሥተ ሰማያትን በመግለጥ ይጠናቀቃል።

ብሩህ አዕምሮ ላላቸው ሰዎች እንኳን ብርሃን ግልጽ አይደለም። የፊዚቅስ ሊቃውንት ስለሚሰራው ነገር ብዙ ያውቃሉ ፣ ስለምንነቱ የሚያውቁት ግን ጥቂት ነው። በሳይንስ በረሃን ፍጹማዊ ነው። በሰኮንድ ውስጥ 300,000 ኪሎ ሜትሮችን ይጓዛል። በፊዚክስ አልበርት አንስታይን E=mc2 ባገኘ ጊዜ አስፈሪው የአቶሚክ ኒኩሊየር ዘመን ጀመረ። ብርሃን በአካባቢው ተጽዕኖ አይደረግበትም። በሚሸት ቆሻሻ ላይ ሊያንጸባርቅ ይችላል ነገር ግን ብርሃኑ ንጹህ ነው። ብርሃን እና ጨለማ አብረው ሊኖሩ አይችሉም። ብርሃን ጨለማን ያባርረዋል።

እግዚአብሔር የብርሃን ምንጭ ነው ፣ የመጨረሻ ፍጹማዊውም እሱ ነው። በመገኘቱ ውስጥ ለመኖር ያልተዘጋጀ ሰው የሱ አስገራሚ ነጸብራቅ ለየትኛውም ሕያው ፍጡር አስፈሪ ነው።

እግዚአብሔር ንጹህ እና ቅዱስ ነው።

ቅዱስ የሚለው ቃል፦ የሚመስለው የሌለ፣ የተለየ ወይም ሌላ ማለት ነው። እሱን የሚመስለው የለም። የሚያንጸባርቀውን ዙፋኑን የከበቡ መላዕክት በተከታታይ “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ጌታ እግዚአብሔር” (ኢሳያስ 6:3) ሲሉ ይጮኻሉ። ቅድስና የእግዚአብሔር ባህርይ ሲሆን አጽንኦት ለመሰጠት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሶስት ጊዜያት ተጠቅሷልል። እሱ ቅዱስ “ሊቀረብ በማይቻል ብርሐን ውስጥ የሚኖር።” (1ጢሞቴዎስ 6:16)

እግዚአብሔር ከእኩዩ ጋር ሊኖር አይችልም። እሱ ብርሐንን ከጨለማ ይለያል። ንጽሐን የሆኑ ጻድቃን ብቻ ከእስ ጋር ይኖራሉ።

> “እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት። ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤” (1 ዮሐንስ 1፡5-6)

በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን እግዚአብሔር **ቅዱስ** እንደሆነ ይታወጃል።

## 2ኛ ቀን፦ አየር እና ውሃ - እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

> “እግዚአብሔርም፦ በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን፥ በውኃና በውኃ መካከልም ይክፈል አለ። እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ፥ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውኆች ለየ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ሁለተኛ ቀን።” (ዘፍጥረት 1:6-8)

ሁለተኛው የፍጥረት ቀን ሕይወት ያላቸው ፍጡራን ጥገኛ የሚሆኑባቸውን ሁለት ነገሮች ላይ ያተኩራል፦ አየርና ውሃ

ሰማያት የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ከራሳችን በላይ የሚገኘውን ሰማይ የሚያሳይ ሲሆን ደመና እና ከባቢ አየር የሚገኝበትን እና ከዋክብት የሚገኙበትን ቦታ ያሳያል። እስቲ እንደ ኦኦክሲጅን እና ናይትሮጂን ፣ የውሃ ተን እና ካርቦን ዳይኦክሳይድ ፣ ኦዞን እና ሌሎች ጋዞች በፍጹም ሚዛናዊ ቅንብር ያሉበትን ከባቢ አየር አስቡ። ይሄ ድብልቅ ከተቀየረ እንሞታለን። እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር።

ከላያችን በሚገኘው ከባቢ አየር ውስጥ የተንጠለጠለውን በትሪሊዮን ጋሎን የሚሆን ውሃ እስቲ አስቡት። በመናገር ብቻ ይህንን ከባድ ውስብስብ ድብልቅ ለመፍጠር እና ለማስቀመጥ ምን አይነት ጥበብና ኅይል እንደሚያስፈልግ አስቡ?

> “እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም።” (መዝሙር 33:9)

ልክ እንደ ሌላው የፍጥረት ቀን ሁለተኛው ቀን ፈጣሪያችን **ሁሉን ቻይ** መሆኑን ያስተምረናል።

## 3ኛ ቀን፦ ባህር፣ መሬት፣ እና ተክሎች - እግዚአብሔር መልካም ነው

> “እግዚአብሔርም፦ ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፥ የብሱም ይገለጥ አለ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውኃ መከማቸውንም ባሕር አለው፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም፦ ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ፤ እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።”
> (ዘፍጥረት 1:9-12)

በሦስተኛ ቀን እግዚአብሔር ምድርን ከባህር ለየ ፣ ተክሎችን በሙሉ እንዲሆኑ ተናገረ “እግዚአብሔርም እርሱ መልካም እንደሆነ አየ” በፕላኔታችን ውስጥ ትክክለኛ መጠን ያልወ ውሃ አሰቀመጠ። ከዚያ ቀን በኋላም መጠኑን መጨመር አላስፈለገውም።[101]

እግዚአብሔር እያንዳንዱ ተክል እና ዛፍ ዘር እንዲሰጥ እና አትክልትና ፍራፍሬ “እንደ ዝርያው” እንዲሰጥ ነደፈው። እግዚአብሔር ይሄንን ሁሉ ምግብ የፈጠረው ለምንድን ነው? የፈጠረው “እርሱም ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም፥ መኖሪያም ልትሆን” (ኢሳያስ 45:18) ስለፈለገ ነው። በስርዓተ ጸሐይ ውስጥ ምድር ልዩ ነች። ሕይወትን ለማስቀጠልና እና ለማበልጠግ የተዘጋጀች ፕላኔት ይህች ብቻ ነች።

እስቲ ለምሳሌ ከተክሎች የምናገኘውን ጥቅም አሰቡ፦ ወሳኝ ኦክሲጅን፣ የሚያበለጽጉ አትክለቶች ፣ የሚጣፍጡ ፍራ ፍሬዎች ፣ የምናርፍባቸው መጠለያዎች ፣ ጠቃሚ ጫካዎች፣ ጠቃሚ መድሐኒቶች ፣ ባለቀለም እና በላሸት አበባዎች ፣ የሚያማምሩ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጦች እና ከዚህም በላይ።

ስለ ምግብ ስናስብ እግዚአብሔር ልንመገባቸውን የምንችላቸው ጥቂት ነገሮች ማለትም ሙዝ፣ ባቄላ እና ሩዝ ብቻ መፍጠር ይችል ነበር። ሳይንቲስቶች እንደሚገምቱት ለምግብ እና ለመኖር የሚያገለግሉ ሁለት ሚሊዮን ዝርያዎች አሉ።

በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ እግዚአብሔር ፍጥረትን ሰባት ጊዜ “መልካም” ይለዋል። በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ

ውስጥ ሰባት ፈጹምነትን የሚያሳይ ቁጥር ነው። እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር በሙሉ ፍጹም መልካም ነው።

ለዚህም ምክንያቱ እሱ ፍጹም መልካም መሆኑ ነው።

> “…ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ…” (1ጢሞቴዎስ 6:17)

ሶስተኛው ቀን እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ ያስተምራናል።

## 4ኛ ቀን፦ የሰማይ ብርሃናት - እግዚኣብሔር ታማኝ ነው

> “እግዚአብሔርም አለ፦ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለዓመታትም ይሁኑ ፤ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን ፥ ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ።”
> (ዘፍጥረት 1:14-16)

አራተኛው ቀን የስርዓት አምላክን ያስየናል። እሱ “ፀሐይን በቀን የጨረቃንና የከዋክብትን ሥርዓት በሌሊት ብርሃን አድርጎ የሚሰጥ” (ኤርሚያስ 31:35 አመት) የሚያደርግ ነው።

በጨለማ በምድር እና በባህር ለሚጓዙ ሰዎች ስርዓቱን ጠብቆ የተቀምጡት ከዋከብት ተዓማኒ አቀጣጫ ጠቋሚ ይሆናሊ። በቀን ጸሐይ ቀናትን እና ዓመታትን ታሳያለች። ጨረቃ ወራትን እና ወቅቶችን ታመለክታለች።

ልክ እንደ ጸሐይና ከዋክብት የምድር ጨረቃ የፈጥራት ታማኝ እንደሆነ ምስክርነቷን ትሰጣለች። እግዝአብሔር ጨረቃን “ምስክርነቱ በሰማይ የታመን ነው።” (መዝሙር 89:37) ይላታል። ከምድር ከየትኛውም ቦታ ይህች ፕላኔት ምድር ካይ ብርሃኗን የምታበራ ሲሆን የጀርባዋን ክፍል አታሳያትም ልክ እንደ ሰዓት መዘውር ባለ ብቃት እና ትዞራለች ፣ ትሽከረከራለች።[102] ልክ እንደ ግድግዳ ሰዓት ጊዜዋን ጠብቃ ትደበዝዛለች፣ ትደምቃለች። ጨረቃ ታማኝ የሆነችው የፈጠራት አምላክ ታማኝ ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነ ሊያደርገው የማይችለው ነገር አለ። የራሱን ባህርይ ሊቃረን አይችልም የራሱንም ህግጋት ችላ ሊል

አይችልም፡፡ “ባናምነው፥ እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና፡፡ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል” (2ጢሞቴዎ 2:13፡ ዕብራውያን 6:18) ብዙ ሰዎች እግዚአብሒር “ታላቅ” አምላክ ስለሆነ ከባህርይው ተቃራኒ የሆነን ነገር ሊያደርግ ወይም ቃሉን ሊያጥፍ ይችላል ይላሉ፡፡ የእግዚአብሔር ታላቅነት ፍቺ ግን ይሄ አይደለም፡፡

ታማኝነት እንጂ ተለዋዋጭነት የእግዚአብሔር ባህርይ አይደለም፡፡ ልክ እንደ ፕላኔቶች እና ሰማያት ቋሚ ሥርዓት ፈጣሪያችን እና ደጋፊያችን ልንመካበት የምንችለው ነው፡፡

ልትታመኑበት ትችላላችሁ፡፡

> “በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ፡፡”
> (ያዕቆብ 1:17)

አራተኛው ቀን ፍጥረት ለእግዚአብሔር ታማኝነት ምስክር ነው፡፡

## 5ኛ ቀን - እግዚአብሔር ሕይወት ነው

በአምስተኛቀን፣በማይገደበውጥበቡእናሳይሉእግዚአብሔር ሁሉንም አይነት ፍጥረታት ባህርና ሰማይን እንዲሞሉ አዘዘ ፣ በተለየ አካባቢያቸው ላይ በበቂ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ዓሶች በውሃ ውስጥ በስንጥባቸው እና በክንፎቻቸው ፣ ወፎች በሰማይ ላይ በክንፎቻቸው እና በቀላል አጥንቶቻቸው አደረገ፡፡

> “እግዚአብሔርም አለ፦ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፡ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ፡፡ እግዚአብሔርም አለ፦ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፡ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ፡፡”
> (ዘፍጠረት 1:20-21 አመት)

የቃላት አቀማመጡን ተመልከቱ “ባህር በሕያዋን ፍጡራን ትሞላ” ትሙላ ማለት “መጨናነቅ፣ ጢም ማለት ማለት ነው፡፡ ማይክሮ ባዮሎጂስቶች አንድ የኩሬ ውሃ ጠብታ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕይወት ያላቸው ጥቃቅን ፍጥረታት ልትይዝ እንደምትችል ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም አንዳንዶቹ እንደ ግዙፉን እንስሳት በላይ ውስብስብ ናቸው፡፡ ከባህሮች መካከል ታላቁ ባህር በርካታ ዝርያ ያላቸው ፍጥረታት ፣ ፕላንክቶን የተሰኙትን ጥቃቅን

ተክሎች እና የሚንሳፈፉ እንስሳትን የሚመገበውን ሰማያዊ ዓሳነባሪ ይዟል።

ባህር የእግዚአብሔር ሕያው ተዓምራት ታላቅ ስብስብ ነው።

በሰማይ ላይ ስለሚበሩ ወፎች ዝርያም ተመሳሳይ ነገር ማለት ይቻላል።

"እንደ ዝርያቸው" የሚልውን ቃል ልብ በሉ። ይሄ ቃል በዘፍጠረት አንድ ብቻ አስር ጊዜ ተጠቅሷል፣ ይሄ የእያንዳንዱን የእንስሳት ዝርያ ቋሚነት የሚያሳይ ነው። የሕየወት ጀማሪ እያንዳንዱ የተክል ፍጥረት "እንደ ዝርያው" እንዲሆነ አዟል። የሰው ልጅ የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ ከዚህ የማይለዋወጥ የተፈጥሮ ሕግ ጋር ይጋጫል። ምንም እንኳን ልዩነቶችን፣ አነስተኛ ለውጦች እና ከአካባቢ ጋር መመሳሰል በእያንዳንዱ ሕያው ፍጡራን መካከል ቢኖርም የትኛውም በፈጣሪ ከተቀመጠው ገደብ አልፎ "ሊለወጥ" አይችልም። በቁፋሮ የተገኙ ቀሪተ አካላት ለዚህ ምስክር ናቸው።

ሕይወት ትብሎ የሚጠራው ኃይል ፈጣሪ ጸጋፊ እግዚእብሔር ብቻ ነው። ከእሱ ውጪ ያለው ሞት ነው።

> "ሁሉ በርሱ ሆነ፤ ከሆነውም አንድስንኳ ያለርሱ አልሆነም። **ሕይወት በእርሱ ነበረች**።" (ዮሐንስ 1:3-4)

በአምሰተኛው ቀን የተፈጠሩ ሕያው ፍጡራን ብዛት የሚያሳያን እግዚአብሔር ሕይወት እንደሆነ ነው።

## 6ኛ ቀን ፦ እንስሳት እና ሰው — እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

በስድስተኛው ቀን መጀመሪያ ፈጣሪ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ አስገራሚ አጥቢ፣ ተሳቢ እንስሳትንና እና ነፍሳትን ፈጠረ።

> "እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፥ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።" (ዘፍጥረት 1:25)

እግዚአብሔር ሁሉን ፈጠረ፣ አንዳንዶቹ ትልቅ አንዳንዶቹን ትንሽ፣ ለእያንዳንዱ ደግሞ ለመኖር እና ለተፈጥሯዊው ዓለም አሰተውጽኦ ለማበርከት የሚያስፈልጋቸውን ደመ ነፍሳዊ ዕውቀት በመስጠት። በራሳቸው መልክ ዘርያቸውን እንዲተኩ በማድረግ፣

ጨቀላቸውን እንዲንከባከቡ በማድረግ ፈጠራቸው።

እግዚአብሔር የእንስሳትን ዝርያ በፈጠረበት ጊዜ ሁሉ "መልካም ነበር"። ምንም እኩይ ወይም ደም መፋሰስ ወደ ትዕይንቱ ውስጥ አልገባም ነበር። እንስሳት የተፈጠሩት አትክልት እንዲበሉ ሆነው ነበር። "ለምድርም አራዊት ሁሉ፥ ለሰማይም ወፎች ሁሉ፥ ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችም ሁሉ የሚበቅለው ሐመልማል ሁሉ መብል ይሁንላቸው፤ እንዲሁም ሆነ።" (ዘፍጥረት 1:30) ፍጥረት ፍጥረትን የሚበላበት የተፈጠሮ ስርዓት አልነበረም። ጠላትነት እና ፍርሽት አይታወቅም ነበር።

የእግዚአብሔር መልካምነት በሁሉ ነገር ይታይ ነበር። አምበሳ ከጠቦት አጠገብ ይግጥ ነበር። ድመት እና ወፍ አብረው ያሳልፉ ነበር። ዓለም ፍጹም ሰላም የተሞላ ነበር።

እግዚእብሔር አንድ ጊዜ እንስሳትን ከፈጠረ በኋላ ዋናውን ፍጡሩን የመስሪያው ጊዜ ተቃርቦ ነበር ፦ ወንድና ሴት። እግዚአብሔር የሰው ልጆች በከበረው ፣ በሚያስደስተው ዘላለማዊ የፍቅር መንግስቱ ውስጥ በሙሉ ልባቸው ተገዢዎቹ እንዲሆኑ ዕቅድ ነበረው።

ለፈጣሪያችን፣ ፍቅር ከድርጊቱ በላይ ነው። ፍቅር ማንነቱ ነው።

> "እግዚአብሔር ፍቅር ነው።" (1ዮሐንስ 4:8)

የእግዚአብሔር የስድስተኛ ቀን የፈጠራ ተግባራት የሚያሳዩት እሱ ፍቅር እንደሆነ ነው።

## "እንፍጠር (እኛ)"

እግዚአብሔር ይህንን የሚያምር ዓለም የፈጠረው የፍቅሩ ማረፊያዎችና ተቀባዮች እንዲሆኑ ለሚፈጥራቸው ሰዎች ሲሆን ይህንን ያደረገውም ፍቅር ስለሆነ ነው። ስለዚህም በሰደስተኛው ቀን፦

> "እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካቸን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር..." (ዘፍጥረት 1:26)

አቁሙ! እስቲ ቆይ! ይሄ ነገር ምንድን ነው? እግዚአብሔር "ሰውን **በመልካችን** እንፍጠር" አለ?

እግዚአብሔር አንድ ከሆነ "እኛ" የተባለው ማን ነው ?

ይነጋገር የነበረውስ ከማን ጋር ነው?



# 9

# እሱን የሚመስል የለም

> “እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ፣ **ታላቅ አምላክ** ኃያልም የሚያስፈራም…” - ነብዩ ሙሴ (ዘዳግም 10:17)

**ማስጠንቀቂያ፦** የጉዟችን ቀጣይ ክፍል አንባቢያንን ከለመዱት ነገር ወጣ እንዲሉ የሚያደርግ ነው፡፡ አዕምሯችን ይለጠጣል፣ ልባችን ይመዘናል፡፡

## እግዚአብሔር መልካም ነው

ብዙዎቻችን በተፈጥሮ ሰለሱ ከምናስበው በላይ እግዚአብሔር ታላቅ ነው የሚለውን እምነት እንጋራለን፡፡

የእምነታችን እውነተኛነት ሊፈተን ነው፡፡

በስድስተኛው የፍጥረት ቀን እግዚአብሔር የእንሳስትን ዝርያ ከፈጠረ በኋላ እንዲህ አለ “እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር…” (ዘፍጥረት 1:26)

በሚቀጥለው ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ ወንድ እና ሴት እግዚአብሔርን መልክና ምሳሌ እንዴት እንዲያንጸባርቁ ተደርገው እንደተፈጠሩ እናያለን ፣ ነገር ግን ሌላ መመለስ ያለበት ጥያቄ አለ፡፡

እግዚአብሔር አንድ እንደ መሆኑ መጠን ለምን “**እንፍጠር**” አለ? ለምን “ሰውን **በመልኬ** እና **በምሳሌዬ** እፈጥራለሁ” ለምን አላለም? እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ራሱን እኛ ፣ የእኛ እና እኛ እያለ የሚጠቅቅሰው ለምንድን ነው? [103]

አንዳንዶች እግዚአብሔር “እኛ” “እንፍጠር” የሚለውን ቃል መጠቀሙ “የማዕረግ እኛ” ማለትም ንጉስ ስለራሱ ሲናገር “እኛ” እንደሚለው ነው በማለት ይሞግታሉ፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔር በኀይል እና በክብር ተወዳዳሪ የሌለው ቢሆንም፣ የዕብራውያን ሰዋሰው ለዚህ ጉዳይ የተጨበጠ ማብራሪያ አይሰጥም፡፡

ሌሎች ደግሞ ምንም እንኳን መላዕክት በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱ ባይሆንም እንዲሁም የሰው ልጅ በመልዐክት ምሳሌ ባይፈጠርም ፣ እግዚአብሔር “ሰውን መልካችን እንፍጠር” ሲል የተነጋገርው ከመላዕክት ጋር ነው ይላሉ፡፡

ቅዱሳት መጻህፍትን በቁማቸው በማንበብ እና ሰዋሰውን በጥልቀት በማጥናት በግልጽ የምናየው ፈጣሪያችን ራሱን በነጠላነት መልክ ራሱን በብዙ ቁጥር በመጥራት መግለጥ እንደፈለገ ነው፡፡

> በብዙ ቁጥር፦ “እግዚአብሔርም አለ በብዙ ቁጥር ‘ሰውን **በመልካችን እንደ ምሳሌአችን** እንፍጠር…’”
> በነጠላ ቁጥር፦ “በእግዚአብሔር **መልክ** ፈጠረው፤”
> (ዘፍጥረት 1:26-27)

እግዚአብሔር ራሱን በብዙነትም በነጠላነት መግለጡ ከአሁናዊ ማንነቱ እና ከሁልጊዜያዊ ማንነቱ ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

የእግዚአብሔር አንድነት ውስብስብነት እና ልክ በዙ ሰዎች ከሚሰጡት ግልብ የ “አንድነት” መግለጫ በላይ ነው፡፡ ልክ የሌው አንድነት በሰው የታሰበ የትኛውንም አይነት ምሳሌ የተከተለ አይደለም፡፡

እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው፡፡

> “ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ፡፡”
> (መዝሙር 90:2)

## የእግዚአብሔር ውስብስብ አንድነት

የእግዚአብሔር መጽሐፍ የሚጀምረው በሚከተሉት ቃላት ነው፦

“በመጀመሪያ **እግዚአብሔር** [ኤሎሂም—ባለብዙ ቁጥር ተባእት] ሰማይንና ምድርን ፈጠረ[ነጠላ ግስ]፡፡… **የእግዚአብሔርም መንፈስ** በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር፡፡ **እግዚአብሔርም፦** ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ፡፡”[104]

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በቃሉና በመንፈሱ ነው፡፡

> “በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።” (መዝሙር 33:6)

## የእሱ ቃል

ስለ ፈጣሪያቸው ውስብስብ ማንነት ለማጥናት ለሚፈልጉ ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍት በቂ የሆነ መረጃ ይሰጣሉ። ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል በሚከተሉት ቃላት ይጀምራል፦

> “በመጀመሪያው **ቃል** ነበረ፥
> ቃልም **በእግዚአብሔር ዘንድ** ነበረ፥
> ቃልም **እግዚአብሔር ነበረ**።
> በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።
> ሁሉ **በእርሱ** ሆነ፥” (ዮሐንስ 1:1-3)

በቀደመው ምዕራፍ ውስጥ እንደተመለከትነው ፣ ቃል የእግዚአብሔር ውስጣዊ ሐሳብ ውጪያዊ መገለጫ ነው። እናንተ ከሐሳባችሁ እና ከቃላችሁ ጋር አንድ እንደሆናችሁ ሁሉ እግዚአብሔርም ከቃሉ ጋር አንድ ነው። ቃል “በእግዚአብር ዘንድ” (ከእሱ የተለአየ) ነበረም “እግዚአብሔር ነበረ” (ከእሱ ጋር አንድ) ተብሎም የተገለጠው ለዚህ ነው።

ቃልን በተመለከተ “እሱ” እና “የእሱ” የሚሉ ተወላጠ ስሞች ጥቅም ላይ መዋላቸውን መመልከት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው።

## የእሱ መንፈስ

ጌታ እግዚአብሔር ቃሉን ልዩ እና አካላዊ በሆነ መንገድ እንደገለጠው ሁሉ መንፈሱንም በእኩል አካላዊ መንገድ ይገልጠዋል።

> “**መንፈስህን** ትልካለህ ይፈጠራሉም፥ የምድርንም ፊት ታድሳለህ።” (መዝሙር 104:30)

> “**በመንፈሱ** ሰማያት ውበትን አገኙ፥” (ኢዮብ 26:13)

> “**ከመንፈስህ** ወዴት እሄዳለሁ? **ከፊትህስ** ወዴት እሸሻለሁ?” (መዝሙር 139:7)

> “መንፈስ ቅዱስ ...**እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል**...” (ዮሐንስ 14:26)

ልክ እንደ ቃል (ፍጥረትን የተናገረው)፣ መንፈስ ቅዱስ (የቃልን ትዕዛዝ የፈጸመው) ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም አንድ ነው።

## እግዚአብሔር ታላቅ ነው

ብዙ አንድ አምላኪዎች በዚህ ከዳዊት የተጻፉ ጸሎቶች መካከል በተወሰደው በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ፦ "አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ እንደ አንተ ያለ የለምና፥ በጆሮአችንም እንደ ሰማን ሁሉ ከአንተ በቀር አምላክ የለምና አንተ ታላቅ ነህ።" (2 ሳሙኤል 7:22)

"እግዚአብሔር ታላቅ ነው! እግዚአብሔር አምላክ ነው አምሳያ የለውም !" ለማለት የሚፈጡን በርካቶች እግዚአብሔር ራሱ የገለጠውን የብዙነትና ነገር ግን የነጠላነቱን ምስጢር ላለመቀበል የዚያኑ ያህል ፈጣን ናቸው።

"አምሳያ የለውም!" ካለን ሁሉን ቻዩ አምላክ ራሱን ሰው በተፈጥሮ ከሚገምተው በላይ በታላቅነት እና የበለጠ ወሰብስብ በሆነ በመግለጡ ሊደናገጥ አይገባም።

> "እኔ እንደ አንተ እሆን ዘንድ ጠረጠርህ፤ እዘልፍሃለሁ በፊትህም እቆማለሁ።" (መዝሙር 50:21)

## እግዚአብሔር አንድ ነው።

አክራሪ አይሁዳውያን የዕብራውያን ሼማ የሚባለው ጸሎት በየዕለቱ ይደግማሉ፣ እሱም "አዶናይ ኤሎሄኑ ፣ አዶናይ **ኤኻድ**" የሚል ሲሆን ፍቺውም "ጌታ አምላካችን፣ እሱ **አንድ** ነው" ይሄ ጽሎት የተወሰደው ከቶራ ውስጥ ው፡ - "እስራኤል[ሽማ] ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን [ያህዌ] እግዚአብሔር አንድ [ኤኻድ] እግዚአብሔር ነው" (ዘዳግም 6:4)

የእግዚአብሔርን አንድነት ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋለው የዕብራይስጥ ቃል ኤኻድ ነው። ይሄ ቃል በዚ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ብዝኸነት ያለው አንድነትን ለማሳየት ነው ፣ ለምሳሌ የወይን ፍሬ አይነት የብዛት አንድነትን ለመግለጥ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ቦታ ኤኻድ አዛዥንና ወታደሮቹን ለመግለጥ "እንደ ኤኻድ" ተተርጉሟል።[105] በሚቀጥለው ምዕራፍ ይሄ ቃል የመጀመሪያው ወንድ ሴት **አንድ** ኤኻድ ማለትም "**አንድ** *ሥጋ*" (ዘፍጥረት 2:24) ሲሆኑ ዳግመኛ ይመጣል። ሌሎች ይሄ የዕብራይስጥ ቃል ጥቅም ላይ የዋለባቸውን ቦታዎች በመመልከት እግዚአብሔር የራሱን አንድነት ለመግለጥ ጥቅም ላይ ያዋለው ከአንድ በላይ አካላትን ያካተተ ነው።

ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር የብዝኸነት አንድነት የሚያመላክቱ እና የሚያረጋግጡ በርካታ ምንባባትን ይዟል።[106] አንድ ምሳሌ እነሆ፦

> “ከሆነበት ዘመን ጀምሮ **እኔ** በዚያ ነበርሁ፥ አሁንም **ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ** ልከውኛል።” (ኢሳያስ 48:16)

“ጌታ እግዚአብሔር” ማን ነው?

“መንፈሱ” ማን ነው?

ከመጀመሪያ የነበርኩት “እኔ” የተባለው እና “ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል” ያለው ማን ነው?

ቅዱሳት መጽሐፍትን ስንመረምር እነዚህ ጥያቄዎች ይመለሳሉ።

## የምንስማማባቸው ስሉስ አሐዱነቶች

አንድ የምንለው የአማርኛ ቃል የመጣው ከግዕዙ አሐዱ ነው ፍቺ አንድማለት ነው። ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ አሐዱ ስሉስነት ቢክዱም የዕለት ከዕለት ሕይወታችን ውስጥ የሚገኙ ሶስትነት በአንድነት ግን አይክዱም።

ለምሳሌ ጊዜ የአላፊ ፣ የአሁን እና የወደፊት **ጊዜ** በሶስትነት አንድነት ነገር አለው።

**ቦታ** ቁመት፣ ርዝመት እና ሰፋትን ያካትታል።

**ሰው** የመንፈስ፣ ነፍስ እናሥጋ ውጤት ነው።

**አንድ ሰው** አባት ፣ ልጅ እና ባል ሊሆን ይችላል።

**ፀሐይ** እራሷ በሦስትነት አንድነት ነች። ምንም እንኳን ምድር አንድ **ፀሐይ** ቢኖራትም ነገር ግን ሰማያዊ አካል የሆነችው **ፀሐይ**፣ ብርሃን የምትሰጠው ፀሐይና ሙቀት የምትሰጠው **ፀሐይ** ናቸው።

ይሄ ታዲያ ሦስት ፀሐዮች ያደረጋቸዋለን? በፍጹም። ፀሐይ አንድ እንጂ ሦስት አይደለችም። በፀሐይ አንድነት እና ሦስትነት መካከል ግጭት የለም፣ እግዚአብሔርም እንደዚያው ነው። ከጸሐይ ብርሐን እና ሙቀት እንደሚመነጩ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ከእግዚአብሔር ይመነጫሉ። ነገር ግን ጸሐይ እንደሆነችው ሁሉ እነሱም አንድ ናቸው።

እርግጡን ለመናገር ምድራዊ የሆኑ ምሳሌዎች ሁሉ የአንዱን አምላክ እግዚአብሄርን ወስብስብነት ለመግለጥ አቅም

ያንሳቸዋል። ከጸሐይ በተለየ መልኩ እርሱ አፍቃሪ፣ አካላዊ፣ እና ሊታወቅ የሚችል አካል ነው። ብዙኸን ስሉስ አሐዱነት በፍጥረተት ውስጥ እንዳለ ካመኑና ብዙኸን ፈጣሪ ከፍጥረት በላይ ምጡቅ እንደሆነ የሚስማሙ ከሆነ ምሳሌዎቹ ወደ ጋራ ነጥብ ይመሩናል።

> "ቤትን የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው መጠን፣ እንዲሁ እርሱ ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተቆጥሮአልና።" (ዕብራውያን 3:3-4)

የእግዚአብሔር ፍጥረት በውስብስብ አንድነት የተሞላ ከሆነ ፣ እግዚአብሔር ራሱ ውስብስብ አንድ መሆኑ ሊያስገርመን ይገባል? በሳይንሳዊ ዕውቀታችን በሙሉ የምንኖርበትን ዓለም ሙሉ በሙሉ ማብራራት ካልቻልን የፈጠረውን ለማብራራት ደግሞ ምን ያህል አንችል ይሆን?

እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው።

> **"የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?ከሰማይ** ይልቅ ከፍ ይላል፤ **ምን ልታደርግ ትችላለህ?** ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ **ምን ልታውቅ ትችላለህ?** ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፣ ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል።" (ኢዮብ 11:7-9)

"የእግዚአብሔርን ምስጢራት" ስንመረምር አስገራሚ የሆኑትን የዘላለማዊ ባህርዩን ጠባያት ለማግኘት እና ለመለማመድ እንታደላለን፦

> **"እግዚአብሔር ፍቅር ነው።"** (1ዮሐንስ 4:8)

## እግዚአብሔር የወደደው ማንን ነው?

የእግዚአብሔር ፍቅር መረዳት ከምንችለው በላይ የሆነ ከአባታዊ ልቡ የመነጨ ጥልቅ እና ራሱን በተግባራዊ መንገድ የሚገልጥ ፍቅር ነው።[107] እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ፍቅሩ በተፈቃሪው ተፈቃሪነት ላይ የተመሰረተ አይደለም።

"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤ እንዲሁም ነን።"
(1ዮሐንስ 3:1አመት)

ልናስብበት የሚገባን አንድ ነገር እነሆ። ፍቅር ተቀባይ ይፈልጋል። "እወዳለሁ" ብቻ ማለት አልችለም። ነገር ግን "ባለቤቴን እወደላሁ፣ ልጆቼን እወዳለሁ፣ ባልንጀሮቼን እወዳለሁ" ወዘተ ማለት እችላለሁ።

ፍቅር ተፈቃሪን ይፈልጋል።

እግዚአብሔር የፍቅሩ ተቀባይ አድርጎ ሕያዋን ፍጡራንን ከመፍጠሩ በፊት **እግዚአብሔር ይወደው የነበረው ማንን ነው**? መላዕክትን እና የሰው ልጆችን መፍጠር ያስፈልገው ነበር? በፍጹም አምላካቸን በራሱ ሙሉ ነው። እሱ መናፍስታዊ አካላትን እና የሰው ልጆችን ስላስፈለጉት ሳይሆን ሰለ ፈለጋቸው ነው። ልዩነቱ ግልጽ ነው።

ቀደም ብለን እንደተማርነው፦ **እግዚአብሔር ይናገራል**።

ንግግር ትርጉም ባለው መንገድ ሊኖር የሚችለው በግንኙነት ዐውድ ውስ ጥ ነው። መላዕክትን እና የሰው ልጆችን ከመፍጠሩ በፊት **ከማን ጋር ተነጋገረ**? ንግግሩን እንዲረዱት ሌሎች ፍጡራንን መፍጠር አሰፈልጎት ነበር? በፍጹም፣ እግዚአብሔር "የሚያስፈልገው" ሁሉ በእሱ ውስጥ አለ። ምንም አይፈልግም። እግዚአብሔር በራሱ ሙሉ እና የተሟላ ነው። ነገር ግን ለመናገር እና ለማናገር ፣ ለመውደድ እና ለመወደድ መፈለግ የባህርይው አካል ነው።

ይሄ ወደ ሌላ እውነት ይመራናል፦ **እግዚአብሔር ተግባቦታዊ ነው**።

ፍቅርና ንግግር ትርጉም ባለው መልኩ የሚኖሩት በግንኙነት አውድ ውስጥ ነው። ሌሎች አካላትን ከመፍጠሩ በፊት ይህንን ግንኙነት በማድረግ ይደሰት የነበረው ከማን ጋር ነው?

መልሱ በእግዚአብሔር ውስብስብ አንድነት ውስጥ ነው።

በዘላለም ውስጥ መላዕክትን ወይም ሰውን ከመፍጠሩ በፊት ተግባቦታዊ የሆነው አምላካችን የሚያረካና ጥልቅ የፍቅር ግንኙነት ከራሱ ጋር ነበረው ፣ ይኸውም ከራሱ ቃልና መንፈስ ጋር ነበር።

## ሸፋኖቹን መላጥ

ለዚህ አይነት ስለ ብዝኸነት፣ የእግዚአብሔር አካላዊ ባህርይ ያሉ ጥልቅ ሐሳቦችን በተመለከተ አንድ እንዲህ የሚል ኢሜይል ጽፎልኝ ነበር፦

ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

> እግዚአብሒረ ነብያትን የላከው እሱ አንድና ብቸኛ እንደሆነ ሊግረን ነው። ስለዚህ ለምን ቃሉን ስምታችሁ አተቀበሉም? እያንዳንዱን ሽፉን መላጥ እና ሁሉንም አንድ ማድረግ ስትችሉ እያንዳንዱን መለየት ያስፈልጋል?

ምንም እንኳን ስለምጡቁ ፈጣሪያችን ልንረዳው የሚገባንን ሁሉ ማወቅ የማይቻል መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም እግዚአብሔር በነብያቱ ሥነ ጽሁፋት በኩል የገለጠውን ለመረዳት መፈለግ አያስፈልገንም? ስለ እግዚአብሔር ማሰቡ ካስፈለገን ትክክለኛውን ነገር ማሰብ አይገባንም፡፡

ብዙዎቻችን እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ እንምናለን ታዲያ ይሄ አንድ አምላክ ስለ ራሱ የገለጠው ምንድን ነው? “እያንዳንዱን ሽፋን ስንልጥ” በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ስለሱ የምናገኘው ነገር ምንድን ነው?

አካላዊ ፣ ሊታወቅ የሚችል እና ታማኝ ከቃሉና ከመንፈሱ ጋረ አንድ የሆነ አምላክ እናገኛለን፤

ምጡቅ በሆነው ታላቅነቱ እግዚአብሔር ራሱ እንደ **አብ**፣ ቃሉን ደግሞ እንደ **ወልድ** ፣ መንፈሱን ደግሞ እንደ **መንፈስ ቅዱስ** ገልጧል፡፡ በአንዱ እውነተኛ አምላክ ውስጥ የሚገኙ አካላዊ ልዩነቶች እነዚህ ናቸው፡፡

ይህንን እውነት “የሚልጡልን” ጥቂት ምንባባትን እንመልከት፡፡

## የእግዚአብሔር ልጅ

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ቃል የእግዚአብሔር አንድ እና ብቸኛ ልጅ ተብሏል፡፡

> “በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም **በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ**፥ ቃልም **እግዚአብሔር ነበረ**፡፡ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ **በአባቱ እቅፍ ያለው አምላክ እርሱ ተረከው**፡፡ በእርሱ በሚያምን

> አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።"
> (ዮሐን ስ1:1 ፣ 18፣ 3:18 አመት)

በሴኔጋል ሰዎች "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለውን ቃል ሲሰሙ "አስተፍሩላህ!" በማለት ምላሽ ይሰጣሉ። ይሄ የዐረብኛ አባባል የሚከተለውን ሐሳብ የያዘ ው፦ "እንዲህ አይነት የስድብ ቃል ስለተናገርክ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ!" (የስድብ ቃል "እግዚአብሔር ላይ መቀለድ" ተብሎ ሊፈታ ይችላል።) አንዳንድ ጊዜ ለዚህ ተገሳጽ የራሳቸውን አባባል በመጥቀስ ምላሽ እሰጣለሁ፦ "እረኛው አፉ ላይ በጥፊ ከመምታትህ በፊት፣ ስለምን እንደሚያንራጉር ጠይቀው" ይስቃሉ ፣ በመቀጠልም እንዲህ አላቸዋለሁ "'የእግዚአብሔር ልጅ' የሚለውና ቃል ከመቃወማችሁ በፊት ስለእሱ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ማወቅ ያስፈልጋችኋል።"

ቅዱሳት መጽሐፍት የእግዚአብሔርን "ልጅ" በቀጥታ የሚጠቅሱ ከመቶ የበለጡ ጥቅሶችን ይዘዋል፣ ነገር ግን እንዚህ ጥቅሶቹ "ከአንድ በላይ አምላክ" አለ አይሉም ወይም ደግሞ አንዳንዶች ቃሉን እንደሚፈቱት እግዚእብሔር "ሚስት አግብቶ ልጅ ወለደ አይሉም"፤ እንዲህ አይነት ሐሳብ ስድብ ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ቅዱሳት መጽሐፍት ያለንን ግልብ እውቀት የሚያሳይ ነው።[108]
እግዚአብሔር የእሱን ሐሳብ እንድናስብ ይፈልጋል።

> "ሰማይ ከምድር **ከፍ** እንደሚል፣ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ **ከፍ** ያለ ነው።"
> (ኢሳያስ55:9)

ከበርካታ ዓመታት በፊት ታዋቂ ሴኔጋላዊ ነጋዴ በመኪና አደጋ ተገድሎ ነበር። የሴኔጋል ብሔራዊ ጋዜጣ ይሄ ሰው የቀጠራቸው ሰራተኞች "እንደ ራሱ ልጆች" ናቸው ብሎ ነበር። በተጨማሪም "የሴኔጋል ታላቅ ልጅ"[109] ሲል ሐዘኑን ገልጦ ነበር። ይሄ ማለት ሴኔጋል የምትባለው ሐገር ከወንድ ጋር ግንኙነት አድርጋ ልጅ ወልዳለች ማለት ነው። በፍጹም አይደለም! የሴኔጋል ሰዎች ይሄን ተወዳጅ ዜጋቸውን ይህንን መጠሪያ በመስጠት ለማክበር ችግር የለባቸውም። "የሴኔጋል ልጅ" የሚለው ቃል ያለውን ትርጉም ይገባቸዋል። ምን አይነት ትርጉም ሊሰጠው እንደማይገባም ያውቃሉ።

ልጅ የሚለው ቃል በበርካታ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ዐረቦች እርቆ የሚጓዝን ሰው "የመንገድ ልጅ" (ኢብን አል ሳቢል (ሱራ2:177 ፤ 215)] ፣ ምን ማለታቸው እንደሆነ ይገባናል፡፡ ሁሉን ቻዩ አምላክ ቃሉን ልጁ ብሎ ሲጠራ እሱም ምን እያለ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡

ፈጣሪያችን የሚያከብራቸውን ማዕረጎች እና መጠሪያዎች ላይ ልንቀልድ አይገባም፡፡

> "ከጥንት ጀምሮ **እግዚአብሔር** በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት **በልጁ** በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ **ተናገረን**፤እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ **ቃል** እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፤" (ዕብራውያን 1:1-3)

እግዚአብሔር "**በልጁ** በኩል እንደተናገረን" ልናውቅ ይፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ደግሞ በሰማይና በምድር ያሉ ነገሮች የተፈጠሩበት እና የጸኑበት ቃሉ ልጁ እንደሆነ ልንረዳ ይፈልጋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የዐረብኛ ትርጉም "የእግዚአብሔር ቃል" የተሰኘው የልጁ መጠሪያ "ኪልመት አላህ" ተብሎ ተተርጉሟል፣ ይህንን መጠሪያ በጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቁርዓን የሚሰጡት ለመሲሁ ነው፡፡ ወደኋላ ላየ በጉዟችን ይህንን በቅርበት እንመለከተዋለን፡፡

## የእግዚአብሔር መንፈስ

እግዚአብሔር ቃል ከሆነው ልጁ ጋር አንድ እንደሆነ ከቅዱሱ መንፈሱ ጋርም አንድ ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ ዓለምን በመፍጠር ሂደት እና በእግዚአብሔር ቃል የመጻፍ ሂደት ተሳታፊ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ሁለተኛ ጥቅስ እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረ ጊዜ "**የእግዚአብሔር መንፈስ** በውሃ ላይ ይረብብ ነበር፡፡" በስተኋላ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡" (2ጴጥሮስ 1:21 አመት)

አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ መልዐኩ ገብርኤል ነው እያሉ

ያስተምራሉ። ሌሎች ግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ነብይ እንደሆነ ራሳቸውን አሳምነዋል። መላዕክትና ሰዎች የተፈሩ አካላት ናቸው። መንፈስ ያልተፈጠረ “የዘላለም መንፈስ” (ዕብራውያን 9:14)[110]

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዓላማውን በዓለም ላይ የሚፈጽምበት “የእውነት መንፈስ” (ዮሐንስ 14:17) ነው። እሱ እግዚአብሔርን በቅርብ እና ልምምዳዊ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለሚያምኑ ሰዎች የሚገልጥ “ረዳት” (ዮሐንስ 14:16) ነው። በምድር ላይ የሚገኙ በርካታ ሰዎች እግዚአብሔርን ሳያውቁ ስለ እግዚአብሔር ያውቃሉ። እንዲህ አይነት ዕውቀት እግዚአብሔርን ይሕም ሰውን አያረካም። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙት እንዲረኩ የሚያስችለው መንፈስ ቅዱስ ነው። በሰተኋላም ስለ እግዚአብሔር አስደናቂ መንፈስ የበለጠ እንማራለን።[111]

ጉዘው እናንተ እያደረጋቸሁ ነው? ትንሽ ያስገርማል አይደል? ሐሳቦቹን በቀላሉ ለመረዳት ይከብዳል አይደል። አንዳንድ ሰዎች ሐይማኖታቸው እና ስለ እግዚአብሔር የሚሰጡት “ፍቺ በጣም ቀላል ከመሆኑ የተነሳ” እውነት ነው ብለው ያምናሉ። ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ፍቺ ቀላል ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ቀላል አይደለም።

> “እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፤”
>
> (ኢሳያስ 55:8)

## ለዘላለም አንድ

መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው። በዘላለም ውስጥ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያልነበሩበት ጊዜ የለም።[112] ሁሉ ጊዜ አንድ ናቸው። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ቅዱሳት መጽሐፍት ከሰማይ የሚናገረውን አብ ሲሉት ፣ በምድር ላይ የሚናገረው ወልድ ነው፣ ለልብ የሚናገረው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው።[113] ሁሉም በሥራቸው የተለያዩ ቢሆኑም ፣ ነገር ግን አንድ ናቸው።

ሰዎች እግዚአብሔር ራሱን ስለ ገለጠበት መንገድ ያላቸው ዕውቀት እያደገ ሲመጣ ፍቅር ስለሆነው እና የማያልቀውን ፍቅሩን በተግባራዊ መንገድ በሚያሳየው በሱ ባለጠግነት ደስ ይሰኛሉ።

ፍቅር ትርጉም ባለው መንገድ ሊኖር የሚችለው በግንኙነት አውድ ውስጥ ነው። አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በፍጹም ፍቅር እና አንድነት ያው ፍጹምነት ባለው ግንኙነት እርስ በርስ ደስ ይሰኛሉ። በሌላ ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወልድ "አባቴን **እወደዋለሁ**።" ይላል በተጨማሪ "አባት ልጁን **ይወዳል**" ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ቦታ "የመንፈስ ፍሬ **ፍቅር** ነው" ይላል። (ዮሐንስ 5:20 ፤ 14:31 ፡ ገላትያ 5:22)

በባልና ሚስት መካከል ያለ አንድነት ፤ በአባት ፤ በእናት እና በልጅ መካከል ያለ ግንኙነት ምርጡ የሰው ልጅ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ የሚፈልቅ ነው። እንዲህ አይነት ምድራዊ ግንኙነቶች ምንም ያህል የተሟሉ ቢሆኑ የአስገራሚው የእግዚአብሔር አንድነት እና ፍቅር ደካማ ነጸብራቆች ናቸው።

"እግዚአብሔር ፍቅር ነው።" (1ዮሐንስ 4:8)

"እግዚአብሔር ፍቅር ነው።" የሚለው ቃል ልዩ ነገር እኔን እና እናንተን ከእሱ ጋር ለዘላለም ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖረን መጋበዙ ነው! ሙሉ በሙሉ ሊብራራ ባይችልም መታመናችንን ይፈልጋል።

## እግዚአብሔር ታማኝ ነው

በስድስት የፍጥረት ቀናት ስለ እግዚአብሔር ያስተዋልነውን አስቡ። ልክ እንደ ሂሳብ ቀመር የሚከተለውን ይመስላል፦

ቀን 1 ፦ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው
\+ ቀን 2:- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው
\+ ቀን 3፦ እግዚአብሔር መልካም ነው
\+ቀን 4 ፦ እግዚአብሔር ታማኝ ነው
\+ ቀን 5:- እግዚአብሔር ሕይወት ነው
\+ ቀን 6፦ እግዚአብሔር ፍቅር ነው

= የሚታመን አምላክ

እነዚን ጠባያት የማያሟሉ ሰዎችን ማመናችን ነገር ግን እነዚህን ጠባያት በፍጽምና የሚያሳየውን እሱን አለማመናችን እንግዳ አይደል?

ደብዳቤ በፖስታ ሳጥን ውስጥ ሳስቀምጥ ፖስታ ቤቱ ደብዳቤውን እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ። የዚህ ዓለም

ፈጣሪ-አጽኚ-ባልቤት የሆነውን ቃሉን ምን ያህል የበለጠ ላምነው መቻል ይኖርብኝ ይሆን!

> “የሰውን ምስክር ብንቀበል **የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል**፤ ...በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው፤ በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል፡፡” (1 ዮሐንስ 5: 9-10)

## የእግዚአብሔር የግል መጠሪያ ስ ም

እግዚአብሔር እንድናውቅ ፣ እንድምነው እና ስሙን እንድንጠራ ይፈልጋል፡፡

> “**ስምህን የሚያውቁ** ሁሉ በአንተ[ጌታ] ይታመናሉ፤ አቤቱ፤ የሚሹህን አትተዋቸውምና፡፡” (መዝሙር 9:10)

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ስም እግዚአብሔር ወይም ኤሎሒም (ዕብራይስጥ) ወይም አላህ (አረብኛ[114]) ወይም ዴኡ (ፈረንሳይኛ) ወይም ዲዮስ (ስፓኒሽ) ወይም ጎት (ጀርመንኛ) ወይም በሚናገሩት ቋንቋ የተሰጠው የመጠሪያ ስም ይመስላቸዋል፡፡

በእርግጥም እግዚአብሔር እግዚአብሔር (ታላቁ አካል) ነው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የሱ ስም ነው? ይሄም ማለት እኔ ራሴን ሰው ብዬ እንደመጥራት አይሆን ም? እኔ ሰው ነኝ ፣ ነገር ግን የግል የመጠሪያ ስም አለኝ፡፡ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው ነገር ግን ራሱን የገለጠበትና እንደ አካል እንድንጠራው የሚፈልግበት ራሱን የገለጠበት ስም አለው፡፡

በርካቶች እግዚአብሔር የማይታወቅ የኅይል ምንጭ እንደ የመሬት ስበት እና ንፋስ ያለ ነገር አድርገው ወይም በዝነኛ የሳይንስ ልቦለድ ፊልሞች ውስጥ የተገለጠ “ኅይል” አድርገው ይገምቱታል፡፡ ይሄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት አይደለም፡፡

እግዚአብሔር በግላዊ መንገድ እንድናውቀው የሚፈልግ ታላቅ አካል ነው፡፡

እግዚአብሔር አካላዊነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ ሳይሆን ምክንያታዊም ጭምር ነው፡፡ የሰው የዓጽናፈ ዓለሙ ኅይል ኳሶች አይደሉም ፣ ሁሉን የፈጠረውም እንዲዚያ አይደለም፡፡ የግል መጠሪያ ስም ያለው አካላዊ ነው፡፡

የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ስስም በዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጧል፡፡

> “እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን ባደረገ ቀን፥
> በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው።”
> (ዘፍጥረት 2:4)

እግዚአብሔር ራሱን የሚጠራትን ስም ልብ አላችሁ?

መጠሪያ ስሙ “ጌታ” ነው። በትንሹ ወደ አማርኛ የተተረጎው እንዲህ ነው። እግዚአብሔር ሁሉኑም ቋንቋ በብቃት ስለሙቻሉ እና በአንድ የተለየ ቋንቋ ብቻ እንደናናግረው ባለመፈለጉ እናመሰግናለን። እሱ በአፍ መፍቻ ቋንቋችን በየትኛውም ጊዜ፣ በየትኛውም ቦታ ፣ በየትኛውም አቀጣጫ እየተመለከትን እንድንናገር ይጋብዘናል

## እኔ

በዕብራይስጥ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ የግል መጠሪያ ስም “ጌታ” በአራት ተነባቢዎች ይጻፋል፦ የሐወሐ። አናባቢዎች ሲጨመሩበት **ያህዌህ** ተብሎ ይነበባል። ይህም ከዕብራይስጥ የመሆን ግስ የተወሰደ ሲሆን ቀጥተኛ ፍቺውም “**እኔ**” ወይም “**እሱ**” ማለት ነው። ይሄም የሚያሰተምረን እግዚአብሔር በራሱ ኗሪ ዘላለማዊ መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር የግል መጠሪያ በብሉይ ኪዳን 6500 ያክል ጊዜ ከሌሎቹ የእግዚአብሔር መጠሪያ ሰሞች በበለጠ ተጠቅሷል።

ብዙ አምላኪ የነበሩ ግብጻውን ያሳደጉት ሙሴ እግዚአብሔር ስሙን እንዲነግረው በጠየቀ ጊዜ እግዚአብሔር ያለው ነገር አዳምጡ።

> “እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ‘ያለና የሚኖር’ እኔ ነኝ አለው፤
> እንዲህ ለእስራኤል ልጆች፦ ‘ያለና የሚኖር’ ወደ እናንተ
> ላከኝ ትላለህ አለው።” (ዘጸአት 3:14)

“ያለ” ሊል የሚችለው አካላዊ የሆነ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ታላቁ አካላዊ እንደሆነ እንዲረድዱ ይፈልጋል። ስሙም ያለ ነው።

ብቸኛ የማይውጥ እሱ ብቻ ነው።

ለሱ ያለፈው ፣ የአሁኑ እና የሚመው ጊዜ ምንም አይደለም። የእሱ መኖር ጊዜና ቦታ አይወሰነውም።

እሱ ራሱ ለራሱ ብቁ ነው።

እኔ እና እናንተ አየር፣ ውሃ፣ ምግብ፣ መኝታ መጠለያ እና ሌሎች ለመኖር ያስፈልገናል፣ እሱ ግን ምንም አያስፈልገው

ም። ከራሱ ጋር የሚማከር እና በራሱ ሳይል የሚኖር እርሱ ብቻ ነው። እሱ ታላቁ እኔ ፣ ጌታ ነው። (አስታውሱ፦ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለየት ባለ አጣጣል ጌታ ሲጻፍ የእብራይስጡ ያህዌህ ወይም በራሱ ኗሪ ዘላለማዊ ማለት ነው።

እግዚአብሔር የሰው ልጅ እንዲፈታው አልተወውም።
እሱ ራሱን የሚፈታ ነው።

## በመቶዎች የሚቆጠሩ ስሞች

በዘላለማዊ ህልውናው አብ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ጌታ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመጠሪያ እና የማዕረግ ስሞች። የእግዚአብሔር ስሞች ጠባዩን ይገልጣሉ፡ እያንዳንዱ የማዕረግ ስም እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እና ምን አይነት እንደሆነ የበለጠ እንድንረዳ ያደርገናል። ለምሳሌ እሱ በሚከተሉት የመጠሪያ ስሞ ተጠርቷል፦

> የሰማይና የምድር ፈጣሪ ፣ የሕይወት ጀማሪ ፣ ታላቅ፣ እወነተኛ ብርሐን፣ ቅዱስ ፣ ጻድቅ ፈራጅ፣ የሚረዳን ጌታ፣ የሚፈወሰው ጌታ፣ እግዚአብሔር ጽድቃች ን፣ እግዚአብር ሰላማችን ፣ እግዚአብር እረኛችን ፣ የፍቅር እና የሰላም አምላክ፣ የጸጋ ሁሉ አምላክ፣ የዘላለማዊ ድነት ጀማሪ፣ የቅርብ አምላክ...

በአሁን ሰዓት ሰለ ፈጣሪ ያለን መረዳት ምንም ይሁን ምን፣ ሁላችንም እሱ አምላክ እንደሆነ እና እሱን የሚመስል እንደሌለ በትህትና መቀበል አለብን። ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ልናብራራው ወይም ልንረዳው ባንችልም ስሙን እንድናውቅ ፣ እንድንወደው እና ለእሱ ለዘላለም እንድንኖር ይፈልጋል። እግዚአብሔር በሰድስተኛው የፍጥረት ቀን የሚከተለውን ያለው ይህንን ዓላማ አሰቦ ነው፦

> “ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር”
> (ዘፍጥረት 1:26)

ምን ማለቱ ነው? የሚታይ ሰው የማይታየውን አምላክ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?



# 10

# ልዩ ፍጥረት

ከሁለት በፊት በዘመናት መካከል ከሰማናቸው አዋጆች ሁሉ የበለጠውን አዋጅ በተመለከተ ሐሳብ ተለዋወጠናል፦ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድረን ፈጠረ" (ዘፍጥረት 1:1)። ሌላኛው ደግሞ የሚከተለው ነው፦

> "ሰውን በመልኩ ፈጠረው" (ዘፍጥረት 1:27)

እግዚአብሔር የሰው ልጆች የፍጥረት አክሊል እንዲሆኑ ፈጠረው።

## በእግዚአብሔር መልክ

> "እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን **በመልካችን** እንደ **ምሳሌአችን** እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ **ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።"**
> (ዘፍጥረት 1:26-27)

እግዚአብሔር ሰውን "በመልኩ" ፈጠረው ማለት በመጀምሪያ ሰው በሁሉ ነገር እንደ እግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም። "እግዚአብሔር ሰውን **በመልኩ** ፈጠረው" ማለት ሰው ሰው የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋይ ነው ማለት ነው። የሰው ልጅ ንድፍ የእግዚአብሔርን ጠባይ ያንጸባርቃል። ለመጀመሪያው

ወንድ እና ሴት እግዚአብሔር ከእሱ ጋር ትርጉም ያለው መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ጠባያትን ሰጣቸው፡፡

እግዚአብሔር ደስታን እና ርህራሄን እንዲለማመዱ የሚያስችል ስሜት ሰጣቸው፡፡

ዘላለማዊ ውጤት ያላቸውን ምርጫዎች እንዲያደረጉ የሚያስችላቸው ነጻነት እና ሳላፊነት ያለው ፈቃድ ሰጣቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለመናገር ፣ የፊታቸውን ገጽታ ለመለዋወጥ እና ለመዘመር የሚያስችላቸውን የተግባቦት ችሎታ ሰጣቸው፡፡ የረጅም ጊዜ እቅድ እንዲያወጡ እና አሰገራሚ በሆነ የፈጠራ ችሎታ እቅዶቻቸውን ወደ ተግባር መለወጥ እንዲችሉ አደረጋቸው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ፈጣሪ እና ባለቤታቸውን እንዲያመልኩ እና በእሱም ለዘላለም ደስ እንዲሰኙ ዘላለማዊ ነፍስ ናመንፈስ ሰጣቸው፡፡

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የፈጠራቸው ለራሱ ነው፡፡ "ፍቅር" የሆነው እግዚአብሔር (1ዮሐንስ 4:8) ወንዶችን እና ሴቶችን የፈጠረው ስለሚያስፈልገው ሳይሆን ስለፈለጋቸው ነው፡፡ ሰዎች የፍቅሩ ተቀባዮች እና አንጸባራቂዎች ይሆናሉ፡፡

## የሰው ልጅ አካል

ምንም እንኳን የዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፍ እግዚአብሔርን ዓለምን እንዴት እንደፈጠረ አጭር ታሪክ የሚነግረንም ቢሆን ሁለተኛው ምዕራፍ የሰው ልጆችን አፈጣጠር የሚመለከተውን የጎደለ ታሪክ ይሞላል፡፡

> "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ፡፡" (ፍጥረት 2:7)

ምንም እንኳን ጌታ ሰማይን እና ምድርን ከምንም ነገር የፈጠረ ቢሆንም ፣ የመጀመሪያውን የሰው ልጅ ግን ከምድር አፈር ለመፍጠር ወስኗል፡፡ የአሁኑ ዘመን ሳይንቲስቶች ይህንን እውነት ያረጋግጣሉ፦ "ዝም ብለን ስንመለከተው አካላችን ብዙም የሚያስገርም አይመስልም፡፡ ሃያ የሚሆኑት የሰው ልጅ የተሰራባቸው የተለመዱ ንጥረ ነገሮች በመሬት ደረቅ አፈር ውስጥ ይገኛሉ፡፡"[115]

ምንም እንኳን አካላችን ከእንደዚህ አይነት ተራ ነገሮች የተሰራ ቢሆንም በአስገራሚ የግንባታ ጥበብ የተሰበሰቡ 75

ትሪሊዮን (75,000,000,000,000) ሕይወትና የየራሳቸው ስራ ካላቸው ሴሎች የተገነባ ነው።

ሕዋስ የሕይወት መሠረታዊ ቅንጣት ነው። ሕዋስ በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ ሊታይ የሚችለው ከማየክሮስኮፕ ስር ሲሆን በሚሊዮን በሚቆጠሩ ክፍሎች ያሉት ነው። እያንዳንዱ ሕዋስ ሁለት ሜትር ርዝመት (ስድስት ጫማ) ርዝመት ያለው የተጠቀለለ ዲኤንኤ ቅንጣት ለሰው መሠረታዊ ገጾች የሚያገለግል የዘረመል ኮድ ይዟል።

ታዋቂው የኮምፒውተር ሶፍትዌር ባለሙያ እንዲህ ብሏል "የሰው ልጁ ዲኤን ኤ ልክ እንደ ኮምፒውተር ፕሮግራም ነው፤ ነገረ ግን ከተፈጠርሩ የሶፍትዌር ፕሮግራሞች ሁሉ በላይ የላቀ ነው።"[116] በሰው ልጅ አካል ውስጥ በትንሹ 200 የተለያዩ ሕዋሶች ይገኛሉ። አንዳንዶቹ እንደ ደም ያሉ ፈሳሾችን ሲያመርቱ፣ ሌሎቹ ደግሞ የሰው ል ጅ የአካል ክፍሎችን ይስራሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ እንደ አጥንት ያሉ ጠጣር ክፍሎችን ይሰራሉ። ጥቂት ሕዋሳት የአካል ክፍሎቻችን ላይ አንድ ላይ ይይዛሉ ፣ ሌሎቹ ግሞ እነዚህ እንደ ስርዓተ ልመት የሥነ ተዋልዶ ስራዎች ያሰተባበራሉ።[117]

ሰለ ራሳችሁ የአካል ክፍሎች አወቃቀር እና ክፍሎች አስቡ፦ 206 አጥንቶችን ተያይዞ በመቅኒ ፣ ጡንቻዎች ቆዳ እና ጸጉር ተለብጦ ወይም የስረዓተ ደም ደም ቀዳ ፣ደመ መልስ ይዞ ለሕይወት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ይዟል። በመቀጠልም አንጀቶች ፣ ጨጓራ ፣ ጉበት እና ኩላሊት አሉን። በተጨማሪም ደግሞ ውስብስ ብበሆነ ሁኔታ ከአዕምሮ ጋር የተያያዘው ስርዓተ ነርቭ ይገኛል። በተጨማሪም ታማኙን የደም ፓምፕ ልብን አትርሱ ወይም እግዚአብሔር በአይን፣ በጆሮ፣ አፍንጫ ፣ አፍና መላስ ከዚያም ጎን ለጎን የድምጽ ሳጥን ፣ የጣዕም ቅንጣቾና ጥርስ ሰጥቷችኋል። እነዚያ እግሮቻችሁ እና እጆቻችሁም ጠቃሚ ናቸው። እግዚአብሔር አውራ ጣት ስለ ሰጣችሁ አመስግናችሁት ታውቃላችሁ? ያለ አውራ ጣታችሁ መጥረጊያ እና መጶሻ ለመጠቀም ሞከሩ! እነዚያ የእጅ ጥፍሮቻቸሁ በጣም ጠቃሚ ናቹሁ...

ነብዩ ዳዊት የሚከተለውን መጻፉ ሊያስገርማቸሁ አይገባም፦

> *"ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።"*
>
> (መዝሙር 139:14)

## ነፍስና መንፈስ

የሰው ልጅ አካል ምንም ያክል አስገራሚ ቢሆንም ሰዎችን ልዩ የሚያደርገው አካል አይደለም። እንስሳት፣ ወፎች እና ዓሳዎች አስገራሚ አካል አላቸው። የሰውን ልጅ ልዩ የሚያደረገው የሰው ነፍስና ዘላለማዊ መንፈስ ነው። የመጀመሪያዎቹን ወንዶች እና ሴቶች "በእግዚአብሔር መልክ የተሰሩ" ልዩ የሚያደረጋቸው ነፍስና መንፈስ ነው።

ስለዚህም እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የሰውን አካል ከምድር አፈር ካበጀ በኋላ "በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።" (ዘፍጥረት 2:7) እግዚአብሔር ለአዳም የሰራው አካል እግዚአብሔር የአዳምን ልጅ ነፍስና መንፈሰ ያሰቀመጠበት ቤት ወይም ድንኳን ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ አካል የሰጠው በዙሪያው የሚገኘውን ዓለም እንዲረዳ ነው፣ ነፍስ የሰጠው ደግሞ ውስጣዊ ማንነቱን እንዲገነዘብ ነው፤ በተጨማሪም መንፈሰ የሰጠው እግዚአብሔርን እንዲገነዘብ ነው።

አካል የሚገዛው በነፍስ ነው ፣ ነፍስ ደግሞ የሚገዛው በመንፈስ ነው፣ መንፈስ ደግሞ የሚገዛው በእግዚአብሔር ራሱ ነው።[118]

> "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።"
> (ዮሐንስ 4:24)

## ለዓላማ የተፈጠረ

ታላቁ ባለሙያ የሰው ልጅን ስሉስ አሐዱ እንዲሆን አደርጎ "መንፈስ፣ነፍስ እና አካል"(1 ተሰሎንቄ 5:23) በማገናኘት ፈጥሮታል፣ በተጨማሪም የሰው ልጆች ከፈጣሪያቸው ጋር የቅርብ ወዳጅነት በመፍጠር ደስ ይሰኛሉ። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሕይወት ሰለ ሰጠው ለፈጣሪ ባለቤቱ ደስታና ምስጋና መኖር ለሰው ልጅ የከበረ ዕድል ነው።

> "**በስሜ** የተጠራውን **ለክብሬም** የፈጠርሁትን... ምስጋናዬን እንዲናገሩ **ለእኔ** የፈጠርሁት ሕዝብ"
> (ኢሳያስ 43: 7 ፣21)

የሰው ልጆች ለእግዚአብሔር ክብር ተፈጥረዋል።

ምድር የተሰራቸው ለሰው ልጆች ነው፣ የሰው ልጅ ግን የተሰራው ለእግዚአብሔር ነው። የፈጣሪ ዓላማ መጀመሪያ የፈጠራቸው የሰው ልጆች ለዘላለም እንዲያውቁት፣ ደስ እንዲሰኙበት እና እንዲወዱት ነው። ለእኔ እና ለእናንተም ያለው ዓላማ ይኸው ነው።

> "አንተም በፍጹም **ልብህ** በፍጹምም **ነፍስህ** በፍጹምም **አሳብህ** በፍጹምም ኃይልህ **ጌታ አምላክህን** ውደድ የምትል ናት።" (ማርቆስ 12:30)

## ፍጹም የሆነ አካባቢ

እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረ በኋላ፣ ቀንጡ የሆነውንና ኤደን ተብሎ የሚጠራውን የአትክልት ስፍራ ተክሎ አዘጋጀ።

> "እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔድን ገነትን ተከለ የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው። እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፥ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ፤ በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ። ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔድን ይወጣ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር።" (ዘፍጥረት 2:8-10)

ኤደን በአሁኑ ዘመን ኢራቅ[119] በምትባለው አካባቢ ሳትገኝ አትቀርም የምትባለው ኤደን ያልተገደበ ደስታ ያለባት የአትክልት ቦታ፣ አስደማሚ ገጽታ፣ ድምጽ እና ሽታ ያላት ነበረች። የሚያንጸባርቅ ውሃ የአትክልት ቦታውን ያጠጣ ነበር። ዳርቻዎቻቸውን የሚያስጎመጁ የአትክልት ዛፎች ይገኛሉ። በቃላት ሊገለጽ የማይችል ብዛት ያላቸው ሊቀመሱ የሚችሉ አትክልቶች፣ አድናቆት የሚገባቸው ደስ የሚያሰኝ ሽታ ያላቸው አበባዎች ፣ ረጃጅም ዛፎች እና ዐይን የሚያርፍባቸው የተንጣለሉ መስኮች ፣ አራዊት ፣ ወፎች ሊጠኑ የሚገባቸው ነፍሳት ፣ ሊታሰሱ የሚገባቸው ጫካዎች ፣ ሊገኙ የሚገባቸው ወርቅ እና የከበሩ ድንጋዮች ይገኙባታል። በእርግጥም እግዚአብሔር ለአዳም "ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን" (1ጢሞቴስ 6:17)።

እግዚአብሔር በአትክልት ቦታ መካል ሁለት የተለዩ ዛፎችን ተክሏል፦ የሕይወት ዛፍ እና ክፉን እና ደግን የምታሳውቀው ዛፍ።

ኤደን ማለት ደስታ ማለት ነው። እግዚአብሔር ለደስታቸው አስገራሚ ቤት ፈጠረ ፣ ነገር ግን የሰው ልጅ ታላቅ ደስታ ከፈጣሪው ጋር ኅብረትን ማድረግ ነው።

እግዚአብሔርን በግል ከማወቅ እና ከእርሱ ጋር በግል ከመሆን የበለጠ ደስታ የለም። "ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፣ **በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ**።" (መዝሙር 16:11)

## የሚያረካ ስራ

አንድ ጊዜ የአትክልት ስፍራው ዝግጁ ከሆነ በኋላ ጌታ የሰው ልጅን በአትክልቱ ስፍራ አስቀመጠው። እግዚአብሔር አዳምን እዚያ ለመኖር ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን አልጠየቀውም። እግዚአብሔር የሰው ልጅ ፈጣሪን እና ባለቤት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆነውን ስለሚያውቅ ለማንም ማብራሪያ መስጠት አላስፈለገውም።

> "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው።"
> (ዘፍጥረት 2:15)

እግዚአብሔር ለአዳም አዲሱ መኖሪያ በታው ሁለት ኃላፊነቶች ሰጥቶታል።

የመጀመሪያው፣ የአትክልት ስፍራውን "ማበጀት" ነበር፣ ነገር ይህን ሁሉ የሚያደርገው ያለ ላብ፣ ያለ ድካም እና ያለ ጥረት ነው። ሁሉ ነገር መልካም ስለሆነ አጅግ በጣም የሚያስደስት ስራ ነው። የሚዋጋ እሾህ ወይም የሚነቀል አረም አልነበረም።

ሁለተኛ፣ አዳም "እንዲጠብቃት" ኃላፊነት ተሰጥቶ ነበር። ይሄ የመጨረሻ ሃረግ አንድ ተንኮለኛ እና አደገኛ አካል በዓጽናፈ ዓለም ውስጥ ያደፈጠ መሆኑን ይሆን?

ያ ጥያቄ በጣም በቅርቡ ይመለሳል።

## ቀላል ሕግ

ሰው አካላዊ ፍጥረት እንጂ አሻንጉሊት ስላልሆነ ፣ እግዚአብሔር የሚታዘዘው አንድ ቀጥተኛ ሕግ ሰጠው።

> "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ **ትበላለህ**፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን

ከሚያስታውቀው ዛፍ **አትብላ**፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።" (ዘፍጥረት 2:16-17)

እግዚአብሔር ትዕዛዙን የሰጠው ሴት ከመፈጠሯ በፊት ነው። እግዚአብሔር አዳምን የሰው ልጆች ሁሉ ራስ አድርጎ ስለሾመው ፣ ያቺን አንድ ሕግ እንዲጠብቅ ኃላፊነት ሰጠው።

## የመጀመሪያዋ ሴት

በመቀጠልም እግዚአብሔር ሴትን ፈጠረ። ምን አይነት ልዩ አፈጣጠር ነበረ!

"እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት። ...እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም፤ ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር።" (ዘፍጥረት 2:18 ፤ 21-25አመት)

ስለዚህ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ቀዶ ጥገና አደረገ፣ ከአዳምም የጎን አጥንት ቆንጆ እና ተወዳጅ የሆነች ሚስት አበጀለት እና ለአዳም በግሉ አቀረበለት።

አዳምም እግዚአብሔር የቅርብ እና አፍቃሪ "ረዳት" ስለሰጠው ምን ያህል እንደ ተደሰተ! ሟቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር ማቲው ሄንሪ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "ሴት የተፈጠረችው ከአዳም የጎን አጥንት ነበረ፣ በእሱ ላይ ገዢ እንድትሆን ከራስ ቅሉ አጥንት ላይ አልሰራትም፣ ወይም በላይዋ ላይ እንዲረማመድ ከእግሩ አጥንትም አልሰራትም፣ ነገር ግን የእሱ እኩያ እንድትሆን፣ ከክንዱ ስር እንድትጠበቅ እና ከልቡ አቅራቢያ እንድትፈቀር አድርጎ ሰራት።" [120]

ልክ እንደ ወንድ ሴት የተፈጠረችው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ፣ የእግዚአብሔርን ጠባይ እንድታንጸባርቅ እና ከእሱ ጋር መንፈሳዊ አንድነት እንዲኖራት ተፈጠረች። ምንም እንኳን ፈጣሪ ለወንድ እና ለሴት የተለያየ ተዋረድ እና የተለያየ

ሚና ቢሰጣቸውም በዋጋ እና በአስፈላጊነት እኩል እንደሆኑ ተናግሯል።

ዛሬ ከእግዚአብሔር በተቃራኒ በርካታ ማህበረሰብ ሴትን ልክ እንደ ዕቃ ያያል። ሰዎች ወንድ ልጅ ሲወልዱ በጣም ሲደሰቱ፣ ሴት ስትወለድ ይበሳጫል።

ከሚስቶቻቸው ይልቅ የበለጠ እንክብካቤ እና ገደድ ያሳያል። አንዳንድ ማህበረሰቦች ርቀው በመሄድ እግዚአብሔር ለወንዶችን እና ለሴቶች የሰጣቸውን የስራ ድርሻ ቸል ይላሉ። ሁለቱም ጽንፎች ሴቶችን ያዋርዳሉ።

## የመጀመሪያው ጋብቻ

የመጀመሪያውን ጋብቻ ማን እንዳስፈጸመ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ።

ይህን ያደረጋው ጌታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱስ እንዲህ ይላል። “[እሱ] ወደ አዳም አመጣት።” ከመጀመሪያው አንስቶ ፈጣሪ በፈጠራቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ ይገባል። “ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል።” በሎ ያወጀው እሱ ራሱ ነው። “አንድ” የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ኤኻድ ማለት ሲሆን ትርጉሙም የሕብረት አንድነት ማለት ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ጥንዶች በመጣጣም አንዳቸው ሌላውን እንዲያገግሉ እና እንዲያስደስቱ እና በእሱም ደስ እንዲሰኙ እና እንዲያገለግሉት አድርጎ አበጅቷቸዋል። ወንድ እና ሴት በነጠላም ይሁን በቡድን ፈጣና ባለቤታው የሕይወታቸው ማዕከል እንዲያደረጉት ፈልጓል።

በአሳዛኝ ሁኔታም አሁን ባለንበት ዓለም ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ዕቅድ ችላ ብለዋል ተጨማሪም ዓመታት እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር በወንድ እና በሴት መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ ያማረ እየሆነ እንደሚሄድ ፍንጩም የላቸውም። ስለዚህም ጌታ ከመጀመሪያው ለባልና ሚስት ያሰበውን በፈቅር የተሞላ ፣ ታማኝነት ያለበት፣ ራሰ ወዳድ ያልሆነ እና ደስ የሚያሰኝ እግዚአብሔርን ደሰ የሚያሰፕውን ግንኙነት ማሳየት ሳይችሉ አይቀርም።

በወንድ እና በሴት መካከል ያለው ፈጣሪ የጀመረው የጋብቻ አይነት የእሱን የማይለካ የፍቅር ልብ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ከእሱ ጋር አሁን እና ለዘላለም ሊኖራቸው የሚገባውን የሚያስደስት ግንኙነት ጋብቻ ቀረቤታ ያለበት ፣ የሚያሰደንቅ፣ አዳጊ፣ መንፈሳዊ ሆኖ እንዲያሳይ ፈልጎ ነበር።

የጋብቻ ጀማሪ ጋብቻን እንዴት እንደሚፈታው አያችሁ? “ከዚህም የተነሳ ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል ፣ ሁለቱም አንድ ስጋ **ይሆናሉ**።” በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ “አዳምና ሚስቱ ራቁታቸውን ነበሩ ፣ **አይተፋፈሩም** ነበር።”

እግዚአብሔር ለጋብቻ ያለው ዕቅድ ጥንዶቹ በዓላማ እና በአካል ከእፍረት ነጻ በሆነ መልኩ እንዲጣመሩ ነበር። ከፍ ባለ ደረጃ ስንመለከተው የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዘላለምም ያለ እፍረት መንፈሳዊ አንድነትን እንዲለማመዱ ነበር።

## የሰው ልጅ ገዢነት ተሰጠው

እግዚአብሔርን ሴቲቱን ለአዳም ካቀረበለት በኋላ ሁለቱንም በቀጥታ በግል ተናገራቸው። እግዚአብሔር በሚታይ መልኩ የተገለጠላቸው ይመስላል። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ “ከገነት ውስጥ ሲመላለስ” ይላል። (ዘፍጥረት 3:8)

አሁን እስቲ ጌታ ባልና ሚስቱን ፈጣሪ የፈጠረው የከበረ እና አሰደማሚ ፍጥረት እንዲመሚለከቱ ከፍ ወዳለተራራ ሲመራቸው አስቡ…

> “እግዚአብሔርም ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፤ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት፤ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው። እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ፤ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ” (ዘፍጥረት 1:28-29)

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን[121] ዘሮቻቸውን በፍጥረት ላይ ስልጣን ሰጣቸው። የሰው ዘር “ጀማሪ ጥንዶች” ስለሆኑ ዕድልና ሳላፊነት ሰጣቸው። በፍጥረት ሁሉ ላይ የገዢነት ስልጣን ሰጣቸው። ገዢነት ማለት ስልጣን እና ቁጥጥር ማለት ነው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው አዳም፣ ሄዋንና ዘሮቻቸው ምድርን ለደስቱባት፣ ሊንከባከቧት እና በጥበብ እንዲገዟት ነበር። ሊጠቀሙባት እንጂ ሊያበላሿት አይገባም።

ፈጣሪ ፍጥረትን ከሰው ልጅ ጋር እንዲስማማ አደርጎ ስራው። በመጀመሪያ ምድር የሰው ልጅ የፈገለውን እና ያስፈለገውን ነገር ሁሉ ለመስጠት ተባበረች። አዳምና ሄዋን ቀጣዩ ምግባቸው

ከየት እንደሚመጣ በማሰብ መጨናነቅ የለባቸውም ነበር። እነሱ ሊያደረጉት የሚገባው ነገረ ከማይቆጠረው የፍራፍሬ ዛፍ ወደ አንዱ እጃቸው ሰደው መቅጠፍ ነበር። አስቸጋሪ መሬት ፣ አረምና ቆንጥር ፣ ሕመምና ሞት አልነበሩም። እያንዳንዱ የፍጥረት ጥግ ሁሉ ለአዳምና ለሄዋን የተገዛ ነበር። የሰው ልጅ ገዢነት ነበረው። የሰው ልጅ ለፈጣው እስከተገዛ ድረስ ፍጥረት ለሰው ልጅ ይገዛ ነበር።

## እግዚአብሔርና ሰው በአንድነት

ከመጀመሪያው ጀምሮ ጌታ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ከሱ ጋር የቅርብ ጣፋጭ ኅብረት እንዲኖራቸው ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር ለአዳም ለሄዋን እሱን እንዲረዱት አዕምሮ እና ልብ (ሐሳብ እና ስሜት)፣ የመምረጥ ነጻነት (ነጻ ፍቃድ) ማመን እና አለማመን እንዲችሉ ወይም እንዲያዙ ወይም እንዳይያዝ ነው። እውነተኛ ፍቅር እና ታማኝነት በግድ የማይመጡ ስለሆኑ የምርጫ ጉዳይ በጣም አስፈላጊ ነበር። ሉዓላዊው አምላክ አዳምን እና ሄዋንን ሰለ ምርጫቸው ተጠያቂ ያደርጋቸው ነበር።

ምንም ልትሳሳቱት የማይገባው ነገር የዓጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ እና ባለቤት ከእናንተ የሚፈልገው ምንም ነገር ባይኖርም ፣ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ ግንኙነት ፍጠርን ይፈልጋል።

እኛ መታወቅ እንደምንፈልገው ሁሉ እግዚአብሔርም ለራሱ በፈጠረው ሕዝብ መታወቅ እና መወደድ ይፈልጋል። “በመልኩ” ከፈጠራቸው ሰዎች ጋር የልብ ለልብ ግንኙነት ከዘላለማዊ ባህርይው አንደኛው ነው።

ሰዎች እንዲህ ሲሉ እሰማለሁ “እኔ የእግዚአብሔር ባርያ ነኝ እንጂ ከዚያ የበለጠ ምንም አይደለሁም።” እውነትም ባርያ በፈቃዱ ለጌታው እንድሚታዘዝ ጌታን ማገልገል ታላቅ ክብር ነው። የእግዚአብሔር እቅድ ግን የሰው ልጅ “ባሪያ ሳይሆን **ልጅ**” (ገላትያ 4:7) እንድንሆን ነው። “**ባርያም** ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ **ልጁ** ለዘላለም ይኖራል።” (ዮሐንስ 8:35) እግዚአብሔር የልቡን ምኞት በሰውኛ ዘይቤ(እንደ ሰው አነጋገር) ሲግልጥ በእርሱ ለሚታመኑ ያቀደውን ነገር ይነግረናል፦

> “ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆቸና ሴት ልጆች ተሆናላችሁ ይላል።” (2 ቆሮንቶስ 6:18)

በተጨማሪም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ወላጅ

ለልጁ ካለው ፍቅር ጋር ማነጻጸር በማነጻጸር ብቻ አያቆምም፡፡ ፈጣሪያችን ምሳሌው ተጨማሪ ጥልቀት በመስጠት ከሕዝቡ ጋር ያለውን ቁርኝትና ፍቅር ሰው ከእጮኛው ጋር ካለው ፍቅር ጋር አነጻጽሮ ይገልጠዋል፡፡

> “በዚያ ቀን ባሌ ብለሽ ትጠሪኛለሽ እንጂ ዳግመኛ በኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም፣ ይላል እግዚአብሔር፤... ለዘላለምም ለእኔ እንድትሆኚ አጭሻለሁ፤ በጽድቅና በፍርድ በምሕረትና በርኅራኄ አጭሻለሁ፡፡ ለእኔም እንድትሆኚ በመታመን አጭሻለሁ፤ አንቺም እግዚአብሔርን ታውቂአለሽ፡፡” (ሆሴዕ 2:16 ፣ 19-20)

በዚህ ምድር ላይ በሁለት ሰዎች መካከል ያለን በጣም አሰደሳች ግንኙነት አስቡና ከሚከተለው ጋር በማነጻጸር አስቡት፦ እግዚአብሔር ከእሱ ጋር እንዲኖረን የሚጋብዘን አስገራሚ ግንኙነት በምድር ላይ ካለ ምርጡ የሰው ለሰው ግንኙነት እጅግ በጣም የበለጠ ነው፡፡

ከፈጣሪ ጋር የግል ግንኙነት ከሌላችሁ ሕይወታችሁ ያልተሟላና የማያረካ ይሆናል፡፡ ምንም ዐይነት ምድራዊ ሐብት፣ ደስታ፣ ስልጣን፣ ሰዎች እና ጸሎት በነፍሳችሁ ውስጥ ያለውን ክፍተት ሊሞላ አይችልም፡፡ ጌታ ራሱ ብቻ ነው በልባችሁ ለራሱ በሰራው ባዶ ክፍል ውስጥ ሊገባ የሚችለው፡፡

> “የተራበችን ነፍስ አጥግቦአልና፣ የተራቈተችንም ነፍስ በበረከት ሞልቶአልና፡፡” (መዝሙር 107:9)

ሊያመልጠን የሚገባው ነጥብ የሚከተለው ነው፦ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ በእሱ ከሚታመኑ ሰዎች ጋር ካለው እውነተኛ ግንኙነት ውጪ በሐይማኖታዊ ስርዓት አይደሰትም፡፡

በተለያየ ደረጃ ፣እግዚአብሔር በኅብረት ተደስቷል ወደፊትም ይደሰታል፦

- ራሱ፡፡ ለዘላለም የፍቅር ኅብረት በዘላለማዊ አባት፣ በዘላለማዊ ልጅ እና በዘላለማዊ መንፈስ ቅዱስ መካከል ይፈስ ነበር፡፡ ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ወልድ ለአብ የሚከተለውን ሲል መዝግቦልናል ፦ “አባት ሆይ፣ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ፡፡” (ዮሐንስ 17:24)
- መላዕክት፡፡ መላዕክትን የፈጠረው እንዲያውቁት ፣ እንዲወዱትና ታላቁን ክብሩ ለዘላለም እንዲያወድሱ

ነው። “የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ” (ዕብራውያን 1:6)

- ሰዎች። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የፈጠረው አንድ ቀን ከመላዕክት በበለጠ ከፈጣሪያቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ደሰ እንዲሰኙ በማሰብ ነው። ንጉስ ዳዊት እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “የጣቶችህን *ሥራ* ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን፥ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው።” (መዝሙር 8:3-5) እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መሆን ይፈልጋል። ነገር ግን መጀመሪያ አዳም መፈተን አለበት።

## ቀን 7፦ የፍጥረት *ሥራ* መጠናቀቅ

የፍጥረት ትረካ የሚገባደደው ጠቃሚ መረጃ በመስጠት ነው፦

“እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም **እጅግ መልካም** ነበረ። ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ **ተፈጸሙ**። እግዚአብሔርም የሠራውን ***ሥራ*** በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ***ሥራ*** ሁሉ ዐረፈ።” (ዘፍጥረት 1:31 ፤ 2:1-2)

የእግዚአብሔር የፈጠራ *ሥራ* ተጠናቅቋል። በፍጠረው የሚደሰበትበት ጊዜ ደርሷል። በራሱ የሚኖረው ፣ ስሙ “ያለ” የሆነው ደክሞት አያውቅም።

እግዚአብሔር አረፈ (ስራ መሰራት አቆመ) ምክንያቱም የፈጠራ ስራው ሰለተጠናቀቀ ነው።

ጌታ አምላክ ደስ ተሰኝቶ ነበር።

ሁሉ ነገር ፍጹም ነበር።

እስቲ ፍጹማን ሰዎች የተሞላ ከፍጹም አምላካቸው ጋር እያደገ በመሄድ ግንኙነት ውስጥ ለመግባት ስለሚችሉበት ፍጹም የሆነ ዓለም አስቡ።

ጉድ ዛሬ ፕላኔታችን ከፍጽምና የራቀች ነች። እኩይና ዘላለማዊነት፣ ጸጸትናሐዘን ፣ ድህነት እና ዐመጽ እናም በሽታ እና ሞት የተጣመሩ ናቸው።

ታዲያ ፍጹሟ ምድር ምን ሆነች?

ቀጣዩ የታሪኩ ክፍል ይኸው ነው።



# 11

# የእኩይ መግባት

"ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፤ ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ **የቃሉንም** ድምፅ የምትሰሙ **መላእክቱ** ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ። **ሠራዊቱ** ሁሉ፥ **ፈቃዱን** የምታደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።"
ንጉሥ ዳዊት (መዝሙር 103:2 ፤ 20-22 አመት)

እግዚአብሔር የሰው ልጅን ከመፍጠሩ በፊት የማይቆጠሩ መላዕክት እየተባሉ የሚጠሩ መንፈሳዊ አካላትን ፈጥሯል። እግዚአብሔር የፈጠራቸው ለእሱ ደስታ እና ምስጋና ነበር። እነሱ "የእሱ የሰማይ ሰራዊት" ነበሩ ፤የተሰሩትም የተሰሩትም ፍጣሪ ባለቤታቸውን ለዘላለም እንዲያውቁት ፤ እንዲያገለግሉት ፤ ደስ እንዲሰኙበትና ከፍ ከፍ ከፍ እንዲያደርጉት ነበር። እግዚአብሔር መላዕክትን በዋነኛነት የፈጠረው በደመ ነፍስ እንደ እንስሳት እንዲሆኑ አይደለም። ልክ እንደ ሰው ልጆች የእሱን ፍቃድ መታዘዝ እና ምስጋና ማቅረብን በተመለከተ ሞራላዊ ምርጫ እንዲያደርጉ አደርጎ ፈጠራቸው።

## የሚያበራው መልዐክ

ከፍ ያለ ሳይልና ዕድል የተሰጠው ሉሲፈር ወይም የሚያበራው ለተባለው መንፈሳዊ ፍጡር ነበር።[122] ይሄ የሚያበራ መልአክ እንዲህ ተብሎ ተገልጾ ነበር "ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ።" (ሕዝቅኤል 28:12)

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ዝርዝር ሁኔታውን ባይገለጥ እንኳን እኩይና ችግር ወደዚህ አጽናፈ ዓለም የገባው በዚህ አስገራሚ መልዐክ በኩል ነበር፡፡

እግዚአብሔር ሉሲፈርን እንዲህ ይለዋል፦

> “…**በደል እስኪገኝብህ ድረስ** በመንገድህ ፍጹም ነበርህ፡፡ በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል፤ ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ፤ በምድር ላይ ጣልሁህ ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት ሰጠሁህ፡፡ …አንተን በልብህ፦ ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ **እቀመጣለሁ**፤ ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፣ በልዑልም **እመሰላለሁ** አልህ፡፡”
>
> (ሕዝቅኤል 28:15 ፣ 17፡ ኢሳያስ 14:13-14)

እግዚአብሔርን በማመስገንና በመታዘዝ ፋንታ ፣ አምሥት ጊዜ ያክል ሉሲፈር “እሆናለሁ” አለ፡፡ “እንደ ልዑሉ” መሆን ፈለገ፡፡

በራሱ ውበትና ብስለት ታውሮ እና ሁሉንም የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ረስቶ ይሄ መልዐካዊ ፍጥረት ራሱን ከእግዚአብሔር የበለጠ ጠቢብ አድርጎ በማሰብ ራሱን አሳተ፡፡ አምልኮ እና ምስጋና በሚገባው በፈጣሪ ምትክ የመላእከት ሠራዊት እንዲያመልኩት ፈለገ፡፡

ሉሲፈር የሰማይ መላእክት ሲሦ በዐመጽ ከእሱ ጋር እንዲተባበሩ ገፋፋቸው፡፡[123] ስለዚህም የሚያበራው መልዐክ እግዚአብሔርን ከገዢነቱ አፈናቅሎ በሰማይ በሚገኘው ዙፋን ላይ ለመቀመጥ አሴረ፡፡

ኅጢአትም ወደዚህ ዓለም ገባች፡፡

## ኅጢአት ምንድን ነው?

ቅዱሳት መጽሐፍት ኅጢአትን ይፈቱልናል፦

- “ኃጢአትም ዓመፅ ነው፡፡” (1ዮሐንስ 3:4)
- “ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው” (1ዮሐንስ 5:17)
- “በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው፡፡” (ያዕቆብ 4:17)
- “ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው” (ሮሜ 7:8)
- ሐጢአት “የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል” (ሮሜ 3:23) “የእግዚአብሔር ክብር” የእግዚአብሔርን ንጽህና እንኳን

አልባ ፍጽምና በሙላት ያሳያል። “መጉደል” ማለት ደግሞ የፍጽምናን ግብ ለማሳካት አለመቻል ማለት ነው።

ሳጢአት ማለት ከእግዚአብሔር ቅዱስ ባህርይ እና ፍቃድ ጋር ሙሉ በሙሉ ተስማምቶ ለመኖር አለመቻል ማለት ነው።

አጠር ባለ መልኩ **ኀጢአት** በዘላለማዊ አካል ማለትም በሰውም ሆነ በመልዐካዊ ፍጡር ሊደረግ የሚችል እግዚአብሔርን ከፍ ከማድረግ እና መንገዱንም ከመከተል ይልቅ ራስን ከፍ ማድረግ እና ወደ “ገዛ መንገዱ” ማዘንበል ነው (ኢሳያስ 53፡6)።

በእግዚአብሔር ላይ ሳይደገፉ ማሰብና መመላለስ **ኀጢአት** ነው። ሉሲፈር የመረጠው መንገድ ይሄ ነበር መላዕክትም በሐዘኔታ ተከትሉት። በፈጣሪ ላይ ጥገኛ ከመሆን ይልቅ በልባቸው ትዕቢተኛ በመሆን ወደ ገዛ መንገዳቸው አዘነበሉ።

> “ልቡ የታበየ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው፤ እጅ በእጅም ሳይቀጣ አይቀርም።” (ምሳሌ 16:5)

ማርከስ ከባድ ቃል ነው ፍቺውም የጥላቻ ግብ ማደረግ ፣ ጸያፍ ድርጊት ፣ ማቆሸሽ ወይም ጣኦት ማምለክ ማለት ነው። እግዚአብሔር ራስ ወዳድነትን ይጠላል። ትዕቢት ሳጢአት ነው።

ሳጢአት በእሱ መገኘት ፊት እንዲኖር ማድረግ በቤታችሁ ውስጥ የአሳማ ሬሳ በቤታችሁ እንደማስቀመጥ የሚያቅለሸልሽ ነው። አንድ ሳጢአት ማለት በአንድ ብርጭቆ ውሃ ውስጥ አንድ ጠብታ መርዝ አድርጌ ለመጠጣት እንደምጸየፈው ያለ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው። የሸተተ ሬሳ በቤታችን ውስጥ የማንቋቋመው፣ በሻያችንም ውስጥ የሚገኝ ጠብታ መርዝ የማንፈልገው ለምንድን ነው? እንዲህ አይነት ነገሮች ከተፈሯዊ ባህሪያችን ጋር የምቃረን ነው።

ሳጢአት ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ጋር የሚቃረን ነው።

> “አቤቱ፥ የተቀደስህ አምላኬ ሆይ፥ አንተ ከዘላለም ጀምሮ አልነበርህምን? እኛ አንሞትም፤ አቤቱ፥ ለፍርድ ሠርተኸዋል፥ ለተግሣጽም አድርገኸዋል። ይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው፥ ጠማምነትንም ትመለከት ዘንድ አትችልም፤ አታላዮችንስ ለምን ትመለከታለህ?”
> (ዕንባቆም 1:12-13)

## ሰይጣን ፣ አጋንንት እና ሲዖል

ሉሲፈር የእግዚአብሔርን ክብር ለመንጠቅ እና ሥልጣኑን ለመቀማት በማሰቡ ምክንያት ከእሱ ጋር በምርጫቸው ከወገኑት መላእክት ጋር ከሰማያዊ ስፍራ ከነበረው ቦታ አፈናቀለው። የሉሲፈር ስምም ወደ ሠይጣን ተቀየረ፣ ይህም ጠላት ማለት ነው። እሱም ዲያብሎስ ተባለ ፍቺውም ከሳ ሽማለት ነው። የወደቁት መላዕክትም እርኩሳን መናፍስት ወይም አጋንንት ተባሉ፣ ይህም አዋቂዎቹ ማለት ነው።

ዲያብሎስ እና አጋንንቱ እግዚአብሔርን ያውቃሉ በፊቱም ይንቀጠቀጣሉ፤ ነገር ግን እሱን ለመርታት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ።

ነገር ግን አያሸንፉትም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ፣ ቀድሞ በተቀጠረው ቀን ሠይጣን እና አጋንንቱ "ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት" (ማቴዎስ 25:41) ይጣላሉ። ይሄ "ዘላለማዊ እሳት" እግዚአብሔር ከእሱ ቅዱስ ባህርይ ጋር ያልተስማሙትን የሚያሰቀምጥበት ስፍራ ነው።

ከሠይጣን ጋር የሚስማሙ አካላት የሚቀጡበትን ስፍራ የሚገልጸው የአዲስ ኪዳን ግሪክ ቃል ጌሄና ይሰኛል በዙ ጊዜ ሲዖል ተብሎ ተተርጉሟል።[124] ይሄ ቃልም ቃል በቃል የሚነድድ የቆሻሻ ስፍራ ማለት ነው።

በሴኔጋል እኔና ባለቤቴ ልጆቻችንን ያሳደግንበት አካባቢ ሰዎች ቆሻሸና የማይፈልጉበት ነገር የሚጥሉበት የቆሻሻ መጣያ ቦታ ነበር። ይሄ ቦታ በአቅራቢያው የሚኖሩ ሰዎች አስቀያሚ ሽታ ያለውን ቆሻሻውን ይጥሉበት ስለነበር ሁል ጊዜ እንደነደደ ነበር። የማይጠቅም የሚሉትን ሁሉ ወደ እሳቱ ውስጥ ይጥሉ ነበር።

ሲዖል የእግዚአብሔር "ቆሻሻ መጣያ" ቦታ ሲሆን ከነሳጢአታቸው የሞቱ ሰዎች በአሁኑ ሰዓት የሚገኙበት ቦታ ነው። አንድ ቀን ሠይጣን ፣ አጋንንቱ እና የሲዖል ነዋሪዎች በሙሉ ወደ መጨረሻው የፍርድ ስፍራ ወይም የእሳትና የድኝ ባህር ወደሚባው ውስጥ ይጣላሉ።[125]

ሳጢአት አጽናፍ ዓለሙን ለዘላለም አያቆሽሽም።

## የሠይጣን ዓላማ

ዲያብሎስን እና አጋንንቱን በተመለከተ ፣ አሁን በእሳት ባህር ውስጥ አይደሉም። በዚያ ምትክ በእኛ ዓለም ውስጥ በሰራላይ

ናቸው። "በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ።" (ኤፌሶን 2:2)

ስይጣን ኃይለኛ ቢሆንም ኃይል ሁሉ የእሱ አለመሆኑን መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው። እሱ የተፈጠረ እና የወደቀ ነው። ስይጣን "የዚህ ዓለም አምላክ" ተብሎ ተጠርቷል። ግቡም የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን እውነት እና የተፈጠሩበትን ዓላማ እንዳይቀበሉ ማድረግ ነው።

> "ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው። ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ **የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።**"
>
> (2 ቆሮንቶስ 4:3-4)

የሠይጣን ዓላማ ምንድን ነው? ሰዎች የእግዚአብሔርን መልዕክት ሰምተው እንዳያምኑ አዕምሯቸውን በማሳወር መከልከል ነው። እሱ ከእግዚአብሔር ጋር በጦርነት ውስጥ ነው። ይሄ ጦርነት ሠይጣን የማያሸንፍበት ጦርነት ነው፣ ነገር ግን በሚችለው አቅም የቻለውን ያክል ሕዝብ ከራሱ ጋር ይዞ መጠፋት ይፈልጋል። እናንተንም ለማካተት ተስፋ ያደርጋል።

አዳምና ሄዋን ለእግዚአብሔር ክብር እና ደስታ መፈጠራቸውን በማወቅ ሠይጣን በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጠረውን ግንኙነት ለማበላሸት አሴረ። "የሰውን ልብ የሚያውቅ" (መዝሙር 44:21) ጌታ እግዚአብሔር ዲያብሎስ ያሰበው በሙሉና ምን ሊፈጠር እንድሆነ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔርም የራሱ እቅድ ነበረው።

## አንድ ሕግ

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ፈጣሪውን በመውደድ፣ በማመስገን እና በመታዘዝ ዙሪያ ምርጫ ሰጥቶት ነበር። እውነተኛ ፍቅር በግዴታ ወይም በፕሮግራም የምናመጣው አይደለም። ፍቅር የሰው ልጅን አዕምሮ፣ ልብና ፈቃድ የሚጠይቅ ነው። ምንም እንኳን እግዚአብሔር በራሱ አጽናፈ ዓለም ላይ ሉዐላዊ ንጉስ ቢሆንም የሰው ልጅ ዘላለማዊ አሰከትሎት ባላቸው ነገሮች ላይ ለሚያደርገው ምርጫ ተጠያቂ ያደርገዋል።

ሴትን ከመፍጠሩ በፊት እንኳን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር። አዳም የሰው ዘር ራስ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር በፊቱ ፈተናን አሰቀመጠ።

> “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።” (ዘፍጥረት 2:16-17)

የእግዚአብሔርን ቀላል ትዕዛዝ አስታውሱ። አዳም ከአንዷ በስተቀር በአትክልት ስፍራው ከሚገኙ በርካታ ዛፎች ላይ ጣፋጭ ፍሬዎችን መመገብ ይችል ነበር። እግዚአብሔር መታዘዝ ካልቻለ ምን ሊከሰት እንደሚችል ነግሮት ነበር። “በበላህ ቀን **ሞትን ትሞታለህ**።”

ያንን መሰመር ማለፍ መተላለፍ ነው ፣ ይሄ ቃል ሌላው የሐጢአት ፍቺ ነው። ልክ እንደ ሉሲፈር ሁሉ በአጽናፈ ዓለሙ ጌታ ላይ ማመጽ አስከፊ አደጋን ያደርሳል።

ምንም እንኳን የመጀመሪያ ውሰው ፍጹም ቢሆንም ነገር ግ ንፍጹም የበሰ አልነበረም። ከዚቸ አንድ ሕግ የተነሳ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት እንዲያድግ እድል ተሰጥቶት ነበር። እግዚአብሔር አዳም በምስጋና እና በፍቅር ልብ እንዲታዘዘው ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር ካደረገለት ነገር አንጻር ያ ነገር ቀላል መሆን ይገባው ነበር።

አስቡት! እግዚአብሔር ለአዳም አካል ፣ ነፍስ መንፈስ ሰጥት ነበር። በቅድስና እና በፍቅር ባህርይ ፈጣሪውን እንዲያሳይ አድርጎ ባርኮት ነበር። በአስገራሚ የአትክልት ስፍራም አሰምጦት ነበር፣ ሕይወቱ ንጹህ፣ ደስታና እርካታ ያለበት እንዲሆን ሁሉንም አይነት የሚታሰብ ነገር ሁሉ አቅርቦለት ነበር። በተጨማሪም ደግሞ እግዚአብሔር ሳላፊነት ያለበት ምርጫ እንዲያደርግ ነጻነት እና ችሎታ ሰጥቶት ነበር። ለአዳም የምታምር ሚስት ሰጠውም፣ በተጨማሪም የአትክልን ስፍራ የመቆጣጠር ሳላፊነትም ሰጣቸው። ከሁሉ በላይ ጌታ ራሱ ወደ አትክልቱ ስፍራ በመምጣት ከአዳምና ከሔዋን ጋር ያወራ ነበር። እግዚአብሔር ፈጣሪ እና ባለቤታቸውን እንዲያውቁ ዕድል ሰጣቸው። ፍጹም የሆነ ዓለም ነበር።

ነገር ግን አንድ ቀን እባቡ መጣ።

## “በውኑ እግዚብሔር… አዝዟልን?”

በዘፍጥት ምዕራፍ ሦስት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በጣም አሳዛኙ እና ዘመን ተሻጋሪው ታሪክ ተመዘገበ።

አንድ ቀን አዳምና ሔዋን በተከለከለቸው ዛፍ አጠገብ ነበሩ፣

ስይጣንም በእባብ አምሳል በሚስጥር ለእነሱ ተገለጠላቸው። ስይጣን መሆኑን የምናውቀው መጽሐፍ ቅዱስ “ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ” (ራዕይ 12:9) ብሎ ስለሚገልጠው ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ እንዳቀደው ሁሉ ሠይጣንም ለሰው ልጅ እቅድ ነበረው።

> “እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ **በውኑ እግዚአብሔር** ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።” (ዘፍጥት 3:1)

ስይጣን ከወንዱ ጋር ከማውራት ይልቅ ከሴቷ ጋር ማውራትን መረጠ። ለሄዋን መጀመሪያ ያላትን ነገር ታስታውሳላችሁ።

### “በውኑ እግዚአብሔር… አዝዟልን?”

ስይጣን ሄዋን የእግዚአብሔርን ቃል እንድታምን አልፈለገም። የእግዚአብሔር ጥበብ እና ሥልጣን ጥያቄው ውስጥ እንድታስገባ አደረጋት። ሄዋን ሉሲፈር እንዳደረገው ፈጣሪን እንድትገዳደር ሞገታት። እስከዚህ ዘመንም ድረስ ዲያብሎስ እውነትን ይዋጋል፤ ምክንያቱም እውነት ስለሚያዋርደው እና ትጥቁን ስለሚያስፈታው ነው።

ሠይጣን የእግዚአብሔርን ባህርይ በማንቋሸሽ ሄዋን **የእግዚአብሔርን መልካምነት** እንድትጠራጠር አደረገ።

> “በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።”

ሠይጣን የእግዚአብሔርን ቃል አጣመመ ሕይወት እና ከአንዷ በስተቀር፥ ከሁሉም ዛፎች ላይ በነጻነት እንዲመገብ ያደረገው ለጋሱ ፈጣሪያቸው የከለከላቸው መልካም ነገር እንዳለ አድርጎ አቀረበ።

### “ሞትን አትሞቱም”

> “ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፦ ‘በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ

ፍሬ፤ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።'

እባብም ለሴቲቱ አላት፦ '**ሞትን አትሞቱም**፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።'"

(ዘፍጥረት 3:2-5)

ዲያብሎስ ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል እና መልካምነት እንድትጠራጠር ማድረግ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የተከለከለ ዛፍ ስለቀመሳችሁ የሞት ፍርድ ሊፈርድባችሁ አይችልም በማለት **የእግዚአብሔርንም ጻድቅነት** እንድትጠራጠር አደረጋት።

እግዚአብሔር ግን ግልጽ አድርጎት ነበር፦

"ሞትን አትሞቱም" (ዘፍጥረት 2:17)

ስይጣን ግን "ሞትን **አትሞቱም**" አለ።

የሰይጣን መሠረታዊ ስልት እስካሁን አልተቀየረም። የእግዚአብሔርን መልዕክት ማዛባቱን እና መካዱን ቀጥሏል። የእግዚአብሔርን ቃል፣ መልካምነት እና ጽድቅ እንድንጠራጠር ይፈልጋል።

ስይጣን ፈጣሪያችን ታማኝ እንዳልሆነ አድርገን እንድናስብ የሚለውን እንዳልሆነ አድርገን እንድናስብ ይፈልጋል።

## ሐይማኖተኛው ዲያቢሎስ

ዲያብሎስ ሐይማኖትን በጣም ይወዳል። ዛሬ በዓለም ላይ በ 10,000 የሚቆጠሩ ሐይማኖቶች አሉ። ስይጣን "ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ... **ስለሚያውቅ** ነው እንጂ" በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ወግኖ የተናገረ እንዲስመሰለ ታያላችሁ።

ሠይጣን ሁሉን ቻዩን ማስመሰል ይወዳል። የእግዚአብሔርን እውነት ወሰዶ ከራሱ ውሸት ጋር መቀላቀሉን ያውቅበታል። እሱ ጎበዝ ቀያጭ ፣ ኮራጅ ፣ ቀጂ እና አስመሳይ ነው። እጅግ በጣም ግራ የሚያጋቡ የዓለማችን ሐይማኖቶች ሳይቀር በውስጣቸው የእውነት ቅንጣት አለ። ተዓማኒ የሚያደርጋቸውም ያ ነው። በድጋሚ የዐረቦች ምሳሌ በደንብ ይገልጣቸዋል፦ "ተጠንቀቁ፦ አንዳንድ ውሸታሞች እውነት ይናገራሉ!"

አጭበርባሪ ሐይማኖት ለመጀመር ባደረገው የመጀመሪያ ጥረቱ ሠይጣን ለሄዋን "እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ"። ሠይጣን ለሄዋን "እንደ እግዚአብሔርም" ባላት ጊዜ የተናገረው ውሸት ነው ምክንያቱም ኃጢአትን የሚያደርግ የእግዚአብሔርን ስልጣን ለመንጠቅ እንደሚፈልገው ስይጣን እንጂ እንደ እግዚአብሔር አይሆንም። ነገር ግን ስይጣን "መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ" ባለ ጊዜ እውነቱ ተናግሯል ፣ ነገር ግን ይህንን ተከትሎ ስለሚመጣው መራርነት፣ መከራ እና ሞት አልተናገረም።

ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ስይጣን ስለ እግዚአብሔር ሲናገር የእግዚአብሔር የወል መጠሪያ(ያልሆነ) ይጠቀማል። ትአጠቀመው። ስይጣን አምላክ ሩቅና የማይታወቅ ነው ብላችሁ እስካሰባችሁ ድረስ በአንድ አምላክ ብታምኑ ደስተኛ ነው።

> "እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።"
> (ያዕቆብ 2:19)

ዲያቢሎስና አጋንንት በሁሉን ቻዩ አምላክ ፊት የሚነቀጠቀጡ አንድ አምላኪዎች ናቸው። ይሄ ጉዳይ ከበርካታ ምዕራፎች በኋላ አስደነጋጭ በሆነ ግልጥነት ይገለጣል። ስይጣን እና የወደቁ መላዕክት አንድ እውነተኛ አምላክ እንዳለ ያውቃሉ ነገር ግን በጣም ይጠሉታል!

እናንተ ፈጣሪ እና ባለቤታችሁን እንድታውቁት ፣ እንድትወዱት፣ እንድትታዘዙትና በእውነትና በመንፈስ እንድታመልኩት አይፈልጉም።

## ምርጫ

አዳምና ሄዋን ከአፍቃሪው አምላክ ቃልና ከዋና ጠላቱ ቃል አንዱንየሚመርጡበት ጊዜ ደርሷል።

የድሉ ቀመር ግልጽ ነው፦ የፈጣሪን ጥበብ መታመን። እንዴት ቀላል ነው። አዳምና ሄዋን ሊያደርጉት የሚገባቸው ነገር የእግዚአብሔርን በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተሰጠ፣ ስህተት አልባውን ቃል መጥቀስ ብቻ ነው። "ጌታ እግዚአብሔር "ክፉና ደግን ከምታሳውቀው ዛፍ እንዳትበሉ' ብሎናል። አንበላም አለቀ።"

አዳምና ሄዋን በማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ጽንተው ቢቆሙ ፈታኙ ይሸሽ ነበር። ነገር ግን ያንን አላደረጉም።

> “ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።” (ዘፍጥረት 3:6)

እሷም በላች። እሱም በላ።

ለቅዱሱ እና አፍቃሪው አምላክ ቃል ከመገዛት ይልቅ ለእግዚአብሔር ጠላት ተገዙ። ወደ ተከለከለው ክልል ገቡ።

አዳም የተከለከለውን ፍሬ ከቀመሰ በኋላ ውጤቱ ቅጽበታዊ ነበር።

> “የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ። እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።”
> (ዘፍጥረት 3:7-8)

ለውጡን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። ጌታ ሊጎበኛቸው በመጣ ጊዜ በመደሰት ፈንታ በፍርኀት እና በሐፍረት ተሞልተው ነበር።

እነዚህን ጥብቅ ተግባቦታዊ ፍጡራን ከአፍቃሪ ጌታቸው እንዲሸሹ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው? ሁሉን ከሚያየው ፈጣሪ መደበቅ እንችላለን ብለው እንዲያስቡ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው? የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አካላቸውን በቅጠል ለመሸፈን የፈለጉት ለምንድን ነው?

ኃጢአትን ስርተዋል።



# 12

# የኅጢአትና የሞት ሕግ

"ኅጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው።"
—የናዝሬቱ ኢየሱስ (ዮሐንስ 8:34)

አዳምና ሄዋን ፈጣሪ ባለቤታቸውን አልታዘዙም። ልክ እንደ ሠይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ተቋርጦ የኅጢአት ባርያ ሆነዋል። የአባታቸውን ግልጽ ትዕዛዝ እንደተላለፉ ልጆች አዳምና ሄዋን ከሚወዳቸው እና ከሚንከባከባቸው ከእሱ ጋር መሆን አልፈለጉም። የደስታ እና በራስ የመተማመን ስሜት በፍርኃት ፣ በርኩሰት እና በሐፍረት ተተካ።

> "የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።"
> (ዘፍጥረት 3:8)

አዳምን ሄዋን አሁን በኅጢአት ወድቀዋል፤ ይሄም ከፈጣሪያቸው እና ጌታቸው እንዲደበቁ አድርጓቸዋል። አዲስ ያገኙት ህሊና ክፉን እና ደጉን እንዲለዩ አድርጓቸዋል፤ በደመ ነፍስ ቅዱሳን ሰዎች ብቻ በቅዱስ እግዚአብሔር ፊት እንደሚኖሩ አሰተምሯቸዋል። አዳምና ሄዋን በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን አይደሉም ይህንንም ያውቃሉ። በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ያለው ግንኙነት ተቋርጧል።

ግንኙነቱ አብቅቶለት ነበር።

## የተቆረጠ ቅርንጫፍ



አንድ ቀን ከመስገድ አቅራቢያ ከጥቂት ወንዶች ጋር እየተጨዋወትኩ ነበር፤ ርእሱም ወደ ኅጢአትና ሞት ተለወጠ።

ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍ ቆረጥኩና “ይሄ ቅርንጫፍ ሞቷል ወይስ ሕይወት አለው?” ብዬ ጠየቅኳቸው።

አንዱ ሰውዬ “እየሞተ ነው” ብሎ መለሰ።

ሌላኛው “ሞቷል” አለ።

እኔም “አረንጓዴ መሆኑን እያየህ እንዴት ሞቷል ትላለህ?” ስል ገሰጽኩት።

“ያለ ይመስላል። ነገር ግን ከሕይወት ምንጩ ስለ ተለየ ሞቷል።” ብሎ መለሰ።

“በትክክል” ብዬ መለስኩለት “እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛውን የሞት ፍቺ ስጥተኸል። ሞት ማለት መጥፋት ማለት አይደለም ፣ ሞት ማለት ከሕይወት ምንጭ መለየት ማለት ነው። የምንወደው ሰው ሲሞት ሬሳው ከመቀበሩ በፊት ‘ሞቷል’ የምንለው ለዚህ ነው። ያንን የምንልበት ምክንያትም ስውየው መንፈስ ሰጋውን ተለይታለች። ሞት ማለት መለየት ማለት ነው።”

በመቀጠልም እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠውን ትዕዛዝ ከለስኩላቸው። ከዚያም በኋላ እንዲህ ስል ጠየቅኳቸው “አዳም በእግዚአብሔር ላይ ኅጢአት ቢሰራ እግዚአብሔር ምን የሚል ይመሰላችኋል?የተከለከለውን ፍሬ ከበላ ሐይማኖታዊ ተግባራትን መጸለይ፣መጾም መጸለይ ፣ ምጽዋት መስጠትና መስገድ ወይም ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለብህ የሚለው ይመስላችኋል?”

“በፍጹም እግዚአብሔር አዳም ይሞታል ብሏል” ሲሉ መለሱ

“በትክክል። እግዚአብሔር ያንን ነገር ግልጽ አድርጎታል፦ የኅጢአት ቅጣት ሞት ነው። ነገር ግን ንገሩኝ አዳምና ሄዋን እግዚአብሔርን ባለመታዘዘ የተከለከውን ፍሬ በልተዋል፤ ነገር ግን ወዲያውኑ ሞተዋል?”

“አልሞቱም።” ሲሉ መለሱ።

“እንግዲህ ታዲያ “ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ሞትን ትሞታላችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?”

ከዚያ በመነሳት የእግዚአብሔርን የሞት ፍቺ ማብራራት ጀመርኩ፦ ፈጣሪን ላለመታዘዝ በመምረጡ ባለ ሦስት ገጽታ መለያየትን በራሱ ላይ አመጣ።

## ባለ ሦስት ገጽታ መለያየት የተፈጠረው ከሐጢአት የተነሳ ነው


### 1. .መንፈሳዊ ሞት ፦ የሰው መንፈስ እና ነፍስ ከእግዚአብሔር መለየት።

አዳምና ሔዋን ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ሳጢአት በሰሩ ጊዜ መንፈሳዊ ሞትን ሞተዋል። ከዛፍ ላይ እንደ ተቆረጠ ቅርንጫፍ አዳምና ሔዋን ከጌታ ጋር ያላቸው የቅርብ ግንኙነት ሞቷል። የአዳምና የሔዋን ዝርያዎች በሙሉ መንፈሳዊውን ሞት የሞተው "ቅርንጫፍ" አካል ናቸው።

"ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ..." (1 ቆሮንቶስ 15:22)

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቢያስተምርም እንኳን ፣ የሰው ልጅ በሙሉ የአዳም ዘር ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች አዲስ የተወለዱ ሕጻናት ንጹህና ሳጢአተኛ ባህርይ የሌላቸው ናቸው ብለው ያምናሉ።

ያንን የተቆረጠ ቅርንጫፍ አስቡት።



ከዛፉ በመነጠሉ የሞተው የትኛው ክፍሉ ነው? መላው ቅርንጫፉ፣ ጫፉ ላይ የምትገኘው ትንሽ ለምለም ቅጠል ሳይቀር ሞታለች። እነዚህ ለምለም ቅርንጫፎች የሚናገሩ ቢሆን፣ ምናልባት የሚከተለውን ሊሉ ይችሉ ይሆናል። "ቆይ አንዴ ! ከዛፉ ላይ መቆረጡ የቅርንጫፍጥፋት አይደለም! ሌላ ሰው ባደረገው ነገር እኛ ተጠያቂ ልንሆን አንችልም!" ነገር

ግን ጦሱ ደርሶባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም አጠቃላይ የሰው ልጅ ዝርያ “በአዳም” ነው፡፡ ሁላችንም የተለየው ፣የተቆረጠው “ቅርንጫፍ” አካል ነን ስለዚህም ጦሱ ደደርስብናል፡፡ ወደዳቸሁም ጠላቸሁም አዳም ሐጢአት በሰራ ጊዜ ራሱን እና ከእሱ ሊመጣ ያለውን የሰው ዝርያ በሙሉ በክሎታል፡፡

ይሄንን እየጻፍኩ የምገኝበት መንደር ውሃ የሚያገኘው ከበርካታ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው የሴኔጋል ወንዝ ነው፡፡ መንደራችን ውስጥ የጉድጓድ ውሃ አለ ነገር ግን ማንም ሰው ከዚያ ጉድጓድ አይጠጣም፡፡ ለምንድን ነው የማይጠጣው? ምክንያምቱም ጉድጓዱ ተበክሏል፡፡ ውሃው ሳሊን አለው፡፡ እያንዳንዱ ከዚያ ጉድጓድ ውስጥ የሚወጣው ውሃ በጨው የተበከለ ነው፡፡ ጠብታው እንኳን ፣ በፍጹም አንድ ጠብታ እንኳን ንጹህ አይደለም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ከአዳም የተወለደ የትኛውም ሰው በኀጢአት ተበክሏል፡፡ ትንንሽ ልጆች እንኳን በተፈጥሯቸው ኀጢአትን ያደርጋሉ፡፡ ኀጢአት የማንነታቸው አካል ነው፡፡ መልካም እና ደግ መሆን አስቦ አቅዶ መጣር እና ትግልን ይጠይቀናል፤ ራሰ ወዳድ መሆን እና ጉዳት ማድረስ ግን ምንም አይነት ጥረትን አይጠይቀም፡፡ በደመነፍስ ኀጢአት የምንሰራበትን ምክንት ነብዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ያብራራል፦

> “እነሆ፥ **በዓመፃ** ተፀነስሁ፥ እናቴም **በኃጢአት** ወለደችኝ፡፡” (መዝሙር 51:5) “ኀጥኣን **ከማኅፀን** ጀምረው ተለዩ፤ ከሆድም ጀምረው ሳቱ፥ ሐሰትንም ተናገሩ፡፡” (መዝሙር 58:3) “ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም፡፡” (መዝሙር 14:3)

በሴኔጋል ውስጥ የሚገኙት የወሎፍ ሰዎች ይህንን እውነት ለመረዳት የሚያግዙ በርካታ ምሳሌዎች አሏቸው፡፡

ለምሳሌ “አይጥ መሬት የማይቆፍር ልጅ ሊኖራት አይችልም” በተመሳሳይ መልኩ በኀጢአት የተበከለው አዳም ኀጢአት የማያደርግ ልጅ ሊወልድ አይችልም፡፡

ሌላኛው ምሳሌ ደግሞ እንዲህ ይላል “ተስቦ መጀመሪያ የተያዘው ላይ አያበቃም፡፡” ያሳዝናል ፣ ነገር ግን እውነት ነው፡፡ ነገር ግን በዘር እንደተገኘ ጉዳት ወይም ተላላፊ በሽታ የአዳም ሐጢአት ወደ እኛ እና ወደ ልጆቻቸን ተላልፏል፡፡

> “ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት **በአንድ ሰው** ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም **ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤**” (ሮሜ 5:12)

የመጀመሪያውን ሳረግ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ “ኅጢአት በአንድ ሰው ገባ” እና የመጨረሻው ሳረግ “ሁሉ ኅጢአት አደረጉ” ይላል። ሁላችንም በመወለድም በልምምድም ኅጢአተኞች ነን። እኛ ለምናደርገው ኅጢአት አዳምን ልንወነጅለው አንንችልም። አንድ ጊዜ ሰው ክፉውን ከደጉ ለመለየት የሚያስችል አቅም ላይ ከደረሰ እግዚአብሔር እሱንም እሷንም ተጠያቂ ያደርጋቸዋል።[126]

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

> “ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።” (ኢሳያስ 59:2)

ጠቅላላው የሰው ልጅ ቅርንጫፍ ከሰው ልጅ ተለይቷል። ሰውን በመንፈሳዊ ማንነት “በመተላለፍ እና ሐጢአት ሞቷል።” (ኤፌሶን 2:1)

## 2. አካላዊ ሞት፦ የሰው መንፈስ እና ነፍስ ከአካሉ መለየት።

አዳምና ሄዋን ኅጢአትን ስአሩ ጊዜ መንፈሳዊ ሞትን መሞት ብቻ ሳይሆን፣ በአካልም መሞት ጀምረው ነበር። የተቆረጠው ቅርንጫፍ ላይ የሚገኙ ቅጠሎች ወዲያውኑ እንደማይደርቁ ሁሉ የአዳምና የሔዋን አካል ኅጢአትን በሰሩ ጊዜ ወዲያውኑ አልሞቱም። ቢሆንም እንኳን ስጋቸው ሊያመልጡት በማይችሉት ጠላት በሞት ተወርሮ ነበር።

ለአዳምና ሔዋን እና ዘሮቻቸው አካላዊ ሞት እስኪደርስባቸው ድረስ የጊዜ ጉዳይ ነው። “ሞት ፈጣኗን ግመል ተሳፍሯል” ይላል የዐረቦች ምሳሌ። ማንም ሰው ሞትን አያመልጥም። የእግዚአብሔር ቃል በዚህ መልኩ ያሰቀምጠዋል፦

> “ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው” (ዕብራውያን 9:27)

## 3. ዘላለማዊ ሞት ፦ የመንፈስ ፣ ነፍስ እና ስጋ ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት

ሕያው ቅርንጫፍ ቅጥሎች፣ አበቦች እና ፍሬ እንዲኖረው ተደርጎ ተስርቷል። የሞቱ ቅርንጫፎች ተሰብስበው ይቃጠላሉ። አዳም በእግዚአብሔር ላይ ኅጢአት በሰራ ጊዜ የተፈጠረበትን ዓላማ አስተጓጎለ። ይኼም ዓላማ እግዚአብሔርን ማክበርና ለዘላለም ከእሱ ጋር መኖር ነበረ። ለዘላለም እንዲኖር የተፈጠረው ሰው ፈጣሪና ባለቤቱን አልታዘዘም። ቅጣቱም ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት ነው።

ጌታ በምሕረቱ ለአዳምና ለሔዋን ኅጢአት መድሐኒት ካላዘጋጀ በስተቀር ፣ አካላቸው ሞተ በኋላ ለዲያብሎስ እና ለአጋንንት ወደ ተዘጋጀውና ለዘላለም ወደሚቆዩበት "የቆሻሻ መጣያ" መሄዳቸው አየቀሬ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሞት "ሁለተኛ ሞት" ሲል ይጠራዋል፤ ምክንያቱም ከአካላዊ ሞት በኋላ ስለሚመጣ ነው። በተጨማሪም "ዘላለማዊ ቅጣት"[127] ተብሎ ተጠርቷል። ሰዎች አንድ ቀን ሰለሚወጡበት የነፍስ ማጥሪያ ስፍራ (ፐርጋቶሪ) የሚወራው የሰው ልጅ ፈጠራ ነው።

"ዘላለማዊ ቅጣት" የማይገባ እና ምክንያታዊ ካልመሰላቸሁ ፣ ምናልባት የእግዚአብሔርን ማንነት ፣ የኅጢአትን ክፋት እና የዘላለምን ጽንሰ ሐሳብ አልተረዳቸሁ ይሆናል።

ወድ ኋላ ስለ እግዚአብሔር ንጽሕና እና ሰለ ሐጢአት ርኩሰት እንነጋገራለን።

ስለ ዘላለም ጽንሰ ሐሳብ ሁላችንም እንደምናምነው ማጣቀሻችን ጊዜ ስለሆነ ዘላለም የሚለው ቃል ራሱ የአዕምሮ ብቃታችንን ይፈትናል።

ዘላለም ጊዜ አልባ ነው።

አንድ ሰው ቢሊዮን ዓመታትን በሲዖል ያሳልፋል ብለን ካሰብን አስተሳሰባችን የተሳሳተ ነው። ዘላለም የዓመታት ድምር ውጤት አይደለም። አሁን የምንገኘው ዘላለም ውስጥ ነው። ሰዎች ሊያመልጡ ወደማይችሉበት ክልል ከገቡ ፣ ምጡቅ ምክንያታዊነቱን የዚያን ጊዜ ይዳሉ። ሲዖል ውስጥ ስለገባው ሐብታም ሰው ታሪክ (ምዕራፍ 3) ታሰታውሳላቸሁ ? አሁንም እዚያው ነው ያለው።

እግዚአብሔር ወደ መንግስተ ሰማያት የምትገቡበትን መስፈርት ግልጽ አስቀምጧል፦

"...ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።" (ራዕይ 21:27)

በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ማቅማማት አይኖርም። የእግዚአብሔር የተፈጥሮ ሕግ የተቆረጠው ቅርንጫፍ እንዲሞትና እንዲጠወልግ እንዳደረገው ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕግም መንፈሳዊ፣ አካላዊ እና ዘላለማዊ **የመለየትን** ቅጣት ያስከትላል።

## ሐጢአትና ሐፍረት

አዳምና ሔዋንን ለመጨረሻ ጊዜ በአትክልቱ ውስጥ በሚገኙ ዛፎች ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ሲሞክሩ አይተናቸዋል፤ አሁን ወደዚያ ቦታ የምንመለስበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

ኃጢአት ከመስራታቸው በፊት አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ክብር እና ፍጽምና ተከበው ነበር። በፈጣሪያቸው ፊት በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ደስተኞች ነበሩ። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕግ ባፈረሱ ጊዜ ራሳቸውን በተለየ ሁኔታ አዩ። አሁን ምቾት አልተሰማቸውን ነበር ፣ ምክንያት አካላቸው ራቁት ስለሆነ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ራቁትነት ስለነበረባቸው ነው።

ከመተላለፋቸው በፊት አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ላይ የሚያተኩሩ ነበሩ እና "አይተፋፈሩም ነበር።" (ዘፍጥረት 2:25 አመት) አሁን ግን ተፈጥሯዊ ባልሆነ መንገድ ራሳቸውን ስላወቁ ቅዱሱ እግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ተሰማቸው። እነሱ አሁን ቅድስና የሌላቸው ሆነዋል። በእግዚአብሔር ንጽህና እና ብርሃን ፊት መሆን አልፈለጉም ነበር። ስራቸው ክፉ ከመሆኑ የተነሳ "ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤" (ዮሐንስ 3:19-20) ባትሪ ሲበራባቸው ለመደበቅ እንድሚሯሯጡ እንጭራሪቶች መደበቂያ እየፈለጉ ነበር።

አዳምና ሄዋን ተጋልጠውና አፍረው ነበር። ፍጹም በሆነው የአትክልት ቦታ ባዕድነት ተሰማቸው።የእግዚአብሔርም ድምጽም በፍርሽት ሞላቸው። ከቅዱሱና አፍቃሪው አምላካቸው ጋር ከዚህ በላይ መኖር አልፈለጉም። ቢሆንም እንኳን ሊፈልጋቸው ወደ አትክልት ስፍራ መጣ።

"የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን" (ሉቃስ 19:10አመት) የእግዚአብሔር ባሕርይ አካል ነው።

## እግዚአብሔ ር የሰው ልጅን ይፈልጋል።

“እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ **ወዴት ነህ?** አለው።እርሱምአለ፦በገነትድምፅህንሰማሁ፤ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?” (ዘፍጥረት 3:9-11)

የመጀመሪያው እግዚአብሔር በጽሑፍ የቀረበው የመጀመሪያው ጥያቄ እስቲ ልብ ብላችሁ ተመልከቱት።

“ወዴት ነህ?”

እግዚአሔብር በዚህ በፍቅር በተሞላና ውስን ዘልቆ በሚገባ ጥያቄ እንዲረዳ የፈለገው ኀጢአት በእሱና በሚስቱ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ነው። ትዕዛዙን መተላለፉን እንዲረዳ ፈልጓል። በእነሱ እና በቅዱሱ ጌታ መካከል ኀጢአት ጣልቃ እንደገባ እንዲረዱ ፈልጓል።

የችግራቸው ሁሉ ምንጭ ኀጢአት ነው። ሐፍረት እንዲሰማቸውና በዛፍ እና በቅጠል እንዲሸሸጉ ያደረጋቸው ኀጢአቸው እንደሆነ እንዲያውቁ ፈልጓል። ነገር ግን አዳም እና ሄዋን ከእግዚአብሔር ሊደበቁ አይችሉም ፤ የእሱንም ጻድቅነት እና ሁሉን አወቅ ፍርዱን ሊያመልጡ አይችሉም።

## የኀጢአት ደሞዝ

እግዚአብሔር አዳምን “ከእርሱ በበላህ ቀን **ሞትን ትሞታለህና**።” (ዘፍጥረት 2:17) ሲለው እየቀለደ አልነበርም። በፈጣሪ ላይ የሚያምጹ ከእሱ መለየት እንድሚገባቸው ውስጣችን ያውቀዋል።

ብዙዎቻችን “ከፉዎቹ” ሰዎች የሚገደሉባቸው እና “መልካሞቹ” የሚያሸንፉባቸውን ፊልሞች አይተናል። ለ “ከፉዎቹ” እናዝናለን? በፍጹም የሚገባቸውን ያገኙ መሆኑን እንረዳለን። ፍንትው ያለው እውነታ በእግዚአብሔር ዐይን የአዳም ዘሮች “ከፉዎች” ናቸው።

“ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም።” (መዝሙር 14:3)

እንደ ፈጣሪ የፍትህ መለኪያ ሁላችንም የሞት ፍርድ ይገባናል። የእግዚአብሔር መጽሐፍ ይህንን እንዲህ ይገልጠዋል፦

"የሐጢአት እና የሞት **ሕግ**" (ሮሜ 8:2)

የሐጢአትና የሞት ሕግ እያንዳንዱ እግዚአብሔርን የበደልው በደል ከእግዚአብሔር በመለየት ይቀጣል። ማንም አያመልጥም። ሐጢአት ሞትን ያመጣል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ታማኝ ባህርይ ስላለው እግዚአብሔር ይህንን ሕግ ያብራል። በአንድ የኀጢአት ድርጊት የመጀመሪያዎቹ ዝርያዎቻችን ከእግዚአብሔር የጽድቅ የሕይወት መንገድ ራሳቸውን ለይተው የሰይጣን ፣ የሞትና የኀጢአት መንግስት ተቀላቀሉ።

ከዛፍ እንደተለየ ቅርንጫፍ በቅጽበትም **መንፈሳዊ** ሞትን ሞቱ። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ሞተ።

በተጨማሪም ልክ እንደተቆረጠው ቅርንጫፍ **አካላዊ** ሞት መሞት ጀምሩ። የጊዜ ጉዳይ እንጂ አካሎቻቸው ወደ አፈር መመለሳቸው አይቀርም።

ከሁሉ የከፋው እግዚአብሔር ለኅጢአታቸውን ለሐፍርታቸው መድሐኒት ካላዘጋጀ በስተቀር ለዘላለም የመሞት፣ ለዲያብሎስና እና ለአጋንንት ወደተዘጋጀው **ዘላለማዊ** እሳት ውስጥ በመጣል ከእግዚአብሔር ጋር የመለየትን አሰቃቂ ዕጣ ፈንታን ተጋፍጠዋል፤

መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ ነው፦

"ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች" (ሕዝቅኤል 18:20)

"የኀጢአት ደሞዝ ግን ሞት ነው" (ሮሜ 6:23)

"ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።" (ያዕቆብ 1:15)

ይህንን ፍጥጥ ያለ እውነት የኀጢአትና የሞት ሕግ ያለው በመልካም ምክንያት ነው። ሕግ ነው።

የኀጢአት ቅጣት መፈጸም አለበት።

ይፈጸማል።



# 13

# ምሕረትና ፍትሕ

እግዚአብሔር ሊያደርገው የማይችለው እና ሰው ሊያደርገው የሚችለው ነገር ምንድን ነው?

ይህንን እንቆቅልሽ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ይመልሰዋል፡፡

> “ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፤ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም፡፡ እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን?”
>
> (ዘኍልቊ 23:19)

በየቀኑ ሰዎች ይዋሻሉ፣ ሐሳባቸውን ይቀይራሉ ፣ በተጨማሪም ቃላቸውን ያጥፋሉ፡፡ እግዚአብሔር እነዚን ሊያደርግ አይችልም፡፡ ሊለካ በማይችል ሁኔታ ፍጹም የሆነው እሱ ይህንን ሊያደርግ አይችልም፡፡

> “ራሱን ሊክድ አይችልም፡፡” (2ጢሞቴዎስ 2:13)

ከጥቂት ጊዜያት በፊት የሚከተለው ኢሜይል ደርሶኝ ነበር፦

መልዕክት | ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

አንተ አላህ ዝም ብሎ ይቅር አይልም ትላለህ። የአላህ እጅ በአላህ ሕግ ታስሯል ትላለህ። እንዲህ ብለህ ጽፈኸል “እግዚአብሔር ራሱን ከመካድ እና የራሱን ሕግ ችላ ከማለት ውጪ የትኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል። ” ለምንድን ነው ሩህሩሁ ፈጣሪ ምህረት የማድረግ ችሎታው እያለው ምህረት ለሚጠይቁት አገልጋዮቹ ምህረት ማድረግ የማይችለው ለምንድን ነው? ... ይሄ ምንም አይነት ስሜት ሊሰጥ እንደማይችል ልብ ብለኸል? ምንም እንኳን እንዲህ አይነት ሕግ አውጥቶ

ቢሆን ሁሉን ቻይ ስለሆነ ወዲያውኑ ሊያፈርሰው ይችላል! የአላህ ታላቅ ኀይል በየትኛው መንገድ ተገድቧል ብሎ ማሰብ ምክንያታዊ ያልሆነ ሙግት ነው። ከፈለገ ሁላችንንም ጠቅልሎ ሲዖል ሊያስገባን ይችላል። ነገር ግን እሱ ሩህሩሁ ስለሆነ በፍርድ ጊዜ እንዲሳካላቸው አገልጋዩን ይቅር ለማለት ዘዴ ይፈልጋል። አላህ ለሁላችንም ምህረት ያደርግልን፥ ሁላችንም በእሱ ፊት ተሰብስበን በግላችን በሚፈርድብን ቀን ይቅርታና ምህረቱን ይስጠን!

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ባየነው መሠረት በሰው ልጅ አመክንዮ ውስጥ ክፍተትን ታያላችሁ? ፈጣሪያችን ያወጣቸው ሕግጋት ችላ ሊልና ቅዱስ ባህርይውን ሊቃረን ይችላልን?

## ፍትሕ የሌለበት ምህረት

ዳኛው መቀመጫው ላይ ተቀምጧል። እሱ ፊት የቆመው ሰው በባንክ መዝረፍ እና በጭካኔ ግድያ ጥፋተኛ የሆነ ሰው ነው። ፍርድ ቤት በምሥክሮች ተሞልቷል። የተገደለው ሰው ሚስትና ልጆች ከተዘረፈው ባንክ ሰራተኞች ጋር ተገኝተዋል። የዜና ዘጋቢዎች ሁኔታውን ለመዘገብ ዝግጁ ናቸው።

ይሄ ነፍሰ ገዳይ ሊሰጠው የሚችለው ፍርድ ምን አይነት ይሆን? የሞት ፍርድ? የዕድሜ ልክ እስራት ያለ አመክሮ?

በፍርድ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ እንዲነሱ ታዘዙ።

ዳኛው ጥፋተኛውን ሰውዬ ፊት ለፊት እየተመለከተ እንዲህ አለ "በምጽዋት መስጠት እና በዘወትር ጸሎት ታማኝ መሆንህን አይቻለሁ። እነዛን የጸሎት ጨሌዎች በምታንቃጭልበት ወቅት ጣቶችህ አስገራሚ ናቸው። በዚያ ላይ እንግዳ ተቀባይ መሆንህንም ሰምቻለሁ፤ ማዕድህንም ከእንግዶች ጋር እንደምትካፈል ሰምቻለሁ። ለትንሽ ቢሆንም የሰራኸው መልካም ስራ የሰራኸውን ጥፋት በልጧል። ይቅርታ ተደርጎልኻል በነፃ ሂድ።"

ዳኛው ታላቅ ዱብ ዕዳ ይፈጥራል።

ድንጋጤ አየሩን ይቆጣጠረዋል ፤ የቁጣ ጉርምርምታዎች ክፍሉን ይሞሉታል...

እንዲህ አይነት የፍርድ ቤት ትዕይንት ተሰምቶ አያውቅም። ሚዛን የጥፋተኛውን ጥፋት መመዘን በምልክትነት በማሳየት ያገለግል ይሆናል፤ ነገር ግን አንድ ጊዜ አንድ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ተገቢው ፍርድ መሰጠት አለበት። ጥፋተኛው "መልካም ሥራ" ሰርቷል ወይም አልሰራም የሚለው አስፈላጊ አይደለም። ያንን ሁላችንም እናውቃለን።

ይሄ መልካም ሥራ ከክፉ ስራህ ይበልጣል የሚለው "አሰራር"

በሰው ልጅ ፍርድ ቤት ውስጥ የማይሰራ ከሆነ በእግዚአብሔር ሰማያዊ ፍርድ ቤት ውስጥ ቢሰራስ ፍትሐዊ ይሆናል?

## ጻድቅ ፈራጅ

እግዚአብሔር በምናባዊ ታሪካችን ውስጥ እንዳለው ዳኛ አይደለም፡፡ ከመጠሪያ ስሞቹ መካከል አንዱ "**ጻድቅ** ፈራጅ" (2ጢሞቴዎስ 4:8) ነው፡፡ ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ነበዩ አብርሐም "የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?" (ዘፍጥት 18:25) ብሎ ጠይቆ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ምህረትን ለማሳየት ፍትሑን ችላ አይልም፡፡ ይህንን ቢያደርግ የጽድቅ ዙፋኑን መሰረት ያናጋል እና ቅዱሱን ስሙን ያራክሳል፡፡

> "የዙፋንህ መሠረት **ጽድቅና ፍርድ** ነው፤ **ምሕረትና እውነት** በፊትህ ይሄዳሉ፡፡" (መዝሙር 89:14)

ኢሜይል እንዳጸፈልኝ ሰው ከሆነ እግዚአብሔር ራሱ ያወጣውን ሕግ ችላ ብሎ "ታላቁን ኅይሉን" ሊጠቀም ይችላል ማለት ማለትም "የምድር ሁሉ ዳኛ" የሆነው ከሚዳኛቸው ኅጢአተኞች ያነሰ ጻድቅ ነው እንደ ማለት ነው፡፡

እኛ የሰው ልጆች ጥልቅና ውስጣዊ ፍትሐዊነት ሲኖረን፣ ፈጣሪያችን እንዲህ አይነት የፍትሐዊነት ስሜት እንዳለው የሚያሳየውን ግልጽ እውነት መቃወም ምን አይነት እንግዳ ነገር ነው! በልባችን ክፋትን የማይቀጣ ዳኛ "ታላቅ" የሚያሰኘው ነገር እንደሌለ እንረዳለን፡፡

ነብዩ ኤርሚያስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦

> "ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህ ብዙ ነው፡፡" (ሰቆቃው ኤርሚያስ 3:23-24)

ነብዩ "ተለዋዋጭነትህ ታላቅ ነው!" ወይም "ልፍስፍስነትህ ታላቅ ነው!" አላለም፡፡ እንዲዚህ አይነት ልፍስፍስ አምላክ ምን ተስፋ ሊሆነን ይችላል? እግዚአብሔር በታማኝነቱ ታላቅ ነው፡፡ ብዙዎች በዘለማድ እግዚአብሔርን "ሩህሩህና አዛኝ" ይሉታል፣ የሚረሱት ግን እሱ "ታማኝና ጻድቅ" (1ዮሐንስ 1:9) መሆኑን ነው፡፡

ከአንድ ወገን የሆነ አመለካከት ስለ እግዜአብሔር የተሳሳተ አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡

## የእግዚአብሔር ሚዛናዊ ባህርይ

ወፍ ለመብረር ከፈለገች የትኛው ክንፏ ይጠቅማታል፣ የግራው ወይስ የቀኙ?

በግልጽ እንደምናውቀው ወፎች ለመብረር ሁለቱም ክንፍ ያስፈልጋቸዋል! ወፍ በአንድ ክንፏ ልትበር ትችላለች፣ የሚል የትኛውም ሰው የወፎችን ጠባይ የስበትን ሕግና የአየር ላይ እንቅስቃሴን ሕግ አልተረዳም ማለት ነው።

በተመሳሳይ መልኩም እግዚአብሔር ፍትሑን ትቶ ምህረት ያሳያል፣ የሚል ሰው የእግዚአብሔርን ባሕርይ እና የኃጢአትንና የሞትን ሕግ አልተረዳም።

የእግዚአብሔር ምህረት እና ፍትህ ሁልጊዜ ፍጹም ሚዛናዊ ናቸው። ንጉሱ ዳዊት እንዲህ ብሏል፦

"አቤቱ፣ ምሕረትንና ፍርድን እቀኝልሃለሁ።"

(መዝሙር 101:1)

አሰቃቂ ኃጢአት የሰራው ዳዊት የእግዚአብሔር ምህረት እንደማይገባው ተረድቷል። በፍቺ ደረጃ ካየነው ምሕረት የማይገባ ነው።

**ፍትህ** የሚገባንን ቅጣት መቀበል ነው።

**ምሕረት** የሚገባንን ቅጣት አለመቀበል ነው።

ዳዊት ለእግዚአብሔር ምስጋናን እንዲዘምር ያደረገው ምክንያት ጌታ ጽድቁን ችላ ሳይል፣ ለማይገባቸው ሐጢተኞች ምሕረት ለማሳየት ዘዴ ስለ ቀየሰ ነው። ዳዊት ሰል "ምሕረትና ጽድቅ" የዘመረው ለዚህ ነው።

ለቅዱስ አምላካችን ኃጢአት ይቅር ለማለት ቀላል ነገር አይደለም። የኃጢአተኛው መተላለፍ በተገቢው ሁኔታ ሳይፈረድበትና ሳይቀጣ ኃጢአተኛን ይቅር አይልም። እንደ ሰው ልጆች፣ አንድ ሰው ከሳዘነን እሱን እንዲህ ልንለው እንችላለን "ይሁን። እርሳው። ያን ያህል ከባድ ነገር አይደለም።" ያንን ሰው በዚህ አይነት መንገድ ይቅር ልንለው እንችል ይሆናል፣ ቅዱስ ፈራጅ እንዲህ አያደርግም።

የእግዚአብሔር ምሕረት የእግዚአብሔርን ፍትህ አይቃምም። "እወድሃለሁ ኃጢአትህን ግን አልቀጣም" በፍጹም አይልም። እንዲሁም "ኃጢአት ስለ ሰራህ አልወድህም።" አይልም። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይወዳል፤ ኃጢአታቸውን መገደብና መቅጣት አለበት።

እግዚአብሔር እንዲህ ያለ ከሆነ ለተፈረደባቸው ኃጢአተኞች ምህረት ሊያደርግ የሚችለው እንዴት ነው?

## ምሕረት እና ጽድቅ

የአዳምንና የሄዋንን ሁኔታ አስቡት።

እግዚአብሔር **አምላክ አፍቃሪ እና መሐሪ** ስለሆነ አዳምና ሄዋን ከእሱ ለዘላለም እንዲለዩ እና በዘላለማዊ እሳት ውስጥ እንዲገቡ አልፈለገም።

"...ጌታ...ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።" (2ጴጥሮስ 3:9)

ነገር ግን **እግዚአብሔር ቅዱስ እና ጻድቅ** ነው፣ ነገር ግን የአዳምን እና ሄዋንን ኃጢአት ቸል ሊል አይችልም። መቅጣት አለበት።

"ዓይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው፥ ጠማምነትንም ትመለከት ዘንድ አትችልም" (ዕንባቆም 1:13)

ታዲያ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል? ኃጢአተኛውን ሳይቀጣ ኃጢአትን የሚቀጣበት መንገድ አለ። የሐጢአት ርኩሰት ሊወገድ እና ፍጹም ቅድስና ሊታደስ የሚችለው እንዴት ነው? ነብዩ ኢዮብ "**ሰውስ** በእግዚአብሔር ፊት **ጻድቅ** መሆን እንዴት ይችላል?" (ኢዮብ 9:2) የሚያረካ ምላሽ ይኖረው ይሆን? እግዚአብሔር ይመስገን አለው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር እንደ አዳምና ሄዋን ያሉ የተኮነኑ ኃጢአተኞችን የሚያጸድቅ "ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ" ብቻ ሳይሆን ለእኔ እናንተም እንዚያው ነው (ሮሜ 3:26) ጽድቁን እያስፈጸመ ለእናንተ ምህረት እንዴት እንዳቀረበ ታውቃላችሁ?

መልሱን ወደፊት እናየዋለን። ጉዞውን ቀጥሉ።

## የእኔ ስህተት አይደለም

ለአሁኑ ፈራጃቸው በሆነው ፈጣሪያቸውና በኃጢአት ወደቁት አያቶቻችን መካከል የተደረገውን የሐሳብ ልውውጥ እንመልከት።

> “እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም አለ፦ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ። እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፦ ይህ ያደረግሽው ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፦ እባብ አሳተኝና በላሁ።” (ዘፍጥረት 3:9-13)

እግዚአብሔር አዳምን እና ሄዋንን የጠየቃቸው ለምንድን ነው?

እሱ የጠየቃቸው እንድ ወላጅ ልጁ ምን እንዳጠፋ እያወቀ አልታዘዝ ያለውን ልጅ በሚጠይቀበት መልክ ነው። እግዚአብሔር አዳምን ሄዋን ኅጢአትና ጥፋታቸውም እንዲገነዘቡ ፈልጓል። ነገር ግን ኅጢአታቸውን ከማመን ይልቅ ሁለቱ እርስ በርሳቸው መወነጃጀል ጀመሩ።

አዳም እግዚአብሔርን እና ሄዋንን ከሰሳቸው፦ የእኔ ስህተት አይደለም! የሰጠኸኝ ሴት የእሷ ስህተት ነው።

ሄዋን እባብን ጥፋተኛ አደረገች፦ እባብ አሳተኝ!

ሰዎች እንጂ ሮቦቶች ስላልሆኑ እግዚአብሔር እያንዳንዳቸውን ለጥፋታቸው ተጠያቂ አደረጋቸው። እነሱም ከራሳቸው በስተቀር የሚወነጅሉት ማንም የለም።

> “ማንም ሲፈተን፦ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ **በራሱ ምኞት** ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።” (ያዕቆብ 1:13-15)

የፈጣሪን ዕቅድ ከመከተል ይልቅ አዳምና ሔዋን ወደ ኅጢአት እና ሞት የመራቸውን “የራሳቸውን ምኞት” ተከተሉ።

ሄዋን በሰይጣን ተታላና ተሞኝታ ነበር። ጌታ ክፉን እና ደግን ከምታሳውቀው ዛፍ እንዳይበላ ያዘዘውን አዳም ግን በፈቃዱ ፈጣሪውን ላለመታዘዝ ወስኗል።

> “የተታለለም አዳም አይደለም ፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች፡፡ ” (1ጢሞቴዎስ 2:14)

አውቀውም ይሁን ተሳስተው ሁለቱም ጥፋተኞች ነበሩ ነገር ግን ጥፋተኛ የሆኑት አዳም የተከለከለውን ፍሬ ከበላ በኋላ ነበር “የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፡፡” (ዘፍጥረት 3:7)

እግዚአብሔር ሄዋንን ሳይሆን አዳምን ከጽድቅና ሕይወት መንግስት ወደ ኀጢአትና ሞት አገዛዝ በማሻገር ተጠያቂ አደረገው፡፡ እግዚአብሔር አዳምን የሰው ዘር ራስ የመሆን ዕድል ሰጠው፤ ነገር ግን ከትልቅ ዕድል ጋር ትልቅ ኀላፊነት መጣበት፡፡

የአዳም ኀጢአት ሁላችንን አረከሰን ነገር ግን እኛ ለምንመርጠው ምርጫ እሱን ተጠያቂ ልናደርገው እንችልም፡፡

> “እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን፡፡” (ሮሜ 14:12)



# 14

# እርግማን

የመሸፋፈን እና ስበብ የመስጫ ጊዜ አብቅቷል፡፡

አዳም የራሱን መንገድ መርጧል ፣ ነገር ግን ያ መንገድ የሚያመጣበትን ጦስ መምረጥ አይችልም፡፡ ጽድቅ ፈራጅ በሰው ልጅ ሳጢአት የመጡ ተከታታይ እርግማኖችን እና አሰከትሎታቸውን ሲናገር ፍጥረት ሁሉ ዝም ይላል፡፡

## እባቡ

እግዚአብሔር እርግማን የጀመረው ከ "እባብ" ነው፡፡

> "እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፦ ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ **የተረገምህ ትሆናለህ**፤ በሆድህም ትሄዳለህ፥ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ፡፡ በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ፡፡" (ዘፍጥረት 3:14-15)

እግዚአብሔር እያዋራው ያለው እባብ የትኛው ነው? ፈጣሪ በተሳቢ እንስሳ ላይ ተቆጥቶ ነበር?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በተለይ ደግሞ በኢየሱስ ምሳሌዎችና በትንቢታት ውስጥ ሁለት ደረጃ መልዕክት አለው፡፡ ግልጽ ፍቺ አለ በተጨማሪም በመቀጠል ብዙ ግልጽ ያልሆነ ጥልቅ ፍቺ አለው፡፡ የዚህ ፍርድ ዋና ጉዳይም ይኸው ነው፡፡

በእባብ ላይ የመጣው እርግማን ሁለት ደረጃ አለው።

## ደረጃ 1:- ዘለቄታዊ ምሳሌ

መጀመሪያ ጌታ እባብን በመርገም(ፍርድን በመናገር) ለሰው ልጅ ዘለቄታዊ ተጨባጭ ትምህርት እያስተላለፈ ነበር። ስይጣን ሰውን በኃጢአት ለመፈተን የተጠቀመበት እባብ ከዚህ በኋላ በመሬት ላይ በደረቱ ይሳባል። ሁሉም እባቦች ተመሳሳይ ዝርያ ሊኖራቸው ይችላል። አዳምና ሄዋን ኃጢአት ከመስራታቸው በፊት በግልጽ እንድሚታየው እባብ እንደሌሎች ተሳቢ እንስሳት እግር ነበረው። እሰከ ዛሬም ድረስ የተውሰኑ የእባብ ዝርያዎች እንደ ዝንዶ እና ቦአ የላይኛው እግራቸው አጥንት በውስጣቸው ይገኛል።[128]

ኃጢአት ለጥፋተኛው እና ጥፋት ለሌለበት ሁሉ የሚተርፍ ጦስ ያመጣል። ከኃጢአት የተነሳ "ፍጥረት ሁሉ በምጥ" ላይ ይገኛል (ሮሜ 8:22)። ንጹሁ የእንስሳት ዓለም እንኳን ተጎድቷል።

በዚህ ምክንያት ሰው ኃጢአት ለማድረግ የመረጠበት ሂደት ውድቀት የተባለው ለዚህ ነው።

## ደረጃ 2፦ የሰይጣን አይቀሬ ጥፋት

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤" (2 ጴጥሮስ 1:20) መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ይፈታል ይላል። እግዚአብሔር በሁለተኛው የእርግማኑ ክፍል የተጠቀሰው "እባብ" ቅዱሳት መጽሐፍትን በጥልቀት እንድንመረምር ያስገድደናል።

> "ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም..."
> (ዘፍጥረት 3:15)

እግዚአብሔር ያነጋገረው እባብ ማን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ "እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!" (ኢሳያስ 14:12) ትዕቢተኛው መልአክ እንደ ሆነ ይናገራል። እሱ "ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።" (ራዕይ 12:9)[129] ነው።

እባቡ ሰይጣን እንጂ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም።

ለእባብ በሚገባ ቋንቋ ጌታ በዲያብሎስና በተከታዮቹ ላይ ቁጣውን እየገለጠ ነበር። በስይጣን "ዘር" (ዝርያ) እና በሴቷ

ዘር መካከል “ጠላትነት” ይኖራል። በመጨረሻም “የሴቷ ዘር” የእባብን “ራስ” ይረግጣል።

ይሄ ሁሉ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ይከናወናል።

## ሁለቱ “ዘሮች”

እነዚህ ሁለት ዘሮች ስለምን ይገራሉ? የእባቡ ዘር እና የሴቷ ዘር የሚያመለክተው ማንን ነው?

የእባብ ዘር ስይጣን እንዳመጸው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚያምጹትን የሚመለከት ነው። የስይጣንን ውሸት የሚከተሉ በመንፈሳዊ ዐይን የዲያብሎስ ልጆች ናቸው።

> “እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።” (ዮሐንስ 8:44 አመት)

**የሴቷ ዘር** ታዲያ ማን ነው?

ይሄ ልዩ ጽንሰ ሐሳብ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ሙሉ የሰው ዘር የሚጠራው በወንድ እንጂ በሴት አይደለም። ኀጢአት ወደ ምድር በገባበት ቀን ግን እግዚአብሔር ሰለ ሴቷ ዘር ተናገረ። ለምን?

ይህ በእግዚአብሔር የታወጀ አዋጅ ከወንድ ሳይሆን ከሴት ስለሚወለደው መሲህ የሚያመለክት የመጀመሪያ ትንቢት ነው። መሲህ ማለት የተቀባ ወይም የተመረጠ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ሰው የሕዝብ መሪ፣ ባለ ሥልጣን፣ እንደ ነብይ እንዲሆን ሲመረጥ በእግዚአብሔር የተለየ ተግባር እንደ መረጠ ለማሳየት ይቀባል (ራሱ ላይ ዘይት ይፈስበታል)።[130]

ነገር ግን መሲሁ ከሌሎቹ የተለየ ይሆናል። እሱ የተቀባው ነው። በታሪክ ውስጥ በትክክለኛው ወቅት ወደ ዓለም ይገባ ና “እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።” (ዕብራውያን 2:14-15)

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ኀጢአት የገባ ዕለት ሙሉ ዕቅዱን ባያስተዋወቅ እንኳን ፣ በጥንስስ ደረጃ ያለው

ትንቢት ለአዳምና ለሄዋን እና ለዝርያቸው የተሰፋ ጭላንጭል ነው። የመጀመሪያው የተስፋ ቃል በኋላ ነብያት በዝርዝር የሚያብራሯቸው መሰረታዊ እውነቶችን የያዘ ነው።[131]

## እርግማን

በተመረጡ ቃላት በቀረበው የሴቷ ዘር የእባቡን ራስ ይረግጣል የሚለውን ቃል ተከትሎ ጌታ ለአዳም እና ለሄዋን የሐጢአታቸውን ጥቂት ተግባራዊ አስከትሎት አሳውቋቸዋል። ይሄ አስከትሎትም እርግማን በመባል ይታወቃል።

> “ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል።
> አዳምንም አለው፦ የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን ፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና።” (ዘፍጥረት 3:16-19)

አዳምና ሔዋን በፈጣሪያቸው ላይ ለማመጽ መምረጣቸው አሰቃቂ የሆነን ዋጋ አስከፍሏቸዋል።

ቤተሰብ የማፍራት ደሰታ አሁን በችግር እና ሕመም የታጀበ ይሆናል። ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ እና አትክልት ከማፍራት ይልቅ፣ የመሬት የተረገመ አፈር አረም እሾህና አሜኬላ ያበቅላል። ዕረፍት እና ደሰታ በልፋት እና ድካም ይተካሉ። ከዚያም በከፋ የሰው ልጅ አላፊ ሕይወት ሞት በተሰኘ አምባገነን ጥላ ስር ይወድቃል።

የሰው ልጅ ገዢነቱን ያጣል። ሳጢአት እርግማንን ያመጣል።

## ሞት መደበኛ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስን ቸል የሚሉ ሰዎች ስቃይን፣ መከራን፣ ማጣትን ፣ የተበላሸ ግንኙነት ን፣ በሽታን፣ ማርጀትን እና ሞትን መደበኛ አድርገው ያያሉ። ስለ ለሳጢአት እውነታውን ስንረዳ ነገሮች የሆኑትን ለምን ሆኑ ስንል ቁልፉ ነገር በምጥ ውስጥ

የምትገኘው ፕላኔታችን ናት። በርካታ በሩህ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች የሰው ልጅን አሰቃቂ ሁኔታ ለእግዚአብሔር አለመኖር ምክንያት አድርገው ይጠቅሱታል። በዚህ መልኩ ምክንያት የሚያቀርቡት የኀጢአትን መግባትና ውጤት ስለማያውቁ ነው።[132]

በሴኔጋል ሰዎች አንዳንድ ጊዜ (በተለይ በቀብር ስርዓት ጊዜ) እንዲህ ይላሉ "እግዚአብሔር ሕይወትን ከመፍጠሩ በፊት ሞትን ፈጠረ"። ብዙዎች ከዚህ ፍልሰፍና መጽናናትን ያገኛሉ። ይሄ አባባል ግን አመክንዮንም "የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው" (1 ቆሮንቶስ 15:26) የሚለውን መጽሐፍ ቅዱስንም የሚጋጭ ነው።

እኩይ፣ ሐዘን፣ ስቃይ መከራ እና ሞት የተለመዱ ሊመስሉን ይችላሉ፤ ነገር ግን እንዲህ አይነት የተበላሹ ነገሮች የካንሰር ሕዋስ በጤነኛ ሰው አካል ውስጥ የተለመደ እንዳልሆነ ሁሉ የተለመዱ አይደሉም።

ደስ የሚል ሽታ ባለው በጽጌረዳ አበባ ላይ የሚገኘው እሾህ ፣ ምርት ለማምረት የምንለፋው ልፋት፣ በጣም የሚያምር ሕጻን ልጅ ግትርነት ፣ባል ተወዳጅ ሚስቱን የሚያሰቃይበት መንገድ፣ አስደሳቹን የልጅ መውለድ ሥርዓት ተከትሎ የሚመጣው ሕመም ፣ የሰውን የመከላከል አቅም ከጥቅም ውጪ የሚያደርገው በሽታ፣ የእርጅና ጭካኔ ፣ የሞትና የአካላችን ወደ አፈር የመመለስ እውነታ ፣ እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር የመጀምሪያ ዕቅድ አካል አይደሉም። እግዚአብሔር ፍጥረት ራሱን እንዲዋጋ አደርጎ አልሰራውም።



ኃጢአት ከመግባቱ በፊት የሰው ልጅ በፍጥረት ላይ የበላይነት ነበረው። ሁሉም ነገሮች ለአዳምና ለሚስቱ ሙሉ በሙሉ የተገዙ ነበሩ። ጽድቅና ሰላም ምድርን ሞልተው ነበር። ስለዚህ የመጀመሪያው አባታችን በሐጢአትና ሞት መንገድ ሲጓዝ፣ የረከሰውና እና ጠፊው የሰው ዝርያም ተከትሎት ሄደ።

## ፍጥረት ሁሉ ረከሰ

አንድ ሰው "ነገር ግን ይሄኮ ተገቢ አይደለም!" ሊል ይችላል "የትኛውም ሰው በሌላ ሰው ኃጢአት መከራን የሚቀለው ምንድን ነው?"

በተረገመ ዓለም ውስጥ የመኖራችን እውነታ እንዳለ ሆኖ ሁላችንም የራሳችንን ምርጫ እንመርጣለን እግዚአብሔርም ስለ ምርጫችን ተጠያቂ ያደርገናል። ከዎሎፍ አባባል ጀርባ ያለው እውነታ ለራሱ ምስክር ይሆናል፦ “ወረርሺኝ መጀመሪያ በተያዘው ሰው ላይ አያበቃም።”

ይሄ የኅጢአት ባህርይ ነው። ሕይወት ከዚህ በኋላ የሚገባንን አትሰጠንም። አዳም ካደረገው ከአንድ ኅጢአት የተነሳ “ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።” (ሮሜ 8:22 አመት)

ሁሉ በኅጢአት እርግማን ተበክለዋል።

የምስራቹ ገና ከመጀመሪያው ፈጣሪያችን አስገራሚ የማዳን ዕቅድ ያለው መሆኑ ነው። ልክ ሰዓት ስሪዎች ሰዓት ጊዜን በትክክል እንዳይለካ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገሮች የሚያስተካክል ነገር ውስጡ እንድሚያበጁት ሁሉ ፣ የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪም ስይጣን ፣ኅጢአት እኛ ሞት የሚያመጡትን ጥፋት የሚያስቆም “ዘዴ” ገጥሞበታል። ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ኅጢአት እንዲገባ ሲፈቅድ ዓላማ፣ እርግማኑንም የሚቀለብስበትና ጸጋውን ለሚምኑት ሁሉ የሚያሳይበት ዕቅድ አለው።

ሐዘን ፣ ሕመም እና ሞት በእግዚአብሔር የጅማሬ ታሪክ ውስጥ አልነበሩም፣ በፍጻሜውም አይኖሩም። አንድ ቀን ኅጢአት እና እርግማኑ ያበቃላቸዋል። “**እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፣ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ** ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።… ከእንግዲህም ወዲህ **መርገም ከቶ አይሆንም**።” (ራዕይ 21፡4 ፣ 22:3) በጉዟችን መጨረሻ ስለ ወደፊቱ አስገራሚ ሁኔታ እንነጋገራለን።

## የእግዚአብሔር ጸጋ

አዳምና ሔዋን ከፉን እና ደግን ከምታሳውቀው ዛፍ ከበሉ በኋላ ምን እንዳደረጉ ታስታውሳላችሁ?

ራሳቸውን የሚሸፍኑበት የቅጠል መሸፈኛ አዘጋጁ። ይሄ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ኅጢአቱንና ሃፍረቱን ለመሸፈን ያደረገው ሙከራ ነው። እግዚአብሔር የአዳምን እና የሄዋንን የግል ጥረት አልተቀበለም። በምትኩ እግዚአብሔር አንድ ነገር አደረገላቸው።

"እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፣ አለበሳቸውም።" (ዘፍጥረት 3:21)

እግዚአብሔር አዳምና ሄዋንን ከእንስሳት ቆዳ የተሰራ ልብስ አለበሳቸው። ይህንን ለማድረግም ደም መፍሰስ ነበረበት።

እስቲ ጌታ ጥቂት በጎችን ወይም ድግሞ ሌሎች እንስሳትን ሰውቶ "ቆዳ ልብስ" ለአዳምና ለሔዋን ሲሰራ አሰቡት። እግዚአብሔር የሐጢአትን ከፍተኛ ዋጋ፣ የእሱን ቅዱስ ባህርይ እና ስለ ሐጢአተኞች እያስተማራቸው ነበር፣ ስለዚህ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ የማይመጥን በእሱ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል።

ለአዳም እና ለሄዋን ልዩ ልብስ በማዘጋጀት በእሱ ላይ በቅርቡ ላመጹበት ሰዎች ጸጋውን እያሳየ ነበር። ይሄ መልካምነት አይገባቸውም ነበር፣ ነገር ግን ጸጋ ማለት እንዲዚያው ነው — ያልተገባ ደግነት።

**ፍትህ** ማለት የሚገባንን
(= ዘላለማዊ ቅጣት) መቀበል ማለት ነው።
**ምህረት** ማለት የሚገባንን አለመቀበል
(= አለመቀጣት) ማለት ነው።
**ጸጋ** ማለት የማይገባንን መቀበል ማለት ነው
(= የዘላለም ሕይወት)

## የእግዚአብሔር ጽድቅ

ለአዳምና ለሄዋን እንስሳትን በመግደል እሱ "ባለ ጸጋ አምላክ" ብቻ ሳይሆን "ጻድቅ አምላክ" መሆኑን አሳይቷል (መዝሙር 86:15 አመት ፤ መዝሙር 7:9) ኅጢአት በሞት መቀጣት መቻል አለበት። ከእነዚህ ከሚያምሩ ፍጡራን ውስጥ ደም ሲፈለቅ ሲያዩ አዳምና ሔዋን የሚሰማቸውን ስሜት አሰቡት። እግዚአብሔር ፊት ለፊታቸው የኅጢአት ቅጣት መሆኑን ግልጽ ምሳሌ ሰጥተዋል። አዳምን እና ሄዋን የዚያኑ መገደል ነበረባቸው ነገር ግን ንጹሐን እንስሳት በእነሱ ምትክ ሞቱ። የመጀመሪያውን የደም መስዋዕት እግዚአብሔር ራሱ ፈጸመ። በሚሊዮን የሚቆጠሩም ይከተሉታል።

በተጨማሪም ደግሞ በእንስሳ ቆዳ "ያለበሳቸው" ጌታ መሆኑን እስቲ አስቡት። አዳምና ሄዋን ሀጢአታቸውን እና እፍረታቸውን ለመሸፈን ሞከሩ ነገር ግን የእነሱ ጥረት እግዚአብሔርን

አላረካውም። ከኅጢአታቸው እና ከእፍረታቸው ሊያድናቸው የሚችለው እሱ ብቻ ነው።

## ኅጢአተኞች ተባረሩ

ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 የሚያበቃው በሚከተለው ልኩ ነው፦

> “እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፥ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።” (ዘፍጥረት 3:22-24)

የእግዚአብሔርን ፍቃድ በመቃወም የራሳቸውን ፍቃድ ለማስፈጸም በሞከሩ ጊዜ ሉሲፈርና መላዕክቱ ከመግሥተ ሰማያት እንደተባረሩ ሁሉ፥ ሰውና ሚስቱም የእግዚአብሔርን ፍቃድ በተቃወሙ ጊዜ ከምድራዊ ገነት ተባርረዋል።

ስለዚህም የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር መገኘት እና ከሕይወት ዛፍ(ክፉን እናደጉን ከምታሳወቀው ዛፍ ጋር መምታታት የለበትም) አካባቢ ተባረረ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናደርገው ጉዞ መጠናቀቂያ ላይ በስማያዊው ገነት ሌላ ለየት ያለች ዛፍ እናያለን። የሕይወት ዛፍ እግዚአብሔር በእሱና በዕቅዱ ለሚታመኑ ሰዎች የሚሰጠውን የዘላለም ሕይወት ትወክላለች።

ክፉን እና መልካም የምታሳውቀውን ዛፍ በመብላት አዳምና ሄዋን የዘላለም ሕይወትን መንገድ በመተው የዘላለምን ሞት መንገድን መረጡ። በሰማይና ምድር መካከል የነበረው አስገራሚ ግንኙነት በኅጢአት የተነሳ ተቋረጠ።

አዳምና ሄዋን ከባድ ችግር ነበረባቸው።

እኛም እንደዚያው።



# 15

# ጥንድ ችግሮቻችን

**የተፈረደበት ሰው ከእስር ቤት ካመለጠ ከ 38 ዓመት ሸሸት በኋላ ተያዘ** የሚል ዜና የተዘገበው በግንቦት ወር 2006 እ.ኤ.አ አርዕስተ ዜና ላይ ነበር፡፡

ዘጋቢው አቶ ስሚዝ የተባለ ሰው በ 1968 ከካሊፎርኒያ እስር ቤት በዝርፊያ ታስሮ እያለ አመለጠ ሲል ዘገበ፡፡

ለ38 ዓመታት የተጭበረበረ ስም በመጠቀም ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀስ ነበር፤ ቢሆንም በመጨረሻ በመካከለኛው አሜሪካ ጥቅጥቅ ባለ ድን ውስጥ ተንቀሳቃሽ ቤት ስርቶ መኖር ጀመረ፡፡ ባለስልጣናት ያገኙት እዚያ ነበር፡፡

“ወደ መሬት አቀርቅሮ ተመልክቶ ፣ ቀና ብሎ አያቸውና እንዲህ አለ ‘እኔ ነኝ’” አለን ይላሉ የክሪከ ከተማ ፖሊስ መርማሪ፡፡ “ሰዎች ለዚህን ያህል ጊዜ ይፈልጉኛል ብሎ አላሰበም ነበር፡፡”[133]

አቶ ስሚዝ እንኳን ከሕግ ጥላ ማምለጥ ካልቻለ፤ የትኛውም የእግዚብሔርን ሕግ የተላለፈ ሰው ገደብ የሌለውን የጻድቅ ሕግ ሰጪ እጅ እና ፈራጅ ሊያመልጥ አይችልም፡፡

ታዲያ እነዚህ ሕግ ተላላፊዎች እነማን ናቸው?

> “**ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል**፤ ኃጢአትም ዓመፅ ነው፡፡” (1ዮሐንስ 3:4 አመት)

የእግዚአብሔርን ፍጹም ሕግ የማይታዘዝ ሁሉ ሕግ ተላላፊ ነው፡፡ ሉሲፈር ያደረገው ይሄንን ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ያደረጉት ይሄንኑ ነው፡፡ እኛም ያደረግነው ይሄንኑ ነው፡፡

ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሰርተዋል፡፡ ብዙዎች ኃጢአታቸውን እንደቀላል ያያሉ ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር

ዐይን ፣ ንስሐ የማይገባ ፣ ይቅር ያልተባለ ሰው ሁሉ ምንም ያክል “መልካም” ወይም ሐይማኖተኛ ቢሆን ሕግ የጣሰ ወንጀለኛ ነው፡፡

## ተስፈኛ ሕልም አሳዳጆች

አንድ ጊዜ አንድ ጎረቤቴ እንዲህ አለኝ “እኔ ተሰፈኛ ነኝ፡፡ ወደ ገነት ሳልገባ አልቀርም፡፡”

ለፍርድ ሲቀርብ ተስፈኛነቱ እና የግል ጥረቱ ከዘላለማዊ ቅጣት ሊያድነው ይችላል እንዴ?

አንድ ጊዜ በካሊፎርኒያ ዴዝ ቫሊ (በምድር ላይ ከሚገኙ ሞቃት በረኻዎች አንዱ) ሳልፍ ፣ በርቀት የሚያብረቀርቅ ሐይቅ አየሁ አየቀረብኩ ስሄድ ግን “ሐይቁ” እየራቀ ሄደ፡፡ ወደ ፊት ስመለከት ሌላ “ሐይቅ” አየሁ፡፡ እሱም ጠፋ፡፡

በምናቤ የፈጠርት ነበር፡፡

ይሄ አምሳያ የብርሃን ጨረር የተለያየ ሙቀት ባላቸው የአየር ንብርብሮች ላይ ሲያርፍ የሚፈጥረው ነጸብራቅ ነው፡፡ ሐይቆቹ እውነተኛ ይመስሉ ነበር፡ ግን እውነተኛ አይደሉም፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ሳጢአተ ኛ ሰው ወደ ገነት መግባት ዕድሉን በተመለከተ ተስፈኛ ሊሆን ይችላል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እውነቱን ያጋልጣል፡፡ የአዳም ዘሮች ራሳቸውን ለማዳን “ምንም ብርታት” የላቸውም፡፡ (ሮሜ 5:6)

በደረቅ ምድረ በዳ ውስጥ የሚገኝና በቸኛ ውሃ አቅርቦቱን እንደደፋ ሰው የሰው ልጅ ከሳጢአት የተነሳ ያጣውን ሕይወት መልሶ ማግኘት አይችልም፡፡

> “ሁላችን እንሞታለን፣ በምድርም ላይ እንደ ፈሰሰና እንደማይመለስ ውኃ ነን” (2ሳሙኤል 14:14)

የጠፋ ሰው ሕይወት የሚያድን የበረኸ ውስጥ ሐይቅ እንዳየ በቅንነት ሊያምን ይችላል ነገር ግን ያ “የበረኸ ውስጥ ሐይቅ” የሚያንጸባርቅ የሙቀት ሞገድ ነው፡፡ ተስፋ የቆረጠ እና ውሃ የጠማው ሰው እስኪሞት ድረስ ከአምሳያ ወደ ሌላ አምሳያ ሊጓዝ ይችላል፡፡

የሳጢአተኛ ተሰፈኝት፣ ቅንነት እና ሐይማኖታዊ የራስ ጥረት እንደዚያው ነው፡፡

> “ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፤ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።” (ምሳሌ 14:12)

የረከሰውን ሁኔታቸውን ለመለወጥ፣ በዓለም ላይ የሚገኙ በቢሊዮን ሚቆጠሩ ሰዎች ዛሬ ትክክል የሚመስላቸውን መንገድ ይከተላሉ። ሐይማታዊ ስርዓት ይፈጽማሉ ፣ ስርዓታዊ በሆነ መንገድ አካላቸውን ይታጠባሉ ፣ ተደጋጋሚ ጸሎቶችን ይደግማሉ ፣ ከተወስኑ የምግብ አይነቶች የታቀባሉ፣ ገንዘብ ይሰጣሉ፣ ሻማ ያበራሉ፣ መጠሪያ ይይዛሉ፣ ቀመሮችን ይደጋግማሉ፣ መልካም የሚሉትን ስራ ሁሉ ይሰራሉ። ሌሎቹ ደግሞ መንፈሳዊ መሪዎቻቸው ላይ ያተኩራሉ፣ ሌሎች ደግሞ የተቀደሰ እና ጽድቅ ለሚሉት አላማ ስማእት በመሆን ወደ ገነት ለመግባት ያስባሉ።

እነዚህ ሁሉ አምሳያ ናቸው?

## ራስን በትክክል ማየት

“እውነት ሚጥሚጣ ነች።” የወሎፍ ምሳሌ።

ምንም እንኳን ምቾት ባይሰጠንም እግዚአብሔር ስለ ራሳችን አሳዛኙን እውነት ይነግረናል። ሐጢአታችንን በተመለከተ ከእሱ ጋር በቅንነት እንድነጋገር ይጋብዘናል። ከዚህ ቅንነት ውጪ ፣ ባለቤቴና እኔ የምናውቃትን በጠና የታመመች ሴትዮ እንሆናለን። ደህና እሆናለሁ በማለት ትክክለኛ ሐኪምም ጋር ለመሄድ እምቢ አለች። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ግን ሞተች።

በምድር ላይ ሳለ መሲሁ ራሳቸውን ጻድቅ ለሚያደርጉ የሃይማኖት መሪዎች እንዲህ ብሏቸው ነበር፦

> “ኢየሱስም ሰምቶ፦ ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን[ብቁ ነኝ ብለው የሚያስቡ] ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።” (ማርቆስ 2:17)

ከመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽነት ባሻገር በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ፣ መስጊዶች እና ምኩራቦች ለሰዎች ምን ያህል መልካም እንደሆኑ እና የበለጠ መሞከር እንዳለባቸው ይሯቸዋል። የእግዚአብሔርን እንከን የለሽ ጻድቅነትና የኅጢአትን አስቃቂ አስከትሎት አይነግሯቸውም።

በካናዳ የሚገኝ መስጊድ የሚከተለው ጽሁፍ መግቢያው ላይ ተለጥፏል፦

ሁሉንም ሰው እንቀበላለን ማንንም
ሰው ሐጢአተኛ ነህ አንለውም፡፡

እግዚአብሔር ወደ ገነት መግቢያ በር ላይ ግን የተለየ መልዕክት ለጥፏል፡፡

"ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም
እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፡፡"
(ራዕይ 21:17)

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል" (ሮሜ 3:23) እግዚአብሔር ማንንም በስራው ላይ ተመስርቶ አይቀበልም ፣ ለሁሉም ሰው ሐጢአተኛ መሆኑን ይናገራል፡፡

ወደ ገነት የሚገቡት የእግዚአብሔርን ፍጹም የጽድቅ መለኪያ በማሟላት የነጹ ብቻ ናቸው፡፡

## እግዚአብሔርን በትክክል ማየት

አንድ ቀን ነብዩ ኢሳያስ የጌታን ፍጹም ንጽሕና እና አስገራሚ ክብር የሚያሳይ ራዕይ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ኢሳያስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦

"ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር፡፡ ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፥ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር፡፡ አንዱም ለአንዱ፦ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ **ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤** ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር፡፡ የመድረኩም መሠረት ከጭዋኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፥ ቤቱንም ጢስ ሞላበት፡፡ እኔም፦ **ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ!"** (ኢሳያስ 6:1-5)

በሰማይ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ዙፋን የከበበው የሚነድ ነጸብራቅ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ቅዱሳን መላዕክት እንኳን ፊታቸውን እግራቸውን ይሸፍናሉ። እነዚህ መላዕክት በእግዚአብሔር ቅድስናና ክብር ከመገረማቸው የተነሳ በፊቱ መቀመጥ አይችሉም። ከዚህ ይልቅ በዙፋኑ ዙሪያ እየበረሩ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች" እያሉ ይጮኸሉ።

ብዙ ሰዎች ኅጢአትን በሐጢአትነቱ ማየት የሚከብዳቸው ለምንድን ነው? ምናልባት እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ስላላዩት ይሆናል፡ የሚያንጸባርቅ ቅድስናውን በፍጹም አስበውት ስለማያውቁ ይሆናል። ኢሳያስ እግዚአብሔርን የሚፈራ ነብይ ነበር፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን የሚያንጸባርቅ ቅድስና ባየ ጊዜ የሱን ርካሽነት እና ቆሻሻነት አየ። "ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ" አለ። ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጻጸር ፣ ኢሳያስ መላው እስራኤል ችግር ውስጥ እንዳለ ተረዳ።

በኋላም ኢሳያስ እንዲህ ሲል ጻፈ "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤... ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል።" (ኢሳያስ 53:6፤64:6) ኢሳያስ ምንም አይነት ሥርዓታዊ መታጠብ ወይም የራስ ጥረት በጌታ ፊት ቅዱስ ሊያደርገው እንደማይችል አወቀ።[134] ፈጣሪን በዚህ መልኩ ከመረዳቱ የተነሳ "ሁላችን **እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል**" አለ።

ነብዩ ኢዮብ በተጠየቀ ጊዜ የሰውን የረከሰ ሁኔታ አሳየ "...**ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን እንዴት ይችላል**? ...በአመዳይ ውስጥ ብታጠብ፥ እጆቼንም እጅግ ባነጻ፥" (ኢዮብ 9:2፤ 30-31) እናም ነብዩ ኤርሚያስ የሚከተሉትን ቃላት ጻፈ "በእንዶድ ብትታጠቢም፥ ለራስሽም ሳሙና ብታበዢ፥ በእኔ ፊት በኃጢአትሽ ረክሰሻል ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" (አርሚያስ 2:22 አመት)

እግዚአብሔርን በትክክል ማየት ራስን በትክክል ማየት ነው። ስለ ፈጣሪያችን ያለን አሰተሳሰብ ደካማ ከሆነ ስለራሳችን ያለን አመለካከት በትዕቢት ያበጠ ይሆናል።

የቆሸሸ፣ በበሽታ የተበከለ ጨርቅ የለበሰ ሰው ራሱን ንጹህና ሰው የሚበለው አድርጎ ሊያይ ይችላል፥ ነገር ግን ይሄ እይታው እሱን እንደዚያ አያደርገውም። በተመሳሳይ መልኩም ኅጢአተኛ

ሰው ራሱን ጻድቅ አድርጎ ሊያይ ይችላል ይሄ ዕይታው ግን ጻድቅ ሊያደርገው አይችልም።

ከእግዚአብሔር ክብርና ጽድቅ ጋር ሲነጻጸር ፣ ብርቱ ጥረቶቻችን የመርገም ጨርቅ ናቸው።

## ለሁላችንም የሚሆን ትምህርት

እግዚአብሔር ለሀገረ እስራኤል የፈጠረበት ዋነኛ ምክንያት ሌሎች አሕዛብ ጠቃሚ ትምህርቶችን ለማስተማር ነው። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ለእስራኤል ሁልጊዜ ታማኝ ቢሆንም እስራኤላውን ግን ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ያሳዝኑት ነበር። እግዚአብሔር ከእነሱ እንድንማር ይፈልጋል። "እነዚህም ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን።" (1 ቆሮንቶስ 10:6)

ዘጸአት በተሰኘው የቶራ ሁለተኛ መጽሐፍ ሙሴ እስራኤላውያን ኅጢአትን እግዚአብሔር እንደሚያየው ማየት እንዴት እንደተሳናቸው ያሳያል። እግዚአብሔር በብርቱ ክንድ እስራኤላውያንን ከዘመናት የግብጽ ባርነት ነጻ አወጣቸው። ነገር ግን ስለ ጌታ እና ሰላ ባህርዩ በዙ ያልተረዱት ነገር ነበር። እነሱ እንዳስቡት እንደ ዘበት የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያመልጡ መስሏቸው ነበር።

እስራኤላው በራሳቸው በጣም ከመተማመናቸው የተነሳ ሙሴን እንዲህ ብለውት ነበር፦


"እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን።" (ዘጸአት 19:8)

እራሳቸውን እንደ ረዳት አልባ ኅጢአተኞች አላዩም ወይም ደግሞ የእግዚአብሔርን እንከን አለባ የጽድቅ መሰፈርት አልተረዱም ነበር። አዳምና ሄዋንን ከፈጣሪያቸው ለመለየት ያስፈለገው አንድ ኅጢአት እንደሆነ ረስተው ነበር። እስራኤላውያን ኅጢአታቸውን እንዲያዩና እፍረትም እንዲሰማቸው አስር ነጥቦች ያሉት ፈተና ሰጣቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ የሲና ተራራ ላይ በኃይልና በክብር በሲና ተራራ ላይ ወረደ። "**ነጐድጓድና መብረቅ** ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ በተራራው ላይ ሆነ፤ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ **ተንቀጠቀጡ**።" (ዘጸአት 19:16 አመት) በመቀጠልም አስርቱን ሕግጋት የሚገልጽ ድምጽ ተሰማ፦

## አሥርቱ ትዕዛዛት

1. **“ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።”** ከጌታ በሰተቀር የትኛውንም አምላክ ማምለክ ኅጢአት ነው። በየአንዳንዱ ቅጽበት እና በእያንዳንዱ ቀን በሙሉ ልብ ፣ ሐሳብ እና ብርታት ጌታን መውደድ አለመቻል ኅጢአት ነው። (ዘጸአት 20)[135]
2. **“የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ።”** ይሄ በምስል ፊት መስገድን ወይም አንድ ነገር በማክበር ብቻ የማይወሰን ነው። የእግዚአብሔርን ስፍራ የሚወስድ ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግ ይተላለፋል።
3. **“የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ”** ለአንዱ እውነተኛ አምላክ እገዛለሁ የምትሉ ከሆነ እሱን ለማወቅና ቃሉን ለመታዘዝ የማትፈልጉ ከሆነ ቅዱስ ስሙን በከንቱ እየጠራችሁ ነው።
4. **“የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።”** እስራኤላውያን በሰባተኛው ቀን ከየትኛው ስራ በመታቀብ በሰባተኛው ቀን እንዲያከብሩት እንፈልጋለን።
5. **“አባትህንና እናትህን አክብር”** ከፍጹም መታዘዝ ያነሰ የትኛውም ነገር ኅጢአት ነው። የትኛውም ልጅ ቤተሰቦቹን መጥፎ አመለካከት መያዝ ይህንን ትዕዛዝ መተላለፍ ነው።
6. **“አትግደል።”** በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል “ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፤” (1 ዮሐንስ 3:15) ሰዎችን መጥላት ከመግደል እኩል ነው። እግዚአብሔር ልብን ያያል ፣ ራስ ወዳድነት የሌለበትንም ፍቅር ሁል ጊዜ ይፈልጋል።
7. **“አታመንዝር።”** ይሄ ሕግ አካልን አላግባብ መጠቀምን ብቻ ሳይሆን በአዕምሮ እና በልብ የሚገኝን ንጹህ ያልሆነ ምኞትን የሚገልጥ ነው። “ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።” (ማቴዎስ 5:28)



8. “**አትስረቅ፡፡**” ከሚገባቹሁ በላይ መውሰድ፣ ቀረጥ ወይም ፈተና ማጭበርበር ወይም ለአሰሪዎቻችሁ በትክክል አለመስራት በሙሉ የተለያየ መልክ ያለው ስርቆት ነው፡፡
9. “**በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፡፡**” ስለ አንድ ሰው ወይም ስለ አንድ ነገር ሙሉ በሙሉ እውነት ያልሆነ ነገር መናገር ነው፡፡
10. “**ባልንጀራህን …ማናቸውንም አትመኝ አትመኝ**” የሌላ ሰው የሆነን የትኛውንም ነገር መመኘት ኅጢአት ነው፡፡ ባለን ነገር ደሰተኛ ልንሆን ይገባናል፡፡

**ጥፋተኛ!**

ጌታ እነዚህን አስር ሕግጋት ካሳወቁ በኋላ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል “ሕዝቡም ሁሉ ነጐድጓዱንና መብረቁን፥ የቀንደ መለከቱን ድምፅ፥ ተራራውንም ሲጤስ አዩ፤ ሕዝቡም ባዩ ጊዜ **ተርበደበዱ፥ ርቀውም ቆሙ**፡፡” (ዘጸአት 20:18)

ከዚህ በኋላ “ጌታ የተናገረውን ሁሉ እናደርጋለን!” ብለው መታበይ አልቻሉም፡፡

ፈተናውን ወድቀዋል፡፡

እናንተስ? እንዴት ሆናቹሁ?

በመቶኛ ሲሰላ ሁሉንም አስሩንም ትዕዛዛት(24 ሰዓት፣ 7 ቀናት ከተወለዳቹሁበት ጊዜ ጀምሮ እንከን የለባቹሁም ማለት ነው) በመፈጸም ከመቶ በታቹ ካመጣቹሁ እናንተ ልክ እንደ እስራኤል ልጆቹ እና እንደ እኔ ፈተናውን ወድቃቹኋል ማለት ነው፡፡

> “ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን **በአንዱ** የሚሰናከል ማንም ቢኖር **በሁሉ በደለኛ ይሆናል**፡፡” (ያዕቆብ 2:10)

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የዓለማቸን በብዛት የተሸጠ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን ፣ በዓለማቸን ላይ ብዙ ሰዎቹ የማያነቡት መጽሐፍ ነው፡፡ ዝነኛ ያልሆነበት የመጀመሪያ ምክንያት ሐጢአታቸንን ስለሚገልጥና ትዕቢታቸንን ስለሚገፈን ነው፡፡ ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥” እና “በምድር ላይ መልካምን የሚሠራ ኃጢአትንም የማያደርግ ጻድቅ አይገኝምና፡፡ (ራዕይ 3:17 አመት ፤ መክብብ 7:20)

የእግዚአብሔር ሕግ ስለራሳችን መልካም ስሜት እንዲሰማን አያደርግም። ያንንም እንዲያደርግ አላቀደም።

## አስርቱ ትዕዛዛት ታዲያ ለምን አስፈለገ?

ታዲያ የሕግ ዓላማ ምንድን ነው? ማንም ሰው የእግዚብሔርን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ ፣ ልናሳውቀው የምንደክመው ለምንድን ነው?

አንድ በግልጽ የምናየው እግዚአብሔር ይህንን ትዕዛዝ የሰጠበት ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ ስርዓት እንዲሰፍን ግልጽ የሞራል መለኪያ እንዲሆን ነው። ትክክል እና ስህተት በሆነው ዙሪያ ስምምነት የሌለው የትኛውም ስልጣኔ በስርዓት አልበኝነት ወይም አምባገነንነት ይመራል። እግዚአብሔር የሰው ልጅ በማህበረስቡ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲኖር ይፈልጋል። ነገር ግን እግዚአብሔር አስርቱን ትዕዛዛት የሰጠበት ቁልፍ ምክንያት አለው።

ጌታ ሕጉን የሰጠው "አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን ፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።" (ሮሜ 3:19-20)

## የአሥርቱ ትዕዛዛት ሦስት ዓላማዎች፦

**1. የእግዚአብሔር ሕግ ራሳቸውን ጻድቅ ያደረጉ ሰዎችን አፍ ያዘጋል።** "አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ" አሥርቱ ትዕዛዛት እንዲህ ይሉናል፦ እኔ ምንም ያህል መልካም ብትሉ እንኳን ፣ የእግዚአብሔርን ፍጹም ጽድቅ መስፈርት ልታሟሉ አትችሉም። እናንተ ሕግ ተላላፊ ጥፋተቾ ናችሁ። መታበይ አቁሙ![136]

**2. የእግዚአብሔር ሕግ ኅጢአትን ይገልጣል።** "ኃጢአት በሕግ **ይታወቃልና።"** ሕግ ልክ እንደ ራጅ ነው። ራዲዮ ግራፊ የተሰበረን አጥንት እና የበሰበሰን ጥርስ ሊያሳይ ይችላል ፣ ሊያክማቸው ግን አይችልም። በተመሳሳይ መልኩ "የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ [ጥሩ ነው ሊባል] ነው" ፊቱ ለቆሸሸበት ሰው መስታወት እንደሚያስፈልገው ሁሉ አስርቱ ትዕዛዝት ለሐጢአተኛ እንድዚያው ናቸው። መስታወት ቆሻሻን ሊያሳይ ይችላል ሊያስወግደው ግን አይችለም። የእግዚአብሔር ሕግ ሐጢአታችንን እና ረኩሰታችንን ይገልጣል፣

ሊያስወግዷው ግን አይችልም።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባል ለሆነ ግለሰብ የእግዚአብሔርን ሕግ አስፈላጊነት አብራራሁለት። የሚያስደነግጥ መገለጥ ነበር የሆነለት፣ ተስፋ መቁረጥ በድምጹ ውስጥ እየተሰማ እንዲህ አለ “እሺ አስርቱ ትዕዛዛት ቅዱስና ኅጢአትን መቅጣት ባለበት በእግዚአብሔር ፊት ረዳት አልባ እንደሆንን ያስተምረናል። እናም እኛም ራሳችንን በመልካም ስራችን ወይም በጸሎታችን እና በጾማችን ራሳችንን ልናድን አንችልም። ታዲያ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን የምናገኘው እንዴት ነው? መፍትሄው ምንድን ነው?”

**3. የእግዚአብሔር ሕግ ወደ እግዚአብሔር መፍትሄ ያሳየናል።** በሆስፒታል የሚገኘው የራጅ ባለሙያ እግሩ የተሰበረን ሰው እግን ሊያሰተካከልለት ወደሚችል ባለሙያ እንደሚመራው ሁሉ ሕግና ነብያት ወደ “ሐኪሙ” ያመለክቱናል። “ከሕግ እርግማን ዋጀን” (ገላትያ 3:13) ስለ እሱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በስፋት እንነጋገራለን።[137]

## እርዱኝ!

ልትሰምጡ ቢሆንና ፣ በአቅራቢያችሁ ከመስጠም ሊያድናችሁ የሚችል ሰው ቢኖር ፣ እርዱኝ ብላችሁ ለመጮህ ኩራት ይይዛችኋል?

ከሐጢአት ለሞት የሚያደርስ ቅጣት ራሳችሁን ለማዳን አቅም የሌላችሁ መሆኑን መገንዘብ የድላችሁ የመጀመሪያ ደረጃ ነው። ሰው እግዚአብሔር ብቻ ሊሰጠው የሚችለው እርዳታ ያስፈልገዋል።

ምናልባት “እግዚአብሔር የሚረዳው ራሳቸውን የሚረዱትን ነው” የተሰኘ አባባል ሰምታችሁ ይሆናል። ምንም እንኳን አባባሉ በአንዳንደ የሕይወታችሁ ክፍሎች የሚረዳችሁ ቢሆንም ወደ ኅጢአታችን እና መንፈሳዊ ሙት ስለሆንንበት ጉዳይ ስንመጣ እውነቱ የዚያ ተቃራኒ ነው፦ እግዚብሔር ራሳቸውን መርዳት እንደማይችሉ የሚያውቁ ሰዎች ይረዳል።

እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው የሚምኑ ሰዎችን ይረዳል።

የታወቀ የአፍሪካውያን አባባል እንዲህ ይላል “ለረጅም ዘመናት ውሃ ውስጥ የተነከረ ግንድ አዞ አይሆንም።”

ሰውም የተበከለ ባሕርይውን ቀይሮ ራሱን ጻድቅ ሊያደርግ አይችልም።

## ተበክሏል

ወደ ኋላ ሄዳችሁ እስቲ አዳምን አስቡት፦

ክፉውን እና መልካሙን ከምታውቀው ዛፍ አትብሉ።

አዳምና ሄዋን ፈጣሪ ባለቤቱን ቢታዘዙ ኖሮ ከእሱ ጋር በግንኙነታቸው እያደጉ ለዘላለም ይኖሩ ነበር። የተፈጸመው ግን ያ አይደለም።

አያቶቻችን መተላለፍ በመፈጸማቸው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ተቋረጠ። እንደ ሳጢአተኛም ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ሞከሩ። እፍረት ስለተሰማቸው ራቁታቸውን በቅጠል ለመሸፈን ሞከሩ። ነገር ግን እግዚአብሔር ፈለጋቸው ፣ የምህረቱን እና የጽድቁን ፍንጭ ሰጣቸው እና ከመገኘቱ አባረራቸው። እሱ የመመለሻ መንገድ ካላዘጋላቸው ፣ ለዘላለም እንደተባርሩ ይቀራሉ። እንደረከሱ ቆመዋል ፤በቅዱሱ ፈጣሪያቸው እና ፈራጃቸው ፊት ተኮንነዋል።

ቁልፍ ጥያቄ እነሆ፦ እግዚአብሔር ፍጹም ከሆነው የአትክልት ቦታ እንዲያባርራቸው ምን ያህል ሳጢአት መስራት ይጠበቅባቸል? ያስፈለገው አንድ ሳጢአት ብቻ ነው። የትኛውንም ያክል “መልካም” ነገር ከዚህ በፊት ስርተው ቢሆን ወይም የትኛውም የግል ጥረትየሳጢአትን አሰከትሎት ሊስወግድ አይችልም።

“መልካም” የእግዚአብሔር መደበኛ መስፈርት ነው። አዳም ሳጢአት ባደረገ ጊዜ በእግዚአብሔር መስፈርት “መልካም” አይደለም። እሱ ሳይናይድ መርዝ ጠብታ የገባበት ንጹህ ውሃ ሆኗል። የተመረዘ ውሃ በብርጭቆ ይዛችሁ የበለጠ ንጹህ ውሃ ብትጨምሩበት መርዝነቱ ይወገዳል? በፍጹም። የሳጢአትን ችግር በምንም አይነት መልካም ስራ ሊወድ አይችልም። መልካም ስራ ሳጢአትን ምሊያሰወግድ ቢሆንም እንኳን ፣ እውነታው ወደ ሳጢአታችን የምንጨምረው “ንጹህ ውሃ” ወይም የጽድቅ ሥራ የሌለን መሆኑ ነው።

በእግዚአብሔር ግምት ፣ መልካሙ ጥረታችን ራሱ የተበከለ ነው።

የአዳም ነፍስ በሳጢአት የተበከለ ነው፣ የሄዋንም እንደዚያው ነው። ነብዩ ዳዊት የእግዚአብሔርን ፍርድ ይነግረናል፦

“የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ።

ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም።” (መዝሙር 14:2-3)

## ጥንድ ችግራችን

የከፍለ ዘመናት ርዝመት ያለው ታሪክ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት እንግሊዝ እስር ቤት ውስጥ ስለነበረ ሰው ይናገራል። አንድ ቀን የእስር ክፍሉ በር ተከፍቶ የእስር ቤቱ ጥበቃ ገባ።

“ደስ ይበልህ!” አለው ጥበቃው። “ንግስቲቱ ይቅርታ አድርጋለሃለች።”

ጥበቃው በሚስገርም ሁኔታ በሰውየው ስሜት ላይ ለውጥ አልታየም።

“አንተ ሰውዬ ደስ ይበልህ እያልኩ እኮ ነው!” ሲል ወረቀት በእጁ ይዞ ደገመው። “ይኸው የይቅርታ ወረቀቱ። ንግስቲቱ ይቅርታ አድርጋልኸለች።!”

ይሄን ጊዜ እስረኛው ሸሚዙን ከፍ አደርጎ አስቀያሚ የሆነውን እብጠት እያሳየው “በጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታተ ሊገድለኝ የሚችል ካንሰር አለብኝ። ንግስቲቱ ይህንን ማስወገድ ካልቻለች በስተቀር ይቀርታው ለእኔ ጥቅም የለውም” አለው።

ሰውየው ከወንጀሉ ይቅር ከመባል ያለፈ ነገር እንደሚያስፈልገው ተረድቷል፣ አዲስ ሕይወት ፈልጎ ነበር።

እያንዳንዱ የአዳም ዘር ልክ እንደ ተፈረደበት ሰው ነው። በምርጫም በመወለድም ሐጢአተኛ ነው፣ ሁለት እጥፍ ችግር ነው ያለበት፦ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ሰራነው ሐጢአት ይቅርታ እንፈልጋለን በተጨማሪ ከቅዱሱ እሱ ጋር መኖር እንድንችል የሚያበቃን ጽድቅና የዘላለም ሕይወት እንፈለጋለን።

ጠቅለል ለማድረግ እጥፍ ችግራችን የሚከተለው ነው፦

- **ሐጢአት** ፦ በደለኛ ኀጢአተኞች ነን። ከሐጢአት ሊያነጻን እና ከዘላለም ፍርድ ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
  የእግዚአብሔርን **ይቅርታ** እንፈልጋለን።
- **እፍረት**፦ እኛ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እርቃናችንን ነን። በጽድቅ ሊያለብሰን እና የዘላለም ሕይወት ሊሰጠን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
  ፍጽምናን እንፈልጋለን።

ኃጢአታችን እና ሃፍረታችን እኛ ልንፈጥረው የማንችለው የማንችለው ጥንድ መፍትሔ ያስፈለገዋል። የምሥራቹ እግዚአብሔር ይህንን እግዚአብሔር አዘጋጅቷል።



# 16

# የሴቷ ዘር

በአንድ ቀዘቃዛ እና ደመናማ ምሽት ሁለት ትንንሽ ልጆች ጥልቅና አዳላጭ ጉድጓድ ውስጥ ወደቁ። ሁለቱም ተጎድተው፣ ፈርተው እና ረዳት አልባነት ተሰምቷቸው ነበር። ከጉድጓዱ ውጪ እርዳታ ካልመጣላቸው በስተቀር መሞታቸው አይቀርም። ሦስት ሰዎች ተስፋ የቆረጠ የድረሱልኝ ጥሪያቸውን ሰሙ። አንዱ ሰውዬ በገመድ ታስሮ ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ወረደ። ልጆቹም ወጡ።

ረዳታቸው የመጣው ከላይ ነው።

አዳምና ሔዋን መጀመሪያ ኃጢአት ስሩ፣ እንደነዚያ ልጆችም ሆኑ። ከወደቁት ከኃጢአት ጉድጓድ ውስጥ ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ ረዳት አልባዎች ነበሩ። ከዘላለማዊ ሞት መዳን ካስፈለጋቸው ፣ ከወደቀው ከሰው ልጅ ውጪ ከላይ እርዳታ መምጣት ነበረበት።

ስለዚህ ነገር አትሳሳቱ። የሰው ልጅ ያለበት ሁኔራ በራሱ መድሐኒት ሊገኝለት የማይችል ከባድ ሁኔታ ነው።

ያለምንም ልዩነት በዘመናት መካከል ከአዳምና ከሔዋን የተወለዱ የአዳም ዝርያዎች በሙሉ ወደ ኃጢአት የሚያዘነብል ማንነትን ወርሰዋል። ሁሉም ከኃጢአት እርግማን በታች ተወልደዋል።

እግዚአብሔር ኃጢአታችን ከኃጢአት እርግማን እና አስከትሎት ነጻ ለማውጣት ፣ከኃጢአት ጉድጓድ መውጣት ለሚፈልጉ ነጻ የሚወጡትን መንገድ ለመስጠት ኃጢአት የሌለበት ሰው ወደ ዓለም ለማምጣት አቅዶ ነበር።

እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው እንዴት ነው? አንድ ሰው እንዴት የአዳምን ኃጢአተኛ ባህርይ ሳይወርስ ወደ ሰው ልጅ ዝርያ

ሊወድ ይችላል? እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ፍንጭ የሰጠው ኀጢአት የሰውን ልጅ በበከለበት ቀን ነው።

እግዚአብሔር "እባብን" አሰቀድሞ እንዲህ ሲል አስጠነቀቀ፦

> "በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።" (ዘፍጥረት 3:15)

ጌታ ሰለ "ዘሯ" ሲናገር ጌታ አስቀድሞ እየተናገረ ያለው ከሴት በሚወለድ ወንድ ልጅ በኩል ኀጢአተኞችን እንደሚያድን እና ሰይጣንን ቀጥቅጦ እኩይን እንደሚያሰወግድ ነው። ይሄ በሰተኋላ የሚመጡት በመቶዎች የሞቆጠሩ ትንቢታት የመጀመሪያው ሲሆን እያንዳንዱ ትንቢትም በአንድ ታሪካዊ ወቅት አዳኙ መሲህ ይህን ዓለም እንደሚጎበኝ በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው።

## ለምን ዘሯ ተመረጠ?

የመሲሁ ሰዋዊ ዝርያ ለምን "የእሷ ዘር መሆን አሰፈለገው ? "**ከሴት** የተወለደ" እንጂ ከወንድ የተወለደ ያልተባለው ለምንድን ነው? (ገላትያ 4:4)

መልሱን እነሆ ፦ የኀጢአተኞች አዳኝ የአዳምን ኀጢአተኛ ዘር ሲጎበኝ ፣ መምጣት ያለበት ከኀጢአት ጉድጓድ ውጪ ነው። ከሰማይ የወረደ ነው።

ጌታ የሴቷ ዘር የሚለውን የመጀመሪያ ትንቢት ከተናገረ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነብዩ ኢሳያስ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር፦

> "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።" (ኢሳያስ 7:14)

አዳኙ ወደ ሰው ቤተሰብ የሚገባው ከወንድ ጋር አካላዊ ግንኙነት በሌላት ሴት በኩል ነው። ይሄ መሲህ የሰውን የወደቀ ዝርያ የሚጎበኘው የአዳምን ኀጢአተኛ ዝርያ ሳይወርስ ነው።

"ቆይ ግን" ንድ ሰው እንዲህ ቢልስ "ሴቶች በሙሉ ኀአተኞች ናቸው፣ በእናቱ ኀጢአተኛ ባህርይ አይበከልም?"

ጥቂት ገጾችን አልፍ ብለን ይህንን ተዓምራዊ ጽንሰት ስላመጣው ሰለ መንፈስ ቅዱስ እንነጋገራለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ኀጢአት የሌለበትን ልጁን በድንግል ማህጸን በኩል

ወደዚህ ዓለም ያመጣበትን ብዙም በግልጽ የማይታይ ስራውን በተመለከተ እንነጋገር፡፡ መሲሁ በአዳም ዘር ውስ ከተሰራጨው ሳጢአት ላይበከል የሚችለው እንዴት ነው?

## በሳጢአት ያልጎደፈ


በምዕራፍ 13 ላይ እንደተነጋገረነው እግዚአብሔር አዳምን የሰው ልጅን ዝርያ ወደ ሰይጣን የሳጢአትና የሞት መግሥት እንዴት እንደመራ ተምረናል፡፡ የተታለለቸው ሄዋን እንጂ አዳም አይደለም፡፡ ሴቶች እንደ ወንዶች ከሳጢአተኛ ባህርይ ጋር ይወለዳሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያሰቀምጠው ከሳጢአተኛ ባህርይ ጋር እንድንወለድ የሚያደርገን ከአዳም ጋር ያለን ግንኙነት ነው፡፡ [138]

በዕብራይስጥ አዳም ማለት ቀይ አፈር ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር የአዳምን አካል የሰራው ከምድር አፈር ነው፡፡ አዳም ሳጢአት ከሰራ በኋላ እግዚአብሔር “ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ **ወደ አፈርም ትመለሳለህና**፡፡” (ዘፍጥረት 3:19) አለው፡፡

በተነጻጻሪነት ሄዋን ማለት ሕይወት ማለት ነው፡፡ ይሄ መጠሪያ ስም የተሰጠው ለመጀመሪያዋ ሴት ነው “አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ፥ **የሕያዋን ሁሉ** እናት ናትና፡፡” (ዘፍጥረት 3:20)፡፡ ሳጢአት ወደ ምድር በገባበት እለት እግዚአብሔር የሳጢአታችንን ችግር የሚፈታበትን መንገድ እና “በዘሯ” በኩል የዘላለም ሕይወትን ለዓለም የሚሰጥበትን መንገድ አዘጋጀ (ዘፍጥረት 3:15)

ምንም እንኳን መሲሁ የሰው ሥጋና ደም የሚኖረው ቢሆንም ከአዳም በሳጢአት ከተበከለ ዘር ግን የሚገኝ አይደለም፡፡ እሱ በሳጢአት ያለተበከለ አይሆናል፡፡

በአስገራሚ ሁኔታ ከስነ ሕይወት አንጻር ስንመለከተው ፣ የሕጻን ልጅ ጾታ የሚወሰነው በአባትየው “ዘር” (ስፐርም) እንጂ በእናትየዋ “ዘር” አይደለም፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ከጽንሰት ጀምሮ ሕጻኑ ከእናቱ የተለየ የደም ዝውውር ሥርዓት እንዳለው እናያለን፡፡ ሜዲካል ሳይንስ እንደሚነግረን “የእንግዴ ልጅ ምግብና ኦክሲጅን ወደ ጽንሱ እንዲደርስ አድርጎ የእናትየዋን ደም ይለያል” [139] እግዚአብሔር እንኳን የመጀመሪያውን ሰው ከመፍጠሩ በፊት ፣ መሲሁ ወደ ምድር የሚመጣበትን መንገድ አቅዷል፡፡



የተቆረጠውን ቅርንጫፍ ታሪክ አስታውሱ። እንደዚያ እንደተነጠለ ሙት ቅርንጫፍ፣ የሰው ልጅ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሙት ፣ ከሕይወት ምንጭ የተለየ ነው። ምንም እንኳን አዳኙ የሚኖረው በአዳም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሙት በሆነ እና በኀጢአት በተበከለ ቤተሰብ መካከል ቢሆንም ከእሱ የተገኘ ግን አይደም። እሱ ራሱ “እውነተኛ የወይን ግንድ” (ዮሐንስ 15:1) ፣ የሕይወት ምንጭ ይሆናል።

እሱ ፍጹም ይሆናል።

“ፍጹም” ማለት ጭረት፣ ጠባሳ ወይም ጭረት አይኖረውም ማለት አይደለም። በባህርይ ፍጹም ይሆናል ማለት ነው። ኅጢአት የሌለበት ባህርይ ይኖረዋል ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ አይተላለፍም ማለት ነው። እሱ “ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ፣ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና” (ዕብራውያን 7:26 አመት) ይሆናል ማለት ነው።

ታዲያ ኅጢአት የሌለበት አዳኝ **ሁለተኛው** አዳም ወይም **የመጨረሻው** አዳም መባሉ ያስድንቃል?

## ሁለተኛው አዳም

> “እንዲሁ ደግሞ፦ **ፊተኛው ሰው አዳም** ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ። ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም። **የፊተኛው ሰው** ከመሬት መሬታዊ ነው፤ **ሁለተኛው ሰው** ከሰማይ ነው።” (1 ቆሮንቶስ 15:45-47)

“የመጀመሪያው ሰው” የሰው ልጅን በሙሉ ወደ ሰይጣን የርኩሰት እና የሞት አገዛዝ እንደመራ ሁሉ ፣ “ሁለተኛው ሰው” በርካታ ሰዎችን ከሰይጣን አገዛዝ አውጥቶ ወደ እግዚአብሔር የከብር የጽድቅና የሕይወት አገዛዝ ያስገባል። በዚህም ምክንያት ሐጢአት የሰው ልጅን በበከለበት ቀን ጌታ አንድ ቀን የሴቷ ዘር ወደ ምድር እንደሚመጣና እንድሚያቆስለው በመጨረሻም እንደሚያጠፋው ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

ነብዩ ሚኪያስ ተስፋ ስለተሰጠው አዳኝ ሲናገር፦

> "አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን **አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ**፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል። እርሱም ይቆማል፥ በእግዚአብሔርም ኃይል በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ግርማ መንጋውን ይጠብቃል፤ እነርሱም ይኖራሉ፤ እርሱ አሁን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናልና።"
> (ሚኪያስ 5:2 ፤ 4-5)

ሚኪያስ የመሲሁን በ"ቤቴልሄም"[140] ከተማ በወለድ ተናግሯል ነገር ግን የመሲሁንም ዘላለማዊነት" አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥" በማለት ተናግሯል።

ዘላለማዊው እሱ ከዘላለም ወደ ጊዜ ውስጥ ይገባል።

## በነብያት አሰቀድሞ ተነግሯል

መሲሁ ከድንግል ተጸንሶ በቤተልሄም እንደሚወለድ የተናገሩ ነብያት መምጣቱን የሚናገር ሰው ደሞ እንድሚመጣ በተጨማሪ ተናግረዋል። በተጨማሪ የእግዚአብሔር ምርጥ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እና የሰው ልጅ የተሰኘ መጠሪያ እንደሚኖረው ተናግሯል። ለዕውራን ማየትን ፣ ለድንቆሮዎች መስማትን እና ለሽባዎች መፍታትን እንድሚሰጥ አሰቀድመው ተናግረዋል። ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ይገባል፣ ወገኖቹም አይቀበሉትም። ይላገጥበታል፣ ይተፋበታል፣ ይገረፋል እናም ይሰቀላል። እሱ ሳጢአት የለበትም ነገር ግን ስለ ሌሎች ለጢአት ይሞታል። በሐብታም መቃብር ይቀበራል፣ ነገር ግን ሙት አካሉ አይበሰብስም። በዚያ ምትክ ሞትን ያሸንፋል፣ ሕያው መሆኑን ያሳያል በተጨማሪም ወደመጣበት ወደ ሰማይ ይመለሳል።[141]

በነብያት የተጻፈውን መስፈርት በሙሉ የሚያሟላ ሰው ማን ነው?

ይሄው ተመሳሳይ ሰው የዓለምን ታሪክ ለሁት ይከፍላል።

ስሙ **ኢየሱስ** ነው።

## እግዚአብሔር ቃን ይጠብቃል

በዘመናት መካከል እግዚአብሔር መሲሁን ወደ ዓለም በአብርሐም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ፣ይሁዳ፣ ዳዊት እና ሰለሞን ዝርያ በኩል ለመላክ ቃል ገባ። ስለዚህም የአዲስ ኪዳን የመጀመሪያ መጽሐፍ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል (በአረብኛ ፦ ኢንጂል)

በሚከተሉት ቃላት ይጀምራል፦

> “የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤”

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው የዘር ሐረግ “ንጉሱ ዳዊት ሰለሞንን ወለደ” በተጨማሪም “ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ።” (ማቴዎስ 1:1-2 ፤16) ክርስቶስ የሚለው የግሪክ ቃል በዕብራይስጥ መሲህ ሲሆን ትርጉሙም የተቀባ [የተመረጠ ]ማለት ነው።[142] እነዚህ የዘር ሐረጎች ኢየሱስ ለዳዊት ዙፋን መብት እንዳለው እና ኢየሱስ የአብርሐም ፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ ቀጥተኛ ዝርያ እንደሆነ እና እግዚአብሔር በረከቱን ለምድር አሕዛብ ሁሉ ለመስጠት የመረጠው መሆኑን ያሳያል።

እግዚአብሔር የማዳን እቅዱን ወደ ተግባር የሚልወጥበት ጊዜ መጥቷል “በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው… ስለ ልጁ ነው።” (ሮሜ 1:2-3)

## የልዑል ልጅ

የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ መልዐኩ ገብርኤል በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደስ መስዋዕት ማቅረብ እና ጸሎት ሰራው የሆነውን ዘካሪያስን የመጎብኘቱን ልብ የሚያንጠለጥል ታሪክ ይናገራል። ምንም እንኳን ዘካሪያስ እና ባለቤቱ ኤልሳቤጥ በጣም ስላረጁ ልጅ መውለድ ባይችሉም ፣ ገብርኤል ግን ሚስትህ ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ብሎ ነገረው። ይሄ ዮሐንስ ከመሲሁ ቀድሞ ይነሳል የተባለው ሰው ይሆናል።

ታሪኩ ሲቀጥል ገብርኤል ማርያም የተባለች እግዚአብሔርን የምትፈራ ወጣት ሴት ለመጎብኘት ይሄዳል።

> “በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፥ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።
>
> መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ፦ ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች

መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና፦ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች።

መልአኩም እንዲህ አላት፦ ማርያም ሆይ፤ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። **እነሆም፤ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ** ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።

ማርያምም መልአኩን፦ **ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።**

መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፦ **መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። …ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና**።" (ሉቃስ 1:26-37)

## የኃጢአተኞች አዳኝ

ከጥቂት ወራት በኋላ ዮሴፍ የታቸችለት ሴት መጸነሷን ይረዳል። በስህተትም በዐይኑ የሚያየው ነገር እውነት እንደሆነ ታሳቢ አደረግ ፦ ማርያም ዝሙት ፈጽማለች። ሊፈጽም ያለውን ጋብቻ ሊያፈርሰው አሰበ።

"እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፤ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፤ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፤ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ **ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ**።"
(ማቴዎስ 1:19-21 አመት)

በዘፍጥረት የመጀመሪያው እንደተገለጠው ፣ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው።[143] በማርያም ማህጸን ዘላለማዊ ቃሉን በማርያም ማህጸን መለኮታዊ በሆነ መንገድ ያስቀመጠው እሱ ነው።

ኢየሱስ የተሰኘው የአማርኛ ቃል የሱስ ከተሰኘው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ፣ የመጠውም የሁሹዋ ከሚለው ወይም በአጭሩ የሹዋ ከሚለው ቃል ነው።

ስሙም ፦ "**ጌታ ያድናል**" ማለት ነው።

"በነቢይ ከጌታ ዘንድ፦እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ **እግዚአብሔር ከእኛ** ጋር የሚል ነው።

ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውንም ወሰደ፤ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤

ስሙንም ኢየሱስ አለው።" (ማቴዎስ 1:22-25አመት)

## የተፈጸመው የእግዚአብሔር ቃል

እግዚአብሔር ሳጢአት ወደ ዓለም በገባበት ቀን የጀመረውን ዕቅድ እየፈጸመ ነው። "ዘሯ" ሊወለድ ነው!

ከጥቂት ገጾች በፊት መሲሁ ስለሚወለድበት ቦታ ሚኪያስ የተናገረውን ትንቢት አይተን ነበር። ጌታ በንጉሱ ዳዊት ከተማ ቤቴልሄም እንደሚወለድ ተናግሮ ነበር።

ነገር ግን ችግር ነበር።

ማርያምና ዮሴፍ ይኖሩ የነበረው በናዝሬት ከተማ ሲሆን ከቤተልሄም በርካታ ቀናት ርቀት ላይ ይገኝ ነበር።

ታዲያ የሚኪያስ ትንቢት የሚፈጸመው እንዴት ነው?

ችግር የለም።

እግዚአብሔር ይህንን ትንቢት ለመፈጸም መላውን የሮም አገዛዝ ያስተባብራል።

"በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች። ቄሬኔዎስ በሶርያ አገር ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆነ። ሁሉም እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ።

ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ።

በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፥ የበኩር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።" (ሉቃስ 2:1-7)

ቃል የተገባው መሲህ ወደ ምቹ እና ውብ ቤተ መንግስት አልገባም። ከዚያ ይልቅ በመጠለያ ውስጥ ተወልዶ ፣ የከብቶች መመገቢያ በረት ውስጥ ተኛ። ወደ ዓለምም የመጣው በጣም ደሃና ተራ ሰዎች እንኳን ቢመጡ እንዳይፈሩት በሚያደርግ መንገድ ነው።

## የመልዐኩ አዋጅ

"በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ። እነሆም፥ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፥ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ።

መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ **እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።** ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችሁ።

ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፦ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።" (ሉቃስ 2:8-14)

በዓለም ታሪክ ውስጥ አስገራሚ የሆነ ምሽት ነው። ረጅሙ ጥበቃ አብቅቷል።

"የበኩር ልጅዋንም ወለደች፥" (ሉቃስ 2:7) [144]

የሴቷ ዘር መጥቷል። ነገር ሁሉ ነብያት አሰቀድመው እንደተናገሩት በእግዚአብሔር መንገድ እና በእግዚአብሔር ጊዜ እየሆነ ነው። [145]

እግዚአብሔር መላእክትን ልኮ የኢየሱስን ልደት ማስታወቁ እና ማክበሩ አይደለም፤ ይህንን አሰደናቂ ሌሊት ለማክበር በምሽቱ

ሰማይ ላይ ልዩ ኮከብ አዘጋጅቷል። በምስራቅ የሚገኙ የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎችና ባለጠጋ ጠቢባን ኮከቧን ተመልክተው ተከተሉ። ተስፋ የተሰጠውን መሲህ መምጣት የሚያመለክት እንደሆነ አውቀው ነበር። ከሩቅ ፋርስ ጀምሮ ያለውን ፈታኝ ጉዞ ካጠናቀቁ በኋላ ፣ እንዚህ የተከበሩ ሰዎች በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ንጉስ ሄሮድ ስ ሄዱ። እንድ ጥያቄም ነበራቸው፦

> "**የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?** ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።" (ማቴዎስ 2:2)[146]

## በሕፃኑ ውስጥ ያለው አካል

በመጠለያ ውስጥ የተወለደው፣ በረት ውስጥ የተቀመጠው ፣ ነብያት አስቀድመው የተናገሩለት፣ መላዕክት ያበሰሩት፣ በእረኞች የተበኘው፣ በኮከብ የተከበረው፣ በጠቢባን የተመለከው ይሄ ልጅ ማን ነው?

እስቲ መላዕክት ለእረኞች የነገሯቸውን ነገር ደግመን እናዳምጥ፦

> "እነሆ፣ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም **ክርስቶስ ጌታ** የሆነ ተወልዶላችኋልና።"
> (ሉቃስ 2:10-11)



በዚያች ትንሽ ሰውነት ውስጥ ይገኝ የነበርው ጌታ ነው።



# 17

# ማን ሊሆን ይችላል

"የሚዘሉ ሚዳቋዎች የተረጋጋ ልጅ ሊወልዱ አይችሉም።"
— የወሎፍ ምሳሌ

ልክ የሚዳቋ ዘር የሚዳቋ እንደሚሆነው ሁሉ ፣ ኀጢአተኞች የሚፈጥሩትም ዘር የኀጢአተኛ ባህርይ ያለው ነው። በራሱ ከተተው የሰው ልጅ ከኀጢአት ዑደት ነጻ የሚወጣበት ምንም አይነት መንገድ የለም። ይሄ ደግሞ ያስታውቃል።

## ኀጢአተኞቹ

በአሜሪካን ሐገር የሚገኘውን የፊልም ኢንዱስትሪ ተመልከቱ። በያንዳንዱ ዓመት ሆሊዉድ የራስ ወዳድ ፣ የርኩሰት፣ የሥነ ምግባራዊ ዝንፈት፣ የጸያፍ ንግግር ፣ የዓመጻ ፣ የበቀል እና የማታለል ጠባይ ያሉባቸው ሴትና ወንድ ጀግኖች የሚታባቸው በዙ ገንዘብ የሚስገኙ ፊልሞችን እያመረተ ያሰራጫል። የፊልም ጸሐፊዎች ግን አሰበው እና አቅደው በፊልማቸው ውስጥ የሚገኙ "መልካም ሰዎች" ኀጢአተኛ ባህርይ እንዲኖሯቸው የሚያደርጉት? ለምንድን ነው በፊልሞቻቸው ውስጥ ያሉ "ጀግኖችን" ጻድቅ፣ ቸር ፣ ራስ ወዳድ ያልሆኑ፣ ይቅር ባይ እና ቅን የማያደርጓቸው? የሰው ልጅ በኀጢአት ስለተበከለ ነው። የሰው ልጅ በምናቡ የፈጠራቸው ገጸ ባህሪያት እንኳን በኀጢአት የተበከሉ ናቸው። እንዲህ አይነት ብክለት ደግሞ በሆሊውድ ብቻ የተገደበ አይደለም።

የሰው ልጅ ወደ ኀጢአት ያዘነበለ ጠባይ በተለያዩ ስውር

መንገዶቹ ራሱን ይገልጣል። ለምሳሌ፣ ከዐረብ ሐገራት ከሆናችሁ፣ የከፍለ ዘመናት ያክል ረጅም እድሜ ያለው አፈ ታሪክ ገጸባህርይ የሆነ ጁሃ የሚባለ ሰው ምናልባት ልታውቁ ትችላላችሁ። የጁሃ እና የአህያው ታሪክ ሊያስቀን ይቾላል። ስለዚህ ብልሕ ገጸ ባህርይ ብልጠት እና ቀልድ የተሞላባቸው ቃላት እና ዘዴዎች በራ ወዳድነት፣ በተሳዳቢነት መንፈስ ፣ ርኩስ ሐሳቦች፣ በቀል፣ ማታለል እና ቃልን በማፍረስ የተሞሉ ናቸው። አስቡት እስቲ! ምርጥ የምትሏቸው ገጸ ባህሪያት እንኳን በኃጢአት የተበከሉ ናቸው። ከጁሃ ታሪኮች ውስጥ የተሰወዱ ቀላል ታሪኮች እነሆ፦

አንድ ጎደኛው ወደሱ መጣ።

ጎደኛው እንዲህ አለው "ጥቂት ገንዘብ ልታበድረኝ ቃል ገብተኸል። ያንን ቃልህን እንድታከብር ልጠይቅህ መጥቻለሁ።"

ጁሃ እንደዚህ አለው "ወዳጄ እኔ ለማንም ሰው አላበድርም፣ ደስ እንዲልህ ግን ቃሌን እሰጥኸለሁ።"[147]

ከዚህ ጅሃ ልቦለዳዊ ታሪክ እንደምንረዳው እኛም ልናከብው ያልሰብነውን ቃል እንደምንገባ ነው። በወደቀው ማንነታችን ፣ እኛም ልክ እንደ ጁሃ ነን።

ነገር ግን በታሪክ ውስጥ ቃሉን ሙሉ ያከበረ አንድ ሰው[148] ነበር። ሁልጊዜ ይናገር የነበረው እውነት ነው። አታሎ፣ ተሳድቦ ፣ አስፈራርቶ ወይም በቀልን ፈልጎ አያውቅም ነበር።

ስሙ **ኢየሱስ** ነው።

> "እርሱም **ኃጢአት** አላደረገም፤ **ተንኰልም** በአፉ አልተገኘበትም ፤ ሲሰድቡት **መልሶ አልተሳደበም** መከራንም ሲቀበል **አልዛተም**፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤"
>
> (1 ጴጥሮስ 2:22-23 አመት)

## ኀጢአት አልባው

ኀጢአት ከበረታበት የዓለም ባህል ጋር አንጻር የኢየሱ ስሕይወት ለየት ባለ ሁኔታ ጎልቶ ይታያል። ከተወለዱ ሁሉ ኀጢአት የሌለበት እሱ ብቻ ነበር። "ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፤" (ዕብራውያን 4:15) የርኩስት ሐሳብ በአዕምሮው ውስጥ አልፎ አያውቅም። በከንፈሩ ላይ የጭካኔ ቃል ታይቶ አያውቅም። ከእናቱ ልጆች ወንድሞቹ እህቶቹ ጋር

በተራ ቤተሰብ ውስጥ በናዝሬት[149] ሲያድግ፣ አስርቱ ትዕዛዛትንና የእግዚአብሔርን ሕግ በሙሉ በውስጡም በውጪውም ይታዘዝ ነበር። ምንም እንኳን ኢየሱስ እንደኛ ያለ አካል ቢኖረው ም፣ ወደ ኀጢአት ያዘነበለ ማንነት ግን አልነበረውም።

> "እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፤ በእርሱም ኃጢአት የለም።" (1ዮሐን ስ 3:5)

በሰላሳ ዓመቱ በምድር ላይ ዋነኛ ስራውን ጀመረ።[150] በእግዚአብሔርና በሰይጣም መካከል ያለው ጦርነት ተባባስ። ሰይጣን የእግዚአብሔር ልጅ ሊቀጠቅጠው መምጣቱን አውቆ ነበር። እንዴት ሊያደርገው እንዳሰበ ግን አያውቅም ነበር።

ሰይጣን የመጀሪያውን ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲተላለፍ እንደፈተነው ሁሉ ሁለተኛውን ፣ ፍጹሙን ሰው ከእግዚአንብሔር ሕግ በተቃራኒ እንዲያደርግ ለመፈተን ይሞክራል።

> "ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ፤ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ፤ አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ። በነዚያም ቀኖች ምንም አልበላም፤ ከተጨረሱም በኋላ ተራበ።
>
> ዲያብሎስም፦ **የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ**፣ ይህን ድንጋይ፦ እንጀራ ሁን ብለህ እዘዝ አለው።
>
> ኢየሱስም፦ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል ብሎ መለሰለት።" (ሉቃስ 4:1-4)

ልብ በሉ ስይጣን ኢየሱስ ምንም አይነት "ክፉ" ነገር እንሰራ አልፈለገም። ዲያቢሎስ የፈለገው ይሄ ሐጢአት የለሽ ሰው ("የእሱን" ግዛት የወረረው ሰው) በሰማይ ከሚገኘው አባቱ ተለይቶ በራሱ እንዲመላለስ ማድረግ ነው። በምዕራፍ 11 እንዳየነው በእግዚአብሔር ላይ ሳንደገፍ የምናስበውም ሆነ የምናደርገው ነገር **ኀጢአት** ነው።

ዋናውም ነጥብ፦ መሲሁ አንዲት ነጠላ ኀጢአት ቢሰራ ኖሮ የአዳምን የተረገመ ዘር ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ የማውጣት ተልዕኮውን መፈጸም አይችልም ነበር።

በርካታ ብድር ያለበት ሰው የሌላን ሰው ብድር መክፈል እንደማይችለው ሁሉ ኀጢአተኛም የሌላኛውን ኀጢአተኛ

ዕዳ ሊከፍል አይችልም። ነገር ግን የሰው ልጅ[151] የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ የራሱ የኃጢአት ዕዳ የለበትም።

በዚህ መካከል ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፍጹም ዕቅድ ውጪ በራስ በመስራት ሐጢአት እንዲሰራ ለማድረግ ደጋግሞ ሞክሯል። በእያንዳንዱ ጊዜም ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ መልሷል።[152]

> "ዲያብሎስም ረጅም ወደ ሆነ ተራራ አውጥቶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው። ዲያብሎስም፦ ይህ ሥልጣን ሁሉ ክብራቸውም ለእኔ ተሰጥቶአል ለምወደውም ለማንም እሰጠዋለሁና ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ስለዚህ አንተ በእኔ ፊት ብትሰግድ፥ ሁሉ ለአንተ ይሆናል አለው።
>
> ኢየሱስም መልሶ፦ ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው።" (ሉቃስ 4:5-8)

እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ የገዢነት ስልጣን እንደ ሰጠው ሁሉ ፣ ሰይጣን ደግሞ አዳም እሱን በተከተለ ጊዜ የሰረቀውን ኢየሱስ እንዲገዛ እያቀረበለት ነበር።[153]

በተቃራኒው ፣ ኢየሱስ ስይጣንን አልታዘዘውም።

የእግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆኗል።

## የኢየሱስ ተከታዮች

ኢየሱስ ይፋዊ ግንኙነቱን ከጀመረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በሚሄድበት ቦታ ሁሉ እንዲከተሉት አሥራ ሁለት ሰዎችን መረጠ። በርካታ ሴቶችም ተከተሉት። እነዚህ ወንዶችና ሴቶችም ኢየሱስ ለተናገረው ነገር የዐይን ምስክሮች ሆኑ።

> "ከዚህም በኋላ እየሰበከና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች እየተናገረ በየከተማይቱ በየመንደሩም ያልፍ ነበር፤ አሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፥ …ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።" (ሉቃስ 8:1-3)

ኢየሱስ ክርስቶስ ለወንዶች ፣ ሴቶች እና ሕጻናት እኩል ክብር ያሳይ ነበር። ወንጌላት ኢየሱስ ሴቶችን በአክብሮት ሲያስተናግድ

ያም ደግነቱ የአይሁድና የሮማውያንን የዚያን ዘመን ባህል የተሻገረ ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ የሚገኙ ሰዎችን በሙሉ ዋጋ ያላቸው ፍጡራን አድረጎ ያያል ነገር ግን እንዲያዳምጠው፣ እንዲያምነው እና እንዲከተለው ሲል ማንንም አስፈራርቶ አያውቅም። እውነትን ለመስማትና ለመቀበል አዕምሯቸውና ልባቸው ከተዘጋጀ ሰዎች ጋር ምንም ዋጋ ቢያስከፍለው ጊዜ ማሳለፍ ይወድ ነበር።

## ቁልፍ ጥያቄ

ምንም እንኳን በርካታ ተራ ሰዎች ኢየሱስን ቢከተሉም ፣ የአይሁድ መሪዎች ግን አልተከተሉትም።

ኢየሱስ አንድ ቀን ወሳኝ ጥያቄ ጠየቃቸው፦

> **“ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?”** (ማቴዎስ 22:42)

እነሱም መሲሁ የንጉስ ዳዊት ዘር ይሆናል ሲሉ መለሱለት። ኢየሱስም ተሰፋ የተገባው አዳኝ ምድራዊ የዳዊት ልጅ ሰማያዊ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን ዳዊት በትንቢቱ ተናግሯል አላቸው። [154]

አሰቀድሞም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቋቸው ነበር፦

> “ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ።
>
> እነርሱም፦ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።
>
> እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።
>
> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።” (ማቴዎስ 16:13-17)

እኛም አሁንም ሆነ ዘግይተን ተመሳሳይ ጥያቄ መመለሳችን አይቀርም፦ ስለ ኢየሱስምን ታስባላችሁ? የማንስ ልጅ ነው?

## አንዳንዶች ምን ይላሉ

ለበርካታ ምዕራባውያን ፣ኢየሱስ ከእርግማን ቃል የዘለለ አይደለም፡፡


ሌሎች ደግሞ ታላቅ የሥነ ምግባር መምህር እንደነበረ እንጂ ከዚያ የበለጠ አይደለም ይላሉ፡፡

ኦርቶዶክስ አይሁድ የኢየሱስን ስም መጥራት ስለማይፈልጉ "ያ ሰውዬ ሲሉ ብቻ ይጠሩታል፡፡

የሂንዱ እምነት ተከታዮች ከበርካታ መለኮታዊ ግልጠት ከሆኑ ወንድ እና ሴት አማልክቶቻቸው መካከል አንዱ አድርገው ያዩታል፡፡


ሙስሊም ጎረቤቶቼ ደግም እንዲህ ይሉኛል፦ "እንደ ታላቅ ነብይ እናከብረዋለን ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም፡፡"

አንድ ከእኔ ጋራ የተጻጻፈ ሰው እንዲህ ሲል ይገልጠዋል፦



የምኖረው በሳዑዳአረቢያ ነው ... እኛ ኢየሱስ ነብይ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እንዳልሆነ እናምናለን። ኢየሱስ አልተገደም። ተመልሶ ይመጣል የዚያን ጊዜ ከማን ጋር እንደሚቆም ሁላችንም እናያለን። ይሄ ነገር በአንተ የሕይወት ዘመን ተፈጽሞ ውቡን ሐይማኖታችንን ተቀላቅለህ እውነተኛውን ብርሃን እንድታይ ስፉ አደርጋለሁ።

ማሌዢያዊ ግለሰብም እንዲህ ብሎኛል፦



እኔ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ እና ሰው ሆኖም መስሎም እንደማያውቅ አውቃለሁ። እግዚአብሔር በሰው መልክ ይገኛል ብሎ የሚያስብ ሰው ካለ ያ ሰው እግዚብሔርን በትልቁ የሚሳደብ ነው።

እነዚህ አመለካከቶች የሚመነጩት ቁርዓን ስለ መሲሁ ኢየሱስ ከሚናገረው ነው፡፡

## ቁርዓን ምን ይላል

ቁርዓን በተደጋጋሚ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከነብይ የበለ እንዳልሆነ" ይናገራል (ሱራ 4:171-173 ፤ 5:75 ፤ 2:136) ነገር ግን በሙስሊሞች የተከበረው መጽሐፍ ኢየሱስ ከነብያት መካከል የተለየ እንደሆነ የሥጋ አባት እንደሌው ፣ ኢሳ ኢብን መርያም "የማርያም ልጅ ኢየሱስ" (ሱራ 19:34) ቁረዓን የነብያትን ሳጢአት ሲናገር ኢየሱስ ሳጢተኛ እንደሆነ አይናገርም፡፡ "ቅዱስ ልጅ"[155]

ተብሏል። ቁርዓን ኢየሱስን ሕይወትን የመፍጠር፣ የዕውራንን ዐይን ማብራት ፣ ለምጻሞችን ማንጻት፣ ሙታን የማስነሳት ሳይል እንዳለው ይናገራል።[156] ቁርዓን የተከበሩ መጠሪያዎችን አል መሲህ (መሲህ)፣ ሩአህ አላህ(ነፍስ/ የእግዚአብር መንፈስ) እና ቂልመት አላህ (የእግዚአብሔር ቃል) ለኢየሱስ ብቻ ሰጥቷል።[157]

ቁረዓን ሰለ ኢየሱስ ልዩ መሆን የሚሰጠው ማረጋገጫ ስንገነዘብ፣ ቁረዓን "ስለማርያም ልጅ መሲሁ" የሚሰጠን መረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚሰጠን መረጃ የተለየ ነው። ለምሳሌ ከላይ የጠቀሰናቸውን መጠሪያዎች የሚሰጠው ያው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡፡ "የመርየም ልጅ አልመሲህ ዒሳ **የአላህ መልዕክተኛ** ወደ መርየም የጣላት (የኹን) ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው። በአላህ እና በመልክተኞቹም እመኑ(አማልክት)ሦስት ናቸው አትበሉ ተከልከሉ ለእናንተ የተሻለ ይሆናልና **አላህ አንድ አምክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው**።" (ሱራ 4:171 ፒክታል)

በሴኔጋል ልጆችና አዋቂዎች "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም ! እግዚአብሔር ልጅ የለውም!" ለማት መፈጠናቸው ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ እርግጠኝነት "ኢየሱስ አልተሰቀለም!" ይላሉ።

ኢየሱስ አልተሰቀለም የሚለውን ሐሳብ ያገኙት ከየት ነው?

ይሄ ሐሳብ የተገኘው ከቁርዓን ውስጥ ሲሆን እንዲህ ይላል፦ "በመካዳቸውም በመርየም ከባድ ቅጥፈትን በመናገራቸውም ምክንያት (ረገምናቸው)፦እኛ የአላህን መልዕክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲህ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው) **አልገደሉትም አልሰቀሉትምም** (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ) እዝኢያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ ከርሱ (መገደል በመጠራጠር) ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ነገር ከመከተል በሰተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም **በእርግጥም አልገደሉትም**። ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው፣ አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነው።" (ሱራ 4:156 – 158)

## መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል

ቁርዓን ከመጻፉ ከክፍለ ዘመናት በፊት ፣ የብሉይ ኪዳንን እና የአዲስ ኪዳንን ቅዱሳት መጽሐፍት የጻፉት አርባዎቹ ነብያት እና ሐዋርያት ሰለ መሲሁ እና ተልዕኮው የሳሉት ምስል የተለየ ነው።

የኢየሱስን "የእግዚአብሔር ልጅ" የተሰኘ መጠሪያ ከሶስት ዓመታት በላይ አብሮት የተመላለሰው ዮሐንስ ስለ እሱ እንዲህ ሲል መስክሯል፦

"ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ነገር ግን **ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ** እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም **በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ** ዘንድ ይህ ተጽፎአል።" (ዮሐንስ 20:30-31አመት)

ሐዋርያው ዮሐንስ በተጨማሪ እንዲህ ብሏል፦

"በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። ...ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።" (ዮሐንስ 1:1-3 ፣ 14 አመት)

ከዓመታት በፊት ሙስሊም ወዳጄ እንዲህ ሲል ነገረኝ "ርዓን ለኢየሱስ ቂልመት አላህ እና ሩህ አላህ የሚል መጠሪያ ይሰጠዋል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እና ነፍስ ከሆነ አምላክ ነው ማለት ነዋ!"

በስተኋላም ጓደኛዬን አንዳንዶች እግዚአብሔርን በመሳደብ እና ሺርቅ (በዐረብኛ ፦ ለእግዚአብሔር እኩያ ማበጀት[158]). ፈጽሟል በለው ከሰሱት። ጥሩ ሰዎች ነው ያጋጠሙት! ኢየሱስ በአይሁድ የሐይማኖት መሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተከሶ ነበር።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፦

"'**እኔና አብ አንድ ነን።**'

**አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።**

አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።

ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው።

አይሁድም፦ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ **ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት።**" (ዮሐንስ 10:30 -33)

አይሁድ ሉሲፈር ሊያደርገው የሞከረውን አይነት ነገር አድርጓል ብለው ከሰሱት፣ እሱም ልዩና የከበረውን እግዚአብሔር

ብቻ የሚገባውን ቦታ ለማግኘት መሞከር። ኢየሱስ ራሱን እግዚአብሔር ለማድረግ ሞክሯል ሲሉ ከሰሱት።
ነገር ግን የተገቢጦሽ ነው የተረዱት።

## ሥጋ መልበስ፣ ወደ መልኮትነት መለወጥ

ኢየሱስም ቢሆን ነብያት ሰው አምላክ ይሆናል ብለው አላስተማሩም፣ በዚያ ምትክ ግን አምላክ ሰው ይሆናል ብለው ያስተምራሉ።

ለምሳሌ፣ መሲሁ ከመውለዱ ከ700 ዓመታት በፊት ፣ ነብዩ ኢሳያስ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር፦

> "በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው። **ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና**፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ **ኃያል አምላክ**፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።"
>
> (ኢሳያስ 9:2 ፣ 6)[159]

ኢሳያስ የሚከተሉትንም ቃላት ስለ መሲሁ ጽፎ ነበር፦

> "የምስራች የምትነግሪ ጽዮን ሆይ፥ ከፍ ወዳለው ተራራ ውጪ፤ የምስራች የምትነግሪ ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ድምፅሽን በኃይል አንሺ፤ አንሺ፥ አትፍሪ፤ ለይሁዳም ከተሞች፦ **እነሆ፣ አምላካችሁ!** ብለሽ ንገሪ።"
>
> (ኢሳያስ 40:9)

ከመጀመሪያው ጀምሮ የእግዚብሔር ዕቅድ ሥጋ መልበስ እንጂ ሰውን መለኮት ማድረግ አልነበረም። ሰው አምላክ ሆነ ብሎ ሐሳብ ማቅረብ አምላክን መሳደብ ነው፣ ነገር ግን ዘላለማዊ ቃል ሰው እንደሆነ መገንዘብ ግን የእግዚአብሔርን ዘመን የማይሽረው ዕቅድ መቀበል ነው።

## በወረቀት እና በአካል

አንድን ሰው በአግባቡ ማወቅ ከፈልጋችሁ ፣ ተመራጩ መንገድ የትኛው ነው?

- ግንኙነታችሁ በጽሁፍ ደብዳቤ ብቻ ማደረግ
- ወይም ደብዳቤ ለጊዜው ከተለዋወጣችሁ በኋላ ሰውየውን ፊት ለፊት ማግኘት እና አብሮ ጊዜ ማሳለፍ

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ቢሆንም ከአዳምና ከሄዋን ጋር የተመላለሰው ፣ ያወራው እና ዘሮቻቸው በግላቸው እንዲያውቁት የሚፈልገው እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለው ግንኙነት በወረቀት ብቻ ተገድቦ እንዲቀር ስላልፈለገ ነው። ከመጀመሪያውም ከእኛ ጋር በአካል ለመገናኘት አቅዷል። ለበርካታ ክፍለ ዘመናት ነብያት ቃሉን በፓፒረስ ጥቅልል እና በእንስሳት ቆዳ ላይ እንዲጽፉ የፈቀደው ጌታ ፣ ለሰው ልጅ የሰው ልጅን ቆዳ ለብሶ ሊገለጥ ቃል ገብቷል። እግዚአብሔር ቃሉን በመጽሐፍ መልክ ብቻ ሳይሆን ቃሉን በአካል ሊያቀርብልንም አቅዷል።

> "ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ፦ መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ።"
> (ዕብራውያን 10:5) [160]

> "እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥" (1ጢሞቴዎስ 3:16 አመት)

## ከክብሩ በታች?

በተደጋጋሚ በሰዎች መካከል እንደሚያድር ቃል መግባቱ ባሻገር ሰዎች እንዲህ ሲሉ እሰማለሁ፦ "የእግዚአብሔር ምጡቅ ክቡርነት ሰው ለመሆን አይመጥነውም!"

ምንም እንኳን የስጋ መልበሱ ነገር ለመረዳት የሚያስቸግር ቢሆንም ግን ከክብሩ በታች ነውወይስ ደግሞ የእግዚአብሔር ባህርይ ዋና አካል ነው በተጨማም ለራሱ ከፈጠራቸው የሰው ልጆች ጋር ግንኙነቱን ለማስቀጠል ዕቅዱ ነበረ?

በሕይወታችን ብዙ ጊዜ ቀረቤታ የሚኖረን እኛ የተለማመድነውን ነገር ከተለማመዱ ሰዎች ጋር ነው። እኛን ለማጽናናት የበለጠ ብቃት የሚኖራቸው በተመሳሳይ ትግልና መከራ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ናቸው።

> "**እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ… በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ**። እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና። **ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ**፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።"
> (ዕብራውያን 2:14 ፣ 18 ፤ 4:15)

ከመጀመሪያውም የእግዚአብሔር ዕቅድ የነበረው የሰው ልጅን ውሱንነት እና የሥጋን ምኞት የለሽነት ለመውሰድ

እጆቹን ለማቆሸሽ ፣ ለመራብ፣ ለመጎዳት እና የተለማመድነውን ለመለማመድ ነው። ከዚህ በተቃራኒ የሚያስተምሩ የእግዚአብሔርን ነብያት እና የእግዚአብሔርን ዕቅድ መናቃቸው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ባህርይ እና ጠባያት መናቃቸው ነው። እግዚአብሔር ራሱን ሰዎች በግል እንዲያውቁት እንደሚፈልግ ታማኝና አፍቃሪ አድርጎ ራሱን መግለጡን ከመቀበል ይልቅ እሱን የማይጨበጥ እና የማይታወቅ እንደሆነ ይናገራሉ።

ሌሎችን ለማገልገል እና ለመባረክ ወደ እነሱ ደረጃ ዝቅ ለማለት አለመፍቀድን "ክብር" የሚያደርገው ምንም ነገር የለም። ፈጣሪያችን በየትኛውም የታሪክ ወቅት ወደኛ ደረጃ ዝቅ ማለትን ሲያጣጥል አናይም። [161]

> "የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ **ሀብታም ሲሆን**፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።" (2ቆሮንቶስ 8:9)

ዘላለማዊው ቃል ይህንን ዓለም የጎበኘው ለእኔ እና ለእናንተ ሲል ነው። የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ በክብር እና በአክብሮት "ሐብታም ሲሆን" ቢሆንም "ደሀ ሆነ" የአገልጋይን ቦታ ያዘ ነገር ግን ይህንን ያደረገው እኛ እንደ ይቅርታ፣ ጽድቅ፣ የዘላለም ሕይወት ፣ ፍቅር፣ ደስታ ፣ ሰላም እና ቅዱስ ምኞት እንጂ በገንዘብና በቁሳዊ ነገሮች ባለጠጋ እንድንሆን አይደለም።

## የታላቅነት ፍቺ

ብዙሃን እግዚአብሔር ስጋና ደም አካል ለብሶ ወደምድር መምጣቱ እጅግ በጣም ታላቅ ነው ይላሉ።

ይሄን ሊሉ የቻሉት የእነሱ የታላቅነት ፍቺ ከእግዚአብሔር የታላቅነት ፍቺ ስለሚለይ ይሆን?

ኢየሱስ የሚከለውን ባለ ጊዜ እውተኛ ታላቅነትን ፈትቶታል፦

> "ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ የአሕዛብ አለቆች ተብሎ የምታስቡት እንዲገዙአቸው ታላላቆቻቸውም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ **ታላቅ** ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ **እንዲሁ**

**የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም**።”
(ማርቆስ 10:42-45 አመት)

ታላቅ ሰው ራሱን በጣም ዝቅ የሚያደርግና ሌሎቹን በጥሩ ሁኔታ የሚያገለግል ነው። [162]

ፈጣሪያችንም ያረገልን ይሄንኑ ነው።

## የንፋሱና የወጀቡ ጌታ

አንድ ቀን ኢየሱስ ከደቀመዛርቱ ጋር በዓሳ ማጥመጃ ጀልባ በገሊላ ባህር ላይ ነበር።

“እነሆም፣ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር **ታላቅ መናወጥ** ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር።

ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ጌታ ሆይ፥ አድነን፥ ጠፋን እያሉ አስነሡት።

እርሱም፦ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ።

ሰዎቹም፦ ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ **ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ**።”
(ማቴዎስ 8:24-27)

የደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ እንዴት መመለስ ትቻላላችሁ?

## “ይሄ ማን ሊሆን ይችላል?”

በግልጽ እንደታየው ኢየሱስ ሰው ነው። ጀልባዋ ውስጥ ተኝቶ ነበር፣ እነሱም እንደደከመው እንደ ተራበ እና እንደተጠማ ያውቁ ነበር። ነገር ግን ተነስቶ ማዕበሉን ገሰጸ ው። በቅጽበትም ቁጡው ንፋስ ጸጥ አለ የሚናወጠው ባህርም ተረጋጋ።

ደቀ መዛሙርቱ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቃቸው አያስደንቅም።

“ይሄ ማን ነው?”

ከሺህ ዓመታት በፊት የእግዚአብሔር ነብያት እንዲህ ብለው ነበር፦

> “አቤቱ የሠራዊት አምላክ፥ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? … የባሕርን ኃይል አንተ ትገዛለህ፥ የሞገዱንም መናወጥ አንተ ዝም ታሰኘዋለህ።” (መዝሙር 89:8-9)

ይሄ ማን ነው? ወንጌል በተጨማሪም ይሄ ሰው በባህር ላይ እንደሄደ ይናገራል።[163] የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንድ ጊዜ በድጋሚ “በራሳቸውም ያለ መጠን እጅግ ተገረሙ” (ማርቆስ 6:51) አሉ። ነገር ግን ኢየሱስ በውሃ ላይ የሄደው ሰው እንዲደነቅበት ፈልጎ ሳይሆን ማንነቱን እንዲያውቁ ሊያግዛቸው ፈልጎ ነው።

ከሁለት ሺህ ዓመት ፊት ነብዩ ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ነበር፦

> “ሰማያትን **ብቻውን** ይዘረጋል፥ **በባሕሩም ማዕበል ላይ ይረግጣል**።” (ኢዮብ 9:8)

ይሄ ማን ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር ነጥቦቹን እንድናገናኝ እና ኢየሱስ ማን እንደ ነበር እና እንደ ሆነ እንድንረዳ ይጋብዘናል።

በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙዎቹ ይህንን አያደርጉም።

> “በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ **ዓለሙም አላወቀውም**።” (ዮሐንስ 1:10 አመት)

ይሄ ማን ሊሆን ይችላል? አንድ ቀን ኢየሱስ ራሱ ተቃዋሚ ከሆኑ የሐይማኖተኛ ሰዎች ስብስብ ጋር በተነጋገረ ጊዜ ይህንን ጥያቄ መልሷል።

## “እኔ”

> “ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም።
>
> አይሁድ፦ ጋኔን እንዳለብህ አሁን አወቅን። አብርሃም ስንኳ ሞተ ነቢያትም፤ አንተም፦ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አይቀምስም ትላለህ። በእውኑ አንተ ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያትም ሞቱ፤ ራስህን ማንን ታደርጋለህ? አሉት።

> አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፤ አየም ደስም አለው።
>
> አይሁድም፦ ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት። ኢየሱስም፦ **እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።**
>
> ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ።" (ዮሐንስ 8:12 ፣ 51-53 ፣ 56-59)

ኢየሱስን ሊወግሩት የፈለጉት ለምንድን ነው? "**ቃሌን** የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም **ሞትን አይቀምስም** ትላለህ።" እና "አብርሃም **ሳይወለድ እኔ አለሁ** አላቸው።" ኢየሱስ በሞት ላይ ያለውን ሥልጣን ብቻ ሳይሆን በኣብርሐም ላይ ያለውን የበላይነት (ከ 1900 ዓመታት በፊት የሞተው) ማሳየት ብቻ ሳይሆን እራሱን በእግዚአብሔር የመጠሪያ ስም "**እኔ አለሁ**" ብሎ ጠራ።[164]

ኢየሱስን የሚያዳምጡ ሰዎች ማለት የፈለገውን ተረድተው ነበር። እግዚአብሔርን በመሳደብ ከሰውት ሊወረውሩበት ድንጋይ ያነሱት ለዚህ ነው።

## እግዚአብሔርን ብቻ አምልኩ

ኢየሱስ መመለክ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ደጋግሞ አሰተምሯል። "ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ" (ማቴዎስ 4:10) ያለውም በዚህ ምክንያት ነው። ነገር ግን ወንጌላት ከአሥር ባላነሱ ሁኔታዎች ሰዎች በኢየሱስ ፊት ተደፍተው ሲያመልኩት ተዘግቧል።

አንድ ቀን "እነሆም፣ ለምጻም ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ **ሰገደለት**።[165] እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፦ እወዳለሁ፥ ንጻ አለው። ወዲያውም ለምጹ ነጻ።" (ማቴዎስ 8:2-3) ኢየሱስ ለምጻሙ ሰውዬ ስላመለከው ገስጾታል?

በፍጹም፣ ዝም ብሎ ዳሰሶ ፈወሰው።

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ቶማስ የተባለ ደቀ መዝሙር "ጌታዬ እና አምላኬ!" ብሎ ሰገደለት። ኢየሱስ ለምጻሙ ስላመለከው ገስጾታል?

በፍጹም "ቶማስም፦ ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።" (ዮሐንስ 20:28-29) ብሎታል።

ይሄ ስለ ኢየሱስ ማንነት የሚያስተምረን ለምንድን ነው?

## አናንተ ወስኑ

ምንም እንኳን ስለ ኢየሱስ የምናምነው ነገር የግል ምርጫችን ቢሆንም ፤ ስለ ግን እሱ እርስ በርሱ የሚጋጭ አመለካከት ሊኖረን አይገባም። ጎረቤቶች እንደሚነግሩኝ ኢየሱስ "ታላቅ ነብይ" ከሆነ፣ ዘላለማዊ ቃል እና የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ያለውም እሱ ነበረ። ስለዚህ ኢየሱስ "ከነብይ ያልበለጠ" ነው ካልን ፤ የኢየሱስን ምስክርነትና የነብያትን መልዕክት መካዳችን ነው።[166]

ሲ. ኤስ. ሉዊስ የተባለው ቀድሞ ተጠራጣሪ የነበረና የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ታላቅ አሳቢ የነበረ ሰው ስለ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦

> ሰዎች ስለ ኢየሱስ በተደጋጋሚ ከሚናገሩት የሞኝነት ንግግር ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ እየሞከርኩ ነው፦ 'ኢየሱስን እንደ ታላቅ የሥነ ምግባር መምህር ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ፣ ነገር ግን አምላክ ነኝ የሚለውን ነገር አልቀበልም። ልንናገራቸው ከማይገቡን ነገሮች መካከል አንዱ ይሄ ነው። ተራ ሰው የሆነ እና ኢየሱስ የሚናገራቸውን ነገሮች የሚናገር ሰው ታላቅ የሥነ ምግባር መምህር ሊሆን አይችልም። ወፈፌ ወይም ከሶዖል የመጣ ዲያብሎስ ሊሆን ነው የሚችለው። ምርጫችሁን ማድረግ አለባችሁ። ይሄ ሰውዬ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር ፣ አሁንም ነው፤ ወይም ወፈፌ ወይም ከዛም የባሰ ነው። ሞኝ ነው ብላችሁ በራችሁን ልትዘጉበት፣ ልትተፋበት፣ እንደ አጋንንት አይታችሁ ልትገድሉት ትችላላችሁ ወይም ደግሞ በፊቱ ተደፍታችሁ ጌታ እና አምላክ ልትሉት ትችላላችሁ። ነገር ግን ታላቅ መምህር ነው እያልን አንናንቋሸው። ይህንን ለመሆን ሐሳቡም የለውም።[167]

## "በግልጽ ንገረን"

በተደጋጋሚ አንድ ሰው እንዲህ ይለናል ፦ ኢየሱስ "እኔ አምላክ ነኝ!" የሚልበትን ቦታ አሳየኝ ይለኛል። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ የሐይማኖት ሰዎች ተመሳሳይ ዐርፍተ ነገሮች እንዲናገር ገፋፍተውት ነበር።

> "በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማርያም ያገኛል። አይሁድም እርሱን

ከበው፦ እስከ መቼ ድረስ በጥርጣሬ ታቆየናለህ? አንተ ክርስቶስ እንደ ሆንህ ገልጠህ ንገረን አሉት።

ኢየሱስም መለሰላቸው፤ እንዲህ ሲል፦ ነገርኋችሁ አታምኑምም እኔ በአባቴ ስም የማደርገው ሥራ ይህ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ **እኔና አብ አንድ ነን**።

**አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ**።

ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ?

ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም፦ **ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት**።" (ዮሐንስ 10:9 ፣ 24-25 ፣ 30-33)

ብዙ ሐይማኖተኞች ሊወግሩት የፈለጉት ለምንድን ነው?

ኢየሱስ "እኔ እና አብ አንድ ነን።" ስላለ ነው። በእነሱ አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነኝ ማለት መሳደብ ነው። ነገር ግን እነዚሁ አይሁድ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት "አዶናይ ኤሌሆኑ አዶናይ **ኤኻድ**።" በማለት ይገልጹ ነበር ትርምጉሙ "እግዚአብሔር አምካህ **አንድ** ነው [የብዙኸነት አንድነት]" ማለት ነበር። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይገልጣል።[168] ኢየሱስን አይሁድ እግዚአብሔርን ተሳድቧል ብለው የከሰሱት ለዚያ ነው።

ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ቃልና ልጅ ለዘላለም መኖሩን በፍጹም አልካደም። በየቦታው እየዞረ "እኔ አምላክ ነኝ! እኔ አምላክ ነኝ!" አላለም። በዚያ ምትክ የሰው ልጅ ሊኖር እንደታቀደለት በምድር ላይ በፍጹም ትህትና እና በፍቃዱ ለእግዚአብሔር ፍቃድ በመታዘዝ ኖረ።

የሚከተለውን ሊል የሚችል ሰው ኢየሱስ ብቻ ነው፦ "**ፈቃዱን ለማድረግ አይደለም** እንጂ **የላከኝን ፈቃድ** ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።" (ዮሐንስ 6:38) የኢየሱስ ሕይወት ክብር **የእግዚአብሔር** የከበረ ልጅ ቢሆንም ራሱን ዝቅ አድርጎ **የሰው ልጅ** ሆኗል።

ጌታ ኢየሱስ ማንነቱን በትህትና ግን በኃይለኛ መንገድ ለማስታወቅ ወደዷል።

በአንድ ወቅት አንድ ባለጠጋ ሰው ወደ እሱ መጥቶ "ቸር መምህር" በሚል ማዕረግ ጠራው። ስለዚህም ኢየሱስ ሰውየውን "ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ **ከእግዚአብሔር** በቀር ቸር

ማንም የለም።" (ሉቃስ 18:19)[169] አለው። ይሄ ባለጠጋ ሰው ኢየሱስ አምላክ ነው ብሎ አላመነም ፣ ነገር ግን ኢየሱስ የመለኮታዊ መልካምነት መገለጫ ነው ብሎ አምኖ ነበር፣ ኢየሱስም እነዚህን ነገሮች አገጣጥሞ የእሱን ማንነት እንዲረዳ ዕድል ሰጥቶት ነበር።

እሱም ለመረዳት ፈልጎ ነበር።[170]

## ቃልን በምግባር ማስደገፍ

ኢየሱስ የሰራቸው የማይቆጠሩ ታላላቅ ተዓምራት በወደቀውና በኃጢአት በተረገመው ፍጥረት እያንዳንዱ ቅንጣት ላይ ያለውን ሥልጣን እና ኃይል ያሳየ ነበረ። የሰዎችን ሐሳብ ያውቅ ነበር ፣ ኃጢአትን ይቅር ይል ነበር፣ ዳቦን ዓሳን ለሺዎች ያባዛ ነበር፣ ወጀብን ጸጥ ያሰኝ ነበር ፣ እርኩሳን መናፍስትን እንዲወጡ ያዝ ነበር። በቃል ወይም በመንካት ፣ የታመሙትን ይፈውስ፣ ሽባዎች እንዲራመዱ ፣ዕውራን እንዲያዩ ፣ ደንቆሮዎች እንዲሰሙ እና ሟቾችን እንደገና እንዲኖሩ አድርጓል። ነብያት አስቀድመው እንደ ተናገሩት መሲሁ በምድር ላይ "የጌታ ክንድ" ሆኖ እንደሚያገለግል ተናግሯል።[171]

በአንድ ወቅት ጌታ ኢየሱስ ከአራት ቀናት በፊት በሞተው በዓላዛር መቀብር አጠገበ ተገኝቶ ነበር። የዓላዛር ሬሳ የተቀበረው በተፈለፈለ ዋሻ ውስጥ ነበር። ኢየሱስ የምታለቅሰውን የሟቹን እህት ወንድሟ እንደሚነሳና እንዳታለቅስ ነገሯት ነበር።

እህትየዋ ኢየሱስ እንዲህ አለችው "በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው።"

ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት "**ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ**፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" (ዮሐንስ 11: 24-25)

ይህንንም ንግግሩን ለማረጋገጥ ኢየሱስ "አልዓዛር ሆይ፣ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ። የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር።

ኢየሱስም፦ ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው።

እንግዲህ ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገድሉት ተማከሩ። የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ፥ ከአይሁድ ብዙዎች ከእርሱ የተነሣ ሄደው በኢየሱስ ያምኑ ነበርና።" (ዮሐንስ 11:43-46 ፣ 53 ፤ 12:10-11)[172]

የሰው ልጅ ልብ ምን ያክል ጠጣር ነው!

## ደንዳና ልብ

ኢየሱስ ከሚናገረው ነገር እና እያደገ ከመጣው ዝነኝነቱ የተነሳ የቀኑበት የሐይማኖት እና የፖለቲካ መሪ የሆኑ አይሁድ በአንድ ዓላማ ዙሪያ ተደራጁ። ይኸውም ዓላማቸው ኢየሱስን ዝም ማሰኘት ነው! እነሱም የትኛውንም አይነት ምክንያት ፈልገው፣ከሰውት ሊገድሉት ጓጉተው ነበር። ነገር ግን እስከ ዛሬ ታይቶ የማያውቀውን ፍጹም ሰው የሚከሱት እንዴት ነው?

አንድ ሰንበት ፣ ኢየሱስ በምኩራብ ሲያስተምር...

"ደግሞም ወደ ምኩራብ ገባ፤ በዚያም እጁ የሰለለች ሰው ነበር፤ ሊከሱትም፣ በሰንበት ይፈውሰው እንደ ሆነ ይጠባበቁት ነበር። እጁ የሰለለችውንም ሰው፦ ተነሥተህ ወደ መካከል ና አለው። በሰንበት በጎ ማድረግ ተፈቅዶአልን? ወይስ ክፉ? ነፍስ ማዳን ወይስ መግደል?

አላቸው፤ እነርሱም ዝም አሉ።

ስለ ልባቸውም **ድንዛዜ አዝኖ ዙሪያውን እየተመለከተ በቍጣ አያቸው**፤ ሰውየውንም፦ እጅህን ዘርጋ አለው።

ዘረጋትም፤ እጁም ዳነች።

**ፈሪሳውያንም** [የሐይማኖት ቡድን] **ወጥተው ወዲያው እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ከሄሮድስ**[የፖለቲካ ቡድን] ወገን ጋር ተማከሩበት።

ኢየሱስም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ባህር ፈቀቅ አለ፤ ከገሊላ የመጡም ብዙ ሰዎች ተከተሉት፤ እንዴት ትልቅ ነገርም እንዳደረገው ሰምተው ብዙ ሰዎች ከይሁዳ ከኢየሩሳሌምም ከኤዶምያስም ከዮርዳኖስ ማዶም ከጢሮስና ከሲዶና ምድርም ወደ እርሱ መጡ።

ሰዎቹም እንዳያጋፉት ታንኳን ያቆዩለት ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው፤ ብዙ ሰዎችን አድኖ ነበርና፤ ስለዚህም ሥቃይ ያለባቸው ሁሉ እንዲዳስሱት ይወድቁበት ነበር። ርኵሳን መናፍስትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ተደፍተው፦ **አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ** እያሉ ጮኹ።" (ማርቆስ 3:1-11)

## አጋንንታዊ መረዳት

አጋንንት፣ ፈዋሹ ማን እንደሆነ አውቀው ስለነበር ይጠሩት የነበረው በትክክለኛ መጠሪያው ነበር፣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!" ይሉት ነበር። እነዚህ የወደቁ መላዕክት የኢየሱስን የቀደመ ታሪክ ያውቁ ነበር። ከሺህ ዓመት በፊት ሰማይና ምድርን በንግግሩ ወደ ህልውና ሲያመጣቸው የታየውን አሰገራሚውን ሳይሉን እና አስደናቂ ጥበቡን መስክረው ነበር። ሠይጣንን እና የሱን ዐመጽ በተከተሉ ጊዜ በተለየ የጽድቅ ቁጣ ከስማይ ያበረረበትን ቀን ሲያስታውሱ ተንቀጠቀጡ።[173] አሁን ደግሞ በሰዎች መካከል በምድር ላይ እየኖረ ነው!

ጉዳዩ ግልጥ ነበር።

የጌታቸው ሥልጣን እየተንኮታኮተ ነው።

የሳጢአት እርግን እየተቀለበሰ ነበር።

ዘላለማዊ የኾነው ወልድ የሴቷን ዘር ሆኖ ክልላቸውን ወረሯል። ስለዚህ አጋንንት "ርኵሳን መናፍስትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ተደፍተው፦ **አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ** እያሉ ጮኹ።" በዚህ መካከል ግን የሐይማኖት መሪዎች "እንዴት አድርገው **እንዲያጠፉት** ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት።"

አንድ ጊዜ ለጥቂት እንግዶች ይህንን ታሪክ ከተናገርኩ በኋላ አንዱ እንዲህ አለ፣ "ያስገርማል! አጋንንት ለኢየሱስ ከሐይማኖት መሪዎች የበለጠ ከበሬታ ነበራቸው!"

አስገራሚ ግን እውነት ነው።



# 18

# የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ

“ከጥንት ጀምሮ ሥራው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው።” (ሐዋርያት 15:18)

ጊዜ መቆጠር ሳይጀመር በፊት ፣ እግዚአብሔር ለሰዎች ግልጽ የሆነ ዕቅድ ነበረው። ኃጢአት የሰውን ቤተሰብ ባረከሰበት ቀን ጌታ ዕቅዱን ማስታወቅ ጀመረ ፣ ነገር ግን ይህንን ያደረገው ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ዕቅድ “የእግዚአብሔር **ምሥጢር**።” (ራዕይ 10:7)

እስከዛሬ ድረስ ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ዕቅድ እና ዓላማ ለብዙ ሰዎች ምስጢር ነው። እንደዚያ ሊሆን አይገባም። መጽሐፍ ቅዱስ “ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ **ምሥጢር** ነው፥ **አሁን** ግን ለቅዱሳኑ **ተገልጦአል**” (ቆላስያስ 1:26) ይላል።

## ከነብያት የበለጠ ዕድል የነበረው

አስገራሚ ሐሳብ እነሆ። የእግዚብሔርን ታሪክና መልዕክት ከመረዳት አንጻር እኔ እና እናንተ ቅዱሳት መጽሐፍትን ከጻፉት ነብያት የበለጠ ዕድል አለን።

እኛ የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ አለን ፥ እነሱ ግን የላቸውም።

እኛ የእግዚአብሔርን መጽሐፍ መጨረሻ ማንበብ እንችላለን፣ እነሱ ግን አይችሉም።

"ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፥ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ፥ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር። **ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ።"**
(1ጴጥሮስ 1:10-12አመት)

## እግዚአብሔር እቅዱን የመሰጠረው ለምንድን ነው

አንዳንዶች "እግዚብሔር ለወደቀው የሰው ልጅ ዕቅዱን ለምን ወዲውኑ አልነገረውም? መልዕክቱን በምስጢራት የከበበው ለምንድን ነው?"

ምንም እንኳን ለሉዐላዊው አምላክ ማብራሪያ መስጠት ባይገባውም ፣ በቸርነቱ ለሰው ልጅ ያለውን ዕቅድ ምስጢራዊ ያደረገበትን ምክንያት ፍንጭ ሰጥቶናል። እግዚአብሔር ምስጥሩን በሂደት እና በጥንቃቄ ለምን እንደገለጠ የሚያስረዱን ሦስት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፦

አንደኛ ፣ በምዕራፍ አምስት እና ስድስት እንደተብራራው፣ ዕቅዱን በሂደት በመግለጥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በርካታ **አረጋጋጭ** ትንቢቶች እና ተምሳሌቶች እንዲሁም በርካታ አረጋጋጭ የዐይን እማኞች ሰጥቶታል። ይህንን ያደረገው በሰተኋላ የሚመጣው ትውልድ መልዕክቱ የብቸኛው አምላክ እንደሆነ በእርግጠኝነት እንዲያውቅ ነው።

ሁለተኛ ፣ እግዚአብሔር እውነቱን በዚህ አይነት መንገድ የገለጠው መልዕክቱን ለማግኘት የፈለጉ ብቻ በትጋት ፈልገው እንዲያገኙት ነው። "የእግዚአብሔር ክብር ነገርን መሰወር ነው፤ የነገሥታት ክብር ግን ነገርን **መመርመር** ነው።" (ምሳሌ 25:2) ብዙ ሰዎች መልዕክቱን ማግኘት የማይችሉት ሌባ ፖሊስን መፈለግ እንደማይፈልገው ሁሉ መፈለግ ስለማይወዱ ነው።[174]

ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር ዕቅዱን **የሰወረው** ሰይጣን እና ተከታዮቹ እንዳያገኙት ነው።

"ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፥ ተሰውሮም የነበረውን

> የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን። ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፤" (1 ቆሮንቶስ 2:7-8)

ስይጣንና ከእሱ ጋር የወገኑት እግዚአብሔር እነሱን ለማሸነፍ ያለውን ዕቅድ ተረዱ ፣ ያደረጉትን አያደርጉትም ነበር። እግዚአብሔር እቅዱን የነደፈው ሊያሰናክሉት ያሰቡት ራሳቸው ለፍጻሜው ድጋፍ እንዲያደርጉ አሰቦ ነው!

ታዲያ ዕቅዱ ምንድን ነው?

**መዋጀት!**

መዋጀት እግዚአብሔር ሳጢአት የሌለበትን አዳኝ (የሴቷን ዘር) ወደ ዓለም በመላክ የአዳምን ያፈነገጡ ፣ ሕግ ተላላፊ ዘሮችን ከዘላለማዊ እርግማን ማዳን ነው። በሰው ልጅ ታሪክ ትክክለኛ ጊዜ ፣ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ፈጸመ።

> "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፣ ከሕግ በታች ያሉትን **ይዋጅ** ዘንድ።" (ገላትያ 4:4-5)

መዋጀት ማለት አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽሞ እንደገና መግዛት ማለት ነው።

ልጅ እያለሁ ካሊፎርኒያ እያለሁ ትንሽ ውሻ ነበረኝ። እመግባታለሁ፣ እንከባከባታለሁ አብሬያትም እጫወታለሁ። እሷም በየቦታው ትከተለኛለች በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ስመለስ በጣም ደስ ይላል። ነገር ግን አንድ ችግር ነበረባት። አንዳንድ ጊዜ እኛ ሰፈር ውስጥ ትዞር ነበር። ነገር ግን ተመልሳ ትመጣለች። አንድ ቀን ግን የተለየ ነገር ሆነ።

ከትምህርት ቤት ወደ ቤት መጣሁ ፣ ነገር ግን ውሻዋ ሰላም ልትለኝ አልመጣችም። በመኝታ ሰዓት ፣ የትም ቦታ ላገኛት አልቻልኩም። በሚቀጥለው ቀን ፣ አባቴ በአካባቢው ወደ ነበረው የጠፉ ድመቶችን እና ውሻዎችን ለተወሰነ ጊዜ ወደሚያቆየው የእንስሳት እንድደውል መከረኝ። ባለቤት የሌላቸው እንስሳት ይገደሉ ነበር።

ወደ መጠለያው ደወልኩ። እውነትም የኔን ገለፃ የምታሟላ ውሻ ነበርች። የከተማው "ውሻ አሳሪዎች" ይዘዋት ነበር። ውሻዬ ራሷን ማዳን አትችልም ነበር። አንድ ሰው መጥቶ ካላዳናት ትገደል ነበር።

ወደ መጠለያው ሄድኩ። ውሻዬን ላገኝ ነበረ! ነገር ግን በር ላይ ተቀምጦ የነበው ባለ ስልጣን ውሻዬን መውሰድ ከፈለግኩ ቅጣት መክፈል አለብህ አለኝ። ውሻ አላግባብ በጎዳና ላይ መዘዋወር በሕግ የተከለከለ ነው። አስፈላጊውን ገንዘብ ከፍዬ ውሻዬ ተለቀቀች። ከዚያ አሰቀያሚ ማቆያ ወጥታ ከተንከባካቢዋ ጋር እንደገና መገናኘቷ የሚስደስት ነበር! ተዋጅታለች።

በልጅነቴ ያጋጠመኝ ዙረት ምትወደውን ውሻዬን መልሺ መግዛቴ ስለ ሁኔታው ፍንጭ ይሰጠናል። ዐመጸኞች፤የተፈረደብን ሐጢአተኞች እንደ መሆናችን መጠን ራሳችንን የምናድንበት መንገድ የለንም። እግዚአብሔር የሚያስፈልገውን የቤዛነት ክፍያ በመፈጸም እኛን ሊዋጀን ልጁን ልኳል።

> "ወንድም ወንድሙን አያድንም፥ ሰውም አያድንም፤ ቤዛውን ለእግዚአብሔር አይሰጥም፥ ለዘላለም እንዲኖር፥ ጥፋትንም እንዳያይ፤ **የነፍሳቸው ለውጥ ከብሮአልና**፥ ለዘላለምም ቀርቶአልና። ነገር ግን እግዚአብሔር ይቀበለኛልና ነፍሴን ከሲኦል እጅ ይቤዠታል።"
> (መዝሙር 49:7-8 ፣ 15)

ታዲያ ለመዋጀታችን የተከፈለው ክፍያ ምን ያህል ነበር?

## ነብያት ተናግረውታል

በዘፍጥረት 3 የእግዚአብሔርን ኅጢአተኞችን ከሠይጣን መዳፍ ለመቤዠት ያቀደውን ምስጢራዊ፣ጥንስስ እናገኛለን። እስቲ እንደገና እግዚአብሔር ለሠይጣን ያለውን ነገር እናዳምጥ።

> "በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።" (ዘፍጥረት 3:15)

በእነዚህ ቃላት እግዚአብሔር ስይጣንንና ሐጢአትን ከጻድቅ ባህርይው ጋር በሚስማማ መልኩ ለማስወገድ ያለውን ምስጢራዊውን እና ስልታዊ ዕቅድ ገለጠ። እግዚብሔር

ስይጣንን "ራሱን" በማፍረስ የሚያሸንፈውን የሚዋጇውን መሲህ ለሰው ልጅ እንደሚሰጥ ተናገረ። ትንቢቱ በተጨማሪም ስይጣን የመሲሁን "ተረከዝ" እንደሚያቆስል ይናገራል።

"እርሱ [መሲህ] ራስህን ይቀጠቅጣል[የሰይጣን]፥ አንተም[ስይጣን] ሰኰናውን [መሲሁ] ትቀጠቅጣለህ።"

የሴቷ ዘር የሠይጣንን ራስ የሚያፈርሰው እንዴት ነው? "ማፍረስ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል ፍቺው "ማፈረስ፣ መስበር፣ ማቁሰል ወይም ማድቀቅ" ማለት ነው። እንደ መጀመሪያው ትንቢት ከሆነ ሠይጣንም መሲሁም "ይፈርሳሉ" ነገር ግን የማይሽረው ቁስል የአንደኛው ነው። የፈረሰ ራስ ለሞት ያበቃል፣ የቆሰለ ተረከዝ ግን ይድናል።

እግዚአብሔር አሰቀድሞ እየተናገረ ያለው ምንም እንኳን የሚዋጇንን በሠይጣንን ተከታዮቹ ቢቆስልም ፣ በመጨረሻ ሠይጣንን ያሸንፋል።

በስተኋላም እግዚአብሔር ነብዩ ዮሐንስ ስለ መሲሁ የሚከተለውን ቃል እንዲጽፍ አንሳስቷል፦

**"እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።"** (መዝሙር 22:16)

ምንም እንኳን ዳዊት መሲሁ እንደሚገደል ቢተነብይም፣ አካሉ ግን በመቃብር እንደማይበሰብስ ተናግሯል። ተስፋ የተሰጠው ነፃ አውጪ ሞትን ያሸንፋል።

"**ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።**"
(መዝሙር 16:10)

ነብዩ ኢሳያስስ ሰለ መሲሁ መከራ፣ ሞት እና ትንሳኤ አስቀድሞ ተግሯል፦

"እርሱ ግን **ስለ መተላለፋችን ቈሰለ**፥ **ስለ በደላችንም ደቀቀ**፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። ... እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን **ስለ ኃጢአት መሥዋዕት** ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል።"
(ኢሳያስ 53:5 ፣ 10)[175]

ምንም እንኳን ሠይጣን በእግዚብሔር የተላከውን መሲህ እንዲሰቃዩት እና እንዲገድሉት ቢያነሳሳቸውም፣ ሁሉ የሚከናወነው በነብያት እንደ ተገለጸው ነው። የመጨረሻ ውጤቱም ለጌታ እና እሱ ለቀባው ሙሉ ድል ያስገኛል።

## የጥበብና የማስጠንቀቂያ ቃላት

መሲሁ ከመወለዱ ከሺህ ዓመታት በፊት ፣ ዳዊት እንዲህ ሲል ጽፏል፦

> “**አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ?** ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ፤ አለቆችም **በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ**። በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፤ ጌታም ይሣለቅባቸዋል። በዚያን ጊዜ በቍጣው ይናገራቸዋል፤ በመዓቱም ያውካቸዋል። እኔ ግን **ንጉሤን** ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ። አሁንም እናንተ ነገሥታት፤ ልብ አድርጉ፤ እናንተ የምድር ፈራጆችም፤ ተገሠጹ። ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ፤ በረዓድም ደስ ይበላችሁ። ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቈጣ እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፤ ቍጣው ፈጥና ትነድዳለችና። **በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።**”
>
> (መዝሙር 2:1-2 ፣ 4-6 ፣ 10-12)

ነፃ ትግል ብሔራዊ ስፖርት በሆነባት በሴኔጋል ፣ ሰዎች የሚከተለውን ምሳሌ ይናገራሉ፦

> “እንቁላል ከድንጋይ ጋር መታገል የለበትም።”

እንቁላል ከድንጋይ ጋር መታገል የሌለበት ለምንድን ነው? ምክንያቱም እንቁላል ምንም የማሸነፍ ዕድል ስለሌለው ነው! በተመሳሳይ መልኩም “በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ።” አይሳካላቸውም። የእግዚአብሔርን ዕቅድ መቃወም “ተማከሩ”[176] ነው።

ሴኔጋላውያን የሚከተለውም አባባል አላቸው።

> “ዛፍ ቆራጭ የሰዎች መሰብሰቢያ የሆነውን ዛፍ አይቆርጥም።”

በዚህ በዓለማችን እጅግ በረሃማ በሆነ አካባቢ ብዙዎቹ መንደሮች ትልቅ እና በመካከለኛ ስፍራ የሚገኝ ዛፍ አለ። ይሄ "ሰዎች የሚሰባሰቡበት ዛፍ" ሰዎች ዕኩለ ቀን ጸሐይ እንዳያገኛቸው መጠለያ ሆኖ ያገለግላል። እዚህ ቦታ ላይም ሰዎች ይዝናናሉ ፣የጨዋወታሉ ሻይ ይጠጣሉ። ዛፍ ቆራጭ "ሰዎች የሚሰባሰቡበት ዛፍ" ቢቆርጥ መንደረተኞቹ ምን የሚሰማው ይመስላችኋል? በታላቅ ቁጣ ወዲያውኑ ዛፉን መቁረጥ እንዲይቆም ያደርጋሉ።

በእግብሔር ዕቅድ ላይ ራሳቸውን የሚያተኩሩ ሰዎች መንደረተኛው የሚወደውን ዛፍ መቁረጥ እንደ ተነሳው ሰው ነው።

አይሳካለትም።

"አሁንም እናንት ነገሥታት፥ ልብ አድርጉ፤ እናንት የምድር ፈራጆችም፥ ተገሠጹ። ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቈጣ እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፥ ቍጣው ፈጥና ትነድዳለችና። በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።" (መዝሙር 2:10 ፣12)

## የእግዚአብሔርን ዕቅድ አለማስተዋል

በምድር ላይ በአገልግሎት ባሳለፋቸው የመጨረሻ ሳምንታት ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንደ የፖለቲካ እና የሐይማኖት መሪዎች ንጉሳቸውን አድርገው ከመቀበል ይልቅ እንዲገደል እንደሚጠይቁ መናገር ጀምሮ ነበር። ኢየሱስን ሊገድሉ እያሴሩ ያሉት ግን ነብያት አሰቀድመው የተናገሩትን ነገር የመፈጸሙ አካል እንደሆኑ አላወቁም ነበር። ይኸውም የአዳምን አፈንጋጭና ፣ ረዳት አልባ ዝርያዎች ለመዋጀት የመሲሁ እጅና እግር እንደሚወጋ መናገራቸው ነበር።

"ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር። ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።

እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ **ወደ ኋላዬ ሂድ፤ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።**”
(ማቴዎስ 16:21-23)

አንድ ታዋቂ ተከራካሪ ሲናገረ እንደሰማሁት ሁሉ የጴጥሮስም አሰተሳሰብ ተመሳሳይ ነበር “የተሰቀለ መሲህ ማለት ያገባ ላጤ ማለት ነው!”።

ልክ እንደ ተከራካሪው ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ዕቅድ አልገባውም ነበር። መሲሁ ወደያውኑ ተሰፋ የተናገረውን ዓለማቀፋዊ መንግሥት የሚመሰርት እንጂ ከመስቀል ጋር በመጣበቅ ስቃይና ውርደት የሚደረሰበት አልመሰለውም ነበር!

ጴጥሮስ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርሰቶስን በምድር ላይ ሁሉ ሉዓላዊ ገዢ ያደርገዋል ብሎ ማሰቡ ትክክል ነበር። ነገር ግን መሲሁ የመስቀሉን መከራና ውርደት አይደርስበትም ብሎ ማስቡ ግን ትክክል አልነበረም። በስተኋላ ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተረድቶ በድፍረት ይህንን ብሎ ነበር፦ “ነቢያት ... በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፣ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ፥” (1ጴጥሮስ 1:10-11 አመት)[177]


የመሲሁ መሰቀል አደጋ አልነበረም።

እግዚአብሔር “ከዘላለም ጀምሮ” ጠብቆትም አቅዶትም ነበር።

ነብያት አስቀድመው ተናግረውት ነበረ።

የሴቷ ዘር የመጣው ይህንን ሊፈጽም ነበር።

ከጥቂት ጊዜያት በፊት የሚከተለውን ኢሜይል አገኘሁ፦


ርሰስ ጉዳይ የኢሚይል ምላሽ

እግዚአብሔር የገዛ ልጁን ከመሰቀል አይደነውም ብለህ በማመንህ ማስተዋል የማትችል ነህ። ይሄ ማለት እኮ እግዚአብሔር ገደብ አለው ማለት ነው። በተጨማሪም በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ልጁ በሰዎች እንዲዋረድና እንዲሞት ፈቅዷል እያልክ ነው። እግዚአብሔር ታላቅ ኀይል አለው። እሱ አንድ እና ብቸኛ ነው ምንም ነገር አቡያው ሊሆን አይችልም።

አላኋከበር።

ጴጥሮስ በመጀመሪያ እንዳደረገው ፤ ይሄም የኢሜይል ጸሐፊ መሲሁ “ሊገደልና በሦስተኛው ቀን ከሞት ሊነሳ **ይገባል።**” ለምን እንዳለት አልገባውም።

እንዲህ አይነት አሰቃቂ ዕቅድ ያሰፈለገው ለምንድን ነው? በእርግጥ ኢሜይል የጻልን ሰው እንዳለው “እግዚአብሔር ታላቅ ሳይል አለው”። ታዲያ እግዚእብሔር ሰይጣንን ወደ ሲዖል ያልጣለው እና ሳጢአተኞቹን የአዳም ዘሮች ይቅር ተብላችኋል ብሎ ያላወጀው ለምንድን ነው? ጌታ ዓለማትን የፈጠረው በመናገር ከሆነ ዓለምን ለምን በመናገር አልተቤዠም?

ፈጣሪ ቃል ሰው መሆን ያስፈለገው ለምንድን ነው? የእግዚአብሔር ዕቅድ መከራን የሚቀበል፣ የሚደማና የሚሞት መሲህ ያካተተው ለምንድን ነው?

የጉዟችን ቀጣይ ክፍል ምላሹን ይሰጠናል።



# 19

# የመሰዋዕት ሕግ

> “ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።”
> —ጌታ (ዘሌዋውያን 17:11)

የመጀመሪያው ቤተሰብ ታሪክ በዘፍጥረት ምዕራፍ አራት ተመዝግቦ ይገኛል። በዚህ ቦታ አዳምና ሔዋን ከሚያምረው የኤደን ገነት በመባረራቸው የተነሳ መላው የሰው ዘር እንደተባረሩ እንረዳለን። መላው ዝርያዎቻቸው በጠላት ቁጥጥር ስር በሚገኝ በተረገመ ምድር ላይ ይወለዳሉ።

## በኩር ሳጢአተኛ

> “አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ፤ ፀነሰችም፥ ቃየንንም ወለደች። እርስዋም፦ ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ አለች።”
> (ዘፍጥረት 4:1)

ሄዋን ተሰፋ የተሰጠው አዳኝ “ከጌታ ዘንድ” ይመጣል ብላ ማመኗ ትክክል ነበር። በተጨማሪም ደግሞ መሲሁ ከሴት ይወለዳል ብላ ማመኗ ትክክል ነበር ፣ ነገር ግን የባሏ ዘር ተስፋ የተሰጠው አዳኝ ነው ብላ ማመኗ ትክክል አልነበረም።

እንዲህ አይነት የተሳሳተ አመለካከት ቢኖር እንኳን ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አዳምና ሄዋን ወዲያው እንደተረዱት በጣም የሚወዱት የበኩር ልጃቸው የውርስ ሳጢአት አለበት። ቃየን በተፈጥሮው

ኅጢአት ያደርጋል። እንደ ቤተሰቦቹ እና እንደ ሠይጣን ትዕቢት እና የራስ ፈቃድ ያሳይ ነበር። ተስፋ የሌለው መዋጀት የሚያስፈልገው ሌላ ኅጢአተኛ ነበር።

አዳምና ሄዋን ሁለተኛ ልጃቸውን ሲወልዱ ፣ የሰው ልጅን ሁኔታ በተመለከተ ተጨባጭ አመለካከት ነበራቸው።

> "ደግሞም ወንድሙን **አቤል**ን ወለደች።" (ዘፍጥረት 4:2)

አዳምና ሄዋን ሁለተኛ ልጃቸውን አቤል ብለው ሰየሙት ትርጉሙም **ከንቱ** ወይም ምንም ማለት ነበር። ጻድቅ ሕጻን ለመውለድ የሚያስችላቸው ምንም ነገር የለም። ተስፋ የተሰው የኅጢአተኞች አዳኝ ከአዳም የኅጢአተኛ ዘር ሊመጣ የሚችልበት ምንም መንገድ የለም። አዳምና ሄዋን በአንድነት ሊፈጥሩ የሚችሉት እንደነሱ ያለ ሌላ ኅጢአተኛ ነው። ከኅጢአት ቅጣት ሊያድናቸው የሚችል ጻድቅ ሰው ካለ ሊመጣ የሚችለው ከጌታ ዘንድ ነው።

በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ እንደተማርነው የመጀመሪያው ወንድ እና የመጀመሪያዋ ሴት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ ነበር። ይሄ አሰገራሚ ዕድል ትክክለኛ ምርጫን የመምረጥን አስገራሚ ዕድል ያካትት ነበር። ለአዳምና ለሔዋን እና ለዘሮቻቸው የእግዚአብሔር ፍቃድ የነበረው የፈጣሪያቸውን ቅዱስና አፍቃሪ ጠባይ እንዲያንጸባርቁ ነበር። ነገር ግን አዳምና ሄዋን ፈጣሪ ባለቤታቸውን ላለመታዘዝ በወሰኑ ጊዜ የእሱን ምሳሌ ማንጸባረቅ አቆሙ። በቅጽበትም እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረጉ ከመሆን ራሳቸውን ማዕከል ያደረጉ ሆኑ። እነሱን የሚመስሉ ልጆችንም ወለዱ።

> "አዳምምልጅንም **በምሳሌው እንደ መልኩ** ወለደ ... ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ።" (ዘፍጥረት 5:3-4)

የውሎፍ ምሳሌ እንደሚለው፦ "ሚዳቋዎችን አብሮ ማሰር የምትዘል ሚዳቋ አይፈጥርም" ኅጢአተኛ ወላጆችም ጻድቅ ዘር ሊኖራቸው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

> "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት **በአንድ ሰው** ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው **ሁሉ ደረሰ**፤" (ሮሜ 5:12)

## የኀጢአተኞች አምልኮ

"ደግሞም ወንድሙን **አቤልን** ወለደች። አቤልም በግ ጠባቂ ነበረ፤ **ቃየንም** ምድርን የሚያርስ ነበረ። አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኲራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤" (ዘፍጥረት 4:2-4)

ቃየን ገበሬ ሆነ ፣ አቤልም እረኛ ሆነ። ምንም እንኳን የኀጢአት ውጤት በዙሪያቸው እና በውስጣቸው ቢሆንም በእግዚአብሔር ፍጥረት ክብር ተከበው በፍቅሩ ጽናትን አግኝተው ነበር። ምንም እንኳን ቃየን እና አቤል ኀጢአተኞች ቢሆኑም እግዚአብሔር ይወዳቸው ስለነር ወደሱ በአምልኮ እንዲቀርቡ ይፈልግ ነበር። ነገር ግን ይሄ እንዲሆን ከኀጢአት ችግራቸው የሚፈውሳቸው ነገር ያስፈልጋቸው ነበር። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው "…የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።" (ዮሐንስ 4:24)

በግል እንደሚታየው ልጆቹ ከወላጆቻቸው በአግባቡ የተማሩ እና ከፈጣሪ ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው። ቃየን እና አቤል ኀጢአት እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝን ተረድተው ነበር። እንደ ወላጆቻቸው ከእግዚአብሔር መገኘት ተለይተው ነበር። ከእሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ካስፈለግ ፣ በእሱ መመሪያ ላይ ተመስርተው ነበር።

የምስራቹ እሱን ከታመኑ እና እሱ ባስቀመጠው መንገድ ከቀረቡት ቃየን እና አቤል ኀጢአታቸው መሸፈን የሚችሉበት መንገድ ተከፍቶ ነበር።

ትረካውን ድጋሚ እናዳምጠው፦

"ከብዙ ቀን በኋላም ቃየን **ከምድር ፍሬ** ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ፤ አቤልም ደግሞ **ከበጎቹ በኲራትና** ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።" (ዘፍጥረት 4:3-5)

በጥሩ ሁኔታ እንደተተረከ የትኛውም ታሪክ ፣ ዝርዝር ሁኔታው ወዲያውኑ አልተሰጠንም። ተራኪው ቃየን እና አቤል ምን እንዳደረጉ ብቻ ይነግረናል። ለምን አደረጉት የሚለው የተብራራው በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ሁለቱም

ወጣት ወንዶች አንዱን እውነተኛ አምላክ ለማምለክ ፈልገው ነበር። ሁሉም "ለእግዚአብሔር መሰዋዕት አቀረበ።"

ቃየን በትጋት ከሚያመርተው አትክልትና ፈራፍሬ የሚያምረውን መራርጦ አዘጋጅቶ ነበር።

አቤል ንጹህ ፣ ያለነቀፋ የሆነ ጠቦት አምጥቶ አረደ እና ከመሬት ላይ ባገኘው ድንጋይ በሰራው መሰዊያ ላይ ሥጋውን አቃጠለ።[178]

ነገር ግን ውጪያዊ ገጽታው ሲታይ የአቤል መስዋዕት በጭካኔ የተሞላ እና ቀፋፊ ሲሆን የቃየን የግብርና ምርት አቀርቦት ውብና ሳቢ ነበር። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

> "**እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።** ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።"
> (ዘፍጥረት 4:4-5)

እግዚአብሔር የአቤልን መሰዋዕት ተቀብሎ የአቤልን ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

አቤል የእግዚአብሔርን ዕቅድ ታመነ።

ቃየን ደግሞ አልታመነም።

## የአቤል እምነት እና ጠቦት

መጽሐፍ ቅዱስ አቤል ወደ እግዚአብሔር የቀረበው በእምነት ነበር፣ ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔር ለቃየን እና ለአቤል የሚያስፈልገውን ነገር እንደገለጠላቸው ነው።

> "**አቤል** [በእግዚአብሔር ዕቅድ ያመነው]**ከቃየል** [በእግዚአብሔር ዕቅድ ያላመነው] **ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፤** በዚህም፥ እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር፥ እርሱ **ጻድቅ** እንደ ሆነ ተመሰከረለት፤ ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል።" (ዕብራውያን 11:4 ፣6)

እግዚአብሔርን የሚያሰደስተው እምነት በእሱ የሚታመን እና ለዕቅዱ የሚገዛ እምነት ነው።

አዳምና ሄዋን መጀመሪያ ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ፣ የኃጢአት ችግራቸውን ለመፍታት የሚያደርጉትን የግል ጥረት እግዚአብሔር

አልተቀበለውም፡፡ በምትኩ ግን እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የእንሰሳ መስዋዕት በማድረግ ለአዳምና ለሄዋን ለኃጢአታቸው እና ሃፍረታቸው ሽፋን አዘጋጀ፡፡ ንጹሐን እንስሳትን በመግደል እግዚአብሔር እያስተማራቸው ያለው "የኃጢአት ደመወዝ **ሞት** ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ...የዘላለም ሕይወት ነው፡፡" (ሮሜ 6፡23)

በስተኋላም ቃየን እና አቤል ይሄንኑ ተመሳሳይ ትምህርት ተምረው ነበር ፣ ያመነው ግን አንዱ ብቻ ነበር፡፡

አቤል ወደ እግዚብሔር የቀረበው በእምነት ፣ በትህትናና በመታዘዝ የመጀመሪያውን ጤናማ የበኩር ጠቦት በማቅረብ ነበር፡፡



እስቲ አቤልን እጁን በጠቦቷ ላይ አድርጎ እግዚአብርን እሱ አቤል የሞት ፍርድ የሚገባው ቢሆንም የዚህችን ጠቦት ደም እግዚአብሔር ጊዜያዊ የኃጢአት ክፍያ አድርጎ በመቀበሉ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን እስቲ አሰቡት፡፡ በመቀጠልም አቤል ቢላዋውን ይዞ የገራሟን እንስሳ አንገት ቆርጦ ሕይወቷ የሆነው ደሟ ከውስጧ ሲፈስ ሲመለከት አስቡት፡፡

ጠቦቷን በማረድ አቤል ለእግዚአብሔር ቅዱስ ባህርይ እና ለኃጢአት እና ለሞት ሕግ ያለውን አክብሮት አሳየ፡፡ እሱ በእግዚአብሔር ዕቅድ ስለተማመነ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ብሎ ጻድቅ ብሎ ጠራው፡፡ አቤል ቅጣቱ በጠቦቷ ላይ ከመፈጸሙ የተነሳ ከኃጢአት ቅጣት ነፃ ሆነ፡፡ የአቤል መሰዋዕት እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአት እንዲያሰወግድ አቀርበዋለሁ ብሎ ቃል የገባውን የሚወክል እና የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህም ነው "እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ"

## የቃየል ሥራዎች እና ሐይማኖት

በመቀጠልም ቃየል ነበር፡፡ በጣም ሐይማኖተኛ ወጣት ነበር! በርትቶ በመስራት ያገኛቸውን በእግዚአብሔር ፊትም አስገራሚ

በዛት ያላቸው ፍራፍሬችና አትክልቶችን አሰቀመጠ። ነገር ግን እግዚአብሔር ቃየንና መሰዋዕቱን አልተቀበለም።

የቃየን ስህተት ሐሰተኛ አምላክ ማምለክ ሳይሆን አንዱን እውነተኛውን አምላክ በሐሰተኛ መንገድ ማምለክ ነው።

በእምነት ወደ ፈጣሪው ከመቅረብ ይልቅ ቃየን የራሱ ሐሳብ እና መንገድ ነበረው። እግዚአብሔር የእሱ ቤተሰቦች በራሳቸው ያፈለቁትን የቅጠል ልብ አልተቀበለም እንዲሁም ቃየን ራሱ ያፈለቀውን የአትክልት መሰዋዕት አለተቀበለም።

አንዳንነዶች "ቃየን እኮ ያለውን ነው ያመጣው!" ሲሉ ይሞግታሉ።

እግዚአብሔርየቃየንንመሰዋዕትአልፈለገም።እግዚአብሔር የፈለገው ቃየን እንዲያመልከው የፈለገው በ ሞት ክፍያ ማለትም በጠቦት ደም መሠረትነት ነው። ቃየን ጠቦት ባይኖረው እንኳን ፣ የአቤልን ጠቦቶች በአትክልቱ መቀየር ይችል ነበር ወይም ደግሞ የጠቦት ደም በፈሰሰት በአቤል መሰዊያ በትህትና መቀረብ ይችል ነበር። ቃየን ከኩራቱ የተነሳ ይህንን ማድረግ አልቻለም። እግዚአብሔርን በእጅ ስራዎቹ "ማምለክ" ፈለገ።

ለዚህም ነው "ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።"

## የኀጢአት ዕዳ

ጌታ እንደዚህ የተለየ ነገር የፈለገው ለምንድን ነው? ለምንድን ነው የአቤልን የታረደ ጠቦት ተቀብሎ የቃየንን ትኩስ አትክልት ያልተቀበለው?

እግዚአብሔር የቃየልን መሰዋዕት ያልተቀበለበት ቀላል ምክንያት የኀጢአት ቅጣት ሞት እንጂ የራስ ጥረት ስላልሆነ ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ለአዳም ያስታወቀው የኅጢአትና የሞት ሕግ አልተለወጠም። የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፉ ሰዎች ሁሉ በሞት በቻ ሊከፈል የሚችል ዕዳ አለባቸው።

ምንም አይነት የዋህነት፣ የራስ ጥረት ወይም መልካም ስራ የኅጢአትን ዕዳ ሊደመስስ አይችልም።

ይህንን ምሳሌ ለማስረዳት አንድ ትልቅ ባንክ በርካታ ሚሊዮን ብር አበድሮኛል እንበል። ይህንን በርካታ ገንዘብ በጥበብ ከመጠቀም ይልቅ አባክኜው ብድሬን መክፈል አልቻልኩም እንበል። ፖሊስ ቤቴ ድረስ መጥቶ አሰረኝ። ፍርደ ቤትም ዳኛውን እንዲህ አልኩት "ያለብኝን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር

በሕይወት ዘመኔ መክፈል አልቻልም ነገር ግን የገንዘብ ዕዳዬን የማስወግድበት አንድ ዘዴ አለኝ። የማደርገው እንደሚከተለው ነው፦ ዕዳዬን በገንዘብ ከመክፈል ይልቅ ፣ በመልካም ስራ እከፍለዋለሁ! በየቀኑ ለባንኩ ፕሬዝዳንት አንድ አንድ ቀይ ወጥ አመጣለታለሁ። በሳምንት አንድ ቀን ደግሞ ለእሱ ያስብኩትን ምግብ ደሆቸን እመግባለሁ። በየቀኑ ደግሞ የመታጠብ ሥርዓት እየፈጸምኩ ዕዳዬ ያመጣብኝን እፍረት እታጠበዋለሁ። ይህንንም ዕዳዬን ከፍዬ እስክጨርስ አደርገዋለሁ።"

ዳኛው ይህንን ምክንያታዊ ያልሆነ የገንዘብ ዕዳ ክፍ መንገድ ይቀበለዋል? በፍጹም! የምድር ሁሉ ዳኛ የሆነው እሱም ጸሎትን ፣ ጾምን እና መልካም ስራን የኀጢአት ዕዳ ክፍያ አድርጎ አየቀበለውም። መከፈል ያለበት በሞት ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም በመለየት ነው።

ረዳት አልባ ኀጢአተኞች ከዚህ ከማይለዋወጥ የኀጢአትና የሞት ሕግ ነጻ የሚወጡበት መንገድ አለ?

እግዚአብሔር ይመስገን አለ።

## የመሰዋዕት ሕግ

ካርታ አልጫወትም ነገር ግን አንዳንድ ካርታዎቸ ሌሎቹን እንደሚበልጡ አውቃለሁ። ከካርታው ዋጋ የተነሳ ትንንሽ ዋጋ ያላቸውን ካርታዎቸ ይበልጣቸዋል።

በብሉይ ኪዳን የሚገኙት የዳንኤልና የአስቴር መጻሕፍት ጥንታውያን ነገስታት "እንደማይለወጠው እንደ ሜዶንና እንደ ፋርስ ሕግ፥ እንዳይለወጥ ትእዛዙን አጽና፤"(ዳንኤል 6:8) ይነግሯቸዋል። ንጉስ አንድን ሕግ መተላለፍ ከፈለግ ፣ ሕጉን ከመሻር ይልቅ ከቀደመው ሕግ የበለጠ "ጽኑ" ሕግ ያጸድቃል። [179]

በተመሳሳይ መልኩም ጻድቁ እግዚእብሔር "የኀጢአትን እና የሞትን ሕግ" ለማሸነፍ የበለጠ ብርቱ የሆነውን **"የሐጢአት መሰዋዕት ሕግ"** (ዘሌዋውያን 6:25) ወይም በሌላ መጠሪያው **"የመስዋዕት ሕግ"** (ዘሌዋውን 7:11) የሚባለውን አመጣ።

ሕጉን ሁሉ አጽንቶ የሚይዘው እግዚአብሔር የመሰረተው የመሰዋዕትን ሕግ አሁንም ገዢ ከሆነው ከኀጢአትና ሞት ሕግ ብልጫ ያለው ነው።

የመስዋዕት ሕግ ለጥፋተኛ ሐጢአተኞች ምህረትን ሲሰገኝ በተመሳሳይ ጊዜም በሐጢአት ላይ ፍትህን ይፈጽማል። (እግዚብሔር ምህረትን እና ፍትሕን ፍጹም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለምን እንደሚስቀጥል ለመከለስ ምዕራፍ 13 ተመልከቱ)

የደም መሰዋዕት ሕግ እግዚአብሔር ሐጢአተኛውን ሳይቀጣ ኃጢአትን የሚቀጣበትን መንገድ ፈጠረ፦

> “የሥጋ ሕይወት **በደሙ** ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ **ማስተስረያ** ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።” (ዘሌዋውያን 17:11)

ሕጉ ሁለት መሠረታዊ መርሖዎችን የያዘ ነው፦

1. **ደም ሕይወት ይሰጣል** — እግዚአብሔር እንዲህ አለ **“የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና”** ዘመናዊ ሳይንስ ቅዱሳት መጻሕፍት ከሺህ ዓመታት በፊት ያረጋገጡትን ነገር ይነግረናል፦ የፍጡር ሕይወት በደሙ ውስጥ ነው። ጤነኛ ደም ሕይወትን ለማቆት የሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮችን ያመላልሳል በተጨማሪም ቆሻሻ ነገሮችን ያስወግዳል። ደም የከበረ ነው ፣ ያለሱ ሰውም ሆነ እንስሳት ይሞታሉ።
2. **ሐጢአት ሞትን ይፈልጋል** — እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል “ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ **ማስተስረያ**” ማስተሰረያ የሚለው ቃል ከዕብራይስጡ ከፋር ከሚል ቃል ውትርጉሙም “መሸፈን፣ መደምሰስ ፣ማንጻት ፣ ይቅር ማለት እና ማስታረቅ”[180] ነው። ኃጢአተኞች ሊነጹና ከጻድቁ አምላካቸው ሊታረቁ የሚችሉት በፈሰሰው ደም በኩል ብቻ ነው። የኃጢአት ቅጣት ሞት እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው እንስሳ ደም (በሕይወት ምትክ) ለሰው ኃጢአት ከፍያ እና ሽፋን አድርጎ ይቀበላል።

## ምትክ

የመሰዋዕት ሕግ መሰረት የሆነው መርሕ ምትክ በሚል ቃል ሊጠቃለል ይቸላል። ንጹህ የሆነ እንስሳ በተፈረደበት ኃጢአተኛ **ምትክ** ይሞታል።

ከመሲሁ መምጣት በፊት በሚገኘው ትውልድ ጌታ ጌታ ለአዳም ዘሮች የእንሰሳት ንማለትም የጠቦቶችን ፣ የበጎችን፣ የፍየሎችን ወይም የኮርማ ደም በምትክነት እንደሚቀበል አሳውቆ ነበር። ርግቦቸና ወፎች እንኳን ለመስዋዕትነት ይቀርቡ ነር።[181] አንድ ሰው የቱንም ያህል ባለጠጋ ወይም ደሐ ፣ መልካም

ወይም መጥፎ ይሁን ወደ እግዚአብሔር በሚቀርብበት ጊዜ ሐጢአተኝነቱን መገንዘብ እና ከፈሰሰው ደም የተነሳ እግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚሰጠው ማመን አለበት።

የተኮነነው ፍጡር "ያለ ነቀፋ" መሆን አለበት።[182] ምንም አይነት ሕመም ፣ የተሰበሩ አጥንቶች፣ ጠባሳ ወይም ጭረት ሊኖርበት አይገባም። ፍጹምነትን የሚወክል መሆን አለበት። መሰዋዕቱን የሚያቀረበው ኃጢአተኛ "በፍየሉም ራስ ላይ እጁን ይጭናል፤ የሚቃጠልም **መሥዋዕት** ሚታረድበት ስፍራ በእግዚአብሔር ፊት ያርደዋል፤ እርሱ የኃጢአት መሥዋዕት ነው።" ይገባል። የእንሰሳው ስብም አመድ እስኪሆን ድረስ በመሰዊያው ላይ ይቃጠላል።

እግዚአብሔር ይሄን አይነት መሰዋዕት የሚያከናውነውን ነገር በተመለከተ ምን ይላል?

> "ኃጢአቱን ያስተሰርይለታል፥ እርሱም **ይቅር** ይባላል።"
> (ዘሌዋውያን 4:23-26)

ኃጢአተኞች ነቀፋ በሌለት እንስሳ ራስ ላይ እጃቸውን ሲያኖሩ ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ኃጢአታቸው ወደ እንስሳው ይዘዋወራል። ኃጢአትን የሚሸከመው ፍጥረት በእነሱ ቦታ ይሞታል።

ይቅር ተብለዋል!

በምትክነት መርሕ ላይ በመመስረት ኃጢአት ይቀጣል ፣ ኃጢአተኛው ደግሞ ይቅር ይባላል። የሞት ፍርድ ከጥፋተኛው ኃጢአተኛ ይልቅ በንጹሁ እንስሳ ላይ ያርፋል።

የኃጢአት መስዋዕት ሕግ ኃጢአተኞችን እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እና "**ደምም** [የሐጢአት ክፍያ] ሳይፈስ **ስርየት** [የሐጢአት ቅጣት መወገድ] የለም።" (ዕብራውያን 9:22 አመት)

በእንስሳት መሰዋዕት በኩል እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ፍትሁን እና በእሱና በዕቅዱ ሚታመነው ኃጢአተ ደግሞ ምሕረቱን እያሳየ ነበር። ለዚህም ነው ጌታ ለጥንታዊው ሕዝቡ አስርቱ ትዕዛዛትን የሰጠው፣ ሕጉን ሰለ ማፈረሳቸው ይቅር ለመባል በሰማይና በምድር በእግዚብሔርና በሰው መካከል በተንጠለጠለ መሰዊያ ላይ እንስሳ የደም መስዋዕት በኩል ወደሱ በማቅረብ መሆን አለበት።

> "የጭቃ መሠዊያ **ሥራልኝ**፥ የሚቃጠለውንና የደኅንነት
> መሥዋዕትህን በጎችህንም በሬዎችህንም **ሠዋበት**፤

**ስሜን በማሳስብበት ስፍራ ሁሉ ወደ አንተ መጥቼ እባርክሃለሁ።”** (ዘጸአት 20:24)

ደም የኃጢአት ምትክ ሆኖ የመቀረቡ ሚስጥርም በተቀጠረው ጊዜ ተስፋ የተሰው መሲህ እስከሚመጣ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ጻደቅ ቁጣውን ለማሳየት ነው። የመሲሁ ተልዕኮ የመስዋዕትን ሕግ እውነተኛ ትርጉም መፈጸም ነው።

በእግዚአብሔር እይታ የአንድ ሰው ሕይወት በምድር ላይ ከሚገኙ እንስሳት ሕይወት ሁሉ የበለጠ ነው። እንስሳት በእግዚአብሔር ምሳሌ አልተፈጠሩም። እንስሳት ዘላለማዊ ነፍስ የላቸውም። ከመሆኑም የተነሳ የእንሰሳት ደም የሰው ልጅን ኃጢአት ለማስወገድ የሚያስፈልገውን ነገር የሚወክል ብቻ ነው።

የአቤል የታረዱቸ ጠቦት በብሉይ ኪዳን ተረካ ውስጥ ከሚገኙ እግዚአብሔርን ለማምለክ ንጹህና ነቀፋ የሌለባቸው እንስሳት ደም ከሚፈስባቸው በርካታ ምንባባት መካከል አንዱ ነው። ከበርካታ የእንስሳት መሰዋዕት ታሪኮቸ ውስጥ ከሌሎቹ አንዱ ከሌሎቹ ጎልቶ ይታያል።

ይሄም በዓለም ላይ በሚገኙ ሙስሊሞቸ በየዓመቱ ይታሰባል።



# 20

# ቅጽበታዊ መሰዋዕት

ቤተሰቡ በሙሉ ተሰባስቧል። አሳዛኙ ፍጡር ከመሬት ጋር ተጣብቆ ተይዟል። አዋቂዎቹና ሕፃናት በሙሉ በበጉ ላይ ወይም ደግሞ ቢላዋውን በያዘው አባት ላይ እጃቸውን ጭነዋል።

አስተራረዱ ፈጣን ነበር፣ የእንሰሳውም ሕይወት በአሸዋው ላይ ፈሰሰ።

እስከሚቀጥለው ዓመት መስዋዕቱ አብቅቷል።

በኢድ አል አድሃ፣ "የመሰዋዕት በዓል ቀን"፣ ሙስሊሞች የአራት ሺህ ዓመታት ዕድሜ ያለውን እግዚአብሔር በአብርሐም ልጅ ምትክ በግ መሰዋዕት እንዲሆነን የሰጠበትን ዕለት ያከብራሉ።[183] ቁርዓን የዚህን ጥንታዊ ታሪክ አጭር ገለፃ በሚከተለው ዐርፍተ ነገር ያጠቃልላል፦ "በቅጽበታዊ መስዋዕት አደረግንለት።" (ሱራ 37:107)

የዚህን አስገራሚ ታሪክ ሙሉ አስፈላጊነት ለማየት በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ወደሚገኘው ታሪክ መመለስ አለብኝ።

## አብርሐም

አብርሐም[184] በዘመናዊቷ ኢራቅ በምትገኘው የዑር ምድር በ2000 ዓዓ አካባቢ ተወለደ። ልክ እንደ አዳም ዘሮች የተወለደው ከኅጢአተኛ ባህርይ ጋር ነበር። ምንም እንኳን አብርሐም ያደገው ጣዖት አምላኪዎች መካከ ል ቢሆንም አብርሐም ግን የአንዱ እውነተኛ አምላክ አምላኪ ሆነ። አብርሐም በዚህ ዘመን ሰዎች ለአባቶቻቸው ሐይማኖት ታማኝ መሆን አለባቸው የሚለውን አስተያየት አይቀበልም ነበር።

እንደ አቤል አብርሐም ወደ እግዚአብሔር የቀረበው የእንስሳትን ደም መስዋዕት በማድረግ ነበር፡፡

አብርሐም የ75 ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ ባለቤቱ ስልሳ አምስት ዓመቷ ብር ጌታም ለእሱ ተገለጠለትና እንዲህ አለው፦

> “እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። **ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥** ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ **የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ**።” (ዘፍጥረት 12:1-3 አመት)

እግዚአብሔር ለአብርሐም በምድር ላይ ለሚገኙ ሰዎች ድነት የምሰጥበት “ታላቅ ሕዝብ” አደርግኸለሁ ብሎ ቃል ገባለት፡፡ ይህ ሕዝብ “ታላቅ” የሚሆነው በመጠን ሳይሆን በአስፈላጊነት ነው፡፡ ይህንን ሕዝብ እውን ለማድረግ ምንም እንኳን አሁን ዘር ባይኖራቸውም አብርሐምና ልጅ የሌላት ሚስቱ ሳራ ለዘራቸው ሊሰጠው ወዳሰበው ምድር እንዲገቡ ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል፡፡

የእግዚአብሔር የማይቻል የሚመስል የተስፋ ቃል በተመለከተ አብርሃም የሰጠው ምላሽ ምንድን ነው? የአባቱን ቤተሰቦች በመተው፣ ዛሬ እስራኤልና ፍልስጤም ወደሚባለው ወደ ከነዓን በመሄድ እግዚአብሔርን በመታመን ታዘዘ፡፡

## የአብርሐም እምነት

አብርሐም ከነዓን ከደረሰ በኋላ ጌታ እንዲህ አለው “ይህችን ምድር **ለዘርህ** እሰጣለሁ አለው፡፡ እርሱም ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር በዚያ ስፍራ መሠውያን ሠራ፡፡” (ዘፍጥረት 12:7)

የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል አስደናቂ ነበር፡፡ የከነዓን ምድር በተለያዩ ሕዝቦች የተሞላ ምድር ነበር፡፡ አብርሐም እና ዘር የሚይዙት እንዴት አድርገው ነው? እሱና ባለቤቱ ደግሞ ዝርያም የላቸውም፡፡

እስቲ አረጋውያን ባልና ሚስቶችን የእናንተን ሐገር ሊጎበኙ እንደመጡ አድርጋችሁ አሰቡት፡፡ በሚደርሱት ጊዜም “አንድ ቀን እናንተ እናንተና ዘሮቻችሁ ይህንን ሐገር በሙሉ ትቆጣጠራላችሁ!” ብትሏቸው፡፡ ሽማግሌው ሰውዬ “ያስቃል!

እኔኮ ዘር እንኳን የለኝም! እኔ ሽማግሌ ሰው ነኝ፣ እኔ ልጅ የለኝም ባለቤቴም ልትጸንስ አትችልም ፣ እናንተ ደግሞ ዘሮችህ በዝተው ይህችን ምድር ይወርሳሉ? ያምኸል?”

እግዚአብሔር ለአብርሐም የገባለት ተሰፋ ይህን ያህል የማይሆን ነበር። ታዲያ አብረሐም ምን አይነት ምላሽ ሰጠ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል “በእግዚአብሔር **አመነ፤ ጽድቅም** ሆኖ ተቈጠረለት።” (ዘፍጥረት 15:6)። ምክንያቱም አብርሐም በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ላይ የነበረው እንደ ልጅ ያለ እምነት የተነሳ እግዚአብሔር ጻድቅ አለው። ከሞተ በኋላ አብርሐም ከጌታ ጋር በሰማያዊ መንግስቱ ይኖራል።

በዋናው የዕብራይስጥ ምንባብ ውስጥ የሚገኘው “አመነ” የሚለው ቃል አማን ሲሆን “አሜን” ማለትም “እንደዚያው ይሁን!” ማለት ነው ወይም “እሱ ተዓማኒ እና እውነት ነው!” ማለት ነው

ይህንን አትሳቱ። በጌታ ማመን ማለት የተናገረውን መስማት እና ከልብ በመነጨ “አሜን” መመለስ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘን እንደ ልጅ ያለ እምነት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላችንን ወይም አለመቀበላችን የሚታየው በድርጊታችን ነው። የአብርሐም እምነት እውነተኛነት የተረጋገጠው ከባዱን መንገድ በመምረጡ ከአባቱ እምነት ጌታን ለመከተል በማፈንገጡ ነው።

> “**አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ** ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም **ወዳጅ** ተባለ።” (ያዕቆብ 2:23)

አብርሐም የእግዚአብሔርን ቃል ስላመነ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆኖ ነበር። ይሄ ማለት አብርሐም ሁል ጊዜ በሁሉም የሕይወቱ ክፍል እግዚአብሔርን አምኗል ማለት አይደለም። በንግግርም እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅ ብሎታል ፣ በዕለት ከዕለት ሕይወቱ ግን አብርሐም ፍጹም አልነበረም።

መጽሐፍ ቅዱስ የነብያትን ሳጢአት እና ደካማ ጎን አይደብቅም ነበር።

## እስማኤል

አብርሐምና ሳራ በከነዓን ምድር እንደ አርብቶ አደር፣ በድንኳን ውስጥ በመኖር እና ከቦታ ቦታ በመንሳቀስ ይኖሩ ነበር። ከጊዜ በኋላ

አብርሐም በከብቶቹ ብዛት እጅግ በጣም ባለጠጋ ሆነ።

አብርሐምን ታላቅ ሕዝብ አደርግኻለሁ ካለው ከአስር ዓመታት በላይ አልፏል። በአሁኑ ሰዓት አብርሐም ዕድሜው ሰማኒያ ስድስት ባለቤቱም ሰባ ስድስት ዓመት ሆኗት ነበር። እስካሁን አንድም ልጅ አልነበራቸውም። አብርሐም ልጅ ከሌለው እንዴት ታላቅ ሕዝብ ሊሆን ይችላል? አብርሐምና ሚስቱ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንዲፈጽም "ሊረዱት" ሞከሩ።

ጌታ የራሱን ዕቅድ በራሱ ጊዜ እንዲፈጽም ከመጠበቅ ይልቅ ፣ ደመ ነፍሳቸውን እና የአባቢውን ባህል ተከተሉ። ሳራ አብርሐም አብሯት እንዲተኛ እና ከእሷ ልጅ እንዲወልድ ግብጻዊዋን የቤት ሠራተኛዋን ሃጋርን ለአብርሐም ሰጠቻው። አጋር ለአብርሐም እስማኤል ብሎ የሰየመውን ልጅ ወለደችለት።

ከአስራ ሦስት ዓመታት በኋላ አብርሐም የዘጠና ዓመት ሰው ሲሆን ሁሉን ቻዩ አምላክ ተገለጠለትና ሚስቱ ሳራ ልጅ እንደምትወልድ ተናገረው።

> "አብርሃምም በግምባሩ ወደቀ፤ ሳቀም፤ በልቡም አለ፦ የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን? አብርሃምም እግዚአብሔርን፦ **እስማኤል** በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው። እግዚአብሔርም አለ፦ በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ። ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፤ ፍሬያምም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋለሁ፤ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፤ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ። ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ።"
> (ዘፍጥረት 17:17-21)

## ይስሐቅ

እግዚአብሔር የተሰፋ ቃሉን ጠበቀ። ሳራ በሰተርጅና ለአብርሐም ይስሐቅ የተሰኘ ወንድ ልጅ ወለደችለት።

> "ሕፃኑም አደገ፥ ጡትንም ከመጥባት ተቋረጠ፤ አብርሃምም ይስሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ትልቅ

ግብዣን አደረገ። ሣራም ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን ልጅ ሲስቅ አየችው።” (ዘፍጥረት 21:8-9)

እስማኤል እግዚአብሔር በይስሐቅ በኩል እውነቱን የሚያካፍልበት እና ድነቱን ለዓለም የሚሰጥበትን ሕዝብ ማስነሳቱን አልወደደውም። ከዚህም የተነሳ እሰማኤል የኣባቱን ልጅ አንቋሸሸው። ውጥረቱ በመጨመሩም አብርሐም እስማኤልንና አጋርን እስከ ማባረር አደረሰው። ይሄ ልጁን ይስሐቅን ለሚወደው ለአብርሐም የሚያሳምም ነበር።

“አብርሃምንም፦ ይህቸን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ፤ የዚህች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይወርስምና አለችው። እግዚአብሔርም ከብላቴናው ጋር ነበረ፤ አደገም፥ በምድረ በዳም ተቀመጠ፥ ቀስተኛም ሆነ። በፋራን ምድረ በዳም ተቀመጠ፤ እናቱም ከምድረ ግብፅ ሚስት ወሰደችለት።” (ዘፍጥረት 21:12 ፣ 20- 21)

ጌታ ተሰፋ እንደሰው እስማኤል አግዚአብሔር በብዙ መልኩ የባረከው ሕዝብ አባት ሆነ። ነገር ግን ጌታ ለዓለም ደነትን ለመስጠት የገባውን ኪዳን የሚፈጽመው “በይስሐቅ በኩል” መሆኑን ግልጽ አደረገ።

## እስራኤል

በስተኋላም ይስሐቅ አግብቶ ዔሳው እና ያዕቆብ የተባሉ መንታ ልጆች ወለደ። እግዚአብሔር በሰተኋላ ለያዕቆብ አዲስ ስም ሰጠው “ስሙንም **እስራኤል** ብሎ ጠራው።” (ዘፍጥረት 35:10) አለው። ያዕቆብ የእስራኤል ነገድ አባቶች የሆኑትን ፣ በስተኋላ በሙሴ ዘመን አስራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች የሆኑትም እና እግዚአብሔር እንደ ሐገር ያደራጃቸውን አስራ ሁለት ልጆች ወለደ። ጌታም እነዚህን የአብርሐም የይስሐቅ እና የያዕቆብ ዘሮች የተመረጡ ሕዝቦች አላቸው።[185]

ለምንድን ነው የመረጣቸው? ከሌሎች ሐገራት ተሻሉ ነበሩ? በፍጹም እንዲያውም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንደነገራቸው “በቊጥር **ጥቂቶች** ነበራችሁና” (ዘዳግም 7:7) ነበሩ። እግዚአብሔር ደካሞች ፣ የተዋረዱ ዕብራውያን ሰዎችን የመረጠው ፣ እሱ ሊፈጽመው ባቀደው ነገር ማንም ሰው ዕውቅና ወይም ምስጋና እንዳያገኝ ነው።

ጌታ እግዚብሔር መስራት የሚወደው እንዲህ ነው።

> “ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን **ሞኝ** ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን **ደካማ** ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር **የተናቀውንም ነገር** ያልሆነውንም ነገር መረጠ፥ **ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ።**” (1ቆሮንቶስ 1:27-29)

## የግንኙነት መስመር

እግዚአብሔር መልዕክቱን እስከ ምድር ዳርቻ ለማድረስ እንደ መስመር የሚጠቀምባትን ሐገር አስነሳ። እግዚአብሔር ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት ከመፈጠሩ በፊት ከሱ ያልተናነሰ በቃት ያለው “የግንኙነት መስመር” ፈጠረ። በዚህች ሃገር ውስጥ በቸኛው እውነተኛ አምላክ የሚያደርጋቸውን ታላላቅ ተግባር በዓለም ሁሉ ይሰማል። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ የከነዓናዊቷን ሴት ምስክርነት ይዘግባል “ከግብፅ ምድር በወጣችሁ ጊዜ እግዚአብሔር የኤርትራን ባሕር በፊታችሁ እንዳደረቀ፥ … ሰምተናል። …አምላካችሁም **እግዚአብሔር** በላይ በሰማይ በታችም በምድር **እርሱ አምላክ** ነውና ከእናንተ የተነሣ ከዚያ ወዲያ ለማንም ነፍስ አልቀረለትም።” (ኢያሱ 2:10-11)

ከዚህም በላይ መጽሐፍ ቅዱስን የሚጽፉ ነብያትን የመረጠው ከዚሁ ሃገር ነው።

በተለይም ደግሞ እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ የበረከት መሰመር የሚሆነውን ዘር የሚስነሳው ከዚችው ሐገር ነው። አስቀድመን እንደመለከትነው (ምዕራፍ 16) ይሄ ዘር ተሰፋ የተሰጠው የሴቷ ዘር ራሱ፣ ከሰማይ መጥቶ ከድሃሐ የአይሁድ ድንግል ብላቴና የሚወለደው ተስፋ የተሰጠው አዳኝ ነው።

ተስማማንም አልተስማማንም ይህች ጥንታዊት ሃገር የእግዚአብሔርን እውነትና ዘላለማዊ በረከት በምድር ላይ ለሚገኙ ሕዝቦች ለማዳስ እግዚአብሔር የመሠረታት የግንኙነት መስመር ናት።

የእግዚአብሔር ኪዳን ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፦

> 1) “**ታላቅ ሕዝብም** አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ”
> 2) “**የምድር ነገዶችም ሁሉ** በአንተ ይባረካሉ።”
> (ዘፍጥረት 12:2፣3)

የእግዚአብሔር ፍቅር ለአንድ የተለየ ቡድን የተገደበ አይደለም። አብርሐምን እና እስራኤልን ብቻ ለመባረክ አልፈለገም። ሩህሩህ ልቡ "የምድር ነገዶችም ሁሉ" ይናፍቅ ነበር። ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ትንሿን እና ልበ ደንዳናዋን ሐገር እስራኤልን ለአሕዛብ እና ቋንቋ ቡድኖች ጸጋውን ለማዳረስ እንዴት እንደተጠቀመባት በሚናገሩ ታሪኮች የተሞላ ነው።[186] ምንጊዜም ጌታ እስራኤልን ሊያጠፋት ከሚፈልጉ ሰዎች እንደጠበቃት መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን በዚህች በተዋረደች ሐገር በኩል እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ ለመባረክ ያለው ዓላማ ወደ አዕምሯችን ሊመጣ ይገባል። እግዚአብሔር እየጠበቃቸው የነበረው ከሌሎች ሃገራት የተሻሉ ስለሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔር ሳይሉን እና ክብሩን ለማሳየት እና ድነትን ለዓለም ሁሉ ለመስጠት መስመር ስለሆነ ነው። የአብርሐም፣ የይስሐቅን እና የያዕቆብን ዘሮች በመጠበቅ ፣ "የምድር አሕዛብ ሁሉ" ያለውን በረከቱን እየጠበቀ ነበር።

ከዚህም በላይ የእግዚአብሔር ስም አደጋ ላይ ነበር። አሕዛብን ሁሉ በደካማና በተናቀች ሃገር በኩል ለመባረክ በታላቅ ስሙ ምሎ ነበር።[187] እግዚአብሔርም ለስሙ ክብር ሲል መኻላውን ይፈጽማል።

ስማችን ፣ ክብራችን እና ቤተሰባችን ለአደጋ ቢጋለጥ እኛስ ይሄንኑ አናደርግም?

## እግዚአብሔር አብርሐምን ፈተነው

እስቲ አሁን ደግሞ ፊታችንን የአብርሐምን ቅጽበታዊ መሰዋዕትነት ወደሚያሳየው ተወዳጅ ታሪክ እንመልስ።

መቼቱ ይኸውላችሁ፦ አብርሐም በጣም አርጅቷል። ከበርካታ ዓመታት በፊት እስማኤል ከቤት ወጥቷል። የአብርሐምና የሳራ ልጅ የሆነው ይስሐቅ ብቻ በቤት ውስጥ ይገኛል።

እግዚአብሔር የአብርሐምን እምነት እስከ መጨረሻ ሊፈትነው ፈለገ። ጌታ እግዚአብሔር የኃጢአት የሞት ፍርዴ የተፈረደባቸውን የአዳም ልጆች ለመዋጀት እሱ ራሱ ያዘጋጀውን ዕቅድ የሚያሳዩ ጥቂት ምልክቶችን እና ትንቢቶችን በዓለም ፊት ለማስቀመጥ ፈልጓል።

> "ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ እንዲህም አለው፦ አብርሃም ሆይ።

> አብርሃምም፦ እነሆ፤ አለሁ አለ። የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።” (ዘፍጥረት 22:1-2)

እግዚአብሔር አብርሐምን ወደ አንድ ተራራ ጫፍ ሄዶ የሚወደውን ልጁን በመሰዊያ ላይ አረዶ እንዲሰዋ አዘዘው። ምን አይነት አስደንጋጭ ጥያቄ ነው። ይሄ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ማንንም ጠይቆ የማያውቀው ወደፊትም የማይጠይቀው አይነት ጥያቄ ነው። ነገር ግን ይስሐቅ እንደ ሌሎቹ የአዳም ዘሮች የኀጢአት ዕዳ አለበት ከዚህም ፍርድ የተነሳ ሞት ፍትሐዊ ፍርድ ነው።

> “አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፤ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፥ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ፤ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ።” (ዘፍጥረት 22:3)

አብርሐም እግዚአብሔርን ታመነ ፤ ነገር ግን ቀላል አልነበረም። ለሦስት ከባድ ቀናት አብርሐም፣ ልጁ እና ሁለት አገልጋዮቹ ተጓዙ ፤ እያንዳንዱም እርምጃ ወደሚገደልበት ቦታ የሚያቀረበው ነበር።

> “በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አነሣና ቦታውን ከሩቅ አየ። አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው፦ አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፤ ወደ እናንተም እንመለሳለን።” (ዘፍጥረት 22:4-5)

አብርሐም አገልጋዮቹን “ወደ እናንተም እንመለሳለን። “አላቸው

ይስሐቅ በመሰዊያ ላይ ታርዶ የሚቃጠል ከሆነ አብርሐም እና “ተመልሰው ሊመጡ” የሚችሉት እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ስፍራ ምላሽ ይሰጣል። እግዚአብሔር ለይስሐቅ ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆን ቃል ስለገባለት አብርሐም ሊጁን መሰዋዕት አድርጎ ካቀረበ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና እንደሚያስነሳው አምኖ ነበር።[188] አብርሐም ጌታ ሁል ጊዜ የተስፋ ቃሉን እንደሚጠብቅ አውቋል።

## እግዚአብሔር ምትክ አዘጋጀ

"አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም አብረው ሄዱ።" (ዘፍጥረት 22:6)

አባትና እናት ወደ ተራራ በሄዱ ጊዜ ይስሐቅ እንዲህ አለ

"ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው፦ አባቴ ሆይ አለ።

እርሱም፦ እነሆኝ፥ ልጄ አለው።

እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ **የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው**? አለ።

አብርሃምም፦ ልጄ ሆይ፥ **የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው**፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ።

እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው። አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ።

የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና፦ አብርሃም አብርሃም አለው፤ እርሱም፦ እነሆኝ አለ።

እርሱም፦ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ።

አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።" (ዘፍጥረት 22:7-13ሀ)

ጌታ ጣልቃ ገባ። የአብርሐም ልጅ ከሞት ቅጣት ተረፈ።

አብርሐም ፊቱን መለሰ ኣንድ በርቀት በተራራው ጠርዝ ላይ በቁጥቋጦው ውስጥ እንቅስቃሴ አየ። ምንድን ነው? እንትን ይሆን እንዴ? አዎ! እግዚአብሔር ይመስገን ! ያለነቀፋ የሆነ "በቁጥቋጦ ቀንዱ የተያዘ በግ"

በራሱ "የመሰዋዕት ሕግ" ላይ ተመሰርቶ እግዚአብሔር ምትክ አቀረበ።

"አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ **በልጁም ፋንታ** መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።" (ዘፍጥረት 22:13)



የአብርሐም ልጅ በላዩ ላይ ካጠላው የሞት ፍርድ ያመለጠው እንዴት ነው?

በእሱ ምትክ በጉ ሞተ።

እግዚአብሔር ምትክ አቀረበ።

## ጌታ ያዘጋጃል

"አብርሃምም ያንን ቦታ **ያህዌ ይርኤ** ብሎ ጠራው፤ እስከ ዛሬም ድረስ **በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል** ይባላል። "(ዘፍጥረት 22:14)

አብርሐም ጠቦቱን በልጁ ምትክ ከሰዋ በኋላ ቦታውን "ጌታ ያዘጋጃል" ብሎ የሰየመው ለምንድን ነው?

ለምንድን ነው ጌታ አቀርቧል ብሎ ያልሰየመው ለምንድን ነው?

"ጌታ ያዘጋጃል" በማለቱ ነብዩ አብርሐም ከሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ በኋላ የሚከሰተውን የወደፊት ሁኔታ እያስታወቀ ነበር። በዚህ ተራራ ጠርዝ (በስተኋላ ኢየሩሳሌም በምትገነባበት) ላይ ጌታ አንድን ሰው ከሞት ለማስመለጥ ሳይሆን ለዓለም ሁሉ ሙሉና የመጨረሻ መስዋዕት ለማቅረብ ሌላ መሰዋዕት ያቀርባል።

አብርሐም መሰዋዕት ወደሚቀርብበት ተራራው በሚወጡበት ጊዜ ያለውን ታስታውሳልቸሁ? እንዲህ ብሎት ነበር

**“ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው”**

አብርሐም ስለምን እያወራ ነው? እግዚአብሔር በአብርሐም ልጅ ምትክ የሚሰዋ ጠቦት አዘጋጅቷል? በፍጹም፣ ጠቦት አላቀረበም። እግዚአብሔር ያቀረበው በግ ነው። ስለዚህ ነብዩ አብርሐም “እግዚአብሔር ለራስሱ”?

አሰገራሚው መልስ ወዲያውኑ ይገለጣል፣ ከዚያ በፊት ግን ጥቂት ታሪኮቸ ሊነገሩ ይገባል።



# 21

# ተጨማሪ ደም መፋሰስ

እስቲ ቅን እንሁን፡፡

መንፈሳዊ እውነትን በተመለከተ ዘገምተኛ ተማሪዎች ነን፡፡ እግዚአብሔርም ይህንን ነገር ያውቃል፡፡

“ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት **መጀመሪያ ያለውን** የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም፡፡” (ዕብራውያን 5:12አመት)

ወይኔ!

እንደ አጋጣሚ ሆኖ እግዚአብሔር በጣም ታጋሽ መምህር ከመሆኑ የተነሳ ከብዙ ዓመታት በፊት ልንማርው የሚገባንን እውነት ለማስተማር ይደጋግማል፣ በሌላ መልክ ያስቀምጣል፡፡ እኛንም ለመርዳት እጅግ በጣም ወሳኝ የሆኑትን በመቶዎች የሚቆጠሩ እውነቶች በግልጽ በሆነ ሁኔታ ሊስተምረን በመጽሐፉ ውስጥ አካትቷቸዋል፦

“ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም፡፡” (ዕብራውያን 9:22አመት)

የኃጢአት ይቅርታ ፍጹም ለሆነው ቅዱሱ ፈጣሪያችን በጣም ቀላል ሆኖ አያውቅም፡፡ ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመሰዋዕት ተሰማሚ የሆነ ደም ብቻ ለኃጢአት ቤዛ(ሽፋን) እንደሚሆን ማስተማር ጀመረ፡፡ ጻድቅ

ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሳይቀጣ ኃጢአትን ሊቀጣ የሚችለው እንዲህ ነው።

ጌታ አምና ሄዋን ኃጢአታቸውን ለመሸፈን የሚያደርጉትን የግል ጥረት አልተቀበለም። ከሞት ዋጋ በስተቀር እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ሊል አይችልም። የቃየን እና የአቤል ታሪክ የሚያስተምረን ተመሳሳይ ትምህርት ነው። የአብርሐምና የይስሐቅም እንዲዚያው።

ዘፍጥረትን ተከትው የሚገኙ እንደ ዘጸአት እና ዘሌዋውያን ለዚህ የመሰዋዕት ሕግ ተገዢ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች ታሪክ የተሞላ ነው።[189]

## "አልፋለሁ"

የዘጸአት መጽሐፍ እግዚአብሔር ቃል እንደገባው እግብሔር የአብርሐምን ዘሮች እንደ አንድ ሐገር ያደራጀበትን የማይረሳ ታሪክ ይናገራል።

አብርሐም መለኮታዊ በሆነ ሁኔታ በተቀናጁ ተከታታይ ታሪኮች በኩል አስቀድሞ እንደተናገረ[190] የእስራኤላውያን ዘሮች በግብጽ ፈረዖኖች ስር ባሮች እንደሚሆኑ ይነግረናል። የእግዚአብሔር ከባርነታቸው መቤዠትና ሂደቱ የአዳምን ዘሮች የኀጢአት ባርነት የመቤዠት ዕቅዱን የሚያሳዩ ዓለማዊ "ምስሎችን" ያሳያል።

ይሄ የፋሲካ ታሪክ ነው።

በ1490 ዓዓ ጌታ በሙሴ ቃል ላይ ተመስርቶ በግብጽ ሐገር ላይ አስር መቅሰፍቶችን አመጣ። የግብጽን ሐሰተኛ ባዕዳን አማልክት ያሸነፉት የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ተዓምራዊ ምልክቶች ፈርዖን ለብቸኛው እውነተኛ አምላክ እንዲገዛ እና እስራኤላውያን ነጻ እንዲያደርግ አላስቻለውም።[191] አሥረኛው መቅሰፍት ግን እንዲለቃቸው ገፋፋው። እግዚአብሔር ሙሴን የእያንዳንዱን የግብጽና የእስራኤላውያንን ቤተሰብ የበኩር ልጅ የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት እንዲናገር አዘዘው። በተቀጠረው ቀን እኩለ ሌሊት የሞት መልዐክ በምድሪቷ ላይ አለፈና ከእያንዳንዱ ቤት በኩርን ቀሰፈ።

ይሄ መጥፎ ዜና ነበር።

የምሥራቹ እግዚአብሔር ከዚህ መቅሰፍት የማምለጫ መንገድ ያዘጋጀ መሆኑ ነው። ጌታ ሙሴ ለሁሉም ቤተሰብ "የእናንተ ጠቦት ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ይሁን፤ ከበጎች ወይም ከፍየሎች ውሰድ።" (ዘጸአት 12:5) አዘዘው።

ከዚያም በተቀጠረው ጊዜ ጠቦቱ ታረደ እና ደሙም በእያንዳንዱ ቤት መቃን ከላይ እና ከጎን ተቀባ። የሞት መቅሰፍት በምድቷ ላይ ባለፈ ጊዜ የጠቦቱን ደም በበራቸው መቃን ላይ ያደረጉና በቤት ውስጥ የተቀመጡ ይደናሉ።

ጌታ እንዲህ ሲል የተስፋ ቃል ሰጠ፦

> "ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ **ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ፤**" (ዘጸአት 12:13)

የተፈጸመው ሁሉ እግዚአብሔር የተናገረው ነው። በዚያ ምሽት በግብጽ በደሙ ስር የነበሩ የበኩር ልጆችን ሁሉ አዳነ፣ ሌሎቹ የፈርዖንን የበኩር ልጅ ጨምሮ ሞቱ።

እያንዳንዱ ቤት ሞት እንደደረሰ ልናስተውል ይገባናል። አዎ ሁሉም ቤት።

ወይ ጠቦት ሞቷል ወይም ደግሞ የበኩር ልጅ ሞቷል።

በዚያ ምሽት በበራቸው መቃን ላይ ደም ያደረጉ ከጭቆናና የባርነት ሕይወት አመለጡ። ነጻና የተዋጁ ሕዝቦች ሆነው ወጡ።

ለነጻ መውጣታቸው የቤዛነት ዋጋው ምን ነበር?

የጠቦቱ ደም።

በድጋሚም የመሰዋዕት ሕግ በሐጢአትና ሞት ሕግ ላይ በርትቷል። ከዚያ በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት አይሁድ እግዚአብሔር በጠቦቱ ደም በኩል የሰጣቸውን ታላቁን ነጻነት ዓመታዊ ክብረ በዓል የፋሲካን በዓል ያከብራሉ።

## እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲመራ

የዋናው ፋሲካ አንደኛው ምሽት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከአራት መቶ ዓመታት የግብጽ ግዞት ብኋላ ወደ በምድረ በዳ መራቸው። እግዚአብሔር ለአብርሐም ፣ ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ እና ዘሮቻቸው ሊመልሳቸው ወደ አቀደው ምድር አስገባቸው። በጉዟቸውም ወቅት እግዚአብሔር አምላክ ራሱ ሳይታይ ሊያጸናና በሚችል መልኩ ተከተላቸው።

> "በቀንና በሌሊትም ይሄዱ ዘንድ፣ መንገድ ሊያሳያቸው ቀን በደመና ዓምድ፣ ሊያበራላቸውም ሌሊት በእሳት ዓምድ እግዚአብሔር በፊታቸው ሄደ።" (ዘጸአት 13:21)

ጌታ ሕዝቡን በምድረ በዳ መምራትና ብርሃን መስጠት ብቻ ሳይሆን ብቻ ሳይሆን በብርቱ ክንዱ በቀይ ባህር ውስጥ መንገድ አዘጋጅቶ ከሚያባርራቸው የፈርዖን ሠራዊት ነጻ አስወጣቸው። በመቀጠልም ለሙሴ ቃል እንደገባው ወደ ሲና ተራራ አመጣቸው።[192]

እዚያ በዚያ ተራራ ግርጌ ይህቸ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ሃገር ለአንድ ዓመት ያህል ሰፈሩ። በዚያ ጭው ባለ ምደረ በዳ ሊኖሩ የሚችሉት እንዴት ነው? እግዚአብሔር በልካምነቱና በጸጋው መና ከሰማይ ወሃ ከዐለት እያፈለቀ አጠጣቸው።[193] ምንም እንኳን እስራኤላውያን ከባርነት ያወጣቸውን አንዱን በተከታታይ ለማመስገን፣ ለመታመን እና ለመታዘዝ ባይችሉም ጌታ ግን ሁልጊዜ ለእነሱ ታማኝ ነው። በእሱ ላይ ኅጢአት ሲሰሩ ይፈረድባቸውና ሲታመኑት ደግሞ ይባርካቸው ነበር። ጌታ በመረጣት ሐገር በኩል እንደዚህ የሰራው በዙሪያዋ የሚገኙ አሕዛብ አይተው፣ ተገንዝበው የመዋጀቱን መንገድ እንዲማሩ ነው።

አሥርቱን ትዕዛዛት (ምዕራፍ 15 ይመልከቱ) እና ሌሎች ሕግጋትን ለእስራኤል ከሰጠ በኋላ ጌታ ሕዝቡን ቤተ መቅደስ ወይም የመገናኛው ድንኳን ተብሎ የሚጠራ ልዩ ቦታ እንዲሰሩ አዘዛቸው።

## ቤተ መቅደስ

> “**በመካከላቸውም አድር** ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ። ኔ **እንደማሳይህ ሁሉ፥ እንደ ማደሪያው** ምሳሌ እንደ **ዕቃውም ሁሉ** ምሳሌ፥ እንዲሁ **ሥሩት**።” (ዘጸአት 25:8-9)

ጥንታውያን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይህንን ልዩ ድንኳን መስራት ያስፈለጋቸው ለምንድን ነው? “እንደማሳይህ” እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው መዘጋጀቱ ለምን አስፈለገ?

እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን በሚታይ መልኩ እንዴት እሱ ማን እንደሆነ እና ወደሱ እንዴት እንዲሚቀርቡ ማስተማሪያ ለማድረግ አቅዶ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰል መቅደሱ እና ተከትሎት ስለሚመጣው ነገር አምሳ ምዕራፍ ይዟል፣ ስለዚህ ሁሉንም በዚህ ስፍራ ማብራራት አይቻልም። አንዳንድ መሰረታዊ ነገሮችን ብቻ ማመልከት እንችላለን።

## አንዱ መንገድ

እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን የነደፈው ምንም እንኳን እሱ ፍም ቅዱስ ቢሆንም ፣ ከሰዎች ጋር መኖር እንደሚፈልግ ለማስተማር ነው። ነገር ግን በእግዚብሔር እና በሰው መካከል ዋና እንቅፋት አለ።

የእንቅፋት ኀጢአት ነው።

በሰዎች መካከል የሚገኘውን የእግዚአብሔርን መገኘት እንዲከልል የተቀመጠው ይሄ ልዩ ድንኳን አራት ማዕዘን ባለው ትልቅ አደባባይ የተከበበ ነው። የዚህ አደባባይ አጥር የተሰው በነሐስ ምሰሶ እና በስስ የናይለን ጨርቅ ነው፡ ሁለት ሜትር ተኩል ቁመት ርዝመት ሲኖረው ፣ ከፍታውም ሰው ውስጥ ማየት እንዳይችል የሚያደርግ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ከእግዚአብሔር መገኘት ርቀው እንደሚገኙ ደሆኑ እንዲረዱ ፈልጎ ነው። ያ ደግሞ መጥፎ ዜና ነው።

የምሥራቹ እግዚአብሔር ሰዎች ወደሱ እንዲቀርቡ መንገድ መክፈቱ ነው። ግድግዳው በሰማያዊ ፣ ሐምራዊ እና ቀይ ክር የተፈተለ ቀጭን በፍታም የተሰራ በር አለው። ሐጢአተኞች ጠቦት ወይም ደግሞ ሌላ ተስማሚ የመስዋዕት እንስሳት በመያዝ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚችሉት በዚያች አንድ በር[194] በመግባት ነበር።

ጌታ ለእስራኤላውያን ከግራር ዛፍ ትልቅ መሰዊያ እንዲሰሩ እና በነሐስ እንዲለብጡት ነገራቸው። መሰዊያው በበሩ እና በእግዚብሔር ልዩ ድንኳን መካከል ይቀመጣል። የኀጢአት መስዋዕት የሚያመጡ ሰዎች በንጹሁ እንሰሳ ራስ ላይ እጃቸውን ያደርጋሉ በመቀጠልም ረዳት የለሽ ኀጢአተኞች የመሆናቸውን ሁኔታ ይናዘዙበታል። እንስሳው ይታረድና ስጋው በመሰዊያው ላይ ይቃጠላል። እግዚአብሔር በድጋሚ ለሰዎች እያሳያቸው ያለው የኀጢአት እና የሞት ሕግ ሊሻር የሚችለው በመስዋዕት ሕግ ብቻ ነው።[195]

የእግዚአብሔር ሕግ ግልጽ ነው፦ ደም ሳይፈስ ፣ የኀጢአት ስርየት ሊኖር አይችልም። ኀጢአት ሳይሸፈን ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራቅ (ትክክለኛ ግንኙነት) አይቻልም።

በተጨሪም እግዚአብሔር ከእንጨት ተሰርቶ በወርቅ የተለበጠ ልዩ ሳጥን እንዲያዘጋጅ አዘዘው። ይሄ ትንሽ ዕቃ የኪዳኑ ታቦት ይባል ነበር። በሰማይ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ዙፋን ይወክል ነበር። እግዚአብሔር አሥርቱን ትዕዛዛት የቀረጸባቸው

ሁለት ገበታዎች በዚህ የወርቅ ሳጥን ውስጥ ተቀመጡ። ከንጹህ ወርቅ የተሰራው የሳጥኑ መክደኛ ስርየት መክደኛ ይባል ነበር። ክዳኑም ላይ ከወርቅ የተስሩ ሁለት የተንበረከኩ ኪሩቤሎች ነበሩ። እግዚአብሔር ሙሴን የኪዳኑን ታቦት በቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል እንዲያሰቀምጠው አዘዘው።

## ቅድስተ ቅዱሳን

መቅደሱ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው። የፊት ለፊቱ ክፍል ቅድስት ሲባል የውስጠኛው ክፍል እጅግ በጣም ቅዱሱ ስፍራ ወይም ቅድስተ ቅዱሳን ይባላል። ውስጠኛው መቅደስ "የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት... **ሰማይ**" (ዕብራውያን 9:24 አመት)

ቅድስተ ቅዱሳን መንግስተ ሰማያትን የእግዚአብሔርን መኖሪያ ይወክል ነበር። ይሄ ልዩ ክፍል አራት ዕኩል ማዕዘኖች ያሉት ሲሆን ርዝመቱ፣ ስፋቱ እና ቁመቱ እኩል ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናደርው ጉዞ አንድ ቀን የሁላችንም መኖሪያ የምትሆነውን ሰማያዊቷ ከተማ አራት እኩል ማዕዘን እንደሆነች እናያለን።

ሰዎች ስለ ካቴድራል፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ፣ መስጊድ ፣ ምኩራብ ወይም የአምልኮ ቦታ ቅዱስ ናቸው ቢሉም፣ እነዚህ ቦታዎች ግን የእግዚአብሔርን የመዋጀት ዕቅድ በማይቀበሉ ሰዎች የተሞሉ ናቸው። እውነተኛ ቅድስና የሚገኘው ወደተለየ ሕንጻ በመግባት ሳይሆን የእግዚአብሔርን የይቅርታ እና የጽድቅ አቅርቦት በመቀበል ነው።

## *መጋረጃው*

የቤተ መቅደሱ ውጫዊ ገጽታ ቀላል ነበር፣ ከእንስሳት ቆዳ የተሰራ ትልቅ ድንኳን ነበር። ከውጪ ስናየው አይስብም ፣ ከውስጥ ስናየው ግን ውብ ነው።[196]

የመቅደሱ ሁለት ክፍልች መሸፈኛ ተብሎ በሚጠራ መጋረጃ የተከፈሉ ናቸው።

> "መጋረጃውንም **ከሰማያዊ ከሐምራዊም ከቀይም ግምጃ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታም** አድርግ ብልህ ሠራተኛ እንደሚሠራ ኪሩቤል በእርሱ ላይ ይሁኑ።" (ዘጸአት 26:31)

መሸፈኛው ሰውን የእግዚአብሔርን መገኘት ክብርና ብርሃን የያዘውን ቅድስተ ቅዱሳንን እንዳያይ ይከልለዋል። ለአንድም ሰው ይሁን ለብዙ ሰው ከዚህ **ዞር በል ወይም ትሞታለህ** ይላል!

ይሄ ልዩ መጋረጃ የእግዚአብሔርን የጽድቅ መለኪያ ያሳያል። ጌታ ለሙሴ አስርቱን ትዕዛዛት በመስጠት ለሰው ልጆች በሙሉ መለኪያውን አሳውቋል። እነህ አሥር ሕግጋት እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር በከፊል የሚያሳዩ ናቸው። የእግዚአብሔር ዋና ዕቅድ ከእሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር የሚያስፈልገውን ፍጹም ቅድስና በተግባር የሚያሳየውን ልጁን ወደ ምድር መላክ ነበር።

መሲሁ የእግዚአብሔር መለኪያ ይሆናል። እግዚአብሔር መጋረጃውን ያዘጋጀው ስለ **እሱ** እንድናስብ ስለ ፈለገ ነው።

ይሄ የሚያምር መጋረጃ ከንጹህ ላይነን የተሰራ ሲሆን የሚያሳየውም የመሲሁን ንጹህነት ነው። እሱ ቅዱስና ያለ ኀጢአት ይሆናል።

በዚህ በንጹህ ጨርቅ ውስጥ የተፈተሉ የሚያማምሩ ቀለሞች ነበሩ፦ ሰማያዊ፣ ሐምራዊ፣ ቀይ

**ሰማያዊ**፦ የሰማያት ቀለም ነው። መሲሁ ከሰማይ የሚመጣ ጌታ ነው።

**ቀይ**፦ የምድር፣ የሰው እና የደም ቀለም ነው።[197] መሲሁ በኀጢአተኞች ምትክ መከራን ለመቀበል እና ለመሞት ሰጋና ደም ይወርሳል።

**ሐምራዊ**፦ የሰማያዊ እና የቀይ ድብልቅ መሲሁ አምላክ - ሰው ነው። ሐምራዊ የ ንገስታት ቀለም ነው። መሲሁ በእሱ በሚታመኑ ሰዎች ልብ መንፈሳዊ መንግስቱን ይመስርታል። በስኋላም አካላዊ የሆነውን መንግስቱን በምድር ላይ ይመሰርታል።

ሐምራዊ በሰያዊ እና በቀይ መካከል የሚገኝ ቀለም ነው፤ ስለሆነ መሲሁ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መካከለኛ ይሆናል።

> “አንድ እግዚአብሔር አለና፣ **በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ**፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፣ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ”
>
> (1ጢሞቴዎስ 2:5-6)

## የክብር ደመና

አንድ ጊዜ ቤተ መቀደሱ ከተሰራ እና በእግዚአብሔር ዕቅድ መሰረት ሁሉ ነገር ስፍራውን ከያዘ በኋላ በክብር ደመና ውስጥ የሚገኘውን የመገኘቱን ክብር ከሰማይ ላከ፡፡



"ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፤ **የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ**፡፡ ደመናውም በላዩ ስለ ነበረ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ስለ ሞላ ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ይገባ ዘንድ አልቻለም፡፡" (ዘጸአት 40:34-35)

ጌታ የክብርን መንጸባረቅ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በኪዳኑ ታቦት ላይ በሚገኙት ሁለት ኪሩቤሎች በሚገኘው ምህረት ዙፋን ላይ አኖረ፡፡

እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ መካከል በሚታየ መልኩ መጥቷል፡፡

"እግዚአብሔር ነገሠ፤ አሕዛብ ይደንግጡ በኪሩቤል ላይ **ተቀመጠ**፤ ምድር ትናወጥ፡፡" (መዝሙር 99:1)

ክብሩን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በማኖርና በመቅደሱ ላይ ደመናውን በማድረግ ፈጣሪ የዓለምን አሕዛብና አዲስ ለሚመጠው ትውልድ ከብቸኛው እውነተኛ አምላክ፣ ከሱ ጋር ግንኙነት እንዲመሰርቱ ይጋብዛል፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው በተገደቡ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ ነው የሚያደርገው የሚል ትምህርት ያስተላለፋል፡፡

## የሚታይ ምሳሌ

ቤተ መቅደሱ እግዚአብሔርንና እሱ ለሕዝቡ ያለውን ነገር ለማወቅ ለሚፈልጉ የማይቆጠሩ የሚታዩ ማስተማሪያዎች አቅርቧል።

እስቲ ሁኔታውን አስቡት።

እንደ እግዚአብሔር ትክክለኛ ትዕዛዝ ከሆነ የተዋጁ ባሪያዎች ፣ አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች በሲና ተራራ ግርጌ የመስቀል ቅርጽ ባለው መልክ ድንኳናቸውን ጥለዋል። ቤተ መቅደሱም በደቡብ ሦስት ነዶች ፣ በሰሜን ሦስት ነገዶች ፣ በምዕራብ በሦስት ነገዶች በምስራቅ ሦስት ነገዶች ተከቦ መሐከላቸው ይገኝ ነበር።[198] አንጸባራቂው ክብር ደመና በላዩ ላይ ይንሳፈፍ ነበር ፣ ማንኛውም ሰው ብቸኛው ሉአላዊ አምላክ በመካከላቸው መኖሩን አይክድም።

ሌሎች የሚታዩ ትምህርች ደግሞ ነጭ ናይለን ጨረቅ የተከበበውን አንድ በር ብቻ ካለው ቤተ መቅደስ ድንኳን በመካከላቸው ከመገኘቱ የተነሳ ትምህርት ይወስዳሉ። በበሩ በኩል አልፎ መሰዊያው ነበር። ፍጹም መሰዋዕትን በሚወክለው የፈሰሰ ደም መሠረትነት ወደሱ ካልቀረቡ በስተቀር ኅጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር ክብር ሊቀርቡ አይችሉም።

> “የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ **ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ** እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።” (ዘሌዋውያን 17:11)

ከሕይወት ክፍያ ውጪ የኅጢአት ይቅርታ ሊኖር አይችልም። ሰዎች ኅጢአት በሰሩ ቁጥር ወደ መሰዊያው መሰዋዕት ማምጣት ከባድ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር በዓመቱ ውስጥ በሚገኝ እያንዳንዱ ቀን ጠዋትና ማታ ጠቦት ታርዶ እንዲቃጠል አዘዘ። በጌታ እና በማዳን ዕቅዱ የሚታመኑ ሰዎች በዕለታዊው መሰዋዕት በሚገኘው የታደሰ ግንኙነት ተጠቃሚ ይሆኑ ነበር።

> “በመሠዊያውም ላይ የምታቀርበው ይህ ነው፤ **በቀን በቀን ዘወትር ሁለት የዓመት ጠቦቶች ታቀርባለህ።** አንዱን **ጠቦት** በማለዳ ቍርባን አድርገህ ታቀርበዋለህ ሁለተኛውንም ጠቦት በማታ ቍርባን አድርገህ ታቀርበዋለህ። **...ለአንተ እናገር ዘንድ ከእናንተ**

**ጋር በምገናኝበት** በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ፣ በእግዚአብሔር ፊት ይህ ዘወትር ለልጅ ልጃችሁ የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆናል።" (ዘጸአት 29: 38-39 ፣ 42)

## የመቤዠት ቀን

ይህንን እውነት ይበልጥ አጉልቶ ለማሳየት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኅጢአተኛ ሰው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን (ስማይን ወደሚወክለው ልዩ ክፍል) መግባት የሚችለው በአንድ መንገድ እንደሆነ አስረዳቸው። በዓመት አንድ ጊዜ በተለየ ሁኔታ የተመረጠ ሊቀ ካህን የተባለ ሰው ወደዚያ ውስጣዊ መቅደስ እንዲገባ ይፈቀድለታል። በመቤዠት ቀን [199] ሊቀ ካህኑ መሸፈኛውን አልፎ ወደ ውስጥ ይገባል። ይህን የሚያደርገው የተሰዋ ጠቦት ደም ይዞ ይገባና በምህረት ዙፋኑ(የኪዳኑ ታቦት መሸፈኛ) ፊት እና በምህረት ዙፋኑ ላይ ሰባት ጊዜ ይረጫል። ሊቀ ካህኑ ከዚህ በተለየ መንገድ ከገባ ይሞታል። በተረጨው ደም መሠረትነት እግዚአብሔር በእሱ እና በስጦታው ብቻ የታመኑ እስራኤላውያንን ኅጢአት ለቀጣይ አንድ ዓመት ይቅር ይላል።

የመቅደሱ ዝርዝር ፣ ዕቃዎቹ እና ተግባራቶቻቸው የተፈረደባቸው ኅጢአተኞች ኅጢአታቸው እንዴት እንደሚሸፈን እና ፍጹም ቅዱስ የሆነው ፈጣሪያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዴት እንደሚታደስ ቁልጭ ያለ ምሳሌ ለዓለም የሚሰጡ ናቸው። ሁሉም የሚያመለክተው ወደሚመጣው መሲህ እና ተልዕኮው ነው።

ስለዚህም በዘመናት መካከል የተመረጠቸውን ሐገር በመጠቀም ጌታ በርካታ ምስሎችን በማሰራጨት በኅጢአት ለጠፋው ዓለም በርካታ የተስፋ ቃሎችን አስተላልፏል።

## ቤተ መቅደሱ እና መሰዋዕቱ

ሙሴ ካለፈ ከአምስት መቶ አመታት በኋላ የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔር መገኘት የሚያድርበት ልዩ ድንኳን ሰሩ እግዚአብሔርም ንጉሥ ሰለሞንን ከተንቀሳቃሽ ድንኳን ይልቅ ቋሚ ቤተ መቅደስ እንዲሰራ አዘዘው። በኢየሩሳሌም የተሰራው ቤተ መቀደስ አቀማመጥ በጣም ትልቅና ያማረ ቢሆንም ልክ እንደ መገናኛው ድንኳንን ነበር። የሰለሞን ቤተ መቅደስ የጥንታዊው ዓለም ኪነ ሕንጻዊ ድንቃ ድንቅ ነበር።

በተመረቀ ቀን የመገናኛውን ድንኳን እግዚአብሔር መገኘት ከሰማይ መጥቶ ቅድስተ ቅዱሳኑን በእግዚአብሔር ክብር እንደሞላው ሁሉ የከበረ እና ያልተፈጠረ የእግዚአብሔር መገኘት ብርሃን ከሰማይ መጥቶ ቤተ መቅደሱን ሞላው።

> “ሰሎሞንም ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕቱን በላ የእግዚአብሔርም ክብር ቤቱን ሞላ። **የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበርና** ካህናቱ ወደ እግዚአብሔር ቤት መግባት አልቻሉም።”
>
> (2 ዜና 7:1-2)

ቤተ መቅስደሱ የተገባው ከሺህ ዓመታት በፊት አብርሐም በልጁ ምትክ ጠቦት በሰዋበት ቦታ ላይ ነው።[200] ይህንን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለማስመረቅ ንጉሥ ሰለሞን 120ሺህ በጎቸ እና 22ሺህ ኮርማዎቸን እንዲሰው አዘዘ።[201] ይህ የተትረፈረፈ መስዋዕት ከሺህ ዓመታት በኋላ እዚያ ኮረብታ አቅራቢያ ላይ የሚፈሰውን የማይለካ ዋጋ ያለውን ደም የሚያመለክት ነው።

ስለዚህም አዳም ፣አቤል፣ አብርሐም፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ሰምኦን እና ከእነሱ በኋላ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተምሳሌታዊ የደም መሰዋዕቶቸ፣ ከአንድ አድካሚ ዓመት እስከ ሌላው አድካሚ ዓመት ኅጢአትን ለመሸፈን በመሰዊያው ላይ ቀርበዋል።

ከዚያም መሲሁ መጣ።



# 22

# ጠቦቱ

“እግዚአብሔር ፍቅር ነው።” (1 ዮሐንስ 4:8)
“እግዚአብሔር ታላቅ ነው” (ኢዮብ 36:26)

**ፍቅር** የሆነው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የቅርብ ግንኙነት ይፈልጋል። የእግዚአብሔር ማህበራዊ — ግንኙነታዊ ባህርይ በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ተገልጧል።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን “በመልኩ ፈጠራቸው”፣ ይህንንም ያደረገው ከእነሱ ጋር ሳብረት ለማድረግ ነው (ዘፍጥረት 1:27)። ይኸው “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው” የተሰኘ ጭብጥ[202] የተዋጀው ሕዝብ “ፊቱን ያያሉ” እና ከእሱ ጋር እስከ ዘላለም (ራዕይ 22:4) እስኪኖር ድረስ ይቀጥላል። ይህንን ማየት የማይችል የትኛውም ሰው የእግዚአብሔርን መጽሐፍ ማዕከላዊ ጭብጥ ስቷል።

**ታላቅ** የሆነው እግዚአብሔር የፈለገውን ነገር ሁሉ ያደርጋል።

“እነሆ፥ እኔ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ፤
በውኑ እኔን የሚያቅተኝ ነገር አለን?” (ኤርሚያስ 32:27)

የትኛውም ቅን የሆነ አንድ አምላኪ እግዚአብሔር ከፈለገ ሰው ሊሆን አይችልም አይልም። ሁሉን ቻዩ ማድረግ የማይችለው ካለ (ከራሱ ጋር ከመጋጨት ውጪ)፣ ከአምላክ ያነሰ ነው ማለት ነው።

ጥያቄው “እግዚአብሔር ሰው መሆን ይችላል?” የሚል አይደለም።

ጥያቄው “እሱ ሰው ለመሆን መረጠ ወይ?” የሚል ነው።

## የእግዚአብሔር እውነተኛ ቤተ መቅደስ

እግዚአብሔር እስራኤውያንን “በመካከላቸው እንዲያድር” (ዘጸአት 25:8) ልዩ መቅደስ ደንኳን እንዲሰሩለት ካዘዛቸው ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አለ፦

> “በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።... ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ **በእኛ አደረ**፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው **ክብር** የሆነው ክብሩን አየን።”
> (ዮሐንስ 1:1፣14አመት)

“በእኛ አደረ” የሚለው ቃል የተተረጎመው በግሪኩ ድንኳን ወይም መቅደስ መስራት ከሚለው ነው። ቃል በቃል እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፦ ድንኳኑን በመካከላችን ጣለ። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን አካል ነፍስና መንፈስ የሚያርፉበት እንደ ድንኳን ወይም መቅደስ አድርጎ ያቀርበዋል።[203] በምዕራፍ 16 እንድተማርነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ የተወለደው እንደ ወንድ ሕፃን ነው። የእሱ ሰብዓዊ አካል ሊያርፍበት የመረጠው ድንኳን ነው።

በሙሴ ዘመን እግዚአብሔር የከበረ፣ ያልተፈጠረ የመገኘቱ ብርሃን በቤተ መቅደሱ ላይ ባረፈ ጊዜ የተሸፈነው በእንስሳት ቆዳ ነበር። ነገር ግን በኢየሱስ ማንነት የከበረ፣ ያልተፈጠረ የመገኘቱ ብርሃን የመጣው በሰው አካል ውስጥ ነበር። ስለዚህም ደቀመዛሙርቱ “አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።” አሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን “...**የእውነተኛይቱ ድንኳን**... በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት።” (ዕብራውያን 8:2) ይለዋል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ቤተ መቅደሱ በስተኋላም ቤተ መቅደሱ ኃጢአተኞች ኃጢአታቸውን ለመሸፈን የእንስሳት መስዋዕት የሚያቀርቡበት ቦታ ነበር። ኢየሱስ ልጅ በነበረበት ጊዜ እና ወደ አዋቂነትም ሲያድግ ቤተ መቅደሱን በተደጋጋሚ ጎብኝቷል፣ የኃጢአት መሰዋዕት ሲያቀርብ ግን አናነብም። ለምን አላቀረበም? ኃጢአት የለበትም። ኢየሱስ “በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል።” (ዕብራውያን 9:26) እሱ መሰዋዕት የሮማውያን መስቀል ደግሞ መሰዊያ ይሆናል።

ከተምሳሌቶቹ ጀርባ ያለው እውነታ ኢየሱስ ነው።

> “**በሥጋ** የተገለጠ [እግዚአብሔር]” (1 ጢሞቴዎስ 3:16)

በአንድ ወቅት ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አጠገብ ቆሞ ነበር እና ለተሰበሰቡ ወንዶች እንዲህ አላቸው፦

> “**ይህን ቤተ መቅደስ** አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።
> ስለዚህ አይሁድ፦ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት።
> **እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር።** ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።” (ዮሐንስ 2:19 -22)

አይሁድ ኢየሱስ የተናገረው “ቤተ መቅደስ” ስጋው መሆኑን አላወቁም። የተናገረው ስለሚያምረው የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ነው የመሰላቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር መገኘት ብርሃንና ክብር ሰው በሰራው ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አልበረም።

“ቤተ መቅደሱ” የኢየሱስ ስጋ ነበር።

በምድራዊ አገልግሎቱ ማብቂያ ላይ ኢየሱስ ሶስቱ ደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔርን ብርሃንና ክብር እንዲያዩ ለሦስቱ ደቀ መዛሙርቱ ፈቀደ።

> “ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፥ **ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ።**
> እነሆም፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ። እርሱም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ **ብሩህ ደመና ጋረዳቸው**፥ እነሆም፥ ከደመናው፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ **የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት** የሚል ድምፅ መጣ።” (ማቴዎስ 17:1-5)

የሰማይ መላዕክት ፊታቸውን እንዲሸፍኑ የሚያደርገው የሚንጸባርቀው የሚበለጭለጨው ንጹሁ የእግዚአብሔር ብርሃን በኢየሱስ ውስጥ ነበር።

ቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ይገኝ የነበረው ያው የከበረ የጌታ መገኘት በኢየሱስ ውስጥ ነበር።



በቤተ መቅደሱ ላይ በአንድ ወቅት ያበራው የሚያምር ደመና ኢየሱስ የቆመበት ቦታ ላይ ያበራ ነበር።

ኢየሱስ በምድር ላይ የሚገኝ የሚያበራ የእግዚአብሔር መገኘት ነበር።

የእግዚአብሔር ልጅ የሚይበራው ነጽብራቅ ከሰማይ በተሰማው የአብ ንግግር የታጀበ ነበር፦

> "በእርሱ ደስ የሚለኝ **የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት**"

እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደርጋል።

የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ከመሆኑ አስቀድሞ ነብዩ ዳዊት እንዲህ ብሏል "ልጁን ሳሙት እንዳይቈጣ እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፥ ቍጣው ፈጥና ትነድዳለችና። በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።" (መዝሙር 2:12)

"ልጁን ሳሙት" ማለት **ልጁን አክብሩት** ማለት ነው።

አልፎ አልፎ ሰዎች የሐይማኖት መሪዎችን ራስና እጅ ሲስሙ አያለሁ እነዚ ህሰዎችም ልክ እንደሱው ረዳት አልባ ሳጢአተኞች ናቸው። የሐይማኖት ተጓዦች ደጎሞ ስጋቸው ወደ አፈርነት

የተለወጠ ሰዎችን ለማክበር ሲጓዙ አያለሁ።

በዚህም መካከል ፣ እግዚአብሔር ለዓለም እንዲህ ሲል አስታወቀ "**ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ**፣ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም። ...አብ ወልድን ይወዳልና፤" (ዮሐንስ 5:23 ፣ 20)

## መንገድ ጠራጊው

"የጌታን መንገድ አዘጋጁ" (ኢሳያስ 40:3) ስለሚለው የምስራች ተናጋሪ ከጻፉ ሁለት ሰዎች መካከል አንዱ ኢሳያስ ነው። ያ መንገድ ጠራጊ የዘካሪያስ ልጅ ነብዩ ዮሐንስ ነበር።[204] የቀደሙት ነብያት "እግዚአብሔር መሲሁን ወደ ዓለም ይልከዋል" ያሉ ሲሆን ነብዩ ዮሐንስ "ተስፈ የተገባው መሲህ፣ ጌታ እዚህ ነው!" የማለትን ልዩ ክብር አግኝቶ ነበር።

> "በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፦ **መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ** ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። በነቢዩ በኢሳይያስ፦ **የጌታን መንገድ አዘጋጁ** ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።" (ማቴዎስ 3:1-3)

## ንሰሐ

ለጌታ ምጽዓት ሰዎችን ለማዘጋጀት የዮሐንስ መልዕክት በጣም ቀላል ነበር።

**"ንስሐ ግቡ!"**

ንሰሐ የሚለው ቃል የመጣው ግሪኩ ሜታኖያ ከሚለው ቃል ነው። ሁለት ክፍሎች አሉት ፦ ሜታ እና ኖያ። የመጀመሪያው ክፍል እንቅስቃሴ ወይም ለውጥ ማለት ነው። ሁለተኛው ሐሳብን አዕምሮን የሚያመለክት ነው። የንሰሐ መሰረታዊ ፍቺ የተለወጠ አዕምሮ እንዲኖረን ማድረግ ፣ የተሳሳተ አስተሳሰባችንን በትክክለኛ አሰተሳሰብ መተካት ማለት ነው።

ንሰሐ መግባትን በዕለት ተዕለት ሕይወት ዐውድ ውስጥ ለማስቀመጥ በአውቶብስ ወደ ሌላ ከተማ ምናልባትም ከቤሩት ወደ አማን ለመጓዝ አሰቤያለሁ እንበል። ትክክለኛ ነው ብዬ ያሰብትን አውቶብስ ተሳፈርኩ እና እንዲያሽልበኝ ተመቻቸሁ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ አውቶብሱ በፈጣኑ መንገድ ሲጓዝ እየተጓዝኩ ያልሁት ወደ ደቡብ አማን ሳይሆን ወደ ሰሜን ኢስታንቡል ነው! ምን ማድረግ አለብኝ?

ሁለት አማራጮች አሉኝ፦

ስህተቴን ለማመን ኩራት ካለብኝ በዚያው አውቶቡስ ጉዞዬን ቀጥዬ የተሳሳተ ቦታ እደርሳለሁ።

ወይም ደግሞ በትህትንና ንሰሐ ገብቼ ማለትም አሳቤን ቀይሬ የተሳሳተ አውቶቡስ እንደተሳፈርኩ አምናለሁ። ይሄ የንሰሐ እውነተኛነት የሚረጋገጠው በሚቀጥለው ፌርማታ ሰቆምና ትክክለኛው አስውቶብሱ ውስጥ ስገባ ነው።

እውነተኛ ንሰሐ ሰውን ከስህተት ተመልሶ እውነትን እንዲያምን ያደርገዋል።

ንስሐ የአንድ ሳንቲም አንድ ገጽታ ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

አንደኛው ገጽታ እንዲህ ይላል፦ **ንሰሐ ግባ!**

ሌላኛው ገጽታ እንዲህ ይላል ፦**እመን!**

ሁለቱም ገጽታቸ እግዚአብሔር የሚፈለገውን ያሳያሉ።

> "ወደ እግዚአብሔር ዘንድ **ንስሐን**ና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ **ማመን**ን..." (ሐዋርያት 20:21)

ንሰሐ ማለት ለድነታችሁ የምትታኑትን ነገር በተመለከተ ሐሳብን መለወጥ ማለት ነው። እምነት ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር የድነት ሥጦታ መታመን ማለት ነው።

ከንሰሐ ውጪ እውነተኛ እምነት የለም።

በተመሳሳይ መልኩም የነብዮ ዮሐንስ መልዕክት የሚከተለውን የሚመስል ነው፦ "ከተሳሰተ ሐሳባችሁ ንሰሐ ግቡ! ራሳችሁን እንደማታድኑ እመኑ፣ ከሰማይ የመጣውን መሲህ-ንጉስ ተቀብሉ! የመጣው በራሳችሁ መተማመን አቁማችሁ በእሱ መተማመን ብትጀምሩ ከሰይጣን ፣ ከኅጢአትና ከሞት ነጻ ሊያወጣችሁ ነው።

ኅጢአተኙነታቸውን በእግዚአብሔር ፊት ያመኑ በወንዝ ውስጥ በዮሐንስ ይጠመቁ ነበር። ዮሐንስ መጥምቁ ዮሐንስ የተባለው ለዚህ ነው። በውሃ ውስጥ መጠመቅ ከሐጢአት ሊያነጻ አልቻለም፣ አይችልምም። በወንዝ ውስጥ መጥለቅ እግዚአብሔር ንሰሐ የገቡ እና የሚያምኑ ኅጢአተኞችን ለማንጻት የመጣውን መሲህ በተመለከተ እግዚአብሔር ያስተላለፈውን መልዕክት በውስጣችሁ መቀበላችሁን የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ነው።

## የተመረጠው

በምድራዊው አገልግሎቱ ጀማሬ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሊጠመቅ ወደ ኢየሱስ መጣ፡፡ ኅጢአት የሌለበት መሲህ ምንም ንስሐ አያስፈልገውም ነበር፤ነገር ግን በመጠመቁ ሊያድነው ከመጣው ከወደቀው የሰው ልጅ ጋር ራሱን አምሳሰለ፡፡

የኢየሱስን ጥምቀት ተከትሎ የተከሰተው ነገር በፍጹም የማይረሳ ነው፡፡ የብቸኛውን እውነተኛ አምላክ ውሰብስብ አንድነት እና ክብር ሌላ ገጽታ ያሳየናል፡፡

> "**ኢየሱስም** ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ **የእግዚአብሔርም መንፈስ** እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፥ **ድምፅ ከሰማያት መጥቶ**፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡" (ማቴዎስ 3:16-17)

በፍጥረት የመጀመሪያ ቀን እንደሆነው ይሄ ትረካ የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን መገኘት ይገልጥልናል፡፡ ነገር ግን በዚህ በዚህ ቁልፍ ታሪካዊ ወቅት የብዝኸነት አንድነቱን በበለጠ ግልጽነት እየገለጠ ነበር፡፡ በመጽሐ ፍ ቅዱስ ውስጥ በምናደርገው ጉዞ ተጓዡ ቆም ሊል ፣ ፎቶ ሊነሳና ሊያስብ ከሚገባው ልዩ ቦታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

ትዕይንቱ ይህንን ይመስላል፡፡ በሚያስገርመው የሚያበራ ሰማይ ስር **የእግዚአብሔር ልጅ** (ሰማይና ምድር የተፈጠሩበት ቃል)ወደ ወንዝ ይሄዳል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ **የእግዚአብሔር መንፈስ** (ፍጥረት የመጀመሪያ ቀን በውሃ ላይ ሲሰፍ የነበረው መንፈስ) ከሰማይ ይወርዳል በእርግብ አምሳልም በኢየሱስ ላይ ያርፋል፡፡ በመጨረሻም **እግዚአብሔር አብ** ከሰማይ "በእርሱ ደስ የሚለኝ ምወደው ልጄ" ይላል፡፡

ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ኢየሱስ በትንሿ የናዝሬት ከተማ ከደሃ ቤተሰቡ ጋር ተደብቆ ይኖር ነበር፡፡ ምንም እንኳን ከሕዝብ ዐይን የራቀ ቢሆንም በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በሰማይ ያለው አብ ዐይን በሚወደው ልጁ ላይ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እግዚአብሔር በኢየሱስ ሕይወት ላይ የሚያስተላልፈውን ውሳኔ ተመልከት፦ **"በእርሱ ደስ የሚለኝ"**

እግዚአብሔር ለሌላ ሰው ይህንን ሊል አይችልም፡፡ በውስጡም በውጪውም በሁሉም ነገር ያስደሰተው ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ ከሰማይ እንደ መጣ ልጅ የተቀደሰ፣ ያለረከሰ እና ሊሰራው

የመጣውን ለመስራት የበቃ ነበር። እሱ መሲሁ ፣ የተቀባው ፣ የእግዚአብሔር ምርጥ ነበር። እግዚአብሔር የቀባው በዘይት (ለካህናትና ለነገስታት እንደሚደረገው[205]) ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ በራሱ ነበር።

> "**እግዚአብሔር** የናዝሬቱን ኢየሱስን **በመንፈስ ቅዱስ** በኃይልም ቀባው..." (ሐዋርያት 10:38)

ኢየሱስ ነቢያት ስለ እሱ የጻፉለት እርሱ ነበር።

## የእግዚአብሔር በግ

> "በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፦ **እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።**" (ዮሐንስ 1:29)

የነብዩ ዮሐንስ ማስታወቂያ በትርጉም የተሞላ ነው።

- "እነሆ... **የእግዚአብሔር በግ**"
  የዮሐንስ አድማጭ የበጉን ትርጉም እስከ እስከተወሰነ ድረስ ተረድቷል። ከኅጢአት መግባት ጀምሮ ሰዎች ለኅጢአታቸው መሰዋዕት በጎችን ያቀርቡ ነበር። ለአሰራ አምስት ክፍለ ዘመናት ያክል በእነሱ መሰዊያ ላይ ቀንና ማታ ጠቦት ይሰዋ ነበር። አሁን ግን የእግዚአብሔር የራሱ በግ መጥቶ ነበር።
  ከሁለት ሺህ ዓመታት አሰቀድሞ አብርሐም ለልጁ "ልጄ ሆይ፣ የመሥዋዕቱን **በግ** እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው" (ዘፍጥረት 22:8) በሎት ነበር።
  በርግጥም እግዚአብሔር በአብረሐም ልጅ ምትክ የሚሰዋ መሰዋዕት አዘጋጅቶ ነበር፣ ነገር ግን "ጠቦት" አልነበረም። "አንድ በግ" ነበር (ዘፍጥረት 22:13) በአብርሐም ትንቢት ውስጥ የሚገኘው "በግ መሲሁ ራሱ ነው። አብርሐም ወደፊት ኢየሱስን እያሳየ ነበር። ለዚህም ነው ኢየሱስ የሚከተለውን ያለው፤ "አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፤ አየም ደስም አለው።" (ዮሐንስ 8:56)

- "...የዓለምን ሐጢአት **የሚስወግድ**..."

ከአዳም ጊዜ ጀምሮ የንጹህ እንስሳ ደም ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ በእግዚአብሔርና በዕቅዱ የታመኑትን ሰዎች ኀጢአት ሸፍኖ ነበር ፤ኢየሱስ ሊያደርገው የመጣው ነገር ግን ከዚያ የተለየ ነበር። የኀጢአትን ቅጣት ለዘላለም አስወግዷል።

- "…**የዓለምን**…"
  ባለፈው ዘመን የኀጢአት የደም መሰዋዕት ይቀርብ የነበረው በግለሰብ፣ ቤተሰብ ወይም ሐገር ምትክ ነበር። ነገር ግን የኢየሱስ ደም ላለፈው፣ የዓለምን ሁሉ ለአሁኑ እና ለወደፊት የኀጢአት ዕዳ ሙሉ እና የመጨረሻ ክፍያ ነበር።

የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኀጢአት ያሰወግዳል ማለት እያንዳንዱ የተወለድ ሰው በቅጽበት በእግዚአብሔር ይቅር ይባላል ማለት ነው? በፍጹም ኀጢአት ወደ ሰው ዝርያ ሐጢአት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በእሱና በስጦታው ማመንን እግዚአብሔር ግድ ይላል።[206]

> "የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። **ለተቀበሉት ሁሉ** ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" (ዮሐንስ 1:11-12)



## ጥላና ምልክት

ባለፉት ዓመታት እያንዳንዱ ለኀጢአት መሰዋዕት የሆነ በግ ሁሉ "ሊመጣ ያለው…የነገር ጥላ አለውና" (ዕብራውያን 10:1)

ጥላ ጥላውን ከጣለው አካል ጋር መምታታት የለበትም። ጓደኛችሁ ወደናንተ ሲመጣ መሬትን ብትመለከቱ እሱን ከማየታችሁ በፊት ጥላውን ታያላችሁ ፊታችሁ መጥቶ ከቆመ በኋላ ከጥላው ይልቅ ፊታችሁ የቆመውን ወንድማችሁን አታዋሩትም?

የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች እግዚአብሔር ያዘጋጃቸው

የመሲሁን መምጣት የሚያስታውቁ አስተዋጽዖዎቸን የሚያሳዩ ጥላዎቸ ናቸው። እግዚአብሔር እሱን እንድንመለከት እና እንድንሰማ ይፈልጋል።

> “የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ **የማይቻል ነውና**። ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ [መሲሁ]፦ መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ***ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ***፤ በዚያን ጊዜ፦ እነሆ፥ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ፥ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ **መጥቼአለሁ** አልሁ ይላል።... ቀጥሎ፦ እነሆ፥ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሎአል። ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል። በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን *ሥጋ* አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።” (ዕብራውያን 10:4-7 ፣ 9-10)

የእንስሳት የደም መሰዋዕት እግዚአብሒር በዋነኛነት የሚፈልገውን የመጨረሻ ነገር የሚያሳይ ተምሳሌት ነው። እንስሳት በእግዚአብሔር መልክ አልተፈጠሩም። የበግ ዋጋ ከሰው ዋጋ ጋር እኩል አይደለም። ወደ መኪና ሻጭ አሻንጉሊት መኪና ወሰዳችሁ ለእውነተኛ መኪና የሚከፈለውን ዋጋ እንደማትጠይቁ ሁሉ የጠቦት ደም የሰውን የሐጢአት ዕዳ ሊከፍል አይችልም። እኩል ወይም የበለጠ ዋጋ ያለው መስዋዕት ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ያንን መሰዋዕት ሊያቀርብ ነው።

## ደካማ ዕቅድ አውጪ

ከጥቂት ዓመታት በፍልስፍና ዶክትሬት ካለው ሰው ጋር እጻጻፍ ነበር። ኢየሱስ የመጣው “የዓለምን ኅጢአት ሊያሰውግድ” ነው የመጣው ለሚለው ንግግር ምላሽ ሲሰጥ፦

> መልዕክት | ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ
>
> ይህንን ከንቱ ድሪቶ ከ2000 ዓመታት ከማምጣቱ በፊት የሞቱ ሰዎች ምን ይሆናሉ? የክርስቲያኖች አምላክ በጣም ደካማ ዕቅድ አውጪ እና ዘግይቶ የሚያስብ ነው ምክንያቱም የሰው ልጆችን “ኅጢአት” ይቅር የሚባልበትን መንገድ ለማግኘት በሺዎች የሚቆጠሩ ሚሊዮን ሊሞላ የሚችል ዓመታት ፈጅቶበታል።

ይሄ ሰው እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ እንደሚመስለኝ በሚሊዩን የሞቆጠሩ የተሰው በጎች ጀርባ ያውን ትርጉምንና በመቶዎች የሚቆጠሩ ትንቢታት መሲሁ የሰው ልጆችን ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን ኅጢአት ቀጣት እንደሚናገሩ ትንቢታትን መገንዘብ አልቻለም፡፡ ከመጀመሪያው ጀምሮ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ "ይህም **በፊት** የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ቸሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፤" (ሮሜ 3:25-26) ከፍያን የሚያካትት ነው፡፡

እግዚአብሔር ኅጢአተኞችን ከክርስቶስ መምጣትም ሆነ ከመምጣቱ በፊት የሚድነው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እና አቅርቦት ላይ ባለው እምነት ነው፡፡


በእርግጥ ልዩነት ነበረ፡፡

ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን በፊት የነበሩ አማኞች ኅጢአት ተሸፍኗል፡፡ ኢየሱስ ደሙን አፍስሶ ሞትን ካሸነፈ በኋላ ብቻ ነው የኅጢአተኛ ዕዳ ከመዝገብ ውስጥ ለዘላለም የተሰረዘው፡፡

የእግዚብሔር በግ የሆነው ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ፊት በመሰዊያ ላይ እንሰሳ የሚያቀረብ ሰው እየተፍጨረጨረ ያለ ነጋዴ ከባንክ ብድር ከሚወስድበት መንገድ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ባለጠጋ የሆነ ወዳጅ ለባልንጀራው ዕዳውን ይዋሳል፤ ነጋዴው የተበደረውን ገንዘብ መመለስ ለመክፈል ይስማማል፡፡ እያንዳንዱ ዓመት እያለፈ ሲሄድ ነጋዴው ገንዘቡን መመለስ ሳይችል ይቀርና ዕዳ ውስጥ ይዘፈቃል፡፡ በየዓመቱም ባለጠጋ ጓደኛው ሌላ ቼክ በመፈረም የሚፍጨረጨረውን ሰው ዕዳ ይሸፍናሉ፡፡ ታዲያ እየከሰረ ያለውን ነጋዴ ከኪሳራ እና ከእስር ቤት የሚያደነው ምንድን ነው? ዕዳዎቹ ከባለጠጋው እና ታማኙ ጓደኛው በኩል እየተከፈለ መሆኑ ነው፡፡

ብሉይ ኪዳን የእንስሳት መስዋዕት በጊዜያዊነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው የኅጢአተኛው "የመተማመኛ ቼክ" ነው፡፡ በሰማይ የሚገኘው ስምምነቱን በማክበር እና ሂሳቡን በመዝጋት እንከን የሌለው ታሪክ ያለው መዝገብ ያዥ፣ ነቀፋ የሌለባቸውን እንስሳት የኅጢአት መሸፈኛ አድርጎ ይቀበላል፡፡ ነገር ግን የእንስሳት ደም የተጠራቀመውን የሰው የኅጢአት ዕዳ ሊከፍሉ አይችሉም፡፡ የሚያገለግለውም "ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ **የኃጢአት መታሰቢያ** አለ፤የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና፡፡" (ዕብራውያን 10:3-4)




ኅጢአት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ዷም ብቻ የሚፈታው ከባድ ችግር ነው። የእግዚአብሔር በግ የሆነው ኢየሱስ የመውጣው የሰውን ልጅ የኅጢአት ዕዳ ሊከፍል ነው።

ምን ታስባላቸሁ?

እግዚአብሔር "ጄካማ ዕቅድ አውጪና ዘገምተኛ አሳቢ" ነው? ወይም ነብዩ ዮሐንስ እና ተከታዮቹ የናዝሬቱን ኢየሱስን "ሙሴና ነብያት የተናገሩለት **መሲሁ**" እና "የዓለምን ሐጢአት የሚያስወግድ **የእግዚአብር በግ**"? (ዮሐንስ 1) ብለው ለመጥራት በቂምክንያት አላቸው።

ፈጣሪያችን ምርጡ ዕቅድ አውጪ ነው፤ የኅጢአትን ዕዳ ለመክፈል ሌላ ዕቅድ የለውም። ከእሱ ጊዜ የለሽ ዕቅድ አንጻር ፤ ውድ ልጁ ሁል ጊዜ እና ለዘላለምም የሚከተለውን ነው፦

"ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው **በግ**..." (ራዕይ 13:8)



# 23

# የመጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜ

“**ተስፋ** ደመና ነው፣ **ፍጻሜው** ዝናብ ነው” —የአረብ ተረት

ለበርካታ ሺህ ዘመናት እግዚአብሔር አዳኝ ለመላከ ተሰፋ እንደ ሰጠ ይናገሩ ነበር “ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታቾ የተወለደውን ልጁን ላከ፤” (ገላትያ 4:4)

የእግዚአብሔር ነብያት የተስፋውን ደመና ሰጥተውናል፡፡

የናዝሬቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር የፍጻሜ ዝናብ ነው፡፡

**“በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው** ለእግዚአብሔር ወንጌል… እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡” (ሮሜ 1:2-3)

ቅዱሳት መጻሕፍት ደመና ናቸው፣ መሲሁ ዝናብ ነው፡፡

## በአህያ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት

ጌታ ኢየሱስ ተልዕኮውን ያውቅ ነበር፡፡ ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ነብዩ ዘካርያስ ከመሲሁ መስዋዕታዊ ሞት አሰቀድሞ ስለሚመጣው ስለዚህ ሁኔታ ጽፏል፡፡

> “አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ **…እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል፡፡”** (ዘካርያስ 9:9)

ኢየሱስ ይህንን ትንቢት ፍጽሟል። አራቱም ወንጌላት ይህንን ሁኔታ ይዘግባሉ። የኢየሱስ አይን ምሥክርና ደቀ መዝሙር የሆነው ማቴዎስ እንዲህ ብሏል፦

> “ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥እንዲህም አላቸው፦ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም የታሰረችን **አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ**፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ። ማንም አንዳች ቢላችሁ፦ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል። ለጽዮን ልጅ፦ **እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት** ተብሎ በነቢይ የተነገረው **ይፈጸም ዘንድ** ይህ ሆነ።” (ማቴዎስ 21:1-5)

ስለዚህም ኢየሱስ ለሀገሪቷ ራሱን እንደ ንጉስ አቀረብ ነገር ግን ነብያት እንደተናገሩት አልተቀበሉትም።[207]

ኢየሱስ በአህያ ላይ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ከገባ በኋላ ሰለ ተከተለው ነገር ይዘግባሉ። ወደ ቤተ መቀደሱ በመሄድ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ሕዝቡን ይበዘብዙ የነበሩትን አስወጣ። ለደነገጡት ነጋዴዎች ኢየሱስ እንዲህ አለ “ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው። በመቅደስም ዕውሮችና አንካሶች ወደ እርሱ ቀረቡና ፈወሳቸው።” (ማቴዎስ 21:13-14)

በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት፣ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ተቀምጦ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ንግግር ሕዝቡን አሰተማረ። የሐይማኖት መሪዎች አንድ ነገር ተናግሮ ከሰው ለስማስገደል ሊያታልሉት ሞከሩ፣ ግን አልተሳካላቸውም። ኢየሱስ ጥያቄያቸውን በሰማያዊ ጥበብ ስለ መለሰ ሁሉም ሰው ተገረመ።[208]

ከዚያም ጊዜው ደረሰ።

## ጊዜው ደርሷል።

ኢየሱስ መቼ እንደሚሞት። የት እንደሚሞት ፣ በምን እንደሚሞትና ለምን እንድሚሞት እርግጠኝነት የሚያውቅ ብቸኛ ሰው ነው።

"ኢየሱስም እነዚህን ቃሎች ሁሉ በፈጸመ ጊዜ፥ለደቀ መዛሙርቱ፦ **ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል** አለ።

በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆች የሕዝብም ሽማግሎች ቀያፋ በሚባለው በሊቀ ካህናቱ ግቢ ተሰበሰቡ፥ኢየሱስንም በተንኰል ሊያስይዙት ሊገድሉትም ተማከሩ፤ነገር ግን፦ በሕዝቡ ዘንድ ሁከት እንዳይነሣ በበዓል **አይሁን** አሉ።"
(ማቴዎስ 26:1-5)

ራሳቸውን ማገልገል የሚወዱት የሐይማኖት መሪዎች ተረብሸው ነበር። በበርካታ ጊዜያት ሊይዙት ቢፈልጉም "**ጊዜው ገና ስላልደረሰ** ማንም እጁን አልጫነበትም።" (ዮሐንስ 7:30)

የሚፈልጉትን ክፍተት አገኙ።

ከውጪ ሲታይ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረው በውስጡ ግን ያልሆነው ይሁዳ፣ ወደ ቤተ መቅደስ ካህናት ሄዶ ኢየሱስን በእጃቸው አሳልፎ ሊሰጣቸው ተስማማ። ካህናትም ሠላሳ ስቅል ከፈሉት። ይሄ የክህደት ተግባር በርካታ የብሉይ ኪዳን ትንቢታትን ተፈጻሚ አደረገ።[209]

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "**ሰዓቱ ደርሶአል።**" (ዮሐንስ 12:23) አላቸው።

የእግዚአብሔር በግ የሚሞትበት ጊዜ ደርሶ ነበር።

## የፋሲካ ሳምንት

የኢየሩሳሌም ጠባብ ጎዳናዎች ለዓመታዊው የመሰዋዕት በዓል በተወላጆች እና በእንግዶች ተሞልተው ነበር። የበጎች ጩኸት የኮረማዎች ጩኸት አየሩን ሞልቶት ነበር። ገዢዎች ከነጋዴዎች ጋር ትክክለኛውን በግ በተመለከተ እየተከራከሩ ነበር።

የፋሲካ ሳምንት ነበር'።

ፋሲካ በእግዚአብሔር ከአሥራ አምስት ክፍለ ዘመናት አስቀድሞ የተመሰረተ የሳምንት ርዝመት ያለው በዓል ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር"የግንኙነት ሕዝቡን" ካባርነት እና ሞት በዚያ አሰቀያሚ አያቶቻቸው የበጉን ደም በቤታቸው መቃን ላይ ባደረጉባቸው ምሽት እንዳወጡ የሚያስታውሱበት ሁኔታ ነው። ከእግዚአብሔር አቅጣጫ መሲሁ የፋሲካን ጥልቅ ፍቺ የሚፈጽምበትን ፍቺ በግልጽ የሚያሳይበት የሚጠበቅ ወቅት ነው።

ነገር ግን ካሉም ከጥቂቶቹ በስተቀር የናዝሬቱ ኢየሱስ የመጨረሻው የፋሳካ በግ ሆኖ ደሙን ሊያፈስ እንደሆነና ከሙሴ ዘመን ጀምሮ ከዓመት እስከ ዓመት የሚሰው በጎችን ተምሳሌትን የሚፈጽመበት መሆኑን የሚያውቁ ጥቂቶች ናቸው። በተቃራኒው የሙሴ ተልዕኮ ከሰብዓዊ አሠሪዎች አካላዊ ግዞት ነፃ ሲያወጣቸው፣ የመሲሁ ተልዕኮ ሕዝቡን ከሠይጣን፣ ሳጢአት እና ሞት መንፈሳዊ ግዞት ነጻ ማውጣት ነው።

የሐይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ለመግደል እያሴሩ ነበር። ነገር ግን "በሕዝቡ ዘንድ ሁከት እንዳይነሣ በበዓል አይሁን አሉ።" (ማቴዎስ 26:5) ነገር ግን ኢየሱስ ሊሞት ያቀደው በዚያው የድግስ ሰሞን ነው! የእግዚአብሔር በግ የሚታረደው በፋሲካ በዓል ወቅት ነው።[210] ሁሉ ነገር የሚከናወነው እግዚአብሔር እንዳቀደው ነው።

የሚያስገርመው ነገር የእግዚአብሔርን ዕቅድ የተቃወሙ ሰዎች ለፍጻሜው ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ሠይጣን የሐይማኖት መሪዎች ኢየሱስን እንዲያገለግሉ በማነሳሳት ለጥፋቱ ሁኔታችን እያመቻቸ ነበር! "ነገር ግን እግዚአብሔር **አስቀድሞ ከዘመናት በፊት** ለክብራችን የወሰነውን፥ **ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን።** ከዚቹም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር" (1 ቆሮንቶስ 2:7-8)

## እንጀራው እና ጽዋው

በተቀጠረው ምሽት ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ለፋሲካ ላይኛው ደርብ ላይ በሚገኝ አንድ ቤት ውስጥ ተሰባስበዋል። የበግ ሥጋ ና መራር ዕጽዋት ያለበት ራት ከተካፈሉ በኋላ ጌታ ሕብስቱን አነሳና አመስግኖ፣ ቆርሶ፣ ሰጣቸውና እንዲበሉት "ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።" (ሉቃስ 22:19) ብሎ ሰጣቸው።



**የተቆረሰው ስጋ** ሊመታ እና ሊቀጣ ያለውን የእሱን አካል የሚወክል ነበር።

በመቀጠልም ከእንጆሪ ተጨምቆ የተሰራውን ጽዋ ሰጣቸውና ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው "ጽዋንም አንሥቶ... ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" (ማቴዎስ 26:28)

**ጽዋው** የአዲሱን ኪዳን ተሰፋ ለማስፈጸም የሚፈሰውን የኢየሱስ ደም ይወክላል።

እነዚህ ሁለት ቀላል ተምሳሌቶች የእግዚአብሔር ነብያት ዋነኛ መልዕክቶችን የሚያመለክቱ ናቸው፦ ፈጣሪያችን መከራን ለመቀበል እና ለአዳም ኃጢአተኛ ዘር ደሙን ለማፍሰስ የሰው ስጋ ለብሶ መከራን ይቀበላል በተጨማሪም ለአዳም ሐጢአተኛ ዘር ደሙን ያፈስሳል

ደቀ መዛሙርቱን በበርካታ ወደር በሌላቸው የተስፋ ቃሎች እና እውነቶች[211] ካጽናና በኋላ፣ ኢየሱስ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ጌቴሴማኔ ወደሚል የአትክልት ስፍራ ወሰዳቸው። ወደ መሬትም በመደፋት በከፍተኛ የነፍስ ሐዘን ፣ እንዲህ ሲል ጸለየ "አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህቺ ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።" (ማቴዎስ 26:39)

ኢየሱስ እንዲህ የፈራው "ጽዋ" ምንድን ነው? ሊለማመደው ያለው ያለተለመደው ከአባቱ ጋር መለያየት ፣ ለአንተ እና ለእኔ የሚበለው የተጠራቀመው የሲዖል ስቃይ የኃጢአት መከራ ጽዋ ነው።

ተመሳሳይ ጸሎት ለሶስት ጊዜ ከጸለየ በኋላ ወልድ በፈቃዱ ለአባቱ ፍቃድ ተገዛ፦ ነብዩ ዳዊት እንደተነበየ ው፦ መሲሁ ያልወሰደውን ለማስመለስ ይሞክራል "በዚያን ጊዜ ያልቀማሁትን መለስሁ።" (መዝሙር 69:4)

ኢየሱስ ሙሉ እና የመጨረሻ መስዋዕት ይሆናል።

## መታሰር

ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ተነጋግሮ እንደ ጨረስ በሊቀ ካህናት ፣ በጸሐፍትን በሽማግሌዎቸ የተላኩ ወታደሮች ወደ አትክልት ስፍራው ገቡ። ችቧቸውን፣ ቆመጣቸውን እና ሰይፋቸው ይዘው ወጀብን ያቆመውን፣ አጋንንት ያስወጣውን እና ሙታንን ያስነሳውን ለማሰር መጡ።

> "**ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና**፦ ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው።
>
> የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት።
>
> ኢየሱስ፦ **እኔ ነኝ** አላቸው። ...እንግዲህ፦ **እኔ ነኝ** ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ። ደግሞም፦ ማንን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው።

> እነርሱም፦ የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት።
> ኢየሱስ መልሶ፦ **እኔ ነኝ** አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደ ሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ፤"
> (ዮሐንስ 18:4-8)

እሱን ሊያስሩ ለመጡት ሰዎች ኢየሱስ ራሱን በእግዚአብሔር ስም "እኔ ነኝ"[212] አላቸው። በግልጽም ኢየሱስ ከእነሱ ጋር እንዲሄድ ከተፈለገ ሊሆን የሚችለው ስለመረጠ ብቻ ነው።

ወታደሮቹ በቀረቡ ጊዜ ደቀ መዛሙሩ ጴጥሮስ ሰይፍ አወጣ ፤ ነገር ግን ሊያደርግ የቻለው የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ መቁረጥ ብቻ ነው። ኢየሱስ በርህራሄ የሰውየውን ጆሮ ከፈወሰ በኋላ ለጴጥሮስ እንዲህ አለው፦

> "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ። ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?እንዲህ ከሆነስ፦ **እንደዚህ ሊሆን ይገባል የሚሉ መጻሕፍት እንዴት ይፈጸማሉ?**"
> (ማቴዎስ 26:52-54)

ኢየሱስ በሐይማኖት ስም ዓመጽ ለሚያስነሱ የሚያሰደስት ንጽጽር ይሰጣቸዋል! ምንም እንኳን ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ሊያላግጡበት፣ ሊገርፉት እና ሊገድሉት እንዳሰቡ ቢያውቅም ከጥላቻ እና በቀል ይልቅ ትዕግስት እና በጎነት አሳያቸው።

## በነብያት አስቀድሞ እንደተነገረው

በመቀጠልም ላስሩት ሰዎች ኢየሱስ እንዲህ አላቸው "ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ ወጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ስቀመጥ ሳለሁ አልያዛችሁኝም።"

በመቀጠልም መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን ማብራሪያ ይጨምራል፦

> "ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነ የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ነው አለ።
> በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።

> ኢየሱስን የያዙትም ጸፎችና ሽማግሎች ወደ ተከማቹበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ **ወሰዱት**።"
> (ማቴዎስ 26:55-57)

በነፋስ ላይ እና በወጀቡ ላይ ኃይል ያለው እሱ ራሱን ለመያዝ፣ ለመታስር እና ለመወሰድ አሳልፎ የሚሰጠው ለምድን ነው?

ይህንን ያደረገው ለአባቱ ካለው ፍቅርና መታዘዝ የተነሳ ነው።

ይህንን ያደረገው ከዘላለማዊ ፍርድ እኔን እና አንተን ለማዳን ነው።

ይህንን ያደረገው "የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ" ነው።

ከመቶዎች ዓመታት በፊት ነብዩ ኢሳያስ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር "ለመታረድ እንደሚነዳ **ጠቦት**..." (ኢሳያስ 53:7)

ነብዩ አብርሐም እንዲህ ብሎ ነበር "የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል" (ዘፍጥረት 22:8)

ነብዩ ሙሴም እንዲህ ሲል ጽፏል "ካህኑም አንዱን **ጠቦት** ወስዶ ስለ በደል መሥዋዕት ያቀርበዋል...የኃጢአትን መሥዋዕትና የሚቃጠለውን መሥዋዕት በሚያርዱበት በተቀደሰው ስፍራ **ጠቦቱን ያርደዋል**" (ዘሌዋውያን 14:12-13)

ምጽቱን ቸላ አትበሉት።

በቤተ መቅደሱ ውስጥ በጉን የማረድና የማቃጠል ኃላፊት ያለባቸው ካህናት ኢየሱስን ለማስገደል ያሳሰሩት እነሱው ነበሩ። ነብያት በሙሉ የጻፉትን **ጠቦት** ሊሰው እንደሆነ አላወቁም ነበር።

## በታላላቅ መሪዎች ተፈረደበት

> "ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰዱት፤ የካህናት አለቆችም ሁሉ ሽማግሌዎችም ጻፎችም ተሰበሰቡ።"
> (ማርቆስ 14:53)

የአይሁድ የሐይማኖት መሪዎች ሕገወጥ የምሽት ፍርድ አዘጋጅተው ነበር።

> "የካህናት አለቆችም ሸንጎውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ ምስክር ይፈልጉ ነበር፤ አላገኙምም፤ ብዙዎች በሐሰት ይመሰክሩበት ነበርና፥ ምስክርነታቸው ግን አልተሰማማም።...
>
> ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ፦ አንዳች አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው።

እርሱ ግን ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም።
ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና፦ የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው።
ኢየሱስም፦ **እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ** አለ። ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና፦ ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮችን ምን ያስፈልገናል? ስድቡን ሰማችሁ!”
(ማርቆስ 14:55-56 ፣ 60 -63)

ሊቀ ካህኑ በጣም የተናደደው ፣ ልብሱን የቀደደው እና ኢየሱስን እግዚአብሔርን በመሳደብ የከሰሰው ለምንድን ነው? ይህንን ያደረገው ኢየሱስ ራሱን ሁሉም ነብያት የጻፉለትን መሲህ የሰው ልጅና የእግዚአብሔር ልጅ ሰላደረገ ነው። በተጨማሪም ኢየሱስ ራሱን በእግዚአብሔር የመጠሪያ ስም “እኔ ነኝ” ብሎ ጠራ። በተጨሪም “የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ” ሲል ኢየሱስ ራሱን የምድር ሁሉ ፈራጅ በማድረግ ነብያት ከጻፉት መጽሐፍ ውስጥ እየጠቀሰ ነበረ።[213]
ለዚህ ነው “ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና ፣

ስድቡን ሰማችሁ፤ ምን ይመስላችኋል? አለ። እነርሱም ሁሉ፦
**ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት**።
አንዳንዶችም ይተፉበት ፊቱንም ሸፍነው ይጐስሙትና፦ ትንቢት ተናገር ይሉት ጀመር፤ ሎሌዎችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።” (ማርቆስ 14:63-65)

ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት ነብዩ ኢሳያስ የመሲሁን መከራ የመቀበል ፈቃደኛነት አስቀድሞ ተናገረ “ጀርባዬን ለገራፊዎች ጕንጭጌንም ለጠጕር ነጪዎች ሰጠሁ፥ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም።” (ኢሳያስ 50:6)

## በሐይማኖት መሪዎች ተፈረደበት

ሊነጋጋ ሲልም ካህናትና የሐይማኖት መሪዎች ኢየሱስን የይሁዳ ሮማዊ ሐገረ ገዢ ወደሆነው ወደ ጲንጤናዊው ጲላጦስ ወሰዱት። የሐይማኖት መሪዎች ኢየሱስ በስቅላት እንዲገደል እንዲፈርድላቸው ጠየቁት። በዚህ ወቅት ታሪክ ውስጥ አይሁድ በሮም አገዛዝ ሥር ስለነበሩ ወንጀለኛን በሞት የመቅጣት መብት የላቸውም ነበር።

በፍርድ ሂደቱ ወቅት ጲላጦስ ሦስት ጊዜ“ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም።” አለ፤ ነገር ግን ሕዝቡ በሠይጣን በተቀሰቀስት ካህናቱ ቀስቃሽነት በከፍተኛ ድምጽ “ይሰቀል” ሲል ጮኹ።[214]

ጲላጦስ ለሃይማኖት መሪዎች ተጽዕኖ ተንበርክኮ ኢየሱስን በሮም ሕግ ከባድ የሆነውን ቅጣት ፈረደበት፦ ጭካኔ የተሞላበት አጥንትን የሚያራቁት ግርፋት ከዚያም ስቅላት ፈረደበት።

> “ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ።
>
> በዚያን ጊዜ የገዢው ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ውስጥ ወሰዱት ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ አከማቹ። ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት፤ከእሾህም አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ፣ በቀኝ እጁም መቃ አኖሩ፣ በፊቱም ተንበርክከው፦ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ ዘበቱበት፤ ተፉበትም መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት።
>
> ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፣ ልብሱንም አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት።” (ማቴዎስ 27:26-31)

## የጌታ ተራራ

ስለዚህም የክብር ጌታ ቅዱስ አካሉ የተተለተለ ስጋ ሆኖ ፣ ራሱ የተገመደ የእሾህ አክሊል እና በጀርባው የእንጨት መስቀል ተሸክሞ ከከተማው ወጥቶ አብርሐም ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ትንቢት የተናገረበት ተራራ ላይ እንደተናገረው ሆነ፦

> **“ልጄ ሆይ፣ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው…በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል”**
> (ዘፍጥረት 22:8 ፣14)

ሁሉም ነገሮች ተገጣጠሙ ፦ ሰዎች ፣ ሂደቱ፣ ሰውየው ፣ ቦታው። ሁሉ ነገር ነብያት አሰቀድመው እንደተናገሩት ሆነ።

በዘመናት መካከል የሚካሄድ ልውውጥ ነበር።



# 24

# በሙሉ ተከፍሏል

ስቅላት እጅግ በጣም በጭካኔ የተሞላ መንግስት የሚፈጽመው ታይቶ የማይታወቅ የግድያ መንገድ ነበር። የሮም አገዛዝ ይህንን ቅጣት የሚፈጽመው በጣም አደገኛ በሆነ ወንጀለኛ ላይ ነው።

በስቅላት የሚፈጸም ግድያ፣ እኛ የሰው ልጆች ሊጎበኝ ለመጣው ፈጣሪያችን የመረጥንለት የግድያ መንገድ ነበር።[215]

> "ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ። ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፣[216] በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ።"
>
> (ሉቃስ 23:32-33)

**ተሰቀለ!**

ስቅላት የተዘጋጀው፣ በተቀጪው ላይ እጅግ ከፍተኛ ስቃይና የመጨረሻውን ታላቁን ውርደት ለማከናነብ የታቀደ ነው።

የሠዓሊ ስዕል ወይ ም ፊልም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተነጠልጥሎ የደረሰበትን ውርደት በተገቢው ሁኔታ ሲገልጥ አይቼ አላውቅም ለማየትም አልፈልግም። ለምሳሌ ሠዓሊዎች እና የፊልም ጸሐፊዎች ልብስ ያለብሱታል፣ ነገር ግን ታሪካዊው እውነታ የሮም ወታደሮች የተፈረደባቸውን ወንጀለኞች ዛፉ ላይ ከማስተኛታቸው ወይም በሰዓት ማሰሪያቸው በኩል እና በተረከዛቸው በኩል ችንካር ከመምታታቸው በፊት ልብሳቸውን ገፈፈው እርቃናቸውን ያደርጓቸዋል።

በስቅላት መሞት የሚያሳፍር፣ የሚያሳምም እና ዘገምተኛ ነው።

ኢየሱስ ይህንን ቅጣት ማለትም ስቃዩን እና ውርደቱን በፈቃደኝነት የተሸከመው ለአንተ ለእኔ ለመላው የአዳም ዘር ሲል

ነው። በኢየሱስ ላይ ያረፈው ብርቱ ቅጣት ዓላማው ሳጢአታችን የሚገባውን ብርቱ ቅጣት ለማስረዳት ነው።

ሮማውያን ስቅላትን መፈጠራቸው ከበርካታ ክፍለ ዘመናት በፊት ነብዩ ዳዊት የመሲሁን የመስቀል ላይ ቅጣት እንዲህ ገልጦት ነበር ፦

> "ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፋተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ **እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ**። አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ። በእግዚአብሔር ተማመነ፥ እርሱንም ያድነው፤ ቢወድደውስ ያድነው።" (መዝሙር 22:16-18 ፣8)

ነብዩ ኢሳያስ እንዲህ ሲል አስቀድሞ ተናገረ፤

> "ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።" (ኢሳያስ 53:12)

ከወንጌላት በተወሰደው የሚከተለው ክፍል ውስጥ ካነበብናቸው ትንቢታት በመነሳት ምን ያህል ፍጻሜዎችን ማየት ትችላላችሁ።



"ቀራንዮም [ከ2000 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር በአብርሐም ልጅ ምትክ ጥቦት ያቀረበበት ቦታ] ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። ኢየሱስም፦ **አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።** ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት። ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር። መኳንንቱም ደግሞ፦ ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር።

…ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ፦ አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው።

ሁለተኛው ግን መልሶ፦ አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም ብሎ ገሠጸው።

ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው።

ኢየሱስም፦ **እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።**

ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ፥ ጨለማም እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ፥ ፀሐይም ጨለመ…”

(ሉቃስ 23:33-36. 39-45)

## ልውውጥ

በክፍለ ዘመናት መካከል በርካታ ጥፋተኞች የስቀላትን መከራ ተቀብለዋል። በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ከመውደቋ በፊት የሮም ወታደሮች በቀን 500 አይሁድ ይሰቅሉ ነበር።[217] አንዳንድ ወንጀለኞች ከመሞታቸው በፊት ለቀናት ያጣጥሩ ነበር። ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ለአጭር ጊዜ ለሰድስት ሰዓታት ያህል በመስቀል ላይ ተሰቃይቷል። የእሱን መከራ ልዩ ያደረገው ምንድን ነው?

አንድ ጎልቶ የሚታይ ልዩነት ነብያት የኢየሱስን መከራ እና ሞት አሰቀድመው መናገራቸው ነው። ሌላኛው ልዩነት ብዙዎቾቾ በመስቀል ላይ ተጣብቀው ደማቸውን ያፈሰሱ ቢሆንም ኢየሱስ ያፈሰሰው ፍጹም የሆነ ደም ነው። ያነበብናቸው ትረካዎች የኢየሱስን ሞት ፍጹም ሌላ ገጽታ ያሳያሉ።

“ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ፥ **ጨለማም እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ**፥ ፀሐይም ጨለመ፥”

(ሉቃስ 23:44)[218]

ኢየሱስ መሰቀል ላይ የተንጠለጠለው ጠዋት ሦስት ሰዓት ላይ ነው። ከዚያ ሰዓት ጀምሮ እሰከ ዘጠኝ ሰዓት ምድር ሁሉ በጨለማ ተውጣ ነበር። ለምን? በእነዚህ ሦት ሰዓታት ከሰው ዕይታ ተሰውሮ ሰፊ እንድምታ የነበረው ልውውጥ እየተካሄደ ነበር። እግዚአብሔር ሳጢአታችን ለዘላለም ላለማስታመም እየፈታው ነበር።

በእነዚያ ሦስት የመለኮታዊ ጨለማ ሠዓታት የሰማዩ አምላክ

በውዱ ጻድቅ ልጁ ላይ ሳጢአት የሚያስፈልገውን የተጠራቀመ፣ ዘላለማዊ ቅጣት እየጫነበት ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋና ደም የለበሰው ለዚህ ዓላማ ነበር።

> “እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ[የእግዚአብሔርን ቁጣ ሊያበረድ የሚችል በቂ የሐጢአት መሰዋዕት] ነው፤ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።” (1 ዮሐንስ 2:2)

ከሰባት ክፍለ ዘመናት አሰቀድሞ ነብዩ ኢሳያስ ይሄንን ልውውጥ ገልጦት ነበር ፦

> “እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ **እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ**። ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።… እግዚአብሔርም በደዌ ያደቀቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል።” (ኢሳያስ 53:5-7 ፤ 10-11)

በመስቀል ላይ በነበረባቸው በእነዚያ ሠዓታት ፕላኔቷ በጨለማ በተዋጠችበት ግዜ ጌታ በፈቃደኛው፣ ሳጢአት የለሹ ልጁ ላይ የሳጢአታችንን ብክለት እና ኩነኔ እያኖረ ነበር። በአባትና በልጅ መካከል የተከናወነውን ነገር መቼም ላንረዳ እንችላለን ነገር ግን ሰለ አንድ ነገር እርግጠኛ ነን፦ በዘመናት መካከል ታላቁ ልውውጥ ነበር።

## ብቻውን!

ድቅድቅ ጭለማ ምድሪቷን ምድርን በሸፈነ ገዜ ፡ “ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም፦ **አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?** ማለት ነው።” (ማቴዎስ 27:46)

ኢየሱስ ይሄን አንጀት የሚያላውስ ጩኸት ከመስቀል ላይ ያሰማው ለምን ነበር? በዚህ ሁኔታ የጮኸው እግዚአብሔር የኃጢአትን ቅጣት እንዲከፍል ስለ ተወው ነው…

ብቻውን

ኢየሱስ በሁሉ ምትክ ከኃጢአት የተነሳ ሦስት ደረጃ ባለው መለያየት ውስጥ አለፈ።

- መንፈሳዊ ሞትን ተለማመደ። የሰማዩ አምላክ በሰው ዘር ኃጢአት የተሞላውን ልጁን ቅዱስ ፊቱን መለሰበት።
- በአካላዊ ሞት ውስጥ አለፈ። ኢየሱስ በሞተ ጊዜ መንፈሱና ነፍሱ አካሉን ጥለው ወጡ።
- ሁለተኛ ሞትን ቀመሰ። ለእኔ እና ለእናንተ የሲዖልን ቅጣት ቀመሰ።

ሲዖል ማለት በእግዚአብሔር የተተወ የጭለማ እና የብቸኝነት ቦታ ነው ፤ መልካም ነገር የማይገኝበት ከሰማዩ አባት መገኘትና ፍቅር የምንለይበት ቦታ ነው። በመስቀል ላይ እያለ በዘላለም ውስጥ ለመጀመሪያ እና ለመጨረሻ ጊዜ ዘላለማዊው ልጅ ከዘላለማዊ አባቱ ተለየ። ኢየሱስ ያንን ዝግናኝ መለያየት እኛ እንዳንቀምሰው ሲል ተቋቋመው።

የእግዚአብሔርቅዱስበግየእኛንኃጢአትተሸካሚምትክሆነ። የኃጢአትን እርግማን ስቃዩን፣ ውርደቱን ፣ እሾሁን እና ምስማሩን ሙሉ ክብደት ተሸከመ። በመሰቀል መሰዊያ ላይ በሰማይና በምድር መካከል ተሰቅሎ ኢየሱስ ሙሉውናየመጨረሻው ለኃጢአት "የሚቃጠል መሰዋዕት" ሆነ።[219]

## ሲዖል ለጥቂት ሰዓታት?

ኢየሱስ የእኛን ሲዖል ወሰደ። እንዴት አንድ ሰው የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ሊከፍል ይችላል? ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ቅጣትን በጥቂት ሰዓታት መከራ ሊወጣ ቻለ?

ይህንን ሊያደርግ የቻለው ከማንነቱ የተነሳ ነው።

እኛ ማድረግ እንድሚገባን ለኃጢአታችን ለዘላለም መክፈል ያላስፈለገው ከማንነቱ የተነሳ ነው። ዘላለማዊ ልጅ እና የእግዚአብሔር ቃል እንደ መሆኑ መጠን ለራሱ ሊከፍለው የሚገባው የኃጢአት ዕዳ የሌለበት ሲሆን በተጨማሪም ደግሞ እንደኛ በጊዜ የተገደበ አይደለም።

በተገደበ ጊዜ ውስጥ "ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ" (ዕብራውያን 2:9) የቻለው ከማንነቱ የተነሳ ነው።

ልክ ጌታ እግዚአብሔር ይህንን ውስብስብ ዓለም ለመፍጠር የተገደበ የጊዜ መጠን (ምንም እንኳን በምርጫው ስድስት ቀን ቢያደርገገውም) እንዳላስፈልገው ሁሉ የሰው ልጅን ለመቤዠትም የተወሰነ ጊዜ መጠን (ምንም እንኳን በምርጫው ስድስት ሰዓት ቢያደርገውም) አላስፈለገውም።

ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ነው።

> "...ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ። ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፣ እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና።" (መዝሙር 90:2 ፣4)

## "ተፈጸመ!"

> "ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ፦ ተጠማሁ አለ። በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት። ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፦ **ተፈጸመ አለ**፤ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።" (ዮሐንስ 19:28-30)

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት ይህንን ብሎ ነበር ፦

"**ተፈጸመ!**"

ይሄ ዐርፍተ ነገር ከአንዲት ቴቴሌስታይ ከምትባል የግሪክ ቃል ጋር የተያያዘ ነው። በሮም የንግድ *ሥራ* ቋንቋ ውስጥ የተለመደ ቃል ነው። የዕዳን ሙሉ በሙሉ መከፈልን ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ጥንታውያን ደረሰኞች ላይ አግድም "ቴቴሌስታይ" የሚል ቃል ተጽፎ ተገኝቷል፤ ትርጉሙም የሚከተለውን ማለት ነው፦

"ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል።"

ቴቴሌስታይ የሚለው ቃል የሥራን ፍጻሜ የሚያሳይ ቃል ነው። ለዚህ ተልዕኮ ወደ ላከው ዘገባ ሲያቀርብ አገልጋይ "ቴቴሌስታይ" ሊል ይችላል ይህም ማለት፦

"ተልዕኮው ተፈጽሟል!"

ሌሎቹ የወንጌል ጸሐፍት "ኢየሱስም **በታላቅ ድምፅ ጮኾ** ነፍሱንም ሰጠ።" (ማርቆስ 15:37) ብለው ዘግበዋል።

የድል ጩኸት ነበር!

የእግዚአብሔርን የመስዋዕት በግ የሚያሳዩ ትንቢታት እና ምልክቶች ተፈጽመዋል።

የሰው ልጅና የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ የእርግማን ምንጭ በሆነው ኅጢአት ላይ ወሳኝ ድል ተቀዳጅቷል። ለተደፈረው ለእግዚአብሔር የረከሰውን እና የተረገመውን የአዳም ዘር ነፃ ለማውጣት የሚያሰከፍለው የቤዛነት ክፍያ ተከፍሏል። የእግዚአብሔር ጻድቅ ባህርይ እና በኅጢአት ላይ ያለው ቁጣ ሙሉ በሙሉ ተመልሷል። ሕጉ ተፈጽሟል።

ተፈጽሟል። ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል። ተልዕኮው ተፈጽሟል

> "ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፥ ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም **በክቡር የክርስቶስ ደም** እንደ **ተዋጃችሁ** ታውቃላችሁ። ከሙታን ባስነሣው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ **ስለ እናንተ** በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ።" (1 ጴጥሮስ 1:18-20)

በዘመናት መካከል ከነቀፋ ነፅ የሆኑ በሚሊዮን የሚጠሩ እንሰሳት ደም ፈስሷል። አሁን ደግሞ ከኢየሱስ ከኅጢአት ነጻ የሆነ ደም ፈስሷል፤ "የከበረው የኢየሱስ ደም" ኅጢአትን ለጊዜው ብቻ የሚሸፍን ሳይሆን ከመዝገብ ላይ ለዘላለም የሚደመስስ ነው። የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ኪዳን የተናገረው ይሄንን ነው።

> "…**አዲስ ቃል** ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር… በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።"
> (ኤርሚያስ 31:31 ፧34)

አዲስ ኪዳን ሲያብራራ "**አዲስ** በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል፤ አሮጌና **ውራጅ** የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል።" (ዕብራውያን 8:13) ተጨማሪ የሐጢአት መሰዋዕት አያስፈልግም። በመሰዊያ ላይ እንስሳት መሰዋት በመሲሁ የመስቀል ላይ ሞት ተሽሯል።

ጌታ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የደም መሰዋዕት (አዳምና ሔዋን ሐጢአት በሰሩ ጊዜ) እንዳደረገ ፣ የመጨረሻውን

ተቀባይነት ያለውን የደም መስዋዕትንም አቅርቧል፡፡

አብርሐም "የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል" (ዘፍጥረት 22:8) ብሎ እንደተነበየው እግዚአብሔር አቅርቧል፡፡ የአብርሐምን ልጅ እንዳላዳነ "ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ" (ሮሜ 8:32) ሰው፡፡

የኢየሱስ የፈሰሰ ደም የኅጢአትና የሞትን ሕግ ያሟላ ሲሆን የመሰዋዕትን ሕግ ደግሞ ፈጽሟል፡፡

"**ተፈጸመ!**" ብሎ በመጮኹ ልንደነቅ አየገባም፡፡

## የተቀደደው መጋረጃ

ኢየሱስ "ተፈጸመ" ካለ በኋላ ምን ተከሰተ?

> "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ፡፡ **የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፡፡**" (ማርቆስ 15:37-38)

አንድ ጥንታዊ ታሪክ አዋቂ የቤተ መቅደስ መጋጃ የመዳፍ ያህል ውፍረት እንዳለውና ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ለማንቀሳቀስ 300 ሰዎች ያስፈልጉት እንደነበር ተናግሯል፡፡[220]

ይሄ ግዙፍ መጋረጃ ለሁለት እንዲቀደድ ያደረገው ምንድን ነው?

ምዕራፍ 21 ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በኋላም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ልዩ መጋረጃ እንዲጠቀሙ አዝዟቸው ነበር፡፡ መሸፈኛው እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ለማየት የሚስቸግር የመገኘቱን ብርሃን ካደረገበት ውስጠኛው መቅደስ ሰዎች እንዳይገቡ ያደርግ ነበር፡፡ ይሄ መሸፈኛ ከሰማይ ወደ ምድር የመጣውን የእግዚአብሔርን የራሱን ልጅ በሚወክሉ በሰማያዊ፣ ሐምራዊ እና ቀይ የተገጠ ነበር፡፡ በተጨማሪም ኅጢአተኞችን ከቅዱስ ፈጣሪያቸው ለመለየት ያገለግል ነበር፡፡ የእግዚአብሔር የጽድቅ መስፈርት የሚያሟሉ ሰዎች ብቻ ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ማደሪያ ይገቡ ነበር፡፡

በዓመት አንድ ጊዜ በመቤዥት ቀን በተለየ ሁኔታ የተቀባው ሊቀ ካህን ከመጋረጃው አልፎ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዲገባ ይፈቀድለት ነበር፡፡ ሊቀ ካህኑ ሳይሞት ወደ እግዚአብሔር መገኘት የሚገባበት ብቸኛው መንገድ የተሰዋ የፍየል ደም (ክርስቶስን የሚፈስ ደም ሚወክል) በገበቴ ከያዘ ብቻ ነው፡፡ ካህኑ ነጭ ላይነን (የክርስቶስን ጽድቅ የሚወክል) መልበስ

ነበረበት። ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ከገባ በኋላ ሊቀ ካህኑ ሰባት (ፍጽምናን ያመለክታል) ጊዜ ደሙን በኪዳኑ ታቦት የጸጋ ዙፋን ላይ ይረጭ ነበር። ታቦቱ ሳጢአተኞች ላይ ሞት የሚፈርደውን የእግዚአብሔርን ሕግ የያዘ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ንጹህ እንስሳ በምትካቸው እንዲሞት በማድረግ በማድረግ ምህረቱን አሳያቸው።

ለአስራ አምስት ክፍለ ዘመናት መሸፈኛው የእግዚብሔርን ፍጹም ቅድስናና ክርስቶስ የፈሰሰ ደም ባሻገር ዘለቄታዊ ቤዛነት እንደሌለ መሰከረ። በመጋረጃው የተወከለው የእግዚአብሔር የመረጠው ሳጢአት የለሹ እሱ ብቻ የሳጢአትን ዋጋ መክፈል ይችላል። ለዚህም ነው በትክክለኛው ጊዜ እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ሕግ በፍጹም እየታዘዘ ፍጹም ሕይወት እንዲኖር እና በፈቃዱ በራሱ ደም ሕግ ተላላፊ የሆነውን የአዳም ዘር ሙሉ ቅጣት እንዲከፍል ልጁን ላከው።

ታዲያ መጋረጃውን ከላይ ወደታች የቀደደው ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። ይሄ ድርጊት እግዚአብሔር ለልጁ "ተፈጸመ!" የሚል ንግግር እግዚአብሔር "አሜን!" ማለቱን የሚያሳይ ነው።[221]

እግዚአብሔር ረካ።

## ከዚህ በኋላ የሳጢአት መሰዋዕት የለም

በኢየሱስ የመስቀል ላይ መስዋዕት ሙሉ መዋጀትት (የሳጢአት ይቅርታ እና ከእግዚብሔር ጋር መታረቅ) ተከናወነ። ፍጹም የሆነው ምትክ ለዓለም ሳጢአት ደሙን አፈሰሰ።

ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሳጢአት በሚቀርብ ዓመታዊ መሰዋዕት ሸክም ስር አይሆንም።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እና ካህናት አያስፈልጉትም።

ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሰዋዕት ቀረቧል። ከጥላውና ከተምሳሌቱ ጀርባ ያለው "ተፈጸመ!" ሲል ተናግሯል።

ለሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ ይላል፦

> "ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል። የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም። እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት **በሥጋው**

**በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፤**በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፤ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤”
(ዕብራውያን 10:17-22)

## ሞተ

ኢየሱስ በሞተበት ቅጽበት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ መቀደዱ ብቻ ሳይሆን ምድርም ተንቀጠቀጠች የፈራው ሕዝብም ተበተነ።

“የመቶ አለቃም ከእርሱም ጋር ኢየሱስን የሚጠብቁ መናወጡንና የሆነውን ነገር አይተው፦ ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ብለው እጅግ ፈሩ።”
(ማቴዎስ 27:54)

በመጨረሻም መሞቱን ለማረጋገጥ አንድ የሮም ወታደር ኢየሱስን ጉኑ ላይ በጦር ወጋው። መሞቱን በሕክምና ሳይንስ በሚረጋግጥ መልኩ ደምና ውሃ ፈሰሰ። የወታደሩ ተግባር ተጨማሪ ትንቢታት እንዲፈጸሙ አደረገ።[222]

## ተቀበረ

“በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፤ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ፤ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፤ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፤ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ።” (ማቴዎስ 27:57-60)

ነብዩ ኢሳያስ እንደተናገረው የመሲሁ መቃብር “ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፤ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ” (ኢሳያስ 53:9) የእግዚአብሔር ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ተፈጸመ። ቢሆንም እንኳን ደቀ መዛሙርቱ አሁንም ዕቅዱን አልተረዱም። እነሱ ኢየሱስ ምድራዊ አገዛዝን የሚመሰረተው እንደሆነ አምነዋል፣ ሲሞት ባዩት ጊዜ ተሰፋቸውም ከእሱ ጋር አብሮ ሞተ ተዓምር አድራጊው ጌታቸው እና የቅርብ ወዳጃቸው ተገደለ ፤ተቀበረ።

አለቀ ወይም እንደዚያ ብለው አስበው ነበር።

በሚገርም ሁኔታ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በሦስተኛው ቀን የመነሳቱን ትንቢት የረሱት ቢሆንም እነዛ ክፉ የሐይማኖት መሪዎች ግን አልረሱትም።

“በማግሥቱም ከመዘጋጀት በኋላ በሚሆነው ቀን፤ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ተሰበሰቡና፦ **ጌታ ሆይ፤ ያ አሳች በሕይወቱ ገና ሳለ፦ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አለን**። እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም፦ ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ፤ የኋለኛይቱ ስሕተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩ እስከ ሦስተኛ ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት።

ጲላጦስም፦ ጠባቆች አሉአችሁ፤ ሄዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ አላቸው።

እነርሱም ሄደው ከጠባቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ።” (ማቴዎስ 27:62-66)



የኢየሱስን አስከሬን የያዘው ዋሻ የድንጋይ በር ታትሞ ተዘግቶ ነበር። በደንብ የታጠቁ የሮም ወታደሮችም በመቃብሩ አካባቢ ነበሩ። የናዝሬቱ ኢየሱስ ፍጻሜ እንዲህ የሚሆን መስሎ ነበር።

በመቀጠልም እሁድ ማለዳ ደረሰ።



# 25

# ሞት ተሸነፈ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አዳም **“ሞተም”** (ዘፍጥረት 5:5) ይላል፡፡ ምድራዊ ታሪኩም የሚያበቃው እንዲዚሁ ነው፡፡ ከአዳም ዘሮች የተለየ አልነበረም፡፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ አምስተኛ ምዕራፍ

“እናም ሞተ

…እናም ሞተ

…እናም ሞተ

…እናም ሞተ

…እናም ሞተ፡፡”

በኃጢአት የረከሱ ወንዶችና ሴቶች ፍጻሜ እንዲዚህ ነው፡፡ ኖሩ፣ ሞቱ ፣ ተቀበሩ፣ ከትወልዷ ወደ ትወልድ ፣ ከክፍለ ዘመን እስከ ከፍለ ዘመን ታሪኩ እንዲሁ ነው፡፡

የመሲሁ ታሪክ ግን በመቃብር ውስጥ አያበቃም፡፡

## ባዶ መቃብር

“በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ፡፡ እነሆም፤ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ፡፡ መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ፡፡ ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ፡፡ መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፡፡

እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤ **እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤**



የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና፦ ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው። እነሆም፥ ነገርኋችሁ።

በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ። እነሆም፥ ኢየሱስ አገኛቸውና፦ **ደስ ይበላችሁ** አላቸው።

እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ፦ **አትፍሩ**፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው።”

(ማቴዎስ 28:1-10)

ሞት መሲሁን ሊይዘው አልቻም። የራሱ የሆነ ኀጢአት ስለሌለበት እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው። ኢየሱስ የዓለምን ኀጢአት ቅጣት መክፈል ብቻ ሳይሆን ከቅጣቱ በላይ ድል አደረገ። ሞትን ራሱን አሸነፈው!

ሠይጣን እና አጋንንቱ ሳይንቀጠቀጡ አልቀሩም።

የሐይማኖት መሪዎች ታወኩ።

> "ሲሄዱም ሳሉ እነሆ፥ ከጠባቆቹ አንዳንድ ወደ ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ። ከሽማግሎች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው።
>
> ከሽማግሎች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው። እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተውሰረቁት በሉ። ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፥ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሉአቸው።
>
> እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል።" (ማቴዎስ 28: 11-15)

የኢየሱስ ጠላቶች መቃብሩ ባዶ መሆኑን አወቁ። እውነቱን ለመሸፋፈን ተሯሯጡ። የገደሉት ሰው እንደ ተነሳ ማንም ሰው እንዲያውቅ አልፈለጉም!

## ሞት ተሸነፈ

በኤደን ገነት እግዚአብሔር አዳምን የፈጣሪውን አንድ ሕግ ካልታዘዘ "በእርግጥ ሞትን ትሞታለህ" ብሎ አስጠንቅቆት ነበር። ሠይጣንም "ሞትን አትሞትም ብሎ አዳምን እና የሰው ዘርን ወደ ሞትና ጥፋት ጎዳና መርቷል። ለበርታ ሺህ ዓመታት ሞት ወንዶችን ፣ ሴቶችን፣ ሕጻናትን በማይላላው መዳፉ ይዞ ኖሯል። የእግዚአብሔር ልጅ ሞትን ሞገተው ፣ አሸነፈው እና የዘላለም ሕይወትን በር ወለል አድርጎ ከፈተ።

> "ሁሉ **በአዳም እንደሚሞቱ** እንዲሁ ሁሉ **በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና**።" (1 ቆሮንቶስ 15:22)

ትላንትና አንድ አዛውንት ጎረቤቴ "በዚህ ሕይወቴ የምፈራው አንድ ነገር ሞት ነው" አልቺኝ። ለዚህች ሴትዮ በሞት ውስጥ አልፎ ሕያው ስለሆነውና ያንን አሰፈሪ ጠላት ስላሸነፈው ብነግራት ምንኛ ደስ ባለኝ።

> "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ [ኢየሱስ] ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም

ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፤ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።”
(ዕብራውያን 2:14-15 አመት)

እስቲ ኢየሱስ የሞተው ለኀጢአታችን ሞቶ ከሞት አልተነሳም ብላችሁ አስቡ። እንዲህ ቢሆን ኖርሮሞት እስከ አሁን አስፈሪ ይሆን ነበር።

ሞትን በማሸፍ ጌታ ኢየሱስ ኢየሱስ ከሠይጣን እጅግ በጣም ኀያል መሳሪያ እና ከሰው በጣም አስፈሪ ጠላት በላይ መሆኑን አሳየ። ኢየሱስ ሞትን ስላሸነፈ፣ በእሱ የሚታመኑ በዚህኛውና በሚመጣው ሕይወት የሚፈሩት ነገር የላቸውም።

የእግዚአብሔር መልዕክት ቀጥተኛ ነው ፦ ለእናንተ ሲል በመሰቀል ላይ መከራን በተቀበለው ፣ ወደ ሞት በሄደው እና በሦስተኛው ቀን ስለ እናንተ በተናሳው ከታመናችሁ እሱ ከሞት ቀንበር ነፃ አውጥቶ የዘላለም ሕይወት ይሰጣችኋል።

በኀጢአት ለታገተው ዓለም እግዚአብሔር ያለው የምሥራች ይሄ ነው።

“...መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤” (1ቆሮንቶስ 15:3-4)

ለሚያምኑ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ይላል፦

“...እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ። ...አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፤ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።”
(ዮሐንስ 14:19 ፤ ራዕይ 1:17-18)

## ሠይጣን ተሸነፈ

ኢየሱስ ወደ ሞት ክልል በገባ እና በሦስተኛው ቀን በወጣ ጊዜ በጦርነት ቋንቋ ገዢ መሬት ያዘ ይኸውም ሊያጣው የማይችለውን ዕድል አገኘ።

ሠይጣን የተሸነፈ ጠላት ነው። ምንም እንኳን እሱ እና አጋንንቶቹ በጉጉት ቢዋጉም ሊያሸንፉ አልቻሉም።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ኀጢአት በሰሩ ጊዜ በኤደን ገነት ቃል የገባውን ነገር እንዴት እንደፈጸመው አያችሁ? ቀድሞ

እንደ ተነገረው የሴቷ ዘር (ኢየሱስ) በአባቡ ዘር (ሰይጣን) ቆስሎ ነበር ያ ቁስል ራሱ የሰይጣንን ውድቀት አረጋግጧል፡፡

> “ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፤ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና፡፡” (1ዮሐንስ 3:8)

በሞቱ፣ ቀብሩ እና ትንሳዔው ኢየሱስ በሚከተለው መልኩ የተገለጠውን የኅጢአት እርግማን አሸንፏል፦

> “…ነህና፤ ወደ **አፈርም** ትመለሳለህና፡፡” (ዘፍጥረት 3:19)

ለበርካታ ሺህ ዓመታት ሠይጣን የአዳምን ዘሮች ወደ አፈር የሚመልሰውን የመበስበስ ሕግ ላይ አላገጠ፡፡ አሁን ግን ስጋውን ወደ አፈር **የማይለውጠው** አጋጠመው!

ሥጋው በመቃብር ውስጥ ያልበሰበሰው ለምንድን ነው?

ሞት ኅጢአት በሌለበት በእሱ ላይ ስልጣን የለውም ነበር፡፡ ከሺህ ዓመታት በፊት ዳዊት እንዲህ ተናግሯል፦

> “…ቅዱስህንም **መበስበስን** ያይ ዘንድ አትተወውም፡፡” (መዝሙር16:10)

ቅዱሱ ሠይጣንን፣ ኅጢአትን እና ሞትን አሸንፏል፡፡

## ማስረጃ

ስለ ኢየሱስ ከሙታን መነሳት የቀረቡ ማስረጃዎች በርካታ እና አሳማኝ ናቸው፡፡[223]

መቃብሩ ባዶ ነበር፡፡

ሬሳውም አልተገኘም ነበር፡፡

ሴቶቹ የባዶው መቃብር፣ የመልዐኩን የምስራች ለመስማት ፣ ኢየሱስን በአካል ለማየት ፣ ለመንካት እና ከእሱ ጋር ለመነጋገር የመጀመሪያ ምሥክሮች ናቸው፡፡ በወንጌል ውስጥ ያለው መረጃ የተፈጠረ ቢሆን ኖሮ ይህንን መረጃ የጻፉት አራት ወንዶች በሁሉ ነገር የመጀመሪያ የሚለውን ክብር ለሴቶች ይሰጧቸው ነበር?!

ከትንሳዔ በኋላ የኢየሱስን መታየት የሚዘግቡ መዛግብት በርካታ ነበሩ፡፡ ከዚህ በኋላ በመጡት አስርት ዓመታት በመቶዎች የሚቆጠሩ ተዓማኒ ምስክሮች ከተነሳው መሲህ ጋር መመላለሳቸውን እና መነጋገራቸውን መሥክረዋል፡፡

ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን መከራ ሲቀበል እና ሲሞት አይተዋል። ልባቸው ተሰብሮ ነበር። መሲሁ ሊሞት አይችልም የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ስለ ነበራቸው ተስፋቸው ተሟጦ ነበር። ወደ ቤታቸው የተመለሱት ተስፋ ቆርጠው ፈርተው ነበር። በመቀጠልም አንድ ነገር ሆነ። ኢየሱስን በሕይወት አዩት። በድንገትም ኢየሱስ እንደሚሰቀል እና በሦስተኛው ቀን እንደሚነሳ የነገራቸው ነገር ትዝ አላቸው።[224] በመጨረሻም የነብያትን ቃል ተረዱ።

ቀድሞ ሲፈሩ የነበሩት ሰዎች የክርስቶስ ደፋር ምስክሮች ሆኑ።

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ግራ የተጋባው እና የፈራው ጴጥሮስ በተቃዋሚ በተሞላው የኢየሩሳሌም ጎዳና ላይ ያለ ፍርኸት ኢየሱስን ለመግደል ባሴሩት ፊት እንዲህ ሲል ተናገረ፦

> "እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፥ **የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፤ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥** ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን። በስሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው። አሁንም፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁ፤እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል **አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው።** ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።"
>
> (ሐዋርያት 3:14-19አመት)

ለጴጥሮስ እና ለደቀ መዛሙርቱ የዘላለም ሕይወት ለሰጣቸው ለእሱ ሲሉ የሚበዛባቸው መከራ የለም።

የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት (ክርስቲያኖች እየተባሉም ይጠራሉ[225]) ስለ ኢየሱስ በድፍረት ስለ መሰከሩ በርካቶች ተሰድበዋል፣ ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተገድለዋል። ጴጥሮስ ራሱ ተሰዶ ነበር፥ እንደ ታሪክ አዋዎች ከሆነ ደግሞ ተዘቅዝቆ ተሰቅሏል። ነገር ግን ጴጥሮስ እና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት አዳኛቸው እና ጌታቸው ሞትን እና ሲዖልን እንዳሸነፈ ስላወቁ

እንዲህ አይነቱን ስደት በደስታ ይቀበሉ ነበሩ፡፡[226] እግዚአብሔር ይቅርታ፣ ጽድቅ እና የዘላለም ሕይወት እንደሰጣቸው አውቀዋል፡፡ አካላቸው እንደ ሞተ በቅጽበት ዘላለማዊ ነፍሳቸው "በጌታም ዘንድ ማደር" (2ቆሮንቶስ 5:8) እንደሚሆን ስለሚያውቁ ሞት አያስፈራቸውም ነበር፡፡

አሁን ምንም ነገር አያስፈራቸውም፡፡ ከሕይወት ከራሱ የበለጠ ትርጉም ያለው መልዕክት ለዓለም የሚያስተላልፉት አላቸው፡፡

በጥንታዊቷ የአቴንስ ከተማ አንዱ የክርስቶስ ተከታይ ለተጠራጣሪ እና አላጋጭ ብዙ ሕዝብ እንደዚህ ገልጦታል፦

> "እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን **በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ** ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ ቀን ቀጥሮአልና፥ **በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል**፡፡"
>
> (ሐዋርያት 17:30-31)

ማጠቃለያው ቀላል እና ግልጽ ነው፦ ንሰሐ ግቡ! ከእግዚአብሔር የማይቀር ፍርድ ራሴን እድናለሁ ብላችሁ አታስቡ፡፡ በምትኩ ለኃጢአታችሁ ላይ ደም ካፈሰሰው እና ከሞት በተነሳው መሲህ ሙሉ በሙሉ መታመን ይገባችኋል፡፡

## አዎንታዊ ማረጋገጫ

እናንተና እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝና ፈራጅ መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው ? መልሱንኮ አነበብነው፡፡ እግዚአብሔር "**ከሞት በማስነሳት** ለሁሉም ሰው **ማረጋገጫ** ሰጠ፡፡"

ኢየሱስ አንዱ እና ብቸኛው አዳኝ መሆኑን ለማወቅ ምን አይነት ተጨማሪ ማስረጃ ያስፈልጋል? ዘላለማዊ ፍጻሜያችንን ለሌላ ሰው አሳልፈን የምንሰጠው ለምንድን ነው? በሚያሳዝን ሁኔታ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ታሪክ እና መልዕክት የተቃወሙ የሞቱ ሰዎችን ያከብራሉ፡፡ አንድ ሰው የእግዚአብሔር ምርጥ ሞትን ያሸነፈ እና የነብያትን ቃል የፈጸመ እያለ፣ ሞትን ማሸነፍ ያልቻለን የእግዚአብሔርን ቃል የተቃወመ ሰው ላይ እምነቱን የሚያደርገው ለምንድን ነው?

የተፈጸመ ትንቢት ለመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል የማያጠራጥር ማስረጃ ሆኖ እንደቀረበ ሁሉ የኢየሱስ የሦስተኛ ቀን ትንሳኤ፣ እሱ ብቻ ከዘላለም ሞት እንደሚያድን እና የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጥ የማያሻማ ማስረጃ ነው።

## የሰዎች ሁሉ አዳኝ

መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ ነው። የኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ "በሁሉም ቦታ ለሚገኙ ሁሉ" ነው። ይሄ ነገር አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል ምክንያቱም እንዳንዶች ኢየሱስ የመጣው ለአይሁድ ብቻ ነው ይሏችኋል።

ይሄ ደግሞ ከእውነት የራቀ ነው።[227]

ምንም እንኳን የመሲሁ ምድራዊ አገልግሎት በአይሁድ ላይ ያተኮረ ቢሆንም ፣ የመጣበት ምክንያት ለዓለም ሁሉ ድነትን ለማስገኘት ነው። ከሰባት መቶ አመታት በፊት ነብዩ ኢሳያስ እግዚአብሔር ለልጁ የገባውን ቃል አሰቀምጧል፦ "እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል።" (ኢሳያስ 49:6)

ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው የአይሁድ መሪዎች እንደ ንጉሳቸው እንደማይቀበሉት እያወቀ ነው። በተጨማሪም ደግሞ በዚሁ ተቀባይነት ማጣት ውስጥ ለዓለም መዳን የሚያስፈልገውን የኀጢአት ዋጋ ከፍሎ ለዓለም ድነት እንደሚያስገኝ ያውቅ ነበር።

> "በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት **ሁሉ** ግን፥ **በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ** የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" (ዮሐንስ 1:10 -12)

ኢየሱስ የሰዎች ሁሉ አዳኝ ነው ነገር ግን የሚያድነው "በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ" (ይኸም ማለት በእሱ **ማንነት** እና ለሐጢአተኞች **በሰራው ስራ**) "የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" ይሰጣቸዋል።

ወዳጄ እግዚአብሔር ይወድኸል ፣ የልጁን ሕይወት እስከመክፈል ዋጋ ሰጥቶኸል። ነገር ግን እንድታምን አያስገድድህም።

ምርጫውን ለእናንተ ይተዋል።

“**በእርሱ የሚያምን** ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” (ዮሐንስ 3:16አመት)

## ግራ መጋባት የለም

ኢየሱስ ከሞት በተነሳ በዚያው ቀን ግራ ከተጋቡ እና መሲሁ ደሙን ማፍሰሱና እንደገና የመነሳቱ አስፈላጊነት እስካሁን ካልገባቸው ደቀ መዛሙርት ጋር አብሮ እየተጓዘ ያወራ ነበር። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦

“እርሱም፦ **እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ**፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው።

ከሙሴ [ቶራ/ዘፍጥረት]ና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ **ስለ እርሱ** በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።” (ሉቃስ 24:25-27)

በመጨረሻም ግራ መጋባታቸው ተስተካከለ። ይህን ያህል ማስተዋል ያልቻልነው ለምንድን ነው? መሲሁ የመጣው ጊዜያዊ ፖለቲካዊ ጠላቶቸን ለመዋጋት አይደለም፣ ከዚያ የበለጠ ጨካኝ የሆኑ ጠላቶቸን ማለትም ሠይጣን፣ ሳጢአት፣ ሞት ኣና ሲዖል ለማሸነፍ ነበር የመጣው!

በዚያው ቀን ቆየት ብሎ፣ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በላይኛው ደርብ ለሚገኙት ደቀ መዛሙርት ተገለጠ። እሱም በሚስማር የተወጋውን እጁንና እግርን አሳያቸው ፣ አብሯቸው ተመገበ እንዲህም አላቸው፦

“እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ **በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል** ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል። እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።” (ሉቃስ 24:44-48)

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ለአሕዛብ “ስለ እነዚህ ነገሮች” ምስክር እንዲሆኑ ነገራቸው። መልዕክቱ ግልጽ ነበር፦ የሰማይ አምላከ የኀጢአትን ቅጣት ከፍሎ ለእያንዳንዱ ሰው ሞትን አሸንፏል። በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ስንገባ (የአዕምሮ ለውጥ) እና እምነታችንን (የልብ መታመናችንን) በጌታ በኢየሱስ እና በእሱ የመዋጀት ስራ ላይ ስናድርግ እግዚአብሔር ይቅርታን እና የዘላለም ሕይወትን ይሰጠናል።

## የእረፍት ግብዣ

ስለ ሰባተኛው የፍጥረት ቀን ዞር ብላችሁ አስቡ።

በዚያ ቀን እግዚአብሔር ምን አደረገ? አረፈ።

“ተፈጸሙ። እግዚአብሔርም የሠራውን *ሥራ* በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው *ሥራ* ሁሉ ዐረፈ።” (ዘፍጥረት 2:1-2)

በእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ ላይ ምንም ነገር ሊጨመርበት አይገባም። ያለቀ ስራ ነበር። በተመሳሳይ መልኩ በእግዚአብሔር የመዋጀት ስራም ምንም ጭማሪ አያስፈልገውም። “ተፈጸመ!”

እግዚአብሔር ሰላረፈና በስራውም ደስ ስለ ተሰኘ እኔ ንእና እናንተን እንድናርፍ እና ባለቀው የማዳን ስራው ደስ እንድንሰኝ ይጋብዛል። “ወደ **ዕረፍቱ የገባ**፥ እግዚአብሔር **ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና**።” (ዕብራውያን 4:10)

በዓለም ላይ የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ሐይማኖቶች “ምንም ያለቀ ነገር የለም። ይህንን ስሩ። ያንን ስሩ! በደንብ ጣሩ ሲሉ ይጮኻሉ። አየሱስ ደግሞ “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ **እኔም አሳርፋችኋለሁ።**” (ማቴዎስ 11:28)

እግዚአብሔር በሰራላችሁ ስራ እያረፋችሁ እየተደሰታችሁ ነው?

## አርባ ቀናት ከጌታ ጋር

ጌታ ኢየሱስ ከተነሳ በኋላ ከአርባ ቀናት በላይ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አሳለፈ። ሰለ እግዚአብሔርም መንግስት ብዙ አስተማራቸው። እሱን ትኩር ብለው አዩት የተነሳውን አካሉን ነኩ፤ አካሉ አንድ ቀን ሁሉም እውነተኛ አማኞች የሚቀበሉት ዘለቄታዊ፣ በጊዜና በቦታ የማይወሰን የከበረ አካል ነው።

ደቀ መዛሙርቱ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተጓዙ፣ አወሩ፣ በሉ። በቅርቡ ጥሏቸው እንደሚሄድ ነገር ግን አብ በነሱ ውስጥ የሚኖረውን

መንፈስ ቅዱስን ከላይ እንደሚልክላቸው ነገራቸው። የእሱም መንፈስ በዓለም ላይ ለሚገኙ አሕዛብ ሲመሰክሩ እንደሚመራቸው እና እንደሚያበረታቸው፣ በመቀጠልም አንድ ቀን እሱ ኢየሱስ በፍጹም ጽድቅ ለመፍረድ ወደ ምድር እንደሚመለስ ነገራቸው።

ከኢየሱስ ትንሳዔ ከአርባኛው ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ በሚገኘው የቀርሜሎስ ተራራ ላይ አገኛቸው።

ወደ "በአባቴ ቤት" (ዮሐንስ 14:2) መመለሻው ጊዜ ነበር።

## ዐረገ

"ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን፦ ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ። እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት። እርሱም፦ አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ **ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።**

ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው።

እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም፦ የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? **ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።**"

(ሐዋርያት 1: 4-11)

## የሰማይ የድል ክብረ በዓል

ስለዚህም በነብያት እንደ ተነገረው የእግዚአብሔር ልጅ "ወደ ስማይ ዐረገ"[228] ከሰላሳ ዓመታት በፊት የመላዕክትን አምልኮ ሰው ልጅ ማላገጥ የቀየረው እሱ ወደ ቤት ተመለሰ! ነገር ግን የተለየ ነገር ነበረ። ሰውን በመልኩ የፈጠረው እሱ የሰውን መልክ ይዞ ነበር።

ቅዱሳት መጽሐፍት የእግዚአብሔርን ልጅ ወደ ሰማይ መመለስ በተመለከተ ብዙ ዝርዝር ነገር አይናገሩም። ይህንን ግን እናውቃለን ፦ ነገር ግን የከበረ ክስተት ነበር።

የማይቆጠሩ የመላዕክት ሰራዊትና የተዋጁ የአዳም ዘሮች ጌታ በሰማይ በር ሲገባ እስቲ አሰቡት። እንደ እግዚአብሔር ልጅና እንደ ክብር ጌታ ያውቁታል ነገር ግን አሁን የሚያገኙት እንደ ሰው ልጅ እና እንደ ጌታ በግ ነው።

ሰማይ ሁሉ ጸጥ ብሏል።

ድንገት ጸጥታው በሚያስገርም የመለኮት ህብረ ዝማሬ ድምጽ እና የመላዕክት ድምጽ ደፈረሰ ፦ "እናንተ መኳንንቶች፣ በሮችን ክፈቱ፣ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፣ የክብርም ንጉሥ ይግባ።" (መዝሙር 24:7)

በሚያስገመግመው ሰማይ ጭብጨባ በሮቹ በሰፊው ተከፈቱ ጀግናው የእግዚአብሔር የራሱ ልጅ፣ ቃል፣ በጉ፣ በጦርነት የቆሰለው የሰው ልጅ **ኢየሱስ** አሸናፊው ገባ።

በአምልኮ አጀብ ውስጥ እየተራመደ ገባ ወደ አባቱ ዙፋንም ቀረበ። ዘር ሲልም የማይቆጠር የአዳምን የተዋጀ ዘር አየ ከዚያም ተቀምጠ።[229]

ተልዕኮው ተፈጸመ።

ሰራዊቱ ሁሉ በፊቱ ተደፍቶ በአንድ ድምጽ በሚመስል ሁኔታ እንዲህ አለ፦

**"የታረደው በግ... ይገባዋል አሉ።"** (ራዕይ 5:12)

ምን አይነት ክብረ በዓል ይሆን! አስገራሚ ክብረ በዓል ነው። የማያበቃ ክብረ በዓል ነው።

# 26

# ሐይማኖተኛ እና ከእግዚአብሔር የራቀ

እንዲህ የሚለውን አባባል የምታውቁ ይመስለኛል፦ወደ ኋላ ማየት 20/20 ነው። ይሄ 20/20 የሚለው የተወሰደው ከሰሜን አሜሪካ የዐይን ሐኪሞች የትክክለኛ እይታ መለኪያ ነው።

የኋላ እይታ ማለት ነገርን ከተፈጸመ በኋላ ማየት ማለት ነው። የኋላ እይታ እኛ ወይም አንድ ሰው ሊወስደው የሚገባውን ግን ከረፈደ ያወቀውን ነገር የሚያሳይ ነው። እንዲህ አይነት የኋላ እይታ ብዙ አይረዳንም።

ነገር ግን በበርካታ ዘመናት መካከል በእግዚአብሔር የተገለጠውን መልዕክት መረዳትን በተመለከተ ግን የኋላ እይታ በጣም ጠቃሚ ነው። ብዙ እንቅፋቶችን አልፈን ዋና ዋና ስህተታችን አልፈን እውነትን ከሐሰት መለየት ያስችለናል። ለዚህ ነው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚከተለውን ያላቸው፦

> “የእናንተ ግን **ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ** ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ **ብፁዓን ናቸው**። እውነት እላችኋለሁ፤ ብዙዎች **ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኙተው አላዩም**፤ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኙተው አልሰሙም።” (ማቴዎስ 13:16-17)

ከመሲሁ የመጀሪያ ምጽዓት በኋላ እንደሚኖሩ ሰዎች ፣ታሪክን ወደ ኋላ ዞር ብለን ለማየትና የተጠናቀቀውን የቅዱሳት መጽሐፍት ስብስብና የእግዚአብሔርን ዕቅድ በግልጥ ለማየት በመቻላችን የተባረክ ነን።

ይህንን ሐሳብ በአዕምሯችን ይዘን፣ በተጨማሪም በመጽሐፍ

ቅዱስ ውስጥ ያደረግነውን ጉዞ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ወደ የጅማሬ መጽሐፍ እንመለስ።

## ቃየንን እና አቤልን መለስ ብሎ ማየት

የዘፍጥረት ምዕራፍ አራት በግልጥ እንደሚያስቀምጠው፦ አቤል እና ቃየል የተወለዱት ከኀጢአት ችግር ጋር ነው። ወደ አዋቂነት ባደጉ ጊዜ ሁለቱም እግዚአብሔርን ለማምለክ ሞከሩ ተቀባይነትን ያገኘው የአንዳቸው ብቻ ነው።

> "እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።" (ዘፍጥረት 4:4-5)

በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የኋላ እይታ ኢየሱስ የኀጢአተኞች አዳኝ መሆኑ ይዘን ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ "እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ **ተመለከተ**፤ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን **አልተመለከተም**።" ለምን እንደተባለ መረዳት ቀላል ነው።

የአቤል የታረደ በግ ወደፊት የሚያመለክተው ደሙን ለኀጢአተኞች ወደሚያፈሰው፣ የእግዚአብሔር በግ ወደ ሆነው ኢየሱስ ነው። የቃየን አትክልቶች ግን ምንም የሚያሳዩት ነገር የለም።

አቤል ወደሚፈጸው ወደ ፊት አየ፤ ዛሬ ደግሞ ኢየሱስ በሞቱ እና ትንሳኤው የፈጸመውን ነገር ወደፊት እናያለን።

> "የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ **ያነጻናል**።" (1ዮሐንስ 1:7)

## የሚያድን እምነት

እግዚአብሔር አቤልን ይቅር ያለው ዛሬ ኀጢአተኞችን ይቅር በሚልበት መንገድ ነው። ኀጢአተኛ ጻድቅ አለመሆኑን ሲያምን እና በጌታና በድነቱ ሲያምን ያ ሰው ይቅር ይባላል፤ በተጨማሪም የእግዚአብሔር የጽድቅ ስጦታ ለእሱ ይቆጠርለታል። ይሄ በነቢያት ዘመን ነበር በዚህ ዘመንም ላሉ አማኞች የሚሆነው ይሔው ነው።

ለምሳሌ ቀደመን እንዳወቅነው አብርሃም "አብራምም በእግዚአብሔር **አመነ**፥ **ጽድቅም** ሆኖ ተቈጠረለት።"

(ዘፍጥረት 15:6) አብረሐም "በእግዚአብሔር አመነ" ማለት አብርሐም እግዚአብሔር እውነት ነው ባለው ነገር ታመነ ማለት ነው። አብርሐም የእግዚአብሔርን ቃል አመነ። እምነቱ በእግዚአብሔር ብቻ ነበር።

ልክ እንደ ነብዩ አብርሐም ፣ ንጉስ ዳዊትም በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃለ አመነ። በደስታ በተሞላ ልብም ዳዊት እንዲህ ሲል ጻፈ "መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው። እግዚአብሔር በደልን የማይቈጥርበት በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው።" (መዝሙር 32:1-2 አመት) ዳዊት በተጨማሪም እንዲህ ብሏል "ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።" (መዝሙር 23:6)

ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት እንደ ነበሩ ሰዎች፣ እንደ አቤል፣ አብርሐም እና ዳዊት ያሉ ሰዎች የኀጢአት ዕዳ የተሸፈነው እምነታቸውን በጌታና በዕቅዱ ላይ ስላደረጉ ነው። ነገር ግን ክርስቶስ ሲሞት የኀጢአት ዕዳቸው ለዘላለም ከመዝገብ ላይ ተሰረዘ።

ዛሬ የምንኖረው ከክርስቶስ ዘመን በኋላ ነው። የምስራቹ ኢየሱስ ክርስቶስ በምትካዊ ሞቱ እና ድል አድራጊ ትንሳዔው ያደረገውን ነገር ካመናችሁ፣ ሒሳባችሁን በክርሰቶስ ጽድቅ ሙሉ እና "በጌታ ቤት ለዘላለም" ያላችሁን ቦታ አረጋግጡ።

ይሄ ሁሉና ከዚህ የበለጠም የናንተ ይሆናል።

ማመን ማለት በጌታ ኢየሱስ እና በሰራላችሁ ስራ ላይ ሙሉ እምነታችሁን ማድረግ ማለት ነው። የእምነትን ትርጉም ይበልጥ ለመረዳት ፣ ወደ አንድ ብዙ ወንበር ወዳለበት ክፍል ስትገቡ አስቡ። አንዳንዶቹ በግልጥ እንደሚታየው የተሰበሩ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ አሮጌና ሊሰበሩ የደረሱ ናቸው። አንዳንዶች መልካም ይመስላሉ፥ ነገር ግን ቀረብ ተብለው ሲመረመሩ በርካታ ተሰባሪ ቦታዎች እንዳሏቸውን እንደማትተማመኑባቸው ታያላችሁ። አስተማማኝ የሆነ መቀመጫ የለም ብላችሁ ስታስቡ ጠንካራንና በአግባቡ የተሰራ ወንበር ታያላችሁ። ወደሱ ትሄዱና ትቀመጡበታላችሁ። እምነታችሁን በእሱ ላይ ታደርጋላችሁ። በእርሱ ታርፋላችሁ። ይሄ ነገር እንደሚይዛችሁ እና እንደማይጥላችሁ ትተማመናላችሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በእና ባለቀ ስራው የሚያርፉ ሰዎችን አያሳፍርም።

## ሙት እምነት

የእምነታችን መልምካነት የሚለካው እምነታችንን ባሳረፍንት ነገር ነው። ሁሉ ሰው እምነት አለው ነገር ግን ሁሉ የሚያምንበት ተመሳሳይ አይደለም።

አቤል እምነቱን በእግዚአብሔርና በእሱ የይቅርታ መንገድ እና ጽድቅ ላይ አደረገ።

ቃየል እምነቱን በራሱ ሐሳብና በራሱ ጥረት ላይ አደረገ።

ቃየል እና የእግዚአብሔርን የኅጢአት ምርመራና ውጤት የማይቀበሉ ሰዎች በቴሌቪዥን ያየሁትን እባብ አጫዋች ይመስላሉ። ሰውየው በትልቅ ኮብራ ተነደፈ ሕይወቱን ሊያድን የሚችለውን ፀረ መርዝ መረፌ አልወጋም አለ። የእባቡን መርዝ ለመቋቋም ብርቱ እንደ ሆነ አሰበ።

ይሄ ሰው እምነት ፣ ብርቱ እምነት ከንቱ እምነት አለው። እምነቱን ከሐኪሙ መድሐኒት ይልቅ በራሱ ላይ አደረገ።

ምርጫው ሕይወቱን አስከፈለው።

መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው። እምነታችንን ከእግዚአብሔር ማዳን ይልቅ በራሳችን ጥረት ላይ ማድረግ "በቃየን መንገድ" መሄድና "የጨለማን ጥቁረነት ለዘላለም መጋፈጥ ነው" (ይሁዳ 1:11 ፣13) ሰው በራሱ ጥረት የእግዚአብሔርን ሞገስ ያገኛል የሚለው የቃየን ሐሳብ ከእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ በተቃራኒ የቆመ ነው።

ነገር ግን እስከ ዛሬ ሰዎች "የቃየንን መንገድ" ይከተላሉ፤

## የሰው ሚዛን

አንድ ቀን ሐይማኖተኛ አይሁድ እንዲህ ሲሉ ጠየቁ "እንግዲህ፦ የእግዚአብሔርን *ሥራ* እንድንሠራ ምን **እናድርግ**? አሉት። ኢየሱስ መልሶ፦ ይህ የእግዚአብሔር *ሥራ* እርሱ **በላከው እንድታምኑ** ነው አላቸው።" (ዮሐንስ 6:28-29) ጠያቂዎቹ "*ሥራ*" ፈለጉ። ኢየሱስ በእሱ እንዲያምኑ ነገራቸው።

በእነዚህ አይሁድ የተገለጠው ግራ መጋባት የተስፋፋ ነው።

የእኔ እህትና ባለቤቷ የሚኖሩት በፓፓዎ ኒው ጊኒ ተራራማ አካባቢዎች ነው። በዚያ አካባቢ ያሉ ጥንታውያን ሰዎችን ተጭባጭ በሆነ መንገድ ይረዳሉ፤ በተጨማሪም ስለ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እና የዘላለም ሕይወት መልዕክቱ ያስተምሯቸዋል። ከዚህ በታች የእነሱ ባልደረባ "የእግዚብሔርን ንግግር" (እነ ፓፓዋ ጊኒ መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ነው) ሰማሁ

ከሚል አንድ ሰው ጋር ያረገውን ምልልስ በተመለከተ የጻፌውን ማስታወሻ ይሄውላቸሁ፦


> ኢየሱስ 'የሕይወት እንጀራ' መሆኑን ከሰማሁ በኋላ በህይወቴ ሁሉ ገነት ለመግባት እና በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስ ለመሆን ስጥር ስለ ነበር ቀላል ነበር፤ አሁን ግን አንተ መጣህና ማድረግ የሚገባቸሁ ነገር ማመን ብቻ ነው አልከን?'
>
> ኢየሱስ ያለውን እንዷገና እንዲያዳምጥ አደረግኩ "እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ" (ዮሐንስ 6:35) በመቀጠልም ዮሐንስ 6:29 "ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።" እንዲያነብ አደረግኩ። በተጨማሪም ዮሐንስ 3፡16 "እርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ" አነበበ። እግዚአብሔር እኛን ለማዳን አቅም ስለሚያንሰው የእኛ ድጋፍ ያስፈለገው እንደሆነ ጠየቅኩት።
>
> ሳቅ 'በፍጹም! እግዚአብሔር በፍጹም ድጋፋቸንን አይፈልግም'
>
> 'በመቀጠልም እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ እግዚአብሔር እናንተን ገነት ለማስገባት የእናንተ እርዳታ ያስፈልገዋል።
>
> ሰውየው ራሱን አውዛወዞ በጥልቅ ሐሳብ ውስጥ ሆኖ ሄደ።'

ምንም እንኳን መልዕክቱ ግልጽ ቢሆንም ለብቻቸው የሚኖሩ ቀደምት ነዋሪዎቸ ሆኑ የሰለጠኑ በምኩራብ፣ በቤተ ክርስቲያን እና በመስጊድ የሚገኙ በዓለም ላይ የሚገኙ ሰዎቸ በፍርድ ቀን እግዚአብሔር መልካምና መጥፎ ስራቸውን ሚዛን ላይ አስቀምጦ የሚመዝን ይመስላቸዋል። በትንሹ በመልካም ስራቸው 51% ካመጡ ወደ ገነት እንደሚገቡ ነገር ግን ሚዛኑ በእኩይ ስራ ረገድ 51% ካመጡ ወደ ሲዖል የሚላኩ ይመስላቸዋል።

በሰው ልጅ ምድራዊ ፍርድ ቤት እንኳን መልካም ስራ ክፉ ስራን በልጦ ሲገኝ የሚባል የፍርድ ሂደት የለም። በእግዚአብሔር ሰማያዊ ፍርድ ቤትም የለም።

በደንብ አስቡት።

ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታቸሁ በእናንተ መልካምነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ትፈልጋላቸሁ?



የሚዛን ጽንሰ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለመኖሩ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

## የእግዚአብሔር መለኪያ

እግዚአብሔር ፍጽምናን ይፈልጋል።

የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስጦታ የሚቀበሉ ብቻ ከእሱ ጋር አብረው ይኖራሉ። በፍርድ ቀን ስንጥር የምታክል ኅጢአት ቢኖርባችሁ እንኳን ወደ ገነት አትገቡም።

እግዚአብሔር ፍጹም ጽድቅ ይፈልጋል።

ቀደም ብለን እንዳየነው በቤታችን ውስጥ የሚገኝ የበሰበሰ የአሳማ ሬሳ እንደሚስጠላን ሁሉ ኅጢአታችን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁ ነው። በበሰበሰው ሬሳ ላይ ሽቶ ማርከፍከፍ ብክለቱን እና ሽታውን ያሰወግደዋል፡፡ በፍጹም! ምንም ያህል መጠን ያ ሐይማኖታዊ ሥርዓት በእግዚብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖረን ሊያደርግ አይችልም።

ሻያችን ውስጥ ጠብ ያለን መረዝ እንደማንታገሰው ሁሉ አንዲት ኅጢአትንም እግዚአብሔር ሊታገስ አይችልም። ተጨማሪ ውሃ ወደ ተበከለው ሻይ መጨመር ገዳይነቱን ሊያሰወግደው ይችላል? በፍጹም! የትኛውንም አይነት መልካም ስራ ሊያነጻን ከዘላለማዊ ፍርድ ሊያድነን አይችልም።

የኅጢአት ዕዳችንን ስለማስወገድ ወይም በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ትክክል ስለማድረግ ስንነጋገር ረዳት የለሾች ነን። ነገር ግን ተስፋ የለሾች አይደለንም። በእሱ ንጹህና ፍጹም ሆኖ መገኘት ውስጥ ለዘላለም ለመኖር የሚስፈልገንን ነገር ሁሉ አዘጋጅቷል።

## እምነትና ስራ

የኅጢአትን ሙሉ ቅጣት በከፈለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ ይላል "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።" (ኤፌሶን 2:8-9)

በሰማይም ምንም አይነት መታበይ አይኖርም።

ድነት "በጸጋ" ነው። ድነት "የእግዚአብሔር ስጦታ" ነው። እሱ ለፍትን ልናገኘው የምንችለው፣ ለፍትን የምናገኘው ሜዳለያ ሳይሆን አመስግነን የምንቀበለው ሥጦታ ነው፤ ስለዚህ "ማንም እንዳይመካ"። ነገር ግን ከዚህ በታች እንደምናየው የተጻጻፍኩትን ሰው ይመስል ብዙ የሐይማኖት ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ግራ ሲጋቡ እናያለን፦

> ርሰሰ ጉዳይ: የኢሜይል ምላሽ
>
> በእምነት ውስጥ በጣም አስፈላጊው ነገር በብቸኛው እውነተኛ አምላክ ማመን፣ መልካም ማድረግ፣ መጥፎ ነገሮችን ማሰወገድ ነው። ድነታችን ይሔው ነው።

ከዘላለም ፍርድ መዳን እና ከእግዚአብር ጋር መኖር በእኛ ጥረት ላይ የተመሰረተ ቢሆን ኖሮ ፣ ምን ያህል በጎ ሥራ እንዷ ሰራሁ ወይም ምን ያህል ክፉ እንዳስወገድኩና በገነት የሚገባኝን ቦታ ያገኘሁ መሆኔን እንዴት አውቃለሁ? ስለ ድነታችን በፍጹም እርግጠኛ መሆን አንችልም።

ከሦስት ሚሊኒየም በኋላ ነብዩ ዮናስ እንዲህ ሲል ተናገረ ፦ "ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።" (ዮናስ 2:9አመት)

ስለዚያ እግዚአብሔር ይመስገን!

> "ጸጋው **በእምነት** አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ **ከሥራ አይደለም**።" (ኤፌሶን 2:8-9)

የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ነው፦ ከኅጢአት ቅጣት እንዲያድነን በሰራችን መታመን የእግዚአብሔርን የድነት ስጦታ አለመቀበል ነው።

ታዲያ ኅጢአትን ማስወገድ እና መልካም ስራ ሰፍራው የት ነው? የሚቀጠለው ጥቅስ፦

> “እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን **መልካሙን ሥራ** ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።” (ኤፌሶን 2:10)

ልዩነቱ ግልጽ ነው። እኛ **በ**መልካም ስራ አልዳንነንም። **ለ**መልካም ስራ ግን ድነናል።

> “የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ...**ከዓመፅ ሁሉ** እንዲቤዠን፥ **መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን** ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።” (ቲቶ 2:13-14)

የዚህ መጽሐፍ መግቢያ የሚጀምረው የአንድ መንደር ሽማግሌ ለጓደኛዬ በሰጡት አስተያየት ነው “ለሰራኸው መልካም ስራ ገነት መግባት ይገባኸል...

የእግዚአብሔር ቃል የዚህን ሰውዬ ንግግር ጥልቅ ስህተት ያሳያል።

ማንም ሰው “መልካም ስራው” ላይ ተመስርቶ “ወደ ገነት መግባት ሊገባው” አይችልም። ነገር ግን አስገራሚ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን የዘላለም ሕይወት የተቀበሉ ግን ለእግዚአብሔር ክብር እና ለሌሎች መባረክ ክፋትን ሊያስወግዱ መልካም ስራ ሊሰሩ ይችላሉ።

## ፍሬው ስሩ አይደለም

መልካም ስራ የድነት **መስፈርት** ሆኖ አያውቅም ነገር ግን ሁልጊዜ የድነት **ውጤት** ሊሆን ይገባዋል።

> “እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።” (ዮሐንስ 13:34-35)

ሰዎችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወደደው እና እንደ ተንከባከበው መውደድና መንከባከብ የድነት **መስፈርት** ነው? በፍጹም! ቢሆን ኖሮ ሰዎችን በፍጹምና ሁልጊዜ ወደደው ኢየሱስ ብቻ ስለሆነ የተኛችንም ገነት መግባት አንችልም ነበር።

ሰዎችን መውደድና መንከባከብ የእውነተኛ አማኞች ጠባይ መሆን ይኖርበታል? በትክክል። "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ **ሰዎች ሁሉ** በዚህ ያውቃሉ።"

እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች እምነታቸውን በስራቸው ያሳያሉ።[230]

የድነት ስርን እና የድነት ፍሬን መለየት በጣም አስፈላጊ ነው። አማኞች ጌታን ሰለድ ድነት (ስር) ስጦታው በቅድስና በፍቅር፣ ራስ ወዳድ ባለመሆን እና ራስን በመግዛት (ፍሬ) ምስጋናቸውን መግለጥ አለባቸው።

የእግዚአብሔር ሰዎች የእሱን ሞገስ ለማግኘት ብለው መልካም ስራ አይሰሩም ፣ መልካም ስራ የሚሰሩት የማይገባ ሞገስ ስለ ሰጣቸው ነው።

## ሐሰተኛ ሐይማኖት

ቃየል "ራስህ አድርገው" የተስፕ ሐይማኖት የመጀመሪያው መስራች ነው። በመስዋዕት በግ ደም ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ ይልቅ የራሱን ሐሳብና ጥረት አመጣ። ስለዚህም የቃየል ጸሎት እግዚአብሔር የሚያስቀይምና አስጸያፊ ነበር።

> "ሕግን ከመስማት ጆሮውን የሚመልስ **ጸሎቱ አስጸያፊ ናት**።" (ምሳሌ 28:9)

የእግዚአብሔር ሕግ የፈሰሰ የበግ ደም ወይም ሌላ ተስማሚ የኅጢአት መሰዋዕት ያስፈልገዋል። ቃይን በእግዚአብሔር ፊት የቀረበው እንደ ተጠበቀው ስይሆን "ጸሎቱ [ነበር] አስጸያፊ[ተቀባይነት የሌለው] ናት"። ቃይን ሐይማኖት ነበር ግን ሐሰተኛ ነው። መሰዋዕቱ ተስፋ የተደረገውን መሲህ እና የመስቀል ላይ ሞቱን አላሳየም። በተጨማሪም፦

> "አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።
>
> እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፦ ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ?መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት

> በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።” (ዘፍጥረት 4:4-7)

ጌታ ከቃየን ጋር ተነጋገረ ፣ ለንስሐ ፣ ጽድቅ ካልሆነ ስራው እንዲመለስ እና ለእግዚአብሔር ጻድቅ ዕቅድ እንዲገዛ ጊዜ ሰጥቶት ነበር።

ቃይን ግን ተቆጣ። የራሱን የምታምር የራስ ጥረት ሐይማኖት በደም በተጥለቀለቀ በግ መለወጥ አልፈለፍም። በእግዚአብሔር ስም ፣ ነገሮችን በራሱ መንገድ አደረግ።

ታዲያ ይሄ መንገድ ወዴት እየመራው ነው።

## ጠበኛ ሐይማኖት

> “ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው። በሜዳም ሳሉ **ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥ ገደለውም።**” (ዘፍጥረት 4:8)

ለኅጢአት መሰዋዕት ጠቦት ለመግደል ፍቃደኛ ያልሆነው ቃይን ፣ የራሱን ውንድም ለመግደል ግን አልኮራም ነበር።

ቃየን ወድፊት ለሚመጡሰውን ለሚያንቋሽሹ ፣ ለሚያሳድዱ እና ለሚገድሉ ለራሳቸው ሕግና ባህል ለመገዛት እምቢ የሚሉ ሐይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ተቋማትን ፈጠሩ።

ልክ እንደ ቃየን በርካታ ሐይማኖተኛ ሰዎች እምነታቸን ለመከላከል ጠብን እና ግድያን መሳሪያ አድርገው ይቀመጣሉ። በድርጊታቸው፣ንምያህልበእምነታቸውመተማመንእንደሌላቸው እና ፈጣሪ ባለቤታቸው ነገሮችን እንድሚይስተካከል ያላቸው እምነት አናሳ ነው።

ብዙ የኢሜይል ልውውጥ እናደርግ የነበረ በአሜሪካን ሃገር ይኖር የነበረ ግለሰብ እንዲህ ብሎ ጻፈልኝ፦

> ርሰሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ
>
> ቅዱሱን ነብይ ፊት ለፊቴ የተሳደበ ከሶሣስት ሰከንድ በኋላ ሁለቱንም የፊት ጥርሶቹን ዋጠ። በጣም ደስ ያሰኘኝ ነገር ከዚህ በኋላ ነብዩን በተመለከተ ስድብ ሲናገር እየተኮላተፈ መሆን ሳስብ ደስ አለኝ።
>
> አረማውያን እምነታቸውን መለወጥ ወይም መሞት አለባቸው። አበቃ።

የዚህ ሰው ንግግር እና ድርጊት ጌታ ኢየሱስ ያለው ተቃራኒ ነው “ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው

ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና። ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፤ **ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤** ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፤” (ሉቃስ 6:27-28 አመት)

በተመሳሳይ መልኩም ኢየሱስ ለሰቀሉት ጸለየላቸው “ኢየሱስም፦ **አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።**” (ሉቃስ 23:34)[231]

## ንሰሐ የማይገባ ኅጢአተኛ

ወደ ቃየን ታሪክ ስንመለስ ፣ ወንድሙን ከገደለ በኋላ እግዚአብሔር ለቃየን የተሳሳተ አስተሳሰቡን እና ክፉውን መንገዱን በተመለከተ ንስሐ እንዲገባ ዕድል ሰጠው።

> “እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፦ ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? እርሱም አለ፦ አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?አለውም፦ ምን አደረግህ?
>
> የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል። አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።”
>
> (ዘፍጥረት 4:9-11)[232]

ቃየን ኅጢአቱን በተመለከተ ንሰሐ ለመግባት እና በትህትና በበግ ደም ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እምቢ አለ። “ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፤ ከዔድንም ወደ ምሥራቅ በኖድ ምድር ተቀመጠ።” (ፍጥረት 4:16)

ቃየን ንስሐ አልገባም። ለእግዚአብሔር ከመታዝዘ ይልቅ ፣ የራሱን ሐሳብ መከተሉን ገለጠ። ቃየን አስገራሚ ስልጣኔ መሠረተ ነገር ግን ለፈጣሪ በእውነት ከመገዛት የራቀ ማህበረሰብ ነበር።[233] ልክ እንደ ቃየን የእሱ ዘሮችም ራስ አጥፊ በሆነው ራስን ማዕከል ባደረገ ሕይወት ቀጠሉ።

የዘፍጥረት አራተኛው ምዕራፍ የቃይን ስድስተኛ ትውልድ የሆነውን የላሜቅን ታሪክ ይዘግባል። ላሜቅ ልክ እንደ አባቱ አታላይ ፣ዝሙተኛ ፣ በቀለኛ እና ነፍሰ ገዳይ ነበር። ልጆቹ ሳይንስና ኪነ ጥበብን አጎለበቱ። ስለ በርካታ ነገሮች ብዙ እውቀት ነበራቸው ፣ እግዚአብሔርን ግን አያውቁም ነበር።

ሰዎች ከእግዚአብሔር ድነት ፊታቸውን መመለሳቸው ብቻ አይደለም፣ ከእግዚአብሔራዊው የሕይወት መንገድም ፊታቸውን መልሰው ነበር።

## ንሰሐ የማይገባ የሰው ልጅ

ከቃየን ከዘጠኝ ትውልድ በኋላ ጌታ የሰው ልጅን በተመለከተ ይህንን ግምገማ ሰጠ፦

> "እግዚአብሔርም የሰው ክፉት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም **ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ** እንደ ሆነ አየ።" (ዘፍጥረት 6:5)

በነብዩ ኖህ ዘመን ፣ በምድር ላይ በፈጣሪ ባለቤት መኖር የሚያምነው የእሱ ቤተሰብ ብቻ ነበር። የሰው ልጅ የእግዚብሔርን ፍቃድ በአንገተ ደንዳናነት አላደርግም ማለቱ ዓለም አቀፋዊውን የጥፋት ውሃ አመጣ። በጸጋው እግዚአብሔር ማምለጫ አዘጋጀ የተገኙት ግን ስምንት ሰዎች ብቻ ነበሩ። የኖህ ሚስት እና ልጆቻቸው ሴም ሃምና ያፌት ከሚስቶቻቸው ጋር ብቻ ነበሩ በእግዚአብሔር መልዕክት ያመኑት (ዘፍጥረት 6-8)።

> "ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ስዎቹን ለማዳን መርከብን **በእምነት** አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኰነነ፥ **በእምነትም** የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።" (ዕብራውያን 11:7አመት)

ምንም እንኳን በርካታ ሳይንቲስቶች ዓለም አቀፋዊ [ወይም "ሉላዊ"] የጥፋት ውሃን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘገባ የሚቀልዱበት ቢሆንም[234] ማናቸውም የዛሬው ደረቅ መሬት በውሃ ተሸፍኖ እንደ ነበር እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የውሃ ውስጥ ፍጥረታት በዓለማችን ታላላቅ በረሃዎችና የተራራ ክልሎች መገኘታቸው ማናቸውም አይክዱም። በተጨማሪም፣ ምንም እንኳን ዓለምን በውሃ ዳግመኛ እንደማያጠፋ ቃል የተስፋ ቃል የመስጠቱ ምልክት መሆኑ ላይ ባያላግጡም ፣ ከዝናብ በኋላ ቀስት ደመና እንደሚወጣም አይክዱም።

## ዐመጸኛ እና ግራ የተጋባ

ምንም እንኳን ከጥፋት ውሃ ፍርድ በኋላ በአዲስ ጅማሬ የተባረኩ ቢሆንም በጥቂት ትውልዶች ውስጥ ሰዎች በፈጣሪ ባለቤታቸው ላይ አምጸው የራሳቸውን ሐሳብ መከተል ጀምረው ነበር። ለምሳሌ እግዚአብር ለሰው ልጆች እንዲበታተኑና "ምድርን

ሙሏት" (ዘፍጥረት 1:28፤9:1) አዝዟቸው ነበር። ሰዎች ምን ለማድረግ ወሰኑ? ምርጫቸው የእሱ ተቃራኒ ነበር።

> "ኑ ለእኛ ከተማና **ራሱ** ወደ **ሰማይ የሚደርስ ግንብ** እንሥራ፤ በምድር ላይ ሳንበተንም **ስማችንን እናስጠራው** አሉ።" (ዘፍጥረት 11:4)

የእቅዳቸውን ራስን ማዕከል ያደረገ መሆን እና ዐመጻቸው ልብ በሉ። የእግዚአብሔርን መልካም እና ፍጹም ዕቅድ ከመከተል ይልቅ የራሳቸውን ጥበብ መከተል እና ስማቸውን ማስጠራት ፈለጉ። ይህንንም ለማድረግ ያሰቡት "ሰማይ የሚደርስ ግንብ" በመስራት ሌላ የጥፋት ውሃ ቢመጣ ለመጠበቅ ነበር። በራሳቸው ብርቱ ጥረት ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚያመልጡ የሚመስላቸው በርካታ ሐይማኖተኛ ሰዎች ናቸው።

እግዚአብሔር የሰው ልጅን አንድ ቦታ የመኖር ዕቅድ አሰቀመ። ጌታ እንዲህ ያለው ዕቅድ የሰው ልጅን ወደ ፈጣን ንቅዘት እና ጥፋት የሚመራ መሆኑን አውቋል። ያንን በአዕምሯቸው በመያዝ እስካሁን ድረስ "ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች።" (ዘፍጥረት 11:1)፣ እግዚአብሔር ያረገውን እስቲ እንመልከት።

> እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ፥ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፥ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህንም ለማድረግ ጀመሩ፤ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም። ኑ፥ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።
>
> እግዚአብሔርም ከዚያ በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው፤ ከተማይቱንም መሥራት ተዉ። ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ፥ እግዚአብሔር በዚያ የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና፤ ከዚያም **እግዚአብሔር** በምድር ሁሉ ላይ እነርሱን **በትኖአቸዋል**።" (ዘፍጥረት 11:6-9)

ሕዝቡ እርስ በርሳቸው መግባባት ባለመቻሉ ማማቸውን ሳይጨርሱ በመተው እግዚአብሔር መጀመሪያ እንዳቀደው በዓለም ዙሪያ ተበታተኑ። "ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ"

ባቢሎን ማለት "ግራ መጋባት" ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ዕቅድ ችላ ማለት ወደ ግራ መጋባት ይመራል።


## የብዙኹኑ መሳሳት

ማማውን ለመስራት ሞከሩና በኖህ ዘመን ከነበሩ ሰዎች የምንማረው አንድ ትምህርት፦

ብዙኹኑ ተሳስቷል።

ምንም እንኳን ሳጢአተኞች ሚሊዮኖች የእነሱን ንጽረተ ዓለም ስለተጋሩ ደስ ቢላቸውም እንኳን የእግዚአብሔር ፍርድ በእነሱ ላይ መጥቷል። እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር እና ሰለ መልዕክቱ ያላቸው መረዳት ብዙ ሰዎች ስለሚያምኑት እውነት ነው ብለው ያምናሉ።

በእንግሊዝ አገር የሚኖር አንድ ሰው ይህንን መልዕክት ላከልኝ፦




ፈጣን ዕድገትና ተራ ቁጥር እውነትን ሚያረጋገጡ ቢሆን በኖህ ዘመን የነበሩት የቃየን ዘሮች እና የባቢሎን ሰዎች ራሳቸው ትክክል በሆኑ ነበር። ነገር ግን ተሳስተው ነበር፣ በእርግጥም ተሳሰተው ነበር።

> "በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ **ሰፊ**፥ መንገዱም **ትልቅ** ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ **ብዙዎች** ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ **የጠበበ**፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም **ጥቂቶች** ናቸው።" (ማቴዎስ 7:13-14አመት)

## የእግአብሔር የማይገታ ዕቅድ

ወደ ቤተሰቡ ትረካ ስንመለስ ቃየን አቤልን ከገደለ በኋላ ተከሰተውን ነገር እንመልከት።

> "አዳም ደግሞ ሚስቱን አወቀ፤ ወንድ ልጅንም ወለደች። ስሙንም፦ ቃየን በገደለው **በአቤል ፋንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው**። ለሴት ደግሞ

> ወንድ ልጅ ተወለደለት ስሙንም ሄኖስ አለው፤ በዚያን ጊዜም **በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ**።"
> (ዘፍጥረት 4:25-26)

የእግዚአብሔር ምኞትና ዕቅድ በእሱ የሚታመኑ ሰዎች እንዳይሰናከሉ ነው።

ሴት ማለት "በምትክ የተሾመ" ማለት ነው። ሔዋን እግዚአብሔር "ሌላ ዘር" ቃየን በገደለው በአቤል ምትክ እንደሰጣት ገብቷት ነበር። ተስፋ የተገባው የሴቷ ዘር የሚወደው በሴት ዘር በኩል እንደሆነ አውቃ ነበር። የኢየሱስ እናት የሆነችው ማርያም የሴት ዘር ነበረች። በተጨማሪም እግዚአብሔር ቃል እንደገባው የአብርሐምና የዳዊት ዘር ነበረች።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሊያፈርስ ምንም ያህል ቢፈጠርም ዕቅዱ በጌታ እግዚአብሔር "ከፍጥረት በፊት" መፈጸም የተጀመረ ነው።

ምንም ማንም ሊያስቆመው አይችልም።

## የጌታ ስም

ልክ እንደ አቤል ሴት በእግዚአብሔር እና በመንገዱ አመነ "በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ።" (ዘፍጥረት 4:26) ጠራ። በዘመናት መካከል በዓለም ሕዝቦች መካከል የሚገኙ እንደ ባቢሎን ሰዎች ለራሳቸው ስም ለማግኘት የሚሞክሩ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ እንደ አቤል እና ሴት ደግሞ **በእግዚአብሔር** ስም የሚያምኑና ስሙኑም የሚጠሩ ሰዎች አሉ።

አንዳንድ ወዳጆቼ አምላክ መቶ ስሞች አሉት ይላሉ የሚያውቁት ግን ዘጠና ዘጠኙን ነው። ምናልባት የማይእውት ስም "ጌታ ያድናል' የሚል ይሆን።

ያ ስም የትኛው ነው።

አዎ ኢየሱስ የሚለው ስም ነው።

በስሙ ማለትም በስሙ እና በስራው አለማመን እግዚአብሔር አለመገዛት ማለት ነው።

እስቲ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሐይማኖተኛ እና አመጸኛ አይሁድ የሃገሩ ሰዎች የጸለየውን ጸሎት እናዳምጥ፦

> "ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው። **በእውቀት አይቅኑ** እንጂ **ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ**

> እመሰክርላቸዋለሁና። **የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ** ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ **ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም።** የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና። ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ መጽሐፍ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።”
>
> (ሮሜ 10:1-4 ፤9 ፤ 11-13 [ኢዩኤል 2:32])

## ዋጋ የሌለው ወይስ ዋጋ ያለው

እኔ ለሚሊዩን ዶላር የባንክ ቼክ ልጽፍ ነው ብላችሁ አስቡ። ቼኩ ሕጋዊ ነው፤ ነገር ግን ዋጋ የሌለው ነው። ለምን?

ምክንያቱም ያን ያህል ገንዘብ በባንክ ውስጥ የለኝም!

አሁን በምድር ላይ ለጠጋው ሰው ለእናንተ የሚሊዮን ብር ቼክ ሊጽፍላችሁ ቢፈልግስ?

ችግር የለውም። ሙሉ ዋጋ ያለው ይሆናል።

በእኔ ስሜ የተጻፈውን ቼክ አልቀበልም ያለው ባንክ የባለጠጋውን ሰውዬ ስም የያዘውን ያከብራሉ።

ዓለማችን እግዚአብሔርን በብዙ ስሞች ሊቀርቡ በሚፈልጉ ሰዎች ስም የተሞላች ነች፤ ነገር ግን ቅዱስ አምላክ የሰው ልጅን የኅጢአት እዳ እንዲከፍል በላከው በእሱ ፊት ዋጋ የሌላቸው እና በኅጢአት የረከሱ ስሞች ናቸው።

ልክ በእኔ ስም እንደተጻፈው 1,000,000 ብር ቼክ ባንኩ እንደማያከብረው ሁሉ እግዚአብሔርም **ከኢየሱስ** ስም በስተቀር በሌላ ስም የኅጢአት ይቅርታን እና ሕይወትን አይሰጥም።

> “መዳንም **በሌላ በማንም** የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።” (ሐዋርያት 4:12)

የኅጢአት ዕዳችሁ ከእግዚአብሔር መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ እና በእሱ ጽድቅ ባለጠግነት እንዲከፈል ትፈልጋላችሁ? የኅጢአትን እርግማን አሸንፋችሁ ከፈጣሪያችሁ ለጊዜውም ቢሆን ለዘላለም የቅርብ ግንኙነት መመስረት ትፈልጋላችሁ?

ይህንን ሊያደርግ የሚችል አንድ ስም ብቻ ነው ያለው፡፡

“**የእግዚአብሔር ስም** የሚጠራ ሁሉ ይድናል”
(ኢዮኤል 2:32)

“**በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ** እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት፡፡” (ሐዋርያት 16:31)

ኢየሱስ ክርስቶስ መከራን የተቀበለው፣የሞተው እና የተነሳው የኅጢአት ዕዳችሁን ለመሰረዝ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? የዚያን ጊዜ “ትድናላችሁ”

## ሁለት ሐይማኖቶች ብቻ

ይህንን ጉዞ የጀመርነው ዓለማችን በአሁኑ ሰዓት ከአስር ሺህ በላይ ሐይማኖቶች እንዳላት በመናገር ነው፡፡

እውነቱን ለምናገር ያሉት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡



- ***ራሳችሁን አድኑ*** የሚላችሁ የሰው ልጅ ብቃት ላይ የተመሰረተ አለ፡፡
- **አዳኝ ያስፈልጋችኋል** የሚላችሁ የመለኮት ብቃት ላይ የተመሰረተ አለ፡፡

ራሳችሁን ለማዳን እስከሞከራችሁ ድረስ የትኛውም ሃይማኖትና ስም ሊያድናችሁ ይችላል፡፡ አዳኝ እንደሚስፈልጋችሁ ከተረዳችሁ ግን ፣ አንድ ስም ብቻ ያስፈልጋችኋል፡፡ ያ ስም **ኢየሱስ** ነው፡፡

“**በእርሱ** የሚያምን ሁሉ **በስሙ** የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል፡፡”
(ሐዋርያት 10:43)

# ክፍል ፫
# የጉዞ ማብቂያ

## እርግማኑን መስበር




27 ደረጃ 1 ፦ የእግዚአብሔር ያለፈ ጊዜ መርሐ ግብር

28 ደረጃ 2፦ የእግዚአብሔር የአሁን ፕሮግራም

29 ደረጃ 3፦ የእግዚአብሔር የወደፊት ፕሮግራም

30 የገነት ቅምሻ

መውጪያ ቃል

የግርጌ ማስታወሻዎች

ጉዞውን በተመለተ ማሰላሰል



# 27

# ደረጃ 1 ፦ የእግዚአብሔር ያለፈ ጊዜ መርሐ ግብር

"ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።"
— ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ሉቃስ 23:43)

ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የኮምፒውተሬ ባትሪ ሞቶ ነበር፤ ነገር ግን አሁን በአዲስ ሕይወት ተሞልቷል። የመሞት ሂደቱ ሊቀለበስ የሚችለው እንዴት ነው?

ኤሌክትሪክ ሶኬት ላይ ሰካሁት።

ኮምፒውተርም ይሁን ፣ ሞባይል ስልክ ወይም የእጅ ባትሪ ከእነሱ በበለጠ ኃይል ቻርጅ እስከሚሞሉ ድረስ በተደጋጋሚ ይሞታሉ፤ ማለትም ኃይላቸውን ይጨርሳሉ።

የአዳም ዝርያዎች ልክ እንደሚሞት ባትሪ ያሉ ናቸው። በኃጢአት ምክንያት የመጣብንን እርግማን መቀልበስ በማንችልበት መንገድ መሞት የምንጀምረው በተጸነስንበት ቀን ነው።

ወደ ጉዟችን መጨረሻ ስንገባ የወደፊት ሕይወቱ እየሞተ እንዳለ ባትሪ ተስፋ የሌለ ስለሚመስል ተረንከራታች ስለሆነ ፈረንሳያዊ ግለስብ ታሪክ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ።

## ለ ሚዘሬብል

የ26 ዓመቱን ብሩኖን ያገኘሁት በመጋቢት ወር 1987እ.ኤ.አ ነው።

ከብዙ ዓመታት አስቀድሞ ይሄ ወጣት ልጅ የሕይወትን ትርጉም ማሰላሰል ጀምሮ ነበር። እንደ ካቶሊክ ያሳላፈው ልጅነቱ ወይም ዓለማዊ ደስታ ሊሞላው በማይችለው ሁኔታ ውስጡ ባዶነት ይሰማው ነበር።

እንደ ልጅ ብሩኖ ስለ እግዚአብሔር ያስተማሩት ሰዎች የሚሰብኩትን መኖር የማይችሉ ሰዎች ነበሩ። እንደ ዐመጸኛ አዳጊ ወጣት ፣ ኢፍትሐዊነት የተሞላበትን ዓለም አየ። በ 18 ዓመቱ የብሩኖ የሕይወት ዓላማ በሳምንቱ መጨረሻ ከጓደኞቹ ጋር መገናኘት መጠጣትና መከራውን መርሳት ነበር። የሴት ጓደኛው በመኪና አደጋ ከሞተችበት በኋላ ተስፋ መቁረጡ ተባባሰበት። በእግዚአብሔር ላይ ተቆጣ።

ብሩኖ ወደ ሕንድ ሐገር ለመጓዝ ወሰነ። ምናልባትም ከበርካታ ሐይማኖቶቻቸው ውስጥ የሕይወትን ትርጉም ለማግኘት ፈለገ። ብሩኖ በየብስ ካደረገው አስጨናቂ ጉዞ በኋላ ከሕንድ የተጨናነቁ ከተሞች መካከል አንዷ ደረሰ፤ በዚያም ስፍራ ጽኑ ሐይማኖታዊ ቅንዓት እና ሊገለጥ የማይችል የሰው ልጅ መከራን ተጋፈጠ። በብሩኖ በራሱ አገላለጽ "ሐይማኖት እና እምነት ያላቸው ሰዎች ቢሆኑም ከእኔ በላይ ሰቆቃ ውስጥ ያሉ ሰዎችን አየሁ።"

በሕንድ ሐገር አንድ ዓመት ያህል ካሳለፈ በኋላ፣ ብሩኖ ተጨባጭ እውነት ለማግኘት ከፈለገ ፣ እግዚአብሔር ሊገልጥለት እንደሚገባ አመነ። ስለዚህም ይህንን ቀላል ጸሎት ወደ ፈጣሪው አደረሰ ፣ "ካለህ ፣ ራስህን ግለጥልኝ!"

አንድ ቀን በካላኩታ ጎዳናዎች ላይ እየተመላለሰ ፣ ብሩኖ የመጽሐፍ ቅዱስ ቤት የሚል ምልክት ያለበት ሱቅ አየ። በደመ ነፍስ ወደ ውስጥ ገባና አሰተናጋጁን "በፈረንሳይኛ የተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስ አላችሁ?" ሲል ጠየቀው። አንድ ቅጂ ነበራቸው።

ገዝቶ ማንበብ ጀመረ።

ብዙ ነገሮች አስገረሙት። ለምሳሌ እግዚአብሔር "ከእኔ በቀር **ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ**። ...የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። **አትስገድላቸው**፡ አታምልካቸውምም" (ዘጸአት 20:3-5) በሚልበት የመጀመሪያና ሁለተኛ ትዕዛዛት ተገረመ። ነገር ግን ብሩኖ ዙሪያውን ሲመለከት በርካታ ሰዎች ለጣዖታት የሚሰግዱባቸው ቤተ መቅደሶች ተመለከተ። እሱ ያደገበትን ሐይማኖት፡ ሲያስብም የሚያውቃቸው የሐይማኖት ሰዎች ለማርያም እና ቅዱሳን እየሰገዱ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እያፈረሱ እንደሆነ ተረዳ።

ብሩኖ በሌላ ጥቅስም እኩል ተገረመ ፦ "የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፡ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።" (ኢያሱ 1:8)

ብሩኖ ይፈልገው የነበረው እውነት የሚገኘው በመጽሐፍ

ቅዱስ ውስጥ ብቻ እንደሆነ ሲረዳ ሕንድን ትቶ ወደ ፈረንሳይ ተመለሰ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ከመቀጠል ይልቅ ፣ መደርደሪያው ላይ አድርጎ የሕይወቱን ጣዕም መራር ወዳደረገው እና ልቡን ባዶ ወዳደረገው የሕይወት መንገድ ማለትም ወደ ስራና ጭፈራ ተመለሰ።

አራት ዓመታት አለፉ።

አንድ ቀን ትርጉም ስለሌለው ሕይወቱ አሰበና እግዚአብሔር የተስፋ ቃል የሰጠበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አስታወሰ፦ "እናንተ ትሹኛላችሁ፥ **በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ።**" (ኤርሚያስ 29:13) ብሩኖ "እሺ እግዚአብሔር በሙሉ ልቤ እፈልግሃለሁ ተስፋ የሰጠኸው እውነት መሆኑን እና አለመሆኑን ለማወቅ እፈልጋለሁ።" ሲል ጸለየ።

ራሱን ከአካባቢው ተጽዕኖ ለማራቅ ብሩኖ ሌላ ጉዞ ወደ አፍሪካ ለማድረግ ወሰነ። በየብስ ሲጓዝም መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ ይጸለይ ነበር፤ "እግዚአብሔር ወደ እውነት ምራኝ ከስህተትም ጠብቀኝ" ሰኸራና ካቋረጠ በኋላ ወደ ሰሜን አፍሪካዊቷ ሴኔጋል መጣ። የመጀመሪያ ምሽቱንም እኔና ቤተሰቤ በምንኖርበት ከተማ ውስጥ አሳለፈ።

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ፣ ብሩኖ ከተማዋ ውስጥ በእግሩ መጓዝ ጀመረ። ልክ እንደ ካላኩታ ሁሉ በር ላይ ያለው ምልክት ትኩረቱን ሳበው። ይሄኛው እንዲህ ይላል፦

ኤኩቴዝ !ካር ለትርናሌ ዱኡ አ ፓርሌ!

(አዳምጥ! ጌታ እግዚአብሔር ተናግሯል!)

ብሩኖ ገባ።

የኔ ቢሮ ነበር። ከስራዬ ቀና ብዬ ስመለከት ፣ በጢም የተወረረ ግለሰብ ትንሽ፣ ሰማያዊ ፣ ያረጀ መጽሐፍ ማለትም ከሕንድ ሐገር የገዛውን መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ ይዟል። የመጀመሪያው ጥያቄው እስካሁን ድረስ ይሰማኛል፦

"ምንድን ነህ፣ ካቶሊክ ወይስ ፕሮቴስታንት?"


"እኔ ክርስቲያን ነኝ። የክርስቶስ ተከታይ" ስል መለስኩለት። ብሩኖ በምላሼ ደነገጠ ደስም ተሰኘ፤ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ሲያነብ ካቶሊክ ወይም ፕሮቴስታንት የሚል ነገር ተጠቅሶ አላየም ፤ ነገር ግን የክርስቶስ ተከታይ ክርስቲያን የሚል ነገር ግን አይቷል። በስተኋላ ብሩኖ እንደነገረኝ "እኔ ካቶሊክ ነኝ!" ወይም "እኔ ፕሮቴስታንት ነኝ!" የሚል ነገር ቢሰማ ዘወር ብሎ ይወጣ እንደ ነበር ነገረኝ። ሐይማኖት አድክሞት ነበር። የፈለገው እውነታን ነበር።

በሚቀጥሉት በርካታ ቀናት ብሩኖ በጥያቄ አጣደፈኝ። እኔም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን የእግዜብሔርን ምላሽ አሳየሁት። ከመሄዱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ (ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመሄድ አስቦ ነበር) "መጽሐፍ ቅዱስን እንደገና አንብብና እግዚአብሔር ያደረገልህን ነገር ተመልከት" ስል ሞገትኩት።

ከስድስት ሳምንታት በፊት እኔና ባለቤቴ ብሩኖ አቅራቢያችን በሚገኝ የዓሳ አጥማጆች መንደር ቤት ሊከራይ መሆኑን ያብራራበት ደብዳቤ ደረሰን። ብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን እያነጻጸረ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ አንብቦ ጨርሶ ነበር።

በሁሉም መጽሐፍት ውስጥ ክርስቶስን አይቶ ነበር።

በብሩኖ በራሱ አንደበት "አንድ ቀን ምሽት ብቻዬን ውጪ ነበርኩ ፣ የኢየሱስ የተስፋ ቃል በሳይል ወደ ልቤ መጣ "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ **እኔም አሳርፋችኋለሁ**።" (ማቴዎ ስ11:28) ሕይወቴን ወደ ኋላ ከነውድቀቱ፣ መራርነቱ እና ጸጸቱ ስመለከተው በልቤ ውስጥ ይለኛ ግጭት ተፈጠረ። ክርስቶስን ብከተል ፣ የራሴን ምኞት እና መሻት ለመከተል ነጻ እንደማልሆን ተረድቻለሁ። በመጨረሻም ተሸነፍኩ። እግዚአብሔር አይኔን ከፈተ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው እና ዳግመኛ የተነሳው ለእኔ እንደሆነ አመንኩ። ሰላም ነፍሴን ሞላት። ማልቀስ ጀምሬ ማቆም አልቻልኩም። የሐጢአቴ ከባድ ሸክም ተነስቶልኝ ነበር!" በሩኖ ቀጥሎ "ኢን ሶሜ ጄ ሱኤስ ኔ ዴ ኑቮ!" ("በጥቅሉ ዳግም ተወለድኩ!") አለ።



ብሩኖ ሲፈልገው የነበረውን ነገር አገኘ ፦ ንጹህ ልብ እና ሕሊና ፣ ከፈጣሪው ጋር ግንኙነት እና የዘላለም ሕይወት። በምድር ላይ ለምን እንዳለ እና ወዴት እየሄደ እንደሆነ አሁን ተረዳ።

ፍለጋው አበቃ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ማንም **በክርስቶስ** ቢሆን **አዲስ ፍጥረት ነው**፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ **እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል**።" (2 ቆሮንቶስ 5:17)

ወዲያውኑ የብሩኖ ሕይወት በትንንሽ እና ትልልቅ መንገዶች መለወጥ ጀመረ። ለምሳሌ ከአሥራ አንድ ዓመቱ ጀምሮ ሲጋራ

ያጨስ የነበረ ቢሆንም ፣ እግዚአብሔር ከዚህ አመሉ ነጻ አወጣው። ራስ ወዳድ ፣ ሰካራም እና አስጸያፊ ነገር ያለፈ ሕይወቱ አሳፋሪ ትዝታ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ገባው ፣ ጸሎትም እንደ መተንፈስ ተፈጥሯዊ ሆነለት።

ብሩኖ ጉዞውን ከመቀጠል ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ፣ በክርስቶስ ከሚያምኑ አማኞች ጋር ጊዜ ለማሳለፍ እና እግዚአብሔር ለእሱ ያደረገለትን ነገር ለሌሎች ለመናገር ቀጣዮቹን ስድስት ወራት በሴኔጋል አሳለፈ

ብሩኖ አዲስ ፍጥረት ሆነ።

ምንም እንኳን ብሩኖን ለመጀመሪያ በአካል ካገኘሁት ስድስት ወራት ቢሆነኝም፣ እስካሁን እንገናኛለን። ዛሬ አዲሱ ብሩኖ የሚኖረው በፈረንሳይ ሃገር ሲኖር እሱና ባለቤቱ ጌታን የሚከተሉ ሲሆን አራት ልጆቻቸው በጌታ እውቀትና ባርኮት ያሳድጋሉ።

ታዲያ ይሄ ማለት ከችግር፣ ከትግል እና መከራ ነጻ ነው ማለት ነው? አይደለም ቤተሰቡ የተለያዩ መከራ እና ፈተና ያጋጥመዋል ነገር ግን ብቻቸውን አይደሉም።

ጌታ ራሱ ከእነሱ ጋር ነው።

## የእግዚአብሔር ባለ ሶስት ደረጃ መርሐ ግብር

አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ሊያስብ ይችላል፦ "ቆይ እስቲ። ኢየሱስ ሰይጣንን፣ ሐጢአትን እና ሞትን ስለኛ ካሸነፈ ፣ አማኞችን ጨምርሮብዙ ሰዎች እስካሁን ድረስ በበርካታ መንገዶች በትግል ውስጥ ያሉት ለምንድን ነው? ታዲያ ዓለም በእኩይ እና በብጥብጥ የተሞላው ለምንድን ነው? ነጻ የመውጣት እና የፍጹምነቱስ ዜና የታለ?

የዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚገኘው እግዚአብሔር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በሶስት ደረጃ ጣልቃ ለመግባት ያወጣው ዕቅድ ውስጥ ነው፦

**ደረጃ 1** ፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከኅጢአት **ቅጣት** ነጻ ያወጣል።
**ደረጃ 2** ፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከኅጢአት **ኅይል** ነጻ ያወጣል።
**ደረጃ 3**፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከሀጢአት **መገኘት** ተነጻ ያወጣል።[235]

የሚከተለው የአዲስ ኪዳን ጥቅስ የእግዚአብሔር ባለ ሦስት ደረጃ ዕቅድ ማለትም ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን አሳጥሮ ያቀርብልናል፦

> እግዚአብሔረ "እርሱም ደህን ከሚያህል ሞት **አዳነን** [ደረጃ 1]፥ **ያድነንማል** [ደረጃ 2]...**እንዲያድን** [ደረጃ 3]በእርሱ ተስፋ አድርገናል።" (2ቆሮንቶስ 1:10)

ቀሪው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናደርገው ጉዞ እግዚአብር የስይጣንን ፣ የሐጢአትን እና የሞትን ወጤት ለዘላለም የሚያስወግድበትን ባለ ሦስት ደረጃ መርሐ ግብር ላይ ያተኮረ ነው። የጉዟችን የመጨረሻ ክፍል እጅግ በጣም አስደሳችና ስለ መንግስተ ሰማያት ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

## እርግማንን መቀልበስ ፦ ክፍል አንድ

አዳምን ሔዋን ሰይጣንን ባደመጡ ጊዜ ከፈጣሪ ባለቤታቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት አበላሹ በተጨማሪም በዘሮቻቸው ላይ የኅጢአትን እርግማን አመጡ። የመጀመሪያው ፣ ፍጹም ዓለም በድንገት ተለውጦ ሰዎች ከእግዚአብሔር ለመደበቅ የሚፈልጉበት እና በራሳው መንገድ የሚሄዱበት ቦታ ሆነ። ሕይወት ሐዘን እና መከራ፣ በሽታና እክል ፣ ድህነት እና ረሃብ፣ ሐዘንና ብጥብጥ፣ እርጅናና ሞት መገለጫዋ ሆኑ።

ኃጢአት እርግማን አመጣ። ነገር ግን በተቀጠረው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ቃል እንደገባው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ የአዳምን ዘሮች ከሰይጣን፣ ከኃጢአት እና ከሞት ለማዳን የሴቷን ዘር ሆኖ መጣ።

> "ከጥንት ጀምሮ **እግዚአብሔር** በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ **በዚህ ዘመን መጨረሻ** ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ **ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ**፤" (ዕብራውያን 1:1-3)

ጌታ ኢየሱስ በኅጢአት ያልተበከለ ነበር።
በኅጢአት እርግማን ስር ባለው እያንዳንዱ ገጽታ ላይ

ሙሉ ስልጣኑን አሳየ። ከአንደበቱ በወጣ ቃል ወይም በእጁ በመንካት፣ እርኩሳን መናፍስትን አባረረ ፣የማያዩ አይኖችን ከፈተ፣ ለመጻሞችን አነጻ በተጨማሪም ሙታንን አስነሳ። በውሃ ላይ ተራመደ፣ ወጀቡን ዝም አሰኘ እና ለተራቡ እንጀራን አብዛ። ኃጢአትንም ይቅር ብሎ ለተጎዱ ልቦች ሰላምን አመጣ።

በመቀጠልም የመጣበትን ዓላማ ፈጸመ።

መከራን ተቀበለ፣ ሞተ፣ አባቱን ለማክበር፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመፈጸም፣ የሚያምኑበትን ለመቤዠት ተነሳ።

> “**በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤** የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።”
>
> (ገላትያ 3:13-14[ዘዳግም 21:23])

## አሰገራሚ ጸጋ

የእግዚአብሔርን ሕግ ሳያጓድል የፈጸመው ኢየሱስ የመጣው ሕግ ተላላዎቻችን ሊቤዥ ነው “ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን [ፍጹም መታዘዝን ይጠይቃል] ዋጀን።” ኢየሱስ እኛን ከዘላለማዊ ቅጣት ለማዳን ለእኛ የሚገባውን ቅጣት ተቀበለ።

ጌታ በመስቀል ላይ መከራ እየተቀበለ እንኳን ፣ የኃጢአታችን እርግማን ለመቀልበስ ያለውን ዓላማ አሳየ።

ኢየሱስ በሃገር ክህደት፣ ስርቆት እና ግድያ ከተፈረደባቸው ሁለት ወንጀለኞች መካከል ተሰቀለ። በእነዚህ ሁለት ኃጢአተኞች እና በጌታ መካከል የተደረገውን ምልልስ እስቲ እንደገና እናዳምጠው። በመጀመሪያ ሁለቱም ሰዎች ኢየሱስ ላይ አላገጡበት፣ ነገር ግን ጊዜው እየገፋ ሲሄድ አንደኛው ንሰሐ ገባ።

> “ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ፦ አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው።
>
> ሁለተኛው ግን መልሶ፦ አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን?ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም ብሎ ገሠጸው።

> ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፤ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው።
>
> ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።" (ሉቃስ 23: 39-43)

እነዚህ ሁለት ሕግ ተላላፊዎች ሊሞቱና ሲዖል ሊገቡ ተቃርበው ነበር። ነገር ግን በመጨረሻው ሰዓት አንደኛው በእግዚአብሔር ፊት ያደረገውን ኅጢአት ተገነዘበና በመስቀሉ መካከል በሚገኘው ኅጢአት የሌለበት አዳኝ ላይ እምነቱን አደረገ።

ኢየሱስም የተስፋ ቃል ሰጠው፦

"ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው!"

ለዲያብሎስና ለወደቁ መላዕክት በተዘጋጀው ስፍራ ዘላለምን ከማሳለፍ ይልቅ ፣ ይሄ ይቅርታ ተደረገለት ሕግ ተላላፊ በፈጣሪ - ተቤዢው መገኘት ያሳልፈዋል።

ምን አይነት ለውጥ ነው!

በዚያች ቅጽበት የኅጢአትን ቅጣት ሊከፍል ደሙን ሲያፈስ በነበረው በእግዚአብሔር በግ ላይ ባለው እምነት፤ እግዚአብሔር የዚህን ሰው ሐጢአት ከመዝገቡ ላይ ፋቀ፤ የኢየሱስን ጽድቅ እሱ ቆጠረለት በተጨማሪ የእግዚአብሔርን የማዳን ስጦታ የተቀበሉ ሰዎችን ስም ለዘላለም በሚይዘው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስሙን ለዘላለም መዘገበው።

ይሄ ረዳት የሌለው ኅጢአተኛ ፣ የሐጢአት እርግማን ተደምስሶለት ነበር።

## ነፍስ ያጠፉ ሰዎች ይቅር ሊባሉ ይችላሉ?

ከአንድ ጠያቂ የሚከተለው ኢሜይል ደረሰኝ፦

> መልስነት ርዕሰ ጉዳይ የኢሜይል ምላሽ
>
> "ኢየሱስ (ሰ.ዐ.ወ) በእኛ ምትክ ስለ ኀጢአታችን ሞተ" ከሚለው ዐርፍተ ነገር አንጻር "ፍትሕ" የሚለውን ቃል እንዴት እንደምታብራራ ማወቅ እፈልጋለሁ። ይሄ ማለት በሕይወት ዘመኔ በሙሉ ስለ ሰራሁት መጥፎ ነገር ሁሉ ተጠያቂ አልሆንም ማለት ነው? ወደ ፍትሕ ሳይቀርብ ይህንን ዓለም ትቶ ያለፈ ነፍሰ ገዳይ ሰው ኢየሱስ ስ ለኀጢአቱ ስለከፈለ በሚመጣው ሕይወት ነጻ ይሆናል ማለት ነው ... ይሄንን አመለካከት ለመቀበል አቸገራለሁ... ሁላችንንም ወደ ትክክለኛው መንገድ ይምራን !

የኢየሱስ በኃጢአተኞች ምትክ በመስቀል ላይ መሞት ከፍትህ ጋር የሚጣጣም? “ነፍሰ ገዳይ” እንኳን በእግዚአብሔር ይቅር ሊባል ይችላል? የመጨረሻውን ጥያቄ የመጀመሪያ በማድረግ ይቅር ስለተባሉ እና ስለተለወጡ “ነፍሰ ገዳዮች” ጥቂት ምስክርነት በማካተት እንመልስ።

## የሰው ስጋ በል ሰዎች

“የምድር ጌቶች” (Lords of the Eart) በተሰኘው መጽሐፉ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚው እና ሥነ ስብ ባለሙያው ዶን ሪቻርድሰን በኢራን ጃያ ፣ ኢንዶኔዥያ የሚገኙ አሰፈሪ፣ የተራራ ላይ ኗሪዎች የሰው ስጋ በል ስለሆኑት የያሊ ሰዎች ይናገራል። ለክፍለ ዘመናት ልማዳቸው ግርፋት፣ ግድያ እና በእርግጥም በዙሪያቸው በሚገኙ መንደሮች የሚገኙ ጠላት የሚሏቸውን ሰዎች ይበሉ ነበር። በቀል እና ፍርሽት “መደበኛ” የሕይወት ዘያቸው ነው።

ከዚያም ወንጌልን ሰሙ።

ያሊ እና በዙሪያቸው የሚገኙ ነገዶች ሰለ ኃጢአት ይቅርታ በክርስቶች ስለሚገኘው አዲስ ሕይወት የእግዚአብሔር የምሥራች ስምተዋል። ብዙዎቹ አመኑ። የአሰተሳሰብና የአኗኗር መንገዳቸው ተለወጠ። ዳግም እንደ ተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች ፣ የተለመዱ ስለሚሉት ነገር አሁን የተለየ መለኪያ አላቸው። ከዚህ በፊት ይጠሉና ይፈሯቸው የነበሩ ሰዎች ወንድሞቻቸው ሆኑ። ከቀድሞ ጠላቶቻቸው ወደጅነት ለማመቻቸት “የያሊ መንደሮችን የሚያገናኙ የተሻለ ጥራት ያላቸው መንገዶች”[236] ሰሩ።

የእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን በመለወጡ እና “እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፣ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።” (ኤፌሶን 4:32) ሰላስተማራቸው፣ ዛሬ እነዚህ የቀድሞ ገዳዮች ሊጎዷቸው ለሚሞክሩ ሰዎች ቸ ርህራሄ ያሳዩ ነበር

## ተስፋ የቆረጠች ልጃገረድ

ኤማ ያደገችው በአጥባቂ ሙስሊም ቤተስብ በሲንጋፖር ተወላጅ ሆነች። ከቤተሰቦቿ ፍቺ እና ጥሩ ካልነበረው የቤተሰቦቿ ሁኔታ የተነሳ የ16 አያለች እራሷን ለመግደል ወሰነች።

ኤማ አሥር ፎቅ ርዝማኔ ካለው የአፓርትመንታቸው ሕንጻ ሰገነት ላይ ዘልላ ለመሞት ወሰነች። ዕቅዷን ወደተግባር

ለመለወጥ እየተዘጋጀች እያለ ፣ ለማታውቀው አምላክ በቁጣና በተስፋ መቁረጥ "ካለህ በሆነ መንገድ ፣ በሆነ መንገድ አሳየኝ!" በመቀጠልም ወደ አሥረኛ ፎቅ የሚያመራውን ደረጃ ተከትላ አሥረኛ ፎቅ ወደ ሚገኘው ሰገነት አመራች…

ደረጃው ላይ መጽሐፍ ቅዱስ አገኘች።

አንሳችውና ወደ ክፍሏ እየሮጠች ሄደች። መጽሐፍ ቅዱሱ የሚከተለው ቦታ ተከፈተ፦



**"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም።** በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፤ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፤ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፤ ጽዋዬም የተረፈ ነው። **ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፤ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።"** (መዝሙር 23)

ኤማ ይህንን መዝሙር ስታነብ፣ የእግዚአብሔር መገኘት እና ፍቅር አሰደነቃት። ከአጭር ጊዚ በኋላም **"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።"** (ዮሐንስ 10፡11) በሚለው በጌታ ኢየሱ ስላይ እምነቷን አደረገች።

ኤማ ከበጎቹ መካከል አንዷ ሆነች። ከዚያ በኋላ ራሷን መግደል አልፈለገችም። በዚያ ምትክ ደስተኛ ሚስት እና የአምስት ልጆች እናት ሆነች። የሕይወቷ ትኩረትም በክርስቶስ ያገኘችውን የተትረፈረፈ ሕይወት ሌሎች እንዲያገኙ መርዳት ሆነ።

የዚህን ታሪክ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወደ ኤማ በላኩ ጊዜ ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚገልጥ ነገር ጎላ አድርጋ ጨምራበት መልሳ በኢሜይል ላከችልኝ። በዓለም ላይ የሚገኙ ሴቶች አሰገራሚ ውጥረትና ተግዳሮት እየተጋፈጡ ባለበት ዘመን ፣ ኤማ ከጌታ በምታገኘው አሰገራሚ ፍቅር እና እንክብካቤ ዕለታዊ አቅም ታገኛለች።

## ዐመጸኛው ሰው

በመጨረሻም በእግዚአብሔር ስም ሰዎችን የገደለውን የጠርሴሱን ሳውልን እንመልከት፡፡

ሳውል የተወለደው በታናሻ ኢሲያ (በዘመናዊቷ ቱርክ)፣ በክርስቶስ ዘመን ተወለደ፡፡ ሳውል ኢየሱስ መሲሁ እና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አያምንም ነበር፡፡ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከተመለሰ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ ሳውል የኢየሱስን ተከታዮች እንዲያስር፣ እንዲፈርድ እና እንዲገድል በአይሁድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመደበ፡፡ በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች በማሰር፣ በመግረፍ እና በኢየሱስ ያመኑ አይሁድን በመግደል እግዚአብሔርን ያገለገለ ይመስለው ነበር፡፡[237] ጳውሎስ እና አብረውት ያሉ ሰዎች አይሁድ ክርስቲያኖችን ለማሰር ተልዕኮ ሲጓዙ አንድ ቀን የሆነው ይሄ ነበር፡፡

> “ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ፤በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ፦ ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን **ታሳድደኛለህ**? የሚለውን ድምፅ ሰማ፡፡ ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው፡፡
>
> እርሱም፦ አንተ የምታሳድደኝ እኔ **ኢየሱስ** ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው፡፡
>
> እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ፦ ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው፡፡
>
> ጌታም፦ ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው፡፡” (ሐዋርያት 9:3-6)

ሳውል ስለ ኢየሱስ ያለው አመለካከት ተለወጠ፡፡ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተማሪ እንደሆነ ሰው ፣ ኢየሱስ ነብያት ሁሉ የጻፉለት መሲሁ እንደሆነ አመነ፡፡

ከታላቅ ተቃዋሚ ወደ ታላቅ ደጋፊነት ተለወጠ፡፡[238]

ስሙን በስተኋላ ወደ ጳውሎስ(“ትንሽ” ማለት ነው) የቀየረው ሳዖል እንዲህ ሲል መሰከረ፦

> “አስቀድሞ **ተሳዳቢና አሳዳጅ እንገላችም** ምንም ብሆን፥ ይህን አደረገልኝ፤ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን

> ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ፥ የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ካሉ ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ። **ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ**"
>
> (1ጢሞቴዎስ 1:13-15 አመት)

## የክርስቶስ ልዩ መሆን

"ነፍሰ ገዳዮች" ይቅር ሊባሉ እና ሊለወጡ ይችሉ ይሆን?

ለኢራን ሰው በሎች፣ ለሲንጋፖሯ ኤማ እና ለጠርሴሱ ጳውሎስ የሆነው ይሄ ነው። ከኢየሱስ አጠገብ ለተሰቀለው ንስሐ የገባ ሐጢአተኛ የሆነለት ይሄ ነው። እግዚአብሔርን በሚወዱበት ጊዜ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ በእስር ቤትም ከእስር ቤትም ውጪ ላሉ ሳጢአተኞች እየሆነ ያለው ይሄው ነው።

የመጨረሻዎቹን እና "ምርጦቹን" ሳጢአተኞች ልብ መቤዠትና ልባቸውን መለወጥ የክርስቶስ ልዩ ስራ ነው። የእግዚአብሔር ምህረት እና ጸጋ ስራ ይኸው ነው።

እርግጥ ነው ሳጢአት አስከትሎት አለው።

በመስቀል ላይ የነበረው ወንጀለኛ ስለ ወንጀሉ ቅጣትን ተቀብሏል። በዚህ ዓለም እያለ ጌታን በማወቅ ፣ ለእሱ በመኖር እና ሌሎች እሱን እንዲያውቁ በመርዳት የሚገኘውን ሰላምና ደስታ ተለማመደ።

ቢሆንም እንኳን ሳጢአተኛ ይቅር የሚባልበት እና በእግዚብሔር ፊት ጻድቅ የሚሆንበት መንገድ ሁልጊዜ አንድ አይነት ነው፦ ያለበትን በሳጢአት የተሞላ ሁኔታ መረዳት እና በእግዚአብሔር የጽነት አቅርቦት ማመን ነው።

በጌታ በኢየሱስ አለማመን ከኢየሱሰ አጠገብ የተሰቀለው ንስሐ ካልገባው ሳጢአተኛ ጋር አብሮ መጥፋት ነው።

## ምህረት እና ፍትሕ በአንድነት

ከጥቂት ገጾች በፊት የሰማነው ጸሐፊ እንዲህ ሲል ጠየቀ፦ "ኢየሱስ በእኛ ምትክ ሰለ ሐጢአታችን ሞተ" ከሚለው ዐርፍተ ነገር አንጻር "ጽድቅ" የሚለውን ቃል እንዴት ታብራራዋለህ?" አሕመድም ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ጥያቄ አንስቶ ነበር።

ርዕሰ ጉዳይ | የኢሜይል ምላሽ

> እግዚአብሔር ለሰዎች ሊነግራቸው የሚፈልገው ነገር ለመናገር እና ውዱ ልጁን ሳይሰዋና ሳያሰቃይ ኀጢአታቸውን መሰረዝ የሚያስችውን ያህል ታላቅነት የለውም???!

ደጋግመን እንዳየነው፣ እግዚአብሔር በፍትሁ እና ታማኝነቱ ታላቅ ስለሆነ የሰዎችን ኀጢአት በተገቢው ሁኔታ ሳይፈርድ እና ሳይቀጣ "መሰረዝ" አይችልም፡፡

በምዕራፍ 13 ፍትሕን ሳይፈጽም ምህረትን ስለሰጠው ዳኛ የሰጠነውን ምሳሌ ታስትውሳላችሁ? ድርጊቱ የፍርድ ቤቱን በሙሉ ቁጣ እና ሐዘን ቀሰቀሰ፡፡

እግዚአብሔር ልፍስፍስ ዳኛ አይደለም፡፡ ምንም አይነት ነቀፋ በባህርይውና በስሙ ላይ ሊገኝ አይችልም፡፡ ያለፍርድ ምህረትን በፍጹም አይሰጥም፡፡ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሰቀል ከሰማይ ወደ ምድር የላከው ከዚህ የተነሳ ነው፣ ይኼም የእግዚብሔርን ምሕረትና እውነትን በፍጹም ውህደት ያሳየው በዚህ ነው፡፡

> "**ምሕረትና እውነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ፡፡** እውነት ከምድር በቀለች፥ ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች፡፡" (መዝሙር 85:10-11)

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቁጣ ስለኛ ስለ ተሸከመ፣ እግዚአብሔር "ከላይ ተመልክቶ" የይቅርታ፣ የፍጹምነት እና የዘላለም ሕይወት ስጦታውን ሊሰጠን የቻለው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ የእኛን ቦታ በመውሰድ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ጽድቅ፣ ምህረት እና ጸጋ አሳየ፡፡ አስቀድመን እንደተመለከትነው ፦

ፍትህ የሚገባንን መቀበል ነው፡፡
ምህረት የሚገባንን አለመቀበል ነው፡፡
ጸጋ የማይገባንን መቀበል ነው፡፡

በክርስቶሰ የሚያምኑ ሁሉ ማንም የማይገባውን ከኀጢአት መንጻት፣ የክርስቶሰን የራሱን ጽድቅ ፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስፍራ እና የዘላለም ሕይወት ተቀብለዋል፡፡ ጌታን የማይቀበሉ ወይም ቸላ የሚሉ ሁላችንም የሚገባንን ዘላለማዊ ቅጣት ይቀበላሉ፡፡

ክርስቶስ ከመምጣቱ ከሰባት ክፍለ ዘመናት በፊት ፣ ነብዩ ሚኪያስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “የእስራኤልን ፈራጅ ጕንጩን በበትር **ይመታሉ**።” (ሚኪያስ 5:1) አስቡት! የምድር ሁሉ ዳኛ ሊያድናቸው በመጣው አክብሮት በሌላቸው ኅጢተኞች ለመገደል የሰው ሥጋ ለበሰ።

ፍትህ፣ ምህረት እና ጸጋ ከዚህ የተሻሉ ሊሆኑ አይችሉም።

> “**ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና።** ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።” (ሮሜ 5:6-8)

## ጻድቁ አጽዳቂ

በዕቅዱ የመጀመሪያ ደረጃ ፣ የራሱን ፍጹም መሰፈርት ሳይቀንስ ኅጢአተኞችን ይቅር የሚልበትን በር ከፈተ። እሱ “ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን **እንዲያጸድቅ** አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው።” (ሮሜ 3:26) ነው።

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ምክንያቱም ኅጢአትን በበቂ ሁኔታ ቀጥቷል።

እግዚአብሔር በላከው አዳኝ ለሚያምኑ ሁሉ ጻድቅ አድራጊ ነው።

በራሴ ጥረት መደገፍ ባቆምኩበት እና በክርስቶስ እና ለእኔ በሆነው ሞትና በትንሳዔው ላይ መታመኔን ባደረግኩ ቅጽበት ጻድቅ ፈራጁ በጥፋቴ መዝገብ ላይ አግድም የሚከተለውን ጽፏል

ጸ ድ ቋ ል!

መጽደቅ ማለት በእግዚብሔር የፍርድ አሰጣጥ ሂደት ጻድቅ መባል ነው። መዝገቤን ፍቆ እኔን ጻድቅ ያደርገኛል።

ይሄንን የሚደርገው እንዴት ነው?

ይህንን የሚያደርግበት ምክንያት በመስቀል ላይ የሐጢአቴን ቅጣት ስለከፈለ ነው።

አዳም ሐጢአት በሰራ ጊዜ ፣ እግዚብሔር መላውን የሰው ዘር ኅጢአተኛ ብሎታል። ነገር ግን ኢየሱስ ከመሞቱና ከመነሳቱ የተነሳ ፣ እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ጻድቅ ብሏቸዋል።

> “በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች **ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ**፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች **ጻድቃን ይሆናሉ**።” (ሮሜ 5:19)

የአዳም ኅጢአት ርኩሰት እና ሞት እንዳመጣ ሁሉ፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሳዔ መንጻትን እና ሕይወትን አምጥቷል።

> “ሁሉ **በአዳም እንደሚሞቱ** እንዲሁ ሁሉ **በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና**።” (1 ቆሮንቶስ 15:22)

ጻድቅ ፈራጁ ከሰማይ ሲመለከት፣ የሚያያችሁ በአዳም የረከሰ ኅጢአተኛነት ነው? ወይስ እግዚአብሔር የሚያያችሁ በክርስቶስ እና ንጹህ ጽድቁ ነው?

የሰማይ ፍርድ ቤት ሦስተኛ አማራጭ የለውም።

## የሰው እጥፍ ችግር

በዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ ሶስት እንደምናነበው፣ አዳምና ሄዋን ፈጣሪያቸውን ባልታዘዙ ጊዜ በራሳቸው ላይ እጥፍ ችግር ኅጢአትና እፍረት አመጡ።

**ኅጢአት** ወደ መደበቅ መራቸው።

**እፍረት** እርቃናቸውን እንዲሸፍኑ አነሳሳቸው።

እግዚአብሔር በጻድቅነቱ ራሳቸው የሰሩትን የቅጠል ልብስ አልተቀበለውም፣ በምህረቱ ግን ከተሰው እንስሳት ቆዳ የተሰራ ልብስ አለበሳቸው። የእንስሳው ደም ሐጢአታቸውን ለማስወገድ የሚያስፈልገውን ነገር ያሳይ ነበር፣ በተጨማሪም የእንስሳት ቆዳ እፍረታቸውን ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ነገር ይገልጥ ነበር።

እኛ የዘሮቻችንን ኅጢአት እና እፍረት ተካፍለናል። በእግዚአብሔር ፊት የረከስን ሐጢአተኞች እና በመንፈሳዊ ሕይወታችን የተራቆትን ነን። በመገኘቱ ውስጥ ለመኖር በሚያሳፍር ሁኔታ የማንበቃ ነን። **ይቅርታውን** እና **ፍጽምናውን** እንፈልጋለን።

የእኛ እጥፍ ችግር በሁለት ጥያቄዎች ሊጠቃለል ይችላል፦

1. ከፈጣሪያችን የለየንን ኅጢአት **መንጻት** የምንችለው እንዴት ነው?

2. ከእሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር ፍጽምናውን **መልበስ** የምንችለው እንዴት ነው?

## የእግዚአብሔር ሁለት መፍትሄ

ለሰው ኃጢአተኛነት እና የጽድቅ እጦት መፍትሄ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ደሙን ሲያፈስ ፣ **ቅጣታችንን ወሰደ** ፤ በተጨማሪም ሞትን እንዳሸነፈ **የእሱን ጽድቅ** ሰጠን።



“ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ **ማጽደቅም** የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን **ለእኛ ይቈጠርልን** ዘንድ አለው።”
(ሮሜ 4:24-25 አመት)



“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው…እኛ **በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ** እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።”
(2 ቆሮንቶስ 5:17-18 ፣ 21)

በራሳችሁ እና በሐይማኖታችሁ መታመናችሁን በምታቆምበት ቅጽበት እና ተስፋችሁን በክርስቶስ እና ለእናንተ በፈሰሰው ደሙ ተስፋችሁን ስታደርጉ፦

1. ከኃጢአት ርኩሰት ያነጻችኋል በተጨማሪም
2. በፍጹም ጽድቁ ይሸፍናችኋል።

እግዚአብሔር ሌላ መድሐኒት አይሰጣችሁም።

## የእግዚአብሔር የልውውጥ ፕሮግራም

በሞቱና በትንሳዔው ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን ወሰደ እና ጽድቁንም ሰጠን። ይሄ የእግዚአብሔር ታላቅ ልውውጥ ነው፦ **ሐጢአቴን በጽድቁ**።

እንዲህ አይነት ቸር ስጦታን ሰው እምቢ የሚለው ለምንድን ነው?

አሳዛኙ እውነት ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስጦታ አለመቀበልን መረጡ። ነገር ግን ስጦታው አሁንም ቀርቧል፦

የእግዚአብሔርን የድነት ስጦታ የሚቀበሉ ሁሉ ጻድቅ ይባላሉ። አልፈልገውም ያሉ ሁሉ ስለሐጢአታቸው ክፍያ ይፈጽማሉ፣ በሐሳብ ፣ በጊዜያዊ ፐርጋቶሪ ሳይሆን ነገር ግን ለዲያቢሎስ እና ለአጋንንት በተዘጋጀው ዘላለማዊ ሲዖል ውስጥ ነው።

ብዙ የሐይማኖት ሰዎች እንዲህ ሲሉ ድርቅ ይላሉ "እያንዳንዱ ሰው ስለሐጢአቱ መቀጣት አለበት"። የእግዚአብሔርን የይቅርታ እና የጽድቅ ሥጦታ የማይቀበሉ ሰዎች ያንን እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። ምንም እንኳን የኀጢአት ዕዳቸው በፍጹም ሊከፈል አይችልም፣ ምክንያቱም ዘለቄታዊ ዕዳ ነው። ከዚህ በበለጠ ምንም እንኳን ኀጢአተኞች ስለ ሐጢአታቸው በእሳት ባህር ውስጥ ለዘላለም ሰለሐጢአታቸው ቢከፍሉም ፣ በገነት ለመኖር የሚያስፈልውን ጽድቅ በፍጹም ሊያገኙ አያገኙም። እግዚአብሔር ረዳት አልባ ለሆኑ ሐጢአተኞች ከእሱ ጋር ለመኖር የሚያስፈልጉ ይቅርታና ጽድቅ ሊሰጣቸው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

አዳኙ ከመምጣቱ ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት፣ ነብዩ ኢሳያስ ሰለ ታላቁ የእግዚአብሔር ልውውጥ ፕሮግራም ጽፏል፦

> "ሁላችን እንደ **ርኩስ ሰው** ሆነናል፤ **ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው**፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፤ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም **የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፤ የጽድቅንም መጎናጸፊያ ደርቦልኛልና** በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፤ ነፍሴም በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች።" (ኢሳያስ 64:6 ፧ 53:6 ፧ 61:10)

እስካሁን በእግዚአብሔር ፊት የረከሳችሁ ናችሁ? ወይስ በክርስቶስ ደም **ነጽታችኋል**?

የመርገም ጨርቅ የሆነውን የራስ ጽድቅ ለብሳችኋል? ወይስ የክርስቶስን ጽድቅ ንጹህ መጎናጸፊያ **ለብሳችኋል**?

ሁሉ ነገር ወደ አንድ ጥያቄ ያመራል።

> "የሰማነውን ነገር ማን **አምኖአል**? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል?" (ኢሳያስ 53:1)

የእግዚአብሔርን የምሥራች አምናቸኋል? የእሱን እውነት ለመቀበል ስትሉ ሌሎቹን እውነቶች ትታቸኋል?

## **“ታውቁ ዘንድ”**

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፦ “የዘላለም ሕይወት እንዳላቸሁ **ታውቁ ዘንድ** በእግዚአብሔር ልጅ ስም **ለምታምኑ** ይህን ጽፌላቸኋለሁ።” (1ዮሐንስ 5:13)

ከዓመታት በፊት ፣ በጣም ሐይማኖተኛ ከሆነች አንድ ሴቲዮ ስለ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ሥጦታ ተነጋገርኩ። ምንም እንኳን ራሷን ክርስቲያን ብላ ብትጠራም፣ የእግዚአብሔር ሥጦታ በሆነው በክርስቶስ በሚገኘው ድነት እምነቷን በፍጹም አድርጋ አታውቅም።

“በምሞትበት ጊዜ ወደ ገነት እንደምሄድ አውቃለሁ” ብዬ ስነግራት፣ በቁጣ “ኦ በጣም መልካም ሰው ስለሆንክ በቀጥታ ወደ ገነት እገባለሁ ብለህ ታስባለህ አይደል?”

“በፍጹም ! እኔ መልካም ሰለሆንኩ አይደለም። እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ ነው። በእሱ እና እሱ በሰራልን ነገር ካመንን ፣ “የዘላለም ሕይወት እንዳላቸሁ **ታውቃላችሁ**።” ብሎ የነገረን እሱ ራሱ ነው።”

> “የኃጢአት ደመወዝ **ሞት** ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም **ሕይወት** ነው።” (ሮሜ 6:23)

## **አሊ ወደማወቅ እንዴት መጣ**

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን መልዕክት ስላመነ ቤተሰቡ ያባረረው አሊን ጠቅሼው ነበር።

እንደ ብሩኖ አሊን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳገኘው የ26 ዓመት ወጣት ነበር። ነገር ግን ደስታ ፈላጊ ከሆነው ብሩኖ በተለየ ፣ አሊ በቅንነት በተለየ ሁኔታ የዕለት ጸሎቱን ይቀራል፣ ዓመታዊውን የአንድ ወር ርዝመት ያለውን ጾም ይጾማል በተጨማሪም ሌሎችን ሰዎች በአግባቡ በመያዝ ሐይማኖትን ይለማመድ ነበር። በልቡ ውስጥ ግን ዕረፍት የሚነሳ የሠላም እጦት ነበረበት።

አሊ ምሽት በአልጋው ላይ ተኝቶ “ሐይማኖታዊ ሳላፊነቴን ተወጥቻለሁ ፣ ታዲያ ዘላለምን የምፈራው ለምንድን ነው? ጌታ ሆይ ከሞትኩ በኋላ የት እንደምሄድ የማውቅበት መንገድ አለ?” ያስብ ነበር።

አሊ ይህንን ጥያቄ ለአባቱ እና ለአካባቢው የሐይማኖት መሪዎቸን ጠየቀ "አምላኬ ወደ ገነት እንደሚያስገባኝ እርግጠኛ መሆን የምችለው እንዴት ነው?" ሁሉም ሰው ተመሳሳይ መልስ ይሰጠው ነበር፦ "ማወቅ አይቻልም። ማንም ሰው የራሱን እጣ ፈንታ አያውቅም። እግዚአብሔር ብቻ ያውቃል።"

ምላሻቸው አሊን አላረካውም።

በቤትና በትምህርት ቤት፣ አሊ ከቁርዓን እንደተማረው፣ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ከድንግል የተወለደ ጻድቅ ነብይ ነው። በተጨማሪም ደግሞ ታላቅ ተዓምር አድራጊ ፣ መሲህ፣ የአላህ ቃል እና የአላህ ነፍስ የሚሉ መጠሪያዎችን የተሸከመ ነው። "ምናልባት ነብዩ ኢየሱስ የምፈልገውን ምላሽ ሊሰጠኝ ይቸላል"ሲል አሰበ።

አሊ ስለ ኢየሱስ የሚናገር መጽሐፍ መፈለግ ጀመረ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ተገናኘን። መጽሐፍ ቅዱስ ሰጠሁት ፣በጥልቅ ፍላጎት ማጥናት ጀመረ። በራሱ አባባል መጽሐፍ ቅዱስን ሲፈትሽ ከአንድ ዓመት በኋላ የሚከተለውን አገኘ፦

> ሁሉም ነብያት ወደ ኢየሱስ እንደሚያመለክቱ ተረዳሁ። ኢየሱስ ራሱ የሚከተለውን ያለበትን ቦታ አገኘሁ፦ "**እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ**፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። ...እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን **የዘላለም ሕይወት አለው**፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ **ወደ ፍርድ አይመጣም።**" (ዮሐንስ 14:6 ፤ 5:24 አመት)
>
> ይሄና ሌሎች ጥቅሶች ኢየሱስን እንድረዳና እንደቀበለው ረዳኝ፦ እሱ አንዱና ብቸኛው ደሙን ያፈሰሰ እና ድነትን ለማስገኘት ከሞት የተነሳው አዳኝ ነው። እምነቴን በእሱ እና በእኔ ምትክ ለሐጢአቴ መከራን በመቀበሉና በመሞቱ ላይ አደረግኩ። ባመንኩም ጊዜ ከዚህ በፊት የማላውቀው ውስጣዊ ሰላም ተሰማኝ። አስገራሚ ለውጥ።
>
> ከዚህ በኋላ ስለ ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ አልጨነቅም ምክንያቱም እኔን ለሚኮንኑኝ ሳጢአቶቼ ጌታ ሙሉ ቅጣት መክፈሉን አውቃለሁ። አሁን እኔ መልካም ስለንኩ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከተሰጠኝ ጸጋ የተነሳ ወደ ገነት እንደምሄድ አውቃለሁ። አሁን እግዚአብሔርን በሁሉ ነገር ማስደሰት እፈልጋለሁ፣

> ይህንን የማደርገው ድነቴን ለማግኘት ሳይሆን እግዚአብሔር ስላዳነኝ እና ልቤን ስለ ለወጠው ነው።

ለአሊ የሳጢአት እርግማን ተቀልብሷል። ዛሬ እሱ ፣ ባለቤቱ እና ወንዶች ልጆቹ ሲሞት ወደየት እንድሚሄዱ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ፣ በምድር ላይ ያሉት ለምን ጉዳይ እንደሆነ ያውቃሉ፦ አዳኝና ፈጣሪያቸውን ለማወቅ፣ ለመውደድ እና ለማገልገል እና ሌሎች እሱን እንዲያውቁ ለመምራት ነው።

## ሞት ፦ የአማኞች አገልጋይ

ወደ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ በመጣ ጊዜ መሲሁ የእግዚአብሔርን ባለ ሦስት ደረጃ የሳጢአትን እርግማን የመቀልበስ ዕቅድን ፈጽሟል። በሕይወቱ፣ ሞቱ፣ መቀበሩ እና መነሳቱ ፣ ኢየሱስ የሳጢአትን የማይሰበር የሚመስውን ግድግዳ አፈረሰ። በመስቀል ላይ የነበረው ሌባ ፣ የሰው ሥጋ በሎቹ፣ ኤማ፣ ሳዖል፣ አሊ፣ ብሩኖ እና የእግዚአብሔርን መለዕክት የተቀበሉ ሰዎች ተጠቃሚ ናቸው።

በክርስቶስ ለሚምኑ ሰዎች ፣ ጭካኙ አምባገነን ሞት፣ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ፣ የገነት በር የመከፈት ሳላፊነት ያለበት ትሁት አገልጋይ ሆኖ ተመድቧል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "የቅዱሳኑ **ሞት** በእግዚአብሔር ፊት **የከበረ** ነው።"[239] (መዝሙር 116:15)

ማንነው "የከበረ" የሚለው ቃል ከ "ሞት" ጋር ተያይዞ ሊነገር ይችላል ብሎ ማን ሊያምን ይችላል? ነገር ግን ለሚያምኑ ሁሉ እንዲዚያ ይሆናል።

> "**ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ?** ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?... ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።" (1ቆሮንቶስ 15:55፣57)

ያለፈው የሳጢአት እርግማን ተቀልብሷል።



# 28

# ደረጃ 2፦ የእግዚአብሔር የአሁን ፕሮግራም

"ሕጌን **በልቡናቸው** አኖራለሁ፥
**በልባቸውም** እጽፈዋለሁ"
— ጌታ (ኤርሚያስ 31:33)

ስለ ኅጢአት ገዳይ እርግማን በዙ ሰዎች ብዙ ባያስቡም እንኳን፣ ብዙዎች የሕይወት ዕለታዊ እርግማን ተብሎ ሊጠራ በሚችል ቀንበር ስር ይኖራሉ።

የዓለማችን አብዛኛው ሕዝብ በእኩይ ነገር ፍርኸት፣ በሕመም ናሞት ፍርኸት ይኖራሉ። ብዙ ሰዎች ምግብ ለመግዛት ወይም ዕዳ ለመክፈል የሚበቃ ገንዘብ ስለሌላቸው ይጨነቃሉ። ሌሎች ደግሞ ገደ ቢስነትን፣ ድግምትን ቡዳን ይፈራሉ፣ ስለ ደስታቸው ጮክ ብለው ተናግረው እኩይ መንፈስ ሰምቷቸው የደስታቸው ምንጭ በሆነው ነገር ላይ መጥፎ ነገር እንዳያደርስቸው ይጨነቃሉ። ክፉ መናፍስትን እና መቅስፍትን ለማራቅ አንዳንዶች ቁሳቁሶችን ወይም ድጋም ለራሳቸው እና ለልጆቻቸው ፣ ለቤታቸውም ያደርጋሉ። ብዙዎች ማርከሻ ይጠጣሉ ወይም የመከላከያ ድግምትን ይደግማሉ።[240]

ምስጋና ይግባውና፣ ፈጣሪ ተቤዢያቸውን የሚያውቁ እና የሚታመኑ እንዲህ አይነት ጥንቃቄ አያስፈልጋቸውም፣ እሱ በአዕምሯችን ከምንፈጥራቸው ይሁን ከእነዚህኞቹ እኩያን ኅይላት እጅግ በጣም የበለጠ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ጨምሮ በኅይላት ሁሉ ላይ ስልጣን ስላለው አማኞች የሚያስፈራቸው ምንም ነገር የለም።

ኢየሱስ የመጣው በዘላለማዊ ዕጣ ፈንታችን ላይ የመጣውን

የኀጢአት እርግማን ለመቀልስ ብቻ ሳይሆን በዕለት ሕይወታችን ውስጥ ሚገኘውን የኀጢአት እርግማን ለመቀልበስ ነው።

## እርግማንን መቀልበስ፦ ደረጃ ሁለት

መጽሐፍ ቅዱስ “ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ **በእናንተ ያለው ታላቅ** ነውና።” (1 ዮሐንስ 4: 4) ይላል።

በአማኞች “በእናንተ ዘንድ የሚገኘው” ማን ነው?

ከስቅለቱ ቀን ቀድሞ ባለው ምሽት ኢየሱስ ስደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ብሏቸው ነበር፦

> “እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር **ሌላ አጽናኝ** ይሰጣችኋል፤እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው **የእውነት መንፈስ** ነው፤ ነገር ግን **ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር** በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።
>
> ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ **ወደ እናንተ እመጣለሁ**።
>
> ...ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤አብ **በስሜ** የሚልከው ግን **መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ** እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።
>
> ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። **ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።**” (ዮሐንስ 14:16-18፣25-27)

## ሌላ አጽናኝ

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ አብ “**ሌላ አጽናኝ** ... መንፈስ ቅዱስ” እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶ ነበር።

ረዳት ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል ጰራቅሊጦስ ሲሆን ትርጉሙም ረዳት፣አጽናኝ፣አማካሪ፣ጠበቃ ማለት ነው።በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጰራቅሊጦስ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ልጅም ለመንፈስ ቅዱስም ጥቅም ላይ ውሏል።[241]

ወልድ ኀጢአተኞችን ከኀጢአት ቅጣት ሊያድን እንደመጣ

ሁሉ ፣ መንፈስ ቅዱስም የመጣው አማኞችን ከኀጢአት ኀይል ለማዳን ነው።

ወልድ ሁልጊዜ እግዚአብሔር እንደ ነበረ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ እግዚአብሔር ነበር። በእግዚአብሔር መጽሐፍ የመክፈቻ መግለጫ ላይ **"የእግዚአብሔር መንፈስ"** (ዘፍጥረት 1:2) የተባለው ለዚህ ነበር።

ብዙዎች እንደሚሉት[242] መንፈስ ቅዱስ የወደፊቱ ነብይ (ወይም መልዐኩ ገብርኤል!) ነው ማለት የነብያትን መጽሐፍ ቅዱስ መጣረስ ብቻ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ካለው እና ካደረገው ጋር መጋጨት ነው።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶ እንደገና ከተነሳ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ እና የእግዚአብሔርን መልዕክት ባነበቡት ልብ ውስጥ እንዲቀመጥ፣ እሱ ወደ ሰማይ እንደሚያደርግ ነግሯቸው ነበር። ወልድ ወደ ላይ ሲሄድ መንፈስ ወደ ምድር ይመጣ ነበር። ኢየሱስ ደቀ መዛርቱንም እንዲህ ብሏቸው ነበር፦ "እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ **አጽናኙ** ወደ እናንተ አይመጣምና፤ **እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ**።" (ዮሐንስ 16:7)

በታሪክ ውስጥ እስከዚህ ድረስ መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ ከአማኞች ጋር የሚሆነው ኀይልን ሊሰጣቸው፣ ሊመራቸው እና ለባርካቸው ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ የዓለምን የኀጢአት ጉዳይ ከፈታ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በመምጣት እና በአማኞች ውስጥ በቋሚነት መኖር ቻለ።

ጌታ ኢየሱስ ለየት ያለ ክስተትን እያስተዋወቀ ነበር። "የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን..." (ዮሐንስ 14:17)

## መንፈስ ቅዱስ እየመጣ ነው

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

> "ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን፦ ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ። ...**ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥**

**በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።"**
(ሐዋርያት 1:4-5፣8)

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ ከአምሳ ቀን በኋላ እና ወደ ሰማይ ካረገ ከአ\ሥር ቀን በኋላ በዕለተ ጰንጤቆስጤ የሆነው ይሄ ነው፡፡ [243]

> "በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም[ወደ 120አማኞች፣ወንችእናሴቶች(ሐዋርያት1:14)]በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። **በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው**..."(ሐዋርያት 2:1-4)

አዲስ ኪዳን ይህንን አሰደናቂ ክስተት በሁለተኛ ምዕራፉ ዘግቦታል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፣ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከኢሲያ፣ አረብያና ሌሎች በርካታ የዓለም አካባቢ በኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡ እንግዶች በተለያዩ ቋንቋዎች የእግዚአብሔርን የምሥራች ተናገሩ።

መንፈስ ቅዱስ በወረደበት በዚያው ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች የእግዚአብሔርን መልዕክት አምነው የዘላለም ሕይወት ስጦታን ተቀበሉ። የአማኞች ቁጥርም በፍጥነት አደገ።

የሐዋርያት *ሥራ* መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹን በኢየሱስ ያመኑ ሰዎች ታሪክ ይናገራል በተጨማሪም ከሞት የተነሳው መሲህ የምሥራች በመላው የሮም አገዛዝ ያለ መሳሪያ ኃይል በእግዚአብሔር ፍቅር እና በመንፈስ ቅዱስ እንደተስፋፋ ይናገራል።

## የተጠሩ

በዚህ በእሁኑ ወቅት እግዚአብሔር እዚህ ምድር ላይ ያለው ዕ፥ ቅድ "እግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ..." (ሐዋርያት15:14) ነው፡፡

በዕለተ ጴንጤ ቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ቤተ ክርስቲያን እየተባለ የሚጠራ የአማኞች ቤተሰብ ፈጠረ። የቤተ ክርስቲያ ዋነኛው የግሪክ መጠሪያ ኤክሌሲያ የሚል ሲሆን ትርጉሙም ፡- ጉባዔ ወይም የተጠሩ ማለት ነው። ዛሬ ቤተ

ክርስቲያን የሚለው ቃል በተሳሳቱ ጽንሰ ሐሳቦች እና የማይቆጠሩ ቤተ እምነቶች የተተበተበ ቃል ነው። ብዙ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ሰዎች በአኗኗራው የክርስቶስን ስም ያስነቅፋሉ። ብዙዎች ሐይማኖት አላቸው ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ግን እውነተኛ ግንኙነት የላቸውም። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ማመን ከኅጢአታቸው አልነጹም።

የምሥራቹ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ የሚገኙ ሁሉም ሰዎች በልጁ በማመን፣ ልዩ አዲስ ፍጥረት ይሆናሉ። በተጨማሪም ከእሱ ጋር ዘላለምን የሚያሳልፉ የአማኞች ቤተሰብ አባል ይሆናሉ።

ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ያመኑ (የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች) የእግዚአብሔር ቤተሰ ብ አባላት ናቸው፤ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ ያመኑት "ቤተ ክርስቲያን" የምትባለው ህዋስ አካል ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በተጨማሪም "የክርስቶስ አካል" እና "ሙሽራ"[244] ትባላለች። በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላቸዋል፦

> "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ **የተመረጠ ትውልድ**፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን **የእግዚአብሔር ወገን** ናችሁ..." (1ጴጥሮስ 2:9-10)

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ምዕራፎች እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሰው ልጆችን እንዴት የራሱ ልዩ ፍጥረት አድርጎ እንደ ፈጠራቸው ይናገራል። ሦስተኛው ምዕራፍ አዳም እንዴት ኅጢአት እንደሰራና ራሱን እና የሰው ዘርን በሙሉ ከእግዚአብሔር እንደለየ ይናገራል። ነገር ግን ተከታዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር የረከሱ ኅጢአተኞችን እንደገና "የእሱ ልዩ ሕዝብ" እንዲሆኑ ምን እንደሰራ ይናገራል።

የተለየውው የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል ናችሁ? ከሆናችሁ እግዚአብሔር ርግማንን ለመቀልበስ ያወጣው ፕሮግራም ሁለተኛው ደረጃ ውስጥ ግብታችኋል ማለት ነው።

## የዳነ እና የታተመ

የእግዚአብሔር የድነት ሥጦታ በተቀበለ አማኝ ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው የመጀመሪያ ነገር አዲስ

ሕይወት መስጠት ነው። በራሳቸው እና በጥረታቸው ከመታመን ይልቅ በኢየሱስንና በመስቀል ላይ በሰራው ስራ የሚታመኑ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በመንፈሳቸው ዳግም ይወለዳሉ።

ኢየሱስ እንዲህ ይላል፦

> "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። **ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል** ስላልሁህ አታድንቅ። **...በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ** እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐንስ 3:6-7 ፤ 16አመት)

"ዳግም መወለድ!" እንዴት የሚያሰደስት ነገር ነው! ሳጢአተኛ በመንፈስ ዳግም እንዲወለድ የሚያደርገው እግዚአብሔር በውስብስብ ማንነቱ ነው። ዳግም መወለድ የተቻለው አብ ወልድን ስለ ላከው ፤ ወልድ ስለ ሳጢአት ደሙን ስላፈሰሰ ፤ መንፈስ ቅዱስ አማኙን በአዲስ ሕይወት ሰለሞላው ነው።

መንፈስ ቅዱስ የዘላለምን ሕይወት መስጠት ብቻ አይደለም፣ ለዘላለም ያትመናል ፣ የእግዚአብሔር ንብረት እንደሆንን ምልክት ያደርግብናል፣ በተጨማሪም ውስጣችን ለዘለቄታው ይኖራል። በተጨማሪም ዓለምን የመልቀቅ ተራችን ሲደርስ ወደ አባታችን ቤት ሰለ መግባችን ማረጋገጫ ይሰጠናል።

> "እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ **አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤** ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።" (ኤፌሶን 1:13-14)

ምንም ነገር እውነተኛ አማኝን ዘላለማዊ ድነቱን እንዲያጣ አያርገውም "መንፈስ ቅዱስ ...**የርስታችን መያዣ ነው**"

## ነፃ የወጣነው እንደገና ሳጢአት ለማድረግ ነው?

አልፎ አልፎ ሰዎች በመጠራጠር "እሺ በገነት ቦት ማግኘቴን እርግጠኛ ለመሆን ማድረግ የሚገባኝ፥ ኢየሱስ ስለ ሐጢአቴ መሞቱን ማመን ነው፤ ከዚያም ደስ እንዳለኝ ሳጢአት ማድረጌን

ማድረግ መቀጠል እችላለሁ አይደል?” ሲሉ እሰማለሁ፡፡

ይህንን ተመሳሳይ አምክንዮ በመጠቀም አንድ ሰው ከአዝቅት ውስጥ ካዳናችሁ በኋላ ያዳናችሁን ሰው “አመሰግናለሁ! አሁን እንደገና ለመግባት ነጻ ነኝ!” ትሉታላችሁ?

ወይም አበዳሪያችሁ ታላቅ ብድራችሁን ይቅር ካላችሁ በኋላ ፣ እሱን የሚያስከፉ ነገሮችን አስባችሁ አቅዳችሁ ታደርጋላችሁ፡፡፡

ወይም ንጹህና በጥሩ ሁኔታ የተተኮሰ ልብስ ለብሳችሁ “መልካም እንግዲህ አሁን አቧራ ላይ መንደባለል እችላለሁ!” ብላችሁ ታስባላችሁ?

ይሄን አይነት አመለካከት የማይታሰብ ነው፡፡

ኅጢአትን እና የሚያስከትለውን ችግር በተመለከተ አዳምና ልጆቹ እንደዚህ የሚያስቡት ለምንድን ነው?

አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ መልሱ ግልጽ ነው፡፡ ኅጢአት መልካምና ተፈላጊ እንደሆነ እስከሚያሳምነን ድረስ በአዕምሯችንና በልባችን ላይ ላይ ሳይለኛ ተጽዕኖ አለው፡፡ አዳምና ሔዋን ኅጢአትን ማለትም የተከለከለውን ፍሬ መብላትን “ለጥበብም **መልካም** እንደ ሆነ አየች” (ዘፍጥረት 3:6) ነው ያዩት፡፡

ልንረዳው የሚገባን ነገር ኅጢአተኛው በእግዚአብሔር መልዕክት በሚያምንበት ጊዜ ፣በኅጢአት በረኸ ውስጥ የጠፋ አይደለም፡፡ ሽክም የሆነበት ዕዳ በሙሉ ተከፍሏል፡፡ አማኙ አሁን የክርስቶስን ንጹህ ጽድቅ ለብሷል፡፡

መንፈስ ቅዱስ አዲስ በተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ልብ ውስጥ ሐጢአት መልካም ሳይሆን መጥፎ ነው የሚል ቅዱ ስመረዳትን ይገጥማል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእሱን ቅዱስ ጠባይ እና አመል የሚያንጸባርቅ ሕይወት እንዲኖር አቅም ይሰጣል፡፡ እንደ ሰማያዊ ቤተሰብ አባል ፣ የእግዚአብሔር አዳዲስ ልጆች የቤተሰቡን ክብር የሚያስጠብቅ ሕይወት መኖር ይፈልጋሉ፡፡

ምንም እንኳን አማኞች መንፈስ ቅዱስን ችላ ቢሉም በኑሯቸው ጌታን ሊያዋርዱም ቢችሉም እውነተኛ በክርስቶስ ያመኑ አማኞች በውስጣቸው ሰማያዊው እንግዳ ይኖራል፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ያመኑ አማኞችን እንዲህ ሲል የሚገስጸው፡-

> “ለቤዛም ቀን **የታተማችሁበትን** ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ **አታሳዝኑ**፡፡” (ኤፌሶን 4፡30)

በጌታ ኢየሱስ ያመኑ አማኞች በእምነት የተቀበሉትን ድነት ሊያጡ አይችሉም፤ ነገር ግን እንደማያምኑ ሰዎች በመኖር “መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን” ይችላሉ። የጌታ ሕዝብ **በ**ዓለም ቢኖርም እንኳን “እኔ **ከ**ዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም።” (ዮሐንስ 17:16) አይደሉም

ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር ያሉ እግአብሔርን የማያከብሩ ልምምዶችን እንደሚጠላ ሁሉ ደቀመዛሙርቱም መጥላት አለባቸው።

> “እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? **አይደለም**። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?”
> (ሮሜ 6:1-2)

> “እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው፤ በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል፤ እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ። አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ፤ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ **አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥ የፈጠረውንም ምሳሌ** እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል” (ቆላስያስ 3:5-10አመት)

## በአማኞች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሕይወት

የእግዚአብሔር ልጅ ያመኑ ኅጢአቸ ን ከኅጢአት ቅጣት ለማዳን እንደመጣ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ የመጣው አማኞችን ከሐጢአት ዕለታው ጉልበት ነጻ ለማውጣት ነው።

የሚሰራው እንደሚከተለው ነው።

አንድ አማኝ እምነቱን በክርስቶስ ላይ በሚያደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ውስጡ በውስጣዊው የማዘዣ ክፍሉ ውስጥ መንግስቱን መስርቶ ይኖራል። እግዚብሔርን ለማስደሰት የሚፈልግ አዲስ ማንነት ይሰጠዋል። ይሄ ማለት የሰውየው ራስ ወዳድ ኅጢአተኛ ባህርይ ተወግዷል ማለት አይደለም። አሮጌው

ማንነቱ የሚወገደው አማኙ ከጌታ ጋር በሰማይ ሲሆን ነው፡፡ በዚህ ዓለም ወደ ሐ2ጢአት አልባ ፍጽምና አይደርስም፡፡ ነገር ግን ጌታን ሲያሳዝን ጥልቅ ሐዘን ይሰማዋል፡፡[245]

በእያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ ሕይወት ውስጥ በአሮጌው ማንነት (ከአዳም በወረሰው) በአዲሱ ማንነት (በመንፈስ ቅዱስ በተተከለው) ማንነት መካከል ቀጣይነት ያለው ውጊያ ይኖራል፡፡ በውስጡ ያለው የክርስቶስ መንፈስ አማኙ እግዚአብሔርን የማስደሰት ፍላጎት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ሳጢአት "**ጊዜያዊ** ደስታ" (ዕብራውያን 11:25) የሚሰጥ ቢሆንም "የዚህ ነገር መጨረሻው **ሞት** ነውና፡፡ አሁን ግን **ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ**… **ልትቀደሱ ፍሬ** አላችሁ" (ሮሜ 6:21-22) ሲል ሕዝቡን ያስተምራል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ልብ ውስጥ ዐብይ ለውጦችን ይፈጥራል፡፡

> "የመንፈስ ፍሬ ግን
> ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣
> ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣
> እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡
> እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም፡፡"
> (ገላትያ 5:22-23 አመት)

ሐይማኖታዊ የራስ ጥረቶች መንፈሳዊ ፍሬዎቸን ሊያፈሩ አይችሉም፡፡ ሐይማኖታዊ ሕግጋት የሰውን ውጪያዊ ጠባያት እስከተወሰነ ድረስ ቢለውም ፣ የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚለውጠው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሔር ሕጉን በውስጣችሁ መፈጸም ይፈልጋል፡፡ የምትፈጽሙት የሕግ ዝርዝር ከመስጠት ይልቅ በውስጣችሁ ይኖራል፣ በእናንተም በኩል ለስሙ ክብር ሲል ሌሎችን ይባርካል፡፡

## ዝርዝር ወይስ ፍቅር?

ሚስት ሰለ ሞተቸበት አንድ ሰው የሚነገር ታሪክ አለ፡፡ ሚስቱ የሞተችበት ግለሰብ በሳምንት ቤቱን እንደታጸዳለት እና ልብሱ እንድታጥብለት አንዲት ሴት ቀጠረ፡፡ የጽዳት ሠራተኛዋም በመጣች ቁጥር እንድትሰራለት የሚፈለው ዝርዝር ፍሪጁ ላይ ለጠፈላት፡፡ እናም በእርግጥም ለሰራችው ስራ ይከፍላት ነበር፡፡

ከጊዜያትም በኋላ፣ ሰውየው ከሴትየዋ ፍቅር ያዘው እና ሚስቱ እንድትሆን ጠየቃት፡፡ ተስማማች፡፡ ከተጋቡም በኋላ

በፍሪጁ ላይ የሚገኘውን የስራ ዝርዝር ከፍሪጁ ላይ አነሳ። መደበኛ ደሞዝ መክፈሉንም አቆመ። ለምን? "የቤት ጽዳት ሰራተኛዋ" ውዷ ባለቤቱ ሆናለች! አሁን በደስታ ቤቱን ታጸዳለች፣ ልብሱን ታጥባለች በተጨማሪም በዝርዝሩ ላይ የሌሉ ሥራዎችን ታከናውን ነበር። ለምን? ባለቤቷን ስለምትወድ እና ልታገለግለው ስለምትፈልግ ነበር። ፍሪጁ ላይ የነበሩ ሕግጋት አሁን በልቧ ተጽፏል።

እግዚአብሔር የእሱ ለሆኑት የሚያደርገው ይሄንን ነው።

> "ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።" (ኤርሚያስ 31:33)

ልክ በፍሪጁ ላይ እንደነበሩ ዝርዝሮች፣ የሰው ልጅ ሐይማኖትም "እግዚአብሔር ከፈቀደ" በፍርድ ቀን ሊከፈላችሁ ይችላል የሚችል ተስፋ ይሰጣችሁና፣ ልትፈጽሟቸው የሚገቡ ተግባራትን ዝርዝር ይሰጣችኋል።

በአስገራሚ ንጽጽር ጌታ ከእሱ ጋር ግንኙነት እንድትመሰርቱ ይፈቅድላችኋል። ቀጣታችሁን ተቀጥቶ የዘላለም ሕይወት መስጠት ብቻ ሳይሆን ግብዣውን ከተቀበላችሁ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእናንተው ውስጥ መኖር ይፈልጋል።

በፍጹም ልታደርጉት የማትችሉትን የስራ ዝርዝር በላያችሁ ላይ ከሚጭንባችሁ ፣ እግዚአብሔር ከልብ በመነጨ ፍቅር እንድታገለግሉት ፍላጎት እንደሚሰጣችሁ ቃል ይገባል። ግንኙነት ከዝርዝር እና ሕግጋት ሐይማኖት የበለጠ ተነሳሽትን ይፈጥራል። ይህም የሆነበት ምክንያት፦

> "...ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።" (ሮሜ 13:10)

ሐይማኖት በገነት ምትክ አዲስ ሕይወት ሊሰጣችሁ ቃል ይገባ ይሆናል ፣ የሚሰጣችሁ ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም እና ዘላለማዊ ጥበቃ ሊሞላችሁ የሚችለው እሱ ብቻ ነው።

> "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ **የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።"** (ሮሜ 5:5)

## በደስታ የተሞላ መታዝ መታዘዝ

በእርግጥ አማኞች ጌታን እና ሰዎችን በእግዚአብሔር ፍቅር ሞልቶ በሚፈስ ልብ ማገልገላቸው በምንም አይነት የሚታዘዙት ትዕዛዝ የላቸውም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ፣ ጌታ ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት ደቀመዛሙርቱን እንዲህ ብሏቸው ነበር፦

> "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና **አሕዛብን ሁሉ** በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም **እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤** እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" (ማቴዎስ 28፡ 18-20)

ኢየሱስ ተከታዮቹ የድነቱን የምስራች "ለአሕዛብ ሁሉ" እንዲናገሩ አዟቸዋል። አንድ ሰው የድነትን ስጦታ ከተቀበለ በኋላ ፣ ኢየሱስ ያዘዘውን "ሁሉን ነገር እንዲፈጽም" መማር አለበት። ለምሳሌ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠላቶቻቸውን እንዲወዱ እና ሁሉንም በደስታ እንዲያገለግሉ አዟቸዋል። የክርስቶስ ተከታዮች ፍላጎት በቸኛው እውነተኛ አምላክ በዓለም ሁሉ መታወቅ ፣ መታመን እና መመስገን መሆን አለበት።

ኢየሱስ ደቀዛሙርቱን አዳዲስ አማኞችን "በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም" እንዲያጠምቁ አዟቸዋል። ልብ ልትሉ የሚገባው "ስም" (ነጠላ) አለ እንጂ "ስሞች"(ብዙ) አላለም። ራሳቸውን እንደ ረዳት አልባ ኅጢአተኞች የሚያዩ እና ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሳዔ የሚያምኑ ብቻ ከአንዱ አብ ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ከሆነው ከአንዱ አምላክ ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት ይመሰርታሉ።

ይህንን መልዕክት ያመኑ ሰዎች እምነታቸውን በወንዝ ወይም በሌላ ውሃማ አካል በመጠመቅ ማሳየት መቻል አለባቸው።

## ጥምቀት ለምን?

አማኝ ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ውሃ ውስጥ መጠመቅ የሚያስፈልገው ከኅጢአት ለመንጻት ነው? በፍጹም በክርስቶስ ሞትና ትንሳዔ ካከናወነው ነገር የተነሳ አማኙ ነጽቷል ፣ በእግዚአብሔርም ጻድቅ ተብሏል። የውሃ ጥምቀት የውስጣዊ እውነታ ውጫዊ መገለጫ ነው። አንድ ጊዜ በእግዚአብሔር

መልዕክት ካመንን በኋላ ለአዳኛችን እና አዲሱ ጌታችን በመታዘዝ መጠመቅ መቻል አለብን ነገር ግን ለገነት የሚያበቃን እንዲህ ያለው ጥምቀት አይደለም።[246]


ታዲያ የውሃ ጥምቀት በታው የት ነው? በሚታይ መልኩ ከጌታ ኢየሱስ ሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ ጋር በሚታይ መልኩ ያስማማል። የውሃ ጥምቀት አማኞች በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ማመናቸውን የሚመሰክር ነው። ውሃ ሞትን የሚያሳይ ነው። ሰው ከውሃ በታች ሲሆን የሚያሳየው "ኢየሱስ ስለ ኅጢአቴ ሞቶ ተቀብሯል"የሚለውን ነው። ሰውየው ከውሃ ውስጥ ሲወጣ የሚያሳየው ፦ "ኢየሱስ ስለኔ ሞትን አሸንፏል። እሱ በእኔ ምትክ ስለሞተ ፣ ስለ ተቀበረ ስለ ተነሳ፣ ከኅጢአቴ ነጽቻለሁ፣ ጻድቅ ተብያለሁ የዘላለም ሕይወትም ተስጥቶኛል።"

ስለዚህ ነገር አትሳሳቱ። ኅጢአተኛ በእግዚአብር ፊት ተቀባይነትን የሚያገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ጽድቅ እና በተጠናቀቀው ስራው ነው። ይቅር እንደ ተባለ ኅጢአተኛ ከጌታ ጋር ለዘላለም እንደምኖር የማውቀው ፣ መልካም ስለሆንኩ ሳይሆን ነገር ግን "**ክርስቶስንም አገኝ** ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት **ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ** እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ" (ፊሊጲሲዩስ 3:9) ነው።

የሰዎች ሐይማኖት ራሳችሁን እና የራሳችሁን ጥረት ተመልከቱ ይላችኋል። የእግዚአብሔር ወንጌል ክርስቶስን እና እንከን የሌለበት ጽድቁን እንድንመለከት ያስተምረናል።

## አማኞች ፍርድ የለባቸውም?

ክርስቶስ ኅጢአተኞችን ከዘላለማዊ ኩነኔ ለማዳን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አድርጓል የሚለው እውነታ በብዙ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ ጥያቄ ያስነሳል። አንድ ኢሜይል የጻፈልኝ ሰው እንዲህ ብሏል፦




በፍጹም የኢየሱስ ስለ ኅጢአታችን በመስቀል ላይ መሞት አማኞች ስለራሳቸው የሚጠየቡበትን እውነት ውድቅ አያደርገውም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "**ፍርድ**

**ከእግዚአብሔር ቤት** ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን?" (1 ጴጥሮስ 4:17 አመት)

## ሁለት የፍርድ ቀናት

መጽሐፍ ቅዱ ቻችን ወደፊት ሁለት የተለያዩ የፍርድ ቀናት እንዳሉ ይገልጣል። የመጀመሪያው ፣ የጻድቃን ትንሳዔ እና ፍርድ ሲኖር ከዚያ በኋላ በመቀጠል የሳጢአትን ትንሳኤና ፍርድ ይኖራል።[247]

- **የጻድቃን ፍርድ**፦ የዚህ የፍርድ ቀን አካል መሆን ትፈልጋላችሁ። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በስፍራው የሚገኙትን ገነት ነው ሲያል መግባት ያለባቸው የሚለው ጉዳይ ጥያቄ የለው። በምድር ላይ በኖሩበት ጊዜ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስጦታ በምድር ላይ ሳሉ ሰለ ተቀበሩ በዚያ ምክንያት በገነት ይገኛሉ። ነገር ግን እንደ አማኞች በሰሩት ሥራ መነሻ ሐሳብና እሴት አንፃር እግዚአብሔር በሚሰጠው ግምት ፣ ይሸለማሉ ወይም ሽልማት ያጣሉ። እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ የኖረ ፣ ሌሎችን በትህትና ያገለገለ ፣ በፈተና ውስጥ እግዚአብሔርን የታመነ፣ ቃሉንም የወደደ እና ያሰራጨ ፣ የጌታን ምጽዓት በጉጉት የሚጠብቅ ከሆነ ይሸለማል፣ ራሰ ወዳድ አማኝ "የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።" (1ቆሮንቶስ 3:11-15ተመልከቱ) መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች አምስት የተለያየ አይነት "አክሊሎች" ሊቀበሉ እንደሚችሉ ይገልጻል፣ እነሱንም በአምልኮ በጌታ ፊት ያሰቀምጧቸዋል።[248] "ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና። ...እንግዲያስ **እያንዳንዳችን** ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።" (ሮሜ 14:10 ፣12)

- **የሳጢአተኞች ፍርድ** ፦ የዚህ አሰፈሪ የሆነው የታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ በተሰኘው ፍርድ ላይ መገኘት አያስፈልጋችሁም። በምድር ላይ እያሉ የእግዚአብሔርን የድነት አቅርት ሳይቀበሉ ከነሳጢታቸው ለሞቱ ሰዎች የተዘጋጀ ፍርድ ነው። ወደ ገነት ነው ወይስ ወደ ሲያል የሚሄዱት የሚል ጥያቄ የለም። ምንም እንኳን እያንዳንዱ በተቀበሉት እውነት ምን እንዳደረጉበት ተጠይቀው የሚቀጡት የቅጣትደረጃ የተለያየ ቢሆንም ፣ሁሉም ወደ እሳት ባህር የሚሄዱ ናቸው። "ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ

**እንደ ሥራቸው መጠን** ተከፈሉ። ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።" (ራዕይ 20:11-15 ተመልከቱ)

የምሥራቹ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶሰ ከኅጢአት ቅጣት ነፃ የሚወጡበት መንገድ ሰላቀረብ፣ ይህንን ቃል የሚያነብ የትኛውም ሰው ሊጠፉ አይገባም።

## የእግዚአብሔር ልጆች

አስቀድመን እንደተገነዘብነው እምነታችሁን በጌታ ኢየሱስ እና በሰራው ሰራ ላይ በምታደርጉበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ትሆናላችሁ።

እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ ሩቅ አይመስለኝም።
አባታችሁ ይሆናል።

> "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ **የእግዚአብሔር ልጆች** ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" (ዮሐንስ 1:12) "**ልጆችም ስለ ሆናችሁ** እግዚአብሔር **አባ አባት** ብሎ የሚጮኽ **የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ**።" (ገላትያ 4:6)

ዓለማችን ሩቅ ፣ ሰርዓት ፈላጊ የሆነና ከእሱ ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖረን የማይፈልግ አምላክ ባላቸው ሐይማኖቶች የተሞላ ነው። በተቃራኒው ልጁን ወደ ምድር የላከው አምላክ ራሱን ኅጢአተኞችን እንደሚወድ ሰማያዊ አባት ራሱን ገልጿል። ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ ፣ ሊያነጻቸው የክርስቶስ ፍጽምና እንደሚያለብሳቸው እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ወደ ልባቸው እንደሚልክ ቃል ይገባል።

"አባት ብዬ ጠራሁት" (I Dared to Call Him Father) በሚለው መጽሐፏ የፓኪስታኗ ቢልቂስ ሼክ የአንዱን እውነተኛ አምላክ መልዕክት ለማግኘት ያደረገቸውን ፍለጋ ተነግረናለች። ለበርካታ ወራት መጽሐፍ ቅዱስን እና ካደገቸት እምነት መጽሐፍ ጋር ካወዳደረች በኋላ፣ እግዚአብሔር እውነቱን እንዲያሳያት ስትጮህ ያለፈችበትን ልምምድ ትናገራለች፦

> "ሁለቱንም መጽሐፍት፣ አንዳቸውን በአንደኛው ሌላኛውን በሌላኛው እጄ ይዤ "የትኛው አባት?"

አልኩኝ። "የአንተ መጽሐፍ የትኛው ነው?" በመቀጠል የሚያስገርም ነገር ሆነ። ልክ በዚህ አይነት መንገድ በሕይወት የሆነ ነገር አላስታውስም። በራሴ ውስጥ ድምጽ ሰማሁ፣ ድምጹ በአዕምሮዬ ቃሉን እንደምደግም ይመስል በውስጤ ይሰማኝ ነበር። አዲስ፣ በደግነት የተሞሉ፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ሁኔታ በስልጣን የተሞሉ ነበሩ።

**"በየትኛው መጽሐፍ ነው እንዳባት የምትገናኘኝ?'**

ራሴን "ከመጽሐፍ ቅዱስ" መልስ ስሰጥ አገኘሁት ይኼው ነው በቃ።"[249]

ልክ እንደዚቺ ፓኪስታናዊት ሴት እግዚአብሔር የእኔም አባት ነው። የእግዚአብሔርን መልዕክት ባመንኩ ዕለት ፣ በመንፈሴ ዳግም ተወልጃለሁ። የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነቴን ማንም እንዳጣ ሊያደርገኝ አይችልም። ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኛማል፤እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።" (ዮሐንስ 10:27-28)

## ግንኙነት እና ኅብረት

ታዲያ ኅጢአት ሳደርግ ምን ይፈጠራል? እንደገና ከእግዚአብሔር ጋር እንድለያይ ያርገኛል?

ልጅ ምድራዊ አባቱን ባይታዘዝ ፣ የቤተሰቡ አካል መሆኑ ያበቃል።

በፍጹም።

የልጅ አለመታዘዝ እንዳልተወለደ እንዲቆጠር ምክንያት ሊሆን አይችልም። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸሁ መንፈሳዊ ትስስርም እንደዚያው ነው። ዳግም የተወለዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች የሆናችሁበትን ስልጣን ማንም ሊያሳጣችሁ አይችልም። የሚያምን ሁሉ "**ዳግመኛ የተወለዳችሁት** ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና **ለዘላለም** በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።" (1ጴጥሮስ 1:23) አለው። እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችሁ ነው። የለበሳችሁት የክርስቶስ ጽድቅ መቼም ቢሆን ከእናንተ አይወሰድም። መንፈስ ቅዱስ መቼም ቢሆን አይተዋችሁም።

ለዘላለም የተጠበቃችሁ ናችሁ።

> “ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን …በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።”
> (ሮሜ 8:38-39)

ከእኔ በኩል ያለ የትኛውም ድርጊት ከእግዚአብሔር ጋር የመሰረትኩትን ዘላለማዊ **ግንኙነት** ሊለውጠው አይችልም። ነገር ግን ኃጢአት በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን **ግንኙነት** ያውከዋል።

## ቦታ እና ሁኔታ

አባት ለልጁ የአትክልት ቦታውን አሰተካክል ብሎ ያዘዋል እንበል፣ ልጅየው ግን ያንን ከማድረግ ይልቅ ከጓደኞቹ ጋር ኳስ ለመጫወት ይሄዳል። እንደ ልጅ ከአባቱ ጋር ያለው ቦታ ለውጥ አይኖረውም ፣ ልጅ ከአባቱ ጋር ያለው ሁኔታ ወይም ኅብረት ግን በእርግጠኝነት ይለወጣል! ልጁ ወደ ቤት በሚመለሰበት ጊዜ ይጠየቃል፣ ጠንከር ያለ ንግግር እና ተመጣጣኝ የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል። ልጅ ከአባቱ ጋር ባለው የቅርብ ግንኙነት ደስተኛ እንዲሆን ከፈለገ አለመታዘዙን መናገር አለበት።

በተመሳሳይ መልኩ የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች፡፡ ኃጢአትን በሚያደርጉ ጊዜ ይቀጣቸዋል።

> “ልጄ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፥ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር። እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ **አባት** የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ።”
> (ምሳሌ 3:11-12)

ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ዕለታዊ ግንኙነት ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

> “ከእርሱ ጋር **ኅብረት** አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም … ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።”
> (1ዮሐንስ 1:6 ፣ 8-9)

በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልጆች በሙሉ የትኛውንም የኃጢአት መልክ ምንም ያህል ትንሽ ይሁን

እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር ሌሎች እንኳን ሳጢአት ባይሉትም በሕይወታችን ስላለው ሳጢአት ስሱዎች እንድንሆን ይፈልጋል።

ለምሳሌ ባለቤቴን ጥሩ ባልሆነ መንገድ ባናግራት ወይም ሰለ በደለኝ አንድ ሰው የጥላቻ አመለካከት ቢኖረኝ ለአንድ ሰው ሙሉ በሙሉ እውነት ያልሆነ ነገርን ብናገር ፣ መንፈስ ቅዱስ ስለ ሳጢአቴ ይወቅሰኛል።

ስለዚህም ማርከሻው ለጌታ “ሳጢአቴን መናዘዝ” እና ጌታን ባሳዘንኩበት ነገር ይቅርታ መጠየቅ ነው። አንድ ጊዜ ይህንን ካደረግኩ በኋላ ከጌታ ጋር የቅርብ እና ደስ የሚያሰኝ ግንኙነት ይኖረኛል።

ልዩነቱን አያችሁ?

በክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ያለኝ ቦታ ፍጹም ነው፤ ነገር ግን በዕለታዊ ሕይወቴ ሁኔታዬ ከፍጽምና ያነሰ ነው።

እሱ ለኔ የሰራው የማዳን ስራ ለዘላለም ተጠናቋል፤ በእኔ ውስጥ የሚሰራው ስራ ግን እስከምንገናኝ ድረስ የሚቀጥል ነው።

## ለዓላማ የተዋጀሁ

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያስብበትን፣ የሚናገርበትን እና የሚመላስበትን መንገድ መለወጥ ይፈልጋል። ስለዚህም እንዲህ ይላል፦

“እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ” (1ጴጥሮስ 1:16)

በተጨማሪም ሕዝቡን እንዲህ ይላል ፦ “ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ። **መንፈስ ይሙላባችሁ** [መገዛት፣ በቁጥጥር ስር መሆን] እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤” (ኤፌሶን 5:17-18 አመት)

መንፈስ ቅዱስ ስብዕናችንን አይጫነውም፤በምትኩ ግን እግዚአብሔር ለእኛ ያሰበውን ዕለታዊ የጽድቅ እና የድል ሕይወት እንድንኖር ነጻ ያደርገናል። እግዚአብሔር ያዳነን ለዓላማ ነው። በምናስበው፣ በምንናገረውና በምንሰራው እሱን እንድናከብረው ተጠርተናል።

> “ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው **የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ** እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ

> አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" (1 ቆሮንቶስ 6:19-20)

ይሄ በወንጌል ላመኑ ሰዎች ምን ያህል ሕይወት ለዋጭ እውነት ይሆን! የእግዚአብሔር አካላዊ መገኘት በውስጣችን ነው! ሕይወታችን ስሙን የሚያከብር እና ለሌሎች በረከት የሚሆነው ለእሱ ስንገዛ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በሕዝቡ ውስጥ ስለሚሰራው ስራ ከዚህም የበለጠ ነገር ማለት ይቻላል።

ያጽናናል፣ ያበረታል፣ ይመራል፣ ያነቃል እንዲሁም ያዛል።

አማኞች ቅዱሳት መጽሐፍትን እንዲረዱ ይረዳል።[250]

ከእግዚአብሔር ጋር በሚያገናኝ መልኩ እንዲጸልዩ ያግዛቸዋል።[251]

ሌሎች ሰዎችን እንዲረዱ እና እንዲያንጹ ለሰዎች ልዩ ስጦታዎችን እና ችሎታዎችን ይሰጣል።[252]

ተቃውሞው ምንም ያህል ይሁን፣ የክርስቶስ ተከታዮች ለእሱ እንዲሰሩ እና እንዲመሰክሩ ያስታጥቃቸዋል። ኢየሱስ ተከታዮቹን እንዲህ ብሏቸዋል፦

> "እነሆ፣እኔእንደበጎችበተኵላዎችመካከልእልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ። ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ በምኵራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ፤ለእነርሱና ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን፥ ስለ እኔ ወደ ገዥዎች ወደ ነገሥታትም ትወሰዳላችሁ። አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ **አትጨነቁ፤በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።"** (ማቴዎስ 10:16-20)

## የልጁን መልክ እንዲመስሉ

በአጭሩ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዓላማ የሆነውን፥ የብቸኛውን እውነተኛ አምላክ መልክ እንዲያንጸባርቁ ከእሱ ጋር ለዘልዓለም ከእሱ ጋር ጥልቅ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

> "እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ... እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን። ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፣ አስቀድሞ **ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ** አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና" (ሮሜ 8:26 ፣ 28-29)

እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት የሚመጣውን እያንዳንዱን ክስተት እና ፈተና "ልጁን መልክ እንዲመስሉ" ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል፡፡

የእግዚአብሔር መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ወንድና ሴት የተፈጠሩ በእሱ "መልክንና ምሳሌ" እንደሆነ ይናገራል። ሰው በፈጣሪው ላይ ኃጢአት ለመስራት መምረጡ ያንን መልክ ፈጽሞ አጠፋው። ነገር ግን በትክክለኛው ጊዜ ፣ ፍጹምና የከበረ ልጁን ወደ ዓለም ላከ፡፡

የኢየሱስ የጽድቅ ሕይወት ፣ሞትና ትንሳዔ በኃጢአት የደረሰውን ጉዳት የሚያስተካከልበት ደረጃ አንድ ነበር። ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ እንዳየነው ዕቅዱ ከዚህ የበለጠ ፣በጣም የበለጠ ነው፡፡

እንደ እኔ እና እናንተ ያለን ረዳት የለሽ ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር የድነት የምስራች ስናምን፣ እሱ ሐሳባችንን፣ ሰበባችንንም ፣ቃላችንን እና ድርጊታችንን ወደ እሱ መልክና ምሳሌ የመለወጡን ስራ የሚጀምረውን መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል። ይሄ የኃጢአት እርግማን የሚቀለብስበት የእግዚአብሔር ፕሮግራም ደረጃ ሁለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ልጆቹ የክርስቶስን ጠባይ እና አመል እንዲያንጸባርቁ ይፈልጋል። ክርስቲያን የሚለውም ቃል የዚህን እንድምታ የሚገልጥ ነው። ቢሆንም እንኳን እኔ የክርስቶስን መልክ የማስመሰሉ የመንፈስ ቅዱስ ቀጣይነት ያለው ሂደት ሲሆን የሚጠናቀቀውም እሱን ፊት ለፊት ስናየው ነው፡፡[253]

> "**የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤ እንዲሁም ነን**። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም፡፡

> ወዳጆች ሆይ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና **እርሱን እንድንመስል** እናውቃለን።" (1 ዮሐንስ 3:1-2 አመት)

የእግዚአብሔር ልጅ በእሱ ለሚያምኑ ሁሉ ከስራው የመዋጀት ስራ የተነሳ እና ለእሱ ለሚገዙ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰራው የመለወጥ ስራ የተነሳ የሠይጣን ኃይል ተሰብሮ የእግዚአብሔር መንግስት ፍቅር፣ ደስታ እና ሰላም ታድሷል።

በዓላማ ከተሞላው ሕይወታችን የተነሳ የእግዚአብሔር ፕሮግራም የመጨረሻ ደረጃ የሆነውን የሠይጣንን፣ የኃጢአትን እና የሞትን ለዘላለም መወገድ በጉጉት እንጠብቃለን።

ኢየሱስ ይመጣል።



# 29

# ደረጃ 3፦ የእግዚአብሔር የወደፊት ፕሮግራም

“የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች **ፈጥኖ** ይቀጠቅጠዋል።” (ሮሜ 16 ፡20 አመት)

ይሄ የአማኞች ተስፋ የሚመነጨው እግዚአብሔር ሐጢአት የሰው ልጅን ባረከሰበት ቀን ከተናገረው ምስጢራዊ የመጀመሪያ ትንቢት ነው፦የሴቷ ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል።

ፈጣሪና ባለቤታችን ተስፋ የሰጠውን በሙሉ ይፈጽማል። ነገር ግን የሚፈጽመው እንደ ራሱ አጀንዳ እና የጊዜ ሰሌዳ ነው።

## እርግማኑን መቀልበስ ፦ ደረጃ ሦስት

ተሰፋ የተገባው መሲህ ከመጣ በኋላ ሠይጣንን ያሸነፈው የሐጢአትን ቅጣት ሙሉ በሙሉ በመክፈል ነው። ለአማኙ ገነት መግባቱን እርግጠኛ ስለሆነ የሲዖል እጩ ሊሆን አይችልም። ከዚህም የተነሳ ሠይጣን ውድ መሳሪያው የሆነውን ሞትን አጥቶታል። የኅጢአት ቅጣት ተቀልብሷል።

ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ ሕዝቡን ሠይጣን እና ኅጢአት በዕለት ሕይወቱ ውስጥ የሚኖረውን ተጽዕኖ ለማሸነፍ እና ወደ እግዚአብሔር መልክ እንዲያበጃቸው “አጽናኙን” መንፈሱን ልኳል። የኅጢአት ኃይል እየተቀለበሰ ነው።

ነገር ግን ኢየሱስ ሠይጣንን የሚቀጠቅጥ እና ሕዝቡን ከኅጢአት ህልውና ነጻ የሚያወጣው ወደ ምድር ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ብቻ ነው።

## የሚመጡት ነገሮች

የእግዚአብሔር ነብያት አስቀድመው የመሲሁ የመጀመሪያ ምጽዓት እንደተነበዩት ሁሉ ሁለተኛ ምጽዓቱንም ተንብየዋል፡፡[254] የመጀመሪያው ጉብኝቱ በተነገረበት መልክእንደ ተፈጸመው ሁሉ ፣ መመለሱም እንደዚያው ይሆናል፡፡ ይሄ ነገር ከሰማይ የሚያስተጋባበትቀን እየተቃረበ ነው፦

> **"የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ፡፡"** (ራዕይ 11:15)

ጌታ ወደ ምድር በሚመለስት ጊዜ የአዳም ልጆች የእሾህ አክሊል አድርገው በመስቀል ላይ አይቸነክሩትም፡፡ ስሙንም በከንቱ አይጠሩም ወይም ከነብይ አይበልጥም አይሉም፡፡ እንዲህ አይነት ለንጉስ የማይመጥን አቀባበል ከዚህ በኋላ አማራጭ አይሆንም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው፡፡ ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ "ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል" (ኢሳያስ 45:23 ፤ ፊሊጲሲዩስ 2:9-11)፡፡ ነገር ግን ያ ነገር ከመሆኑ በፊት ሌሎች ተከታታይ ትንቢታት መፈጸም አለባቸው፡፡

## ደስታ በሰማይ

አሕዛብ በፈጣሪ ባለቤታቸው ፊት ፣ በጉልበታቸው ከመንበርከካቸው በፊት የሚሆን አንድ ነገር አለ እሱም ኢየሱስ የተቤዣቸውን ሰዎች ለመቀበል ወደ ምድር ከባቢ አየር ይወርዳል፡፡

> "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡ (1ተሰሎንቄ 4:16 -17)

ምስጥሩ ይሄ አሰገራሚ ክስተት በየትኛውም ጊዜ ሊከሰት መቻሉ ነው፡፡ በሚከሰትበት ጊዜ ነፍሳቸው በሰማይ የምትኖር አማኞቸች በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ካሉ አማኞች ሁሉ ጋር

“ጌታን በአየር ለመቀበል ይነጠቃሉ”፡፡ [255] በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞች በቅጽበት ክርስቶስን ወደ መምሰል ይለወጣሉ፡፡ ለዘላለም የሚያገለግል እና በጊዜ እና በቦታ የማይወሰን አዲስ አካል ይቀበላሉ፡፡

“በአየር ከተነጠቁ” ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ አማኞች ራስ ወዳድ ሳይሆኑ ለእግዚአብሔር ክብር እና ለሌሎች መባረክ ስላደረጓቸው ነገሮች ሽልማቶችን ይቀበላሉ፡፡ [256] በመቀጠልም የእግዚአብሔር ሕዝብ ለዘላለም “ቅዱስና ያለነቀፋ” ይሆናል በይፋም ለዘላለማዊ “ሙሽራው” [257] ከዘላለማዊ ፍርድ ሊያስመልጠው ራሱን ለሰጠው ለአሸናፊው አልፎ ይሰጣል፡፡

> “የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ፡፡ ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቶአታል፡፡ ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና፡፡ እርሱም፦ ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ፡፡ ደግሞም፦ ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው አለኝ፡፡”
> (ራዕይ 19:7-9)

ለዘላለም ደስ የሚያሰኘን ግንኙነት በምድር ላይ ከተለማመድናቸው ግንኙነቶች በሙሉ እጅግ በጣም የላቀ ነው፡፡

## መከራ ምድር ላይ

በዚህ መካከል ታች በምድር ላይ እግዚአብሔር በአልሸነፍ ባዩ ምድርላይ ቁጣው ያፈሳል፣ ለልጁ ዳግም ምጽዓትም መንገድን ያዘጋጃል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ “ታላቁ መከራ” [258] የሚለው ነገር ይከሰታል፡፡ ይሄ ጊዜ ሃገረ እስራኤልን ወደ ንሰሐ ለማምጣት የተዘጋጀ በመሆኑ “የያዕቆብ ታላቅ መከራ” (ኤርሚያስ 30:7) ተብሎ ተጠርቷል፡፡

በዚህ ጊዜ “ጸረ ክርስቶስ” እና “አውሬው” (1 ዮሐንስ 2:18 ፤ ራዕይ 13) ተብሎ የሚጠራ አሰደንጋጭ እና ሳያል ገዢ ወደ ሥልጣን ይመጣል፡፡ ብዙኸን በጭፍን እሱን እና ተዓምር አድራጊውን ሐሰተኛ ነብይ ይከተላሉ፡፡ በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ “የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፤ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው፡፡” (ራዕይ 13:16) ይደረጋል፡፡

አንገዛም ያሉ ሁሉ አንገታቸው ይቀላል። ሐሰተኛው መሲህ ሰላም እና ብልጥግናን ቃል ይገባል ነገር ግን ሰዎችን ወደ ስህተት፣ ጥፋት እና ሞት ይመራል።

## አርማጌዶን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ የእግዚአብሔር ነብያት ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ ወደ ምድር ሲወርድ እየተካሄደ ስለሚጠብቀው የመጨረሻው የዓለም ጦርነት ጽፈዋል። ይሄ አስገራሚ ጦርነት የሚካሄደው ኤስድራሎን በሚባለውና ከዮርዳኖስ ወንዝ ጀምሮ እስከ ሜድትራኒያን ባህር በተዘረጋው ሰፊ ክልል ላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን የወደፊት ጦርነት አርማጌዶን ማለትም የእልቂት ተራራ ሲል ይጠራዋል።

> "ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፣ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ። እነሆ፣ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው። በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተተቱአቸው።" (ራዕይ 16:14-16)

ነብዩ ዘካርያስ በዚያ ወቅት የመሲሁን መመለስ ተከትሎ ስለሚከሰቱ ነገሮች ግልጽ መረጃ ይሰጠናል።

> "እነሆ፣ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል... አሕዛብንም ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ እሰበስባለሁ፤ ከተማይቱም ትያዛለች፣ ቤቶችም ይበዘበዛሉ፣ ሴቶችም ይነወራሉ፤ የከተማይቱም እኩሌታ ለምርኮ ይወጣል፣ የቀረው ሕዝብ ግን ከከተማ አይጠፋም።" (ዘካርያስ 14:1-2)

"አሕዛብ ሁሉ" ኢየሩሳሌምን ይከብባሉ። ወደር የሌለው እልቂት ይሆናል።

## የመሲሁ መመለስ

ተስፋ ሁሉ በጠፋ ጊዜ የተረፉት የከተማዋ ነዋሪዎች ፣ ወደ ሰማይ ካልሆነ በስተቀር ረዳት ከየትም በማያገኙበት ጊዜ ፣ ጌታ

እንዲያድናቸው ይጣራሉ። ስሙ "ጌታ ያድናል" የሆነው እሱ ከሰማ ይወርዳል። እነሱን የሚያስደነግጣቸው እና እንግዳ የሚሆንባው አዳኛቸው ሌላ ሳይሆን የሰቀሉት **ኢየሱስ** መሆኑ ነው! ነገር ግን በዚህ ጊዜ በጥልቅ ንሰሐ እና የነፍስ መታወክ ንጉሳቸውን ይቀበላሉ።

> "የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፤ **ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ**፤ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፥ ሰውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል።"
>
> (ዘካርያስ 12:10)

በመጨረሻም መንፈሳዊ ዕውርነት የገጠመው የአይሁድ አይን ይከፈታል ፣ኢየሱስ አንዱ እና ብቸኛው መሲህ እንደነበረ እና እንደሆነ ያምናሉ።[259]

ቀጥሎ የሚከናወነው ነገር በዓለም ታሪክ ውስጥ ውጤታማ የሆነ የውጊያ ስልት የሚታይበት ነው፤ ቃል የሆነው ኢየሱስ ይናገራል፤ ጠላት ይቀልጣል።

> "እግዚአብሔርም ይወጣል፥ **በሰልፍም ቀን እንደ ተዋጋ ከእነዚያ አሕዛብ ጋር ይዋጋል**። በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ፤ ደብረ ዘይትም በመካከል ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ይሰነጠቃል፥ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል፤ የተራራውም እኩሌታ ወደ ሰሜን፥ እኩሌታውም ወደ ደቡብ ይርቃል።
>
> …እግዚአብሔርም ከኢየሩሳሌም ጋር የተዋጉትን አሕዛብ ሁሉ የሚቀሥፍበት ቸነፈር ይህ ነው፤ በእግራቸው ሲቆሙ ሥጋቸው **ይበሰብሳል**፥ ዓይኖቻቸውም በዓይነስባቸው ውስጥ **ይበሰብሳሉ**፥ ምላሳቸውም በአፋቸው ውስጥ **ይበሰብሳል**።
>
> አንድ ቀንም ይሆናል፥ እርሱም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ይሆናል፤ ቀንም አይሆንም፥ ሌሊትም አይሆንም፤ ሲመሽም ብርሃን ይሆናል።
>
> **እግዚአብሔርም በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል**፤ በዚያ ቀን **እግዚአብሔር አንድ፥ ስሙም አንድ ይሆናል።**"
>
> (ዘካርያስ 14:3-4 ፣ 12 ፣7 ፣ 9)

በመጨረሻም ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ይከብራል ይመሰገናል።

## ግዛትን ማስመለስ

ያነበብነውን ትንቢት ዘካርያስ ከመጻፉ ከአሥርት ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ተመሳሳይ የሆነ ትንቢት ለነብዩ ዳንኤል ሰጥቶት ነበር።

> "በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ **የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት** ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ **ግዛት**ና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ **ግዛቱ**ም የማያልፍ የዘላለም **ግዛት** ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።"
>
> (ዳንኤል 7:13-14)

ግዛት የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ ያህል ተጠቅሶ ነበር።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ወንድና ሴትን በፈጠረ ጊዜ "በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።" (ዘፍጥረት 1:26-28) ሰጥቷቸው ነበረ። አዳም በፈጣሪው ላይ ባመጸ ጊዜ ግዛቱን ለሰይጣን አስረበ። ነገር ግን "የመጀመሪያው ሰው" አዳም አሳልፎ የሰጠው ግዛት፣ ስልጣን እና ቁጥጥር ኢየሱስ "ሁለተኛው ሰው"[260] ያስመልሰዋል።

እግዚአብሔር ለኢየሱስ ደቀ መዝሙር ዮሐንስ፥ ከዘካርያስ እና ከዳንኤል ትንቢት ጋር ትይዩ የሆነ እና የተጣጣመ ትንቢት ሰጥቶት ነበር፦

> "ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም። ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፥ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፥ ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው፤ በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል፥ **ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል**። በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር። አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ

የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል። በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት፦ **የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ** የሚል ስም አለው።"

(ራዕይ 19:11-16)

የነገሥታት ንጉስ በሚመለስበት ጊዜ ዕልፍ አዕላፍ መላዕክት እና ቤዛነትን ባገኙ የአዳም ዘሮች "በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው" ታጅቦ ነው።[261] ኢየሱስ በመጀመሪያ ምጽዓቱ ወቅት በርህራሄ ያሳየው ሳይልና ሥልጣን በዳግም ምጽዓቱ ከሚታየው ገዷብ የሌላው ሳይል እና አስገራሚ ክብር ጋር ሲናጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

## የሰማይ አገዛዝ በሰዎች ልብ ውስጥ

እስቲ ንገሩኝ ጫካ ውስጥ እየሄዳችሁ ነው እንበልና ጫካ ውስጥ ማግኘት የምትፈልጉት ጠቦት ነው ወይስ አንበሳ ?

መሲሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድር ሲመጣ ሳጢአተኞችን ለማዳን እንደ "በግ" መጥቷል፤ ነገር ግን ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ሳጢአተኞች ላይ ለመፍረድ እንደ "አንበሳ" ይመጣል።[262]

ኢየሱስ ምድርን እየጎበኘ በነበረበት ጊዜ "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀረባለችና ንስሐ ግቡ።" (ማቴዎስ 4:17) ሲል ሰብኮ ነበር። የተሳሳተ ሐሳባቸውን በተመለከተ ንስሐ እንዲገባ እና ንጉሳቸውን እንዲ መቀበል፣ አይሁድና አሕዛብ ንጉሳቸውን ለመስቀል ተባበሩ። ስለዚህም መሲሁ የዓለም የሳጢአት ዕዳ ለመክፈል ዷሙን ያፈሳል የሚለውን ዘመናት የቆየ የእግዚአብሔር ትንቢት ያለፈቃዳቸው ፈጸሙ።

የምሥራቹ ሳጢአተኞች መታመናቸውን በጌታ ኢየሱስ እና ባደረገላቸው ነገር ላይ በሚያደረጉበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ ገዥ ይሆንና እነሱንም ለዘላለም ተገዢ ያደርጋቸዋል።

እያንዳንዱ እውነተኛ የክርስቶስ አማኝ የተመዘገበ የሰማይ ዜጋ እንደሆነ ታውቃላችሁ?

"እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤ እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፥ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።"

(ፊሊጲሲዩስ 3:20-21)

## የሰማይ አገዛዝ በምድር

ጌታ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ ምድርን ለሺህ ዓመታት በሚገዛበት በኢየሩሳሌም መንግሥቱን ይመሰርታል። በመጨረሻም መንግሥቱ ትመጣለች ፈቃዱም "በሰማይ እንደሆነች እንሁም በምድር" ማቴዎስ 6:10) በየትኛውም ሐገር ውስጥ እኩይ ቦታ አይኖረውም ምክንያቱም "እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል" (ራዕይ 19:15)

በዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር በአካል ይመለሳል ብለው አያምኑም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በግልጽ ይናገራል። የእግዚአብሔር ልጅ በመጀመሪያ ምጽአቱ ሥጋን እንደ ለበሰ በመቀጠልም ወደ ሰማይ ያረገው በአካላዊ እና ገደብ የለሽ ሥጋ እንደ መሆኑ መጠን የሚመለሰውም በሥጋ ነው። ወደ ሰማይ በተመለሰበት ቀን መላዕክቱ ለደቀ መዛሙርቱ የነገሯቸው ነገር ይኸው ነው፦

> "የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።" (ሐዋርያት 1:11)

## ሰይጣን ታስሯል

የእግዚአብሔር መጽሐፍ ሰለ ኢየሱስ የሚሊኒየም አገዛዝ ብዙ የሚለው ነገር አለው። ዋና ዋና ክስተቶቹን ብቻ መከለስ እንችላለን።

ኢየሱስ ወደ ምድር ከተመለሰ በኋላ ፣ የመጀመሪያ ስራው ከቀደመው "እባብ" ፣ የሰውን ዘር ራስን ወደ ማጥፋት መንገድ ከመራው ከሰይጣን ጋር የሚገናኝ ነው።

> "የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥ሺህ ዓመትም አሰረው፥ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።" (ራዕይ 20:1-3)

ሠይጣን ይታሰራል በተጨማሪም ለሺህ ዓመታት በሙሉ ቀሰባ ይገባል። ከፉው ታስሮ ፣ ጻድቁ ሲነግስ በመጨረሻ "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።" (ሉቃስ 2:14) ይሆናል።

ዓለም የሚናፍቀው የእግዚአብሔር የጽድቅ አገዛዝ እውን ይሆናል።

> "በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል... **ለዘላለምም ትቆማለች።"** (ዳንኤል 2:44)

## እውነተኛ መታዘዝ

ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት ንጉሱ ሰለሞን[263] በምድር ላይ የሚገኙ አሕዛብ እና ግለሰቦች በእውነተኛ መገዛት ሰለሚንበረከኩለት ሰለ መሲሁ የወደፊት አገዛዝ ጽፎ ነበር። ብዙኾን ለብቸኛው እውነተኛ አምላክ እንደሚገዙ ይናገራሉ ነገር ግን የዚያን ቀን ሁሉም ሰዎች በእርግጥ ያውቁታል ይገዙለታል።

> "በዘመኑም ጽድቅ ያብባል፣ ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው።
>
> ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፣ ከወንዝም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ **ይገዛል**። በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፣ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ። የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፤ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ። **ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል፣ አሕዛብም ሁሉ ይገዙለታል።**
>
> **ችግረኛውን ከቀማኛው እጅ**፣ ረዳት የሌለውንም ምስኪን **ያድነዋልና**። ለችግረኛና ለምስኪን ይራራል፣ የችግረኞችንም ነፍስ ያድናል። ከግፍና ከጭንቀት ነፍሳቸውን **ያድናል፤ ስማቸው በፊቱ ክቡር ነው። እርሱ ይኖራል** ከዓረብም ወርቅ ይሰጡታል፤ ሁልጊዜም ወደ እርሱ ይጸልያሉ፣ ዘወትርም ይባርኩታል።
>
> በምድር ውስጥ በተራሮች ላይ መጠጊያ ይሆናል፤ ፍሬውም ከሊባኖስ ይልቅ ከፍ ከፍ ይላል፤ እንደ ምድር ሣር በከተማ ይበቅላል። በምድር ውስጥ በተራሮች ላይ መጠጊያ ይሆናል፤ ፍሬውም ከሊባኖስ ይልቅ ከፍ

> ከፍ ይላል፤ እንደ ምድር ሣር በከተማ **ይበቅላል። ስሙ ለዘላለም ቡሩክ ይሆናል**፣ ከፀሐይም አስቀድሞ ስሙ ይኖራል፤ **የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ፣ አሕዛብ ሁሉ ያመሰግኑታል።** ብቻውን ተአምራትን የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ።
>
> የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ፤ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይምላ። ይሁን ይሁን።”
>
> (መዝሙር 72:7-19)

መዝሙሩ “እስከ ምድር ዳርቻም **ይገዛል**” ስለሚሆንበት የክርስቶስ የወደፊት መንግስት ግልጽ መረጃ ይሰጠናል።

## ፍጹም መንግስት

“የችግረኞችን ነፍስ ያድናል” የመሲሁ አገዛዝ ከነቀዘው፣ ረብሻ ከተሞላው የዛሬ ዓለም ፍጹም ተቃራኒ ይሆናል። ከውድቀት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃነት እና ፍትሕ ለሁሉ ይዳረሳል። የእያንዳንዱ ጭቅላ፣ ልጅ ፣ ሴት እና ወንድ ሕይወት ወደር የሌለው ዋጋ እንዳለው ታውቆ ይከበራል። “ያድናል። ከግፍና ከጭንቀት ነፍሳቸውን ያድናል፤ ስማቸው በፊቱ ክቡር ነው።”

የዜና ሚዲያው በተደጋጋሚ ፖለቲካዊ እና ሐይማኖታዊ መሪዎች ለሰላም እና የመሳሪያ ቅነሳን በተመለከ ድርድር እንዲደረግ በተደጋጋሚ ይማጸናሉ። ነገር ግን ካላቸው የተገደበ ሥልጣንና ኃይል የተነሳ፣እነዚህ ሰዎች እንፈልገዋለን የሚሉትን ሰላም ለመፍጠር አይችሉም። ማዕበሉና ወጀቡ የሚገዙለት እሱ ሲመለስ ግን ምድር እውነተኛ ፍትህ እና “የተትረፈረፈ ስላም” ታገኛለች።

በክፍለ ዘመናት መካከል ፣ የዚህ ዓለም ነገሥታት እና ገዢዎች ኖረው **ሞተዋል**። ነገር ግን ኢየሱስ፣ የነገስታት ንጉስ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው “ስሙ **ለዘላለም** የጸና ነው” ሐጢአትና ሞትን ባሸነፈው የሰው ልጅ አገዛዝ ስር ሆና ምድር ታይቶ የማይታወቅ ሰላምና በልጽግና በሺህ ዓመት ውስጥ ታገኛለች።

> “ነገሥታት ሁሉ **ይሰግዱለታል** ...ስሙ ለዘላለም ቡሩክ ይሆናል ...የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ... አሕዛብ ሁሉ **ያመሰግኑታል።**” (መዝሙር 72:11 ፣ 17)

ጌታ ራሱ ለደከመው ዓለም አይቶት የማያውቀውን ብቸኛ የጽድቅ አገዛዝ ይሰጠዋል፡፡
የእሱ አገዛዝ ከሙስና የጸዳ ይሆናል፡፡

"በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን **ሺህ ዓመት ይነግሣሉ፡፡**" (ራዕይ 20:6)

ምንም እንኳን ሁሉም የአገዛዝ አይነቶች ማለትም ፣ ንጉሳዊ ፣አምባገነን፣ ዲሞክራያዊ፣ ሐይማኖታዊ አገዛዞች ባይሳኩም፥ የእሱ አገዛዝ ግን አይወድቅም፡፡
የእሱ አግዛዝ ልክ እንደሱ ፍጹም ነው፡፡

## የሰላም ንጉስ

አሰቀድመን የክርስቶስን የመጀመሪያ ምጽዓት የሚመለከቱ ትንቢቶችን በተመለከተ ተነጋግረን ነበር፡፡ ለምሳሌ ነብዩ ሚክያስ መሲሁ በቤቴልሄም እንደሚወለድ ተናግሮ ነበር፡፡ ነገር ግን የሚኪያስ ትንቢት በተጨማሪ መሲሁ አንድ ቀን ምድርን ሁሉ እንደሚገዛ መናገሩን ልብ ብላችኋል?

"አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡ ...**እርሱ አሁን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናልና፡፡ ይህም ለሰላም ይሆናል**" (ሚክያስ 5:2 ፤ 4-5)

በሚኪያስ ዘመን የኖረው ኢሳያስ ወንድ ልጅ እንደሚወለድ፣ ዘላለማዊ ልጅ እንደሚሰጠን ትንቢት ተናግሯል፡፡ በተጨማሪም የኢሳያስ ትንቢት የወልድን ዓለም አቀፋዊ አገዛዝ አስቀድሞ አመልክቷል፡፡

"ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ **አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል**፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ

> በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና **በመንግሥቱ ላይ** አለቅነቱ ይበዛል፥ **ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም።** የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።" (ኢሳያስ 9:6-7)

በመጨረሻም ምድር ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጅ በትክክለኛ መጠሪያው ይጠራዋል።

"ስሙም ድንቅ መካር፥
ኃያል አምላክ፥
የዘላለም አባት፥
የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።"

አሕዛብም ፍትህን እና ሰላምን "ከዛሬ ጀምሮ **እስከ ዘላለም**" ያገኛሉ

የእግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር የመሆን ምኞት ይሳካል። ለዘላለም።

> "ብዙ አሕዛብ **ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ**፥ ሕዝብም ይሆኑኛል፤ **በመካከልሽም እኖራለሁ**፥" (ዘካርያስ 2:11)

የዛሬው የምሥራች የክርስቶስ መንፈስ በልባቸው የሚኖር ሰዎች የእግዚአብሔር መገኘት እና ሰላም አሁን ይኖራቸዋል።

## አላዋቂነት ያበቃል

ጌታ ከዚህ በፊት ከሰዎች ጋር በዚህ ምድር በኖረ ጊዜ ብዙ ሰዎች የእነሱን ማንነት መረዳት ሳይችሉ ቀርተዋል። እስከ ዛሬ ድረስ በዙኽን ኢየሱስ ንጉሳቸው መሆኑን አልተገዘቡም። ቢሆንም እንኳን እያንዳንዷ ነፍስ ያለውን እንደሆነ እውቅና የምትሰጥበት ወርቃማ ዘመን መጥቷል።

> "እንዲህ ይሆናል፤ በየመባቻውና በየሰንበቱ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ዘወትር ይመጣል፥ **ይላል እግዚአብሔር።**" (ኢሳያስ 66:23)

(Ishacyaah 66:23)

ከዚህ በኋላ ምድርን የተለያዩ ሐይማኖቶች ፣ ቤተ እምነቶች እና ኑፋቄዎች አይሞሏትም። በተጨማሪም የኢየሱስን በታሪክ

ውስጥ መኖር የሚክድ፣ የእግዚአብሔር ልጅነት፣ በመስቀል ላይ መሞቱን እና ከሞትም እንደገና መነሳቱን የሚክድ ማንም ሰው አይኖር ም። ምንም እንኳን ሁሉም ሰው በእሱ ያምናል ባንልም፣ ሁሉም ሰው ግን ስለ እሱ መልዕክት ያውቃል።

> "እነሆ፥ ነፍሱ ኰርታለች፥ በውስጡም ቅን አይደለችም፤ ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል።" (ዕንባቆም 2:14)

## ጦርነት አይኖርም

ጌታ ምድርን ሁሉ በሚገዛበት ጊዜ በሰሜን እና ደቡብ ፣ በምስራቅና በምዕራብ መካከል ያለው ግጭት ያለፈ ይሆናል። በእስራኤልና በዙሪያዋ ባሉ ሃገራት መካከል ያለው ግጭት ያቆማል። አስቃቂው የአፍሪካ አህጉር መከራ ያበቃል። ይሄም ሌሎቹን አህጉራት ይመለከታል። የሕዝብ ለሕዝብ ጦርነት እና ጭቆና ያበቃል። እውነተኛ ሰላም፣ ብልጽግና እና ባለ ዓላማ ምድርን ያጥለቀልቃል።

> "**ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና** ብዙዎች አሕዛብ ሄደው፦ ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፥ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፥ በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ።
> 
> በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፥ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል ሰይፋቸውንም ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቀጣሉ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፥ **ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም።**" (ኢሳያስ 2:3-4)

ሰዎች ብቸኛውን እውነተኛ አምላክ ሲያውቁ ሰላም እና አንድነት ዓለም አቀፋዊ ይሆናል።

የባቢሎን ግራ መጋባት ይቀለበሳል። በድጋሚ ምድር ሁሉ አንድ ቋንቋ ይናገራል።

> "በዚያን ጊዜም አሕዛብ ሁሉ አንድ ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ ስሙን እንዲጠሩ ንጹሐን ልሳን እመልስላቸዋለሁ።" (ሶፎንያስ 3:9)

## እርግማን ይወገዳል

ከሺው ዓመት ብልጥግና በተጨማሪ ፣ ጌታ ከኃጢአት የተነሳ በምድር ላይ የመጣውን እርግማን ያነሳል።

ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ዘመን እርግማኑን መቀልበስ የሚያስችል ብርታቱን አሳይቷል። አጋንንትን አስወጥቷል፣ አካለ ጎዶሎነትን አስተካክሏል፣ የታመሙትን ፈውሷል፣ የሞቱት አስነስቷል፣ ብዙሺንን መግቧል እና በተፈጥሮ ላይ ያለውን ፍጹም የበላይነት አሳይቷል።

ጌታ ኢየሱስ በመጀመሪያ ምጽዓቱ በናሙና መልክ ያሳየው ነገር ፣ በዳግም ምጽዓቱ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይከናወናል።

ሠይጣን እና አጋንንቱ ይታሰራሉ። አካለ ጎዶሎነትን ፣ በሽታን እና በተፈጥሮ ምክንያት የሚከሰትን ሞት ያሰወግዳል። ምድርም እሾህና አሜኬላ ከዚህ በኋላ አታበቅልም። ገበሬዎች ከዚህ በፊት አይተውት በማያውቁት መጠን የተትረፈረፈ ሰብል ያጭዳሉ። ድህነት እና ረሃብ ጊዜ ያለፈባቸው ቃላት ይሆናሉ።

እያንዳንዱ ሃገር ይሄን የዓለም ታሪክ ወርቃማ ዘመን ይለማመዳል።

በኢየሱስ የመጀመሪያ ምጽዓት በምድራውያን ዜጎች ተቀባይነት ያላገኘው የሰማዩ መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ በዳግም ምጽዓቱ ይመሰረታል።

> “በዚያን ጊዜም የዕውሮች ዓይን ይገለጣል የደንቆሮችም ጆሮ ይከፈታል። በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘልላል፥ የድዳም ምላስ ይዘምራል፤ በምድረ በዳ ውኃ፥ በበረሀም ፈሳሽ ይፈልቃልና። …ተኵላና ጠቦት በአንድነት ይሰማራሉ፥ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል፥ **የእባብም መብል ትቢያ ይሆናል**። በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ አይጐዱም፥ አያጠፉምም፥ ይላል እግዚአብሔር።”
>
> (ኢሳያስ 35:5-6 ፤ 65:25)

የእንስሳት ዘሮች እንኳን ሳይቀሩ በሰላም ወደ ሳር በልነት ተቀይረው በሰላም ይኖራሉ ፣ በተጨማሪም በኤደን ገነት የነበረው ሁኔታ ይመለሳል።

ቢሆንም እንኳን በኢየሱስ የሺህ ዓመት አገዛዝ ውስጥ የተወለዱ ሰዎች ልብ ውስጥ የኃጢአት ስር ይገኛል። በየትኛውም ዘመን እንደሆነው የአዳም ዘሮች በእግዚአብሔር የድነት አቅርቦት በማመን የእግዚአብሔርን ይቅርታ መቀበል መቻል አለበት።

በመጨረሻ ያነበብነው ጥቅስ ስለ ዘንዶው ምን እንደሚናገር አስተውላችኋል? "የእባብም መብል ትቢያ ይሆናል፡፡" በሺው ዓመት ወቅት እባቦች በደረታቸው መሳባቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የእነሱ በደረታቸው መሳብ እግዚአብሔር እርግማንን ለመቀልበስ ያወጣው ዕቅድ በሦስተኛው እና በመጨረሻው ደረጃ ትዕይንታዊ ክስተት እንደሚቀር ያመለክታል፡፡

## የከፉው የመጨረሻ ሙከራ

አስቀድመን እንደተነጋገርነው "የጥንቱ እባብ ዲያብሎስ ሰይጣን" በክርስቶስ የሺህ ዓመት አገዛዝ ወቅት ታስሮ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ይቀመጣል "የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፤ሺህ ዓመትም አሰረው፤ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤ **ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል፡፡**" (ራዕይ 20:2-3)

እግዚአብሔር ሰይጣንን የሚለቀው ለምንድን ነው? ለምን እዚያው ቆልፎበት አያስቀምጠውም?

ጌታ በጥልቅ እውቀቱ የሰው ልጅ ኃጢአተኛ ፤የወደቀ ልብ እኩይ ለመጨረሻ ጊዜ ከመወገዱ በፊት መጋለጥ መቻል አለበት፡፡ የሰው ልጅ ከጊዜ ወደ ዘላለም ሲሸጋገር ፤ ይሄ እውነት በገኸድ ይታያል፡ የአዳም ዘሮች ከወደቀው ማንነታቸው የተነሳ የተለየ ነገር ለማድረግ አቅም የላቸውም፡፡ ኃጢአተኞችን ጻድቅ ሊያደርግ እና አፈንጋጭ ልባቸውን ሊለውጥ የሚችለው ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

> "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኵላሊትንም እፈትናለሁ፡፡"
>
> (ኤርሚያስ 17:9-10)

የሰው ልብ ምን ያህል "እጅግም ክፉ ነው" ነው? ለሺህ ዓመታት ያክል ፍጹም በሆነ ሁኔታ ውስጥ፣ ፍጹም በሆነ መንግሥት እና ፍጹም በሆነ ንጉስ አገዛዝ ስር እየኖረ እንኳን፣ ሠይጣን በተለቀቀበት ቅጽበት በሺው ዓመት ውስጥ የተወለዱ ሰዎች የሠይጣንን ውሸት አምነው ከሠይጣን ጋር ይወግናሉ!

ከእግዚአብሔር ጠላት ጋር ሳይላቸውን ያስተባብራሉ ፣ ቀደምት ወላጆቻቸው እንዳደረጉት በፈጣሪያቸው ላይ ያምጻሉ።

ይሄ የእኩይ የመጨረሻ ሙከራ ይሆናል።

## የሠይጣን የመጨረሻ ሙከራ።

> “ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፣በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው። ወደ ምድርም ስፋት ወጡ የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ **እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው።**” (ራዕይ 20:7-9)

ጌታ የሠይጣን ሌጌዎን አመጸኛ ሕዝብ ኢየሩሳሌምን እንዲከብ ይፈቅዳል ነገር ግን እየተሰባሰብቡ እያሉ ከሰማይ እሳት ወርዶ ይበላቸዋል። ሠይጣን እና ከእሱ ጋር የወገኑ ሁሉ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር።

## ዘንዶው ተቀጠቀጠ

ከዚህ ቀጥሎ የሚሆን በታሪክ ውስጥ እጅግ አሰገራሚ ክስተት ነው፦

> **“ያሳታቸውም ዲያብሎስ** አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት **ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ**፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።
>
> **ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም። ባሕርም** በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ።
>
> ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። **ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።**” (ራዕይ 20:10-15)

በዘመናት መካከል የዘለቀው ግጭት ያበቃል።

የታልቁን የነጭ ዙፋን ፍርድ ተከትሎ የኅጢአት እርግማን ታሪክ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር እኩይን ከቀጣበት መንገድ የተወሰደው ትምህርት ግን ለዘላለም አይረሳም። ፍጥረት ሁሉ የኅጢአትን አሰቀያሚነትን እና የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ይገነዘባል።

በመጨረሻም የሠይጣን ራስ የፈርሳል።

ሠይጣን እና የተከተት ሁሉ "ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት" (ማቴዎስ 25:41) ይገባሉ። የተፈረደባቸውም ከዘላለማዊው እስር ቤት አያመልጡም። ለቅጣታቸውም እግዚአብሔርን አይከሱም ምክንያቱም ምንም እንኳን ለሺ ዓመት በፍጹም ምድር ላይ በፍጹም ነጉስ ስር ለሺህ ዓመት እንዲኖሩ ቢባርካቸውም በፈጣሪ ባለቤታቸው ላይ ማመጽን ምርጫቸው አድርገዋል።

የሰው ልጅ ምክንያት አይኖረውም።

የብቸኛው እውነተኛ አምላክ ስምና መልዕክት እውነተኛነት ለዘላለም ይረጋገጣል።

ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ ሁሉ ለዘላለም ከጌታ ጋር ይሆናሉ "ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኛዎችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።" (ራዕይ21:8)[264]

እኩይም ዳግመኛ አሰቀያሚ ማንነቱን አያሳይም።

## ከእሱ ጋር!

ከዚህ ቀጥሎ የሚሆነው ነገር ሲያስቡት እንኳን በጣም የሚያስደንቅ ነው።

> "ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፦ እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናልእንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። በዙፋኑም

> የተቀመጠው፦ እነሆ፣ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፦ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ።" (ራዕይ 21:3-5)

የመጀመሪያዎቹ ብሉይ ኪዳን ሁለት ምዕራፎች የእግዚአብሔርን ፍጥረት እንደሚገልጡ ሁሉ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ደግሞ የእግዚአብሔርን አዲስ ፍጥረት ይገልጣሉ። ሠይጣን፣ ኅጢአት እና ሞት ስለተወገዱ ሁሉ ነገር እንደገና ከፈጣሪ ቅዱስ ባህርይ ጋር የተስማማ ይሆናል። ከዚህ በኋላ ሰዎችም ቢሆኑ መላዕክት ለኅጢአት የተገዙ አይሆኑም። ተገቢው ትምህርት ተወስዷል በተጨማሪም "እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል"

የእግዚአብሔር ፕሮግራም የአዳምን ኅጢአት ከማስወገድ ያለፈ ነገር አለው። ይሄም "ሁሉን ነገር አዲስ" ማድረግን ያካትታል። የጌታ ሕዝብ ለእሱ አንጸባራቂ መገኘት ብቻ የተገቡትን ሰማያውያን አካላት ያያሉ። ለዘላለምም ከእያንዳንዱ ሕዝብ እና ዘመን ቤዛነትን ያገኙ ሰዎች በአሰደናቂው እና የጊዜ ገደብ በሌለው ዕቅድ ውስጥ ተሳታፊ ይሆናሉ። እንደ አማኞች ከእሱ ጋር ለዘላለም መኖር ደስታችን ነው ፤ እኛም በዚያ በመኖራችን እሱም ይደሰታል።

"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" የሚለው ጭብጥ ሙሉ በሙሉ እውነት ይሆናል።

## እንደሱ!

በተቤዣቸው እና በሕዝቡ መካካል ያለው የሚያስደስት ኅብረት አያበቃም። አዳም በምድራዊ ገነት ያገኘው ነገር ሙሉ በሙሉ ከዚያም በበለጠ ሁኔታ እንደገና ይመለሳል። እግዚአብሔር የመጀሪያዎቹን ወንድና ሴት ሊፈጥር ሲል እንዲህ ብሎ ነበር፣

> "ሰውን **በመልካችን** እንደ **ምሳሌአችን** እንፍጠር።" (ዘፍጥረት 1:26)

ሁሉ ነገር እሱ እንዳቀደው ይሆናል።

ሰማይ በጠባያቸው እና በአመላቸው **የእሱን** መልክንና ምሳሌ በያዙ ሰዎች ትሞላለች። ኅጢአት ሊከሰት የሚችልበት ዕድል እንኳን አይኖረውም። የእግዚአብሔር ሕዝብ በጽድቅ ይሞላል። ነብዩ ዳዊት ይህንን አይቶ እንዲህ ብሎ ጽፏል፦ "እኔ ግን **በጽድቅ** ፊትህን አያለሁ፤ **ክብርህን** ሳይ እጠግባለሁ።" (መዝሙር 17:15)

ቤዛነትን ያገኙ ወንዶች፣ ሴቶች እና ልጆች በእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት ውስጥ “ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ” (ሮሜ 8:29) ሆነው ለዘላለም ይጠበቃሉ።

> “ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና **እርሱን እንድንመስል** እናውቃለን።” (1 ዮሐንስ 3:2)

**ለሱ!**

ከመጀመሪያም ጀምሮ የፈጣሪ ዓላማ የእሱን ክብር፣ ንጽሕና ፍቅር፣ ፍትሒ ምሕረትና ጸጋ እንድናውቅ በሰው ልጆች መካከል እንዲታወቅ መንግስቱን መመስረት ነበር።

ከሰይጣን ጋር በነበረው ረጅም ጦርነት የእግዚአብሔር ዕቅድ “ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን ተርኮአል።” (ሐዋርያት 15:14) ነበር። ጌታ ምድር ላይ ሊያገኘው የመጣውን ነገር ያገኛል፦ በምስጋናና በአድናቆት ከተሞላ ልብ እሱን የሚወድ፣ በእሱ የሚደሰት እና ለዘላለም የሚያመሰግነው በመልኩ የተቤዠው ሕዝብ ነው።

ሦስተኛውና የመጨረሻ የእግዚአብሔር እርግማን የመቀልበስ ስራ በየትኛውም ጊዜ ሊጀምር ይችላል። ዝግጁ ናችሁ? የኢየሱስ የመመለስ ዜና የሚሞላችሁ በደስታ ነው ወይስ በፍርሃት ?

መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ በዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጉዞ በምናደርገበት መጽሐፍ ለመዳሰስ ጊዜ የሌለን በርካታ ፍንጮችን ይሰጠናል። ለአሁን ታማኙ ፈጣሪያችን በመጽሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ ተቀብሮ በምትገኝ ትንሽ ትንቢት ማብቃት መልካም ነው፦

“ከእንግዲህም ወዲህ **መርገም ከቶ አይሆንም።**” (ራዕይ 22:3)

# 30

# የገነት ቅምሻ

አብዛኛው ዓለም እኩይን በተመለከተ ያለው አመለካከት የዩንግ ያንግ አመለካከት ነው፡፡ ዩንግ ማለት ጨለማማ ማለት ያንግ ማለት ደግሞ ጸሃያማ ማለት ነው፡፡ የዩንግ ያንግን ምስል አይታችሁ ጥቁር እና ነጭ በተለየ ሁኔታ የተደባለቁበት ክብ ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ ጥንታዊ የቻይና ፍልስፍና እውነት ቢኖረውም በመልካም እና እኩይ፣ በትክክልና በስህተት፣ በሕይወት እና በሞት መካከል ያለውን ክፍተት ያደበዝዛል፡፡ መልካምን እና እኩይን እንደ ተፈጥሯዊ እና የሰው ልጅ ሕልውና ዘለቄታዊ ገጽታ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡

እንዳየነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መልካም እና እኩይ የተለየ ትንታኔ ይሰጣል፡፡ መከራ እና ሐዘን የአጽናፈ ዓለሙ ዕምብርት ነበሩ፤ ናቸውም፣ የሚለውን ሐሳብ አይደግፍም፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ ናቸው፡፡ እኩይ፣ ሕመም እና ሞት የመጨረሻ ሽንፈታቸውን የሚሸነፉበት እንና ከዓለም ታሪክ ላይ የሚመጡበት ቀን እየመጣ ነው፡፡

የሚከተለው ምስል የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ፕሮግራም ያሳያል፦

| ← **ዘላለም** | [ጊዜ] | ዘላለም → |
|---|---|---|
| **ፍጹም መልካም** | **[መልካም/ ዕኩይ]** | **ፍጹም መልካም** |

የአሁኑ የመልካም እና የእኩይ ድብልቅ የሚገኘው በቅንፍ ውስጥ ነው፡፡ ለዘላለም አይኖርም፡፡[265]

የመጀመሪያዎቹ እና የመጨረሻዎቹ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ምዕራፎች ከኀጢአት ነጻ የሆነ ፣ እግዚአብሔር

ትክክለኛው መንገድ ሚወደድበትን እና የሚከበረበትን ከኅጢአት ነጻ የሆነ ዓለም ያሳያሉ። እግዚአብሔር ኅጢአትንና እርግማንን ለማስወገድ እና እሱን የሚያውቁ ፣ እሱን የሚወዱ እና ዘላለምን ከእሱ ጋር ለማሳለፍ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመቤዠት እየሰራ የምናየው በእነዚህ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ምዕራፎች ነው።

ልክ እንደ የትኛውም መልካም ታሪክ የእግዚአብሔር የመቤዠት እቅድ መጀመሪያ ፣ መካከል እና ፍጻሜ አለው።

**ጅማሬ**፦ ዘፍጥረት 1 እና 2 ፦
ፍጹም ዓለም - እኩይ ከመግባቱ በፊት።
**መካከል**፦ ዘፍጥረት 3 -ራዕይ 20 ፦
የተበላሸ ዓለም - የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት።
**ፍጻሜ**፦ ራዕይ 21 እና 22 ፦
ፍጹም ዓለም - እኩይ ከተወገደ በኋላ።

## የፍጻሜዎች መጽሐፍ

ልክ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ የጅማሬ መጽሐፍ እንደሆነ ሁሉ የመጨረሻውም መጽሐፍ የፍጻሜ መጽሐፍ ነው።

| **Bilowgii** | **Muujintii** |
|---|---|
| ◊ የሁሉ ነገር ጅማሬ | √ የሁሉ ነገር ፍጻሜ |
| ◊ የሰማይና የምድር መፈጠር | √ የአዲስ ሰማይ እና የአዲስ ምድር መፈጠር |
| ◊ እግዚአብሔር ፀሐይን ለምድር ፈጠረ | √ እግዚአብሔር የሰማይ ብርሃን ነው |
| ◊ ሠይጣን የሰው ልጅን ለመጀመሪያ ጊዜ ፈተነ | √ ሠይጣን የሰው ልጅን ለመጨረሻ ጊዜ ፈተነ |
| ◊ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ፍርድ | √ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ |
| ◊ የኅጢአት እና ሞት መግባት | √ የኅጢአትና ሞት መወገድ |
| ◊ "የመጀመሪያው አዳም" ገዢነትን አጣ | √ "ኋለኛው አዳም" ገዢነቱን አስመለሰ |
| ◊ እግዚአብሔር ሠይጣንን እንደሚቀጠቅጥ ቃል ይገባል | √ ሠይጣን ወደ እሳት ባህር ተጣለ |
| ◊ የመጀመሪያው ጠቦት ተሰዋ | √ የእግዚአብሔር በግ ከበረ |
| ◊ ሰው ምድራዊ ገነትን አዘጋጀ | √ ሰው በሰማያዊ ገነት ውስጥ |

| | |
|---|---|
| ◊ የሰው ልጅ ከሕይወት ዛፍ ተለየ | √ የሰው ልጅ ከሕይወት ዛፍ በላ |
| ◊ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ተለየ | √ የዳነው የው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም |

ዝርዝሩ ይቀጥላል ነገር ግን ሐሳቡ ገባቻሁ።

## ራዕይ

የጋራ ጉዟችንን ስናጠናቅቅ ፍጹም አዲስ የሆነ ጅማሬ ምርቃት ስለሆነው የእግዚአብሔርን ታሪክ"ፍጻሜ" ትንሽ እንነጋገር።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ መጽሐፍ እንዲህ ብሎ ይጀምራል፦

> "ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፤ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፤ እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ። ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን **ናቸው። ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፤መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን። እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል**፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን። ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፦ አልፋና ዖሜጋ [የግሪክ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ፊደላት ]እኔ ነኝ ይላል።"
>
> (ራዕይ 1:1-3 ፣ 5-8) [266]

እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት የሰጠው "ለአገልጋዩ ዮሐንስ" ነው"። ዮሐንስ በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ወቅት ይከተሉት ከነበሩ አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ነበር።[267] ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከተመለሰ ከስልሳ ዓመታት በኋላ በእግዚአብሔር ቤተ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን ይህንን የመጨረሻ መጽሐፍ እንዲጽፍ የእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሳው።

ራዕይ ማለት መግለጥ ማለት ነው። ይሄ አሰገራሚ መጽሐፍ የትኛውም የሰው ልጅ ሊያስበው የማይችለውን ክስተት ይገልጣል። ጌታ ቅዱስ ስሙን እንደሚጠብቅ እና የሰው ልጅ በኅጢአት ምክንያት ያጣውን አገዛዝ እንደሚያሰልስ ይናገራል። በተጨማሪም ይሄ መጽሐፍ የገነትን ቀምሻም ይሰጠናል።

## ዙፋኑ

የተመረጡ ጥቂት ነብያት እና ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ማደሪያ በጨረፍታ እንዲያዩ ተፈቅዶላቸው ነበር፤ ነገር ማንኛቸውም እንደ ሐዋርያው ዮሐንስ በበለጠ ግልጽነት አላዩም። ዮሐንስ እንዲህ ይላል፦

> "ከዚያ በኋላም አየሁ፥ **እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ**፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፦ ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ። ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፥ **ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ**፤ተቀምጦም የነበረው በመልኩ የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቍ [ሁለት የከበሩ ድንጋዮች[268]]ይመስል ነበር። በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ።" (ራዕይ 4:1-3 አመት)

ዮሐንስ ሰማያዊውን የዙፋን ቤት ለመግለጥ ተፍጨርጭሯል። በቃላት ሊገለጽ በማይችል ሁኔታ ውብ ነው። በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ እየበረሩ ያለማቋረጥ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም" (ራዕይ 4:8) የሚሉ መላዕክት ነበሩ።

ዮሐንስ የሚዘግበው ምድር ላይ እሱን በትንሹ የሚመስል ነገር ሲያገኝ ብቻ ነው ነገር ግን ሁሉም ነገር ከመጠን በላይ ውብ እና መሳጭ ነው። የሚያብረቀረቅ እና ቦግ ያለ መለኮታዊ ቀለም ያለው ብርሃን አየ። በደስታና በምስጋና የተሞላ ድምጽ ያላቸው እልፍ ሰዎችን የሚያሰገመግም ድምጽ ሰማ፤ ነገር ግን የዮሐንስን ቀልብ የተቆጣጠረው በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ነው።[269]

## ደስታው

በምድር ላይ የሚገኙ ሐይማኖቶች ገነትን በተለያየ መልኩ ይገልጣሉ።

አንዳንድ አገላለጾች ደባሪዎች ናቸው። ምናልባትም አንድ የካርቱን ፊልም አይታችሁ ከሆነ፥ ሰዎች በደመና ላይ ክብ ሰርተው ተቀመጠው በሳላፊነት ስሜት በገናቸውን ያነሳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን አሰገራሚ ማደሪያ የሚገልጠው በዚህ አይነት መንገድ አይደለም።

ሌሎች ደግሞ ገነትን ወንዶችን ያማከለ እና የማያቋርጥ ሴሰኝነት ያለበት አድርገው ያቀርቡታል። ይሄ ጽንሰ ሐሳብ ስህተት ነው። ጌታ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በአባቱ ቤት ቤዛነትን ያገኙሰዎች "በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም።" (ማቴዎስ 22:30) ተናግሮ ነበር።

ገነት እግዚአብሔር ማዕከል ያደረገ ክልል ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት ገደብ የሌለው ጥበብ እና ፍቅር የማይደበዝዝበት ደስታ ፣መገረም ፣ እና ፈንጠዝያ ያለበት ቦታ ነው። ገነት በምድር ላይ ከምናውቀው በበለጠ ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝበት ነው። እግዚአብሔር ጋብቻን የፈጠረው በጌታና እና እሱ በበተቤዠውዠው ሕዝብ መካከል የሚኖረውን የከበረ ግንኙነት በስሱ እንዲያሳይ ነው። በምድር ላይ የሚገኝ ምርጡ ትዳር በክርስቶስ አንድ የሆኑ ሰዎች ከሚያገኙት ደስታና የተቀደሰ ወዳጅነት ጋር ሊስተካከል አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ይሄንን "ታላቅ መሥጢር" (ኤፌሶን 5:32) ይለዋል። በተጨማሪም "ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ።" (ራዕይ 19:9) በማለት ይቀጥላል።

ገነት ከእሱ ጋር መሆን ላይ የሚያተኩር ብቻ ነው።

ሊቆጠሩ የማይችሉ ሺህ ዓመታት በፍት የተፈጠሩት መላዕክት ከመቼውም ግዜ በበለጠ በእግዚአብሔር መገኘት የሚገረሙት አሁን ነው። የጌታ እግዚአብሔርን ክብር፣ ጥበብ እና ፍጽምና ለመረዳት ዘላለም ሁሉ ያስፈልገናል።

> "አቤቱ፥ አሳቦቹህ በእኔ ዘንድ እንደ ምን እጅግ የተከበሩ ናቸው! ቍጥራቸውም እንደ ምን በዛ!ብቈጥራቸው ከአሸዋ ይልቅ ይበዛሉ፤ ተነሣሁም፥ እኔም ገና **ከአንተ ጋር ነኝ።**" (መዝሙር 139:17-18)

ከጌታ ጋር መሆን የሚያስገኘው ደስታ እና ፈንጠዝያ እያረጀ የሚሄድ አይደለም። ጥያቄው መሆን ያለበት ሊደብረን ይችል ይሆን፥ ሳይሆን እይኖቻችንን ከእሱ ላይ ማንሳት እንችላለን ወይ የሚለው ነው?

> “የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ **ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ**፥ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ።”
> (መዝሙር 16:11)

## ብዙኸን

ሐዋርያው ዮሐንስ ጌታን በዙፋኑ ላይ ያየው በጨረፍታ ነው፤ በተጨማሪ ግን ቤዛነት ያገኙ ብዙኸንን ግን አይቷል።

> “ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ **አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ**፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፦ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።”
> (ራዕይ 7:9-10)

እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ለሚገኙ አሕዛብ እና ሕዝቦች በረከትን ከአብርሐም ፣ከይስሐቅ እና ከያዕቆብ ዘር በሚወድለው አዳኝ በኩር ሊሰጥ እንዴ ተስፋ እንደገባ ታስታውሳላችሁ?[270] እግዚአብሔር ዮሐንስን የዚህን ተስፋ የወደፊት ፍጻሜ እንዲያይ እና እንዲመሰክር ፈቅዶለታል።

በምድር ላይ የሚገኝ እያንዳንዱ የሕዝብ ወገን፣ እያንዳንዱ ሃገር እና እያንዳንዱ ቋንቋ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ይወከላል። በምስጋና እና በደስታ ድምጽ እነዚህ የማይቆጠሩ የኀጢአት ስርየት ያገኙ ብዙኸን እነሱን ከዘላለማዊ ሞት ነጻ ለማውጣት እና በዘላለም ሕይወት ለመባረክ ደሙን ያፈሰሰውን በግ ለዘላለም ያመሰግኑታል ያመልኩታልም።

> “መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፤ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።
>
> በታላቅም ድምፅ፦ **የታረደው በግ** ኀይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል **ይገባዋል** አሉ።” (ራዕይ 5:9-12)

**ተቤዢዬ !**

ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ነብዩ ኢዩብ እንዲህ ሲል አመስግኗል፦

> “**እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ**፥ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ **እንዲቆም፥ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፥ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ**። እኔ ራሴ አየዋለሁ፥ **ዓይኖቼም** ይመለከቱታል፥ ከእኔም ሌላ አይደለም።” (ኢዮብ 19:25-27)

ልባችሁ እንደ ኢዮብ ልብ “እግዚብሔርን ማየት” ይጓጓል? የተቤዣችሁን ታውቃላችሁ?

ሁሉም እውነተኛ አማኞች የኢዮብን ተስፋ ይጋራሉ። ወዳጄ አንተን ወክዬ መናገር አልችልም ነገር ግን አዳኜን ፊት ለፊት እንደማየው አውቃለሁ! ከእሱ ጋር ብሬን እንደምመላለስና “በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ” (ገላትያ 2:20) እንደማወራው አውቃለሁ።

አዎ ከተለያየ ዘመን ከሚገኙ ክርስቲያኖች ጋር ፣ በጌታ ከሆኑ ቤተሰቦች እና ወዳጆቼ ጋር የማሳልፈውን አስገራሚ የኅብረት ጊዜ እናፍቃለሁ። በሙሉ ልቤ ደግሞ አንተም ከእነሱ መካከል ትኖራለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ከሁሉ በላይ ግን ኢየሱስን ማየት እፈልጋለሁ!

ሲዖሌን የወሰደልኝ እሱ ነው።

ያለምንም ጥያቄ በአዕምሮዬ ውስጥ የሚመላለሰው አስገራሚ እውነት የሚከተለው ነው፦

**ከእሱ** ጋር ለዘላለም እንድሆን ይፈልጋል!

ኢየሱስ ለፈረድበት እና ለሲቀል በታሰረበት ምሽት እንዲህ ሲል ጸለየ፦

> “**አባት ሆይ**፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ **እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።**”
>
> (ዮሐንስ 17:24)

ይሄ የእግዚአብሔር መልዕክት እምብርት ነው። የሰው ልጆችን የፈጠራቸው ከእሱ ጋር እንዲሆኑ ነው፤ ነገር ግን የእሱን ግብዣ እንድትቀበሉ አያስገድዳችሁም።

ምርጫውን ለእናንተ ይተዋል።

"ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።...ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?" (ራዕይ 2:7 ፤ 1 ዮሐንስ 5:5)

## ፍጹም ቤት

የመጨረዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በየዘመኑ የተነሱ አማኞች ከፈጣሪ ተቤዢያቸው ጋር የሚኖሩበትን እና እሱ ለሕዝቡ ባዘጋጀው ነገር ሁሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ዘላለማዊ ቤታችንን በጨረፍታ ዮሐንስ እንዳየ ይዘግባል።

"**አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ**፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፤ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፤ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፤ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።" (ራዕይ 21:1-2)

ይቺ የከበረች ከተማ እንደ አዲሰ ከተፈጠረቸው ፕላኔት ጋር ለመዋኸድ "ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ"። በአዲሲቷ ምድር "ባሕርም ወደ ፊት የለም።" አህጉራትን የሚለያይ ነገር ይኖርም።

"እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻችን ያብሳል ፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ፤ሳዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና..." (ራዕይ 21:4)

ሁሉ ነገር ፍጹም ይሆናል። ሰማያዊቷ ከተማ ከምትታሰበው በላይ የከበረች ትሆናለች። ዮሐንስ ይሄንን መግለጹ ከብዶታል።

"ከተማይቱም አራት ማዕዘን ነበራት፤ ርዝመትዋም እንደ ስፋትዋ ልክ ነበረ። ከተማይቱንም በዘንግ ለካት አሥራ ሁለትም ሺህ ምዕራፍ ሆነች፤ ርዝመትዋና ስፋትዋ ከፍታዋም ትክክል ነው። ቅጥርዋንም ለካ፤ መቶ አርባ አራት ክንድ በሰው ልክ፤ እርሱም በመልአክ ልክ።

ቅጥርዋም ከኢያሰጲድ የተሠራ ነበረ፤ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች። የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጌጦ

> ነበር፤ ፊተኛው መሠረት ኢያሰጲድ፥ ሁለተኛው ሰንፔር፥ ሦስተኛው ኬልቄዶን፥ አራተኛው መረግድ፥አምስተኛው ሰርዶንክስ፥ ስድስተኛው ሰርድዮን፥ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፥ ስምንተኛው ቢረሌ፥ ዘጠነኛው ወራውሬ፥ አሥረኛው ክርስጵራስስ፥ አሥራ አንደኛው ያክንት፥ አሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ።
>
> አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቆች ነበሩ፤ እየአንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ። **የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ።** ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም። ለከተማይቱም **የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለ ሆነ፥** ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም **ነበር።…**
>
> **ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥** ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።” (ራዕይ 21:16-24 ፣ 27)

እጅግ ግዙፏ ከተማ በሁሉም መልኩ የከበረች ትሆናለች ጎዳናዎቿ “ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ” ይሆናሉ። እያንዳንዱ ንድፍ የእግዚአብሔርን ክብር የሚያሳይ ይሆናል። ጌታ ራሱ የከተማዋ የአምልኮ ማዕከል እና የብርሃን ምንጭ ስለሚሆን ከተማዋ መቅደስ እና ብርሃን አይኖራትም። “በጉ ብርሃኗ ነው” ገነት በፍጥረት የመጀመሪያ ቀን የሚከተለውን ባለው በራሱ ብርሃን ትሆናለች፦

> “ብርሃን ይሁን” (ዘፍጥረት 1:3)

የዚያች ከተማ ብርሃን ከመገናኛው ድንኳን እና በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረው የሚያንጸባርቅ ብርሃን ራሱ እና የሚከተለውን ያለው ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነው፤

> “**እኔ** የዓለም **ብርሃን ነኝ**” (ዮሐንስ 8:12)

ሰማያዊቷ ከተማ ልክ ሰማይን የሚወክለው የመገናኛው ድንኳን ቅዱስ ቦታ ፍጹም ካሬ እንደ ሆነው እንደዚያው ነች። የከተማዋ ልኬት ርዝመት፣ ስፋት እና ቁመት በየአቅጣጫው 2200 ኪሎ ሜትር ይሰፋል። በግልጽ እንደሚታየው ከተማዋ

በአዲሲቱ ምድር ከባቢ አየር ውስጥ እስከ ጠፈር ድረስ ቆማ ትታያለች።

ሁሉም ሰው የማይገባባት "…ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር… ወደ እርሷ ከቶ አይገባም" በትሆንም እንኳን አዲስቷ ከተማ እስከዛሬ ለተወደው ሰው በሙሉ የሚሆን በቂ ቦታ አላት።

የመጨረሻው ምዕራፍ በከተማዋ ውስጥ የሚገኘውን የአትክልት ቦታ ያሳያል።

> "በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ። በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ **የሕይወት ዛፍ** ነበረ፤ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ። ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና **የበጉም** ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፤ስሙም **በግምባሮቻቸው** ይሆናል። ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም **ይነግሣሉ።"** (ራዕይ 22:1-5)

## ፍጹሚቷ ከተማ

የእግዚአብሔር ታሪክ ሙሉ በሙሉ ይፈጸማል።

> "በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ **የሕይወት ዛፍ** ነበረ፤"

ስንጀምር የነበረው አሰደሳች የአትክልት ቦታ የሚያበቃው፣ አሰገራሚ የአትክልት ቦታ ባላት ከተማ ነው። በንጽጽር ሰማያዊቱ ገነት መልካምን እና ክፉን ምታሳውቀው ዛፍ አትኖርበትም ነገር ግን አዳምና ሄዋን ሳጢአትን ከሰሩ በኋላ የተከለከሏት የሕይወት ዛፍ ግን ትኖራለች። ፍጹም ቅድስና እና ዘላለማዊ ሕይወት በአዲሷ ከተማ ውስጥ ብቸኛ አማራጮች ይሆናሉ።

የፈተና እና በእምነት የመኖር ዘመን ታሪክ ይሆናል።

> “የእግዚአብሔርና **የበጉም** ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፥ስሙም **በግምባሮቻቸው** ይሆናል። …ለዘላለምም እስከ ዘላለም **ይነግሣሉ።**”

የእግዚአብሔር ሕዝብ በዘላለም ውስጥ “የእግአብሔር … የበጉ” የእነሱን ርዳት አልባ ነፍስ ከፍርድ ለመቤዠትና ከእሱ ጋር ለዘላለም እንዲኖሩ ለማብቃት የከፈሉትን ዋጋ አይረሱትም።

ጣፋጭ ፣ በጌታ እና በሕዝቡ መካከል የሚኖር የማይቋረጥ ኅብረት ቀጠይነት ያለው ነገር ይሆናል። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናል እና እኛም ከእሱ ጋር መሆናችን አዳምንናሔዋን ኃጢአት ከመስራታቸው በፊት ከነበራቸው የትኛውም ነገር የበለጠ ይሆናል።

የበለጠ አስገራሚ የሚሆነው እንዴት ነው?

መልሱ የሚገኘው **ቤዛነት** በሚለው ቃል ውስጥ ነው።

> “እርሱ ከጨለማ *ሥ*ልጣን **አዳነን**፥ **ቤዛነቱንም** እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግ*ሥ*ት **አፈለሰን**።” (ቆላስያስ 1:13-14 አመት)

እንደ ሕግ አፍራሽ በኃጢአት እና ሞት ጨለማ እስር ቤት **ውስጥ ከመዳን** የከፋ እና የብርሃንን የፍቅር የሆነው እግዚአብሔር መንግስት የተወደደ ዜጋነት **ከመፍለስ** የበለጠ ምን ዕጣ ፈንታ ምን አለ?

ስለድነታቸው በእሱ በቻ ለሚታመኑ ሰዎቻ ፈጣሪ ተቤዢያቻን ያደረገ ይሄንኑ ነው። ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ፣ወደር የሌለው ዋጋ ባለው ደሙ ረዳት አልባ የሆኑ ኃጢአተኞችን ከሲዖል አድኖ ለገነት የበቁ አድርጓቸዋል።

ይሄ ፍጹም ታሪክ የቤዝዎት ታሪክ ለዘላለም መከለስ እና መደነቅ አለበት።

> “ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፦ **በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።**”
> (ራዕይ 7:9-10)

## ለዘላለም በደስታ ኖሩ

በዓለም ዙሪያ በተለያየ ዘመን የኖሩ ሰዎች በሙሉ የፍቅር እና የማዳን ታሪኮች እና አሰደሳች መጨረሻ ያላቸውን ታሪኮች ይወዳሉ፡፡[271]

በምሽት በሚንቀለቀል እሳት ዙሪያ ለተኮለኮሉ ሰዎች በመንደሩ ታሪክ አዋቂ የተተረከ የጥንት ጀብድ ይሁን ወይም ምሽት አልጋ ላይ ላለ ልጅ በወላጅ የተነበበ ታሪክ ተመሳሳይ ሴራ ይጋራሉ፡፡ ታሪኩ የሚከተለውን ይመስላል፦

በጭንቀት ውስጥ የምትገኝ አንዲት ሴት ፣ በአንድ ክፉ ገጸ ባህርይ ባርነት ስር ስትኖር በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት እና ብርቱ ጦረኛ ወይም መልከ ከመልካም በሆነ ልዑል አማካኝ ተስፋ አሰቆራጭ ከሆነው ሁኔታ ውስጥ ነጻ ትወጣለች፡፡ ውዱን ካዳናት በኋላ ፣ ጅግናው በሚያምረው ቤቱ ውስጥ ሙሽራው እንድትሆን ይወስዳታል፡፡

ታዲያ ታሪኩ የሚያልቀው እንዴት ነው?

### ከዚያም በኋላ በደስታ ኖሩ፡፡

ሰዎች እንዲህ አይነት ታሪኮችን የሚናገሩት ለምንድን ነው? የሚናገሩት እግዚአብሔር ከእኩይ ነጻ የመወጣትን፣ የመወደድን እና ከዚያ በኋላ በደስታ የመኖርን ታሪክ በሰዎች ልብ ውስጥ ስላስቀመጠ ነው፡፡ ለዚህም ነው ልጆች እና አዋቂዎች ሳይቀሩ እንዲህ አይነት ታሪኮችን የሚወዱት፡፡

ነገር ግን የእግዚአብሔር ታሪክ ምናባዊ ታሪክ አይደለም፡፡

ምናባዊ ፈጠራ በታሪክ ውስጥ የሚገኝ እና በሥነ ቅርስ ምርምር ሊረጋገጥ የሚችል አይደለም፡፡ የተፈጠረ ታሪክ በአሥራ አምስት ክፍለ ዘመናት በደርዘን በሚቆጠሩ ሰዎች ሊጻፍ አይችልም፣ ብቻ ሳይሆን በመቶዎች በሚቆጠሩ ዝርዝር ትንቢታትም ሊነገር አይችልም፡፡



በምናብ የተፈጠረ ጀግና እንደ ኢየሱስ በሰማያዊ ጥበብ ሊናገር አይችልም ደግሞም ሊያድናቸው ለመጣ ሰዎች እንዲህ አይላቸውም፦

> “እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል፡፡ ለአሕዛብ

አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል።" (ሉቃስ 18:31-33)

ልብ ወለድ ወደ ሲዖል እያመሩ ላሉ ኅጢአተኞች የነጻ ኅሊና እና የዘላለማዊ ሕይወት ማረጋገጫ ሊሰጣቸው አይችልም።

ምኞት ብቻውን ከፈጣሪያችን ጋር የግል ግንኙት እንዲኖረን ሊያደርገን አይችልም በተጨማሪም ኅጢአተኝነታችንን እና ራስ ወዳድ ልባችንን እግዚአብሔርን የማክበር እና ልሎችን የማገልገል ጥማት ወዳለው ልብ ሊለውጥ አይችልም።

ይህንን ሊያደርግ የሚችለው የእግዚአብሔር ታሪክ ብቻ ነው።

እውነተኛ ነገር ነው።

ለማጠቃለል ያክል ፦

የብቸኛው እውነተኛ አምላክ ታሪክ ሰው ስለሆነው ፣ፍጹም ሕይወት ስለርአው ፣ ፍጹም ደሙን ስለ ኅጢአተኞች ስላፈሰሰው እና ረዳት አልባ ሐጢአተኞችን ከሰይጣን፣ ከኅጢአት ፣ ከሞት እና ከሲዖል ለማዳን እና የሚያምኑ ሰዎች ከማያልቀው ጥበቡ እና ፍቅሩ በአባቱ ቤት ክብር እንዲደሰቱ ለማደረግ ሰው ስለሆነው ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ይሄ በጭንቀት ውስጥ ላለ ሰው የምስራች ነው።

ምክንያቱም እኛ ከዚህ በኋላ በደስታ እንድንኖር ያደረገልን ነገር ነው።

"እግዚአብሔር ያደረገው ሁሉ **ለዘላለም** እንዲኖር አወቅሁ" (መክብብ 3:14)

## ግብዣ እና ማስጠንቀቂያ

የእግዚብሔር መጽሐፍ የሚጠናቀቀው በእነዚህ ቃላት ነው፦

"እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። ...አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። **መንፈሱና ሙሽራይቱም**[ከሐጢአት የዳኑ]፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ **የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።**

በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ **ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር** እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤**ማንምም** በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች **ቢያጎድል**፣ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።

ይህን የሚመሰክር፦ አዎን፣ በቶሎ እመጣለሁ ይላል።

አሜን፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ **አሜን**።" (ራዕይ 22 :16 ፣ 13 ፣17-21)

ስለዚህም ጸሐፊው፣ ከእኔ ውጪ የሚኖረው ታሪኩን እና መልዕክቱን የሚያጠቃልለው በመጨረሻው "አሜን" (ማለትም የታመነና እውነተኛ ማለት ነው) ያጠቃልላል።

## እግዚአብሔርና ሰው በአንድነት

አዳም ወደ አትክልት ቦታው እሱን ፍለጋ መጥቶ "ወዴት ነህ?" ብሎ ለጠየቀው ጌታ የሰጠውን ምላሽ ታስታውሳላችሁ። በእፍረት እንዲህ ሲል መለሰ፦

"በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፣ ተሸሸግሁም።" (ዘፍጥረት 3:10)

ወንድየው እና ሴቷ ከፈጣሪ ባለቤታቸው ለመደበቅ የሞከሩት ኃጢአትን ስላደረጉ ነው።

ነገር ግን አሁን በታሪክ መጨረሻ የሚያምኑ ወንዶችና ሴቶች እና ልጆች ለፈጣሪ ተቤዢያቸው የመምጣት እና ከእሱ ጋር ለዘላለም እንዲኖሩ ስለሰጣቸው ተስፋ የሚሰጡት ምላሽ ምንድን ነው?

በደስታ እንዲህ ሲሉ ይመልሳሉ ፦

**"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።"** (ራዕይ 22:20)

እንዲህ አይነቱን ለውጥ ያመጣው ምንድን ነው? ለምንድን ነው ጥቂቶቹ የአዳም ዘሮች ከጌታቸው መደበቅን የማይፈልጉት?

ከዚያ ይልቅ ግን እሱን ፊት ለፊት ለማየት የሚጓጉት ለምንድን ነው?

ምላሹ የሚገኘው በብቸኛው እውነተኛ አምላክ ዘንድ ብቻ ነው፦

"ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፤ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፤አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቶአል። እርሱ ሞትን ሽሮአልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቶአል።"
(2 ጢሞቴዎስ 1:9-10 አመት)

## አንድ አገዛዝ

ልክ እግዚአብሔር አንድ አገዛዙን በምድራዊ ገነት ውስጥ ግልጽ እንዳደረገለት ሁሉ ለአዳም ዘሮች ደገሞ በሰማያዊቷ ገነት የሚኖረውን አንድ ስርዓት በግልጽ አሰምሮላቸዋል።

"ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።" (ራዕይ 21:27)

ስማችሁ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ተጽፏል? ከሆነ ከእሱ በግል የተላለፈላችሁ መልዕክት እነሆ፦

"**ልባችሁ** አይታወክ፤ በእግዚአብሔር **እመኑ**፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን **ባልኋችሁ** ነበር፤ ስፍራ **አዘጋጅላችሁ** ዘንድ እሄዳለሁና፤ሄጄም ስፍራ **ባዘጋጅላችሁ**፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ **እንድትሆኑ** ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።"
(ዮሐንስ 14:1-3 ፤ 6)

# መውጪያ ቃል

ይሄንን መጽሐፍ መጻፍ ለእኔ አስገራሚ ጉዞ ሆኖልኛል። ሰለ ከበረው ፈጣሪ ተቤዢዬ ማንነት፣ ታሪክ እና መልዕክት ማስላሰል ለእኔ መግለጽ ከምችለው በላይ ተባርኬበታለሁ። የእሱ መገኘት እና ምሪት በዚህ ስራ ውስጥ በግልጽ ታይቷል። ምስጋናው ሁሉ ለእሱ ይሁን።

## አመሰግናለሁ

ምንም እንኳን ረጅም የስም ዝርዝር ከመስጠት ብታቀብም ይሄ መጽሐፍ ያለባለቤቴ ካሮል በትዕግስት የተሞላ ድጋፍ እና ተሰጥዖ ካላቸው ወዳጆቼና እና ቤተሰቦቼ አሰተዋጽዖ ውጪ የሆነውን ሊሆን አይችልም። የሽፋን ገጹ እና ስዕሎቹ የተሰሩት በወንድሜ ዴቭ ነው። ሁላችሁንም ከልቤ አመሰግናለሁ።

> “እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።”
> (ዕብራውያን 6:10)

በተጨማም ደግሞ በርካታ ጠያቂ ሙስሊሞች ሰላለኩልኝ እና ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ምክንያት ስለሆኑኝ ኢሜይሎች አመሰግናለሁ።

ከሁሉ በላይ በዚህ አጭር ጉዞ ተሳታፊ ስለሆናችሁ እናንተንም ማመስገን እፈልጋለሁ። አጭር ያልኩት ከዚህ በላይ ሊረዝም እንደሚችል ለማሳየት ነው። እሰካሁን ድረስ ያነበብናቸው ምንባባት በጥቅሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከአራት በመቶ አይበልጡም። ምንም እንኳን የጉዟችን መጨረሻ ላይ ብንደርስም፣ ገና መጀመራችን ነው።

## ቀጣዩ ጉዞ

ምንም እንኳን ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መልዕክቱን ሊረዱት ለሚፈልጉ ሰዎች ግልጽ ያደረገ ቢሆንም እሱ ግን ወስብስብ፣ ልዩ እና ይሄ ቀረህ የማይባል ነው። ስለ እሱ ሊታወቅ

የሚገባውን ሁሉ ሊያውቅ የሚችል ሰውም ሆነ መልዐክ የለም። ሐዋርያው ዮሐንስ እውነታውን በመጨረሻው ጥቅስ ውስጥ መዝግቦት ይገኛል ፦

> “ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል።” (ዮሐንስ 21:25)

እስማማለሁ። ይሄንን አንድ አምላክ አንድ መልዕክት የተሰኘ መጽሐፍ በመጻፍ ሂደት ውስጥ ታኙ ጉዳይ የትኞቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እናካት የትኞቹንስ እናካት የሚለው ጉዳይ ነው። እውነቱን ለመናገር የእግዚአብሔር ቃል የማያልቅ ነው። የሚጣፍጥ እና ነፍስን የሚያረካ ነው። በሊባኖስ የሚገኘው ወዳጃችን እንደ ተገነዘበው (ምዕራፍ 7) “‘መጽሐፍ ቅዱስን አንብቤያለሁ’ ማለት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ተገንዝቤያለሁ። በተደጋጋሚ መነበብ ያለበት መጽሐፍ ነው።”

አሁን ይህንን ጉዞ አጠናቃችኋል ፣ ስለዚህም አንድ አምላክ አንድ መልዕክትን ወደኋላ ተመልሳችሁ በማየት የተጠቀሱትን በርካታ ጥቅሶች እያንዳንዳቸው የሚገኙበትን ክፍል አንብቡ። ከዚያ የተሻው ደግሞ የፈጣሪን ቤተ መጻሕፍት መጽሐፍ በመጽሐፍ የሚከተለውን ጸሎት እየጸለያችሁ አንብቡ፦

> “ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ።” (መዝሙር 119:18)

ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ከፈለጋችሁ የግርጌ ማስታወሻዎቹን ተመልከቱ። ከመጽሐፉ ጀርባ የሚገኙትን የምዕራፍ ክለሳ ጥያቄዎች አሰላስሉ። ጥያቄዎቻችሁን ወይም አስተያየቶቻችሁን ለእኔ ከመጻፍ ወደ ኋላ አትበሉ።

የ 3500 ዓመታት ዕድሜ ባለው ባርኮት እሰናበታችኋላሁ፦

> “እግዚአብሔር ይባርክህ፥ ይጠብቅህም፤እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፥ ይራራልህም፤እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፥ ሰላምንም ይስጥህ። እንዲሁ ስሜን በእስራኤል ልጆች ላይ ያደርጋሉ፤ እኔም እባርካቸዋለሁ።” (ዘኅልቍ 6:24-26)

ፖል ዳን ብራምስን
pdbramsen@rockintl.org
www.One-God-One-Message.com

# የግርጌ ማስታወሻዎች

“የማላየውን ነገር አንተ አስተምረኝ፤” (ኢዮብ 34 ፡32)

## የመግቢያ ቃል

[1] ሳኸል፦ ከፊል በረሃማ የሆነና የአፍሪካን ሰሃራ ከምድር ወገብ የዝናብ ጫካዎች የሚለይ ክልል። ይሄ የአሸዋ ክምር እና ቁጥቋጦ ስብስብ ከሴኔጋል እስከ ሱዳን ይደርሳል።

[2] አንድ አምላኪዎች በአንድ አምላክ ያምናሉ፣ በዙ አምላኪዎች በበርካታ ሴትና ወንድ አማልክት ያምናሉ ፣ ፓንተይስቶች ደግሞ ሁሉ ነገር የአምላክ አካል ነው ይላሉ ሴኩላር ሰዋውያን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ከፍ ከፍ ያደርጋሉ እንዲሁም ኢአማንያን እግዚአብሔር የለም ይላሉ።

## ምዕራፍ 1 ፦ እውነትን ግዟት

[3] በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ውስጥ ይሄ ሐረግ ከ1000 በላይ የሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ጥቅሶች ይገኙበታል። አንዳንድ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ እንደምታዩት ጥቅሶች በከፊል ተጠቅሰዋል። ምሳሌ ምዕራፍ 23 ቁጥር 23 ሙሉ በሙሉ ስናነበው “እውነትን ግዛ አትሸጣትም፥ ጥበብን ተግሣጽን ማስተዋልንም።” ይላል።

[4] Barrett, David B., George T. Kurian and Todd M. Johnson. World Christian Encyclopedia: A Comparative Survey of Churches and Religions in the Modern World. London: Oxford University Press, 2001.

[5] “ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ ከ 2749 በማያንሱ ቋንቋች ይገኛል ፤ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ወደ 451 ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን ፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ ወደ 1185 ቋንቋዎች ተተርጉሟል። በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተጨማሪ 843 ቋንቋዎች ይገኛሉ።” (United Bible Society, 2010, www.ubs-translations.org/about_us)

[6] Foxe, John (edited by G.A. Williamson). Foxe’s Book of Martyrs. Toronto: Little, Brown & Company, 1965.

[7] ኢየሱስ ክርስቶስ “መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው።” (ዮሐንስ 18:36)ስላለ የትኛውንም ሐገር “ክርስቲያን ሐገር” ብሎ መጥራት ትክክል አይደለም።

[8] Wurmbrand, Richard. Tortured for Christ(ለክርስቶስ ተሰቃየሁ) – 30th Anniversary Edition. Bartlesville, OK: Living Sacrifice Book Co., 1998.
[9] "የጽድቅ መንገድ የሬዲዮ" (The Way of Righteousness) ፕሮግራም በዓለም ዙሪያ ለመሰራጨት ወደ 100 የሚጠጉ ቋንቋዎች ተተርጉሟል ወይም በመተርጎም ላይ ይገኛል። www.one-god-one-message.com
[10] ሙሉው የቁርዓን ጥቅስ እንዲህ ይላል፦ "በፈለጎቻቸው (በነብያቱ ፈለግ) ላይ የመርየም ልጅ ዒሳን ከተውረቱ በስተፊት ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን ኢንጅልም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያልቸውን ተወረትን የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆች መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው።" (ሱራ 5:46) በተለየ መንገድ ካልተጠቀሰ በስተቀር በአንድ አምላክ አንድ መንግስት ውስጥ የተጠቀሰው የአብዱላ የሱፍ አሊ ትርጉም ነው። The Qur'an Translation. New York: Tahrike Tarsile Qur'an, Inc., 2003. **ማስታወሻ**፦ ቁርዓን ሱራ ተብለው በሚጠሩ ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው። የጥቅስ ቁጥሮች እንደ ቁርዓን ትርጉም አይነት ሊለያዩ ይችላሉ። ጥቅስን በምትፈልጉበት ጊዜ ዙሪያቸው የሚገኙ ጥቅሶችን መፈተሽ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ሊኖር ይችላል።
[11] በቁርዓን ውስጥ የሚገኘው "እኛ" ምንን ያመለክታል ? በቁርዓን አላህ ራሱን በመጀመሪይያ መደብ ብዙ ቁጥር ይጠራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም አንዳንድ ጊዜ ራሱን በብዙ ቁጥር ይጠራል። **ማሰታወሻ**፦ የአረብኛ ተናጋሪ የሆኑ ሙስሊሞች "አላህ" የሚለውን ቃል በሁለት መንገድ ይጠቀሙበታል፦ "አላህ" በአረብ ክርስቲያኖች ፣ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እና ሙስሊሞች "እግዚአብሔር" ቃል ለመወከል ይጠቀሙበታል። በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ የእግዚአብሔር መጠሪያ ስም አይደለም። በአረብኛ ተናጋሪዎች ዘንድ ፣ አላህ ሚለውን መጠሪያ በባለቤትነት የያዘ አንድም ቡድን የለም። ሙስሊሞች "አላህ" የአምላክ የመጀመሪያ እና መጠሪያ ስም አድርገው ይጠቀሙበታል። በዚህ ዙሪያ ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ በተጨማሪ እንነጋገራለን።
[12] በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ውስጥ የሚቀርቡ የኢሜይል መልዕክቶች የጻፏቸውን ሰዎች ማንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚቀርበው ስም ሳይገልጥ ነው።
[13] "ሰ.በ.ይ" "ሰላም በእርሱ (እርሳቸው) ላይ ይሁን" ማለት ሲሆን ሙስሊሞች የነብያትን ስም ተጠቅመው ሲጽፉ ወይም ሲናገሩ የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ሙስሊሞች የአረብኛውን ቃል የሚጠቀሙት ከነብዩ መሐመድ ስም በኋላ ነው ፦ ሳላ ዐለሁ አላሂ ወ ሳላም (ሰ.ዐ.ወ)፣ ይህም ማለት "የአላህ ጸሎት እና ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን" ማለት ነው። የዚህ ቁርዓናዊ ልምምድ መሰረት የሚከተለው የቁርዓን ጥቅስ ነው፦ "አላህና መላዕክቱ በነብዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወረዳሉ እላንት ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮትን እዝነት አውርዱ፤ የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ።" (ሱራ 33:56)የዚህ ቀመር

አጠቃቀም “ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፣” (ዕብራውያን 9:27) ምኢለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይስማማም። ሰው አንድ ጊዜ ከሞተ ዘላለማዊው ዕጣ ፈንታው ተወስኗል። ምንም ያህል ጸሎት ቢደረግ ዘላለምን የት እና በምን አይነት ሁኔታ ነው የሚያሳልፈው የሚለውን አይቀይረውም። (ራዕይ 22:11)
[14] [ከነ ስህተቱ የተጠቀሰ] የላቲን “ስለዚህ” ማለት ነው። ምንም እንኳን ግልጽ ሆነ ስህተት ቢኖርበትም ዋናው ቅጂ በትክክል መጠቀሱን ለማሳየት በቅንፍ ውስጥ የሚቀመጥ ነው። **ማስታወሻ** ፦ ለማሳጠር እና የፊደል እና የሰዋሰው እርማት ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር (በግልጽ እንድንረዳው ለማድረግ) በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የኢሜይል ጥቅሶች እንደተቀበልኳቸው የቀረቡ ናቸው። ለምሳሌ የ“አሕመድ” ኢሜይል ላይ በእንግሊዝኛው ፍቺ የመጀመሪያዎቹ ፊደላት በተገቢው መንገድ አልተጻፉም። ይሄ ታርሟል።
[15] The Meaning of the Glorious Koran: An Explanatory Translation by Mohammed Marmaduke Pickthall. New York: Meridian, 1997.
[16] ለምሳሌ ቁርዓን በሱራ (ምዕራፍ) 40 ቁጥር 70-72 እንዲህ ይላል፦ “ወደነዚያ በመጽሐፉ በዚያም **መልዕክተኞቻችንም በርሱ በላክንበት ወዳስተባበሉበትም**(አታውቅምን?) ወደፊት ያውቃሉ። እንዛዝላዎቹና ሰንሰለቶቹ በአንገቶቻቸው ላይ በትደረጉ ጊዜ (በርሷ) ይጎተታሉ። በገኸነም ውስጥ (ይጎተታሉ) ከዚያም ከእሳት ውስጥ ይማገዳሉ።” በተጨማሪም “**በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ** ፍላቶቻቸውንም አትከተል። አላህም ወዳንተ ካወረደው ከከፊሉ **እንዳያሳስቱህ ተጠንቀቃቸው** (ማለትን አወረድን) ቢዞሩም አላህ የሚሻውን በከፊሉኃጢአታቸው ሊቀጣቸው መሆኑን ዕወቅ ከሰዎቹም ብዙዎቹ አመጠኞ ናቸው።”(ሱራ 5:49) “እላንተ ያመናችሁ ሆይ በአላህና በመልዕከተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም **ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ** በአላህና በመላእክቱምበመጽሐፎቹቹ መልዕክተኞቹም በመጨረሻ ቀን የካደ ሰው (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግ ተሳሳተ… እኛ ወደ ኑህ እና ከርሱ በኋላ ወደነበሩት ነብያት እንዳወረድን ወዳንተም አወረድን ወደ ኢብራሂምም ወደ ዒስማኢልም ወደ ኢሳቅም ወደ ወደ ያዕቆብም ወደ ነገዶቹም ወደ ዒሳም ወደ አዩብም ወደ ዩኑስም ወደ ሃሩን እና ድአ ሱሌይማንም አወረድን ለዳውድም **ዘቡርን** ሰጠነው።” (ሱራ 4:136 ፣163) ለተጨማሪ የቁርዓን ዐርፍተ ነገሮች የምዕራፍ ሶስትን የመጀመሪያ ገጽ እና ከእሱ ጋር አብረው የሚሄዱ የግርጌ ማስታወሻዎችን ተመልከቱ።
[17] ምሳሌ 23:23። እውነትን “ከመግዛት” ይልቅ ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ሲያጠኑ ተገኝተው ቤተሰቦቻቸው ወይም ወዳጆቻቸው ስለነሱ የሚያስቡት ነገር አስፈርቷቸው እውነትን “ይሸጧታል” (ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያምኑት የሚያዘውን በበዛት የተሸጠ መጽሐፍ እና ጥንታዊውን ቅዱሳት መጽሐፍትን የያዘ ነው)።

**ምዕራፍ 2፦ እንቅፋቶችን ማሸነፍ**

[18] Doyle, Sir Arthur Conan (ሰር አርተር ኮናን ዶይል). Treasury of World Masterpieces: The Celebrated Cases of Sherlock Holmes. (ሼርሎክ ሆልምስ) R.R. Donnelley and Sons Company, 1981, p. 17. (ለመጀመሪያ ጊዜ በታላቋ ብሪታንያ በ 1891 እ.ኤ.አ የታተመ።)
[19] ሮሜ 14:1-15:7 ፤ ማቴዎስ 7:1-5
[20] Doyle፣ ገጽ 16
[21] ዘሳልቁ 12
[22] 2 ነገሥት 5
[23] ዮናስ 4
[24] በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጽሐፍትን ተመልከቱ፦ ዳንኤል፣ እዝራ እና አስቴር
[25] ዮሐንስ 4
[26] "The Greatest Journey," National Geographic Magazine, Mar. 2006, p. 62.
[27] መዝሙር 90:1-12 ፤ ማርቆስ 8:36 ፤ 2 ቆሮንቶስ 4:16-18 ፤ ሮሜ 8:18 ፤ ያዕቆብ 4:13-15
[28] በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የተለያዩ አጥፊ ነገሮች እንዲከሰቱ ፈቅዷል/ ልኳል። ከመቶ ዓመታት ትዕግስትና ማስጠንቀቂያ በኋላ እግዚአብሔር ከስምንት ነፍሳት በሰተቀር ሁሉም ሰው የጠፋበት ዓለማቀፋዊ ጎርፍ ልኮ ነበር (ዘፍጥረት 6-8)። (ምንም እንኳን የሥነ ምድር እና የቅሪተ አካል ማስረጃዎች ቢያረጋግጡትም ብዙዎች ይህንን ዓለም አቀፋዊ ጎርፍ እንደ አፈታሪክ ያዩታል) በአብርሃም ዘመን በሰዶም እና በገሞራ ላይ በወደቀው እሳት ከሦስት ነፍሳት በስተቀር ሰው ሁሉ ጠፍቷል። በሙሴ እና ከሙሴ በኋላ ባለው ዘመን እግዚአብሔር የከንዓናውያንን ሃገር እንዲያጠፉ እስራኤላውያንን አዟል (ኢያሱ 1-10)። እነዚህ ውጊያዎች የተካሄዱት እግዚአብሔር በሰጠው ልዩ ትዕዛዝ ነበር በዙ ጊዜም ከሰማይ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነትም ነበር፣ ለምሳሌ እስራኤላውያን በከተማዋ ቅጥር ዙሪያ ለሰባት ቀናት በስልፍ ከዞሩ በኋላ የኢያሪኮ ቅጥር ወደ ውጪ መውደቅ (በስነ ቅርስ ጥናት ተረጋግጧል)። እግዚአብሔር እነዚህ አሕዛብ ላይ ከመፍረዱ በፊት እግዚአብሔር በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ለንሰሐ እና ከጣዖቶቻቸው፣ ከኃጢአታቸው እና ሰውን መስዋዕት ከማድረግ እንዲመለሱ ጊዜ ለመስጠት ጠብቋል (ዘፍጥረት 15:16 ፤ ዘጸአት 12:40)፤ ነገር ግን እነሱ እንደ አብርሐም፣ ዮሴፍ እና ሙሴ ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎችን ምስክርነት አልተቀበሉም። በግብጽ ላይ መለኮታዊ የሆኑ አስር መቅሰፍቶችን በላከው እና በቀይ ባህር ውስጥ መንገድ በከፈተው እግዚአብሔር ንሰሐ ገብተው ያመኑ ጥቂቶች ናቸው። እግዚአብሔር ጥንታዊውን ሕዝቡን ፍርዱን ለማስፈጸም ሲጠቀም እያዳላ አልነበረም። ለምሳሌ ቶራ እንድሚገልጸው እግዚአብሔር በኃጢአት ምክንያት(ከጣዖት አምልኮ እና ከዝሙት

የተነሳ) የቀጣው እስራኤልውያንን ሲሆን 24000 ሰው አልቋል (ዘሕልቁ 25-31)። እግዚአብሔር በመጀመሪያ እስራኤልን ከቀጣ በኋላ በዙሪያቸው በሚገኙ ሳጢአተኛ እና ክፉ ሃገራት ላይ ፍርዱን እንዲያስፈጽሙ ልኳቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ሕዝቦች ንጹሐን ናቸው የሚለውን ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እነዚህ አሕዛብ ሳጢአተኞች ከመሆናቸው የተነሳ "ምድሪቱም የሚኖሩባትን ሰዎች ትተፋለች።" (ዘሌዋውያን 18:25 አመት) የእግዚአብሔር መልካምነት እና ትዕግስት ታላቅ ነው ነገር ግን ቁጣውም ታላቅ ፍርዱም እርግጥ ነው።

[29] እግዚአብሔር እኩይ ላይ ወዲያውኑ የማይፈርደው ለሳጢአተኞች የንሰሐ ጊዜ እንዲያገኙ እና የድነት አቅርቦቱን እንዲቀበሉ ነው፦ "እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ። ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ **ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል**።" (2ጴጥሮስ 3:8-9 አመት)

[30] የአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ምዕራፍ 8 ፣12 ፣ 28 እና 29 ለእነዚህ ግጭት ለሚመስሉ ነገሮች ምላሽን ይሰጣሉ።

[31] ማቴዎስ 7:1-20 ፤ ከሮሜ 14 እና1 ቆሮንቶስ 6 ጋር አነጻጽሩ።

[32] በርካታ ድረ ገጾች "101 Clear Contradictions in the Bible," በሚል ርዕስ ረጅም ዝርዝሮችን ቢለጥፉም ፣ ሌላ ለበርካታ ዓመታት የቆየ "101 **Cleared-up** 'Contradictions' in the Bible." የተዘጋጀ ልጥፍም ይገኛል። www.debate.org.uk/topics/apolog/contrads

[33] በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የትኞቹንም ጥቅሶች በትክክል ለመፍታት የሚያገለግሉ ሁለት ሕግጋት ፦ ዙሪያውን ያለውን ዐውድ አንብቡ። ጥቅስ ከጥቅስ ጋር አነጻጽሩ። ይህንን በምሳሌ ለማሳየት ዘዳግም (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው 5ኛ መጽሐፍ) ሙሴ ለእስራኤል ልጆች የሚከተለውን ትንቢት ተናግሯል፦ "አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ።" (ዘዳግም 18:15) እግዚአብሔር "ከወንድሞችህ መካከል" እግዚአብሔር ነብይ ያስነሳላቸኋላ ሲል ሙሴ ምን ማለቱ ነው? አንዳንዶች ሙሴ እየተናገረ ያለው ስለ እስማኤላውያን ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ስለ እስራኤላውን ነው ይላሉ። በዙሪያው የሚገኘው ዐውድ ፍንጭ ይሰጠናል (ምሳ. ዘዳግም 17:15 ፣20 ፤ 18፡2 ፣5 ፣ ወዘተ)። እግዚአብሔር "አስነሳለሁ" ያለው "ነብይ" ማን ነው? ብዙዎች የእምነታቸው መስራች ይህንን ትንቢት እንዲያሟላ ለማድረግ ቢሞክሩም እውነተኛ ፍቺው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። ዮሐንስ 5:43-47 ፣ ዮሐንስ 6:14 እና ሐዋርያት 3:22-26 አንብቡ።

[34] ከክልበ - ከክርስቶስ ልደት በፊት/ ዓም - አኖ ዶሚኒ ትርጉሙም "በጌታ ዓመት" ማለት ነው። ብዙዎች ከዚህኛው ዘመን በፊት ወይም በዚህ

ዘመን የሚለውን ይጠቀማሉ፣ ይሄ አጠቃቀማቸው ከንግግራቸው ውስጥ "ክርስቶስ" የሚለውን ቃል ለማስወገድ ቢሆንም የታሪክ እምብርት አሁንም ቢሆን ልደተ ክርስቶስ ነው።
[35] ከባንክ ገንዘብ ተበድራችሁ የምታውቁ ከሆነ ሕጋዊ የሆነ የውል ስምምነት ተፈራርማችኋል። ውላችሁ ውስጥ የባንኩ ድርሻ ተስፋ የገባላችሁን ገንዘብ መስጠት ሲሆን፣ የእናንተ ድርሻ ደግሞ በተወነው የጊዜ ገደብ ብድራችሁን መመለስ ነው። የእናንተን ድርሻ አለመወጣት የማያስደስት ነገር ማምጣቱ አይቀርም። በተመሳሳይ መልኩ መጽሀፍ ቅዱሳችን ፈጣሪያችን ለሰው ልጆች ያቀረበውን ኪዳን ዝርዝር ይገልጻል እሱም እንደ እኔ እና እናንተ ያሉ ሰዎች የዘላለም በረከቱን መለማመድ እንዲችሉ ያደርጋል። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር "ኪዳን" (ኤርሚያስ 31:31) መጋባቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው።
[36] ይሄንን የመለኮት መገለጫ የሆነ ነገር ምዕራፍ 5 ላይ እንመለከተዋለን። አንድ ታሪክ ከመከሰቱ በፊት እግዚአብሔር እንደሚያስውቅ የሚያሳይ ታሪክ የሚገኘው በዳንኤል መጽሐፍ ከምዕራፍ 7እስከ 12 ነው። ዳንኤል ከ 400 ዓዓ እስከ ክርስቶስ ዘመን ድረስ ያለውን የዓም አግዛዞች ታሪክ በተጨሪም በመጨረሻው ዘመን የሚፈጸሙ ታሪኮችን ጭምር ይገልጣል። ዳንኤል ሁሉንም የጻፈው ከ600 እስከ 530 ዓ.ዓ ባለው ዘመን ነው።

**ምዕራፍ 3 ፦ ተበርዟል ወይስ ተጠብቋል?**
[37] መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ እግዚአብሔር እንደተጻፈ የሚያረጋግጡ ተጨማሪ የቁርዓን ጥቅሶች ፦ ሱራ 2:87-91 ፣101፣136፣285፤ 3:3-4፤ 4:47፣54፣136፣163፤ 5:43-48፣68፤ 6:92፤ 10:94፤ 20:133፤ 21:105፤ 28:43፤ 29:46፤ 32:23፤ 40:53-54፣70-72፤ 45:16፤ 46:12፤ 57:27፤ ወዘተ።
[38] በዘመናት መካከል የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በአይሁድ የሐይማኖት ማህበረሰብ በቅንዓት ሲጠበቅ ኖሯል። አስቡት። ብዙኸን ሊሞቱላቸው ፈቃደኛ የሆኑላቸውን ቅዱሳት መጽሐፍት ፣ የትኛውም ሰው እንዲበርዛቸው የሚፈቅዱ ይመስላችኋል? በታሪክ ውስጥ አንድ የሐይማኖት ቡድን በሌላኛው እምነት(ኦርቶዶክስ አይሁድ) በሚከብር እና በሚጠበቅ መጽሐፍ ላይ (ብሉይ ኪዳን) እምነቱን የመሰረተበት በታሪክ ውስጥ የሚታወቅ ክስተት የለም። ይሄ እውነት ብቻ በራሱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ለመበረዝ የማይቻል አያደርገውም?
[39] The Holy Qur'an. Translated by M.H. Shakir. Tahrike Tarsile Qur'an, Inc., Electronic version, 1993.
[40] Metzger, Bruce M. and Michael D. Coogan. The Oxford Companion to the Bible. NY: Oxford University Press, 1993, p. 754.
[41] የግርጌ ማስታወሻ 37 ተመልከቱ።
[42] ከ750 ዓም በፊት የተረጋገጡ ቁርዓናዊ ወይም ኢስላማዊ መዛግብት

የሉም (ከመሐመድ ሞት ከ 100 በኋላ)፡፡ www.debate.org.uk/debate-topics/historical/is-quran

43 Metzger and Coogan, p. 683.

44 በጥንታውያን የእጅ ቅጂዎች ውስጥ የተገኘ ልዩነት የሚመስል ነገር ምሳሌ የሚከተለው ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የሁለተኛ ነሥት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ይላል ፦ "ዮአኪን መንገሥ በጀመረ ጊዜ የአሥራ ስምንት ዓመት ጕልማሳ ነበረ፤" (2 ነገሥት 24:8) የሁለተኛ ዜና መጽሐፍ ግን እንዲህ ይላል፦ "ዮአኪንም መንገሥ በጀመረ ጊዜ የአሥራ ስምንት ዓመት ጕልማሳ ነበረ፤" (2 ዜና 36:9)፡፡ እንዲህ አይነት ስህተቶች ሊብራሩ የሚችሉት እንዴት ነው? አንዳንድ ምሁራን የኢዮአኪን አባት ከመንግስት ጋር እንዲሰራ በስምንት ዓመቱ ነው የወሰደው የአባቱን ሞት ተከትሎ በ18 ዓመቱ ነገሰ ይላሉ፡፡ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ይበልጥ ተቀባይነት ያለው ማብራሪያ ግን ቀደምት ጸሐፍት "8" እና "18" ሲጽፉ የፈጠሩት ስህተት ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ይሄ የተሳሳተ ቁጥር ከዚያ ጸሐፊ በተገኘ ቅጂች ውስጥ ሁሉ ተገልብጥጦ ይገኛል፡፡ ጉዳዩ ምንም ሆነ ምንም እንዲህ አይነት ልዩነቶች እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን መልዕክት በምንም አይነት መልኩ ሊለውጡት አይችሉም፡፡ በብዙ ከስተቶች የጥንታዊው መጽሐፍ ቅዱስ የእጅ ቅጂዎች ምሁራን የተለያዩ ምንባባትን በማወዳደር ትክክለኛውን አገላለጽ እንዲያስቀምጡ ያደርጋቸዋል፡፡

45 ሐዲስ እንዲህ ይላል "ኡስማን በመቀጠል ዛይድ ቢን ጠይብ እንዲህ ሲሉ አዘዙ 'አብደላ ቢን አዝ ዙብይር እንዲህ አለ ሳይድ ቢን አላስ እና አብዱር ራህማን ቢን ሃሪ ቢን ሂሻም **በፍጹም ቅጂ በእጅ እንደገና እንዲጽፉ** አዘዘ ...እንደዚያም አደረጉ እና ብዙ ቅጂዎች ከጻፉ በኋላ 'ኡስማን ቅጂዎቹን ለ ሃፍስ መለሰለት 'ኡስማን የገለበጠውን ለእያንዳንዱ የሙስሊም ክፍለ ሃገር ላከ **ሌሎቹንም ቁረዓናዊ ጽሁፎች በቁርጥራጭ የእጅ ጽሁፍ የተጻፈ ወይም ሙሉ ቅጂ እንዲቃጠል አደረገ፡፡**" (ሐዲስ ፣ ሳሂህ ቡኻሪ ፣ቅ ጽ4 ፣ ገጽ 510) (ሐዲስ (አባባሎች) በመሐመድ ሚስቶች እና የቅርብ ሰዎች የተጻፉ ጥንታውያን ጽሁፎች ናቸው፡፡ ሙስሊሞች ብዙዎቹን እምነቶቻቸውን እና ልምምዶቻቸውን የሚመሰርቱት በእነዚህ ላይ ነው፡፡)

46 ቅዱሳት መጻህፍት ያልተለወጡ መሆናቸውን ከሚያረጋግጠው ከሙት ባህር ጥቅልሎች ከመገኘታቸው በፊት ቢሆን እንኳን፣ ያሁንን ብሉይ ኪዳን ከሰባ ሊቃናት (በ270ዓዓ የተጠናቀቀ የብሉይ ኪዳን የግሪክ ቅጂ) ጋር ማነጻጸር ይቻላል፡፡ ሰባ ሊቃናት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ያልተበረዙ እና የተጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

47 Abegg, Martin Jr., Peter Flint and Eugene Ulrich. The Dead Sea Scrolls Bible. San Francisco: Harper, 1999, page xvi.

48 McDowell, Josh. A Ready Defense. Nashville: Thomas Nelson Publishers, 1993, pp. 42-48.

49 የአዲስን ኪዳን መጽሐፍት ከጥቂት የግሪክ ዋና ምንባባት (ማጁሪቲ

ቴክስት፣ ቴክስተስ ሬሲፕተስ ፤ አሌክሳንድርያን ቴክስት) የተተረጎሙ ናቸው። ለምሳሌ የቀድሞው ትርጉም የታረመው ከማጆሪቲ ቴክስት ሲሆን አሙት የታረመው ከአሌክሳንድሪያ ቴክስት ነው። በአዲስ ግሪክ ኪዳን ምንባባት ውስጥ "ተጨባጭ" የሆኑ ልዩነቶች በሚኖሩበት ጊዜ ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እነዚህን ልዩነቶች የሚያመላክቱ ነገሮች በህዳጋቸው ላይ ያካትታሉ። ጥያቄ ያለባቸው ረጅም ምንባባት ማርቆስ 16:9-20 እና ዮሐንስ 7:53- 8:11 ናቸው ፤ ሁለቱም ርዝመታቸው 12 ቁጥር ነው። ምንም እንኳን እነዚህ ምንባባት በተገኙ የእጅ ቅጂዎች (የአሌክሳንድርያ ቴክት) ውስጥ ባይገኙም በሌሎች በመቶች በሚቆጠሩ ቅጂዎች ውስጥ (ማጆሪቲ ቴክስት) ውስጥ ተገኝተዋል። የተለያዩ ምንባባት ከተለያዩ ጥንታውያን ቅጂዎች የተገኙ እንደ መሆናቸው መጠን፣ ጥንታዊ ነው ማለት ትክክለኛ ነው ማለት ላይሆን ይችላል። ምናልባት ሐሳቡን ሰብስቦ መስራት ያቀተው የቅጂ ጸሐፊ እነዚህን ምንባባት ዘሏቸው ሊሆን ይችላል። ጉዳዩ ምንም ይሁን ምን፣ በእነዚህ በተዘለሉ ምንባባት ውስጥ የሚገኙ ትምህርቶች በሌሎች ምንባባት ውስጥ ተገልጠዋል። የእግዚአብሔር መልዕክት እንዳለ ነው። የእግዚአብሔርን መልዕክት በምንም አይነት መንገድ ሊለውጡ የማይችሉ ጥቂት ምንባባት ጎድለዋል ብሎ መላውን የእግዚአብሔርን መልዕክት አለመቀበል ጥበብ አይደለም?

[50] በቅርብ ጊዜያት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥርጣሬን እንዲፈጥሩ የታሰቡ መጽሐፍት ታትመዋል፣ ፊልሞችም ተሰርተዋል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቺዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩትን "አማራጭ ወንጌላት"ያቀርባሉ። እነዚህ "ወንጌላት" ከመሲሁ መምጣት ከረጅም ዓመታት በኋላ የተጻፉ በመሆናቸው ታሪካዊ ማረጋገጫ የላቸውም።

[51] ይሄ ዐርፍተ ነገር በማቴዎስ 11:15፤ 13:43፤ ማርቆስ 4:9 ፣23፤ 7:16፤ ሉቃስ 8:8፤ 14:35፤ ራዕይ2:7፣11፣29፤ 3:6፣13፣ 22፤ 13:9 ውስጥ ይገኛል።

## ምዕራፍ 4 ፦ ሳይንስ እና መጽሐፍ ቅዱስ

[52] Webster's New World College Dictionary. New York: Simon & Schuster, 1997. See: science.

[53] Bucaille, Maurice. La Bible, le Coran et la science. Paris: Seghers, 1976, p. 35. ለዶ/ር ቡካሊ መጽሐፍ ምላሽ ለመስጠት ዶ/ር ዊልያም ካምፕቤል The Qur'an and the Bible in Light of History and Science. Second Edition; Middle East Resources, 2002. የተሰኘ መጽሐፍ ጽፈዋል። የዶ/ር ካምፕቤል በጥንቃቄ ጥናት የተደረገበት መልስ ሰጪ መጽሐፍ በሰባት ቋንቋዎች ልታነቡ ትችላላችሁ። https://answering-islam.org/Campbell

[54] ሥነ ፍጥረታዊ ዝግመተ ለውጥ እንደ አልጌ እንደ ጦጣ ያሉ የሕይወት ዝርያዎች በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዝርያዎች ሲከፋፈሉ የዕጽዋት እና የሰው ዝርያ ይሆናሉ። እንደ ዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ ከሆነ ሰው፣

ዝንጀሮ እና ሚኖዎች ተመሳሳይ የዘር ግንድ ይጋራሉ። እውነቱ ግን ወጥ ያልሆነ ዝግመተ ለውጥም ሆነ በዓላማ የሚካሄድ ዝግመተ ለውጥ በዘመናውዊ ሳይንስ ሊረጋገጡ አልቻሉም።
http://www.gma.org/space1/nav_map.html
[55] http://www.gma.org/space1/nav_map.html
[56] ተጨማሪ ጥቅሶች የውሃ ዑደትን ያረጋግጣሉ፦ መዝሙር 135:7፤ ኤርሚያስ 10:13፤ መክብብ 1:7፤ ኢሳያስ 55:10
[57] የኒውስ ዊክ መጽሔት ፦ "የዲኤንኤ ሰንሰለት ... ሁላችንም የተገኘነው ከአንዲት ሴት ነው ወደሚል ድምዳሜ አደረሳቸው [ሳይንቲስቶችን]"Newsweek, January 11, 1988, pp. 46-52.
[58] ታይም መጽሔት ፡፦ "በሕብለ በራሄ ውስጥ የሚገኘው የዘረመል ቁሱ ለሁሉም በአሁኑ ሰዓት በምድር ላይ ከሚገኙ ሰዎች ጋር አንድ አይነት የሆነ ጥንታዊ 'አዳም' ነበረ።" Time, December 4, 1995, p. 29. **ማስታወሻ**፦ ሳይንቲስቶች የጋራ የወንድ ዝርያችን በጊዜ ርቀት የጋራ ሴት ዝርያችን ጋር ሊደርስ አይችልም ሲሉ ይናገራሉ። ይሄ ንግግራቸው ሁላችንም ከኖህ መምጣታችንን ከሚያሳየው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል። የጋራ እናታችን ግን ሔዋን ነች፤ ምክንያቱም ኖህ የሰው ሁሉ ምንጭ የሆኑ ሶስት ልጆች እና ሶስት ምራቶች ነበሩት)
[59] https://bcmj.org/premise/history-bloodletting
[60] www.bible.ca/tracks/matthew-fontaine-maury-pathfinder-of-sea-ps8.htm **ማስታወሻ**፦ ማውሪ የባህር መንገዶች የተገኙበ ከመሆናቸው የተነሳ የባህር ላይ ተጓዦች በቀጥታ ባህሩን"ሰንጥቆ" ማለፍ ይችላል። (Rozwadowski, Helen M. Fathoming the Ocean. Cambridge, MA: The Belknap Press of Harvard University Press, 2005, p. 40)ዳዊት "የባህር መንገዶችን" በጻፈ ጊዜ እሱና ሕዝቡ የሚያውቋቸው ብቸኛ ባህሮች የሜድትራኒያን ፣ የገሊላ ባሕር፣ ሙት ባህር እና ቀይ ባህር ናቸው። እነዚህ የውሃ አካላት "መንገዶች" ወይም ተጨባጭ እና የሚታዩ ሞገዶች የሏቸውም።
[61] World Book Encyclopedia 1986; stars
[62] "ገላጣ በሆነ ጨለማ ምሽት፣ በጥቂት ሺዎች የሚቆጠሩ ከዋክብትን በጥሬ ዐይናችን ልናይ እንችላለን። በአጕሊ መነጽር እና ቴሌስኮፕ ለመቁጠር ተስፋ የማናደረገውን ያህል ከዋክብትን እናያለን። ምንም እንኳን እያንዳንዱ ኮከብ ልዩ ቢሆንም ከዋክብት በሙሉ የሚጋሩት ነገሮች አሏቸው" (Cornell University Astronomy website: http://curious.astro.cornell.edu/stars.php) በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ከዋክብት እንደማይቆጠሩ ይናገራል። (ዘፍጥረት 15:5 ፤ 22:17)
[63] Ramsay, Sir William Mitchell. The Bearing of Recent Discovery on the Trustworthiness of the New Testament. Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1953, p. 222.
[64] Ramsay, Sir William Mitchell. The Bearing of Recent Discovery on the Trustworthiness of the New Testament. Grand Rapids, MI:

Baker Book House, 1953, p. 222.ይሄ መጽሐፍ የጲላጦስን የድንጋይ ላይ ጽሁፍና የሄሮድስን ቲያትር ፎቶ ያካትታል።
[65] Bruce, F.F. Archaeological Confirmation of the New Testament. (Revelation and the Bible. Edited by Carl Henry) Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1969.
[66] Josephus, Flavius. Antiquities 18: 2, 2; 4, 3
[67] የቀያፋ የመቀበሪያ ሳጥን ፎቶ እና ዝርዝሩ፦ ANCDOCS/westsem/caiaphas.html
[68] Glueck, Nelson. Rivers in the Desert. NY: Farrar, Strauss & Cudahy, 1959, p. 136. ግሉኤክ የመካከለኛው ምስራቅ የሥነ ቅርስ ቁፋሮዎች ላይ አተኩሮ የሚሰራ ባለሙያ ነው።
[69] ሞርሞኒዝም በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሚከተሉት ሐይማኖት ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በተለየ የ ሞርሞን መጽሐፍ በሥነ ቅርስ የተረጋገጠ አይደለም። በዋሽንግተን ዲስ የሚገኘው ስሚዝሶኒያን ተቋም እንዲህ ሲል ይደመድማል “ስሚዞኒያን የሥነ ቅርስ ባልሙያዎች በአዲሱ ዓለም ሥነ ቅርስና በርዕሰ ጉዳዩ (የሞርሞን መጽሐፍ) መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አላዩም።” (Martin, Walter. The Kingdom of the Cults. Minneapolis, MN: Bethany House Publishers, 1997, pp. 200-202.)በተጨማሪ በምዕራፍ 6 ውስጥ የሚገኘውን በተመሳሳይ ርሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩረውን የግርጌ ማስታወሻ 91 ተመልከቱ። የመጽሐፍ ቅዱስን እና ቁርዓንን ከሥነ ቅርስ አንጻር አነጻጽሮ መመልከት እዚህ ቦታ ይመልከቱ፦ http://www.debate.org.uk/?s=archaeology
[70] Free, Joseph P. and Howard F. Vos. Archaeology and Bible History. Grand Rapids, MI: Zondervan, 1992, p. 294.
[71] ሙስሊሞች እና ሞርሞኖች ቅዱሳት መጽሐፍቶቻቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመገኘታቸው አንደኛው ታላቁ ማስረጃቸው የሚተየው በተጻፉበት የአጻጻፍ ስልት ውስጥ እንደሆነ ይናገራሉ። አንድ የሙስሊም ድረ ገጽ እንዲህ ይላል፦ “የቅዱስ ቁርዓን ትልቁ መሚገቻ... ከአስራ አራት ክፍለ ዘመናት በፊት ቁርዓን ከተገለጠ ጀምሮ በውበት፣ በአገላለጽ እና በሞገስ እንደ ቁርዓን የሚሆነ አንድ ምዕራፍ አንድም ሰው አልጻፈም...” (www.islam-guide. com/frm-ch1-2.htm)። የሞርሞን ደረ ገጽ ተመሳሳይ ነገር ይናገራል፦ “የሞርሞን መጽሐፍ ሙግት፦ ... ጽሁፋችሁን የጥንታዊውን ዕብራይስጥ ቁጥሮችን እና ዘዬ በመጠቀም መጽሐፍ ጽፋችሁ ካሳተማችሁ ከበርካታ ዓመታት በእንግሊዘኛ ተናጋሪው ዓለም ውስጥ እንደገና ሊገኝ እና የማይችል መሆን አለበት...” www.fwrb.org/BOMChallenge.html
[72] በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ረጅሙ ምዕራፍ መዝሙረ 119 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ውስብስብ የሥነ ጽሁፍ አወቃቀር ያሳያል። መዝሙር 119 ቁልቁል ከተቀመጡ 22 ክፍሎች እና እያንዳንዳቸው 8 ቁጥር ባላቸው ፊደላት የተዋቀረ ነው። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙ 8 ጥቅሶች ከዕብራይስጥ የፊደል ገበታ

በተወሰዱ ፊደላት የሚጀመር ነው። በክፍል 1 እያንዳንዱ ጥቅስ የሚጀምረው በአሌፍ (በዕብራይስጥ የፊደል ገበታ የመጀመሪያ ፊደል ነው) የክፍል 2 ስምንት ጥቅሶች የሚጀምሩት በቤት (በዕብራይስጥ የፊደል ገበተ ሁለተኛ ፊደል)፣ እናም በዚህ መልኩ ሁሉንም የዕብራይስጥ ፊደላት ያካትታል። ያንን እንደገና ለመጻፍ ሞክሩ። በፍጹም አትሞክሩት። ከዚያ ይልቅ መዝሙር 119 አንብቡ እና በቃላቱ ኃይል ውስጥ ራሳቸሁን አሰገቡ። "ለዘላለም ለእኔ ነውና ትእዛዝህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ።" (መዝሙር 119 ፡99)

## ምዕራፍ 5:- የእግዚአብሔር ፊርማ

73 Wallenfels, Ronald and Jack M. Sasson. The Ancient Near East. Volume IV. NY: Charles Scribner's Sons, 2000; also see: Carl Roebuck. The World of Ancient Times. NY: Charles Scribner's Sons, 1966, p. 355.

74 "ታላቁ እስክንድር ለዘጠኝ ወራት (332 ዓዓ)ከተማዋን ከከበበ በኋላ መጠኗን ቀነሰው ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አላጠፋትም። ከዚህ ጥቃት ግን ጢሮስ ፈጽሞ አላገገመችም..." (Avery, Catherine B. & Jotham Johnson. The New Century Classical Handbook. NY: Appleton-Century-Crofts, Inc., 1962, p. 1130.)

75 Matthews, Samuel W. "The Phoenicians: Sea Lords of Antiquity," Washington, DC: National Geographic, August 1974, p. 165.

76 ዘፍጥረት 26:3፤ 28:15 **ማስታወሻ** ፦ እግዚአብሔ ር ከአብርሐም፣ ከይስሐቅ እና ከያዕቆብ ዘር ለተገኘቸው ሃገር ቃል የገባው ምድር "በአሕዛብ መካከል"(ሕዝቅኤል 5:5) በሚገኝ ቁለፍ ቦታ ይ ይገኝ ነበር። በተጨማሪም ሐዋርያት 1: 8 ፤ 2: 5 ተመልከቱ።

77 Josephus, Flavius, The Complete Works of Josephus. (William Whiston) Grand Rapids, MI: Kregel Publications, 1967, pp. 566-568, 580-583, 588-589.

78 በምሳሌ ለማሳየት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት በሂትለሯ ጀርመን ውስጥ ይገኙ የነበሩ አይሁድ አይሁድ ተብለው መታወቅ አይፈልጉም ነበር። ይናገሩ የነበረው ጀርመንኛ ነበር ፣ የጀርመናውያንን ታክስ ይከፍሉ ነበር ለጀርመን የመጀመሪያውን የዓለም ጦርነት ተዋግተው ነበር። ነገር ግን ናዚዎች አይሁድ አሏቸው። በጥቂት ዓመታት ውስጥም 6 ሚሊዮን አለቁ "ዕልቂቱ ... በታሪክ ውስጥ በደንብ የተመዘገበ ወንጀል ሆነ።" (Phillips, John. Exploring the World of the Jew. Neptune, NJ: Loizeaux Brothers, 1993, p. 109) አርዕሰተ ዜና የነበረውን መጣጥፍ ተመልከቱ፦ "ናዚዎች በአውሮፓ ውስጥ 6 ሚሊዩን አይሁድ እንደ ፈጁ አመኑ" (Nazis Admit Murdering 6 Million Jews in Europe) Bourne, Eric. The Palestine Post, Sunday, December 16, 1945.

79 ኢሳያስ 44:18፤ ኤርሚስ 5:21፤ ዮሐንስ 5:39-47፤ 2 ቆሮንቶስ 3:12-

16፤ ሮሜ 9-11። ማስታወሻ፦ ከ2600 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የእስራኤል ዳግም ልደት የሚፈጸመው በሦስት የተለያዩ ደረጃዎች እንደሆነ ነግሮት ነበር። እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ አካል በሚሰበሰቡ እና ሕይወት ወደ ውስጣቸው በሚተነፈስባቸው የደረቁ አጥንቶች ጋር አነጻጽሯት ነበር (ሕዝቅኤል 37:1-14)።

[80] ዘፍጥረት 37-50 በወንጌላት ውስጥ ከተመዘገበው ከጌታ ኢየሱስ ሕይወት ጋር አነጻጽሩት። የንባብ ጥቆማ ፦ Joseph Makes Me Think of Jesus, by William MacDonald. Grand Rapids, MI: Gospel Folio Press.

**ምዕራፍ ስድስት ፦ ዘለቄታዊ ምስክርነት**

[81] **"እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፤ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና**። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ **ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ**" (ሮሜ 1:19-20 አመት) መጽሐፍ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎችም ቢሆኑም እንኳን "እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ *ሥራ* ያሳያሉ።" (ሮሜ 2:15)። ነገር ግን ሰዎች ተጨማሪ እውነት ከመፈለግ ይልቅ ፣ በዙ ሰዎች ስህተትን ያሳድዳሉ።

[82] በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡትን የዘር ሐረጋት ዕድሜ በመደመር አዳም የኖህ አባት (የአዳም 9ኛ ትውልድ)የ 50 ዓመት ሰው እስኪሆን ድረስ አልሞተም (ዘፍጥረት 5)።

[83] "ጠንቋዮችም ፈርዖንን፦ ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው አሉት" (ዘጸአት 8:19) በተጨማሪም ዘጸዓት 12:30-33 ተመልከቱ። ሙሉውን ታሪክ ለማግኘት ፦ ዘጸአት 5-14።

[84] ምንም እንኳን ሙሴ ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የጻፈ ቢሆንም የኢዮብ መጽሐፍ ከቶራ በፊት ተጽፎ ሊሆን ይችላል (አብርሐም ዘመን) ይሄም በአሁኑ ጊዜ የሚገኝ እጅግ በጣም ጥንታዊ ተጽፎ ያለቀ ጽሁፍ ያደረገዋል። ይሄ ቀን ትክክል ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በ2000 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው ማለት ነው።

[85] DeHaan, Dennis. Our Daily Bread, May 6, 2006. Grand Rapids, MI: RBC Ministries.

[86] አንዳንዶች "እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነብያት አሳሳች መልዕክታቸውን እንዲናገሩ የሚፈቅደው ለምንድን ነው ሲሉ ይጠይቃሉ?" ሙሴ ይህንን ጥያቄ በቶራ ውስጥ መልሶታል "**በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሣ**፥ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ፥እንደ ነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም፥ እርሱም፦ ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ፥አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወድዱት

እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር **ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ**።" (ዘዳግም 13:1-3)
[87] 1 ነገሥት 18፤ 1 ነገሥት 19:18፤ ሮሜ 11:14
[88] Smith, James E. What the Bible Teaches about the Promised Messiah. Nashville, TN: Thomas Nelson Publishers, 1993, pp. 470-474; በተጨማሪ፦ Phillips, John. Exploring the World of the Jew. Neptune, NJ: Loizeaux Brothers, 1993, pp. 80-81.
[89] Taylor, John. "Jones Captivated San Francisco's Liberal Elite," San Francisco Chronicle, November 12, 1998.
[90] Smith, Joseph. Pearl of Great Price. Joseph Smith – History; 1:15-16.
[91] በታሪክ እና በሥነ ቅርስ ከተረጋገጠው መጽሐፍ ቅዱስ በተለየ የሞርሞን መጽሐፍ የተረጋገጠ አይደለም። ፕሮፌሰር ቶማስ ስቱዋርት "ቅዱስ መጽሐፋቸውን" ለማረጋገጥ በሞርሞኖ በራሳቸው ዩኒቨርስቲ ብሪግሃም ያንግ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሥነ ቅርስ ክፍል አቋቋሙ። ከ25 ዓመታት ብርቱ ጥናት በኋላ የበጋና የክረምት፣ የአቀማመጥ፣ የመልክዓ ምድር ፣ የሰዎች፣ የሳንምቲም ወይም በሞርሞን መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ሰፈራችን የሚያረጋግጡ ነገሮች ማግኘት አልቻሉም። ፈርጉስን የሞርሞን መጽሐፍ መልክዓ ምድር "ልቦለዳዊ" ነው በሚል ደምድመዋል። (Martin, Walter. The Kingdom of the Cults. Minneapolis, MN: Bethany House Publishers, 1997, pp. 200-202)

### ምዕራፍ ሰባት ፦ መሠረት

[92] መጽሐፍ ቅዱስ 66 የተለያዩ መጽሐፍትም ማለትም 39 የብሉይ ኪዳን እና 27 የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን ይዟል። በታሪክ ውስጥ በሰተኋላ የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን (እንደ ብዙ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትትወፊታቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ የሚያደርጉ) በበብሉይ ኪዳን እና በአስ ኪዳን መጽሐፍት መካከል 11 መጽሐፍትን ጨመረች። እነዚህ አዋልድ (የሁለተኛ ቀኖና መጽሀፍት) የተሰኙት መጽሐፍት በብሉይ ኪዳንን እና በአዲስ ኪዳን መካከል ባለው ዘመን ነው። ምንም እንኳን አስገራሚ ታሪካዊ እና ገድላዊ ታሪካትን ቢይዙም ዕብራውያን አማኞች በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፉ ብለው አልተቀበሏቸውም። በ1947 የተገኙ በርካታ የሙት ባህር ጥቅልሎች ማብራሪያ የሚሰጡት በ39 መጽሐፍት ላይ እንጂ በአዋልድ ላይ አይደለም። መሲሁ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ፣ ብዙ ጊዜ ብሉይ ኪዳንን የጠቀስ ሲሆን ከአዋልድ ውስጥ ግን በፍጹም አልጠቀሰም። አዋልድ በአዲስ ኪዳንም አልተጠቀሰም። ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት 39 መጽሐፍት እግዚአብሔር በቀጥታ በተናገራቸው ቃሉን ባረጋገጠላቸው ነብያት የተጻፉ ናቸው "በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ

ልዩ ተአምራትም መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት፡፡" (ዕብራውያን 2:4) እንደ አዲስ ኪዳን ከሆነ ክርስቶስ ምድርን ከጎበኘበት ጊዜ በኋላ የኖሩ አማኞች የሐዋርያትን እና አዲስ ኪዳንን መጽሐፍት ከብሉይ ኪዳንና ነብያት እኩል ይቀበሉት ነበር፡፡ አዋልድን በተመለከተ ይህንን ልንል አንችልም፡፡

93 ሉቃስ 24:25-28 ፤ ዮሐን ስ5:39-47 የእግዚአብሔርን መልዕክት በቅደም ተከተል የሚያስቀምጥ ነገር የምትፈልጉ ከሆነ፦ www.goodseed.com

## ምዕራፍ 8፦ እግዚአብሔር ማን ነው

94 የሥነ ፈለክ ባለሙያዎች የአጽናፈ ዓለሙን ታሪክ "በምልከታ እና ጽንሰ ሐሳባዊ ጥረት" ለመረዳት ይሞክራሉ፡፡ (Loeb, Abraham. "The Dark Ages of the Universe," Scientific American, November 2006) ምንም እንኳን እውቀታቸው በምልከታ እና **ጽንሰ ሐሳብ** ላይ የተመሰረተ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ አማኞች ዕውቀት ግን በምልከታ እና መለኮታዊ ፊርማ ባለው **መገለጥ** ላይ የተመሰረተ ነው(በአንድ አምላክ እና አንድ መልዕክት ምዕራፍ 5 እና ምዕራፍ 6 እንዳየነው)፡፡ እግዚአብሔር እውነቱን እውነት መሆኑን እንድናውቅ አድርጎ ገልጧል፡፡

95 የኢዮብ መጽሐፍ 38:6-7 እንደሚያሳየን መላእክት የእግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥር እያዩ ይመለከቱ እና ይደሰቱ እንደነበር ያሳያል፡፡ ኢዮብ የግጥም መጽሐፍ ነው ፣ ስለዚህም መላዕክት "የማለዳ ከዋክብት"እና "እግዚአብሔር ልጆች" ተብለው ተገልጸዋል፡፡ እነዚህ ሁለት አገላለጾች የተለየ ነገርን የሚያሳዩ አይደሉም፡፡ የድጋሚ ገለጻው የትይዩነት ምሳሌ የዕብራይስጥ ግጥም ምሳሌ ነው፡፡ ኢዮብ 1:6 ፤ 2:1 ተመልከቱ፡፡

96 ከመጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻፍት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መላእክትን ይገልጣሉ፡፡ ለምሳሌ ፦ ዘፍጥረት 3:24፤ 16:7-11፤ 18:1-19:1፤ 1 ነገሥት19:5-7፤ መዝሙር 103:20-21፤ 104:4፤ ዳንኤል 6:22፤ዕብራውያን 1:4-7፣14፤ 12:22፤ ማቴዎስ 1:20፤ 2:13፣19-20፤ 22:30፤ 26:53፤ ሉቃስ 1 & 2፤ 2 ተሰሎንቄ 1:7፤ ራዕይ 5:11፤ 18:1፤ 22:6-16፣ ወዘተ፡፡

97 ዘዳግም 10:14፤ 2 ቆሮንቶስ 12:2፣4፤ ዮሐንስ 14:2፤ መዝሙር 33:13፤ 115:3፤ 1 ነገሥት 8:39

98 Vine, W.E., M.A. An Expository Dictionary of New Testament Words. Westwood, NJ: Fleming H. Revel Company; 1966, p. 229.

99 የእግዚአብሔር ስድስት የፍጥረት እና ሰባተኛ ቀን ዕረፍት ለሰው ልጆች በዓለም ዙሪያ እስካሁን ሚያከብሩትን መለኮታዊ የጊዜ ሠሌዳ መነሻ ሆነ፡፡ ከቀናት፣ ወራት እና ዓመታት በተለየ ሳምንት ከስነ ፈለክ ጋር የተገናኘ አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር የወሰነው ነው፡፡

100 "የቢግ ባንግ" አራማጆች ብርሃን ከፀሐይ እና ከምድር በ

9000000000 ዓመታት ቀደሞ እንደነበረ ይናገራሉ! (Loeb, Abraham. "The Dark Ages of the Universe," Scientific American; November 2006, p. 49.)

[101] ወደፊት ውሃ በምትጠጡበት ፍሬያቸውን "አመሰግናለሁ" በሉት። ውሃ ጥማችንን ከማርካቱ እና በሕይወት እንድንኖር ከማደረጉ ባሻገር አስገራሚ ነው። ውሃ ሲቀዘቅዝ የሚለጠጥ ብቸኛው ፈሳሽ ነው፣ ስለዚህም ይንሳፈፋል። ወሃ እንደሌላ ቁስ ከሆነ እና በሚቀዘቅዝበት ጊዜ ከተኮተር ፣ በባህር፣ በሐይቅ ፣በወንዝ ስር ይዘቅጣል። ብዙውን ጊዜ አይቀልጥም ፣ በመቀጠል ምትኩስ ወሃችን ቆልፎ ፣ ቀዝቅዞ ሊቀር ይችላል። መልካሙ ነገር ፈጣሪ ይህንን አስቦበታል።

[102] የጨረቃ ጨለማ ገጽታ ለመጀመሪያ የታየው ታህሳስ 24 1968 ኣፖሎ 8 መንኮራኩር ጭረቃን በዞረቸ ጊዜ ነው። አስገራሚው ነገር በዚያው ቀን ሦስት ጠፈረተኞች ዘፍጥረት 1 ተመልካቹ በቴሌቪዥን እያየ አነበቡ። (Reynolds, David West. Apollo: The Epic Journey to the Moon. NY: Harcourt, Inc., 2002, pp. 110-111)

## ምዕራፍ 9:- የሚመስለው የለም

[103] እግዚአብሔር ራሱን "እኛ "ብሎ የሚጠራበው ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች ፦ ዘፍጥረት 3:22 ፤ 11:7 ፤ ኢሳ ስ6:8 (ማስታወሻ ፦ በቁርዓን "አላህ" በተደጋጋሚ በብዙ ቁጥር ይናገራል። በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ምዕራፍ 3 የተጠቀሱ የቁርዓን ጥቅሶችን ይህንን ያሳያሉ።

[104] ዘፍጥረት 1:1-3 ይህንን ክፍል ሲጀምር እግዚአብሔር እግዚአብሔር በአሐዱ ሥሉስነት እንደሚኖር በመግለጽ አይጀምርም፣ የቃላት አጠቃቀሙ በመጽሐፍ ቅዱስ በሰተሁላ ተገለጠው ማበራሪያ ጋር የተጣጣመ ነው። ቅዱሳት መጽሐፍት የእግዚአብሔር ሦስት አካላት በፍጥረት ስራ ውስጥ ተካተዋል።

[105] ዳዊት በእስራኤል ላይ በነገሰ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል፦ "የብንያምም ልጆች ወደ አበኔር ተሰበሰቡ፥ **በአንድነትም** [ኤኻድ]ሆኑ፥ በኮረብታም ራስ ላይ ቆሙ።" (2 ሳሙኤል2:25 ይሄንኑ "ጌታ **አንድ** ነው" የሚለው ቃል ራሱ ብዝኀነት ያለበትን አንድነት ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።

[106] በርካታ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ውስብስብ አንድነት ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውለዋል፡-ዘፍጥት 17: 1-3 ፤ 18:1-3 እግዚአብሔር ለአብርሐም በአካላዊ ቅርጽ ተገለጠለት። እነዚህ የፊት ለፊት ግንኙነቶችእንጂ ሕልም ወይም ራዕይ አልነበሩም። ዘፍጥረት 32:9-15 ፤ ዘጸአት 3:1-6 ፤ 6:2-3 ፤ 24:9-11 ፤ 33:10-11፡፥ ዘጸአት 33:10-11 ከ ዘጸአት 33:20 ጋር አነጻጸሩ። ሙሴ ፊት ለፊት የተነጋገረው ከአንዱ የእግዚአብር አካል ጋር ነው(ወልድ)። ወስብስብ ነው? አዎ። እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው። ዮሐንስ 1:1-18 ተመልከቱ። እነዚህ ተጨማሪ የብሉይ ኪዳንን ምንባባት ከእግዚአብሔር ብዝኀነት

ካለው አንድነት ውጪ ልንረዳቸው አንችልም፦መዝሙር 2 ፤ መዝሙር 110 ፡1 (ከማቴዎስ 22:41-46 ጋር አነጻጸሩ) ፤ ምሳሌ 30:4 ፤ ኢሳያስ 6:1-3 (ከዮሐንስ 12:41 ጋር አነጻጽሩ)፤ ኢሳያስ 26:3-4 ፤ ኢሳያስ 40:3-11 ፤ ኢሳስ 43:10 -11 (ኢሳያስ 7:14:፤9: 6-7) ፤ ኢሳያስ 48:16 ፤ ኢሳያስ 63: 1-14 ፤ ኢሳያስ 49:1-7 ፤ ኤርሚያስ 23:5-6 ፤ ዳንኤል 7:13-14 ፤ ሆሴዕ 12:3-5 ፤ ሚኪያስ 5:2 ፤ ሚልኪያስ 3:1-2 ፤ ወ.ዘ.ተ።

107 ሉቃስ 15:11-32 ፤ በተጨማሪ የዮሐንስን መልዕክት አንብቡ።

108 ነብዩ ዳዊት መሲሁን የእግዚአብሔር ልጅ የሚልበትን መዝሙር 2 አንብቡ። በተጨማሪም የወልድን ስሞች እና መጠሪያዎች አስተውሉ። እሱ እንዲህ ተብሎ ተጠርቶ ነበር ፦ "በር" (ዮሐንስ 10) ያ ማለት ግን የእንጨት ወይም የብረት በር ነው ማለት አይደለም። እሱ እንዲህ ተብሎ ተጠርቷል፦ "የሕይወት እንጀራ" (ዮሐንስ 6) ነገር ግን ያ ማለት እሱ ሙልሙል ዳቦ ነው ማለት አይደለም። ወይም ደግሞ "የእግዚአብሔር ልጅ" ማለት እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ ልጅ ወልዷል ማለት አይደለም። ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ፣ 3 ፣ እና 5 ተመልከቱ።

109 Le Soleil, March 14, 1984: «Bienfaiteur sincère, il considérait ses 2.000 employés **comme ses enfants** et partageait leur problèmes, leur soucis et leur joie. Le 'Vieux' comme l'appelaient familièrement et tendrement son personnel, était **un grand fils du Sénégal**.»(ትርጉሙ፦ አንድ ቅን የሆነ ሰው ወዳድ ሰው 2000 ሰራተኞቹን ችግራቸውን ፣ የሚያሳስባቸውን ነገር እና ደስታቸውን በመካፈል አንደ ልጆቹ ያያቸው ነበር። ሰራተኞቹ በፍቅር « ሽማግሌው » እያሉ የሚርሉት ይሄ ሰው **የሴኔጋል ታላቅ ልጅ** ነበር። »)

110 ልክ እንደ እግዚአብሔር እንደ ራሱ መንስ ቅዱስ እኛ ቀድመን የያዝነው አሳቤ አያሟላልንም። ሰማይን በጨረፍታ እንዲያይ የተፈቀደለት እና መንፈስ ቅዱስን ያየ ከእግዚአብሔር ነብያት አንዱ "በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፤ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።" (ራዕይ 4:5) ሌላኛው ነብይ ደግሞ ከእግዚአብሔር ብቻ የሚመነጩትን ሰባቱን ባህርያት የሚያካፍል አድርጎ ገልጾታል ፦ "**የእግዚአብሔር መንፈስ**፤ **የጥበብ**ና **የማስተዋል** መንፈስ፤ **የምክር**ና **የኃይል** መንፈስ፤ **የእውቀት**ና **እግዚአብሔርን የመፍራት** መንፈስ ያርፍበታል።" (ኢሳያስ 11:2)

111 በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ቃል ገብቶ ነበር "**አብ በስሜ** የሚልከው ግን **መንፈስ ቅዱስ** የሆነው አጽናኝ **እርሱ** ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።" (ዮሐንስ 14:26) ይሄ ቃል በአብ ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ሁል ጊዜ ያለውን ፍጹም አንድነት የሚያሳዩ ቃላት ናቸው። እንደ አብና ወልድ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ነው ("እርሱ…")። በመንፈስ ቅዱስ ዙሪያ ተጨማሪ ከፈለጋችሁ ምዕራፍ 16:22 እና 28 ተመልከቱ። ከዚህም በተሻለ መልዕክታትን እና የሐዋርያት *ሥራ* ለመንፈስ ቅዱስ ስራ የበለጠ ትኩረት በመስጠት አንብቡ።

[112] ወንጌል ወልድ ከአብ ጋር ሲያወራ "ዓለም **ሳይፈጠር** በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።" እንዳለ ይናገራል። በተጨማሪም ወልድ "አባት ሆይ፥ ዓለም **ሳይፈጠር** ስለ ወደድኸኝ" (ዮሐንስ 17:5 ፣ 24) ሲል እንሰማዋለን። በተጨማም ሚኪያስ 5:2 ፤ ኢሳያስ 9:6 ተመልከቱ። የመንፈስ ቅዱስ አንደኛው መጠሪያው "**ዘላለማዊ** መንፈስ ነው" ዕብራውያን 9:14)
[113] ዘጸአት 20:22፤ ዕብራውያን 12:25፤ ሉቃስ 3:22፤ 5:24፤ ዮሐንስ 1:1-18፤ 3:16- 19፤ 17:22፤ ሐዋርያት 5:3፤ 7:51፤ ገላትያ 4:6፤ ወዘተ።
[114] በአረብኛ ቋንቋ አላህ የሚለው ቃል ፣በመጀመሪያ ትርጉሙ ፣ የአማርኛው "እግዚአብሔር" የሚል ቃል አቻ ነው። በዘፍጥረት 1:1 እንደሚገኘው ጥቅስ ፦ "በመጀመሪያ **እግዚአብሔር** … ፈጠረ…" ወይም ደግሞ በዮሐንስ 1: 1እንደሚገኘው ጥቅስ ፦ "በመጀመሪያ ቃል ነበር። በ**እግዚአብሔር** ዘንድ ነበረ። ቃለም **እግዚአብሔር** ነበረ።" የእግዚአብሔር የአረብኛ መጠሪያ አላህ ነው፣ ትርጉሙም ታላቁ አካል ማለት ነው። ይሄ ታላቅ አካል ሊታወቅበት የሚፈልገው ስም እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል። ብዙዎች እንደዚያ ቢያምኑም "አላህ" የእግዚአብሔር ተገቢ ፣ የግል መጠሪያ አይደለም። በዙዎች እንደዚያ ቢያስቡም "እግዚአብሔር" ተገቢ ግላዊ መጠሪያ አይደለም።

## ምዕራፍ 10:- ልዩ ፍጥረት

[115] Guinness, Alma E. ABC's of The Human Body. Corporate Author: The Reader's Digest Association, 1987, p. 22.
[116] Gates, Bill. The Road Ahead. NY: Penguin Group, 1995, p. 188.
[117] ከዚህ የጠለቀን መንፈሳዊ እውነት ለመግለጥ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የተጣጣመውን የሰውን ልጅ አካል፦ "ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል። (ኤፌሶን 4:16)
[118] እነዚህ ሐሳቦች የተወሰዱት ከጆን ፊሊፕ አስገራሚ የዘፍጥረት ማብራሪያ ላይ ነው። (Phillips, John. Exploring Genesis. Chicago: Moody Press, 1980) ማስታወሻ፦ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ፣ ስጋን እና አካልን ለያይቶ ያሰቀምጣቸዋል። 1 ተሰሎንቁ 5:23 ፤ዕብራውያን 4:12-13 ፤ ዮሐንስ 4:24።
[119] ኤደን ኢራቅ ክልል ውስጥ ትገኛለች የሚለው ሐሳብ በዘፍጥረት 2:13-14 በሚገኝ መልክዓ ምድራዊ መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው። **ማስታወሻ**፦ አንዳንዶች የኤደን የአትክልት ቦታን የኤደን ገነት ብለው ይጠሩታል መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደዚያ አይደለም። ምድራዊቷ ገነት ከሰማያዊቷ ገነት ጋር መምታታት የለባትም።
[120] Henry, Matthew. Matthew Henry's Commentary. Grand Rapids, MI: Zondervan, 1960, p. 7.

121 አዳም (አዳማ) በዕብራይስጥ ሰው ማለት ነው፤ ቀጥተኛ ትርጉሙም ቀይ አፈር ማለት ነው፤ ምክንያቱም የተወሰደው ከአፈር ነውና። ሔዋን (ካቫ) ማለት ሕይወት ማለት ነው "የሕያዋን እናት ናትና።" (ዘፍጥረት 3:19-20)

## ምዕራፍ 11:- የእኩይ መግባት

122 "አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፣ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!" (ኢሳያስ 14:12) በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሉሲፈር የተሰኘው መጠሪያ ብርሃን ተሸካሚ ማለት ሲሆን በዕብራይስጡ ምንባብ ውስጥ አይገኝም። የዕብይስጡ ሄሌል ወይም አንጸባራቂው የተሰኘ የላቲን ትርጉም ነው። ኢሳያስ 14 እና ሕዝቅኤል 28 የሁለት ትርጉም ሕግን በምሳሌነት የሚያሳይ ነው። ከላይ ስንመለከተው ምንባባቱ ምድራዊ ነገሥታትን የሚያሳዩ ይመስላሉ። ኢሳያስ "የባቢሎን ንጉስ" ሲል ይጠቅሳል ሕዝቅኤል "የጢሮስ ንጉስ" ሲል ይጠቅሳል። ነገር ግን ሁለቱም ምንባባት ለሰው ብቻ የማይሆኑ ነገሮችንም ይጠቅሳሉ። እነዚህ ጥቅሶች ከሌሎች ምንባባት ጋር ተገዝውበው ሲጠኑ (ሉቃስ 10:18 ፤ ኢዮብ 1:6-12 ፤ ራዕይ 12:10 ፤ 1ጴጥሮስ 5:8 ፤ወዘተ)፣ ምንባባቱ የሚናገሩት ከእኩይ ነገስታት ጀርባ ሆኖ ስለሚያነሳሳቸው ተጽዕኖ ስለሚፈጥርባቸው ሰይጣን መውደቅ እንደሆነ ግልጽ ይሆንልናል።

123 ራዕይ 12:4

124 ማቴዎስ 10:28 ፤23:33 ፤ ማርቆስ 9:43-48

125 ራዕይ 20:10-15

## ምዕራፍ 12 ፦ የኀጢአት እና የሞት ሕግ

126 የጋራ ጥያቄ፦ የሚሞቱ ሕጻናት እና ጨቅላዎች ምን ይሆናሉ? በውስጣቸው ስላለው የውርስ ኀጢአት ይኮነናሉ(መዝሙር 51:5 ፤ 58:3)? ጻድቅ ፈራጅ ፍርድን ይሰጣል (ዘፍጥረት 18:25)። ሰው ሊረዳው ስለማይችለው ነገር ፍርድ አይሰጥም። ሰዎችን ስለሚይውቁት ነገር ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፣ የእግዚአብሔርን እውነት ለማግኘት ፈልገው ከሆነም ያውቃቸዋል (ሮሜ 2:11-15 ፤ መዝሙር 34:10 ፤ ኢሳያስ 55:6)። የሰው ልጅ አንድ ጊዜ ሞራላዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን በቂ የሆነ የብስለት ደረጃ ላይ ሲደርስ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ይሆናል (ዘዳግም 1:39 ፤ ኢሳያስ 7:16 ፤ 2 ሳሙኤል 12:23 ፤ ማቴዎስ 18:10 ፤ 2 ጢሞቴዎ ስ3:14-17)። አንድ ግለሰብ በየትኛው የዕድሜ ክልል ላይ ሲደርስ ስለ ሐጢአቱ ተጠያቂ እንደሚሆን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው። መቋጫው ምንም ይሁን ምን እግዚአብር ለእያንዳንዳችን ያለው መልዕክት፦ "እነሆ፣ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ፣ የመዳን ቀን አሁን ነው።" (2 ቆሮንቶስ 6:2)

127 ራዕይ 20:14-15 ፤ 2:11 ፤ 21:8 ፤ ማቴዎስ 25:46

**ምዕራፍ 13:- ምሕረት እና ፍትህ**
ይሄ ምዕራፍ የግርጌ ማስታወሻ የለውም።

**ምዕራፍ 14 ፦ እርግማን**
[128] "ኮብራና በአ ያላቸው ሚዛን መጠበቂያዎች... ከቆዳቸው በታች ትንሽ ወደ አይነ ምድር መውጫቸው በጣም ተጠግቶ የሚገኝ ግማሽ ኢንች የሚረዝም ወጣ ያለ እንደ ጥፍር ያለ ነገር አላቸው። በእርግጥም እንዚህ ጉጦች እግር ሳይሆኑ የላይኛው እግር ቅሬታ የሆኑ አጥንቶች ናቸው። ወንዶቹ አሁንም እነዚህን የአካል ክፍሎቻቸውን ተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ምኢፈልጉበት እና በጠብ ጊዜ ይጠቀሙበታል እንጂ ለመሄድ አይጠቀሙበትም። ሌሎእባቦች ግን እግር የላቸውም"
[አንዳንዶች] ይሄንን የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብን እንደሚግፍ አድርገው ሊፈቱት ይሞክራሉ። ልንረዳው የሚገባን ነጥብ ፦ የእባቦች አካላዊ ገጽታ መጽሐፍ ቅዱስ ከሺህ ዓመታት በፊት ከተጻፈው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ብቻ ነው።
[129] በተጨማሪም፦ ራዕይ20:2 ፤ ሉቃስ 10:18 ፤ 2 ቆሮንቶስ 11:3 ፤14፦ "እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት" ስለዚህ "ሰይጣን ራሱን የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለወጣል።"
[130] ዘጸአት 29:7 ፤ 1 ሳሙኤል 10:1፤ 2 ነገሥት 9:6፤ መዝሙር 45:7
[131] ምዕራፍ 18 እግዚአብሔር የማዳን እቅዱን የዘገበበትን ሦስት ምክንያት ይገልጣል። መጽሐፍ ቅዱስን በቅደም ተከተል የማጥናቱ አንደኛው አስደሳች ነገር፣ እግዚአብሔር ሳጢአተኞችን ከሠይጣን፣ ከሳጢአት እና ከሞት ለማውጣት እግዚአብሔር ያወጣው ዕቅድ እየተገለጠ የሚሄድበት ድራማ ነው። እግዚብሔር ጥበቡ፣ ዕቅዱ በሂደት እንዲፈጸም አሰናድቶታል "ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ነው።" (ኢሳያስ 28:10)
[132] "ያንን አዋቂነት ትለዋለህ ?" በሚል ርዕስ በተዘጋጅ የቀልድ ገጹ የታይም መጽሔት የአዋቂ ንድፍ አውጪ ጽንሰ ሐሳብን (እግዚአብሔርን) ያራክሳል፦ "የዕድሜ ግፋት በተሻለ ክህሎት እና ክብር መከናን አይቻልም ነበር? ለምሳሌ ፦ ያረጁ ሰዎች ሽብሻባና ጨምዳዳ ከሚሆኑ ኪነጥበባዊ በሆነ መንገድ ጥፍት ቢሉ አይሻልም ነበር።" (Handy, Bruce and Glynis Sweeny. Time, July 4, 2005, p. 90) በተጨማሪም (The Improbability of God) "የእግዚአብሔር ሕልውና ዕድል ለሽነት" በተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ (Neither Intelligent nor Designed)አዋቂነትም ንድፍም የሌለበት በተሰኘ ምዕራፍ እንዲህ ይላል "በዚህ አይነት ቀሽም በሆነ ሁኔታ ለተነደፈ ፍጥረት አዋቂ ንድፍ አውጪን ነው ማለት ከሰው ልጅ የደከመ እኔነት ነው ከማለት የበለጠ ምን ይባላል?" (Bruce and Frances Martin in The Improbability of God by Michael Martin and Ricki Monnier. Amherst, NY: Prometheus Books, 2006, p. 220)

## ምዕራፍ 15:- እጥፍ ችግር

[133] Associated Press, May 20, 2006 http://forums.anandtech.com/ archive/index.php/t-1869858.html

[134] ሥርዓታዊ መታጠብ የብሉይ ኪዳን ሕግ ነው (ዘሌዋውያንን ተመልከቱ)። ኀጢአተኞችን በእግዚአብሔር ፊት መንፈሳዊ ቆሻሻ እንዳለባቸው ለማስተማር የተቃዱ ናቸው። በመሲሁ በኩል ሙሉ መንጻት እና ጽድቅን ስለ ሰጠን እንዲህ አይነት ሥርዓቶች ከዚህ በኋላ አያስፈልጉም። ሐዋርያት 10 እና ቆላስያስ 2 አንብቡ። እስከዚህ ዘመን ድረስ በርካታ ሐይማኖቶች ውጫዊ መንጻት ላይ ያተኩራሉ፦ “ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ክርስቲያኖችን ጨምሮ ቆሻሻ … ሙስሊሞች ሰለሚታጠቡ ንጹህ እና ለአላህ የቀረቡ ናቸው”

[135] እግዚአብር ትዕዛዙን በቃል ካሳወቀ በኋላ (ዘጸአት 20) ሙሴን ወደ ተራራው ጠርቶ ፣ እግዚአብሔር ራሱ የጻፋቸውን ትዕዛዛት የያዙ ሁለት ጽላቶች ሰጠው (ዘጸአት 24:12 ፤ 31:18) “ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፤ ጽሕፈቱም በጽላቶች ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበረ።” (ዘጸአት 32:16)

[136] ሉቃስ 18: 9-14 ፤ ኤፌሶን 2:8-9 ያለውን ተመልከቱ።

[137] መሲሁ የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ መጠበቅ እና “አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው።” (መዝሙር 40:8) ብቻ ሳይሆን ሕጉ የሚያመለክተው እሱን ነው። “እንደዚህ **በእምነት** እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤” (ገላትያ 3:24)። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሐጢአት የሰጠው መፍትሄ በሮሜ 3:20-27 በዝርዝር ተቀምጧል።

## ምዕራፍ 16 ፦ የሴቷ ዘር

[138] “ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።” (1ቆሮንቶስ 15:22) ፤ በተጨማሪም ሮሜ ምዕራፍ 5 ፤ ገላትያ 4:4-5 አንብቡ።

[139] ኒኦ በርዝ ፕሬግናንሲ ሴንተር፦ www.neobirth.org.za/development. html

[140] “ቤቴልሄም ኤፍራታ” ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ (ዘፍጥረት 35: 16-19 ፤ 48:7) የምትገኘው የቤተልሄም የድሮ ስም ነበር። ዳዊት የተወለደወ በቤተልሄም ነበር (1 ሳሙኤል 16:1 ፣ 18-19 ፤ 17:12) ፣ ታላቁ የእሱ ዘርም የተወለደው እዚያው ነው (ማቴዎስ 2:1-6 ፤ ሉቃ 2:1-2)። በኢየሱስ ዘመን ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ግራ የተጋቡት በገሊላ በምትገኘው በናዝሬት ስላደገ ነበር (ዮሐንስ 7:41-42)

[141] ለመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ ፣ በምዕራፍ 5 የተዘረዘሩትን ትንቢታት ተመልከቱ።

[142] “መሲህ” በሚለው ቃል ላይ ተጨማሪ ከፈለጋቸሁ ምዕራፍ 14 ላይ ፦ ሁለቱ “ዘሮች” የሚለውን ንዑስ ርዕስ ተመልከቱ።

[143] ዘፍጥረት 1:2 ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ከገብርኤል ጋር

አይምታታም። መልዐኩ ገብርኤል የተፈጠረ መልዐክ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእግዚአብሔር የሚሰራ መንፈስ ነው። ምዕራፍ 9 እና 28 ተመልከቱ።

144 ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ ፣ ማርያም መደበኛ ጥንዶች እንደሚኖሩት ከባሏ ዮሴፍ ጋር ኖረች ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ነበሯቸው (ማቴዎስ 13:55-56 ፤ ሉቃስ 8:19 ፤ ዮሐንስ 7:3-10)

145 ነብያት መሲሁ ከድንግል እንደሚጸነስ አስቀደመው ተናግረው ነበር ፦ ኢሳያስ 7:14 ፣ የአብርሐም ፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ እና የይሁዳ ዘር እንደሚሆንም ተናግረው ነበር ፦ ዘፍጥረት 17:18-21 ፤ 26:3-4 ፤ 28:13-14 ፤ 49: 8-10 ፣ ከዳዊት የንግስና ዘርም እንደሚሆን ተናግረው ነበር ፦ 2ሳሙኤል 7:16 ፣ በቤተልሄምም እንደሚወለድ ተናግረው ነበር ፦ ሚኪያስ 5:2።

146 ማቴዎስ 2። ንጉስ ሄሮድስ ሌላ "ንጉስ" በመወለዱ ቀንቶ ነበር። ስለዚህም በቤተልሄም ዙሪያ የሚገኙ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በታች የሆናቸው ወንድ ልጆች እንዲገደሉ በማድረግ ኢየሱስን ለማጥፋት ሞከሯል። ሠይጣን ከዚህ ሁሉ ጀርባ ነበር። ግቡም "ክልሉን!" የወረረውን የሴቷን ዘር ማጥፋት ነር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሠይጣን ኢየሱስን ለመግደል የሚያደርገውን ሙከራ ለዮሴፍ በማስታወቅ እና ማርያምን እና ጨቅላውን ልጅ በስደት ወደ ግብጽ በመውሰድ እንዲያመልጥ አደረገ። እነዚህ ክስተቶች አስቀድመው በነብያት የተነገሩ ናቸው (ማቴዎስ ምዕራፍ 2 ፤ ሚኪያስ 5:2 ፤ ሆሴዐ 11:1 ፤ ኤርሚያስ 31:15)። ንጉስ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ ዮሴፍ ፣ ማርያም እና ኢየሱስ ልጁ ወዳደገበት ወደ ናዝሬት ተመለሱ።

## ምዕራፍ 17:- ይሄ ማን ነው?

147 ከJayyusi, Salma Khadra. Tales of Juha. Interlink Books. Northampton, MA, 2007, p. 19 የተወሰደ።

148 ጥቂት ጥንታውያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሚገኙ ጸሐፍት ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ የተናገሯቸውን ነገሮች እነሆ ፦ የሮም ባለ ታሪክ ታሲተስ (55 -12) [Tacitus 15:44]፤ ዮሲፈስ ፣ የአይሁድ ባለ ታሪክ (37 -101) [Antiquities 18:3]፤ ታልሙድ ፣ የአይሁድ መምህራን የቶራ ማብራሪያ[The Babylonian Talmud. Sanhedrin, 43a] ግሪካዊው ሉቺያን [The Death of Pereguire, p. 11-13 in The Works of Samasota, translated by H.W. Fowler and F.G. Fowler, 4 volumes. Oxford: Clarendon Press, 1949] ሱስንዮስ (69-122) የንጉስ ሄሪድያን ዋና ጸሐፊ [Claudias, 25]። ማስታወሻ ፦ ጄ. ኦስዋልድ ቻምበርስ እንዲህ ብሏል ፦ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ኢየሱስ የሰው ልጅ የሰው ልጅ የአዕምሮ ውጤት እንጂ ታሪካዊ እውነታ የለውም ብሎ መከራከር ወንጌላት በሥነ ጽሁፉ ዓለም ውስጥ የሚገኙ ተዓምራት ሲያደርጋቸው ሐያዉን ክርስቶስን ደግሞ በታሪክ ውስጥ የሚገኝ ተዓምር ያደርገዋል። ኤርነስት ሬናን ኢየሱስን

ለመፍጠር ኢየሱስ ያስፈልጋል። ጄ. ጄ ሩሶ አንድ ሰው ይህንን ርዕሱን አቀናበረው ከሚለው ይልቅ ሰዎች ይህንን ታሪክ ተስማምተው ጻፉት የሚለው ለማመን ይከብዳል ሲል ይሞግታል።" (Sanders, J. Oswald. The Incomparable Christ. Moody Press. Chicago, 1971, p. 57.)

149 ማቴዎስ 13:55- 56። ኢየሱስ ከሕጋዊ አባቱ ከዮሴፍ (ማርቆስ 6:3) ጋር በአናጢነት ያደገው በናዝሬት ነው (ማቴዎስ 2:22-23 ፤ ሉቃስ 2:51-52)። የኢየሱስ የተዋረደ ማንነት ዝቅ ብሎ የሚያገለግልን ሳይሆን ድል አድራጊ ጀግና የሚፈልጉትን አሰናከላቸው።

150 "ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ፣ የኤሊ ልጅ..." (ሉቃስ 3:23)

151 ኢየሱስ ራሱን በዙ ጊዜ "የሰው ልጅ" ብሎ ይጠራ ነበር ፤ ይሄም "የሰው / የሰው ዘር ልጅ" የሚል ትርጉም ያለው መሲሐዊ መጠሪያ ነው (ግሪክ ፦ አንትሮፖስ)። አስገራሚ መጠሪያ ነው! ወደድነውም ጠላነውም እኛ ሁላች ን "የሰው ዝርያ ልጆች" ነን። ነገር ግን የከበረውን የእግዚአብሔርን ልጅ ስንመለከት የሰው ልጅ ለመሆን **መረጠ** ተጨማሪም ራሱን ከሰው ዘር ጋር አመሳሰለ። ስለዚህም ይሄ መጠሪያ ሰውነቱን የሚያጸናውን ያህል መለኮተነቱንም ያጸናል ምክንያቱም ሚያመለክተው በሰው ልጆች መካከል በአካል መገኘቱን ነው። ዳንኤል 7:13-14፤ ማቴዎስ 8:20 ፤ ሉቃስ 5:24፤ 22:69-70፤ ዮሐንስ 5:27፤ 13:31፤ ራዕይ 1:13-18፤ 14:14።

152 ለምሳሌ ኢየሱስ የጠቀሰው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ (በሉቃስ 4:4) ከሙሴ ቶራ ነው ፦ ዘዳግም 8:3።

153 ከሰው ልጅ ኃጢአተኛነት የተነሳ ሠይጣን በእርግጥም "የዚህ ዓለም ገዢ" እና "በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው" (ዮሐን ስ12:31 ፤ ኤፌሶ ን2:2) ሆኗል። የሰው ልጅ የመጣው የሰው ልጅ ከኃጢአት የተነሳ ያጣውን ገዢነት ለማስመለስ ነው።

154 መዝሙር 110 እና መዝሙር 2 ፤ ማቴዎስ 21:41-46

155 ቁርዓን 19:19 ከ 48:2 ፤ 47:19 ጋር አነጻጽሩ።

156 ቁርዓን 19:19 ፤ 3:45-51፤ 5:110-112፤ 19:19

157 ቁርዓን 4:171

158 በእስልምና ውስጥ ከፍተኛው ኃጢአት "ሺርቅ" (በአረብኛ ማጋራት) ነው። ሺርቅ የትኛውንም ነገር ከአምላክ ጋር እኩል አድርጎ መቁጠር ነው።

159 ለመሲሁ የተሰጡ መጠሪያዎችን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ፦ ድንቅ = ለእግዚአብሔር ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ትርጉሙም ተራ ያልሆነ ማለት ነው። መካር =መሲሁ በጥበብ የተሞላ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ኃያል አምላክ = አምላክ ራሱ በሰው ሥጋ ሲገለጥ ማለት ነው። ዘላለማዊ አባት = የዘላለም ባልቤት ይሆናል ማለት ነው። የሰላም አለቃ = ለሚታመት የሚሰጠውን ነገር የሚገልጥ ነው፦ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም (ሮሜ 5:1)፣ ከሌሎች ጋር ሰላም (ኤፌሶን 2:14-18) ፣ ውስጣዊ

ሰላም (ፊሊጲሲዩስ 4:7) እና በመጨረሻ ዓለም ዓቀፋዊ ሰላም (ምዕራፍ 29 ተመልከቱ)

[160] ነብዩ ዳዊት ጌታ በአካል ወደ ምድር እንደሚመጣ አስቀድሞ ተናግሯል “እነሆ፣ **መጣሁ**፤ ስለ እኔ በመጽሐፍ ራስ ተጽፎአል፤” (መዝሙር 40:7)፡፡ ሚልኪያስ ሕዝቡን “ለጌታ” ምጽዓት የሚያዘጋጅ ቀደሞ የሚመጣ ሰው እንደሚልክ ተንብዮአል (ሚልኪያስ 3:1)፡፡

[161] ወደ እኛ ደረጃ መውረድ ለሁሉን ቻዩ አምላክ ከደረጃው በታች ነው፡፡ እስቲ እናንተ እና ባልንጀራችሁ ኦማር እና አሮን ስለ ተባሉ መንፈሳዊ መሪዎቻችሁ እያወራችሁ ነው እንበል፡፡ ባልንጀራችሁ እንዲህ ይላል “አሮን በአሻንጉሊት መኪና ይጫወታል ኦማር ግን አይጫወትም!” ለአሮን ክፍ ያለ አክብሮት እንዳለው ሰው “በፍጹም! አሮንማ በፍጹም በአሻንጉሊት መኪና አይጫወትም፡፡ በመጀመሪያ ይሄ ምላሽ ምክንያታዊ ይመስላል፡፡ በመቀጠል ታሪኩ ኦማር እና አሮን ትንንሽ ልጆች እንዳላቸው እና ልጆቹ ወለል ላይ ተቀምጠው አብረዋቸው እንዲጫወቱ እንደሚፈልጉ ታሪኩ ይነግራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ኦማር ይሄ ነገር አይመጥነኝም ሲል አሮን ግን ከልጆቹ ጋር በዚህ አይነት መንገድ ጊዜ ለማሳፍ ደስተኛ መሆኑን ብናውቅስ? መልካም አባት፣ ሰው እና መሪ የሚሆነው ኦማር ነው ወይስ አሮን? በተመሳሳይ መልኩ ሰዎች “ሁሉን ቻዩ አምላክ እንደ ሰው በምድር ላይ መግለጥ አይመጥነውም” ሲሉ መነሻ ሐሳባቸው መልካም ሊሆን ይችላል ነገር ግን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ከማጉላት ይልቅ እያንቋሸሹት ነው፡፡

[162] ዮሐንስ 13 ኢየሱስ የአገልጋይ ስራ የሆነውን የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠብ መፈጸሙን ይነግረናል፡፡ ወንጌላትን ማንበብ ዋናኛውን አገልጋይ ማግኘት ነው፦ ጌታን ራሱን፡፡

[163] ማቴዎስ 14 ፤ ማርቆስ 6 ፤ ዮሐንስ 6

[164] መሲሁ ኢየሱስ ዘላለማዊ ነዋሪነቱን እየገለጠ ነው፡፡ ከአብርሐም በፊት ነበርኩ ብቻ ማለት ከፈለገ “ከአብርሐም በፊት **እኔ ነኝ**” ከማለት ይልቅ “ከአብርሐም በፊት ፣ ነበርኩ” ይል ነበር፡፡ ምዕራፍ 9 ስለ የሐወሐ(ዘጸአት 3:14) የተጻፈውን ተመልከቱ፡፡

[165] ኢየሱስን ላመለኩት ሰዎች ጥቅም ላይ የዋለው አምልኮ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ለሚያመልኩ ሰዎች ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፡፡ (ማቴዎስ 8:2 ከራዕይ 7:11 ጋር አነጻጽሩ፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ አምልኮ የግሪኩ ፕሮስኩኔኦ የተሰኘ ቃል ሲሆን ትርጉሙም በአምልኮ በግንባር መደፋት ማለት ነው፡፡)

[166] እስካሁን ድረስ ቅዱሳት መጽሐፍት ተበርዟል የሚለውን ማሰረጃ የሌለው ሐሳብ የምትቀበሉ ከሆነ ምዕራፍ 3 “ተበርዟል ወይስ ተጠብቋል?” የሚለውን ርዕስ አንብቡ፡፡

[167] Lewis. C.S. Mere Christianity. NY: Macmillan-Collier, 1960, pp. 55-56.

[168] የእግዚብሔርን ውስብስብ አንድነት ለመከለስ ምዕራፍ ዘጠኝን በድጋሚ አንብቡ፡፡

[169] ብዙ ሰዎች በኢየሱስ እና በወጣቱ ባለጸጋ ታሪክ ሌላ ገጽታ ይሰናከላሉ። ሰውየው ወደ ኢየሱስ እየሮጠ ተጠጋና እንዲህ ሲል ጠየቀው “መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?” (ማቴዎስ 19:16 ፤ ማርቆስ 10:17 ፤ ሉቃስ 10:25) ለተሰበሰበው ሕዝብ የወጣቱ ጥያቄ መልካም መስሎ ታይቷል፣ ለጌታ ግን እንደዚያ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ይሄ ሐይማኖተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ወደር የለሽ ቅድስናና የሰው ንገዱብ የለሽ ሐጢአተኝነት የሚገልጸውን መሠረታዊ እውነት አለመረዳቱን አውቋል። ራሱን ጻድቅ አድርጎ የሚያየው ይሄ ሰው በራሱ ጥረት ወደ ገነት የሚገባ ፣ በሆነ መንገድ ብቁ የሚሆን መስሎታል። በዓለም ላይ ያለውን ባለጠጋ ሰው አግኝቶ የያዘውን ጭብጥ ሙሉ የመዳብ ፍራንክ ጥብቅ አድርጎ ይዞ “ያንተን ርስት እንድወርስ ምን ያህል ልስጥህ?” ሲል የሚጠይቅን ሕጻን ይመስላል። ኢየሱስ ለዚህ ነው ምን ሲል ነው የመለሰለት? በራሱ ብርታት በፍጹም የእግዚአብሔርን ፍጹም የጽድቅ መሰፈርት እንደማያሟላ ሊያሳየው ፊቱን ወደ ቶራ እና ወደ አሥርቱ ትዕዛዛት እንዲመልስ አደረገው። “ዘላለማዊ ሕይወት” የሆነ “መልካም ስራ” ሰርተን እናገኘዋለን ለሚሉ የሚገባ አይደለም።

[170] በተጨማሪም ኢየሱስ “ልባችሁ አይታወክ፤ **በእግዚአብሔር** እመኑ፥ **በእኔም** ደግሞ እመኑ። …ኢየሱስም፦ **እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። …እኔን ያየ አብን አይቶአል**፤ እንዴትስ አንተ፦ አብን አሳየን ትላለህ? **እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን**? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ **ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ።**” (ዮሐንስ 14:1 ፣ 6 ፣ 9-11)

[171] ኢሳያስ 53:1፤ ዮሐንስ 12:38 ፤ ሉቃስ 1:51፤ በተጨማሪም፦ ኢሳያስ 40:10-11 ፤ 51:5 ፤ 52:10 ፤59:16 ፤ 63:5፤ ኤርሚያስ 32:17።

[172] ምንም እንኳን እግዚአብሔር ነብያትን(ኤልያስ እና ኤልሳእ) የሞተ ሰው እንዲያስነሱ ሳይል ቢሰጣቸውም ፣ የትኛውም ነብይ የሕይወት ምንጭ ነኝ ብሎ አልተናገረም። “**እኔ** ትንሳዔም ሕይወትም ነኝ” ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

[173] መሲሁ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ፣ በሰማይ ነበር። ስለህም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ “ “እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።” (ሉቃስ 10:18)

## ምዕራፍ 18: የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ

[174] ዕብራውያን11:6 ፤ ኤርሚያስ 29:13 ፤ ኢሳያስ 29:11፤ ማቴዎስ 11:25 ፤ 13:13-14 ፤ ሉቃስ 8:4-15፤ ዮሐንስ 6። በዙዎቹ የእግዚአብሔር እውነቶች የተገለጡት በታሰበበት ሁኔታ አንድን ነገር እንዲያመለክቱ ተደርገው አይደለም፣ ምክንያቱም እውነትን የሚፈልጉ ሰዎች እንዲያገኟቸው ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን እንዲያዳምጡ

፣ እንዲረዱ እና እንዲያምኑ አያስገድድም። ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች የእሱን እውነትን ያገኛሉ። በፈቃዳቸው ማየት የተሳናው ሰዎች ደግሞ አያገኙም።

[175] ብዙ ትንቢታት ሁኔታው ከመከሰቱ በመቶች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት የተጻፉ ቢሆኑም የተጻፉት በአላፊ ጊዜ እንደሆነ ልብ ብላችኋል። የእግዚአብሔር ዕቅድ ሊደናቀፍ አይችልም። ፈጣሪ አንድ ነገር ይሆናል ሲል እንደ ተፈጸመ ይቆጠራል። ለዚህም ነው መሲሁ "ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ" (ራዕይ 13:8) የተባለው።

[176] መሲሁ ወደ ምድር ከመምጣቱ ከ 1000 ዓመታት በፊት የተጻፈውን መዝሙር 2 አንብቡ። በሌላ ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መሲሁ በዳግምምጽዓቱወቅት(በአንድአምላክአንድመልዕክትእንደተገለጸው) ከሰማይ እንደሚወድቅ ድንጋይ ተደርጎ ተገልጧል። ያ"ድንጋይ" ለእሱ አልገዛ ያሉትን ሁሉ "ወደ ትቢያነት" ይለወጣል (ዳንኤል 2:34-35 ፤ ማቴዎስ 21: 33-44)

[177] የጴጥሮስን ተጨማሪ ቃላት ለማየት ፣ ሐዋርያት 2-5 ፤ ሐዋርያት 10 ፤ 1 ጴጥሮስ 1፡10-12 ፤ 2:21-25 ፤ 3:18 ፤ ወዘተ አንብቡ። በተጨማሪም በጳውሎስ የተጻፉትን ቃላት ተመልከቱ ፦ "**የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት**፤ ለእኛ ለምንድን ግን **የእግዚአብሔር ኃይል ነውና**። ...ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፤ **የእግዚአብሔርም ድካም** ከሰው ይልቅ ይበረታልና። ...ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤" (1ቆሮንቶስ 1:18 ፣25 ፣27)

## ምዕራፍ 19 ፦ የመስዋዕት ሕግ

[178] አቤል ይህንን ሁሉ ማድረግን ያወቀው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ነግሮታል። ዕብራውያን 11: 4 መሰዋዕቱን "በእምነት" ማለትም እግዚአብሔር ባዘዘው እናተሰፋ በሰጠው ነገር ላይ ባለው እምነት አቅርቧል። በስተኋላም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምትካዊ መሰዋዕትነት በሕጉ ውስጥ በጽሁፍ በዝርዝር አሰቅምጧል ፣ አቤልም ከረጅም ጊዜ በፊት ይህንን በመታዘዝ ፈጽሟል። ዘፍጥረት 4:4 አቤል "በኩር" እንዳመጣ ይናገራል (ከዘጸአት 13:12-13 ጋር አነጻጽሩ) ፣ ጠቦት "ከመንጋው" (ዘሌዋውያን 5:6) እና "የስባውን" አቅርቧል (ዘሌዋውያን 3:16 ተመልከቱ)። አቤል መሰዋዕቱን በመሰዊያ ላይ እንደሰዋ አይናገርም ፣ ነገር ግን ከእሱ በኋላ የመጡ አማኞች እንዳደረጉት ይህንን ሳያደርግ አይቀርም። ዘፍጥረት 8:20 ፤ 12:7፤ 13:4 ፣18 ፤22:8-9፤ ዘጸአት 20:24-26 ፤ ዘሌዋውያን 17:11፤ ወዘተ።

[179] ዳንኤል 6፤ አስቴር 3:8-15፤ 8:7-17

[180] Strong, James. The Exhaustive Concordance of the Bible. NY: Abingdon-Cokesbury Press, 1948, p. 57. ዘፍጥረት 6:14 ("መሸፈኛ") ከዘሌዋውያን 5:18 ("ቤዛ") ጋር አወዳድሩ። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከፋር (ቤዛ) የተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል ነው።

[181] ዘሌዋውያን 5:7
[182] ከ 50 ጊዜ በላይ መጽሐፍ ቅዱስ መሰዋዕቱ "ያለነቀፋ" መሆን እንዳለበት ይናገራል። ለምሳሌ "ቍርባኑም የሚቃጠል መሥዋዕት ከበጎች ወይም ከፍየሎች ቢሆን፥ **ነውር የሌለበትን** ተባቱን ያቀርበዋል።" (ዘሌዋውያን 1:10)

**ምዕራፍ 20:- የመሰዋዕቱ መታሰቢያ**

[183] ኢድ አል አደሃ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነ ዓመታዊ ኢስላማዊ በዓል ነው። እግዚአብሔር ለአብርሐም በልጁ ምትክ እንዲሰዋው ጠቦት ያቀረበበትን ክስተት የሚያስታውስ ነው። ምንም እንኳን ቁርዓን ራሱ የተሰዋው እስማኤል ነው ባይልም ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይስሐቅ ነው ቢልም፣ በስፋት እንደሚታወቀው ኢስላማዊ እምነት ከሆነ የተሰዋው ልጅ ኢስማኤል እንጂ ይስሐቅ አይደለም። የኢድ መሰዋዕት በዓለም ላይ በሚገኙ ሙስሊሞች የሚከናወን ነው። ወደ መካ በሚደረገው ንፈሳዊ ጉዞ(ሃጅ) የሚደረግ የመጨረሻው ስርዓት ነው። የሃጅ መንፈሳዊ ጉዞ የሚጠናቀቀው ከማለዳው የኢድ ጸሎት በኋላ እንስሳ (ብዙ ጊዜ በግ ወይ ላም) በማረድ ነው። ብዙዎቹ ሙስሊሞች እነዚህ ስርዓቶች "አዲስ ልደት "የሚመስል ነገር እንድሚፈጥሩላቸው እና በአግባቡ ከፈጸሙት ሐጢአታቸው እንደሚሰረይላቸው ያምናሉ። ምንም እንኳን ሙስሊሞች እነዚህ ስርዓቶች ለድነታቸው ማረጋገጫ እንደማይሆን ያምናሉ ምክንያቱም ከሃጅ እና ከኢድ መሰዋዕት በኋላ ወዲያውኑ ሐጢአታቸው መከማቸት ይጅምራል። (ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 10 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ተመልከቱ።)
[184] በመጀመሪያ፣ የአብርሃም ስም አብራም ነበር። ከቦታ እጥረት የተነሳ የታሪኩ ይሄኛው ክፍል በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ውስጥ አልተብራራም። ዘፍጥረት 17 ተመልከቱ። ለአብርሐም ሙሉ ታሪክ ዘፍጥረት 11- 25 አንብቡ፣ በተጨማሪም ሮሜ 4 ፣ ገላትያ 4 እና ዕብራውያን 11 አንብቡ።
[185] ዘዳግም 7:6-7 ፤ 14:2
[186] እግዚአብሔር አይሁድ ያልሆኑ ሰዎችን ለመባረክ ሃገረ እስራኤልን የተጠቀመባቸውን ምሳሌዎች ተመልከቱ ፦ ዮሴፍ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ግብጻውያንን አዳነ (ዘፍጥረት 37-50)። የአብርሐም ልጅ የሆነችው ናኦሚ ለሁለት ሞዓባውያን ሴቶች ለኦኦርፋ እና ሩት በረከት ነበረ ች(የብሉይ ኪዳኑን የሩት መጽሐፍ ተመልከቱ)። ነብዩ ኤልያስ ለሲዶናዊዋ መበለት በረከት ነበር (1 ነገስት 17 ፤ ሉቃ4:26)። ዮናስ በዳተኝነት ቢሆንም ለነነዌ ሰዎች የድነት መልዕክት አቅርቧል (ዮናስ)። ንጉስ ሰምኦን ለአረባዊዋ ለንግስት ሳባ በረከት ነበረ (1 ነገስት 10 ፤ ሉቃስ 11:31)። ዳንኤል ባቢሎናውያንን ባርኳል (ዳንኤል 1-6)። አስቴር እና መርደኪዮስ ለፋርስ አገዛዝ በረከት አምጥተዋል (አስቴር) ወ.ዘ.ተ።
[187] ዘፍጥረት 12:2-3፤ 22:16-18 ፤ ዕብራውያን 6:13-20 ፤ ዮሐንስ 4:22 ፤ ሐዋርያት 1–10 ፣ ወዘተ።

[188] “አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፥ የተስፋን ቃል የተቀበለው፦ **በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል የተባለለት እርሱም አንድ ልጁን አቀረበ፤እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻለው አስቦአልና**፥ ከዚያም ደግሞ በምሳሌ አገኘው።” (ዕብራውያን 11:17-19)

## ምዕራፍ 21 ፦ ተጨማሪ ደም ፈሰሰ

[189] በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ “የመስዋዕት ታሪክ” መቁጠር ጀመርኩና 200ኛው ታሪክ ላይ ስደርስ አቆምኩ! አራቱ ቃላት ማለትም “ደም” ፣ “መሰዋዕት” እና “መሰዊያ” በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 1400 ጊዜ በላይ ይገኛሉ (ቀተ)

[190] ዘፍጥረት 15: 13-14 “አብራምንም አለው፦ ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፤ ባሪያዎች አድርገውም **አራት መቶ ዓመት** ያስጨንቋቸዋል። ደግሞም በባርነት በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ፤ **ከዚያም በኋላ በብዙ ከብት ይወጣሉ**።”። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ፍጻሜ በዘጸአት 1:1-12 ፤ 12:35-41 ሰፍሮ ይገኛል። እግዚአብሔር ሉዓላዊ አምላክ ነው። ዕቅዶቹ ሁል ጊዜ ይፈጸማሉ።

[191] ዘጸአት 5-11

[192] ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ በሲና ተራራ ላይ ከሚገኝ የሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ሲል ቃል ገባለት፦ “በእውነት እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ እኔም እንደ ላክሁህ ምልክትህ ይህ ነው ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር ትገዛላችሁ አለ።” (ዘጸአት 3:12)

[193] ዘጸአት 13-17 “ዓለቱን ሰነጠቀ፥ ውኃውም ፈሰሰ፤ ወንዞች በበረሃ ሄዱ፤” (መዝሙር 105:41)

[194] ዘጸአት 28:9-19 ፤ በስተኋላ መሲሁ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ “በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር **ይድናል**፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማርያም ያገኛል።” (ዮሐንስ 10:9) ብሏል። በመቅደሱ ውስጥ ይገኝ የነበረው እያንዳንዱ ነገር የእሱን ማንነት እና ስራ ያሳይ ነበር።

[195] “**እጁንም** ለቍርባን በቀረበው ራስ ላይ **ይጭናል**፥ በመገናኛውም ድንኳን ደጃፍ አጠገብ ያርደዋል፤ የአሮንም ልጆች ካህናቱ **ደሙን በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል**። ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ በእነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ስብ፥ በጕበቱም ላይ ያለውን **መረብ** ከኵላሊቶች ጋር ይወስዳል።” (ዘሌዋውያን 3:2-5)

[196] መቅድሱ ከሰማይ ወደ ምድር የሚመጣውን መሲህ የሚያሳይ ምስል ነው። ያንን አዳኝ ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ልክ እንደ ቤተ መቅደሱ ውስጣዊ ክፍል “እርሱም ፈጽሞ ያማረ ነው” (መሳልየ መሳልየ ዘሰለሞን 5:16) ነው። ለማያውቁት እንደ ቤተ መቅደሱ ውጪ “የተናቀ ከሰውም የተጠላ” (ኢሳያስ 53:2-3)።

[197] አዳም(አዳማ) በቀጥታ “ሰው” እና ቃለ በቃል “ቀይ አፈር” ተብሎ

የሚተረጎም ቃል ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር የአዳም አካል ከምድር አፈር ስላበጀው ነው።
198 ዘሳልቁ 3፡23-39
199 ዘሌዋውያን 16 ፤ ዛሬ አይሁድ የመቤዠት ቀን ዮም ኪፑር ብለው ይጠሩታል ነገር ግን ቀኑ የመጀመሪያ ትርጉሙን ለቋል ምክንያቱም መቅደስ፣ ካህናት፣ እና የመሰዋዕት ጠቦት የላቸውም። አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ከዛሬ ከአይሁድ ምልክቶች መካከል አንዱ ግድግዳ (ምዕራባዊው ግድግዳ፣ የቤተ መቅደሱን አካባቢ ለማስፋት በታላቁ ሄሮድስ የተገነባ የመከለያ አጥር)። አይሁድ በየዕለቱ እሱ አጠገብ በመቆም የመጣው መሲህ እንዳልመጣ በማስብ እንዲመጣ ይጸልያሉ! በነብያት አስቀድሞ እንደተነገረው የአይሁድ መንፈሳዊ እውር ናት (ኢሳያስ 6:10 ፣ 53:1 ፤ ኤርሚያስ 5:21 ፤ ሕዝቅኤል 12:2 ፤ ቆሮንቶስ 3:12 -4:6)። አንድ ቀን አይናቸው ይከፈትና ኢየሱስ (የሽዋ) የመቅደሱን ፣ የክህነቱን እና የመስዋዕቱንምሳሌእንደፈጸመይገነዘባሉ(ዕብራውያን8-10፤ኢፌሶን2)። የመንፈሳዊ ዕውርነት ግድግዳ ይፈርሳል (ኤፌሶን 2:1 4፤ ሮሜ 9-11)። የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ 5 ሰለሰዎች የተነገሩ ትንቢታት የሚለውን ንዑስ ርዕስ ተመልከቱ። በተጨማሪም የግርጌውን ማስታወሻ አንብቡ።
200 2 ዜና 3:1 ፣ ዘፍጥረት 22:2 አነጻጽሩ። ሙስሊሞች በ7ኛው ክፍለ ዘመን ባለው ወርቃማውን ጉልላት መስጊድ የሰሩት እዚህ ቦታ ነው።
201 2ዜና 7:5

**ምዕራፍ 22 ፦ ጠቦት**

202 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጌታ አንደኛው መጠሪያ አማኑኤል ማለትም “ከእኛ እግዚአብሔር” (ኢሳያስ 7:14 ፤ ማቴዎስ 1:23) ማለት ነው።
203 2 ቆሮንቶስ 5:1-4 ፤ 1 ቆሮንቶስ 6:19 ፤ 2 ጴጥሮስ 1:13-14 ፤ ኤፌሶን 2:21
204 ኢሳያስ 40:3-9 ፤ ሚልኪያስ 3:1፤ ሉቃስ 1 ፤ ዮሐንስ 1
205 በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው ካህን ወይም ንጉስ ለመሆን በተመረጠ ጊዜ ስልጣን ያለው ሰው ማለትም እንደ ነብይ ያለ ሰው እግዚአብሔር ለተለየ ስራ እንደመረጠው ለማሳየት በዘይት ይቀባዋል። እግዚአብሔር ልጁን በመንፈስ ቅዱስ የቀባው እሱ ራሱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘይት ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል። **ማስታወሻ**፦ በፍጥረት ስራ ውስጥ ሶስቱ አካላት ተሳታፊ እንደሆኑ ሁሉ አብ ፣ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በቤዝዎት ሰራ ውስጥ ተሳታፊ ናቸው።
206 “ጻድቅ ግን **በእምነቱ** በሕይወት ይኖራል።”(ዕንባቆም 2:4) ምንም እንኳን የሚያርበው መሰዋዕትነት “የዓለምን ሐጢአት ለማስወገድ” በቂ ቢሆንም የሚጠቀመው ደግሞ የኢየሱስ መሰዋዕትነት ለእነሱ መሆኑን የሚያምኑትን ነው። ይሄ እውነት በእኛ “የጽድቅ መንገድ” በተሰኘው የንጋል የሬድዮ ፕሮግራማችን ይገለጻል (www.twor.com; www.lesprophetes.com)። በብዙ ስርጭቶቻችን ላይ አድማጮች ነጻ

የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ ይቀርብላቸዋል። እሱን ፍለጋ በጽሁፍ የሚጠይቁ ሰዎች በነጻ ይሰጣቸዋል። ይሄ ስጦታ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አድማጮች በሙሉ የሚሆን ነው? አዎ። ሁሉም አድማጮች ይህንን ነጻ የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ ለመቀበል ለእኛ ይጽፉልናል? በፍጹም። ብዙዎች ይህንን ዕድል አይጠቀሙም። በተመሳሳይ መልኩ ለሁሉ በቂ በሆነው የልጁ መስዋዕትነት እግዚአብሔር ይቀርታንና የዘላለምን ሕይወት ለሁሉም ሰው አቅርቧል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስጦታ የሚቀበሉት የተወሰኑ የአዳም ልጆች ብቻ ናቸው። ሉቃስ 14:15-24 ተመልከቱ።

**ምዕራፍ 23:- የመጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜ**

207 ኢሳያስ 53 ፤ መዝሙር 22። በተጨማሪም እግዚአብሔር ለዘመናት ያለውን እቅድ የሚገልጠውን ዳንኤል 9:24-27 ተመልከቱ። የዚህ አጠቃላይ ዕቅድ አካል፦ “መሢሕ ይገደላል፥ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም፤” (ዳንኤል 9:26)

208 ማቴዎስ ምዕራፍ 21 እስከ 25

209 ተካደ ፦ መዝሙር 41:9 ፤ ዘካርያስ 11: 12-13 እና ማቴዎስ 26:14-16 ፤ 27 : 3-10።

210 አይሁዳውያን ዓመታዊ የፋሲካ በዓላቸውን ሲያከብሩ ኢየሱስ የመጨረሻው እና ፍጹሙ አማኞችን በሐጢአት ላይ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያድነው የፋሲካ በግ ነው። “**ፋሲካችን ክርስቶስ** ታርዶአልና፤” (1ቆሮንቶስ 5:7)

211 የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 13 እስከ 17

212 ኢየሱስ ሊይዙት ለመጡ ሰዎች በቀላሉ ያለው “እኔ ነኝ” ነበር። “እኔ እሱ ነኝ” የሚለው ቃል ተርጓሚዎች የገለጹበት መንገድ ነበር ነገር ግ ን “እሱ” የሚለው ቃል በግሪኩ ምንባብ ውስጥ አይገኝም። ኢየሱስ ማንነቱን እየተናገረ ነበር ፦ “ያለና የሚኖር” በራሱ ሕልውና ያለው ከሰማይ የመጣው ነው። ኢየሱስ “ያለና የሚኖር” ብሎ ሲመልስ የሐይማኖት መሪዎች እና ወታደሮች ወደ ኋላ ማፈግፈጋቸው እና መሬት ላይ መውደቃቸው የሚያስገርም አይደለም።

213 “በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ **የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት** ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት።” (ዳንኤል 7:13) **ማስታወሻ**፦ ልብስን መቅደድ በዚ ብህል ውስጥ የመጨረሻ የማዘን እና የመናደድ ምልክት ነው። የሚያስርመው ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ሕግ “በራሱም ላይ የቅባት ዘይት የፈሰሰበት፥ የክህነትም ልብስ ይለብስ ዘንድ የተቀደሰ ከወንድሞቹ የበለጠው ካህን ራሱን አይግለጥ፤ ልብሱንም አይቅደድ።” (ዘሌዋውያን 21:10) በዚህ ድርጊት (ማቴዎስ 27:65 ፤ ማርቆስ 14:63) ቀያፋ ራሱን ከሊቀ ካህንነት ነጻ አደረገ። አዲሱ ዘላለማዊ ካህን የራሱን ስጋ መሰዋዕት አድርጎ ሊያቀረብ ወደ ምድር የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። ሳጢአተኛውን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር በእውነት ሊያስታርቅ የሚችለው ብቸኛው እሱ ነው (ዕብራውያን 2:17 ፤ 3:1 ፤ 4:14-

16 ፤ 7:26 ፤ 8:1 ፤ 9:11 ፣ 25 ፤ 10:19-22)።
[214] ዮሐንስ 18:38 ፤ 19:4 ፣ 6 ፤ ዮሐን ስ 19:15 ፤ ሉቃስ 23:21

## ምዕራፍ 24:- ሙሉ በሙሉ ተከፈሏል

[215] እስካሁን ድረስ የአንድ አምላክ አንድ መልዕክትን ምዕራፍ 8 እና 9 እና 17 ካልተረዳችሁ እነዚህን አርፍተ ነገሮች እግዚአብሔርን እንደመሳዷብ ልትቆጥሯቸው ትችላላችሁ። እንዲያውም አንዳንዶች ምጸታዊ በሆነ መንገድ “እግዚአብሔር በድንግል ማሕጸን ውስጥ ሳለ ፣ በስተኋላም በመስቀል ላይ ሳለ አጽናፈ አለሙን ሲያንቀሳቅስ የነበረው ማን ነው?” ይላሉ። ይሄ ጥያቄ ቅዱሳት መጽሐፍትን እና እነሱን የሰጠውን አምላክ በተመለከተ ካላቸው የተሳሳተ መረዳት የመነጨ ነው። “መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።” (ማቴዎስ 22:29)። እግዚአብሔር ወሰብስብ በሆነ ስሉስ አሐዱነት ይኖር የነበረ እንደመሆኑ መጠን በተመሳሳይ ጊዜ በምድር እና በሰማይ መሆን ችግር ሊፈጥርበት አይችልም። ጸሐይ ከምድር ውጪ ሆና የጸሐይ ብርሃንና ሙቀት ከእኛ ጋር በምድር መሆን እንደሚችሉት ሁሉ የጸሐይ ፍጣሪ የሆነው አምላክ በተመሳሳይ ጊዜ በሰማይ እና በምድር መሆን የማይችለው ለምንድን ነው?

[216] ቀራኒዮ (ካራኒዮን) ጎሎጎታ ለተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል የግሪክ መጠሪያ ነው ትርጉሙም የራስ ቅል ቦታ ማለት ነው (ማቴዎስ 27:33 ፤ ማርቆስ 15:22 ፤ ዮሐንስ 19:17)። ይሄ ኢየሱስ የተሰቀለበት ተራራ ከአሮጌዋ ኢየሩሳሌም ውጪ የሚገኝና የባዶ ራስ ቅል ቅርጽ ያለው ሲሆን አብረሐ ምበልጁ ምትክ ጠቦት ያቀረበበት ተራራ ሰንሰለት ውስጥ የሚገኝ ነው።

[217] ዮሲፈስ የተሰኘው የታሪክ አዋቂ ከኢየሩሳም መውደቅ ከ70 ዓም በፊት ሲናገር የሮም ወታደሮች “በየቀኑ አምስት መቶ አይሁድ ይዘው ፣ አንዳንዱም ከዚያ የበለጠ ይይዛሉ ወታደሮቹ ለአይሁድ ካላቸው ጥላቻ የተነሳ የያዟቸውን በመደዳ አንዱን ከአንዱ ፊት ደርድርው እንደ መቀለጃ በመሰቀል ላይ ይጠርቋቸው ነበር ፣ ብዛታቸው ማይቆጠር ሲሆን መሰቀል እና አካል በየቦታው ይታይ ነበር።” ዮሲፈስ ወንጀለኞቹ “መጀመሪያ ይገረፋሉ፣ በመቀጠልም በተለያየ መንገድ ከተሰቃዩ ይሰቃዩ ነበር” ሲል ጽፏል። (Josephus, Antiquities 11:1, p. 563)

[218] አይሁድ ቀንን የሚቆጥሩት ከማለዳ 12 ሰዓት ጀምረው ነበር። “በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ (6:00 + 3 ሠዓት =9)። ስድስት ሰዓትም በሆነ ጊዜ(ቀን 6:00) እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። (ከምሽቱ 9)” (ማርቆስ 15:25 ፣ 33)

[219] ዘፍጥረት 8:20 ፤ 22: 2-8 ፤ ዘጸአት 29:18። “የሚቃጠል መሰዋዕት” የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን 169 ጊዜ ይገኛል። ኢየሱስም የመጨረሻው ለሳጢአት የሚቀርብ የሚቃጠል መሰዋዕት ሆነ። ማርቆስ 12:33 ፤ ዕብራውያን 10:6-14። ማሰታወሻ ፦ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተንጠለጠለ ጊዜ ፊቱን ለምን መለሰ የሚለውን

ለመረዳት ኢሳያስ 53 እና መዝሙር 23 አንብቡ። በተመሳሳይ መዝሙር መሲሁ “አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ?” (መዝሙር 22:1) ይላል ብሎ ዳዊት በተነበየበት መዝሙር ዳዊት እግዚአብሔር በልጁ ላይ ፊቱን እንዳዞረበት ይነግረናል። “በእስራኤል የተመሰገንህ አንተ ግን በቅድስና ትኖራለህ።” (መዝሙር 22:3) እግዚአብሔር ፊቱን በኢየሱስ ላይ ያዞረበት ፍጹም ቅድስ ስለሆነ እና “ጠማምነትን ትመለከት ዘንድ አትችልም” (ዕንባቆም 1:13) ነው። በእነዚያ የጨለማ ሰዓታት ኀጢአት አልባው የሰው ልጅ እንደሐጢአተኛ የእግዚአብሔር ቁጣ በወረደበት ጊዜ በኀጢአተኞች ምትክ ቅጣትን እየተቀበለ ነበር። የእግዚአብሔር ቅዱስ በግ የሆነው ኢየሱስ የኀጢአት ተሸካሚ ሆነ (ኀጢአተኛ ሳይሆን) መዝሙር ጸሐፊው ይህንን በተገቢው መንገድ ገልጾታል “የማይሞተው መሞቱ ምስጢር ነው! ይህንን አይነት እንግዳ ነገርስ ማን ይረዳል?” (Amazing Love, Charles Wesley, 1707–1788)

[220] Edersheim, Alfred. The Life and Times of Jesus the Messiah. 1883, p. 614.

[221] ዕብራውያን 9 እና 10 አንብቡ። **ማስታወሻ** ፦ በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ምዕራፍ 22 እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ክብር በቅድስተ ቅዱሳን እና በቤተ መቅደስ ይገኝ ነበር፤ ከዚህ በኋላ ከመጋረጃው ጀርባ አይገኝም። በኢየሱስ ነበር።

[222] ዮሐንስ 19:31-37፤ ዘጸአት 12:46 ፤ መዝሙር 34:20፤ ዘካርያስ 12:10 ፤13:6

## ምዕራፍ 25:- ሞት ተሸነፈ

[223] ማቴዎስ 28፤ ማርቆስ 16 ፤ ዮሐንስ 20-21 ፤ 1 ቆሮንቶስ 15። **ማስታወሻ**፦ ብዙ የኢየሱስን ትንሳዔ ውሸትነት የሚያረጋግጡ መጽሐፍትን ለመጻፍ የተነሱ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሳቱን የሚያሳዩ የማያሻሙ መረጃዎች አግኝተዋል። ለምሳሌ ፦ Morrison, Frank. Who moved the Stone? Grand Rapids, MI: Zondervan, 1987; McDowell, Josh. Evidence that Demands a Verdict. Nashville, TN: Thomas Nelson, Inc., 1993; Strobel, Lee. The Case for Christ. Grand Rapids, MI: Zondervan, 1998.

[224] ኢየሱስ “**በሦስተኛውም** ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው” (ማቴዎስ 16:21)ማለቱ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን “ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።” (ማቴዎስ 12:40) ብሏል። ብዙዎች ለመረዳት በማያስቸግር ሁኔታ፣ ኢየሱስ አርብ ማታ ወደ መቃብር ከተወሰደ እና እስከ እሁድ ጠዋት በመቃብር ከቆየ፣ ያ ሦስት ሙሉ ቀን አይደለም ይላሉ። ነገር ግን ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ የቆየት ጊዜ የተጠቀሰው የአይሁድ ልማድ እንደሆነው ተጠጋግቶ ነው፤ እንደ አይሁድ አነጋገር ከሆነ ምንም ያህል ትንሽ ቀን ቢሆንም ሙሉ ቀን ይወሰዳል (ምሳ. ማቴዎስ 27:63-64 ፤ ዘፍጥረት 42:17-18 ፤ 1 ሳሙኤል 30 ፤12-13 ፤ አስቴር

4:16 – 5:1) ሌላ ነጥብ እነሆ፦ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ አርብ ተሰቅሏል አይልም። ምንም እንኳን ብዙዎች "ግጭት!" ለማለትቢቸኩሉም በርካታ ይህንን ሊያብራሩ የሚችሉ ጥሩ ማብራሪያዎች አሉ።
[225] ሐዋርያት 11:26 ፤ 26:28 ፤ 1ጴጥሮስ 4:16
[226] ሐዋርያት 5:41 "እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤" ጴጥሮስ ተደብድቦ ታስሮ በር፦ ሐዋርያት 5 ፤ በተጨማሪም ሐዋርያት 12። ኢየሱስ ጴጥሮስ እንደሰማዕት እንደሚሞት አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፦ ዮሐንስ 21:18-19
[227] አንዳንዶች ኢየሱስ ለአሕዛቧ ሴትዮ የነገራት ነገር ይጠቅሳሉ "ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ።" (ማቴዎስ 15:24) ነገር ግን ልጁን ወዲያውኑ እንደፈወሰው ግን አይናገሩም! (ስለኢየሱ ስአግልግሎት እና አይሁድ ላልሆኑ ሰዎች ስላሳየው ርህራሄ ተጨማሪ ምሳሌ ከፈለጋቸሁ ማቴዎስ 12:41-42፤ 21:33-43፤ ሉቃስ 9:51-55፤ 10:30-36፤ 17:11-19፤ ዮሐንስ 4፤ 1 ዮሐንስ 2:1-2፤ ሉቃስ 24:45-48 ተመልከቱ)
[228] መዝሙር 68:18 ፤ 110:1 ፤ መዝሙር 24
[229] ኢየሱስ "በግርማው ቀኝ ተቀመጠ" ምክንያት "ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ" (ዕብራውያን 1:3) "ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ **ቆሞአል**፤እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ **ተቀመጠ**" (ዕብራውያን 10:11-12) በተጨማሪም 8:1 ፤ 12:2 ፤ ራዕይ 3:21 ተመልከቱ።

## ምዕራፍ 26፦ ሐይማኖተኛ እና ከእግዚአብሔር የራቀ

[230] ያዕቆብ 2:18 ፤ ማቴዎስ 5:13-16 ፤ ዕብራውያን 11
[231] ምንም እንኳን እግዚአብሔር መንግሥታት ሕዝባቸውን ከጥቃት የመከላከል መብት ቢሰጣቸውም "ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።" (ሮሜ 13:1-4 ፤ ዘፍጥረት 9:6) "የሰይፍ" ሳላፊነትንም ሰጥቷቸዋል፣ ደም ማፍሰስን የእግዚአብሔርን እውነት ማስፋፊያ አድረጎ መጠቀም ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት እና ምሳሌ ጋር ይጻረራል። "ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ **ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ**፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?" (ማቴዎስ 5:43-47)። ከዚህ በተቃራኒ ቁርዓን እንዲህ ይላል ፦ "እነዚያ በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን አላህን እና መልዕክተኛውን እርም ያደረጉትንም

እርም የማያደርጉትንና እውነተኛ ሐይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነው ግብርን [ጂዛ ፣ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የሚከፍሉት ልዩ ግብር] በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጓቸው፡፡” (ቁርዓን ፣ ሱራ 9:29)

232 “ከመጀመሪያ የሰማቸኋት መልእክት፦ **እርስ በርሳችን እንዋደድ** የምትል ይህቺ ናትና፤ከክፉው እንደ ነበረ ወንድሙንም እንደ ገደለ እንደ **ቃየል አይደለም፤ ስለ ምንስ ገደለው? የገዛ ሥራው ክፉ፤ የወንድሙም ሥራ ጽድቅ ስለ ነበረ ነው፡፡**” (1 ዮሐንስ 3:11-12 አመት) ቃየል አቤልን እንዲገድል ያነሳሱት ሁለት ገዳይ ሳይላት ዲያብሎስ እና ቅናት ናቸው (ከማቴዎስ 27:18 ጋር አንጻጽሩ)፡፡

233 ታዲያ የተጠራጣሪዎቸን የተለመደ ጥያቄ የምንመልሰው እንዴት ነው፦ “ቃየን ሚስት ከየት አገኘ?” ዘፍጥረት 5 ምላሽ ይሰጠናል፡፡ “ወንዶችና ሴቶች” (ዘፍጠረት 5:4)፡፡ በግልጽ እንደምናየውም ቃየን ከእህቶቹ መካከል አንዷን አገባ፡፡ ይሄ በዚያ ወቅት ዘረመልደረጃ ጥፋት የሚያስከትልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ በስተኋላ እግዚአብሔር ይህንን አይነት ጋብቻ ከለከለ፡፡ አቤል ከሞተ በኋላ ምን ሆነ? የአቤል አካል ወደ አፈርነት ተመለሰ፡፡ እግዚአብሔር በእምነቱ ላይ ተመስርቶ ሳጢአቱን ይቅር ብሎ ጻድቅ ስላለው ነፍሱና መንፈሱ ግን ወደ ገነት ሄዱ፡፡ ዕብራውያን 11:4

234 ሙሴ እና ሌሎች ነብያት በኖህ ዘመን የተከሰተውን ዓለም አቀፋዊውን የጥፋት ውሃ እና የተከሰተውን መልከዓ ምድራዊ ቀውስ ገልጸውታል ፦ ዘፍጥረትs 7–8 ፤ መዝሙር 104:6-8፤ ኢዮብ 22:16 ፤ ማቴዎስ 24:37-39፤ 2 ጴጥሮስ 2:5-6፡፡

**ምዕራፍ 27፦ ደረጃ 1 ፦ የእግዚአብሔር ያለፈው ዘመን ዕቅድ**

235 በአንድም በሌላ መልክ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከሦስት ጭብጦች ጋር ይያያዛል፦ እግዚአብሔር የሰራው ፣እግዚአብሔር እየሰራው ያለው እና እግዚአብሔር ወደፊት የሚሰራው ናቸው፡፡ በነገረ መለኮታዊ ቃላት ሦስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጦች በሚከተለው መልኩ ይከፈታሉ ፦ መጽደቅ = በምታምኑበት ጊዜ እግዚአብሔር **በቦታችሁ** ፍጹም ጻድ ቅ ይላችኋል፡፡ (ሮሜ 3-5) ቅድስና = አሁን ጸድቃችኋል እግዚአብሔር በተግባር በቅድስና **እንድትኖሩ** ይረዳችኋል፡፡ (ሮሜ 6-8 እና 12-15)፡፡ መከበር = በሰማይ በቦታም በልምምድም **ፍጹም ጻድቅ** ትሆናላችሁ፡፡

236 Richardson, Don. Lords of the Earth. Oxnard, CA: Regal Books; 1977, pp. 354. (ለተጨማሪ የሰው ሥጋ በል ሰዎች መለወጥ ታሪክ Don Richardson read: Peace Child. Oxnard, CA: Regal Books, 1975. አንብቡ፡፡

237 ሐዋርያት 26:9-11፤ 7:58-60 ፤ 8:1-3፤ 9:1-2

238 ሐዋርያት 9:1-31፤ በተጨማሪ ሐዋርያት ምዕራፍ 11 ፤ 13-14፤ 16-28፡፡ በሐዋርያት ፣ ምዕራፍ 22 እና 26 ፣ ጳውሎስ የመለወጡን ታሪክ

ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም ገላትያ 1:13 ፣ 23 ፤ ፊሊጲሲዩስ 3:6 ፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:9 ፤ ወ.ዘ.ተ፡፡

239 "ቅዱስ" በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእግዚአብሔር የተለየ፣ በእግዚአብሔር የይቅርታና የጽድቅ መንገድ በእምነት ጻድቅ እንድሆነ ቅዱስ የታወጀለት ሰው ማለት ነው፡፡ "ቀኖና" የሞቱ ሰዎችን "ቅዱሳን" የማድረግ ሂደት መጽፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ነገር እጅግ በጣም ተቃራኒ ነው (ዘዳግም 33:2-3 ፤ መዝሙር 30:4 ፤ ምሳሌ 2:8 ፤ ዳንኤል 7:21-27 ፤ ማቴዎስ 27:52 ፤ ሐዋርያት 26:10 ፤ ኤፌሶን 1:1 ፣ 2:19 ወዘተን ተመልከቱ)

## ምዕራፍ 28:- ደረጃ 2፦ የእግዚአብሔር የዚህ ዘመን ዕቅድ

240 ራሳቸውን ለመጠበቅ እንዲህ አይነት መንገድ ሲጠቀሙ ከጠላት ጋር እየተባበሩ መሆኑን በዙ ሰዎች አይረዱም፡፡ (ዘዳግም 18:10-14 ፤ ኢሳያስ 47:13 ፤ ሐዋርያት 19:19 ፤ ገላትያ 5:19-21)

241 1ዮሐንስ 2:1 ፤ ዮሐንስ 14-16

242 በምዕራፍ አንድ አሕመድ በሚከተለው መልኩ የጻፈውን ኢሜይል ጠቅሰን ነበር ፦ "... በመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱሳችሁ እና በብሉይ ኪዳንም ውስጥ ውስጥ የሙሐመድን (ሰዐወ) መምጣት የሚያሳዩ ትንቢታት አሁንም አሉ፡፡" አሕመድ እየጠቀሰው ያለው አንደኛው ቁልፍ ምንባብ ዮሐን ስከ 14-16 ያለውን ነው፡፡

243 ጴንጤቆስጤ ማለት አምሳኛ ማለት ነው፡፡ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት የብሉይ ኪዳን ክብረ በዓል ነው (ዘሌዋውያን 23:16)፡፡ ከመጀመሪያው እግዚአብሔር በዚህ ቀን ታላቁን በረከት መንፈስ ቅዱስን ለመላከ ቃል ገብቷል፡፡

244 1 ቆሮንቶስ 12:27፤ ኤፌሶን 4:21 ፤ 5:25-32፤ ራዕይ 19:7-9፤ 22:17፤ ዮሐንስ 3:29

245 1ዮሐንስ 1:8-10፤ 2:1-2 ፤ ሮሜ 6–8

246 የተሳሳተ አሰተሳሰባቻሁን በተመለከተ ንሰሐ በምትገቡበት እና ለሳጢያታችሁ ሞቶ በተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ ስታምኑ በውሃ (በኋላ የሚከሰት) በመንፈስ ቅዱስ (ሮሜ 6:1-5 ፤ ሐዋርት 1:5 ፤ 1 ቆሮንቶስ 12:13) "በክርስቶስ ተጠመቃላችሁ" (ሮሜ 6:3)፡፡ "ወደሱ መጠመቅ" ማለት "ከእሱ ጋር መተባበር፣ መቆጠር" ማለት ነው፡፡ በምታምኑበት ጊዜ ሳጢአት ከልለት ልጁ ጋር "ከተባበሩት" ጋር (ሮሜ 6:5) የእግዚአብሔር የራሱ ቤተሰብ ትሆናላችሁ፡፡ አዲሱ ዘላለማዊው ቦታችሁ "በክርስቶስ" ይሆናል፡፡

247 ሐዋርያት 24:15፤ ሉቃስ 14:14፤ ዮሐንስ 5:28-29፤ ዳንኤል 12:2 ፤ ራዕይ 20:6 ፣ 11-15፤ ራዕይ 22:12

248 2ቆሮንቶስ 5:10፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ሊቀበሏቸው ስለሚችሉ ከአምስት ያላነሱ አክሊሎች (ዋንጫ/ ሽልማቶች) ይናገራል ፦ 1 ቆሮንቶስ 9:25 ፤ 1 ጴጥሮስ 5:4 ፤ ያዕቆብ 1:12፤ 1 ተሰሎንቄ 2:19-20 ፤ 2 ጢሞቴዎስ 4:8፡፡ እነዚህ አክሊሎች ለእኛ ክብር ሳይሆን ለእሱ

ክብር ናቸው (ራዕይ 4:10)። ጌታ የተቤዣቸው ሰዎች ለእሱ ስም እና ለእሱ ክብር የስሩትን የትኛውንም ስራ አይረሳም (ማቴዎስ 10:41-42 ፤ ዕብራውያን 6:10)።

[249] Sheikh, Bilquis. I Dared to Call Him Father. New York: Fleming H. Revell Company, 1978; p. 53.

[250] 1 ዮሐንስ 2:27፤ ዮሐንስ 4:14፤ 14:26፤ 16:13፤ ኤርሚያስ 31:33-34፤ ኤፌሶን 4:21

[251] ጸሎትን ዝም ብሎ በመደጋገም እና ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት ለጸሎታችን እውነተኛ ምላሽ በማግኘት መካከል ወሳኝ ልዩነት አለ። ሮሜ 8:26-27፤ ኢፌሶን 6:18፤ 1 ዮሐንስ 5:14-15፤ ዮሐንስ 14:13-14፤ 15:7፤ ፊሊሲዩስ 4:6-9

[252] ሮሜ 12 ፤ 1 ቆሮንቶስ 12፤ ኤፌሶን 4

[253] 2 ቆሮንቶስ 3:18፤ ፊሊጲሲዩስ 1:6፤ 3:20-21

## ምዕራፍ 29:- ደረጃ 3:- የእግዚአብሔር የወደፊት ዕቅድ

[254] ከጥቂት ገጾች በኋላ ነብያት ሰለ መሲሁ ዳግም ምጽዓት እና መመለሱን ተከትለው ስለሚሆኑ ክስተቶች አሰቀድመው የተናገሩባቸውን ጥቅሶች ብሉይ ኪዳን እናነባለን። የምንመለከታቸው ጥት ምንባባት ዘካርያስ 14 ምዕራፍ ፣ ዳንኤል 7:13-14 ፤ መዝሙር 72 ፤ ኢሳያስ 9:6-7።

[255] 1 ተሰሎንቄ 4:13-18; 1 ቆሮንቶስ 15:51-58

[256] ምዕራፍ 28 ሁለቱ ፍርዶች በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ተመልከቱ።

[257] ኤፌሶን 5:27 እና ዙሪያው የሚገኙ ምንባባትን ተመልከቱ። አስገራሚው ጭብጥ በምዕራፍ 10 አንድ አምላክ አንድ መልዕክት ስር ተገልጿል። ቅዱሳት መጽሐፍት በተደጋጋሚ ጌታን እንደ “ሙሽራ” ሕዝቡን ደግሞ “ሙሽሪት” አድርገው ይገልጿቸዋል። ብቻ ሀሳባዊ በሆነው ገጽታው ጌታ ከሕዝቡ ጋር እንዲኖረው የሚፈልገውን ዘላለማው የቅርብ እና መንፈሳዊ ግንኙነት በተመለከተ ፍንጭ የሚሰጥ ነው (ኢሳያስ 54:5 ፤ 62:5 ፤ መዝሙር 45 ፤ የሰለሞን መዝሙር፤ ሆሴዕ 2:16 ፣ 19 ፣20 ፤ ማቴዎስ 9:15 ፤ 25:1-13 ፤ ዮሐንስ 3:29: 2ቆሮንቶስ 11:2-3 ፤ ኢፌሶን 5:22-33 ፤ ራዕይ 21:2 ፣ 9 ፤ 22:17)።

[258] ማቴዎስ 24:21 ፤ ራዕይ 7:14 ፤ የመከራውን ዘመን በጣም የተሟላ ገለጻ የሚገኘው በራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ 6 እስከ 19 ነው።

[259] ሮሜ 11:26-27። **ማስታወሻ** ፦ ይሄ ክስተት በዘፍጥረት 37-45 በሚገኘው የዮሴፍ ታሪክ ውስጥ ቀድሞ ተገልጧል። አስገራሚ ትይዩነት ነው!

[260] 1 ቆሮንቶስ 15:45-47 ፤ ሮሜ 5:12-21። “ፊተኛው አዳም” እና “ኋለኛው አዳም” የሚሉ ቃላት በምዕራፍ 16 የአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ምዕራፍ ውስጥ ተጠቅሰዋል። የአዳም ኅጢአት ስአው ልጆች በሙሉ እንዲሞቱ እንዳደረገ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ እና የፈሰሰ ደምም ለሚምኑ ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል።

[261] 2 ተሰሎንቄ 1:7-10፤ ራዕይ 19:6-14 ፤ ይሁዳ 14፤ ዘካርያስ 14:5

[262] ኢሳያስ 53:7፤ ዮሐንስ 1:29 ፤ ራዕይ 5:5፤ 2 ተሰሎንቄ 1:5-10 ፤ ዮሐንስ 3:17-18፤ 12:47፤ዳንኤል 9:24-27፤ ኢሳያስ 53 ከዘካርያስ 14 ጋር አንጻጽሩ። በተጨማሪም ደግሞ "መከራ" እና "ክብር" በሚከተሉት ምንባባት ውስጥ አነጻጽሩ፦ ሉቃስ 24: 25-26 ፤ 1ጴጥሮስ 1:10-12 ፤ ዕብራውያን 2:9 ፤ ፊሊጲሲዩስ 2:5-11 ፤ መዝሙር 22 ፤ ወዘተ።
[263] መዝሙር 72 "የሰለሞን መዝሙር" የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል። ምንም እንኳን "የእሴይ ልጅ የዳዊት መዝሙር ተፈጸመ" (መዝሙር 72:20) ርእግ ቢያበቃም ይህንን መዝሙር ሰለሞን የጻፈው ይመስላል። ይሄ በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን የመጀመሪያዎቹ አምስት ክፍሎች ሁለተኛ ክፍል ማብቃቱን የሚያመለክት ጥቅስ ነው። ዳዊት የዚህ ሁለተኛ ክፍል ዋነኛ ጸሐፊ ነው።
[264] ለዘላለም የሚኮነን ማን ነው? "**ፈሪዎች** እና የማያምኑ" ይሄ ማት ቤተሰቦቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው ምን እንደሚሏቸው እና ምን እንደሚያርጉባቸው ማሰብ የእግብሔርን መልዕክት ያላመኑ ሰዎችን የሚያመለክት ቃል ነው። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ፣ አድማጮቹን በግልጽ አስጠንቅቋል "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ። …በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል። ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤" (ማቴዎስ 10:28 ፣34-37)

## ምዕራፍ 30 ፦ የገነት ቅድመ ዳሰሳ

[265] ማቴዎስ 13:24-30። ይሄ የኢየሱስ ምሳሌ የመልካም እና እኩይ ድብልቅ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንደሚቀጥል ያሳያል።
[266] የራዕይ ምዕራፍ አንድ ቀሪ ክፍል የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን አድናቆት ፈጣሪ ገለጻ ያሳየናል፣ በመጽሐፍት፣ በፊልሞቾ እና በሐይማኖቾ ከተሰጠው ገለጻ የተለየ ነው።
[267] ማርቆስ 3:14-19 ፤ ዮሐንስ 19:26-27 ፤ ዮሐንስ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጽፏል፦ የዮሐንስ ወንጌል ፣ 1 ዮሐንስ ፣2 ዮሐንስ ፣ 3ዮሐንስ እና ራዕይ።
[268] የኢዮጴ ድንጋይ በብዙ ቀለማት የሚገኝ ነው። የካራናሊያን ድንጋይ አንጸባራቂ ቀይ ነው። ለብርሃን ሲጋለጥ ቀለሙ የበለጠ ይጠቁራል።
[269] በዙፋኑ ላይ ያለው ማን እንደሆነ ተመልከቱ። ኢሳያስ 6 (በአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ምዕራፍ 15 የተጠቀሰውን የኢሳያስ ራዕይ) ከዮሐንስ 12:36 -41 ጋር አነጻጽሩ።

[270] ዘፍጥረት 12:2-3 ፤ ማቴዎስ 1። (እግዚአብሔር ለአብርሐም የገባውን ተጨማሪ ተሰፋ ከፈለጋችሁ፣ የአንድ አምላክ አንድ መልዕክት ምዕራፍ 20 ከልሱ።

[271] ለምሳሌ ተወዳጁ የሲንደሬላ ታሪክ መጀመሪያ የተነገረው ቻይና ውስጥ ቢሆንም የአውሮፓ፣ የአሜሪካ፣ የፋርስ፣ የግብጽ ፣ የኮርያ የሕንድ ወዘተ ቅጂ አለው። እያንዳንዱ ሃገር የራሱ ቅጂ ሲኖረው ጭብጦቹ ግን ተመሳሳይ ናቸው። ቤዛነት የማግኘት እና የዘላለም ሕይወት ናፍቆት በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሰዎች ልብ ውስጥ የሚገኝ ነው። ሰለሞን እንዲህ ሲል ጽፏል ፦ "እግዚአብሔርም **ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ** ድረስ የሠራውን *ሥራ* ሰው መርምሮ እንዳያገኝ ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው።" (መክብብ 3:11 አመት)

# ጉዞውን በተመለተ ማሰላሰል

## የውይይት መመሪያ

### የምዕራፍ ክለሳ ጥያቄዎች



በዚህ ክፍል የሚገኙ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምታደርጉት ጉዞ በዙ እንድታተርፉ ለመረዳት የተዘጋጁ ናቸው። የነብያትን ማዕከላዊ መልዕክት ትረዳላችሁ? ያንን መልዕክት ታምናለችሁ? የእግዚአብሔርን ታሪክ እና መልዕክት ለሌሎች ለመንገር ዝግጁ ናችሁ? ይሄንን የመጨረሻ ክፍል ማሰላሳል እነዚህን ጥያቄዎች በግልጽነት እና በራስ በመተማመን ለመመለስ ያዘጋጃችኋል።

የምዕራፉን የክለሳ ጥያቄች በነጻነት ማራባት ትችላላችሁ። ለግል ጥሞና ወይም ለትንንሽ ቡድን ውይይቶች፣ ለክፍል ውስጥ ፣ ለእስር ቤቶች ፣ ለቤቶች ወይም ለተልዕክኮትምህርቶች ልተጠቀሙባቸው ትችላላችሁ።

*“አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ… የዘላለምንም መንገድ ምራኝ።”*

ነብዩ ዳዊት (መዝሙር 139፡23-24)



# 1

# እውነትን ግዛት

1. በዓለም ላይ 10 ሺህ ሐይማኖቶች ካሉ እውነትን ከስህተት መለየት ይቻላል? የግል አመለካከታችሁን አካፍሉ። (ገጽ 7-8)

2. መጽሐፍ ቅዱስ የምንጊዜም ባለብዙ ሽያጭ እና በታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ የተተረጎመ መጽሐፍ ነው? (ገጽ 8)

3. ቁርዓን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገራቸውን ሦስት ነገሮች ግለጹ። (ገጽ 11)

4. አንድን ሰው በተገቢው ሁኔታ ከማመናችሁ በፊት ልታውቋቸው የሚያስፈልጓችሁ ነገሮች ምን ምን ናቸው? እግዚአብሔርን ከማመቻችሁ በፊት ልታወቋቸው የምትፈልጓቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? (ገጽ 11)

5. ዘላለም የት እንደምታሳልፉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል? ምላሻችሁን አባራሩ (ገጽ 16-17)

### በራሳችሁ ቃላት

ምሳሌ 23:23 አብራሩ። “እውነትን ግዛ አትሸጣትም፥ ጥበብን ተግሣጽን ማስተዋልንም።” (ገጽ 7፤17)



# 2

# እንቅፋችን መሻገር

1. ሼርሎክ ሆልምስ ለዶ/ር ዋትሰን "ታያላችሁ ነገር ግን አታስተውሉም" አለው፡፡ "በማየት" እና በ "በማስተዋል" መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? (19)

2. በደንብ የተማሩ ሰዎች የዓለም የምንገዜም ሸያጭ ሰንጠረዥን የያዘውን መጽሐፍ ለማንበብ ጊዜ የማይወስዱባቸው ሦስት ምክንቶች ግለጹ፡፡ እነዚህ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ፡፡ (18-31)

3. እናምነዋለን የሚሉ ጥቂት ሰዎችን የሕይወት ዘዬ አሳፋሪ ከመሆኑ የተነሳ የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክትን አለመቀበል ጠቢብነት ነውን፡፡ (20-21)

4. ስዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚያግዟውን አራት መርሆዎች ግለጹ፡፡ (29)

5. መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን የያዘባቸውን አንድ ወይም ሁለት ምክንያቶች ጥቀሱ፡፡ (29-31)

**በራሳችሁ ቃላት**

ሆሴዕ 4:6 አብራሩ፡፡ "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል" (18)



# 3

# ተበርዟል ወይስ ተጠብቋል?

1. እንደ ቁርዓን እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን (ቶራ፣ መዝሙር፣ ወንጌል) ለሰው ልጆች የገለጠው ለምን ዓላማ ነው? (33)

2. መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚልን አንድን ሰው ልትጠይቁ የምትችሏቸው ሦስት ሞጋች ጥያቄዎች ምን ምን ናቸው? (34)

3. በርካታ ምሁራን መጽሐፍ ቅዱስ በታሪክ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተመዘገበ መጽሐፍ አድርገው ያዩታል፡፡ ትስማማላችሁ? አቋማችሁን አብራሩ፡፡ (38-40)

4. በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የእጅ ቅጂ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? (40)

5. ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ችላ የሚሉበትን ሁለት ወይም ሦስት ምክንያቶች ግለጹ፡፡ (42-44)

**በራሳችሁ ቃላት**

ሉቃስ 16:31፡፡ “ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው፡፡” (43-44)



# 4

# ሳይንስ እና መጽሐፍ ቅዱስ

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሺዎች ዓመታት በፊት የተጠቀሱ እና በቅርብ ጊዜያት በዘመናዊ ሳይንስ የተረጋገጡ ሦስት ሳይንሳዊ እውነታዎች ጥቀሱ። (46-49)

2. መጽሐፍ ቅዱስ የሚፈልገው ጭፍን እምነት ነው ወይስ ብልህ እምነት? ምላሻችሁን አብራሩ። (49-49)

3. ታሪክና ሥነ ቅርስ የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው እንዴት ነው? (49-52)

4. በሱራ 2:23 የቀረበው የቁርዓን ሙግት የሚያረጋግጠው ምንድን ነው? አብራሩ። (53-52)

5. ሳይንስ፣ሥነ ቅርስ እና ሥነ ግጥም “ቅዱስ መጽሐፍ” የተባለ መጽሐፍን እውነተኛነት ማረጋገጥ ይችላሉ? አቋማችሁን ተከላከሉ። (52-54)

**በራሳችሁ ቃላት**

ኢዩብ 38:4 አብራሩ። “ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ? ታስተውል እንደ ሆንህ ተናገር።” (45)



# 5

# የእግዚአብሔር ፊርማ

1. መጽሐፍ ቅዱስ ስላለፈው ጊዜ ፣ ስለ አሁኑ ጊዜ እና ስለ ወደፊቱ ጊዜ የሚናገረው ነገር ትክክለኛ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ? አብራሩ፡፡ (55-56, 64)

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ትንበያዎች እና ዶክተሮች፣ ኮከብ ቆጣሪዎች እና አዋቂዎች በሚናገሯቸው ትንበያዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? (56)

3. ሴኩላሩ ታሪክ በትክክል መፈጸሙን የሚያረጋግጥለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት ተናገሩ፡፡ (56-63)

4. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትንቢት ዓላማ ምንድን ነው? (64)

5. “የእግዚብሔር ፊርማ” ትንቢት የተፈጸመው በምን አይነት መንገድ ነው? (55-56, 64-65)

በራሳቸሁ ቃላት

ዮሐንስ 13:19 አብራሩ፡፡ “በሆነ ጊዜ እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፣ ከአሁን ጀምሬ አስቀድሞ ሳይሆን እነግራችኋለሁ፡፡” (64)



# 6

# ዘለቄታዊዊ ምስክርነት

1. በእናንተ አስተያየት እውነትን ለማረጋገጥ አንድ ሰው ብቻውን በቂ የማይሆነው ለምንድን ነው? (67)

2. እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ የሰጣቸው ሁለት “ምስክሮች” ምን ምን ናቸው? (67)

3. እግዚአብሔር መልዕክቱን ለሰው ልጆች ለመጻፍ የተጠቀመባቸውን አስር ሰዎች ጥቀሱ። (68)

4. ተዓማኒ የሆነ ምስክር የሚረጋገጠው በምንድን ነው? (70)

5. እውነተኛ ነብይን ከሐሰተኛ ነብይ መለየት የሚቻለው እንዴት ነው? (71-76)

**በራሳችሁ ቃላት**

በማቴዎስ 7:15-17 ላይ አስተያየት ስጡ። “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። …እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል።” (72)



# 7

# መሠረት

1. በኢየሱስ የተራራ ላይ ስብከት ፣ የብልሁ እና የሞኙ ሰው ልዩነት ምንድን ነው? ለሕንጻዎች እና ለእምነት መሠረት በጣም አሰፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (77-77)

2. የዘፍጥረት መጽሐፍ (ጅማሬ ማለት ነው) በሕይወታችን ውስጥ ላሉ ታላላቅ ምስጢራት ምላሽ ይሰጣል። የሕይወታችን ታላላቅ ጥያቄዎች ከምንላቸው መካከል ዋና ዋናዎቹ ምን ምን ናቸው? (78)

3. ታሪክ ስንናገር የት ነው የምንጀምረው? ለምን? (79)

4. የእግዚአብሔር የተገለጠ እውነት ከዕጽዋትና ከሽል ጋር የሚነጻጸረው በምን መንገድ ነው? (79-80)

5. በሊባኖስ የሚኖረው የጸሐፊው ጓደኛ መጽሐፈ ቅዱስን በራሱ ካጠና በኋላ ያገኘው ምን ነበር? (81-82)

### በራሳቻሁ ቃላት

በኢሳያስ 55:9 የሚገኘውን የእግዚአብሔር አዋጅ በአጭሩ ጻፉ።
“ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው።” (82)



# 8

# እግዚአብሔር ምን ይመስላል

1. በእናንተ አሰተያየት በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔር መኖሩን ለማረጋገጥ ያልሞከረው ለምንድን ነው? (87-90)

2. መላዕክት ምንድን ናቸው እግዚአብሔር ስለምን ፈጠራቸው? (91)

3. እግዚአብሔር አንድ ሆኖ በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ በላይ የሚሆነው እንዴት ነው? (90, 93-94)

4. ስለ እግዚአብሔር ማንነት እና ጠባይ የተወሰነ ነገር ማወቅ ለእኛ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (95)

5. በስድስቱ የፍጥረት ቀናት የገለጡ ሰደስት የእግዚአብሔርን ጠባያት ዘርዝሩ። (95-102) ከስድስቱ ጠባያት ዛሬ እናንተ እንዲታመስግኑ የሚያደረጋችሁ የትኛው ነው? ለምን?

በራሳችሁ ቃላት

መዝሙር 33:9 አብራሩ። “እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም።” (97)




1. በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ አንድ የሆነው እግዚአብሔር ራሱን “እኛ” በሚሉ የብዝኸነት መጠሪያዎች ያሰተዋውቃል። የእዚህ ጥሩ ማብራሪያ ነው የምትሉት የትኛውን ነው? (103-107)

2. በዕለት ከዕለት ሕይወታችን ውስጥ የምናገኛቸው ሦስት በአንድነቶች የፈጣሪያችንን ውስብስብ አንድነት እንድንረዳ ያደርጉናል? አብራሩ። (107-108)

3. “የእግዚአብሔር ልጅ” የሚለው መጠሪያ እንድምታ የማንለው ምንድን ነው? (110-112)

4. መጽሐፍ ቅዱስ ሰለ መንፈስ ቅዱስ የሚገልጣቸውን ሦስት ነገሮች ግለጡ። (112-113)

5. መጽሐፍ ቅዱሳዊው የእግዚአብሔር ፍቺ እግዚአብሔር ሊታወቅ የማይችል ሳይል ነው ከሚለው ዝነኛ ፍቺ የሚለየው እንዴት ነው? (115-117)

**በራሳችሁ ቃላት**

መዝሙር 9:10 አብራሩ። “ስምህን የሚያውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ፥ አቤቱ፥ የሚሹህን አትተዋቸውምና።” (115)



# 10

# ልዩ ፍጥረት

1. የመጀመሪያው “ወንድ” እና የመጀመሪያዋ “ሴት” የተፈጠሩት “በእግዚአብሔር ምሳሌ” ነው። (118-119)

2. እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን የፈጠረው ከምን አይነት “ቁስ” ነው? የመጀመሪያውን ሰው ከምን ፈጠረው? (119)

3. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረባቸውን ሁለት ዓላማዎች ጥቀሱ። (121, 126-129)

4. ሴቶችን በማዋረድ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ካለው ዓላማ ጋር የሚጋጩ ሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶች ምን ምን ናቸው? (124)

5. ሰባተኛው የፍጥረት ቀን አስፈላጊነት ምንድን ነው? (129)

**በራሳችሁ ቃላት**

ዮሐንስ 8:35 አብራሩ። “ባርያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል።” (127)



# 11

# የእኩይ መግባት

1. እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ ፍጹም መልካም ነበር። ስለዚህ ኀጢአት እና ሰይጣን ከየት መጡ? (130-131)

2. የእግዚአብሔር ነብያት ብዙ ግልጽ የኀጢአት ፍቺዎችን ይሰጣሉ። አንዱን ፍቺ ጥቀሱና በግል ታሪካቸው ምሳሌ ስጡ። (131-132)

3. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲያልን ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋለው ምስል ከሳች ቃል ምንድን ነው? (133)

4. ከሠይጣን ግቦች መካከል አንዱ ምንድን ነው? (133-134)

5. እግዚአብሔር የሰው ልጅ መልካሙን እና ክፉውን ከምታሳውቀው ዛፍ ከበላ ይደርስበታል ያለው ነገር ምንድን ነው? (135) ሠይጣንስ ይከሰታል ያለው ምንድን ነው? (136)

**በራሳችሁ ቃላት**

ያዕቆብ 2:19 አብራሩ። "እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።" (138)



# 12

# የኀጢአት እና የሞት ሕግ

1. ሞትን ምን የሚል ቃል የበለጠ ይገልጠዋል? የተቆረጠ ቅርንጫፍ ይሄንን ምን ያህል ይገልጠዋል? (141)

2. እግዚአብሔር አዳምን “ከእርሷ በምትበሉበት በዚያ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ።” (ዘፍጥረት 2:17) አለው። አዳም የተከለከለችውን ዛፍ በበላ ጊዜ በምን አይነት መንገድ ሞተ? (142, 144)

3. የአዳም ኀጢአት በእናንተ እና በቤተሰቦቻችሁ ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ ምንድን ነው? (142-144)

4. ከአዳም አንድ ኀጢአት የተነሳ በሰው ዘር ውስጥ የተሰራጩ ሦስት የሞት አይነቶችን ጥቀሱ። እጅግ በጣም አስፈሪው የትኛው አይነት ሞት ነው? (142-146)

5. ኀጢአት እፍረትን የሚያመጣው በምን አይነት መንገድ ነው? (146-146)

### በራሳችሁ ቃላት

በሕዝቅኤል 18:20 የሚገኘውን የኀጢአት እና የሞት ሕግ አብራሩ። “ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች” (148)



# 13

# ምህረትና ጽድቅ

1. እግዚአብሔር ሊያደረገው የማይችለው፥ ሰው ግን ሊያደርገው የሚችለው ነገር ምንድን ነው? (149)

2. በምናባዊው የፍርድ ቤት ትዕይንት ፣ የዳኛው ምሕረት ከፍትህ ጋር የሚጋጨው እንዴት ነው? (150-151)

3. እግዚአብሔር ምህርትን ለማሳየት ፍትሕን ችላ ማለት የሌለበት ለምንድን ነው? (151-153)

4. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ያደረትን እያወቀ ለምን ጠየቃቸው? (154)

5. እግዚአብሔር የሰውን ዘረ በሙሉ ቁልቁል ወደ ሳጢአት እና ሞት በመምራት ተጠያቂ ያደረገው ለምንድን ነው? (154-155)

**በራሳችሁ ቃላት**

መዝሙር 89:14 አብራሩ። "የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው፤ ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ።" (151)



# 14

# እርግማን

1. የ “እባብ” አስፈላጊነት ምንድን ነው እግዚአብሔርስ ምን ረገመው? (156-158)

2. ተስፋ የተገባው “የሴቷ ዘር” ማን ነው? ይህንን ቃል ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው? (158)

3. እርግማኑ ዓለም ላይ ተጽዕኖ የፈጠረባቸውን ጥቂት መንገዶች ጥቀሱ። (159-160)

4. ሐዘን፣ መከራ እና ሞት የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ንድፍ መደበኛ አካል ናቸው? አብራሩ። (159-161)

5. አዳምና ሄዋን ኃጢአት ከሰሩ በኋላ ፣ ሐፍረት ተሰማቸው እና ራሳቸውን ለመሸፈን የበለስ ዛፍ አዘጋጁ። እግዚአብሔር የራሳቸውን ጥረት ተቀበለ? እግዚአብሔር እፍረታውን እንዲሸፍኑበት የሰጣቸው ምንድን ነው? (161)

**በራሳችሁ ቃላት**

በዘፍጥረት 3:21 ላይ የተገለጠውን “ጸጋ” ፍቺ አብራሩ። “እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም።” (161-163)



# 15

# እጥፍ ችግር

1. ስለ ራሳችን ትክክለኛ አመለካከት ሊኖረን የሚገባው ለምንድን ነው? (166)

2. ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ አመለካከት ሊኖረን የሚገባው ለምንድን ነው? (167-169)

3. ከአስርቱ ትዕዛዛት ውስጥ በትክክል ስንቱን ታዛቹኋል? (170-171)

4. የመስታወትን ምሳሌ በመጠቀም የአሥርቱ ትዕዛዛትን ዋነኛ ዓላማ አብራሩ። (172-173)

5. የሰው በእግዚአብሔር ፊት “እጥፍ ችግር” ምንድን ነው? (175)

**በራሳችሁ ቃላት**

ያዕቆብ 2:10 አብራሩ። “ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል” (171)



# 16

# የሴቷ ዘር

1. መሲሁ ከወንድ ሳይሆን ከሴት መወለድ ያስፈልገው ለምንድን ነው? (176-178)

2. መጽሐፍ ቅዱስ መሲሁን “ኋለኛው አዳም” እና “ኋለኛው ሰው” ብሎ ለምን እንደሚጠራው አብራሩ። (179)

3. ስለ መሲሁ መምጣት ነብያት አስቀድመው የተነገሯቸውን በትንሹ አምስት ትንቢታት ጥቀሱ። (180 ፤ 61-62)

4. ገብርኤል ማርያም አዲስ የምትወልደው ልጅ “የእግዚአብሔር ልጅ” እንደሚባል ነግሯታል። ሉቃስ 1:26-37 (ገጽ 181) እንደገና አንብቡና ፤ ገጽ 110 እና 112 ከልሱና ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለበትን ምክንያት በአጭሩ አብራሩ።

5. “ኢየሱስ” የተሰኘው ስም ቃለ በቃል ምን ማለት ነው? (183)

### በራሳችሁ ቃላት

ሉቃስ 2:10-11 አብራሩ። “መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።” (184-185)



# 17

# ማን ሊሆን ይችላል?

1. መሲሁ ከሌሎች የሰው ልጆች ፍጹም የተለየ የሆነው እንዴት ነው? (186-187)

2. የአይሁድ የሐይማኖት መሪዎች ኢየሱስን በድንጋይ ለመውገር የሞከሩት ለምንድን ነው? (193 ፤ 198 ፤ 200)

3. "ኢየሱስ ከነብይ የበለጠ አይደለም" ከሚሉት ጋር ትስማማላችሁ? ለምን ትስማማላችሁ? ለምንስ አትስማም? (191 ፤ 200)

4. ኢየሱስ ቃሉን ያረጋገጠው በምን መንገድ ነው? (202)

5. ከሐይማኖት መሪዎች ይልቅ አጋንንት የበለጠ አክብሮት አሳይተዋል በሚለው ትስማማላችሁ? አቋማችሁን ተከላሉ። (203-204)

**በራሳችሁ ቃላት**

ኢየሱስ በማቴዎስ 22:42 የሚያቀርበውን ጥያቄ መልሱ፡፡ "ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?" (190-194)



# 18

# የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ

1. እናንተ ከነብያቱ የበለጠ ዕድል ያገኛችሁት እንዴት ነው? (205)

2. አንድን ነገር ወይም እቃ "መቤዠት" የሚለውን ቃል ለሕጻን ልጅ የምታብራሩት እንዴት ነው? (207-208)

3. ነብዩ ዳዊት ስለ መሲሁ አስቀድሞ የተናገራቸውን ሁለት ዋና ዋና ክስተቶች ጥቀሱ። (209)

4. "እንቁላል ከዐለት ጋር መታገል የለትም" ከሚለው የወሎፍ ምሳሌ ምን ጠቃሚ ትምህርት እንማራለን? (210)

5. ጴጥሮስ ያልተረዳው የእግዚአብሔር የመቤዠት እቅድ ክፍል የትኛው ነው? (211-213)

በራሳችሁ ቃላት

ገላትያ 4:4-5 አብራሩ። "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፥ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።" (207)



# 19

# QAYNUUNKA ALLABARIGA

1. አዳምና ሄዋን የመጀመሪያ ልጃቸው ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ የተረዱት የማያስደስት እውነታ ምንድን ነው? (214-216)

2. እግዚአብሔር አቤልንና መሰዋዕቱን የተቀበለበትን ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ጥቀሱ። እግዚአብሔር ቃየል እና መሰዋዕቱን ያለተቀበለበትን ሁለት ዋና ምክንያቶች ስጡ። (217-219)

3. ኅጢአታችሁን ሊደመስስ የሚችል ለታደርጉት የምትችሉት ነገር አለ? በጸሎት እና በመልካም ስራ የኅጢአትን ዕዳ መደምሰስ የማይቻለው ለምንድን ነው? (219)

4. እግዚአብሔር ኅጢአትን በሙሉ ሊቀጣ ይገባል። ኅጢአተኛን ሳይቀጣ ኅጢአትን የሚቀጣ መንገድ አለ? (220-222)

5. የመሰዋዕት ሕግ የኅጢአት እና የሞት ሕግን "ያሸነፈበትን" መንገድ አብራሩ። (220-223)

**በራሳችሁ ቃላት**

"ቤዛነትን" እና እግዚአብሔር ለሙሴ በዘሌዋውያን 17:11 የተናገረውን ቃል አብራሩ። "የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።" (217-219)



# 20

# ቅጽበታዊ መሰዋዕት

1. እግዚአብሔር አብርሐምን ታላቅ ሕዝብ ለማድረግ እና የከነዓንን ምድር ለዘሮቹ ለመስጠት ቃል ገባለት። እነዚህን የተስፋ ቃላት እንዳይመለስ የሚያደርጉ ምን አይነት ሁኔታዎች በአብርሐም ሕይወት ውስጥ ነበሩ? (225)

2. እግዚአብሔር አብርሐምን ጻድቅ ያለው ለምንድን ነው? “በእግዚአብሔር ማመን” ማለት ምን ማለት ነው? (226)

3. እግዚአብሔር እውነቱን እና ባርኮቱን በጥንታዊቷ እስራኤል በኩል ለአሕብ ሁሉ የሚያዳርስባውን ሦስት መንገዶች ጥቀሱ። (229)

4. እግዚአብሔር አብርሐምን ልጁን የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብ ተናገረው። አብርሐም እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን (በይስሐቅ ዘሮች በኩል ታላቅ ሕዝብ ሊያደርገው) አጥል ብሎ አመነ? አብራሩ። (232 ፤ በተጨማሪም የግርጌ ማስታወሻ #188 ተመልከቱ)

5. የአብርሃም ልጅ በመሰዊያ ላይ ያልሞተው ለምንድን ነው? (223-234)

**በራሳቸሁ ቃላት**

ሰለ ዘፍጥረት 22:14 ያላቸሁን መረዳት ግለጹ። “አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው፤ እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል።” (233)




1. በሉሲካ ታሪክ ውስጥ በመላው ግብጽ የሚገኙ ነዋሪዎች ሞትን የቀመሱት እንዴት ነው? (237)

2. እግዚአብሔር ሰዎች ከቤተ መቅደስ እንዲማሯቸው የፈለጋቸው ሁለጥ ጠቃሚ ትምህርቶች ምንና ምን ናቸው? (238)

3. የኪዳኑ ታቦት የሚያመለክተው ምንን ነው? (240)

4. አንድ ጊዜ ቤተ መቅደሱ ከተጠናቀቀ በኋላ እግዚአብሔር ከሰማይ የላከው ምንድን ነው? (242)

5. የመጋረጃው ዓላማ ምንድን ነው? (240) ሰው ከመጋረጃው አልፎ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት ሚችሉበት መንገድ አለ? አብራሩ። (244)

**በራሳቸሁ ቃላት**

ዕብራውያን 9:22 አብራሩ። "እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፤ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።" (235)



# 22

# ጠቦቱ

1. የእግዚአብሔር መጽሐፍ ማዕከላውዊ ጭብጥ ምንድን ነው? (246)

2. በትንሹ ሁለት መንገድ በመሲሁ የተፈጸሙ የቤተ መቅደሱ ተምሳሌታዊ መገለጫዎችን ጥቀሱ። (247-250)

3. የዕለት ከዕለት ምሳሌን በመጠቀም “ንሰሐ መግባት” ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ አብራሩ። (250-251)

4. እግዚአብሔር ሰለ ሌላ ሰው ሊናገረው የማይችለው ነገር ግን ሰለ ኢየሱስ የተናገረው ነገር ምንድን ነው? (252)

5. የሚሰው ጠቦቶች እግዚአብሔር የሰው ልጅን የኅጢአት ዕዳ ለመክፈል ያለውን ዕቅድ በጥላነት እና በተምሳሌትነት የሚገልጡት እንዴት ነው? (254-257)

### በራሳችሁ ቃላት

ዮሐንስ 1:29 አብራሩ። “በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፦ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።” (253)

# 23

# ቅዱሳት መጽሐፍትን መፈጸም

1. “ተስፋ ደመና ነው፤ ፍጻሜ ዝናብ ነው።” ይሄ የአረቦች አባባል እግዚአብሔር አዳኝ ወደ ምድር ለመላክ ያለውን ዕቅድ ለማብራራት እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል አብራሩ። (258)

2. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በፋሲካ ሰሞን እንድሚገደል ነግሯቸው ነበር። እግዚአብሔር ልጁ በዚህ ጊዜ እንዲሰዋ የፈለገው ለምን ይመስላችኋል? (260-261 ፤ በተጨማሪም ገጽ 236-237 ተመልከቱ)

3. በፋሲካ እራት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ ህብስት ቆርሶ ጽዋውንም ሰጥቷቸው ነበር። ህብስቱ የሚወክለው ምንን ነው? ጽዋው የሚወክለው ምንን ነው? (261)

4. ኢየሱስ ወታደሮች ሊያስሩት ሲመጡ ራሱን ያልተከላከለው ለምንድን ነው? (262-263)

5. ሊቀ ካህኑ ኢየሱስን እግዚአብሔርን በመሳደብ የከሰሰው ለምንድን ነው? (264-265)

**በራሳችሁ ቃላት**

በዘፍጥረት 22 ቁጥር 8 እና 1 4 ላይ የሚገኙትን ሁለት የአብርሐም ትንቢቶች አብራሩ። “ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው… በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል።” (266)



# 24

# ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል

1. ተፈጥሮ የማያውቅ ነገር ግን መንግስት የፈጠረው የመግደያ መንገድ ምንድን ነው ብላችሁ ስባላችሁ? የሐይማኖት እና የፖለቲካ ሰዎች ለኢየሱስ የመረጡለት የግድያ መንገድ ምንድን ነው? (267)

2. ከኅጢአት የተነሳ የተፈጠሩት ባለ ሦስት ደረጃ መለያየቶች ምን ምን ናቸው? ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሦስቱንም የመለያየት ደረጃዎች ተለማምዷል የሚለውን ነገር እንዴት ታዩታላችሁ? (271 [የሞትን ባለ ሦስት ገጽታ መለያየት ለመከለስ ገጽ 141-146 ተመልከቱ])

3. ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ያስፈለገው ለምን ነበር? (269-274)

4. ኢየሱስ ለኃጢአተኞች የዘላለም ኃጢአት ለጥቂት ሠዓታት እንዴት ሊቀጣ ይችላል? (271-272)

5. የቤተ መቀደሱ መጋረጃ ከላይ ወደታች መቀደድ ያለው አስፈላጊነት ምንድን ነው? (274-275)

### በራሳችሁ ቃላት

ዮሐንስ 19:30 አብራሩ። "ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፦ ተፈጸመ አለ፤ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።" (272-274)



# 25

# ሞት ተሸነፈ

1. ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስን አስከሬን ሰርቀውታል የሚለውን ሐሜት ማሰራጨት የጀመረው ማን ነው? ይህን ታሪክስ የፈጠሩት ለምንድን ነው? (280-280)

2. የኢየሱስ ሞት ፣መቀበር እና ትንሳዔ ለሠይጣን ሽንፈት ሊሆን የሚችለው በምን አይነት መንገድ ነው? (281-282)


3. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደገና በሕይወት መኖሩን የሚያረጋግጥ ምን አይነት ማስረጃ ማቅረብ ትችላላችሁ? (282-284)

4. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናደረግውን ጉዞ በመጀመርን ጊዜ እግዚአብሔር የመፍጠር ስራውን በጨረሰ ጊዜ "አረፈ" ብለን ነበር። ከዚህ ጉዳይ አንጻር ከእግዚአብሔር የመቤዠት ሥራ አንጻር የሚንማረው ጠቃሚ ትምህርት ምንድን ነው? (287)

5. ኢየሱስ ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ ለአርባ ቀናት ምን ሲያደርግ ነበር? ስለዚህ ነገር ካገኛችሁ ለታገኙት የምትችሉት አሰደሳች ነገር ምንድን ነው? (287-289)

### በራሳችሁ ቃላት

የ 1 ቆሮንቶስ 15 ፡3-4 አስፈላጊነትን አብራሩ። "ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤" (281)



# 26

# ሐይማኖተኛ ግን ከእግዚአብሔ ር የራቀ

1. ከኢየሱስ ሞትና ትንሳዔ በፊት እግዚአብሔር ኅጢአትን ይቅር ይል የነበረው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ኅጢአትን ይቅር የሚለው እንዴት ነው? ስለ ተሸፈኑ ኅጢአቶች እና ስለተጸመሰሱ ኅጢአቶች አጭር ማብራሪያ አካቱ። (291-293 ፤ በተጨማሪም ገጽ 253-257 ተመልከቱ)

2. ከእምነታችን ብርታት (ወይም መጠን) ይልቅ የምናምንበት ነገር አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (293-293)

3. እግዚአብሔር ሰዎች መልካም ስራቸው ከክፉ ስራቸው በልጦ ስለ መዘነ ወደ መንግስተ ሰማያት የሚስገባቸው ይመስላችኋል? በበድነት የ"ሚዛን ጽንሰ ሐሳብ" ዙሪያ ያላችሁን አቋም አብራሩ። (293-295)

4. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ኅጢአተኛ የዘላለም ፍርድን የሚያመልጠው እና በእግዚአብሔር ንጹህ እና ፍጹም መገኘት ውስጥ መኖር የሚችለው እንዴት ነው? (295-297)

5. መልካም ስራ የድነት ውጤት እንጂ የድነት መስፈርት ያልሆነው ምንድን ነው? (296-298)

በራሳችሁ ቃላት

ሐዋርያት 16:31 አብራሩ። "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (306)



# 27

# ደረጃ 1 ፦ የእግዚአብሔር ያለፈው ዘመን ዕቅድ

1. ምዕራፍ 27 እውነትን ፈላጊ ስለሆነ ተጓዥ ግለሰብ መለወጥ (309-313) ፣ የተሰቀለ ወንጀለኛ (315-317) ፣ የሰው ሥጋ በል ጎሳ (317-317) ፣ራሷን ለማጥፋት የምትፈልግ ልጃገረድ (317-318) ፣ ቀናተኛ ሐይማኖተኛ (319-320) እና አጥባቂ ሙስሊም የሆነ ወጣት (326-328) የሚናገር ታሪክ ይዟል። ከየትኛው ታሪክ ጋር የበለጠ ትመሳሰላላችሁ? ለምን?

2. በመስቀል ላይ የነበረውን ወንጀለኛ “ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” አለው። ንስሐ የገባው ወንጀለኛ ለዘላለም የዳነው ከምንድን ነበር? በተጨማሪም በኢየሱስ የተስፋ ቃል ላይ ተመስርተን የዳነው ወንጀለኛ ከሞተ በኋላ ራሱን የሚያገኘው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? (315-317)

3. ለሕጻን ልጅ የፍትህ ፣ምህረት እና ጸጋን ጽንሰ ሐሳብ ማብራራት የምትችሉት እንዴት ነው? (321)

4. የሰው ልጅ “እጥፍ ችግር” ምንድን ነው? የእግዚአብሔርስ “እጥፍ መፍትሄ” ምንድን ነው? (323-324)

5. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ሰዎች ዘላለምን የት እንድሚያሳለፉ ማወቅ ይችላሉ? ከሞታችሁ በኋላ የት እንደምትሄዱ ታውቃላችሁ? ምላሻችሁን አብራሩ። (326-328)

### በራሳችሁ ቃላት

2ቆሮንቶስ 5:21 አብራሩ። “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።” (324-326)



# 28

# ደረጃ 2 ፦ የእግዚአብሔር የዚህ ዘመን ፕሮግራም

1. በአሁኑ ዘመን ሰዎች በፍርሃት ተይዘው የሚኖሩት ለምንድን ነው? (329)

2. እንደ ቅዱሳት መጽሐፍት መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? እንዲሁም እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ላደረጉ ሰዎችስ የሚያደርገው ምንድን ነው? (330-331)

3. ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ የተወለደ ሰው ኃጢአትን ማድረግና እግዚአብሔርን ማሳዘኑን መቀጠል ይፈልጋል? “ዝርዝሩን ወይም ፍቅርን” ምሳሌ በመጠቀም ሐይማኖትን ብቻ በሚከተል እና ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት ባለው ሰው መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ። (337-339)

4. የውሃ ጥምቀት እውነተኛ ትርጉም ምንድን ነው? (339-340)

5. በአማኞች ቦታ እና በአማኞች ሁኔታ መካከል አስፈላጊ ልዩነት አለ። የአባት/ ልጅ ምሳሌ በመጠቀም ልዩነቱን ግለጡ። (343-345)

**በራሳችሁ ቃላት**

1ጴጥሮስ 1:16 አብራሩ። “እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ” (345)



# 29

# ደረጃ 3:- የእግዚአብሔር የወደፊት እቅድ

1. እግዚአብሔር ሰይጣንን ለመቀጥቀጥ እና ኃጢአትን ለማስወገድ ያለውን ባለ ሦስት ደረጃ ዕቅድ ገለጹ። (349 ፤ በተጨማሪም ገጽ 313 ተመልከቱ)

2. የመሲሁ ሁለተኛ ምጽዓት ከመጀመሪያ ምጽዓቱ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የሚለየው እንዴት እንደሆነ ተናገሩ። (356)

3. መዝሙር 72:7-19 ደግማችሁ አንብቡና ፤ ለመሲሁ ንጉስ መገዛታቸውን በሆነ መንገድ የሚያሳዩ የዓለም ገዢዎች እና ሕዝቦችን ዘርዝሩ። (357-359)

4. በኢየሱስ ክርስቶስ የሺህ ዓመት አገዛዘ ከአዳም ኃጢአት የተነሳ የመጣው እርግማን በአብዛኛው ይነሳል። ይሄ በምድር ላይ የሚኖረው አዎንታዊ ውጤት ምንድን ነው? (362-363)

5. ራዕይ 20:10-15 በታሪክ ውስጥ አስገራሚ የሆነ ታክ ትስማሙበታላችሁ? ምላሻችሁን አብራሩ። (364-365)

**በራሳችሁ ቃላት**

በ 1 ዮሐንስ 3:2 ላይ የምታዩትን አብራሩ። "ወዳጆች ሆይ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።" (367)

# 30

# የመንግሥተ ሰማያት ቅድመ ጥቆማ

1. “ዩንግ ያንግ” የመጽሐፈ ቅዱስን ንጽረተ ዓለም የሚቃረነው በምን አይነት መንገድ ነው? (368-369)

2. ሰዎች ስለ መንግሥተ ሰማያት ያላቸውን ሁለት የተሳሳተ አመለካከት ግለጹ። የእግዚአብሔር ሰማያዊ መኖሪያ ትኩረት ምንድን ነው? (371)

3. በዘፍጥረት የጀመረው አሰገራሚው የመቤዠት ታሪክ በራዕይ ይጠናቀቃል። ከአንድ ወይም ከሁለት ደቂቃ ያልበለጠ ጊዜ (ወይም በጽሁፍ ከሆነ ከ300 ቃላት ያልበለጠ) ወስዳችሁ እግዚአብሔር ረዳት የለሽ አማኝ የሆኑ ኀጢአተኞችን ከሠይጣን ፣ ከኅጢአት እና ከዘላለማዊ ሞት እንዴት እንደዳነ የሚተርከውን ታሪክ አሳጥሩ። (369, 377-380)

4. ሰዎች “በደስታ ለዘላለም ኖሩ” የሚሉ ታሪኮችን መናገር የሚወዱት ለምን ይመስላችኋል? የመልሳችሁ መሠረት ምንድን ነው? (379-382)

5. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያደረጋችሁት ያልተጣደፈ ጉዞ ለእናንተ ጠቃሚ የሆነው እንዴት ነው?

**በራሳችሁ ቃላት**

ራዕይ 21:27 ግለጹና በዚህ ምስል ውስጥ የት ቦታ እንደምትገኙ አብራሩ። “ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፣ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።” (382)



# ማስታወሻ



# ማስታወሻ

# ማስታወሻ

# አንድ አምላክ
# አንድ መልዕክት



# አካፍሉት

አስገራሚ በሆነ ግልጽነት፣ ይሄ አጓጊ እና መረጃ ጠገብ
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚደረግ ጉዞ የተስፋ ለጊዜውም
ለዘላለም የሚሆን ተስፋ ይሰጣል። በበርካታ ቋንቋዎች የቀረበ።




**www.One-God-One-Message.com**

“ይህንን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ምክንያታዊነት ይገባችኋላ በአዕምሯችሁ ውስጥም ቦታ ይይዛል። መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ፍላጎት በውስጤ ፈጥሯል።” — መሐመድ፣ከመካከለኛው ምስራቅ

“ይሄ መጽሐፍ የእውነት ማዕድን ነው፤ የአጻጻፍ ዘዬው ለየት ያለ ነው፤ለሰዎች በሚያስፈልጉ ነገሮች የተሞላ ነው።”
— ዊሊያም ማክዶናልድ፣ የቢሊቨርስ ባይብል ኮመንተሪ ጸሐፊ

ROCK INTERNATIONAL

**www.rockintl.org**

ሮክ ዓለም አቀፍ የኢየሱስን ፍቅ ር ለተጎዳው ዓለም ለማሳየት፣ ልጆች በአደጋ፣ በጥቃት እና ቸል በመባል ውስጥ ዕረፍት፣ ዕድል እና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ቦታ ፣ ወጣቶችም አዋቂዎችም ስምቶ የማይጠገበውን ታሪክ በግልጽ የሚረዱበት ቦታ ለመፈጠር የሚሰራ ድርጅት ነው።